እውነት አንድ ሆና የሰው ልጅ እንዴት በተለያየ ኃይማኖትና ፍልስፍና ተከፋፈለ? አንዲ እውነት እንዴት ተጋረደች? መጽሐፏ መልሱን ይዛ ቀርባለች፡፡

እውቀት እና እምነት

የእስልምና፣

የኦርቶዶክስ፣

የካቶሊክ፣

የፐሮቴስታንት፣

የሐዋርያት፣

የጂሆቫ፣

የአድቬንቲስት፣

የዋቄፈና፣

የራስተፈሪያን፣

የኤቲዝም፣

የባኢ፣

የሞርሞን፣

የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን፣

የሺንቼአንጂ

የክርስቲያን ሳይንስ፣

የአማኝ ኢቮሉሽኒስት፣

የሂውማኒዝም፣

የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ፣

አስተምህሮ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተዳሰዋል፣

አዘጋጅ ታሪኩ ተፈራ

እውቀት እና እምነት

ታሪኩ ተፈራ
2015/2023

የኮፒ ራይት መብት ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ነው።።
All rights reserved.
© Tariku Tefera
2015 ዓ.ም/2023 GC
ለጥያቄ ወይንም አስተያየት በ"tarikutefera2@gmail.com" የኢሜይል አድራሻ ያግኙን።።

.....

በእውቀት ላይ የተመሠረተ እምነት ከፀፀት ያድናል !!

.....

ይቺ መጽሐፍ የተዘጋጀችው የትኛውንም ኃይማኖት ለማንኳሰስ ወይንም ለማቆለጳጰስ ሳይሆን አዘጋጁ በኃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ በተፈጠረበትን ጥያቄ ምክንያት ገለልተኛ ሆኖ የሁሉንም ኃይማኖቶች መጽሐፍት በማጥናቱና በጥናቱ ውስጥም የተመለከተውን እውነት ለሌሎችም አስተማሪ ይሆናል በማለት ለማጋራት በማሰብ ብቻ ነው።።

<u>ማስታወሻ</u>

- ምዕራፍ አንድ ጠለቅ ያሉ ሳይንሳዊና መንፈሳዊ ትንታኔዎችን የያዘ ምዕራፍ በመሆኑ ይህንን መረዳት የሚከብዳችሁ ከምዕራፍ ሁለት ጀምራችሁ ማንበብ ትችላላችሁ፣
- በመጽሐፏ ውስጥ የተጠቀሱት የዘመን አቆጣጠሮች የቀረቡት በሁለት መንገድ ነው፣ ኢትዮጵያዊ ታሪኮች በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር የቀረቡ ሲሆን ዓለማቀፋዊ ታሪኮች ደግሞ የቀረቡት እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር ነው፣
- ከመጽሐፍ ቅዱሱ የተጠቀሱት ጥቅሶች የተወሰዱት ከ1954 ዕትም ሲሆን ጥቅሶቹንም ከመጽሐፍ ቅዱሱ ለመመልከት ምህፃረ ቃላቱ የሚወክሉትን ምዕራፍ በአባሪ 1/Annex I ክፍል ይመልከቱ፣
- ከቁርአኑ የተጠቀሱት ጥቅሶች የቀረቡት የምዕራፉን ቁጥርና የአንቀፅ ቁጥሩን በማስቀመጥ ሲሆን የምዕራፍ ቁጥሮቹ የሚወክሉት ምዕራፍ በአባሪ-2/Annex-II ክፍል ይመልከቱ፣
- መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቁርአን፣ ሀዲሳትን ... ማግኘት ያልቻላችሁ ከኢንተርኔት ላይ ሙሉውን መጽሐፍ Download አድርጋችሁ መጠቀም ትችላላችሁ።።

ማውጫ(Table of Contents)

መቅድም 5
1. ኤቲዝም ("ፈጣሪ አምላክ የለም" እምነት) 8
2. እስልምና 70
3. በተለያየ ምክንያት ከክርስትና የወጡ ኃይማኖቶች 168
   3.1. በፖለቲካ ምክንያት ከክርስትና የወጡ 168
      3.1.1. ዘመናዊው ዋቄፈና 169
      3.1.2. ራስ ተፈሪያን 182
   3.2. መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የራሳቸውን አስተምህሮ ጨምረው ከክርስትና የወጡ (ባኢ፣ ሞርሞን፣ የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን፣ ሺንቼኦንጂ፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒስት፣ ሂውማኒዝምና የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ) 186
4. ኦርቶዶክስ እና ካቶሊክ 195
5. ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት 321
   5.1. የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ("Only Jesus") 322
   5.2. የይሖዋ ምስክሮች (Jhova Witness) 344
   5.3. አድቬንቲስት(Adventism) 368
6. ፕሮቴስታንት 374
7. መጪው የአንድ ዓለም አንድ ኃይማኖት 419
ማጠቃለያ 433
አባሪ(Annex) 435

መቅድም

የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ፈፅሞ የሚለየው በአምላኪነቱ ነው፣ ሌሎች የሰው ልጅ ማንነቶች ብቻ የሚመስሉን እንደ ፍቅር፣ ርህራሄ፣ ተመራማሪነት ... የመሳሰሉት ማንነቶች በተወሰነ መጠን ይሁን እንጂ እንስሳቱም ጋር ይገኛሉ፣ ይህንንም እውነታ በቀላሉ በእንስሳት ሥነ ህይወት ላይ የተሰሩ ዶክመንተሪ ፊልሞችን በመመልከት ማረጋገጥ ይቻላል፣ "አምልኮ" የተባለችውን የሰው ልጅ ብቸኛ ማንነት ግን የትኛውም እንስሳ ጋር አናገኝም::

የሚገርመው ደግሞ ይህ የሰው ልጅ ብቸኛ ማንነት በሰው ልጆች መካከል ወጥነት የሌለው፣ እርስ በርስ የሚቃረንና ሰዎችን እስከ ማገዳደል የሚያዳርስ ጉዳይ ሆኖ ይታያል:: ይህ በእንዲህ እንዳለ ደግሞ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ከስነ ፍጥረት ሳይንሱ ጥናቶችና ከአንዳንድ ፈላስፎች ፍልስፍና በመነሳት አንዳንዶች ይህንን የሰው ልጅ ብቸኛ ማንነት ትክክል እንዳልሆነና [1] "ኃይማኖት የሰው ልጆች እድገት እንቅፋት ነው" እስከማለት ሲደርሱ ይታያል::

<u>እውነት አንድ ሆና ሳለ</u> የሰው ልጆች <u>የተለያየ መንገድ</u> የመከተላቸው እውነታ ደግሞ <u>አንዷን እውነት ከተረዳው ከአንዱ መንገድ ውጪ</u> **<u>ሌሎቹ መንገዶች በሙሉ የስህተት</u>** <u>መንገዶች መሆናቸውን ያሳያል</u>፣ ልክ 1+1=2 ወይንም =3 ወይንም =4 ... ወዘተ እንደማይሆነው ሁሉ አንዷን የእውነት መንገድ ከተከተለው ከአንዱ መንገድ ውጪ ያሉት ሌሎቹ መንገዶች በሙሉ ነገ ፀፀት ውስጥ የሚያስገቡ የኪሳራ መንገዶች እንደሆኑ ግልፅ ነው::

ለዚህች መጽሐፍም ዝግጅት ምክንያት የሆነው "እውነት አንድ ናት፣ ሰዎች በዚህች አንዷ እውነት ላይ የተለያዩት ይህቺ እውነት በተለያዩ ውሸቶች በመጋረዷ ምክንያት ነው፣ በዚህም ከየትኛውም ቡድን ገለልተኛ ሆኖ፣ የውሸት መጋረጃዎችን በመግለጥ አንዷን እውነት ማሳየት ይቻላል" ከሚል መነሻ ነው::

በዚህም መጽሐፏ ፈጣሪ አምላክ እንደሌለ የሚያስተምረውን የኤቲዝም ፍልስፍና እና "ፈጣሪ በኛ መንገድ ብቻ ነው የሚገኘው" የሚሉትን የኃይማኖት ተቋማትን አስተምህሮን በዝርዝር ተመልክታለች::

[1] ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት(1978)፣ **የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት**፣ ገፅ 325፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ

እዚህ ጋር የኃይማኖት ተቋማቱ አስተምህሮ የተለያየና ሰፋፊ በመሆናቸው ምክንያት የየቤተእምነቶቹን አስተምህሮ በደንብ ለመመርመር እንዲያመቸን በመጀመርያ ኃይማኖቶችን በየቡድናቸው ከፋፍለን እንመለከታለን፡፡ [2] በዓለም ላይ ከ4,300 በላይ የሚሆኑ ኃይማኖቶች እንዳሉ ቢነገርም፣ [3] በኃይማኖቶች ጥናት መሠረት እነዚህ ኃይማኖቶች በዋናነት በአምስት ይከፈላሉ፣

1. የአብርሃም ኃይማኖቶች - ክርስትና፣ እስልምና፣ ጁዳይዝም ...
2. የህንድ ኃይማኖቶች - ሂንዱይዝም፣ ቡድሂዝም፣ ሲኪዝም፣ ጃኒዝም...
3. የምስራቅ ኢሲያ ኃይማኖቶች - ኮንፊሺያኒዝም፣ ሺንቶይዝም፣ ታኦይዝም...
4. የኢራናውያን ኃይማኖቶች - ያዝዳኒዝም፣ ዞሮአስተሪአኒዝም፣ ያርሳኒዝም...
5. በየሀገራቱ ውስጥ የሚገኙ በየማኅበረሰቡ የተወሰኑ ባህላዊ ኃይማኖቶች

በመባል ይታወቃሉ፣ ይህ ብዛትም የምንፈልጋትን እውነት እንዳይጋርድብን፣ ለጊዜው የኤቲዝምን ፍልስፍናን ትተን፣ በአማኞች አዕምሮ ሆነን፣ ከነዚህ የኃይማኖት ቡድኖች ውስጥ ትክክለኛ ሊሆን የሚችለውን ቡድን ለይተን በማውጣት ከኤቲዝም አስተምህሮ ጋር እንመለከታለን፡፡

በዚህም በአማኞች አዕምሮ ሆነን ስንመለከት፣ "የሰው ዘር ከመነሻው ዋናውን አምላክ የሚያመልክበት አንድ ትክክለኛ ኃይማኖትን ሲከተል ነበረ ነገር ግን በሰይጣን፣ በሰው ልጆች ግጭት፣ ክፋት፣ ዝናና ነዋይ ፈላጊነት ... ምክንያት የተለያዩ አስተምህሮን የሚከተሉ የተለያዩ ኃይማኖቶች ተፈጠሩ" በዚህም "ዋናውን አምላክ" በትክክለኛው መንገድ የሚያመልከው አንዱ ኃይማኖት ብቻ ነው፡፡ ይህ ኃይማኖት ደግሞ የትኛው ነው? ወደሚለው ከመሄዳችን በፊት አሁንም በአማኞች አዕምሮ ሆነን አንድ ገዢ መስፈርት እናስቀምጥ፣

> "ትክክለኛዋ ኃይማኖት <u>የምታመልከው ዋናውን አምላክ</u> ሲሆን በዚሁ አምላክ በሚኖራት እገዛም ኃይማኖቷ <u>በአንፃራዊነት ዓለማቀፋዊ ናት</u>፡፡"

በዚህ መስፈርት መሠረትም ከላይ የተዘረዘሩትን ኃይማኖቶች ስንመለከት፣ በመጀመሪያ ላይ ያሉት የአብርሃም ኃይማኖቶች "የምናመልከው ዋናውን አምላክ ነው" ስለሚሉና በአንፃራዊነትም ዓለማቀፋዊ ኃይማኖቶች በመሆናቸው ምክንያት የአብርሃም ኃይማኖቶችን በጠቅላላ ለተጨማሪ ምርመራ እንወስዳቸዋለን፡፡

[2] www.thetravelalmanac.com>religion, www.theregister.com
[3] https://en.m.Wikipedia>wiki>major religion groups

ከአብርሃም ኃይማኖቶች ውጪ ያሉትን ሌሎቹን ኃይማኖቶች ስንመለከት ግን አብዛኞቹ ኃይማኖቶች የሚከተሉት በስራ ድርሻ የተከፋፈሉ አማልክትን እንጂ ዋናውን አምላክ አለመሆኑ ሌሎቹ ደግሞ “ዋናውን አምላክ ነው የምናመልከው” እያሉ ነገር ግን በአንድ ማኅበረሰብ ብቻ የተወሰኑና ዓለማቀፋዊ ዕይታ የሌላቸው ኃይማኖቶች መሆናቸውን ስንመለከት በዓለም ላይ ከ50% በላይ የሆነው ህዝብ ከሚከተላቸው ከአብርሃም ኃይማኖቶች ውጪ ያሉትን ኃይማኖቶች ለትክክለኛው ኃይማኖት ፍለጋችን መጠቀም አንችልም፡፡

ከባህላዊ ኃይማኖቶች ጋር በተያያዘ አንዳንድ ባህላዊ ኃይማኖቶች በዘመናዊው ፍልስፍና እየተደራጁና ከላይ የተመለከትናቸውን ሁለቱን መስፈርቶች በተለያየ ፍልስፍና ሲያሟሉ ይታያሉ፣ ሁሉንም ማየት ባይቻልም ለምሳሌ እንዲሆነን ከነዚህ ውስጥ ግዙፉንና አሁን በዘመናዊ መንገድ የተደራጀውን ዘመናዊውን ዋቄፈና እንመለከታለን፡፡

በዘመናዊው ዋቄፈና አስተምህሮ “ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ ነው፤ አይሁድ፣ ዓረብ … ዋናውን አምላክ በራሳቸው እሴት እንደሚያመልኩት አሮሞም ይህን አምላክ በራሱ እሴት ያመልካል፡፡” ይላሉ፣ በዚህም ዘመናዊው ዋቄፈና ከላይ ያስቀመጥናቸውን ሁለቱን መስፈርቶች ስለሚያሟላ ለዝርዝር ዕይታ እንወስደዋለን፡፡

በዚህም “ፈጣሪ አምላክ የለም” የሚለውን ኤቲዝምንና “ፈጣሪ አለ” ብለው ነገር ግን በተለያየ መንገድ እየሄዱ ያሉትን የአብርሃም ኃይማኖቶችንና ዋቄፈናን በቀጣይ ምዕራፎች በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

መልካም ንባብ !!

ምዕራፍ አንድ

1. <u>ኤቲዝም (“ፈጣሪ አምላክ የለም” እምነት)</u>

ኤቲዝም(Atheism) የሚለው ቃል የመጣው “Theo” ከሚል የግሪክ ቃል ሲሆን በግሪክ ቋንቋ “Theo” ማለት አምላክ ማለት ነው፣ “Theism” ማለት ደግሞ “በአምላክ መኖር ማመን” ሲሆን “Atheism” ማለት ደግሞ “በአምላክ መኖር አለማመን” ማለት ነው። Atheist(በአምላክ መኖር የማያምን ሰው) Theology(ስነ መለኮት)፣ Theocracy(የመንፈሳዊ ሰዎች አመራር) … የመሳሰሉ ቃላትም የወጡት ከዚሁ ከግሪኩ “Theo” ነው።

[4]“ኤቲዝም ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ኃይል ማለትም በአማልክት፣ በመናፍስት፣ ከሞት በኋላ ባለ ህይወት ማመንን የማይቀበል ፍልስፍና ነው። ኤቲዝም፣ ኃይማኖት እንዴት እንደመጣና ለምን እንደመጣ ከማስረዳቱም በላይ ዩኒቨርስን በሳይንሳዊ መንገድ በማጥናት የኃይማኖት ቀኖናዎችን ይነቅፋል። ኃይማኖት … ለሰው ልጅ እድገት እንቅፋት መሆኑንና እንዴትም መከሰም እንዳለበት ያስተምራል።”

በዚህ ምዕራፍም ይህን የኤቲዝም እምነት ከአጠቃላይ እውነታና ከአማኞች አስተምህሮ ጋር እያነፃፀርን እንመለከታለን። ከኃይማኖት ቡድኖች ውስጥ ለዋናው አምላክ ፍለጋችን ትክክለኛ የሚሆነን የአብርሃም ኃይማኖቶችንና ዋቄፈናን እንደወሰድነው ሁሉ፣ ከነዚህ ሁለቱ መንገዶች ደግሞ መጽሐፍ ያላቸው የአብርሃም ኃይማኖቶች በመሆናቸው፣ የአብርሃም ኃይማኖቶች ደግሞ የሚመሩት በዋናነት በቁርአንና በመጽሐፍ ቅዱሱ መሆኑና ቁርአኑ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱን የሚቀበል በመሆኑ ምክንያት (ቁርአን 2፡136, 3፡3, 4፡136, 29፡46 …) ለማነፃፀርያነት መጽሐፍ ቅዱሱን እንጠቀማለን።

ኤቲዝም “ፈጣሪ አምላክ የለም” የሚለው በቁስአካልነት ፍልስፍና(materialism)፣ በአመክንዮ (Reasoning) እና በስነ ፍጥረት ፅንሰ ሐሳብ (Creation Theory) ላይ ተመስርቶ ነው።

በዚህ ምዕራፍም እነዚህን የኤቲዝም ፍልስፍና መሠረቶችን እና የፈጣሪ አምላክ መኖርና አለመኖርን ገለልተኛ በሆነ መንገድ በስፋት እንፈትሻለን።

[4] **የማርክሲዝም ሌኒኒዝም መዝገበ ቃላት**፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፣ 1978፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ ገፅ 325

1.1. ቁስአካልነት (materialism)

[5] "Materialism is a form of philosophical monism which holds matter to be the fundanmental substance in nature and all things including mental state and consciousness as results of material interactions."

የቁስአካልነት ፍልስፍና ስለሁሉም ነገሮች ትንታኔ የሚሰጠው ሁሉንም ነገር በቁስነቱ በመመልከት ነው፣ ፍልስፍናው ቁሳዊ ያልሆኑ ክስተቶችን እንኳን የቁስ አካላት መስተጋብር አድርጎ ይመለከታል፣ ቁስአካልነት በዚህ ቁሳዊ ዕይታውም ፈጣሪ አምላክን ስለማያውቀው "ፈጣሪ አምላክ የለም" ይላል።

ይሁን እንጂ ይህ በቁስ ላይ የተንጠለጠለው የቁስአካልነት ፍልስፍና የፈጣሪንም መኖርና አለመኖር ለማረጋገጥ አቅም ያለው ፍልስፍና አይደለም።

ከመነሻው ስንመለከት ቁስአካል የሚለባው ነገር "fundanmental substance" አይደለም፣ ቁስአካል በራሱ የተገነባው ከአተም ነው፣ አተም ደግሞ ከኤሌክትሮን፣ ፕሩቶን... ነው፣ እነዚህ ደግሞ ከምን ተሰሩ? ሲባል ደግሞ ቁሳዊው ነገር ይቀርና ጉዳዩ የኃይልና የሞገድ ጉዳይ ብቻ ይሆናል፣ በዚህም ቁሳዊውን ነገር "መሠረታዊ" ብሎ የተነሳው ቁስአካልነት ፍልስፍና ከመሠረታዊው ነገር ባለመነሳቱ ድምዳሜውን መቀበል አይቻልም።

በመቀጠልም ቁስአካላዊነት (ፈጣሪ ካለ) በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል የሚኖረውን ልዩነት ከግምት ሳያስገባ ሁለቱንም በአንድ ዓይን የተመለከተ ፍልስፍና ነው። በመጀመርያ ፈጣሪ አምላክ ካለ ይህ ፈጣሪ ቁሳዊውን ፍጡር መፍጠር የሚችለው ከቁሳዊው ማንነት በላይ ሲሆን ብቻ ነው፣ ለምሳሌ ጀበና ጀበናን አይሰራውም፣ ጀበናን መስራት የሚችለው ከጀበና በላይ የሆነ ማንነት ያለው አካል ብቻ ነው፣ በዚህም ፈጣሪ ካለ ፈጣሪ ከቁሳዊው ማንነት በላይ ስለሚሆን ይህ ፈጣሪ በቁስአካልነት ዕይታ ሊጠና አይቻልም።

በመቀጠል ፈጣሪ ካለ ይህ ፈጣሪ ይህንን ዩኒቨርስ(ፅንፍ ዓለም) ሳይፈጥር በፊት ነበረ፣ በዚህም ይህ የዩኒቨርስ ፈጣሪ በዚህ ዩኒቨርስ አይገደብም፣ በዚህም የቁስአካልነት ፍልስፍና ስለ ፈጣሪ መኖርና አለመኖር መመራመር የሚችለው ከዩኒቨርሱ ውጪ መመልከት ሲችል ነው፣ ይህ ደግሞ የማይታሰብ ነገር ነው።

ቁስአካልነት እነዚህን ሦስቱን ከፍተቶች ወደጎን አድርጎ የፈጣሪን መኖርና አለመኖር ላይ የሚያደርገው ምርምር (ፈጣሪ ካለ) ፈጣሪ ጋር መድረስ ስለማይችል የጥናቱ ውጤትም አሁን ኤቲስቶች ጋር የምንመለከተው "ፈጣሪ የለም" እንደሚሆን ግልፅ ነው።

አማኞች የአምላክንና የመላዕክቱን ማንነት የሚገልፁበትን መንገድ ስንመለከት ደግሞ የሰው ልጅ ፈጣሪን ይቅርና መንፈሳዊ ፍጡራን የሆኑቱ መላዕክቱን እንኳን ሊያጠናቸው አይችልም፣ ለምሳሌ አንድ መልአክ ብቻውን 180,000 ሰዎችን በአንድ ጊዜ የመግደል

[5] https://en.m.Wikipedia>wiki>Materialism

አቅሙን(2ነገ.19፡35)፣ በሰው ልጅ የማይታሰበውን ከ6-27 ሚሊየን ^{o}C የሚያቃጥል የፀሐይ አካል ውስጥ መገኘት የመቻል አቅሙን(ራዕ.19፡17-18)፣ ከመሬት ስበት ነፃ ሆኖ መንቀሳቀስ የመቻል አቅሙን(መሳ.13፡20) ... ስንመለከት ዋናው ፈጣሪ ይቅርና ሁለቱ ቁሳዊና መንፈሳዊ ተፈጣሪዎች መካከል ያለው ልዩነት በራሱ ተነፃፃሪ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይም ስንመለከት፣ ቁስን "መሠረታዊ" አድርጎ የተነሳውና በፈጣሪን በተፈጣሪ መካከል ሊኖር የሚችለውን ልዩነት ከግምት ሳያስገባ የተነሳው የቁስ አካልነት ፍልስፍና የፈጣሪን ሀለዎት ለማጥናት አቅም የሌለው ፍልስፍና መሆኑን እንመለከታለን፡፡

1.2. <u>አመክንዮ(Reasoning/Logic)</u>

አመክንዮ) የሚለው ቃል ቀጥታ ትርጉሙ "ምክንያታዊነት" ማለት ሲሆን በፍልስፍና ሳይንሱ ደግሞ አመክንዮ ማለት "ማሰላሰልና እውነትን መፈለግ" የሚል ትርጉም አለው፣ በዚህ ክፍልም የምንመለከተው ከፈጣሪ ሀለዎት ጋር የተያያዘውን የኤቲዝምን አመክንዮ ነው፡፡

ኤቲዝም ከተለያዩ አመክንዮዎች በመነሳት "ፈጣሪ አምላክ የለም" ይላል፣ እነዚህ አመክንዮዎችም በዋናነት የተመሠረቱት በዓለም ላይ ያሉትን ችግሮችን በመመልከት "ፈጣሪ ቢኖር ኖሮ እነዚህ ችግሮች ባልኖሩ ነበረ" ከሚል መነሻ ነው፣ እንደ ኤቲዝም አመክንዮ "ፈጣሪ አምላክ ቢኖር ሰዎች እኩል ሊሆኑ፤ በዓለም ላይ ፍትህ፣ ሠላም ... ሊሰፍን፤ በዓለም ላይ ስቃይና መከራ ላይኖር፤ ፈጣሪ ለሰዎች በግልፅ ሊታወቅ፤ ኃይማኖት አንድ ብቻ ሊሆን፤ ሲኦል ላይኖር ... በተገባ ነበረ፡፡" ይላሉ፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የኤቲዝም አመክንዮ ሁለት መሠረታዊ ስህተቶችን ይዟል፣ በመጀመሪያ ይህ አመክንዮ የተሰጠው "ፈጣሪ መልካም ነው፣ ትክክል ነው፣ አይሳሳትም፣ ይወደናል ..." በመሳሰሉ የአማኞች አስተምህሮ ላይ ተመስርቶ የተሰነዘረ ተቃራኒ አመክንዮ እንጂ ራሱን የቻለ አመንክዮ አይደለም፣ "ፈጣሪ አምላክ የለም" መባል የነበረበት ግን የፈጣሪ አምላክን አለመኖር በሚያስረዳ መልኩ እንጂ በአማኞች እምነት ላይ ተንተርሶ መሆን የለበትም፣ ለምሳሌ አማኞች የሚሉትም ስህተት ቢሆንና ፈጣሪ ኃይማኖትን አልፈጠረም ቢሆን ወይ ፈጣሪ ፍጥረታቱን ፈጥሮ ትቷቸው ቢሆን ወይ እየቀጣቸው ቢሆን... ይህ በአማኞች አመክንዮ ላይ ተመስርቶ የተሰነዘረው "ፈጣሪ አምላክ የለም" አመክንዮ ስህተት ይሆናል፡፡

በመቀጠል ኤቲዝም ከመጥፎው የዓለም ገፅታ በተቃራኒ ያሉትን ለምሳሌ ፍቅር፣ ደስታ፣ ህይወት ... የመሳሰሉትን በመመልከት "ፈጣሪ አምላክ አለ" ባይልም፣ እንደ አጠቃላይ እውነታ ግን የዓለም መልካምም ሆነ መጥፎ ገፅታ የፈጣሪ አምላክን ሀለዎት ገላጭ ነገሮች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ፈጣሪ ካለ ይህ ፈጣሪ ፍጥረታቱን የፈጠረው ለራሱ ጥቅም ሲል ነው፣ በዚህም ይህ ፈጣሪ፣ ልክ እንደ ሸክላ ሰሪ፣ አንዱን ለሳሎን ጌጥ፣ አንዱን

ለውሀ መያዣነት፣ አንዱን ለማብሰያት፣ አንዱን ለጌጥ … የመፍጠር ሙሉ መብት አለው፣ በዚህም ለጌጥም ይሁን ለውሀ መያዣነት ይሁን ለማብሰያነት … የተሰራውን ሸክላ በመመልከት ብቻ "ሸክላ ሰሪ የሚባል አካል የለም" ወይንም "ሸክላ ሰሪ የሚባል አካል አለ" ማለት እንደማይቻለው ሁሉ የዓለምን መልካምም ሆነ መጥፎ ገፅታ በመመልከት ብቻ "ፈጣሪ አምላክ አለ" ወይንም "ፈጣሪ አምላክ የለም" ማለት አይቻልም፡፡

በዚህም ኤቲዝም "ፈጣሪ አምላክ የለም" ያለበት አመክንዮ የፈጣሪ አምላክን መኖርና አለመኖር የማስረዳት አቅም የለውም፡፡ ኤቲዝምም በነዚህ የአመክንዮ ክፍተቶች ውስጥ የፈጣሪን ሀለዎት እያጠና ያለበት መንገድ ፈጣሪ ጋር መድረስ ስለማይችል ውጤቱ አሁን የምንመለከተው "ፈጣሪ አምላክ የለም" እንደሚሆን ግልፅ ነው፡፡

1.3. <u>የስነፍጥረት ፅንሰ ሐሳቦች (Creation Theories)</u>

ኤቲዝም "ፈጣሪ አምላክ የለም" የሚልበት ሦስተኛው ማስረጃው የስነፍጥረት ፅንሰ ሐሳብ (Creation Theory) ነው፣ ዋነኞቹ፣ ዓለማቀፍ ተቀባይነት ያገኙትና በዚህ ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ በተለያየ መንገድ እየተደገፉ መጥተው አሁን ያለ ተወዳዳሪ ብቸኛ ሆነው የሚገኙት የስነፍጥረት ፅንሰ ሐሳቦችም፡-

- የዩኒቨርስ/ፅንፈ ዓለም (መሬት፣ ፀሐይ፣ ከዋክብት …) አፈጣጠርን የሚያስረዳው - <u>የታላቁ ፍንዳታ/የቢግ ባንግ ፅንሰ ሐሳብ (Big Bang Theory)</u>
- የህይወታዊው ስነፍጥረት አፈጣጠርን የሚያስረዳው - <u>የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ (Evolution Theory)</u>

እና የነዚህ ፅንሰ ሐሳቦች የቀኝ እጅ የሆነውን የ"Age Dating" ቴክኒክ ሲሆኑ እነዚህን ፅንሰ ሐሳቦችም ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡፡

1.3.1. <u>የታላቁ ፍንዳታ/የቢግ ባንግ ፅንሰ ሐሳብ (Big Bang Theory)</u>

ኤቲዝም ቁሳዊ ፍጥረታት የተፈጠሩት በቢግ ባንግ እንደሆነ ያስተምራል፣ የቢግ ባንግ ፅንሰ ሐሳብ ለመጀመርያ ጊዜ የቀረበው በ1931 ዓ.ም Georges Lemaitre በተባለ ቤልጂየማዊው የካቶሊክ ቄስ ነበረ፡፡ በፅንሰ ሐሳቡ መሠረትም በከፍተኛ እፍጋት(Density) እና ሙቀት ውስጥ የነበረ ፖይንት ማስ(point mass/Initial Singularty) [6] "ከ13.8 ቢሊየን አመታት በፊት በገጠመው የፍንዳታና የመለጠጥ ሂደት ይህ ዩኒቨርስ(መሬት፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት …) ተፈጠረ፣ የፍንዳታው አካላትም በአንድ በኩል በፍንዳታው ጉልበት በተቃራኒው ደግሞ በግራቪቲ ጉልበት መካከል ባለው መስተጋብር ዩኒቨርሱ ይህንን መልክ ያዘ" ይላል፡፡

[6] https://en.m.Wikipedia>wiki>Universe

ለዚህ ፅንሰ ሐሳብ ዋነኛ መነሻ የሆነው ዩኒቨርሱ በየጊዜው እየተለጠጠ ያለበት እውነታ፣ ይንንም የመለጠጥ ሂደት Replay ሲደረግ ሁሉም ነገር ወደ አንድ መነሻ ነጥብ የሚሄድበት እውነታ እና ይህንን የዩኒቨርሱን የመለጠጥ ሂደት በአንስታየን የአንፃራዊነት ቀመር ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑ ነው።።

ፅንሰ ሐሳቡ የዩኒቨርስን አፈጣጠር ለማስረዳት ይነሳ እንጂ ስለ ስነፍጥረት ሙሉ የሆነ ትንታኔ ግን አይሰጥም፣ "ፖይንት ማስ ከየት መጣ?" ለሚለው ጥያቄ ምንም መልስ የለም፣ ይባሱኑ ደግሞ የስነ ፍጥረት ሳይንሱ ስለዚህች ሰማይና ምድርን ፈጠረች ስለተባለች ፖይንት ማስ መጠነ ቁስ ሲናገር [7] "አንዳንዶች የዩኒቨርስ መነሻ ዲያሜትር ከፕሮቶን ዲያሜትር አንድ ትሪሊዮንኛ እንደሆነ ሲገልፁ ሌሎች ደግሞ ምንም ቁስ አካል እንዳልነበረ ይገልፃሉ፣ አልበርት አንስታየንም የዩኒቨርስ ዲያሜትር ዜሮ እንደነበረ ይናገራል።" ይህ እውነታ ደግሞ የቁስአካል መነሻ ከቁስ አካልነት ውጪ ያለ አካል መሆኑን ነው የሚያሳየው።።

[8] የቀደመው የቢግ ባንግ የጥናት ዘዴ (Classical Cosmology/Particle Physics)፣ በአንስታየን የአንፃራዊነት ቀመር ላይ ተመስርቶ፣ የቢግ ባንግን ሂደት በቀመርና በቁጥር አስደግፎ ይተንትን እንጂ የቢግ ባንግን አጀማመር ግን በአግባቡ መግለፅ አልቻለም፣ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ፖይንት ማስ የተባለችው ነገር የቁስ ማንነት የሌላት በመሆኑ ምክንያት ነው።። በዚህም ለቢግ ባንግ አጀማመር መነሻ የሆነችውን ፖይንት ማስ ምንነት ለመግለፅ አልበርት አንስታየንን ጨምሮ ሁሉም ሳይንቲስቶች የተጠቀሙት የኳንተም ኮስሞሎጂን ነው፣ ይህም የጥናት ዘዴ የስነ ፍጥረት ትንታኔውን የሚሰጠው በፖይንት ማስ ቁስ ማንነት ላይ ተመሥርቶ ሳይሆን በፖይንት ማስ የሞገድ/ኃይል ማንነት ነው።።

በዚህም ኳንተም ኮስሞሎጂ ከቢግ ባንግ በፊት ቁስ እንዳልነበረና አሁን የምነመለከተው ቁስ የመጣው ከኃይል እንደሆነ ይናገራል ይሁን እንጂ የዚህ ኃይል ምንጭ

---

[7] ሰለሞን ዮሐንስ(2007)፣ **የሳይንስ ኑዛዜ**፣ ገፅ 13

[8] Quantum Cosmology is the attempt in theoretical physics to develop a quantum theory of the Universe. This approach attempts to answer open questions of classical physical cosmology, particularly those related to the first phases of the universe.

Classical Cosmology is based on Albert Einstein's general theory of relativity, which describes the evolution of the universe very well, as long as you don't approach the Big Bang.

In Quantum Cosmology, the Universe is treated as a wave function instead of classical spacetime. (In physics, spacetime is any mathematical model which fuses the three dimensions of the space and the one dimension of time into a single four dimensional manifold) https://en.m.Wikipedia>wiki>QuantumCosmology

ለሳይንሱ አሁንም ተመልሶ ሌላ ከባድ ጥያቄ ቢሆንበትም፣ ይህ ግኝት ግን ከፊል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታን ይዟል፣ መጽሐፍ ቅዱሱ፣

ዕብ.11፡3 "... <u>የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ</u> ..."

ይላል፣ መጽሐፍ ቅዱሱ "የቁሳዊው ነገር መነሻ "ሁን" ሲል ማድረግ የሚችል ኃይል ያለው ቃል እንጂ ቁስ አይደለም" ሲለን፣ ፅንሰ ሐሳቡም ቁሳዊው ፍጥረት የመጣው ከኃይል እንደሆነ ይነግረናል።።

ስለዚህ ቢግ ባንግ ስነፍጥረትን ለመግለፅ ሲነሳ ፍልስፍናው መነሻ ማድረግ የነበረበት፣ እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ፣ ይህ ቁሳዊ ዓለም እንዲፈጠር ምክንያት ከሆነው ከቁስአካልነት ውጪ ካለው አካል እንጂ ከውጤቱ ከቁሳዊው ነገር መሆን አልነበረበትም፣ በዚህም የቢግ ባንግ ፅንሰ ሐሳብ ከመነሻው ያልተነሳ ፍልስፍና በመሆኑ ፅንሰ ሐሳቡ የስነፍጥረትን መነሻ መግለፅ አይችልም፣ በዚህም ይህንን ፅንሰ ሐሳብ መሠረት አድርጎ የተሰራው "ፈጣሪ አምላክ የለም" አስተምህሮ የተሳሳተ መሆኑን እንመለከታለን።።

1.3.2. <u>የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ (Evolution Theory)</u>

ኤቲዝም ህይወታዊ ፍጥረት የተፈጠረው በዝግመተ ለውጥ ሂደት እንደሆነ ያስተምራል።። የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብን ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው ቻርለስ ዳርዊን የተባለ በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ገዳም ውስጥ የሚኖር መነኩሴ በ1859 ባሳተመው "Origion of Species" በሚባለው መጽሐፉ ነው።።

በፅንሰ ሐሳቡ መሠረት "በመጀመሪያ በአንድ ኩሬ ውስጥ እንደ ኢጋጣሚ የተገኙ ማዕድናት አሚኖ አሲድ ሰሩ፣ አሚኖ አሲዱም(ፕሮቲን) እንደ ኢጋጣሚ በመሰባሰብ በድንገት ሲንግል ሴል ባክቴሪያን አስገኘ፣ ይህቺ ባክቴሪያም በመራባትዋና በዘሮቿ ላይ በሚሊዮን አመታት ውስጥ በተከሰቱት ዝግመተ ለውጣዊ ሂደቶች ምክንያት አሁን የምንመለከታቸው የተለያዩ ህይወታዊ ፍጥረታት ተገኙ።።"

ነገር ግን ፅንሰ ሐሳቡን በዝርዝር ስንመለከት ፅንሰ ሐሳቡ ፡-

- ከመጀመሪያ ያልተነሳ፣
- የህይወት ጅማሬን መግለፅ ያልቻለ፣
- የትውልድን ቀጣይነት መግለፅ ያልቻለ፣
- ሽግግራዊ ቅሪቶች ወይንም ፍጥረታት ያላገኘ (missing link)
- ከሰው ልጅ ስነ ተፈጥሮ ጋር አብሮ የማይሄድ ሆኖ እንመለከተዋለን

ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፣

1. ፅንሰ ሐሳቡ ከመጀመሪያው ያልተነሳ መሆኑ

ፅንሰ ሐሳቡ ቀለል አድርጎ "እንደ ኢጋጣሚ ማዕድናት ተሰበሰቡ ከዚያ አሚኖ አሲድ ሰሩ፣ አሚኖ አሲዱም ባክቴሪያን አስገኘ ..." ይበል እንጂ፣ ዛሬ ላይ ሲንግል ሴል ባክቴሪያን ቻርለስ ዳርዊን ከተመለከተበት ማይክሮስኮፕ በረቀቀ ማይክሮስኮፕ ስንመለከት የሲንግል ሴል ባክቴሪያ አካል የአሚኖ አሲድ(ፕሮቲን) ስብስብ ብቻ አለመሆኑና በባክቴሪያ ሰውነት ውስጥ ከተለያዩ ነገሮች የተሰሩ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎች መኖራቸው ነው፣ በዚህም ባክቴሪያን በአሚኖ አሲድ ብቻ የገደበው ፅንሰ ሐሳብ ከመነሻው የተሳሳተ ፅንሰ ሐሳብ ነው::

በመቀጠል ደግሞ በማንኛውም ሴል ውስጥ የሚገኙት አካላት ዝም ብለው አይገነቡም፣ እነዚህ አካላት የሚገነቡት አስቀድሞ በሚፈጠር ዘረመል(DNA/RNA) በሚባል ማዘዣ ጣብያ ፕሮግራም መሠረት ነው:: በዚህም "የህይወት መጀመሪያ ናት" የተባለችው "ሲንግል ሴል ባክቴሪያ" ከመፈጠሯ በፊት ዘረመል ቀድሞ ሊኖር ይገባል፣ ከዚያም ይህ ዘረመል የባክቴሪያዋ አካላቶች የሚገነቡበትን ሂደት ይመራል::

በዚህም የዳርዊን ባክቴሪያ እውነት ብትሆን እንኳን ስለ ባክቴሪያዋ አፈጣጠር ጥናት መጀመር ያለበት የባክቴሪያዋ የሰውነት ክፍሎችን ግንባታ ከሚመራው ዘረመል ስነፍጥረት አጀማመር እንጂ በዘረመሉ ፕሮግራም አማካይነት ከተገነቡት የሰውነት ክፍሎች መሆን የለበትም፣ "ፕሮግራም" ደግሞ ቁስአካል ባለመሆኑ በዝግመተ ለውጥ ሕግ አይመራም፣ ስለዚህ የህይወታዊውም ስነፍጥረት መነሻ ከቁስአካልነት ክልል ውጪ የሆነ አካል(ፕሮግራመር) መሆኑን እንመለከታለን::

ይህም እውነታ የሚያሳየን የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ ከመጀመርያ ያልተነሳ ፅንሰ ሐሳብ መሆኑን ነው::

2. የህይወት ጅማሬን መግለፅ አለመቻል

ዝግመተ ለውጥ የቁሳዊ ፍጡራንን አፈጣጠር በተለያዩ ፅንሰ ሐሳቦችና መላምቶች ያስረዳ እንጂ ቁሳዊ ስላልሆነችው "ህይወት" ስለምትባለዋ ነገር አጀማመር ግን ምንም አይናገርም፣ ባክቴሪያዋን የሰሩት ቁሶች ዝም ብለው ተሰባሰቡ ብንል እንኳን፣ "ቁስ ያልሆነችው ህይወት በአሚኖ አሲዱ ክምችት ውስጥ እንዴት በቀለች?" ለሚለው ጥያቄ ዝግመተ ለውጥ ምንም መልስ የለውም::

ዛሬ ባለው ዘመናዊው ላብራቶሪ አሚኖ አሲድን ማምረት ይቻላል ነገር ግን አሚኖ አሲዱ በተፈለገው መንገድ፣ የተፈለገውን ያህል መጠን ይመረት እንጂ መስራት የሚቻለው የአሚኖ አሲድ ክምር እንጂ በውስጡ ህይወትን ማብቀል አይቻልም:: የኬሚካል ሂደት የሚፈጥረው ሌላ የኬሚካል ሂደትን እንጂ የኬሚካል ሂደት በምንም መልኩ ባዮሎጂካል ማንነት መፍጠር አይችልም::

ዛሬ ላይ ሳይንስና ቴክኖሎጂው በተራቀቀበት እስከ ሌላ ዓለማት ድረስ ከፍ ተብሎና እስከ አተምና ፎቶንስ ደረጃ ተወርዶ ምርምር በሚደረግበት ዘመን፣ በናኖ ቴክኖሎጂ በአተምና ሞሌኪውል ላይ ለውጥ በማድረግ በአዕምሮ የማይታሰቡ ነገሮች እየተፈበረኩ ባለበት ዘመን፣ በተፈጥሮ ያልነበሩን ኢለመንቶች እስከመፍጠር በተደረሰበት ዘመን፣ የብዙ ዘመናት የኬሚካል ሂደትን በአጭር ጊዜ የሚቋጩ ካታሊስቶች ተፈብርከው በሚገኙበት ዘመን፣ በጂኔቲክ ኢንጅነሪንግ ቴክኖሎጂ ዘረመል ኤዲት እየተደረገ አስደናቂ ነገሮች እየተፈጠሩ ባለበት ዘመን፣ በላብራቶሪዎች አሚኖ አሲድ ማምረት እየተቻለ በውስጡ ግን ህይወትን ማብቀል አልተቻለም።።

ይህ የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ የህይወትን ጅማሮ ላይ ምንም ማለት አለመቻሉና ይህንን መሠረታዊ እውነታ ዘሎ ማለፉ የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ ምናባዊ እንጂ እውነተኛ እንዳይሆን አድርጎታል።።

3. <u>የትውልድን ቀጣይነት መግለፅ አለመቻል</u>

የስነፍጥረት ሳይንሱ የመጀመሪያዋ ህይወት አበቃቀል ላይ ዝም ቢልም፣ ይህቺ ብቻዋን የበቀለች ህይወት(ባክቴሪያ) ከተፈጠረች በኋላ ደግሞ እንዴት ሌሎችን ማምጣት ቻለች? የሚለው ጥያቄ ደግሞ የፅንሰ ሐሳቡ ሌላው ፈተና ነው፣ ይህቺ ሲንግል ሴል ባክቴሪያ ምግብና መጠጥም በተሟላበት፣ መመገብም እንዳለባት በምታውቅበት፣ ለመመገብም አቅም ባላትና ምንም አደጋ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ ብትኖር እንኳን መሰሎቿን ማምጣት ካልቻለች ሞታ በዚያው በመቅረት የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳቡን ውድቅ ታደርጋለች።።

ፍጥረታት የሚራቡት በሁለት መንገድ ነው፣ በሴክሹዋልና አሴክሹዋል የመራቢያ መንገድ፣ ባክቴሪያ አካባቢ ያለው የመራቢያ መንገድ ባክቴሪያው በማዮሲስ/ማይቶሲስ ሕግ እየተከፈለ የሚሄድበት የአሴክሹዋል የመራቢያ ስርዓት ነው፣ ይህ ስርዓት ደግሞ የሚመራው በባክቴሪያው የዘረመል ፕሮግራም ነው፣ ይህ ደግሞ ከላይ እንደተመለከትነው ቁስአካላዊ ነገር ባለመሆኑ የዳርዊን ባክቴሪያ በቁስ አካላዊነት ሳይንሱ መሠረት የምትራባበት መንገድ የለም፤ በዚህ ላይ ደግሞ የባክቴሪያ ዕድሜ(life span) አጭር መሆኑ የባክቴሪያዋ ህይወት በሚሊዮኖች ከሚያስበው የኢቮሉሽን አቆጣጠር ጋር አይገጣጠምም፣ ለባክቴሪያ "ህይወት መጣችና ሄደች" ቅፅበታዊ ነገር ነው።።

በዚህም ፅንሰ ሐሳቡ የአንድ ባክቴሪያ ህይወት ይዞ ድርሰቱን ይጀምር እንጂ ህይወት ከዚህች ባክቴሪያ ወደ ሌሎች ቀጣይ ባክቴሪያዎች መተላለፍ የቻለበትን መንገድ መግለፅ አለመቻሉ ፅንሰ ሐሳቡን ባዶ ያደርገዋል።።

4. <u>ሽግግራዊ ቅሪቶች ወይንም ፍጥረታት ያላገኘ መሆኑ(missing link)</u>

የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ ጀማሪው ዳርዊን ሲናገር "የዝግመተ ለውጥ ሕግ ትክክለኛ የሚሆነው የሽግግር ፍጥረታት ሲገኙ ነው" ይላል፣ ይህን በምሳሌ ብንመለከት፣ በዝግመተ ለውጥ ሂደት የውሀ እንስሳት ወደ ምድራዊው እንስሳት የመለወጥ ሂደት ውስጥ

በውሀም በምድርም መኖር የሚችል “የሽግግር” እንስሳ/ቅሪት መኖር አለበት፣ ይህም እንስሳ ለምሳሌ መሬት ላይ በሳንባው እየተነፈሰ ውሀ ውስጥ ሲገባ ደግሞ በጊሉ “gills” የሚተነፍስ ወይ በሰማይ እንደልቡ ሲበር ውሎ ውሀ ውስጥ ገብቶ የሚተኛን ፍጥረት እንደማለት ነው፣ ይህ ደግሞ በውኑም በቅሪትም የለም።

ይባሱኑ ደግሞ ዳርዊን “ሽግግራዊ ፍጥረታት በሁለቱም ስፍራዎች/ሁኔታዎች መኖር የሚችሉ ፍጥረታት በመሆናቸው ቅሪተ አካላቸው ከሌሎቹ ፍጥረታት በብዛት መገኘት አለበት” ይላል፣ እውነታውን ስንመለከት ግን በተቃራኒው ነው፣ እነዚህን ሽግግራዊ ቅሪቶች በጥቂትም ማግኘት አልተቻለም፣ ይህ እውነታ ደግሞ የዳርዊንን የስነ ፍጥረት ፍልስፍናን ፅንሰ ሐሳብ ያፈርሳል።

ይህ የሽግግራዊ ፍጥረታት አለመኖር እውነታም “missing link” የዳርዊን ፅንሰ ሐሳብ ባዶ ያደርገዋል።

5. <u>ከሰው ልጅ ስነተፈጥሮ ጋር አብሮ የማይሄድ መሆኑ</u>

የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ ፍጥረታት ለምን እንደሚለያዩ የሚተነትንበት ሌሎች ደጋፊ ፅንሰ ሐሳቦች አሉት፣ ይህም “Survival of the fittest”(ለተፈጥሮ ምቹ የሆነው ብቻ የሚኖርበት)፣ “Adaptation”(ራስን ከተፈጥሮ ለውጥ ጋር ማመሳሰል)፣ “Mutation”(ከተፈጥሮ ለውጥ ጋር አብሮ መለወጥ) … ሲሆኑ እነዚህ ፅንሰ ሐሳቦችም በህይወታዊ ፍጥረታቱ መካከል ያለውን ልዩነት እንደሚያብራሩ የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ ይነግረናል።

ነገር ግን እነዚህን ፅንሰ ሐሳቦች የሰው ልጅ ያለበት “የአኒማል ኪንግደም” ጋር ስናመጣው የሰው ልጅ ስነተፈጥሮ ከነዚህ ደጋፊ ፅንሰ ሐሳቦች ጋር ተቃራኒ ሆኖ ነው የምንመለከተው፣ ለምሳሌ፦

- የሰው ልጅ ካለበት የአኒማል ኪንግደም ፍጥረታት በተለየ ሰውነቱ በላባ፣ በፀጉር ወይ በእስኬል(ሽካራ ቅርፊት) የተሸፈነ አይደለም፣ የሰው ልጅ እነዚህን ጠቃሚ የሰውነት መሸፈኛዎችን ያላበቀለው ወይንም አብቅሎ ከሰውነቱ ላይ የጠፋው ለየትኛው የዝግመተ ለውጣዊ ጥቅም እንደሆነ ፅንሰ ሐሳቡ ባይነግረንም፣ የሰው ዘር ግን በዱር ሲኖር እነዚህን መሸፈኛዎች ከብርድ፣ ከትንኞች ንክሻ … የሚከላከሉ በመሆናቸው አብቅሎ መተው ይቅርና እንደ ፅንሰ ሐሳቡ ባያበቅል እንኳን ሊያበቅል የሚገባ እንስሳዊ አካላት ነበሩ።

  በዚህ ላይ ደግሞ የሰው ልጅ ከሁሉም እንስሳት በተለየ አንድ ራሱን የሚከላከልበት፣ የሚያጠቃበት፣ የሚያመልጥበት … የተለየ አካል የለውም፣ እንደ እባብ መናደፊያ፣ እንደ አንበሳ አደገኛ ጥርስ፣ እንደ ጅብ ጉልበት፣ እንደ ነብር አደገኛ ጥፍር፣ እንደ ሚዳቋ የሩጫ ክህሎት፣ እንደ ዝንጀሮ ከዛፍ ዛፍ ዘሎ የሚያመልጥበት ክህሎት፣ እንደ አሞራ ወደ ሰማይ የሚነሳበት … እንስሳዊ አካላት የሉትም።

የሰው ልጅ እንደሌሎቹ ህይወታዊው ፍጡራን በዝግመተ ለውጡ “Survival of the fittest” (ለተፈጥሮ ምቹ የሆነ ብቻ የሚኖርበት) አሰራር የመጣ ቢሆን ኖሮ የሰው ልጅ እነዚህን አካላትና ከህሎቶች በማጣቱ ምክንያት በእንስሳቱ መካከል ተወዳዳሪ ሆኖ መኖር የማይችልና በሂደት ከምድር ገፅ የሚጠፋ ፍጡር በሆነ ነበረ፣ ነገር ግን ይህ አልሆነም፣ የሆነው የዚህ ተቃራኒው ነው፡፡ የሰው ልጅ እነዚህን እንስሳዊ ሰውነት መሸፈኛ፣ አካልና ከህሎት ሳይኖረው <u>ሳይጠፋ ከእንስሳቱ በላይ በዝቶ መገኘቱ</u> የሰው ልጅ ስነተፈጥሮ ከእንስሳቱ ስነተፈጥሮ ጋር የሚታይ አለመሆኑን ያሳየናል፡፡

- እንስሳቱ በሙሉ የሚያስቡበት አዕምሮ ቢኖራቸውም የሰው ልጅ አዕምሮ ስነፍጥረት ግን ከእንስሳቱ አዕምሮ እጅግ የተለየ ነው፣ በአዕምሮ ስነፍጥረት ለሰው ልጅ ትንሽም ቢሆን ተቀራራቢነት ያለው እንስሳ የለም፣ የሰው ልጅ ከእንስሳቱ ጋር በዝግመተ ለውጡ ሂደት ውስጥ በነበረ ኖሮ በዝግመተ ለውጡ “ለሰው ልጅ የቅርብ ናቸው” የተባሉት ቺምፓዚዎች አዕምሮ ላይ ከሰው አዕምሮ በጥቂቱ ያነስ አስተሳሰብ እንኳን በተመለከትን ነበረ፣ በዚህም ለምሳሌ የሰው ልጅ ዘመናዊ መኖርያ ቤት፣ አውሮፕላን … ሲሰራ እነሱ ቢያንስ ዳስ የመሰለ ነገር ወይ በእጅ የሚገፋ ጋሪ መስራት መቻል ነበረባቸው ወይ እንደ የጥንቱ የሰው ልጅ የጋርዮሽ አኗኗር ሌሎችን እንስሳት ሲያላምዱ መታየት ነበረበት፣ ነገር ግን ይህ አልሆነም፣ ቺምፓዚ ላይ ከእንስሳቱ የተለየ አስተሳሰብና የኑሮ ሁኔታ አንመለከትም፡፡

  ይህ የሰው ልጅ ፍፁም ልዩነት የሚያሳየው የሰው ልጅ ስነፍጥረት ከእንስሳቱ ስነፍጥረት ጋር የሚታይ አለመሆኑን ነው፡፡

እነዚህ የሰው ልጅ ስነተፈጥሮ ከዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳቦች ጋር አለመተዋወቅና ይባሱኑ መቃረን፣ የሰውን ልጅ ስነተፈጥሮ ከእንስሳቱ ስነተፈጥሮ ፈፅሞ የተለየ መሆኑንና የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ “ትክክል ነው” ብንል እንኳን የሰው ልጅ እንደ እንስሳቱ በዝግመተ ለውጥ ሂደት አለመምጣቱን እንመለከታለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱና የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ ስለ ስነተፈጥሮ በሚሰጡት ትንታኔ አንድ የሚሆኑባቸው ስፍራዎች አሉ፣ ለምሳሌ ዝግመተ ለውጡ እንደሚለው፣ መጽሐፍ ቅዱሱም፣ በውሀ ውስጥ የሚኖሩት፣ በአየር ላይ የሚበሩትና ምድራዊ እንስሳትን እግዚአብሔር በቀጥታ እንዳልፈጠራቸውና ሌሎች ፍጡራን እንዲፈጥሩአቸው እንዳዘዘ ይናገራል፣

- ዘፍ.1፡20-ውሀ በውሀ ውስጥና በአየር ላይ የሚበሩትን እንድታስገኝ አዘዘ
- ዘፍ.1፡24 - ምድርም የምድር እንስሳትን እንድታወጣ አዘዘ

በዚህም ከሰው ውጪ ባሉት ህይወታዊ ፍጥረታት አፈጣጠር ላይ የዝግመተ ለውጥና የመጽሐፍ ቅዱሱ ትንታኔ በተወሰነ መጠን ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡

ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው የሰው ልጅ በአካላዊ አፈጣጠሩና በአስተሳሰቡ ከእንስሳቱ ፍፁም ልዩ መሆኑና ተመልሶ ደግሞ እንስሳቱ ላይ ገዢ መሆኑ፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ደግሞ ሰዎች የተፈጠሩት እንስሳት በተፈጠሩበት መንገድ ሳይሆን በሌላ መንገድ እንደሆነ መናገሩና የሰው ልጅም የተፈጠረው ፍጥረታቱን እንዲገዛ እንደሆነ መናገሩ(ዘፍ.1፡26, ዕብ.2፡7...)፣ የሰው ልጅ ስነፍጥረትን በአግባቡ የተገለፀው በዝግመተ ለውጡ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱሱ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም የሰው ልጅ ተፈጥሮን በዝግመተ ለውጥ ፍልስፍና መተንተን የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብን ባዶነት የሚያሳይና የመጽሐፍ ቅዱሱን ቃል የሚያጠናክር እውነታ ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳብ ከመጀመሪያ አለመነሳቱ፣ የህይወት ጅማሬን መግለፅ አለመቻሉ፣ የትውልድን ቀጣይነት መግለፅ አለመቻሉ፣ "በብዛት መገኘት አለባቸው" የተባሉትን ሽግግራዊ ቅሪቶች ማግኘት አለመቻሉና ፅንሰ ሐሳቡ ከሰው ልጅ ስነተፈጥሮ ተቃራኒ መሆኑን ስንመለከት ፅንሰ ሐሳቡ ህይወታዊውን ስነፍጥረት መግለፅ የማይችል መሆኑንና በዚህ ፅንሰ ሐሳብም ላይ የተመረኮዘው "ፈጣሪ አምላክ የለም" የሚለው አስተምህሮ የተሳሳተ አስተምህሮ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

1.3.3. የኤቲዝም የስነ ፍጥረት ፅንሰ ሐሳቦች ቀኝ እጅ - Age Dating

የስነ ፍጥረት ሳይንሱ ከላይ የተመለከትነውን የዝግመተ ለውጥንና የቢግ ባንግ የስነ ፍጥረት ፅንሰ ሐሳቦችን በጊዜ ቀመር አስደግፎ ይናገራል፣ ይህንንም የሚሰራው ኤጅ ዴቲንግ(Age Dating) በሚባለው ቴክኒክ ነው፣ ቴክኒኩም የተለያዩ የምርመራ ዘዴዎችን የሚጠቀም ሲሆን [9]ታዋቂዎቹ ዩራኒም - ሊድ፣ ዩራኒየም - ቶሪየም፣ ፖታሲየም - አርጎን፣ ሳማሪየም - ኒዮዲየም፣ ሩቡዲየም - ስትሮንቲየም፣ ፖታሲየም - ካልሲየም፣ ራዲዮ ካርበን (C-14 Dating) ሲሆኑ ከነዚህ ውስጥ በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉት ዩራኒም - ሊድ እና ፖታሲየም - አርጎን ቴክኒኮች ሲሆኑ እድሜያቸው በጥቂት ሺዎች ለሚገመቱት አርኃኒክ ማቴሪያሎች ደግሞ [10] C-14 ጥቅም ላይ ይውላል፡፡

የኤጅ ዴቲንግ የአሰራር ቴክኒክ በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ ግልፅና ትክክለኛ አሰራር ቢሆንም ቴክኒኩ ፈተና ውስጥ የሚወድቀው ግን ተፈጥሮ ውስጥ ባለው ነባራዊ እውነታ ነው፣ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡፡

እንደሚታወቀው ሁሉም ነገር የተገነባው በንጥረ ነገሮች(elements) ነው፣ ከርጉዕነት አንፃር ኢለመንቶች ደግሞ በሁለት ይከፈላሉ የረጉ-ኢለመንቶች(stable elements) እና ያልረጉ-ኢለመንቶች(Radio active elements)፤ የረጉ ኢለመንቶች በውስጣቸው ባለው ቻርጅ ባላንስ ምክንያት ባሉበት ሁኔታ ረግተው መቀመጥ የሚችሉ ሲሆኑ ያልረጉ(ራዲኦ

[9] http://en.m.wikipidia.org>wiki>Radiometric Dating

[10] ካርበን በተፈጥሮ በ "C-12" መልክ የሚገኝ ሲሆን "C-14" የሚባለው በጨረር ምክንያት በጥቂት መጠን በአየር ውስጥ የሚፈጠር ርጉ ያልሆነ(Radio active) ኢለመንት ነው፡፡

አክቲቭ ኢለመንቶች) ደግሞ በውስጣቸው ያለው ቻርጅ ባላንስ ባለመሆኑ በጊዜ ሂደት እየተሰባበሩ ራሳቸውን ወደ ረጉ ልጅ ኢለመንቶች ይቀይራሉ፡፡

የኤጅ ዴቲንግ ቴክኒክ የሚጠቀመው ይህን ያልረጉ ኢለመንቶች ወደ ረጉ ኢለመንቶች የመሰባበር ሂደትን ነው፡፡ ለምሳሌ ለአቶሚክ ቦንብ ስራ የሚውለው ዩራኒየም ያልረጋ ኢለመንት በመሆኑ በጊዜ ሂደት ርጉ ወደ ሆኑት ወደ ሊድና ቶሪየም ይሰባበራል፣ በዚህም ዩራኒየሙ ያልረጋ/ወላጅ ኢለመንት(ራዲአ አክቲቭ ኢለመንት) ሲባል ሊድና ቶሪየም ደግሞ የረጋ(ልጅ) ኢለመንት ይባላል፡፡

ወላጅ ኢለመንት ወደ ልጅ ኢለመንቶች የሚሰባበረው በጊዜ ሂደት ነው፣ አንድ በተወሰነ ክምችት የሚገኝ ራዲአ አክቲቭ ኢለመንት ግማሹ የሚሰባበርበት ጊዜ “half life” ይባላል፣ ለኤጅ ዴቲንግ ዋና መሣሪያ የሆነውም ይኸው የራዲአ አክቲቭ ኢለመንቶች “ሃፍ ላየፍ” ነው፣ ለምሳሌ አንድ ቅሪተ አካልን ወስደን፣ ለምሳሌ በዩራኒም ሊድ ዘዴ ብንመረምረው በውስጡ ከፍርሰት የቀረው ዩራኒየምና በዩራኒየም ፍርሰት የተገኘው የሊድ መጠን ይሰላና ከዩራኒየም ሃፍ ላየፍ ጋር ተነፃፅሮ “ዕድሜው ይህን ያህል ነው” ይባላል፡፡

ይህ በቲዎሪ ደረጃ ትክክል ቢሆንም ወደ አተገባበር ስንሄድ ግን ብዙ ችግሮችን ይገጥሙናል፣ ይህም፡-

1. ቴክኒኩ የተመሠረተው የወላጅና የልጅ ኢለመንቶችን ብዛት በማነፃፀር ነው ነገር ግን በቅሪተ አካሉ/ድንጋዩ ውስጥ ከመነሻው በተፈጥሮ የነበረው የልጅ ኢለመንት መጠን አይታወቅም በዚህም ቴክኒኩ “ልጅ ኢለመንትን ዜሮ ነበረ” ብሎ ቅድመ ግምት ይወስዳል፣ ይህ ደግሞ ትልቅ ስህተት ነው፡፡

   ለምሳሌ ከላይ ባየነው ዩራኒየም-ሊድ ቴክኒክ ውስጥ የሊድ ኢለመንት በተፈጥሮ በመጀመሪያ በተወሰነ መጠነ ቁስ በቅሪተ አካሉ/ድንጋዩ ውስጥ ይገኛል ነገር ግን ይህ መጠን ተለይቶ የሚታወቅበት መንገድ ባለመኖሩ ምክንያት በመጀመሪያ የነበረው የሊድ ኢለመንት ብዛት “ዜሮ ነበረ” ብሎ መነሳት ስህተት ነው፡፡

2. ናሙናው “እድሜ ልኩን ከምንም ንክኪ ነፃ ነበረ፣ ምንም ወላጅ ሆነ ልጅ ኢለመንት ከውጪ ወደ ውስጥ አልገባምም ከውስጥ ወደ ውጭ አልወጣም” ማለቱ ስህተት ነው፣ እንደዚህ አይነት ዝግ ስርዓት ላብራቶሪ ውስጥ እንጂ በተፈጥሮ አናገኘውም፣ ምድር በሂደት ውስጥ ናት እሳተ ገሞራ፣ የመሬት የቀለጠው ክፍል መጠጠር በተቃራኒው ጠጣሩ ክፍል መቅለጥ፣ የከርሰ ምድር ውስጥ የውሀ እንቅስቃሴ ... ብዙ ተፈጥሯዊ ሂደቶች ባሉበት ሁኔታ ውስጥ “አልተነካካም” ማለቱ ስህተት ነው፡፡

   ስህተቱ ደግሞ የሚነላው ወደ ፈሳሽነትና ጋዝነት የሚለወጡት ልጅ ኢለመንቶች “ከምንም እንቅስቃሴ ታቅበው ነበሩ” የሚለው ላይ ነው፣ ለምሳሌ ጋዝ የሆነውን አርጎን የሚጠቀመው የፖታሲየም-አርጎን ዘዴን መመልከት ይቻላል፡፡

3. አሁን በጊዜ ሂደት እየተፈጠረ ካለው C-14 በስተቀረ ሁሉም ራዲኦ አክቲቭ ኢለመንቶች የተፈጠሩት በፍጥረት ጊዜ ነው፣ ከፍጥረት ጊዜ በኋላ ራዲዮ አክቲቭ ኢለመንቶች ወደ ርጉ እየተሰባበሩ ነው ያሉት እንጂ አዲስ ራዲዮ አክቲቭ ኢለመንት የሚፈጠርበት ተፈጥሯዊ ሂደት የለም፡፡
   በዚህም ከ C-14 ውጪ ያሉት ቴክኒኮች በሙሉ ማሳየት ያለባቸው የዕድሜ ልኬት ተመሳሳይ ጊዜ መሆን ነበረበት፣ ፍጥረታቱን የፈጠረው ቢግ ባንግም ይሁን ፈጣሪ የኤጅ ዴቲንግ ልኬቱ ማሳየት ያለበት ይህንን ፍጥረታት የተፈጠሩበትን ጊዜ እንጂ የተለያየ ጊዜን መሆን የለበትም፣ በዚህም C-14 ከሚጠቀመው ቴክኒክ ውጪ ያሉት ቴክኒኮች በሙሉ እየሰጡት ያለው የተለያየ የጊዜ ልኬት ስህተት ነው፡፡
   C-14 የሚጠቀመው ቴክኒክም ቢሆን የሚተማመኑበት ቴክኒክ አይደለም፣ ምክንያቱም C-14 የሚፈጠረው በጨረር ኃይል መሆኑና በዘመናት ውስጥ የነበረው የከባቢ አየር የካርበን መጠንና ወደ ምድር ሲወርድ የነበረው የጨረር መጠን በጊዜ ሂደት ውስጥ የማይታወቅ መሆኑ የC-14 ዘዴም አስተማማኝ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡
4. ቴክኒኩ ለጥናቱ የሚፈልጋቸው ቅሪተ አካላት፣ ድንጋይ … የሚያገኘው በብዙ ቁፋሮና ፍለጋ ነው፣ በዚህም ያልተገኘ፣ ያልተደረሰበት፣ ሊደረስበት የማይቻልና የጠፋ በሙሉ እንደሌለ ይታሰባል፣ ይህ ደግሞ ስህተት ነው፡፡
   ለምሳሌ አርዲ ሳትገኝ በፊት “ሉሲ የመጀመሪያዋ የሰው ልጅ” ስትባል ነበረ፣ ሉሲ ስትገኝ አርዲ እንደሌለች ይታሰብ ነበረ፣ አሁንም ቢሆን መቼም አርዲ ደግሞ ብቻዋን ዱብ አላለችም ከስዋ በፊት የነበሩት “ሰዎች” ቅሪተ አፅም ሲገኝ ደግሞ አባባሉ ይቀየራል፡፡

በዚህም የኤጅ ዴቲንግ ቴክኒክ እነዚህን ስህተቶችና በተፈጥሮ ሊሟሉ የማይችሉ ቅድመ ግምቶች ይዞ የሚሰጣቸው ድምዳሜዎች ትክክለኛ እንደማይሆኑ ግልፅ ነው፡፡

የኤጅ ዴቲንግ ቴክኒክ በነዚህ ችግሮቹ ምክንያትም ብዙ ሊታገሱት የማይገባ የውጤት ስህተቶች ሲያመጣ መመልከቱ የተለመደ ነገር ነው፤ አብዛኞቹ ዛሬ ከብዙ ቅንብሮች በኋላ የሚነገሩት ውጤቶች ብዙ የኤዲቲንግ ስራዎች ከተሰሩባቸው በኋላ ነው ነገር ግን ለኤዲቲንግ ያልተመቹትን የዚህን ቴክኒክ ውርደቶች ለምሳሌ ያህል ብንመልከት፡-

- <u>በአንድ ዓለት ውስጥ ያሉ የተለያዩ ማዕድናት የተለያየ ዕድሜ ማሳየታቸው</u>

[11] “በአሜሪካ፣ ሴንት ሄለንስ በሚባል የላቫ ተራራ ላይ የተወሰዱ የተለያዩ ናሙናዎች በፖታሲየም - አርጎን ዘዴ እድሜያቸው ተሰልቶ ነበር፣ በዚህም ዘዴ ከዓለቱ የተወሰደው ናሙና 350,000 አመታት አሳየ፣ አለቱ ውስጥ ካሉ ሆርንብሌንድ ማዕድኖች ላይ የተወሰደው ናሙና 900,000 አመታት አሳየ፣ ከፓይሮክሲን ማዕድኖች የተወሰደው ናሙና

[11] https://creation.com/learning the lessons of mount st. Helens

2,800,000 አመታት አሳየ፣ የሚያሳዝነው ደግሞ አንዳቸውም ትክክለኛ አልነበሩም ምክንያቱም ናሙናሙ የተወሰደበት ላቫ የፈሰሰው በ1980 ሲሆን በወቅቱ ዕድሜው ገና 10 አመታት ብቻ ነበር።"

- <u>አንድን ናሙና በተለያየ የኤጅ ዴቲንግ ዘዴ ሲመረመር የተለያየ ውጤት ማሳየቱ</u>

[12]"በ1954 ዓ.ም ከናጉዋሩ ተራራ ላቫ ፍሰት የቀዘቀዘ ዓለት በRb-Sr isochron ዘዴ ዕድሜው ተሰርቶ 133 ሚሊየን አመታት አሳየ፣ በ Sm-Nd isochron ዘዴ 197 ሚሊየን አመታት አሳየ፣ በPb-Pb ዘዴ 3.908 ቢሊየን አመታት አሳየ፣ በዚህም ለዚህ ላቭ የተለያዩ እድሜዎች ተለካለት፣ የሚያሳዝነው ግን አንዳቸውም ትክክለኛ አልነበሩም ዓለቱ ከፈነዳ ገና 50 ዓመቱ ብቻ ነበረ።"

- <u>በህይወት ያለን ፍጡር ከሺ አመታት በፊት ሞተ ማለቱ</u>

[13]"በህይወት ያለ የቀንድ አውጣ ሼል በ C-14 እድሜው ተለክቶ ውጤቱ ከ27,000 ዓመታት በፊት ይኖር እንደነበረ አሳየ፣ (Science, Vol.224 1984 pg. 58-61)"

በዚህም የስነፍጥረት ፅንሰ ሐሳቦች የጀርባ አጥንት የሆነው ኤጅ ዴቲንግ ምን ያህል በስህተት ተነስቶ፣ በስህተት አስልቶ የስህተት ድምዳሜ እየሰጠ እንዳለና በዚህም የስነፍጥረት ሳይንሱ የሚሊየንና የቢሊየን አመታት የስነ ፍጥረት ትንታኔዎች በሙሉ ስህተት መሆናቸውን እንመለከታለን።

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ ኤቲስቶች ፍጥረታት የተፈጠሩት በተፈጥሮ ሂደት መሆኑን ለማሳየት የሚጠቀሙባቸው የቢግ ባንግ፣ የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳቦችና የኤጅ ዴቲንግ ቴክኒክ የፍጥረትን አጀማመር መግለፅ የማይችሉ መሆናቸውን፣ በዚህም ፍጥረታት የመጡት ኤቲስቶች በሚሉት የተፈጥሮ ሂደት አለመሆኑን እንመለከታለን።

ከላይ የተመለከትናቸው ኤቲዝም የተመሠረተባቸው የቁስአካልነት ፍልስፍና፣ አመክንዮና የስነ ፍጥረት ፅንሰ ሐሳቦች ትልቅ ክፍተት ያለባቸውና የፈጣሪ አምላክን ህለዎት ለመግለፅ አቅም እንደሌላቸው በተመሳሳይ መልኩም ኤቲዝም ፍጥረታት የተፈጠሩበትን መንገድ የሚያስረዳባቸው የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሐሳብና የቢግ ባንግ ጽንሰ ሐሳብ ስነፍጥረትን ለመግለፅ አቅም እንደሌላቸው ስንመለከት የኤቲዝም አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና "ፈጣሪ አምላክ የለም" የሚለው ድምዳሜም የቸኮለ፣ በበቂ መረጃ ላይ ያልተመሠረተ የተሳሳተ ድምዳሜ መሆኑን ነው።

[12] ዘለቀ በኃይሉ (2008)፣ **ሳይንስና ኢቮሉሽን**፣ ክፍል አንድ፣ ገፅ 154
[13] ibid ገፅ 206

1.4. ከኤቲስቶችና ከአማኞች በተለየ መንገድ የፈጣሪ ህለዎት ምርመራ

ከላይ እንደቀረበው የስነፍጥረት ሳይንሱ "ፈጣሪ የለም" ያለበት መንገድ ስህተት መሆኑን ተመልክተናል ይሁን እንጂ ይህ የስነ ፍጥረት ሳይንሱ የጥናት መንገድ ስህተት በመሆኑ ብቻ "ፈጣሪ አለ" ወደሚለው ድምዳሜ በጭፍን መዝለልም አመክንዮአዊ አይሆንም፣ በዚህም ፈጣሪ አለ? ወይስ የለም? ከሚለው ከሁለቱ ቡድኖች ክርክር ወጣ ብሎ ነገሮችን ገለልተኛ በሆነ መንገድ መመልከቱ አስፈላጊ ነው።

ይህንንም ምልከታ ለማድረግ እንደ ማንኛውም ተመራማሪ በቅድሚያ መመለስ የሚገባንን "Research question" በቅድሚያ እናዘጋጅ፣

1. የፍጡራን ስነ ስርዓት ኤቲስቶች እንደሚሉት በዘፈቀደ የተፈጥሮ ሂደት የመጣ ነገር ነው? ወይስ አማኞች የሚሉትን የፈጣሪ አምላክ እጅ ያሳያል?
2. አማኞች "የፈጣሪ መንገድ ነው" የሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ኤቲስቶች እንደሚሉት የሰዎች የፈጠራ ስራ ነው? ወይስ የፈጣሪ አምላክ እጅ ይታይበታል?
3. ቅዱሳን መጽሐፍቱ "እስራኤል ከሌላው ዓለም ትለያለች" ማለታቸው ልቦለድ ነው? ወይስ በተግባር የሚታይ እውነታ ነው?
4. በቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ የተገለፀት ታሪኮች በዘመናዊው የታሪክና የአርኪዎሎጂ ጥናቶች ማረጋገጥ ይቻላል? ወይስ ልቦለዶች ናቸው?

የሚሉትን "Research questions" በመፈተሽ፣ የፈጣሪን መኖርና አለመኖር በገለልተኛ መንገድ እስኪ እንፈትሽ።

1.4.1. የፍጡራን ስነ ስርዓት ኤቲስቶች እንደሚሉት በዘፈቀደ በተፈጥሮ ሂደት የመጣ ነገር ነው? ወይስ አማኞች የሚሉትን የፈጣሪ አምላክ እጅ ያሳያል?

የፍጡራንን ስነ ስርዓት በመመልከት የፈጣሪ መኖርና አለመኖር ጥያቄን ለመመለስ ለምሳሌ ያህል የሚልክዌይ ጋላክሲ፣ የሶላር ሲስተም፣ የመሬት፣ የህይወትንና የውሀ ስርዓትን እንመልከት፣

1. ሚልክ ዌይ ጋላክሲ

[14]"በዩኒቨርስ(ፅንፈ ዓለም) ውስጥ ብዙ ጋላክሲዎች (የከዋክብት ስብስቦች) ይገኛሉ፣ ከነዚህ ስብስቦች ውስጥ እኛ የምንገኘው "ሚልክ ዌይ" ተብሎ በሚጠራው የወተት መልክ ባለው ጋላክሲ ውስጥ ነው፣ ይህ ጋላክሲ ፀሐይንና ምድርን ጨምሮ እስከ 400 ቢሊየን የሚደርሱ የኮከቦች ስብስብን ይዞ በአማካይ በ2.3×10^{41} ኪሎግራም ክብደት በ600 km/sec ይሽከረከራል።"

[14] http://en.m.wikipidia.org>wiki>milkway galaxy

ይህ ከአዕምሮ በላይ የሆነ ክብደትና እንቅስቃሴ ለዘመናት ሳይዛነፍ እየተከወነ ይገኛል፣ ይህ ቋሚ ሂደትም በ "በዘፈቀደ የቢግ ባንግ የፍንዳታ ሂደት" የመጣ አይመስልም::

2. <u>ሶላር ሲስተም</u>

ሶላር ሲስተም ማለት በሚልክ ዌይ ጋላክሲ ውስጥ ፀሐይን ማዕከል አድርገው የሚገኙ አካላት ስብስብ ነው፣ [15] "ሶላር ሲስተማችንም አንድ ፀሐይ፣ ስምንት ዋና ፕላኔቶች፣ አምስት ድንክዬ ፕላኔቶች፣ ብዙ ጨረቃዎችና ብዙ አነስተኛ የሶላር ሲስተም አካላትን ይዞ በ2.0028×10^{30} ኪሎግራም ክብደት፣ በ220 km/sec ፍጥነት በሚልክዌይ ጋላክሲ ውስጥ ይሽከረከራል::"

ተመልሶ ደግሞ እያንዳንዱን የሶላር ሲስተሙ አካላት(ፕላኔቶች፣ ጨረቃ...) በሙሉ በተሳፈሩት ሶላር ሲስተም እንቅስቃሴ ውስጥ ሆነው በየግላቸው በራሳቸው አቅጣጫ፣ ፍጥነትና ኃይል በሌላ የእንቅስቃሴ ስርዓት ውስጥ ይንቀሳቀሳሉ፣ በቀላል ምሳሌ የጨረቃን እንቅስቃሴ ብንመለከት፣ [16] "ጨረቃ በአንድ ጊዜ በርካታ ውስብስብ እንቅስቃሴዎችን ታደርጋለች፣ ይህም፣

(1) በራስዋ ዛቢያ ላይ ትሽከረከራለች
(2) በምድር ዙሪያ ትዞራለች
(3) ከመሬት ጋር አብራ በፀሐይ ዙሪያ ትዞራለች
(4) ከፀሐይ ጋር የጋላክሲያችንን ሚልክዌይ ማዕከላዊ ስፍራ ትዞራለች
(5) ከጋላክሲያች ጋር ዩኒቨርስ ውስጥ ትዞራለች"

ሌሎቹ የሶላር ሲስተም አካላትም በተመሳሳይ ውስብስብ እንቅስቃሴ ውስጥ ይገኛሉ፣ እነዚህ አካላትም በነዚህን ስርዓቶች ለዘመናት ራሳቸውን ችለው፣ አንዴ በተሰጣቸው ቀመር(Program) ሳይዛነፉ ይንቀሳቀሳሉ::

እነዚህ ሰማያዊ አካላት በዚህ ክብደት፣ ፍጥነትና ውስብስብ እንቅስቃሴ ሳይዛነፉና ሳይንገጫገጩ ስርዓት ይዘው ለዘመናት እየተጓዙበት ያለው ምስጢር ከዘፈቀደ የፍንዳታ ሂደት ይልቅ የመጽሐፍ ቅዱሱ፣

> መዝ.19፡1-3 "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፣ የሰማይም ጠፈር የእጁን ስራ ያወራል ... <u>ነገር የለም መናገርም የለም፣ ድምፃቸው አይሰማም</u> ..."

የሚለው ቃል የበለጠ አሳማኝ ሆኖ ነው የምንመለከተው::

[15] https://en.wikipidia.org>wiki>solar System
[16] ዘለቀ በኃይሉ(2008)፣ **ሳይንስና ኢቮሉሽን**፣ ክፍል አንድ፣ ገፅ 33-34

3. ምድር(Earth)

[17] "ምድር 5.9×10^{24} ኪሎግራም ክብደት፣ በ1,670 ኪሎሜትር በሰዓት(0.46km/sec) የሮቴሽን ፍጥነትና በ107,000 ኪሎሜትር በሰዓት(30km/sec) ሪቮሉሽን ፍጥነት ትሽከረከራለች፣ በዚህ ላይ ደግሞ ከሶላር ሲስተሙ ጋር በ220 km/sec ፍጥነት በሚልክዌይ ጋላክሲ ውስጥ ትሽከረከራለች፣ ከሚልክዌይ ጋላክሲም ጋር በ600 km/sec በዩኒቨርስ ውስጥ ትሽከረከራለች"፡፡

ምድር ይህን ያህል ክብደት ይዛ በነዚህ አራት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ሳትዛነፍ፣ ሳትንገጫገጭ፣ ሳትዘገይና ሳትፈጥን ስርዓት ይዛ በላይዋ ላይ ያለ ፍጥረት እንኳን እንቅስቃሴዋ ሳይሰማው መጓዝዋ ለአዕምሮ የሚከብድ አሰራር ነው፡፡

እነዚህ ውስብስብ እንቅስቃሴዎች በሙሉ ደግሞ ለዘመናት ሳይዛነፉ በተቀመጠው ቀመር መጓዛቸው የሚያሳየው ፕሮግራም ያደረጋቸው አካል መኖሩን እንጂ በቢግ ባንግ "በዘፈቀደ" ነው ብሎ ማሰብ አይቻልም፡፡

4. <u>ለህይወት መኖር ሲባል ከሌሎች ፕላኔቶች ተለይቶ ለምድር የተቸረው ጸጋና የተደረገው ጥበቃ</u>

ህይወታዊው ፍጥረት ራሱን ችሎ ስለማይቆም የግድ የተፈጥሮ ጸጋና ጥበቃ ያስፈልጉታል፣ ህይወታዊን ሐብት ደግፋ እንድትይዝ የተደረገችው ደግሞ ምድር በመሆኗም ምድር በግልፅ ከሌሎቹ ፕላኔቶች ተለይታ ለህይወት መኖር አስፈላጊ የሆኑ ጸጋዎችና ጥበቃዎች በጥንቃቄ ተሟልተውላታል፡-

- <u>ለምድር የተቸረው ጸጋ</u>

  ምድር ህይወታዊ ፍጥረታቱን ማኖር ስላለባት ከሁሉም ፕላኔቶች በተለየ፣ ከዘፈቀደነት ይልቅ በበላይ አካል በተቀመረ ቀመር፣ ፍፁም፣ ሙሉና ውብ ተደርጋለች፣ በርግጥ እነዚህ ጸጋዎች እጅግ ብዙ በመሆናቸውም ያለውን እውነታ በአንድ ርዕስ ወይ በአንድ ምዕራፍ ወይ በአንድ መጽሐፍ ማስቀመጥ አይቻልም፣ ሳይንሱም እያንዳንዳቸውን በተናጠል ዲፓርትመንትና ፋካልቲ እድሜ ልኩን እያጠናቸው ይገኛል፡፡

  በአጭሩ ስንመለከትም ምድር ከሌሎች ፕላኔቶች በተለየ በተመጣጠነ የአየር ይዘት፣ በተመጣጠነ የብርሃን ጨረር፣ በተመጣጠነ የሙቀትና የቅዝቃዜ መጠን፣ በተመጣጠነ የቀንና የሌሊት ርዝማኔ፣ በተመጣጠነ የወቅቶች ፈረቃ፣ በተመጣጠነ የመሬት ስበት፣ በለም መሬት፣ የህይወት ዋና ግብአት የሆነው ውሀ በኡደቱ (Water Cycle) ለህይወታዊ ፍጥረታቱ እየዞረ በሚያጠጣበትና በመሳሰሉ ተዘርዝረው በማያልቁ፣ ለሌሎች ፕላኔቶች እንግዳ በሆኑ ጸጋዎች ተደግፋለች፡፡

[17] https://en.wikipidia.org>wiki>earth

➢ **<u>ለምድር የተደረገው ጥበቃ</u>**

የሰው ልጅ የስነ ፍጥረት ጥናት ከዩኒቨርሱ ጋር ሲተያይ ኢምንት በመሆኑ ምድር ከምን አይነት አደጋዎች እንደተጠበቀች ሁሉንም ነገር ማወቅ ባይቻልም ባለችው ጥቂቷ ጥናትም ቢሆን ምድር ህይወታዊ ፍጥረታትን ስለያዘች ከሌሎች ፕላኔቶች ተለይታ የተደረገላትን ጥበቃ መመልከት ይቻላል፡፡

ምድር በሌሎች ፕላኔቶች ላይ የምንመለከታቸውን እጅግ ተለዋዋጭ ከፍተኛ ሙቀትና ቅዝቃዜ፣ ያልተመጣጠነ የቀንና የለሊት እርዝማኔ፣ ከፍተኛ የፀሐይ ጨረር፣ “Solar wind” የሚባለው የፀሐይ ተፅዕኖ፣ ከተለያዩ የብርሃን አካላት የሚለቀቁ አደገኛ ጨረሮች፣ የሜትርዮራይት(ተወርዋሪ ኮከብ) ድብደባ፣ ከፍተኛ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ፣ መርዛማ ከባቢ አየር፣ ከብናኝ የማይጠራ አየር፣ የአሲድ ዝናብ … ተጠብቃለች፡፡

ምድር የተቀመጠችው በሚልከዌይ ጋላክሲ ውስጥ በተረጋጋ ሰፈር በመሆኑ ለከፍተኛ የስበትና የጨረራ ኃይል እንዳትጋለጥ አድርጓታል፤ በሶላር ሲስተሙ ውስጥም የያዘችው የሦስተኛነት ስፍራም የተመጣጠነ የሙቀትና ቅዝቃዜ፣ የተመጣጠነ የፀሐይ ኃይል እንዲሁም የተመጣጠነ የቀንና የለሊት ርዝማኔ እንዲኖራት አድርጓታል፤ ከባቢ አየርዋም በኦዞን ንጣፍ በመሸፈኑ ከፀሐይና ከሌሎች የብርሃን ምንጮች የሚመጡ አደገኛ ጨረሮች ፍጥረታቱን እንዳይጎዱ አድርጓል፤ ምድር በማግኔቲክ ፊልድ በመሸፈኗ ምክንያት ከፀሐይ የሚለቀቀው “Solar wind” እንዳያገኛት አድርጓል፤ ምድር በሁለቱ ግዙፍ የስበት ኃይል ባላቸው በፀሐይና በጁፒተር መካከል የምትገኝ በመሆኗም ከአብዛኛው የሜቲዎራይት(ተወርዋሪ ኮከቦች) ግጭት እንድትጠበቅ አድርጓታል፣ በነዚህ ሁለቱ ግዙፍ አካላት ሳይሳብ አልፎ የሚመጣው ተወርዋሪ ኮከብም በምድር ከባቢ አየር ውፍረት ምክንያት በሚፈጠርበት ሰበቃና በምድር አየር ውስጥ በብዛት በሚገኘው አክሲጅን ምክንያት መሬት ሳይደርስ በከባቢ አየር ውስጥ ተቃጥሎ ያልቃል፡፡

ምድር ህይወታዊውን ሐብት ደግፋ እንድትሸከም ሲባል ከሌሎች ፕላኔቶች ተለይቶ የተቸራትን ጸጋና ጥበቃ ስንመለከት ከስነፍጥረት ጀርባ የፈጣሪን እጅ እንድናስተውል ያደርገናል፣ ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ከነዚህ ህልቆ መሳፍርት ጸጋዎችና ጥበቃዎች ውስጥ አንዱ ብቻውን ቢጎድል የሌሎቹ ጸጋዎችና ጥበቃዎች መኖር ብቻው ህይወትን አያቆይም፣ ለምሳሌ ሁሉም ጸጋዎችና ጥበቃዎች ባሉበት ሁኔታ ፀሐይ ብቻ ብትጠፋ ህይወት በሙሉ አብሮ ይጠፋል፣ ይህም የሚያሳየው ፈጣሪ የሰራው የመፍጠር ስራ ብቻ ሳይሆን ይህንን በቀጭን ክር ላይ እየሄደ ያለውን ህይወታዊ ዓለም እንዳይወድም የሚጠብቅ መሆኑን ነው፡፡

5. <u>የህይወታዊ ፍጥረት የሰውነት ስርአትና እርስ በርስ ትስስር</u>

ህይወታዊው ፍጥረት የተገነባው እጅግ ውስብስብ በሆኑ ህልቆ መሳፍርት የሰውነት ስርአቶች ነው፣ የምግብ ስርአት፣ የደም ዝውውር ስርአት፣ የስነተዋልዶ ስርአት፣ የነርቭ ስርአት፣ የስሜት ህዋሳት(የዓይን፣ አፍንጫ፣ ምላስ ...) አሰራር ስርአት፣ የበሽታ መከላከል ስርአት፣ የሆርሞን ስርአት ... መመልከት ይቻላል፣ የሚገርው ደግሞ እያንዳንዱ ስርአት ተመልሶ እጅግ በሚያስደንቁ ውስብስብ ህልቆ መሳፍርት ስርአቶች የተሰራ ነው::

ከሰውነት ስርአቶች ውስጥ አንዷን ስርአት ወስደን ብንመለከት በውስጧ ያለው ቅንብር ዘፈቀደ ይቅርና አዕምሮና ቴክኖሎጂውን የያዘው የሰው ልጅ በሙሉ ተረባርቦ፣ ኮፒ አድርጎ እንኳን ሊፈጥረው የማይችለው ጥበብ ነው::

ህይወታዊ ፍጥረታቱ መካከል የተቀመጠው ትስስርም እጅግ የሚያስደንቅ ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- ዕፅዋቱ ያለ ፓምፕ(ወይንም ልብ)፣ ከግራቪቲ ኃይል በተቃራኒ፣ ከሀያና ሠላሳ ሜትር ጥልቀት ውሀ ስበው እስከ ሀያና ሠላሳ ሜትር የሚደርስ ቁመታቸው አድርሰው ምግባቸውን በፀሐይ አማካኝነት እንዴት እንደሚያዘጋጁ፣ እንስሳቱም እነዚህን እፅዋት በመመገብ ሰውነታቸው እንዴት ምግቡን ሰባብሮ ኃይል ከውስጡ አውጥቶ እንደሚጠቀም፣ ሌሎች እንስሳት ደግሞ እነዚህን ቅጠል ተመጋቢ እንስሳት አድነው የሚመገቡበትና አጠቃላይ በህይወታዊው ስነ ፍጥረት መካከል የተቀመጠው የምግብ ሰንሰለት ስርዓት(food chain)፤
- እንስሳቱ ዕፅዋቱን እየተመገቡ ሳያውቁ የእፅዋቱን የመራቢያ (Pollination) እና የመባዣ ስርአት የሚያግዙበት ስነስርዓት (Seed Dispersal)፣
- በእንስሳትና እፅዋት መካከል ያለው የካርበን ዳይኦክሳይድና ኦክስጂን ተመጋጋቢ በሆነ መልኩ የሚያደርጉት የማጣራት ስነስርዓት(Gas Exchange)፣
- እንስሳቱ ለሰው ልጆች ለማጓጓዣ፣ ለእርሻ፣ ለመብል፣ ለጥበቃ ... በተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ ተለይተው የተፈጠሩበት፤ ዕፅዋቱም ለመድኃኒት፣ ለማገዶ፣ ለግንባታ ... አገልግሎቶች ተለይተው የተፈጠሩበት፣

... ብዙ መሰል በህይወታዊ ፍጥረታቱ መካከል ያለውን፣ አንዱ ያለ ሌላው መኖር እስከማይችልበት ድረስ የተቀመጠውን አስገራሚ የትስስር ስርአት ስንመለከትና ይህ ስርአት ደግሞ ለዘመናት <u>ሳይቋረጥ</u> እየተከወነ ያለበትን ሁኔታ ስንመለከት ስርአቱ ከዘፈቀደ የተፈጥሮ ሂደትነት ይልቅ የበላይ አካል <u>ጥበቃ</u> እንዳለበት ያሳያል::

6. <u>ውሀ</u>

የውሀን ምንነትና ጥቅም ዘርዝሮ መግለፅ አይቻልም በደፈናው እንደ ኬሚስተሪው "Universal solvent" ወይ እንደ ውሀ ልማት "ውሀ ህይወት ነው" ብሎ ከማለፍ በስተቀረ፣ ውሀ ከዚህ ፍፁማዊ ባህሪው በተቃራኒው ሌሎቹ ፕላኔቶች ጠብታውን ሳያገኙ

ህይወታዊውን ፍጥረት የምትሸከመው ምድር ከሁሉም ፕላኔቶች ተለይታ 71% አካሏ በውሀ ተሸፍኗል፣ የሚገርመው ደግሞ የስነ ተፈጥሮ ሳይንሱ "በሜትዮራይት ግጭት ከመሬት ተቆርጣ ተወረወረች" የሚላት ጨረቃ ላይ እንኳን ጠብታ ውሀ አልተገኘም፣ ከውሀ በስተቀረ ደግሞ በአንድ ፕላኔት ላይ ብቻ የተገደበ ንጥረ ነገር የለም፣ እንደ ስነ ፍጥረት ሳይንሱ ቢሆን ኖሮ ውሀ ምድርን በ71% ሲሸፍን ሌሎቹ ጎረቤት ፕላኔቶች ላይ ደግሞ ከዚህ አነስ ወይንም በዛ ባለ መልኩ መገኘት ነበረበት ነገር ግን ይህ አልሆነም።።

ህይወታዊ ፍጥረታቱ በሙሉ የተደገፉት በውሀ ላይ በመሆኑ በጥቅም ላይ የዋለው ውሀ በየጊዜው ሊታደስና ዞሮ ለፍጥረታቱ ሊቀርብ ስለሚገባ ውሀ ሁል ጊዜ "የውሀ ዑደት" ሂደት ውስጥ ይኖራል፣ በዚህ ሂደትም የቆሸሸው ውሀ በተፈጥሯዊ ሂደት በትነት መልክ ይነፃል፣ የተነነው ደግሞ ተመልሶ ይዘንባል ...

እነዚህ የውሀ ባህሪያት፣ ይህም ፍፁማዊ ባህሪው፣ በመሬት ላይ ብቻ የተወሰነበት፣ በዑደት እየተመላለሰ የሚነፃበትና በዝናብ መልክ ተመልሶ በየጥጋጥጉ ለሚገኝ ህይወታዊ ፍጥረት የሚታደልበት አሰራር የመጣው "በዘፈቀደው የቢግ ባንግ የፍንዳታ ሂደት ነው" ከማለት ይልቅ አስቦበት እንደዚህ ያደረገ አካል መኖሩን ያሳያል።።

ሌሎች ተዘርዝረው የማያልቁትን በቀመር የሚሰሩትን ስርአቶች፣ ለምሳሌ አተም ውስጥ ያለው የኤሌክትሮን፣ ፕሮቶንና ኒውትሮን ስርአት፣ በአተሞች መካከል የሚደረገው የኬሚካል ስርአት፣ የኤሌክትሪክ ስርአት፣ የማግኔት ስርአት፣ የመሬት ስበት ስርአት የመሳሰሉትን ህልቆ መሳፍርት፣ በጥንቃቄ ተቀምረው ምንም ሳይዛነፉ እየሰሩ ያሉትን ስርአቶችን አስተውለን ስንመለከት ፍጥረታት የተፈጠሩት በዘፈቀደ ከመሆን ይልቅ ቀምሮ በሰራ አካል መሆኑን እንመለከታለን።።

የቪዲዮ ካሜራን ሰው ዲዛይን አድርጎ እንደሰራው እየታወቀ ተመሳሳይ ይባሱኑም የተራቀቀ ስራን የምትሰራዋ ትንሽየዋ ዓይን በዝግመተ ለውጥ ሂደት እንደመጣች መፈላሰፉ፣ የኩላሊትን ስራ የሚሰራው ግዙፉን የዲያልሲስ ማሽንን ሰው ዲዛይን አድርጎ እንደሰራው እየታወቀ የባቄላ ፍሬ የምታክለዋና ተመሳሳይ ይባሱኑም የተሳለጠ ስራን የምትሰራዋ ኩላሊት በዝግመተ ለውጥ እንደመጣች መፈላሰፉ ... አማኞች እንደሚሉት ከፍልስፍናው ጀርባ የተቃራኒ መንፈሳዊ ኃይል ሜራ እንዳለ ያሳያል።።

ማንኛውም ነገር የሚመራው በ"cause and effect" በምክንያትና ውጤት ነው፣ ስዕል ዝም ብሎ አይገኝም ሰዓሊ አለው፤ ቅርፃ ቅርፅ፣ ቤት፣ ሀውልት ... ያለ ሰሪ ዝም ብሎ አይገኝም፤ ይህንን የሚያክል እጅግ የገዘፈና የተወሳሰበ በስርዓት የሚመራ ዩኒቨርስ፣ ሚልክ ዌይ፣ ሶላር ሲስተም፣ ምድር፣ ከህይወታዊ ፍጥረታቱ አንስቶ እስከ አተምና ፎቶንስ ድረስ ያለው ስነ ስርዓት ዝም ብሎ አልመጣም፣ አንድ ስርዓት አስይዞ የፈጠራቸው፣ አንዳንድ ሳይንቲስቶች "Inteligent Designer" የሚሉትን የፈጣሪ አምላክን አሻራ የሚያሳዩ ህያው ምስክሮች ናቸው።።

1.4.2. <u>አማኞች “የፈጣሪ መንገድ ነው” የሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ ኤቲስቶች እንደሚሉት የሰዎች የፈጠራ ስራ ነው? ወይስ የፈጣሪ አምላክ እጅ ይታይበታል?</u>

አማኞች “የፈጣሪ ቃል ነው” የሚሉት መጽሐፍ ቅዱስ የፈጣሪ ቃል ለመሆን “ልዕለ ስብዕናነት” ሊታይበት ይገባል፣ በዚህም፡-

- መጽሐፍ ቅዱሱ ከሰውኛ መጽሐፍት የሚለይ መሆን አለመሆኑ፣
- መጽሐፍ ቅዱሱ ዛሬ “አዳዲስ ናቸው” የምንላቸውን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶችን ቀድሞ የሚያውቃቸው መሆን አለመሆኑ፣
- የትንቢቶቹ ተጨባጭነት በባለፈው፣ በአሁኑና በሚመጣው ዘመን መረጋገጥ አለመረጋገጡን፣

በመመልከት መጽሐፍ ቅዱሱ የሰዎች ድረሰት ነው? ወይስ የፈጣሪ እጅ አለበት? የሚለውን እንፈትሻለን፡፡

1.4.2.1. <u>መጽሐፍ ቅዱሱ ከሰውኛ መጽሐፍት የሚለይ መሆን አለመሆኑ፣</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ ከፈጣሪ ዘንድ የወረደ ከሆነ ከሌሎች መጽሐፍት የሚለይባቸው ባህሪያት ሊኖሩት ይገባል፣ በዚህ አንፃር መጽሐፍ ቅዱሱን ስንመለከት መጽሐፉ ከሌሎች ሰውኛ መፅፍት በብዙ መንገድ ይለያል፣ ይህም፣

- በ1,500 ዓመታት ውስጥ፣ ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎች፣ በአንድ ሐሳብ የተፃፈ ወጥ መጽሐፍ መሆኑ፣
- በ1,900 ዕድሜው አለማርጀቱና ከየትኛውም መጽሐፍ በተለየ “ተራማጅ” መጽሐፍ መሆኑ፣
- እንዲጠፋ እየተሰራበት በተቃራኒው እየተስፋፋ መገኘቱ፣
- ለማንም አለማዳላቱ፣

መጽሐፉ ሰውኛ ድርሰት አለመሆኑን ያሳያል፣ ቀጥሎ በስፋት ቀርቧል፣

1. <u>በ1,500 አመታት ውስጥ፣ ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎች፣ በአንድ ሐሳብ የተፃፈ ወጥ መጽሐፍ መሆኑ፣</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈው በአንድ ሰው አይደለም፣ መጽሐፉ የተፃፈው በ1,500 አመታት እርዝማኔ ውስጥ፣ በተለያየ ሀገር፣ ባህል፣ ንቃተ ህሊና፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ ማኅበራዊ ሁኔታ ... ውስጥ ይኖሩ በነበሩ፣ ከ40 በላይ በሆኑ ሰዎች፣ ፍፁም በሆነ ተግባቦት፣ አንድ ሰው የፃፈው በሚመስል መልኩ ነው የተዘጋጀው፡፡ ይህም እውነታ የሚያሳየው መጽሐፉ ከየትኛው ዓለማዊም ሆነ መንፈሳዊ መጽሐፍ የተለየ መጽሐፍ መሆኑንና መጽሐፉን በበላይነት ያስፃፈውም በ1,500 አመታት ውስጥ የማይሞት ልዕለ ስብዕናነት ያለው አካል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ በ1,500 አመታት እርዝማኔ ውስጥ ሲፃፍ ፀሀፊዎቹ ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ ከመለያየቱ በላይ ደግሞ ሰዎቹም በግል ያላቸው ችሎታና ሙያ እንኳን የተለያየ ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

ተቁ	የመጽሐፉ ስም	ፀሃፊው	ሙያው
1	አሪት ዘፍጥረት፣ ዘጸአት ...	ሙሴ	እረኛ(ዘጸ.3፡1)
2	መጽሐፈ ዕዝራ	ዕዝራ	የስነፅሁፍ ሰው(ዕዝ.7፡6)
3	መጽሐፈ ነህምያ	ነህምያ	ጠጅ አሳላፊ (ነህ.1፡11)
4	መዝሙረ ዳዊት	ዳዊት	እረኛ (1ዜና. 29፡26)
5	መጽሐፈ መክብብ	ሰሎሞን	ንጉሥ(1ዜና 29፡28)
6	ትንቢተ ኤርምያስ	ኤርምያስ	ካህን(ኤር.1፡1)
7	ትንቢተ አሞፅ	አሞፅ	ገበሬ(አሞ.7፡14)
8	የማቴዎስ ወንጌል	ማቴዎስ	ቀራጭ (ማቴ.9፡9)
9	የሉቃስ ወንጌል	ሉቃስ	ሀኪም(ቆላ.4፡14)
10	የጳውሎስ መልእክቶች (ወደ ሮሜ፣ ቆሮንቶስ ...)	ጳውሎስ	የሕግ ባለሙያ(ሐዋ.22፡3)
11	የጴጥሮስ መልእክቶች	ጴጥሮስ	አሳ አጥማጅ(ማቴ.4፡18-22

እነዚህ እርስ በርስ የማይተዋወቁት ፀሀፊዎች የየራሳቸውን ጥቅልል መጽሐፍ ያዘጋጁ እንጂ እነዚህ ጥቅልል መጽሐፍት በመጽሐፍ ቴክኖሎጂው በቅደም ተከተላቸው፣ በአንድ ላይ ተጠርዘው፣ በአንድ መጽሐፍ ሲታተሙ መጽሐፉቱ ፍፁም የሆነ ውስጣዊ አንድነትና ከሮኖሎጂ(የታሪክ ፍሰት) ይዘው ነው የተገኙት፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- ሙሴ ከቁሳዊው ስነፍጥረት አጀማመር በመነሳት "በመጀመርያ" ብሎ የጀመረው መጽሐፍ ከ1,500 አመታት በኋላ የመጣው ዮሐንስ የቁሳዊው ስነፍጥረትን መጨረሻ ምን እንደሚሆን በማሳየት "በዚህ መጽሐፍ ላይ ማንም እንዳይጨምር" ብሎ መጽሐፉን ዘጋው፡፡ በሙሴና በዮሐንስ መጽሐፍት መካከል ያሉት መጽሐፍትም ትክክለኛ የታሪክ ፍሰትና ቅብብሎሽ ይዘው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

  ይህንን በሙሴ ተጀምሮ በዮሐንስ የተዘጋውን መጽሐፍ አጠር አድርገን ስንመለከተው ደግሞ ከገነት ታሪክ ተነስቶ ዞሮ በገነት ታሪክ ላይ የሚዘጋ ሙሉ ክበብ የሚሄድ ታሪክ ነው፣ "አዳም ገነት ውስጥ ተፈጠረ፣ ከዚያም በሰራው ኃጢያት ምክንያት ከገነት

ተባረረ፣ ኋለኛው አዳም የተባለው ኢየሱስ የሰዎችን ኃጢያት ዋጋ በመክፈል የተዘጋውን የገነት መንገድ ከፈተ፡፡"

ይህ ሙሉ ክበብ የሄደ የታሪክ መዋቅርም የመጽሐፍ ቅዱሱን ሙሉዕነት ያሳያል፡፡

- ኢየሱስና ሐዋርያቱ በአስተምህሮዎቻቸው ውስጥ የቀደሙትን መጽሐፍት እያጣቀሱ በማስተማር ተለያይው በጥቅልል የተቀመጡት መጽሐፍት የአንድ መጽሐፍ አካል መሆናቸውን አሳይተዋል(ሉቃ.4፡16-21, ሐስ.8፡30-35 ...)፣
- አንዱ መጽሐፍ "ለወደፊት ይሆናል" ብሎ የተነበየውን ትንቢት ሌላው መጽሐፍ ላይ ደግሞ ፍፃሜውን ማሳየቱ የመጽሐፉን ውስጣዊ አንድነት ያሳያል፣ ይህ አሰራር ደግሞ አጠቃላይ የመጽሐፉ መርህም እንደሆነ ተነግሯል፣

  አሞ.3፡7 "በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነብያት <u>ካልነገረ</u> በቀር <u>ምንም አያደርግም</u>፡፡

ይህንን በምሳሌ ብንመለከትም ከብሉይ ኪዳን አሰራር ወደ አዲስ ኪዳን አሰራር ሲገባ ዝም ተብሎ አልተገባም በቀደምት ነብያቱ በኩል ተደጋጋሚ ትንቢቶች ከተነገሩ በኋላ ነው፡፡ ስለ ዋናው ነቢይ፣ ስለ ኢየሱስ፣ አብዛኞቹ የነብያት መጽሐፍት "ኢየሱስ" የሚለውን ቃል ካለመጠቀም ውጪ ኢየሱስ ስለሚባለው ሰው ሙሉ ስዕል ሲሰጡ ነበረ፡፡ መጽሐፉ ዛሬ ላይ ሆኖ እንኳን ስለሚመጣው ነገር ይናገራል፣ ከዚህ ቁሳዊ ዓለም ፍፃሜ በኋላ ምን እንደሚከሰት እንኳን ይናገራል፡፡

- ከብሉይ ኪዳን ነብያት የብዙ ዘመናትን ርቀት እንደውም እስከ አዲስ ኪዳኑ የመጨረሻው ዘመን ድረስ መጥቶ ትንቢት በተናገረው በነብዩ ዳንኤል የተፃፈው "የዳንኤል መጽሐፍ" የአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱሱ ማስተሳሰርያ መጽሐፍ ሆኖ እንመለከተዋለን፡፡

  ከዳንኤል ትንቢት መጽሐፍ ከስድስት መቶ አመታት በኋላ የመጣው ኢየሱስ ከዳንኤል መጽሐፍ ጠቅሶ ሲያስተምር ነበረ(ማቴ.24፡15, ማር.13፡14 ...)፣ በምሳሌዎች በመነገሩ ምክንያት ለመረዳት የሚከብደው የመጽሐፍ ቅዱሱ የመጨረሻ ምዕራፍ "የዮሐንስ ራዕይ" እንኳን መረዳት የሚቻለው ከዳንኤል መጽሐፍ ጋር አጣምሮ ማንበብ ሲቻል ነው፣ በዚህም የዳንኤል መጽሐፍ የመጽሐፍቱ እርስ በርስ ማሰርያ ገመድ ሆኖ ተቀምጧል፣
- "ብሉይ ኪዳን" የሚባሉት መጽሐፍት እንደ ዛሬ በአንድ መጽሐፍ ተሰብስበው ሳይታተሙ በፊት ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍትን ዛሬ በሚከፈሉበት መንገድ "የሕግ፣ የነብያትና የመዝሙራት መጽሐፍት" ብሎ መጥራቱ(ሉቃ.24፡44) የመጽሐፉን ውስጣዊ አንድነት ያሳያል፣

- አራቱም የወንጌል መጽሐፍት የተፃፉት ክስተቱን በተመለከቱ አራት የተለያዩ ሰዎች ቢሆንም አራቱም ሰዎች ባዘጋጇቸው አራቱ መጽሐፍት መካከል የሚታየው ልዩነት ግን ከሰውኛ የታሪክ የአተራረክ ዘዴ ልዩነት በስተቀረ ሁሉም የተመለከቱትን ድርጊት በተመሳሳይ መንገድ መግለፃቸው የድርጊቱን ተአማኒነት ብሎም የመጽሐፍቱን አንድነት ያሳያል፡፡

  ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ኃኪሙ ሉቃስ የፃፈው "የሉቃስ ወንጌል" የተዘጋጀው ለአማኙ አይደለም፣ ሉቃስ ፅሁፉን ያዘጋጀው ቴዎፍሎስ ለሚባለው ወዳጁ ነው፣ ፅሁፉንም ሲጀምር "በኛ ዘንድ ስለተፈፀመው ነገር … ከመጀመርያው ተከትዬ በየተራው ልፅፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ፡፡" በማለት ነው ኢየሱስ ስለተባለው ሰውና ድርጊቶቹ በመገረም ለወዳጁ ቴዎፍሎስ የፃፈው፣ ይሁን እንጂ ይህ የወዳጆች ግለሰባዊ ደብዳቤ ይዘት ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ካዘጋጁዋቸው ወንጌላት ጋር አንድ ሆኖ ነው የምንመለከተው፣ ይህም እውነታ የወንጌላቱን ውስጣዊ አንድነት ብሎም የክስተቱን እውነታ ያረጋግጥልናል፡፡

ይህ በመጽሐፍቱ ጥቅልሎች መካከል የተመለከተው አንድነት በ1,500 አመታት ውስጥ በተለያየ ሙያ፣ ስፍራ፣ ባህል፣ ንቃተ ህሊና፣ የፖለቲካ ሁኔታ፣ ማኅበራዊ ሁኔታ … ወዘተ በኖሩ ሰዎች የተፃፈ መሆኑ፣ ምንም እንኳን መጽሐፉ የተፃፈው በሰው እጅ ቢሆንም በበላይነት ሲያፅፍ የነበረው በ1,500 አመታት ውስጥ የማይሞት ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መሆኑን ያሳያል፡፡

2. <u>በ1,900 ዕድሜው አለማርጀቱና ከየትኛውም መጽሐፍ በተለየ "ተራማጅ" መጽሐፍ መሆኑ</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ከ1,400 ዓ.ዓ እስከ 100 ዓ.ም ለ1,500 አመታት የተፃፈ መጽሐፍ ሲሆን የመጨረሻው የመጽሐፍ ቅዱሱ ክፍል "የዮሐንስ ራዕይ" ከ1,900 አመታት በፊት ተፃፈ፡፡ በዚህም፣ በሰውኛ ዕይታ፣ ፀሀፊዎቹ በጋርዮሽ እውቀት የፃፉት መጽሐፍ በመሆኑ ለዚህ ዘመን ትውልድ ያረጀና የማያስፈልግ መጽሐፍ መሆን ነበረበት፣ ይሁን እንጂ መጽሐፉ ግን እንደ እኩዮቹ አርጅቶ ወድቆ አልቀረም፣ ዛሬ ከሁለት ቢሊየን በላይ ወዳጆች አሉት፣ ከ2,000 በላይ በሆኑ ቋንቋዎች ተተርጉሟል፣ በአሁኑ ጊዜም በዓለም ላይ ከየትኛውም መጽሐፍ በላይ በሚሊየን ኮፒዎች የሚታተም መጽሐፍ ሆኗል፡፡

በዓለማችን ላይ ታላላቅ ፈላስፎች፣ ደራሲዎች፣ ባለቅኔዎች … በየትውልዱ ተነስተ ለየትውልዱ እጅግ ድንቅ የተባሉ ፅሁፎችን ሲያቀርቡ ቆይተዋል ነገር ግን የስራዎቻቸው ተወዳጅነት ከሁለትና ከሦስት ትውልድ በላይ ሲዘልቅ አልነበረም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ በተቃራኒ ከትውልድ ወደ ትውልድ ተስፋፊነቱ አየጨመረ ይገኛል፡፡

ይህ የሆነውም መጽሐፍ ቅዱስ ምንም እንኳን በጋርዮሽ ዘመን በነበሩ ሰዎች እጅ ቢፃፍም በውስጡ የያዘው እውነታ የአንድ ትውልድ እውነታ ብቻ ሳይሆን የሁሉም ትውልድ እውነታ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ መጽሐፉ ከሌሎች ኃይማኖቶች መጽሐፍት በተለየ በውስጡ የያዘው ታሪክ የአንድ ሰው የህይወት ዘመን ታሪክ ሳይሆን ከ1,500 አመታት <u>የሰው ልጆች ታሪክ ጋር የተሰናሰለ መጽሐፍ በመሆኑ</u>፣ በ1.4.4 ክፍል እንደተመለከተውም መጽሐፉ ቅዱሳኑን ከዘር ሐረጋቸው ጋር እየዘረዘረ መናገሩና ታሪኮቹንም ዛሬ ላይ ሆኖ በቁጥር ማስላት በሚያስችል መንገድ ከክስተቶች ጋር እያሰናሰለ ማቅረቡ መጽሐፍ ቅዱሱ የልቦለድ ስራ እንዳልሆነ ያረጋግጣል፡፡

ብዙ ኃይማኖቶችን መጽሐፍት ስንመለከት ምንም እንኳን መጽሐፍቱ በይዘታቸው ገዘፍ ቢሉም በውስጣቸው የያዟቸው ታሪኮች ግን የአንዱን የኃይማኖት መሪ ዘመን የነበሩ ታሪኮችን ብቻ ነው፣ ይህም ደግሞ የመጽሐፍቱን ልቦለድ የመሆን ዕድል ከፍ እንዲልና ተአማኒነታቸውም የወረደ እንዲሆን ያደርጋል፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ግን ከዚህ ችግር ነፃ ነው፡፡

ከሁሉ በላይ ደግሞ በ1.4.2.3 ክፍል በስፋት እንደምንመለከተው መጽሐፉ ለየትውልዱ ሲናገር የመጣ ከመሆን አልፎ ዛሬም በትንቢቶቹ እየተናገረ ያለና ለወደፊቱም የሚመጣውን ነገር ተጨባጭ በሆነ መንገድ እያሳየ መሆኑ፣ መጽሐፉ ከየትውልዱ ጋር እየተራመደ ለሁሉም ትውልድ የሚናገር ከየትኛውም መጽሐፍ የተለየ ተራማጅ መጽሐፍ መሆኑን ያሳያል፡፡

እነዚህን እውነታዎችንም በአንድ ላይ ስንመለከት ምንም እንኳን መጽሐፉ በጋርዮሽ ዘመን በሰው እጅ ቢፃፍም መጽሐፉን ያፃፈው ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መሆኑን ያሳያል፡፡

3. <u>እንዲጠፋ እየተሰራበት በተቃራኒው እየተስፋፋ መገኘቱ</u>

ከመጽሐፍት ሁሉ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጠላቶች የበዙበት መጽሐፍ የለም፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ከዓለም ላይ እንዲጠፋ ብዙ ሤራዎች ሲሰሩበትና እየተሰሩበት ይገኛሉ፣ ይህ ደግሞ የአንድ ዘመን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የዕድሜ ልክ ታሪኩ ነው፣ አንዳንዶቹ ከሤራቸው ከባድነት የተነሳ “አሁንስ አለቀለት” ሲሉ እንኳን ነበረ፡፡

እነዚህም ጥቃቶች መጽሐፍ ቅዱሱ እንዳይታተም ከመከልከል አንስቶ በሰው እጅ ያሉትን ሰብስቦ ማቃጠልና ለወደፊትም እንዳይታተም “አስተምህሮው ስህተት ነው” የሚል ተቃራኒ አስተምህሮዎች እስከ ማስፋፋት የሚደርሱ ሤራዎችን ያጠቃልላል፡፡

እነዚህም ሙከራዎች ሲደረጉ የነበሩት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱ በአንድ መጽሐፍ ተጠቃሎ ሳይታተም መጽሐፍቱ በጥቅልል ለየብቻ ከነበሩበት ጊዜ አንስቶ ነው፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፡-

- የይሁዳ ንጉሥ ኢዮአቄም፣ እግዚአብሔር ኤርምያስን ያፃፈውን በወቅቱ ብቸኛ የነበረውን የትንቢት ጥቅልል መጽሐፍ በካራ በመቆራረጥ በእሳት አቃጠለው(ኤር.36፡1-23)፣
- አንትዮከስ ኤፒፋንስ የተባለው ንጉሥ(175-164 ዓ.ም) ኢየሩሳሌምን ድል አድርጎ ሲይዝ መጽሐፍ ቅዱስ በእጁ የተገኘ ሰው በሞት እንዲቀጣ በማወጅ "መጽሐፍ ቅዱሱን ሙሉ በሙሉ አጥፍቻለሁ" እስኪል ደርሶ ነበረ፡፡
- ኔሮ(37-68 ዓ.ም) የተባለው የሮማ ቄሳር መጠነ ሰፊ የመጽሐፍ ቅዱስና ክርስቲያኖችን የማጥፋት ስራዎች ሲሰራ ነበረ፡፡
- ዲዮቅልጥያኖስ/Diocletian(284-316 ዓ.ም) የሚባለው የሮማ ቄሳር ሰፊ መጽሐፍ ቅዱስን የማጥፋት ስራዎች በመስራት "ፈፅሜ አጥፍቸዋለሁ" እስከማለት ደርሶ ነበረ፡፡
- ቮልቴር(1,700 ዓ.ም) የተባለው ፈረንሳያዊ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን ለማፋለስ ማተሚያ ቤት አቁሞ "መጽሐፍ ቅዱስን የማራከስ" ስራ ሲሰራ ነበረ "በመቶ አመታት ውስጥም መጽሐፍ ቅዱስ ከዓለም ላይ ይጠፋል" ብሎ ቢተነብይም ከመቶ አመታት በኋላ ግን መጽሐፍ ቅዱስ እሱ ባቋቋመው ማተሚያ ውስጥ ሲታተም ነበረ፡፡
- የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን "መጽሐፍ ቅዱስ ከቤተክርስቲያን ውጪ በግለሰቦች እጅ መግባት የለበትም" በማለት በተለያየ ጊዜ የተባዙ ኮፒዎችን ሰብስባ በማቃጠል ፀሀፊዎቹ ላይ ግድያ ፈፅማለች፣ ጀሮም(405 ዓ.ም)፣ ጆን ዋይክሊፍ(1320 ዓ.ም) እና ዊሊያም ትያንዳል(1500 ዓ.ም) የሚባሉ በወቅቱ ታዋቂ የነበሩ ሰዎች የተገደሉት በዚህ ምክንያት ነበረ፡፡
- [18]በሀገራችንም አፄ ዮሐንስ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ተሰብስቦ እንዲቃጠል አዋጅ አውጥተው ነበረ፣ አባ ገመቺስ ያሳተሙት የኦሮምኛ ቅጂ መጽሐፍ ቅዱስም እንዳይሰራጭ እገዳ ተደርጎበት ነበረ፣ በደርግ ዘመን አብዮት ጠባቂዎች መጽሐፍ ቅዱስን ሰብስቦ ማቃጠልን እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጥሩ ነበረ፡፡
- በአሁኑ ጊዜም ማርክሲዝም/ኮምኒዝም፣ ኤቲዝም፣ ሂውማኒዝም፣ የስነፍጥረት ሳይንስ ... የመጽሐፍ ቅዱሱን አስተምህሮ ተረት ተረት ለማድረግ ከመሞከር አንስቶ አሰባስቦ እስከማቃጠል የሚደርሱ ዘመቻዎችን ከፍተውበታል፡፡

ለወደፊቱም በቴክኖሎጂ እገዛ ተመሳሳይ ጥቃቶች እንደታሰበ ይነገራል፣ ይህም መጽሐፍ ቅዱሱን እጅግ አመቺ በሆኑ ሶፍት ኮፒዎች በመልቀቅና ከሶፍት ኮፒው አመቺነት የተነሳ ሰዎች ከሃርድ ኮፒ ወደ ሶፍት ኮፒው እንዲያዘነብሉ በማድረግ፣ ሃርድ ኮፒውን በተለያየ መንገድ በመሰብሰብ በሰዎች እጅ የሚቀረውን ሶፍት ኮፒ ደግሞ በቫይረስ፣

[18] ጸጋአብ በቀለ(2009)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ**፣ ቅፅ 2፣ ገፅ 225

ሶፍትዌር አፕዴት ... በተለያዩ ሰበቦች ሙሉ በሙሉ በማጥፋት፣ መጽሐፍ ቅዱሱን ሙሉ በሙሉ የማጥፋት ሜራዎች እንዳሉ ይነገራል።

መጽሐፍ ቅዱሱ በታሪኩ ውስጥ እነዚህንና የመሳሰሉት የማጥፋት ሙከራዎች ቢደረጉበትም በተአምራዊ መንገድ ተነስቶ ሲያንሰራራና ተመልሶ እንደ ሰደድ እሳት ዓለምን ሲያጥለቀልቅ ይታያል ይባሱኑ ደግሞ መጽሐፉ በብዛት እንዲጠፋ በተሰራበት መጠን ከዚህ ሜራ በተቃራኒ በማቴ.24፡14 ላይ እንደተነገረለት ትንቢት በስፋት እየተስፋፋ ይገኛል።

ይህ እውነታም አንድ መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ የተዘገበን ክስተት ያስታውሰናል፣ ክስተቱን እስቲ "እንደወረደ" እንመልከተው፣

> ሐስ.25፡34-39 "ነገር ግን በህዝብ ሁሉ ዘንድ የከበረ የሕግ መምህር ገማልያል የሚሉት አንድ ፈሪሳዊ በሸንጎ ተነስቶ ... እንዲህም አላቸው፣ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፣ ስለ እነዚህ ሰዎች ምን እንደምታደርጉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ "እኔ ታላቅ ነኝ" ብሎ ተነስቶ ነበረና፣ አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ። ከዚህ በኋላ ሰዎች በተፃፉበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሳ ብዙ ሰዎችም አሸፍቶ አስከተለ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ። አሁንም እላችኋለሁ፣ ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዉአቸውም፤ <u>ይህ ሐሳብ ወይም ስራ ከሰው እንደሆነ ይጠፋልና፤ ከእግዚአብሔር እንደሆነ ግን ታጠፏቸው ዘንድ አይቻላችሁም፣ ምናልባት ከእግዚአብሔር ጋር ስትጣሉ እንዳትገኙ።"</u>

ይህ ገማልያል የተባለው የሕግ መምህር የነጴጥሮስ የክርስትና እምነት ተከታይ ባይሆንም አንድ እውነታ ገበቶታል "ኃይማኖቱ የሰው ፈጠራ ከሆነ ጊዜያዊ መሆኑንና ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን የማይጠፋ መሆኑን"።

ዛሬ እነዚያ መጽሐፍ ቅዱሱን ለማጥፋት ሲሰሩ የነበሩቱ ነገሥታት ሞተው አስከሬናቸው በየሙዚየሙ እየተነበኘ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ግን ሙዚየም ከመግባት ይልቅ ዛሬ ከሚታተሙት አዳዲስ መጽሐፍቶች በበለጠ በብዙ ሚሊዮኖች ኮፒ ያውም በተለያዩ ቋንቋዎች እየተተረጎመና እየታተመ ይገኛል።

ይህ መጽሐፍ ቅዱሱ በየዘመናቱ በተዘጋጁለት የጥፋት ሜራዎች ሳይከለከል በብዛት እየታተመ ለዓለም እየተዳረሰ ያለበት እውነታም መጽሐፉ በልዕለ ሰብአዊ አካል ጥበቃ እየተደረገለት እንደሚገኝ ያሳያል።

4. ለማንም አለማዳላቱ

መጽሐፍ ቅዱሱ የተፃፈው ለማንም አድልዎ ሳያደርግ አካፋን “አካፋ” እያለ ቅዱሱን ደግሞ “ቅዱስ” እያለ ሚዛናዊና ገለልተኛ ሆኖ ነው።።

አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች የእስራኤላውያን ታሪኮች ቢሆኑም፣ መጽሐፉ ለእስራኤልም መልካም ነገሮችን እንደፃፈው ሁሉ መጥፎ ጎናቸውንም ሳይሳሳላቸው ፅፏል፣ የእስራኤል ህዝብ አልታዘዝ ባለበት ወቅት በፈጣሪ በወረዱበት ቅጣቶች የደረሰበትን ከብረነክ ታሪካቸውን እንኳን ሳይደብቅላቸው ዘግቧል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- እስራኤላውያኑ በደረሰባቸው ቅጣት ከረሀብ የተነሳ የአህያ ስጋ፣ የሰውን ስጋ እና የእርግብ ኩስ መብላታቸውን(2ነገ6፡25-30)፣
- እስራኤላውያን ያለመረዳት(ማቴ.11፡21) እና ያለማመን(ማር.9፡19) ችግር እንዳለባቸው፣
- አጭበርባሪ (ዘፍ.27፡19)፣ አስቸጋሪ (ዘኁ.14፡11) እና ጨካኝ ህዝብ መሆናቸውን(መዝ.137፡9)፣ እግዚአብሔርም የዚህን ህዝብን አስቸጋሪነት ተመልከቶ ይህን ህዝብ ከምድረ ገፅ ለመጥፋት የወሰነበት ጊዜ ሁላ እንደነበረ(ዘኁ.14፡11-20) ነገር ግን በነሙሴ(ሙሳ) ልመና ይህንን ከማድረግ እንደተመለሰ መጽሐፉ ላይ እንመለከታለን።።
- የእስራኤላውያኑን የጥጋብ፣ የጭካኔ፣ የበቀል፣ የእልቂትና የፀፀት ታሪክ፣

  መጽሐፍ ቅዱሱ ይህንን ከስተት የዘገበው በመሳፍንት መጽሐፍ ምዕራፍ 19, 20 እና 21 ላይ ነው።። ታሪኩን አጠር አድርገን ብንመለከት፣

  በተራራማው በኤፍሬም ሀገር የሚኖር አንድ ሌዊ ከሁለተኛ ሚስቱ (ቁባቱ) ጋር በመጋጨቱ ሚስቱ ወደ አባቷ ቤት ወደ ቤተልሔም ትኮበልላለች፣ ከዚያ ይህ ሌዊ ወደ ቤተልሔም ሄዶ ከሚስቱ ታርቆ ይዟት ሲመለስ መንገድ ላይ ይመሽበታል፣ ከዚያም ጊብዓ በተባለች የብንያማውያን ከተማ ያድራል፣ በዚህም ጊዜ የጊብዓ ከተማ ዱርዬዎች የዚህን እንግዳ ሰው ሚስት በጉልበት ወስደው በቡድን ደፈሯት፣ በዚህ ድርጊትም ህይወቷ አለፈ፣ ሌዋዊውም በጣም አዝኖ፣ የተከሰተውን ወራዳ ስራ ለእስራኤል ህዝብ ለማሳየት፣ የሞተች ሚስቱን አካል አስራ ሁለት ቦታ በመቁረጥ ለሁሉም ነገድ ይልካል፣ በዚህ ጊዜ የእስራኤል ህዝብ “የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አልተደረገም ...” በማለት በቁጣ የቢኒያም ነገድን ለመበቀል 400,000 ጦር አዘመተ፣ በግጭቱም ከሁለቱም ወገን በአጠቃላይ ከ70,000 በላይ ሰው አልቆ የብንያም ነገድ ተሸፎ ሲሸሽ የእስራኤል ጦር በብንያም ነገድ ሰፈር ያገኘውን በሙሉ አረደ፣ ይሁን እንጅ በእርስ በርስ ጦርነቱ በደረሰው እልቂትና ውድመት በመፀፀትና የብንያም ዘር ሙሉ በሙሉ እንዳይጠፋ በማሰብ የእስራኤል ሰዎች ከሸሹት የብንያም ወንዶች ጋር እርቅ በማውረድ ደናግል

ሴቶችን ከኢያቢስ ገለዓድ እና ከሴሎ በማሰባሰብ የብንያም ነገድ ተመልሶ እንዲራባና ከእስራኤል ውስጥ እንዳይጠፋ አደረጉ፡፡

- እስራኤላውያኑ መጥምቁ ዮሐንስን፣ ኢየሱስን፣ ሐዋርያቱንና ክርስቲያኖችን እንዴት ባለ ሰይጣናዊ መንገድ ሲያሳድዱ፣ ሲያሰቃዩ፣ ሲያርዱ፣ በመጋዝ በመሰንጠቅ፣ በዘይት በመጥበስ፣ በመስቀል ላይ በቁምና በመዘቅዘቅ ሲገድሉ እንደነበረ በአዲሱ ኪዳን ላይ በስፋት ተዘርዝሯል፡፡

እነዚህ ታሪኮች መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተዘገቡ የእስራኤል የውርደት ታሪኮች ናቸው፡፡

መጽሐፉ እጅግ የተከበሩት ፃድቃን እንኳን በተሳሳቱበት ጊዜ ክብራቸውን ሳይጠብቅ የተባሉትን ነገር ቃል በቃል ፅፏል፣ ሐዋርያው ጴጥሮስ “ሂድ አንተ ሰይጣን … እንቅፋት ሆነህብኛል” ተብሎአል(ማቴ.16፡23)፣ ኤፍሬም “እንዳልተገላበጠ ቂጣ ነው … ሽበትም እንደወጣበት እሱም አላወቀም … አዕምሮ እንደሌላት እንደ ሰነፍ እርግብ ነው” ተብሏል(ሆሴ.7፡8-11)፣ እስራኤላውያን በጀግንነቱ የሚኮሩበት ሶምሶን በፍልስጥኤማውያን ተማርኮ አይኑን አጥፍተውት ወፍጮ ሲያስፈጩት እንደነበረ(መሳ.16፡21)፣ ዳዊት በዝሙት መርከሱንና ይህንንም ጥፋቱን ለመደበቅ የንፁህ ሰው ህይወት እንዲጠፋ ማድረጉን፣ የብሉይ ኪዳን ዋና መሪዎቹ ሙሴና አሮን በሰሩት ኃጢያት ለአርባ አመታት ተስፋ ሲሰጣቸው የነበረውን የከነዓን ምድር እንዳይደርሱ መደረጋቸውን በግልፅ ተዘግቧል፡፡

መጽሐፉ “ጠላት” የሚለውን ሰይጣንን እንኳን ሲገልፀው በተራ የጥላቻ ቃል አይደለም “ሰይጣንን አደገኛ ነው ተጠንቀቁት፣ ሴረኛ ነው ተጠንቀቁት፣ እውቀቱ የመጠቀ ነው፣ ከሰው አዕምሮ በላይ የሆነ ድንቅ የሚያደርግ፣ ሙታንን ማናገር የሚችል፣ ከሰማይ እሳት ማውረድ የሚችል …” በሚል ከሱ ጋር ያለው ነገር በጥንቃቄ እንዲመራ በማሳሰብ እንጂ በተራ ልቦለዳዊ የጠላትነት ስሜት አይደለም፡፡

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ መጽሐፉ “እግዚአብሔር ፍቅር ነው” እንደሚለው ሁሉ እግዚአብሔር በዚህ ፍቅርነቱ ምክንያት የተፈጠሩበትን “ክፍተቶች” እንኳን በግልፅ ተናግሯል፣ እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር “<u>መልካም ነው</u>” ሲል እንዳልነበረው ሁሉ የሰው ልጅ ሲያጠፋ የሰው ልጅን መልሶ ማጥፋት እየቻለ ተመልሶ <u>መፀፀቱንና ማዘኑን</u> ይናገራል(ዘፍ.6፡6)፤ እንደዚሁ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የወደደው በፍፁም ፍቅር በመሆኑ፣ ልክ እጅግ ከሚዋደዱ ሁለት ፍቅረኞች ውስጥ አንዱ በግልሙትና ኃጢያት ሲወድቅ ሁለተኛው እንደሚናደደው ሁሉ እግዚአብሔርም የሰው ልጆች በመንፈሳዊ ግልሙትና(ጣኦት ማምለክ) ኃጢያት ሲወድቁ(ሆሴ.2፡15) የሚቀና መሆኑን በግልፅ ተዘግቧል(ዘፍ.20፡6, ዘዳ.5፡9-10…)፡፡

እነዚህ ለምሳሌ የቀረቡት የመጽሐፍ ቅዱሱ ገለልተኛ አካሄዶች ስንመለከት መጽሐፉን በባለቤትነት ሲያፅፍ የነበረው ገለልተኛ ልዕለ ስብዕና ያለው አካል መሆኑን ያሳየናል፡፡

1.4.2.2. <u>ዛሬ አዳዲስ የሆኑብን የሳይንስና የቴክኖሎጂ ግኝቶችን ቀድሞውኑ የሚያውቃቸው መሆን አለመሆኑ</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ ከ1,400 ዓ.ዓ እስከ 0100 ዓ.ም ድረስ፣ የዛሬ 1,900 አመት ገደማ ተፅፎ ቢያልቅም ዛሬ አዳዲስ የሚመስሉንን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶችን ግን አስቀድሞ ዘግቧቸው ነበረ፣ እነዚህን እውነታዎች መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የምናስተውለው ግን የሚከተሉትን እውነታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡-

- መጽሐፍ ቅዱሱ የሳይንስና የቴክኖሎጂ መማርያ መጽሐፍ ባለመሆኑ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በግልፅ ዘርዝሮ የሚያስተምር አለመሆኑንና የዘመናዊውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ እውቀቶቹን መረዳት የሚቻለው ሳይንሱ የሚጠቀመውን "Connecting the dots" መርህ በመከተል መሆኑን፣
- ቅዱሳኑ በወቅቱ የተገለጠላቸውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ራዕዮች በነበረው የቋንቋ የቃላት ውሱንነት ምክንያት በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ቋንቋ መግለፅ አለመቻላቸውን፣ ለምሳሌ በወቅቱ "አውሮፕላን" የሚባል ሰውኛ ቃል ባለመኖሩ ቅዱሳኑ አውሮፕላንን በራዕይ ሲመለከቱ "አውሮፕላን" የሚባለውን መንኮራኩር በገባቸው መንገድ መግለፃቸውን፣
- በወቅቱ በነበረው ሰውኛ ንቃተ ህሊና ውሱንነት ምክንያት ነገሮችን በደፈናው ተናግሮ የማለፍ ችግር፣ ለምሳሌ በወቅቱ የግራቪቲ እውቀት ባይኖርም ነገር ግን መሬት የታሰረችው በዚህ ኃይል መሆኑን በገባቸው መንገድ መግለፃቸውን፣
- መጽሐፉ የተፃፈበት ቋንቋም ሆነ የተተረጎመበት አማርኛ ለአሁኑ ትውልድ "ያረጀ/Old" የመሆኑ እውነታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው፣

እዚህ ጋር ሁሉንም መጽሐፍ ቅዱሱ ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ጋር አንድ የሚሆንበትን መንገድ መዘርዘር ባይቻልም <u>በዚህ ዘመን አዲስ የሆኑና መጽሐፍ ቅዱሱ በተፃፈበት ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ሊያውቁት የማይችሉትና ልዕለ ስብዕና ያለው አካል ብቻ ሊገለጥላቸው የሚችሉትን</u> ብቻ ወስደን ለምሳሌ ያህል እንመለከታለን፣ በዚህም መጽሐፉ ውስጥ ያሉትን፣

- የቴክኖሎጂ፣
- የተፈጥሮ ሳይንስ፣
- የጤና ሳይንስ፣
- የአካባቢ ጥበቃ ሳይንስ፣
- የዘመናዊው ሕግ መርሆች፣
- የዘመናዊው አመራር ሳይንስ መርሆችን
- የዘመናዊው የስነ ልቦናና የማኅበራዊ ህይወት መርሆች፣

እየቀነጫጨብን እንመለከታለን፡፡

1. ቴክኖሎጂ

ከቴክኖሎጂ ትንቢቶች ውስጥ የአውሮፕላንና የኢ-ኮሜርስ ቴክኖሎጂን መምጣት የሚናገሩትን ትንቢቶችን ብንመልከት፡-

የአውሮፕላን ቴክኖሎጂ

እስራኤሎች ከዓለም ዙሪያ ተሰብስበው ወደ ሀገራቸው የሚመለሱት በአውሮፕላን እንደሆነ ነብዩ ኢሳያስ በራዕይ ተመለከተ ነገር ግን በዘመኑ የአውሮፕላን ቴክኖሎጂ ባለመኖሩ ምክንያት ነብዩ "አውሮፕላን" የሚል ቃል መጠቀም ስለማይችል ራዕዩን በገባው መንገድ በተለያየ አገላለፅ አስረዳ፣ በመጀመርያ ኢሳ.11፡14 "በምዕራብ በኩል በፍልስጤማውያን ጫንቃ ላይ እየበረሩ ይወርዳሉ..." በማለት የሚመጡበትን መንገድ ጠቆም አደረገ፣ በመቀጠል ኢሳ.18፡1 ላይ "ክንፍ ያላቸው መርከቦች" አለ፣ ክንፍ የሚያገለግለው ለመብረር ነው፣ ለመርከብ ክንፍ ብንሰራለት አውሮፕላን ይመስላል፣ ጥሩ አገላለፅ ነው፤ ይኸው ራዕይ ሲደገምበትም ራዕዩን በተሻለ ገላጭ ቃል ኢሳ.60፡8 "ልጆቻሽ ከሩቅ ይመጣሉ ... ርግቦች ወደ ቤታቸው እንደሚበርሩ፣ እነዚህ እንደ ደመና የሚበርሩ..." አለ፡፡

ነብዩ ኢሳያስ "ይህንን ልገልፀው አልችልም፣ ማኅበረሰቡ የማያውቀውን ስፅፍ ይሳቅብኛል ..." ብሎ አልተወውም፣ በወቅቱ የነበረው ማኅበረሰብ ቢገባውም ባይገባውም፣ የተመለከተውን ራዕይ <u>በገባው መንገድ</u> ገልጾታል፣ ዛሬ ግን የአውሮፕላን ቴክኖሎጂን የተመለከተው ይህ ትውልድ መልዕክቱ "እስራኤላውያኑ ወደ ሀገራቸው የሚመለሱት በአውሮፕላን እንደሆነ" መነገሩን በቀላሉ ይረዳል፡፡

የዘመናዊ ግብይት ቴክኖሎጂ

ግብይት ድሮ ዕቃ በመለዋወጥ(Bartering)፣ ከዚያም በኣሞሌ ጨው፣ ከዚያም የገንዘብ ኖቶች የግብይት ስርዓቱን ተቆጣጠሩት፣ አሁን ደግሞ ከገንዘብ ኖት ጎን ለጎን በግብይት ካርድና በሞባይል ባንኪንግ ግብይት እየተፈፀመ ይገኛል፣ ቀጣዩ ግብይት እንዴት እንደሚከናወን መጽሐፍ ቅዱሱ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

በ7.2 በስፋት እንደተመለከተው፣ በቀጣዩ ዘመን ማንኛውም ግብይት የሚከናወነው በቀላል ዘዴ ሰውነት ውስጥ በሚቀበር ረቂቅ የሚሞሪ ሲስተም ነው፣ ይህንንም የብግይት ዘዴ ነቢያቱ በራዕይ ቢመለከቱትም፣ ያዩትን ራዕይ በወቅቱ በነበረው የቋንቋ ውሱንነት ቃል በቃል መግለፅ ባይችሉም በገባቸው መንገድ ፅፈውታል፡-

> ራዕ.13፡16-18 "ታናናሾችና ታላላቆችም ባለጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ... ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይ ሊሸጥ እንዳይችል ..."

ይህ ትንቢት ስለምን እንደሚናገር የሚገባን ዛሬ ቴክኖሎጂውን የተረዳነው ብቻ ነን፣ ቴክኖሎጂውም ዛሬ በሙከራ ላይ የሚገኘውና በረቀቀ መንገድ በቀኝ እጅ ወይንም በግምባር ውስጥ የሚቀበር ቺፕስ(RFID Chips/Bio chips/micro chips) ቴክኖሎጂ ነው፡፡ በቴክኖሎጂውም ሰዎች የገንዘብ ኖት፣ የመገበያያ ካርድና የሞባይል መገበያያ ስርዓትን ሳይጠቀሙ በሰውነታቸው ላይ በሚቀበር ቺፕስና ቺፕሱን በሚያነበው መሣርያ አጋዥነት በቀላሉ ግብይትን ያከናውናሉ፡፡

2. <u>የተፈጥሮ ሳይንስ</u>

መጽሐፍ ቅዱሱን የፃፉት ነብያት፣ መጽሐፉ በሚያዘጋጁበት ወቅት ሰዎች ሊረዱት የማይችሉትን ይባሱኑ በተቃራኒው የሚያስቡትን የዘመናዊ የሳይንስ እውቀቶች ሲገለጥላቸው በገባቸው መንገድ ሲፅፉ ነበረ፣ በዚህም የመሬትን ክብነትና የፅንፈ ዓለም (ዩኒቨርስ) ጠፍጣፋነት፣ መሬት በእስፔስ ውስጥ ያላትን አቀማመጥ፣ የሌሎች ዓለማት(ፕላኔቶች) መኖር፣ የፀሐይ ብርሃን የሚጠፋበት ጊዜ መኖር፣ ቁሳዊው ተፈጥሮ የሚጠፋበት ጊዜ መኖሩን(Big Crunch)፣ ፀሐይን ጠጣር አካል አለመሆኗንና የውሀ ዑደትን ቀጥለን እንመለከታለን፣

<u>የዩኒቨርስ ጠፍጣፋነትና የመሬት ክብነት (Spherical Earth)</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ፣ በድሮ ሰዎች አገላለፅ፣ “ሰማይና ምድር” የሚል ቃል ሲጠቀም እንመለከታለን፣ “ምድር” የሚለው መሬትን ሲሆን “ሰማይ” የሚለው ደግሞ ከመሬት ውጪ ያሉትን የተለያዩ ቀጠናዎችን ነው፣ እነዚህ “ሰማይ” የተባሉት ቀጠናዎችም፣

- ከባቢ አየር (ዘፍ.1፡20, ሐስ.11፡6 …)
- ከዋክብት ያሉበትን ክልል (ኢሳ.13፡10)
- ከቁሳዊው ዓለም ውጪ ያለው የመላዕክት መኖሪያ(1ነገ.8፡30, ማቴ.18፡10…
- ከዚያ ከፍ ብሎ ያለው መንበረ ፀባያት (ማቴ.6፡9, ሮሜ.9፡29 …)

ሳይንሱ ምድር ሉል(Sphere) እንደሆነችና [19] ዩኒቨርስ ደግሞ በአንፃራዊነት ጠፍጣፋ እንደሆነ ይነግረናል፣ እንደዚሁ መጽሐፍ ቅዱሱም የመሬትን ሉልነት “የመሬት ክበብ”(ኢሳ.40፡22, ምሳ.8፡27 …) በማለት ሲገልፅ፣ የሰማይን(ዩኒቨርስን) ጠፍጣፋነት ደግሞ “የተዘረጋች (ኢሳ.40፡22, ምሳ.8፡27…)፣ የምትጠቀለል (ኢሳ.34፡4, ዕብ.1፡10-12)…” በማለት ለያይቶ እንደየተፈጥሯቸው ይገልፃቸዋል፡፡

<u>የ“ጊዜ” እና “ስፍራ” ዕሳቤያችን አጠቃላይ እውነታ አለመሆኑ</u>

ቁሳዊው ዓለም የሚገለፀው በ “Space-Time dimension” ነው ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሱ ይህንን አሁን በቁሳዊው ዓለም የምንጠቀምበት የጊዜ እና የስፍራ ዕሳቤያችን ምድራዊ እንጂ አጠቃላይ እውነታ አለመሆኑን በብዙ መንገድ ይናገራል፡፡ ከጊዜ ዕሳቤያችን

[19] https://en.wikipidia.org>wiki>shape of the universe

ብንነሳ፣ መጽሐፍ ቅዱሱ በመንፈሳዊው ዓለምና በምድራዊው ዓለም መካከል ያለው የጊዜ ቀመር የማይገናኝ መሆኑን ለማመልከት፣

> 2ጴጥ.3፡8 "... በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ አመት፣ ሺህ አመትም እንደ አንድ ቀን እንደሆነ ..."

ይለናል፡፡ አሁን የምንጠቀመው ጊዜና ስፍራ የተፈጠሩት ከቁሳዊው ዓለም ፍጥረት በኋላ ነው፣ የዚህ የጊዜና የስፍራ እሳቤያችንም መሠረታዊ አለመሆኑን አልበርት አንስታየን ሲናገር፣ Albert Einstein noted [20] "Time and space are modes in which we think, not conditions in which we exist" which is a view also expressed in 900 AD by the Arabic physicist Ikhwan al-Sufa, "Space is a form abstracted from matter and exist only in consciousness."

በምድር ላይ የምንጠቀመው የጊዜ ስሌት ከፀሐይና መሬት እንቅስቃሴ አንፃር የተቀመረ አሰራር እንጂ አጠቃላይ እውነታ አይደለም፣ የመሬት እንቅስቃሴ ፍጥነትና አቅጣጫ ቢቀየር የጊዜ ቀመራችን ይፋለሳል፣ ይህንን የምድራችንን የጊዜ ቀመር ሌሎች ፕላኔቶች ጋር ብንወስድም ይፋለሳል፣ ለምሳሌ [21] አንድ አመት ለሜርኩሪ 88 ቀናት ሲሆን፣ ለቬኑስ 225 ቀናት፣ ለመሬት 365 ቀናት፣ ለማርስ 687 ቀናት፣ ለጁፒተር 4,333 ቀናት፣ ለሳተርን 10,759 ቀናት፣ ለዩራነስ 30,687 ቀናት፣ ለኔፕቱን 60,190 ቀናት ነው፣ በዚህም "በአንድ አመት ውስጥ ስንት ቀናት አሉ?" ለሚለው ጥያቄ አንድ አጠቃላይ እውነት የሆነ መልስ ማስቀመጥ አንችልም፡፡

ፀሐይ ላይ ሁል ጊዜ ቀን እንጂ ማታ ስለሌለ፣ ፀሐይ ላይ ያለ አካል ደግሞ ጊዜ የሚባል ዲያሜንሽንን እንኳን መጠቀም አይችልም፣ በመንፈሳዊው ዓለምም እንደ ፀሐይ ብርሃን ተመሳሳይ የብርሃን ምንጭን ነው የምንመለከተው፣

> ራዕ.21፡22-23 "ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደስዋ ናቸውና መቅደስ በእርሷ ዘንድ አላየሁም፡፡ ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራቷም በጉ ስለሆነ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበራላት አያስፈልጓትም ነበረ፡፡"

በዚህም፣ ፀሐይዋ ላይ እንዳለው አካል፣ በመንፈሳዊው ዓለም ያለ አካልም የኛን ጊዜን ዲያሜንሽን መጠቀም አይችልም፡፡

ከስፍራም ጋር በተያያዘ ተመሳሳይ ነገር ነው የምንመለከተው፣ ለምሳሌ መጽሐፉ ፈጣሪ በሁሉም ስፍራ እንደሚገኝ ይናገራል(መዝ.139፡7-12፣ ኢሳ.66፡1...)፣ ይህ በቁሳዊው አዕምሯችን ልንነነዘበው የማንችለው ነገር ቢሆንም እውነታው ግን የ "ስፍራ" ዕሳቤያችን በዚህ ቁሳዊ ዓለም እንጂ አጠቃላይ እውነታ አለመሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡

[20] https://www.quora.com/time-and-space-are-modes-by–which ...
[21] https://spaceplace.nasa.gov/years-on-other-planets/en/

እኛ በቁሳዊው ዓለም የምንኖር ሰዎች የምናስብበት መንገድ ከአጠቃላይ እውነታ ጋር አይገናኝም፣ የ "ስፍራ" ዕሳቤያችን ከምንኖርበት ምድር ወጣ እንዳልን ነው ትርጉም አልባ የሚሆነው፣ በኛ ምልከታ ስፍራ የሚገለፀው በአቅጣጫ (ሰሜን ደቡብ፣ ምስራቅ፣ ምዕራብ)፣ በኮኦርዲኔት(Latitude, Longitude, Altitude)፣ በአንፃራዊነት(እላይ፣ እታች፣ በግራ በቀኝ) ... ነው፣ ነገር ግን እነዚህ አገላለፆች ምድራዊ እንጂ አጠቃላይ እውነታዎች አይደሉም::

ለምሳሌ ከዚህ ምድር ውጪ ሆነን በሁለቱ ፖል ላይ ያሉ ሁለት ሰዎችን ብንመለከት፣ ሁለቱም "ወደ ላይ" ነው የሚሉት አቅጣጫ ፍፁም ተቃራኒ ነው፣ እነዚህ ሰዎች ክብዋ መሬት ይዛቸው ስትገለባበጥ አንዴ ከላይ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከታች ነኝ አይሉም፣ ሁለቱም ሁል ጊዜ ከላይ እንዳሉ ነው የሚያስቡት፣ በተመሳሳይ መልክም "ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ምስራቅ፣ ላቲቲውድ፣ ሎንጊቲውድ፣ ለቲቲውድ ..." የምነለው የአቅጣጫ መጠቆሚያ ከዚህ ምድር ስንወጣ ትርጉም የላቸውም::

በአጠቃላይ ስንመለከትም፣ ሳይንሱ የስፍራና የጊዜ ዕሳቤያችን የተሳሳተ መሆኑን የተመለከተበት እውነታ መጽሐፍ ቅዱሱም አስቀድሞ ያስቀመጠው እውነታ መሆኑን ነው::

<u>ቁሳዊው ፍጥረት ተመልሶ የሚጠፋ መሆኑ (Big Crunch)</u>

ሳይንሱም መጽሐፍ ቅዱሱም ይህ ቁሳዊ ዓለም ተመልሶ የሚጠፋበት ጊዜ እንዳለ እየተነበዩ ነው፣ ሳይንሱ ዓለም በ"ቢግ ባንግ" እንደተፈጠረው ሁሉ ተመልሶ "ቢግ ክረንች" በሚባለው ሂደት እንደሚጠፋ ይናገራል፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ቁሳዊው ዓለም ሙሉ በሙሉ እንደሚጠፋ ይናገራል፣

ማቴ.24፡35 "ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም::"

<u>የሌሎች ፕላኔቶች(ዓለማት) መኖር</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ በተፃፈበት ዘመን ሰዎች በዓይን ከሚታየው ሰማይና ምድር በላይ መናገር በማይችሉበት ጊዜ ቅዱሳን በተገለጠላቸው እውቀት፣ ሌሎች ዓለማት(በአሁኑ አነጋገር ፕላኔቶች) እንደነበሩ በመረዳት በብዙ ቁጥር ሲጠሩ ነበረ፣

- ዕብ.1፡2 "<u>ዓለማትን</u> በፈጠረበት..."
- ዕብ.11፡3 "<u>ዓለሞች</u> በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ ..."

ይህ በወቅቱ የነበሩት ኅብረተሰቦች ሊረዱት የማይችሉት እውቀት ቢሆንም የዛሬው ትውልድ ግን ነብያቱ የተረዱትን እውነታ በደንብ ይረዳል::

<u>መሬት በእስፔስ ውስጥ ያላት አቀማመጥ (Earth in Space)</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ በሚፃፍበት ወቅት የነበረው ማኅበረሰብ "መሬት ጠፍጣፋ ናት እንዳትወድቅም በድጋፍ ተደግፋ ቆማለች" ብሎ በሚያምንበት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱሱ ደግሞ መሬት ያለምንም ድጋፍ በስፔስ ውስጥ እንደ ተንጠለጠለች ሲናገር ነበረ፡-

ኢዮ.26፡7 “... ምድሪቱንም በበታችዋ አንዳች አልባ ያንጠለጥላል፡፡”

መጽሐፉ ምድር ላይ በዓይን የሚታይ ድጋፍና ማንጠልጠያ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ “በበታችዋ አንዳች አልባ” ብሎ ተመልሶ “ያንጠለጠለ” ይላል፣ ይህም የማይታየው ድጋፍና ማንጠልጠያ ፕኔቶች እርስ በርስ የተሳሰሩበት “የመሬት ስበት” መሆኑን የሚረዳው የዛሬው ትውልድ ብቻ ነው፡፡

“ሱፐር ኖቫ”

በመጨረሻው ዘመን የፀሐይ ብርሃን እንደሚጠፋ ሳይንሱም መጽሐፍ ቅዱሱም በአንድ አፍ እየተነበዩ ይገኛሉ፣

ማቴ.24፡29 “... ከነዚያ የመከራ ቀናት በኋላ ፀሐይ ትጨልማለች፣ ጨረቃም ብርሃንዋን ትከለክላለች ...”

በማለት፣ የሚገርመው ደግሞ ይህ ሱፐር ኖቫ ከመከሰቱ በፊት ፀሐይ ከፍተኛ ግለት እንደሚፈጠርባት ሳይንሱ ይናገራል፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ይህንኑ እውነታ ያመለክታል፣

ኢሳ30፡26 “... የፀሐይም ብርሃን እንደ ሰባት ቀን ብርሃን ሰባት እጥፍ ይሆናል፡፡”

ፀሐይ ጠጣር አካል አለመሆንዋን

ጥንታዊው ማኅበረሰብ ፀሐይን ከምድር በሚመለከትበት ምስልና መጠን፣ ጠጣር ሰማይ ላይ የተለጠፈች አነስተኛ አካል አድርጎ በሚመለከትበት ጊዜ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሱ ግን በወቅቱ የነበረው ማኅበረሰብ በተቃራኒ ፀሐይ ከመሬት ሆነን በዓይን በምንመለከተው መጠን አለመሆኗንና ጠጣር አለመሆኗን ስለሌላ ነገር በሚያስተምርበት ክፍሉ ላይ ያመለክተናል፣

ራዕ.19፡17-18 “... አንድም መልአክ በፀሐይ ውስጥ ቆሞ ...”

የውሀ ዑደት

ጥንታዊው ማኅበረሰብ ዝናብ ከሰማይ ውስጥ እንደሚመጣ በሚያስብበት ወቅት መጽሐፍ ቅዱሱ ግን የሚናገረው በሳይንሱ የተማርነውን የውሀ ዑደት ነው፣

- ኢዮ.36፡27 “የውሀውን ነጠብጣብ ወደ ላይ ይስባል፣ ዝናብም ከጉም ይንጠባጠባል፡፡”
- መክ.1፡7 “ፈሳሾች ሁሉ ወደ ባህር ይሄዳሉ፣ ባህሩ ግን አይሞላም፣ ፈሳሾች ወደ ሚሄዱበት ስፍራ እንደገና ወደዚያው ይመለሳሉ፡፡”
- አሞ.5፡8 “... የባህሩንም ውሆች ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈሳቸው”
- አሞ.9፡6 “... የባህርንም ውሀ ጠርቶ በምድር ፊት ላይ የሚያፈስሰው እርሱ ነው፣ ስሙም እግዚአብሔር ነው፡፡”

<u>ውሀና የብስ እንዲለይ የተደረገበት አሰራር</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ፣ በፍጥረት ወቅት በመጀመርያ ውሀ ምድር ላይ ተኝቶ እንደነበና ከዚያም ፈጣሪ ይህንን ውሀ ወደ አንድ ስፍራ እንዲሰባሰብ የብሱ ደግሞ ለብቻ እንዲገለጥ እንዳደረገ ይናገራል፣

> ዘፍ.1፡9-10 “እግዚአብሔርም፣ ከሰማይ በታች ያለው ውሀ በአንድ ስፍራ ይሰብሰብ፣ የብሱም ይገለጥ አለ፤ እንዲህም ሆነ፡፡ እግዚአብሔርም የብሱን ምድር ብሎ ጠራው የውሀ መከማቻውንም ባህር አለው፣ እግዚአብሔርም ያ መልካም እንደሆነ አየ፡፡”

በከርሰ ምድር ጥናት፣ የመሬት የላይኛው ቅርፊት(Crust) በሁለት ይከፈላል፣ “Continental Crust” እና “Oceanic Crust” በሚል፣ Continental Crust የሚባለው የብስ ሲሆን Oceanic Crust የሚባለው ደግሞ ውቅያኖስ የተኛበት መሬት ነው፡፡ እነዚህ ሁለቱ የመሬት ክፍሎች በተለምዶ “Crust” ይባሉ እንጂ አንዱ ወደ ታች ወርዶ የተቀመጠበትና አንዱ ደግሞ ወደ ላይ ከፍ የተደረገበት ሁኔታ ይህንን ፈጣሪ የብሱንና ውሀውን ለመለየት የተጠቀመበትን አሰራር ያሳያል፡፡

ምድር በቢግ ባንግ ሂደት ከቀለጠ ዓለት የተሰራች ቢሆን ኖሮ ከተወሰኑ የእሳተ ገሞራ ተራሮች በስተቀር ምድር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ሜዳ በሆነች፣ ለባህር/ውቅያኖስ ተብሎ የሚዘጋጅ ጥልቅ መሬትና ለየብስ ተብሎ ከፍ የተደረገ መሬት ባልኖረና ውሀ አጠቃላይ ምድር ላይ በተኛ ነበረ፣ ነገር ግን ይህ አልሆነም የምድር ገፅታ ታስቦበት ለውሀ ማቆርያነትና ለየብስነት ተመቻችቶ እንደተቀረፀ በግልፅ መመልከት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ውሀ አጠቃላይ ምድር ላይ ተዘርግቶ እንደነበረና ከምድር ላይ ወደ አንድ ቦታ እንደተሰበሰበ የሚያረጋግጥል የሴዲመንተሪ ዓለት(Sedimentary Rock) በየብስ ላይ የመገኘቱ እውነታ ነው፣ ሴዲሜነተሪ ዓለት የሚፈጠረው በውቅያኖስ ውስጥ ብቻ ነው፣ በዚህም ሴዲሜንተሪ ዓለት በየብስ ላይ የመገኘቱ እውነታ ውሀ በየብስ ላይ ተኝቶ እንደነበረ ያሳያል፣ በከርሰ ምድር ጥናት መሠረት የኢትዮጵያ ምድር በሜሶዞይክ ዘመን በህንድ ውቅያኖስ ስር ነበረ፡፡

<u>የከርሰ ምድር ይዘትና የኮንቬንሽናል ከረንት ሂደት</u>

የመሬት ውስጣዊ ክፍል ብዙ ማዕድናትን የያዘ የቀለጠ ዓለት ነው፣ የሙቀት መጠኑም ወደ ጥልቀት እየጨመረ የሚሄድ በመሆኑ ምክንያት የቀለጠው የመሬት አካል ሁል ጊዜ ተፈጥሯዊ በሆነ የኮንቬንሽና ከረንት(መገለባበጥ) ሂደት ውስጥ ይኖራል፣ ይህንን እውነታ በራዕይ የተመለከቱት ነብያት በገባቸው መንገድ፣ ቢጋርዮሹ ንቃተ ህሊና ገልፀውታል፡-

> ኢዮ.28፡1-5 “በእውነት ብር የሚወጣበት፣ ወርቅም የሚነጠርበት ስፍራ አለ፡፡ ብረት ከመሬት ውስጥ ይወሰዳል፣ መዳብም ከድንጋይ ይቀልጣል… በእሳትም እንደሚሆን <u>ታችኛው ይገለበጣል</u>፡፡ ድንጋይዋ የሰንፔር ስፍራ ነው፣ የወርቅም ድቃቂ አለው፡፡”

ከጂሞሎጂስት በቀር ሌላው ሰው የማይረዳው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል

መጽሐፍ ቅዱሱን ስናጠና ከጂሞሎጂስት(የቅንጦት ማዕድናት ባለሙያ) በስተቀር ሌሎቻችን ስለ ምን እንደተነገረ የማናውቃቸው ክፍሎች አሉ፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- ዘጸ.28፡17-34 "... በፊተኛው ተራ ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮን፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፤ በሁለተኛው ተራ በሉር፣ ሰንፔር፣ አልማዝ፤ በሦስተኛው ተራ ያክንት፣ ኬቄዶን፣ አሜቴስጢኖስ፤ በአራተኛው ተራ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያሰጲድ በወርቅ ፈርጥ ይደረጋሉ ... በፍርዱ በደረት ኪስም ውስጥ ኡሪምንና ቱሪምን ታደርጋለህ ... በታችኛው ዘርፍ ዙሪያ ከሰማያዊ ከሐምራዊ ከቀይም ግምጃ ሮማኖች አድርግ፤ በዚያም መካከል በዙሪያው የወርቅ ሻኩራዎች አድርግ፣ የወርቅ ሻኩራ ሮማንም፣ ሌላም የወርቅ ሻኩራ ሮማንም በቀሚሱ ዘርፍ ዙሪያውን ይሆናሉ።"
- ሕዝ.28፡13 "በእግዚአብሔር ገነት በኤድን ነበርህ፤ የከበረ ዕንቁስ ሁሉ፣ ሰርድዮን፣ ቶጳዝዮን፣ አልማዝ፣ ቢረሌ፣ መረግድ፣ ኢያስጲድ፣ ሰንፔር፣ በሉር፣ የሚያብረቀርቅ ዕንቁ፣ ወርቅ ልብስህ ነበረ ..."
- ራዕ.21፡18-21 "ቅጥርዋም ከኢያሰጲድ የተሰራ ነበረ፣ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች። የከተማይቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጊጦ ነበረ፤ ፊተኛው መሠረት ኢያሰጲድ፣ ሁለተኛው ሰንፔር፣ ሦስተኛው ኬልቄዶን፣ አራተኛው መረግድ፣ አምስተኛው ሰርዶንክስ፣ ስድስተኛው ሰርድዮን፣ ሰባተኛው ክርስቲሎቤ፣ ስምንተኛው ቢረሌ፣ ዘጠነኛው ወራውሬ፣ አሥረኛው ክርስጵራስስ፣ አስራ አንደኛው ያክንት፣ አስራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ። አስራ ሁለቱም ደጆች አስራ ሁለት እነቁዎች ነበሩ፤ እያንዳንዱም ደጅ ከአንድ እንቁ የተሰራ ነበረ ..."

እዚህ ጋር የቀረቡትን ውድ የቅንጦት ማዕድናት ምንነት መረዳት የሚችለው ጂኦሎጂስት ያውም በጂሞሎጂ እስፔሻላይዝ ያደረገ ሰው ብቻ ነው፣ ሌሎቻችን ቃላቱን ከእንግሊዘኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለቅመን ኢንተርኔት ላይ ካልተመለከተ በቀር ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መረዳት አንችልም።

3. የጤና ሳይንስ

እዚህ ጋር የመጽሐፍ ቅዱሱን የጤና ሳይንስ እውቀቶች በሙሉ መመልከት ባይቻልም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱ በወቅቱ ኅብረተሰቡ ከሚያስብበት በተቃራኒ ከዛሬው ሳይንስ በተመሳሳይነት ያስተማራቸውን የጤና መርሆችን ብቻ እንመለከታለን፡-

<u>የሴቶች ግርዛት አለመፍቀዱ</u>

የወንዶችን ግርዛት ዛሬ ዘመናዊው ሳይንሱ እንደሚያዘው መጽሐፍ ቅዱሱም “ወንዶች ይገረዙ” ብሎ ያዛል(ዘፍ.17፡10)፣ እዚህ ጋር መጽሐፍ ቅዱሱ “ሰዎች” ሳይሆን “ወንዶች” ብሎ ነው ለይቶ የሚናገረው፡፡

<u>ዘመናዊ የአመጋገብ ስርዓት ማስተማሩ</u>

በዘመናዊው የስነ ምግብ ሳይንስ ሰዎች ቪጂቴሪያን እንዲሆኑና፣ ለመጠጦችና ለስጋ ምግቦች ያላቸውን ፍቅር እንዲቀንሱና ስብና ደም ደግሞ ፈፅመው እንዳይመገቡ ያስተምራል፣ መጽሐፍ ቅዱሱም እንደዚሁ ያስተምራል፣

- ምሳ.23፡20 “የወይን ጠጅ ከሚጠጡት ጋር አትቀመጥ ለስጋም ከሚሳሱት ጋር፡፡”
- ዘሌ.3፡17 “ስብና ደም እንዳትበሉ …”
- ዘሌ.7፡23 “… የበሬ ወይንም የበግ ወይንም የፍየል ስብ ከቶ እንዳትበሉ፡፡”
- ዘሌ.7፡26-27 “በማደሪያዎቻችሁም ሁሉ የወፍ ወይ የእንስሳ ደም ቢሆን አትብሉ፡፡ ደም የሚበላ ሰው ከህዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ፡፡”

ሌላው የመጽሐፍ ቅዱሱ ዘመናዊ አመጋገብ አስተምህሮን የምንመለከተው ለምግብነት የሚውሉትንና ለምግብነት የማይውሉትን ምግቦች በዘረዘረበት በኦሪት መጽሐፍት ውስጥ ነው፣ ዛሬ የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት የሌላቸው ህዝቦች እነዚህን የመጽሐፉን ትዕዛዛት በመተላለፍ የተለያዩ እንስሳትን በመብላት በተለያዩ ጊዜ በዓለም ላይ ለሚነሱ ወረርሽኞች ምንጭ ሆነው እንመለከታለን፡፡

እነዚህም ህዝቦች መጽሐፉ ለምግብነት እንዳይውሉ የከለከላቸውን እባብ፣ ጦጣ፣ ቺምፓንዚ፣ አሳማ፣ ወፍ፣ የለሊት ወፍ … በመመገብ ከእንስሳት ወደ ሰዎች በሚተላለፉ የኮሮና፣ ኢቦላ፣ ሳርስ፣ በርድ ፈሉ፣ ስዋይን ፍሉ … በሽታዎች ሲሰቃዩና የዓለም ህዝቦችንም አደጋ ውስጥ ሲከቱ እየተመለከትን ነው፡፡

4. <u>የአከባቢ ጥበቃ ሳይንስ</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ፣ እንደ ሳይንሱ፣ ሰዎች ለሚኖሩበትና ለሚጠቀሙበት የተፈጥሮ ሐብት ጥበቃ እንዲያደርጉ ያስተምራል፣ ይህም አስተምህሮ ከፍጥረት ታሪክ የሚነሳና አዳም ሲፈጠር የተሰጠው ዋናው ትዕዛዝ ነበረ፣ “ኤደን ገነትን ይጠብቃትና ያበጃት ዘንድ”(ዘፍ.2፡15)፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ዛሬ በአካባቢ ጥበቃ ሳይንሱ ላይ እንደ አዲስ የምንማረው መሬትን እያሳረፉ የማረስ ስርዓትን(Fallow farming)(ዘሌ.25.3-8) እንደዚሁ በዘመናዊ መንገድ ዕፅዋት የሚራቡበትን የግራፍቲንግ(Grafting) መርህ መጽሐፉ አስቀድሞ ሲያስተምር ነበረ(ሮሜ.11፡17-24)፡፡

የአካባቢ ጥበቃ ጉዳይም ሲሪየስ በመሆኑ ዛሬ ዓለማቀፋዊ ችግር ሆኖ እንመለከተዋለን እንደዚሁ መጽሐፍ ቅዱሱም ጉዳዩን አጠንክሮ ነው የሚመለከተው፣ ይህም ሰው ወደ ምድር ሲመጣ የተሰጠ የመጀመሪያ ትዕዛዝ ከመሆን አልፎ በምድርም ላይ ጉዳት የሚያደርሱ በመጨረሻው ዘመን እንደሚጠፉ እስከ ማስጠንቀቅ ይደርሳል(ራዕ.11፡18)፡፡

5. <u>የዘመናዊው ሕግ መርሆች</u>

መጽሐፍ ቅዱስ፣ እንደ ዘመናዊ ሳይንስ፣ የሕግ የበላይነትን ሲያስተምር የነበረው ከብዙ ሺ ዘመናት በፊት ነበረ፣ በዚህም በመጀመሪያ ዋነኞቹ ህጎች አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ … የሚሉት አስርቱ ትዕዛዛት ሲወርዱ በተከታይነትም ብዙ ህጎች በማውረድ ሰዎችም በሕግ የበላይነት እንዲኖሩ ሲያስተምርና ሕግን የሚተላለፉ እንዲቀጡ ሲያደርግ ነበረ፡፡

ዛሬ ላይ ዘመናዊው ሕግ የሚመራበት መዋቅራዊ አደረጃጀት ከሳሽ፣ ተከሳሽ፣ ጠበቃ እና ዳኛ የተባለው አሰራርም ቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተመለከቱ የፍትህ ስርዓት አደረጃጀቶች ናቸው፡፡

ዘመነኛው ሕግ አንድን ወንጀል “ወንጀል” ለመሆን “ዕቅዱ በመጀመሪያ በአዕምሮ ይሰራል፣ ከዚያ በኋላ ነው ወንጀሉ በድርጊት የሚፈፀመው” በማለት ሰዎች በአመለካከት እንዲለወጡ ያስተምራል፣ መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ መንፈስ ይባሱኑ ከዚህ በተሻለ መንገድ ሰዎች ከህጉ በላይ አዕምሮአቸውን “በፍቅር መርህ” ካነፁ ወንጀል የሚባል ነገር እንደማይኖር ያስተምራል፡፡

- ገላ.5፡14 “ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈፀማልና፣ እርሱም “ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ”
- ማር.12፡31 “… ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ … ከነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትዕዛዝ የለችም፡፡”
- ሮሜ.13፡10 “ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፣ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍፃሜ ነው፡፡”
- ማቴ.7፡12 “እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነብያትም ይህ ነውና፡፡”

በዚህም የመጽሐፍ ቅዱሱ የሕግ ፍልስፍና በጥንታዊያኑ ሰዎች የተፃፈ ቢመስልም፣ በውስጡ ግን ጊዜ የማይሽረው መሠረታዊ የሕግ ፍልስፍና ይዞ እንመለከታለን፡፡

6. <u>የዘመናዊው አመራር ሳይንስ መርሆች</u>

ዘመናዊው የአመራር ሳይንስ በዋናነት የሚያስተምረው መዋቅራዊ አደረጃጀትን፣ ያልተማከለ አስተዳደርንና የመልካም አስተዳደር ዕሴቶችን ነው፣ ይህ ዘመናዊ እውቀት ከ3,500 አመታት በፊት በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ <u>በጥንታዊው ቋንቋ</u> ቀርቧል፣ ይህንም በሙሴና በአማቱ ካህኑ ዮቶር(ዘጸ.18፡1) እንዲሁም በኢየሱስና በደቀ መዛሙርቱ መካከል

በነበረው ንግግር ውስጥ እንመለከታለን፣ ይህ እውነታ መጽሐፉ ላይ ባረጀ ቋንቋና አነጋገር ቢፃፍም ዋና መልክቱን ግን በቀላሉ መረዳት ይቻላል፣

> ዘጸ.18፡14-24 "... የሙሴ አማት ሙሴን ... ህዝቡ ሁሉ ከጠዋት ጀምሮ እስከማታ ድረስ በዙሪያህ ቆመው ሳሉ አንተ ብቻ ስለ ምን ተቀምጠሃል? አለው፣ ሙሴም አማቱን ... በዚህና በዚያ ሰው መካከል እፈርዳለሁ፣ የእግዚአብሔርንም ስርዓትንና ሕግ አስታውቃቸዋለሁ አለው፡፡ የሙሴም አማት አለው፡፡ አንተ የምታደርገው ይህ መልካም ነገር አይደለም ... ከህዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን፣ እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፣ የታመኑ የግፍንም ረብ የሚጠሉትን ሰዎች ምረጥ፤ ከእነርሱም የሺ አለቆችን፣ የመቶ አለቆችን፣ የሀምሳ አለቆችን የአስር አለቆችን ሹምላቸው፡፡ በህዝቡ ላይ ሁል ጊዜ ይፍረዱ፤ አውራውንም ነገር ሁሉ ወዳንተ ያምጡ፣ ታናሹንም ነገር ሁሉ እነሱ ይፍረዱ፣ እነርሱም ከአንተ ጋር ሸክሙን ይሸከማሉ፣ ለአንተም ይቀልልሀል፡፡ ሙሴም ... ያለውን ሁሉ አደረገ፡፡"

እዚህ ጋር ምንም እንኳን አገላለፁ ጥንታዊ ቢሆንም፣ በውስጡ ግን ዋነኛውን የዘመናዊውን የአመራር መርህ እንመለከታለን፣ ይህም የአመራርነት ስራ በአግባቡ የሚሰራው በመጀመሪያ ህዝቡን በተለያየ መዋቅራዊ አደረጃጀት በመከፋፈል፣ ከዚያ በአደረጃጀቶቹ ላይ ብቃት ያላቸውን አለቆችን በመሾም፣ ከዚያ አለቆቹ እስከየት ድረስ ያለውን ውሳኔ መወሰን እንደሚችሉ የስራ ድርሻቸውን ገድቦ በመስጠት፣ የትኞቹን ጉዳዮች ደግሞ ለበላይ አካል እንደሚያቀርቡ በማሳየት ... ነው፣ ይህ በጋርዮሽ ዘመን የተነገረ መርህ በዛሬው የዘመናዊው የሊደርሺፕ ሳይንስ መሠረታዊ አስተምህሮ ነው፡፡

በኢየሱስ ህይወት ውስጥም ሌላ ዘመናዊ የመሪነትን ሳይንስ መሠረታዊ አስተምህሮ እንመለከታለን፣ ይህም፣ መሪ ከንጉሥነት መንፈስ ይልቅ በአገልጋይነት መንፈስ መስራት እንዳለበት፣

> ዮሐ.13፡13-17 "(ኢየሱስም) እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ፡፡ እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ስሆን እግራችሁን ካጠብሁ፣ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል፡፡ እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና ... ይህን ብታውቁ ብታደርጉትም ብፁአን ናችሁ፡፡"

ኢየሱስ መሪ እንደመሆኑ መጠን ለተከታዮቹ ያስተማረው በያዙት ስልጣን ራሳቸውን እንዲኮፍሱ ሳይሆን የሚመሩትን ማጎበረሰብ ወርደው ማገልገል እንዳለባቸው ነው፣ ዛሬ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ እያደገ የመጣው የመሪነት ሳይንስም ይህንን "የደንበኛ ንጉሥ ነው" መርህን አዲስ አድርጎ እያስተማረን ነው፡፡

መጽሐፉ ከነዚህ መሠረታዊ የአመራር መርሆች በተጨማሪም እያንዳንዱ ሠራተኛ ምን አይነት ባህሪዎችን መላበስ እንዳለበት ዘመናዊውን የመልካም አስተዳደር ዕሴቶችንም ያስተምራል፣

<u>የመልካም አስተዳደር ዕሴቶች</u>

ቅንነት(ምሳ.28፡18)፣ ታማኝነት(ቲቶ.2፡9-10)፣ አለማዳላት(ዘዳ.16፡19፣ ዘዳ.24፡17፣ ዘዳ.27፡19 ...)፣ ታታሪነት(ቆላ.3፡23-2) ...

<u>ያለ ስህተት፣ በደልና ሰዓት ባለማርፈድ መስራት</u>

- ዳን.6፡4 "... ነገር ግን (ዳንኤል) የታመነ ነበረና ስህተትና በደል አልተገኘበትም ..."
- ኤር.46፡17 "... ሰአቱን የሚያሳልፍ ጉረኛ ብለው ጠሩት፡፡"

<u>ሠራተኞች "አለቃ አየኝ አላየኝ" ሳይሉ የሚሰሩት ለፈጣሪ እንደሆነ አድርገው መስራት እንዳለባቸው</u>

ቆላ.3፡23-25 "ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፣ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፣ ከጌታ የርስት ብድራትን እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና፤ የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና፡፡ የሚበድልም የበደለውን በብድራት ይቀበላል፣ ለሰው ፊትም አድልዎ የለም፡፡"

<u>ሙስና/ጉቦ መከልከሉ</u>

- ሉቃ.3፡14 "... ደመወዛችሁም ይብቃችሁ ..."
- ኢዮ. 15፡34 "... የጉቦ ተቀባዮችንም ድንኳን እሳት ትበላለች፡፡"
- አሞ.5፡12 "ፃድቁን የምታስጨንቁ፣ ጉቦ የምትቀበሉ ... የችግረኛውን ፍርድ የምታጣምሙ እናንተ ሆይ፣ በደላችሁ እንዴት በዛ ..."
- ዘዳ.16፡19 "ፍርድን አታጣምም፤ ፊት አይተህ አታድላ፤ <u>ጉቦ የጥበበኞችን ዓይን ያሳውራልና</u>፣ የፃድቃንንም ቃል ያጣምማልና ጉቦ አትቀበል፡፡"
- ምሳ.29፡4 "ንጉሥ በፍርድ አገሩን ያፀናል፤ መማለጃ የሚወድ ግን ያፈርሰዋል፡፡"

<u>መንግሥት ቀና ሊሆን እንደሚገባ ማስተማሩ</u>

- ምሳ.16፡12 "ግፍን መስራት በንጉሥ ዘንድ ፀያፍ ነገር ነው፣ ዙፋን በፅድቅ <u>ይፀናልና</u>፡፡"
- ምሳ.14፡28 "የንጉሥ ክብር በህዝብ ብዛት ነው፤ በሰው ጥቂትነት ግን የገዥ ጥፋት አለ፡፡"
- ምሳ.29፡2 "... ኃጥአን በነገሡ ጊዜ ግን ህዝብ ያለቅሳል፡፡"

7. <u>የዘመናዊው የስነ ልቦናና የማኅበራዊ ህይወት መርሆች</u>

የስነ ልቦናና የማኅበራዊ ህይወት ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰዎች እርስ በርስ በመዋደድ፣ በመረዳዳት፣ በይቅርታ መንፈስ፣ ጠንክሮ በመስራት፣ በጎ አመለካከት በማዳበር ... በማንነታቸው ላይ "positive mind/positive energy" እንደሚያዳብሩና ይህም በህይወታቸው ስኬታማ፣ ደስተኛና ውጤታማ እንደሚሆኑ፣ እድሜያቸው እንደሚረዝም፣ ከጭንቀት፣ ዲፕሬሽን፣ ዕንቅልፍ ከማጣት ... ችግሮች ነፃ እንደሚሆኑ፣ ማኅበረሰቡም ሠላማዊ፣ ልማታዊ ... እንደሚሆን ያስተምራሉ፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ ግን ይህንን የስነ ልቦናና የማኅበራዊ ህይወት መርህ ቀድሞ ሲያስተምር ነበረ፣ በአስተምህሮውም ሰዎች "ኣጋፔ" እስከሚባለው የፍቅር ኣይነት ድረስ ይህም፣ የሚወዷቸውን መውደድ ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻቸውን (ማቴ.5፡44-45)፣ በጥላቻ ስሜት የሚመለከቷቸውን (ሉቃ.6፡27)፣ የሚረግሙኣቸውን (ማቴ.5፡44-45)፣ የማያውቋቸውን (ሉቃ.10፡30-35) እንኳን መውደድ እንዳለባቸው ያስተምራል።

ይህንን የመጽሐፍ ቅዱሱን የ"positive mind/ positive energy" አስተምህሮዎችን አጠር አጠር አድርገን ብንመለከት፣

<u>መልካም ባህሪን መላበስ እንደሚገባ</u>

- ሮሜ.12፡21 "ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።"
- ማቴ.5፡5-9 - የዋህነት፣ መሀሪነት፣ ልበ ንፁህነት፣ ማስታረቅ ...
- ገላ.5፡22 - ፍቅር፣ ደስታ፣ ሠላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ ራስን መግዛት ...
- ያዕ.3፡17 - ታራቂ፣ ገር፣ እሺ ባይ፣ በጎ ፍሬ የሞላባት ጥርጥርና ግብዝነት የሌለበት ...
- ቲቶ.1፡7 - የማይኮራ፣ የማይቆጣ፣ የማይሰክር፣ የማይጨቃጨቅ
- ኤር.17፡11, ዕብ.13፡5 - ሰዎች ስግብግብ እንዳይሆኑ
- ማር.10፡24 - ሰዎች በገንዘባቸው መታበይ እንደሌለባቸው

<u>በፍቅር መንፈስ መኖር እንደሚገባ</u>

- ገላ.5፡14 "... ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ ..."
- ሮሜ.13፡10 "ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም ..."
- ፩ቆሮ.10፡24 "እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ ስንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ።"
- ፩ቆሮ.13፡4-6 "ፍቅር ይታገሳል፣ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፣ አይታበይም፤ የማይገባውን አያደርግም፣ የራሱንም አይፈልግም፣ አይበሳጭም፣ በደልን አይቆጥርም፤ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ አመፃ ደስ አይለውም፤
- ማቴ.7፡12 "እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነብያትም ይህ ነውና።"
- ኤፌ.5፡33 "... እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት።"

<u>ግጭትና ጦርነትን አላስፈላጊ እንደሆነ</u>

- ማቴ.26፡52 "... ሰይፍ የሚያነሱ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉ ..."
- ዘፍ.9፡6 "የሰውን ደም የሚያፈስ ሁሉ ደሙ ይፈሰሳል ..."

<u>ይቅር ማለትና ቂም በቀልን ማስወገድ እንደሚገባ</u>

- ማቴ.6፡15 "ለሰዎች ግን ኃጢያታቸውን ይቅር ባትሉ አባታችሁም ኃጢያታችሁን ይቅር አይላችሁም።"

- ሮሜ.12፡17-19 “ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ ... ራሳችሁ አትበቀሉ፣ ለቁጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፣ በቀል የእኔ ነው፣ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ...”
- ፩ተሰ.5፡15 “ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ...”
- ሮሜ.12፡14-20 “... የሚያሳድዷችሁን መርቁ፣ መርቁ እንጂ አትርገሙ... ጠላትህ ቢራብ አብላው፣ ቢጠማ አጠጣው ...”
- ማቴ.5፡40-41 “እጅ ጠባብህንም እንዲወስድ ለሚወድ መጎናፀፊያህን ደግሞ ተውለት፣ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ።”
- ማቴ.6፡12“እኛምደግሞየበደሉንንይቅርእንደምንልበደላችንንይቅር በለን”

<u>የተጎዱትን መደገፍ እንደሚገባ</u>

- ማቴ.25፡35 - የተራቡትን ማብላት፣ የተጠማን ማጠጣት፣ እንግዳን መቀበል፣ የታረዘን ማልበስ፣ የታመመን መጠየቅ፣ የታሰረን መጠየቅ ...
- ያዕ.1፡27 “... ወላጆች የሌላቸውን ልጆች፣ ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ...”
- ምሳ.19፡17 “ለድሀ ቸርነት የሚያደርግ ለእግዚአብሔር ያበድራል።”
- ማቴ.5፡42 “ለሚለምንህ ስጥ፣ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፈቀቅ አትበል።”

<u>የአሸናፊነት ስነልቦና</u>

ኢዮ.3፡10 “... ደካማውም፣ እኔ ብርቱ ነኝ ይበል።

<u>አጥቲሚስት መሆንና ነገሮችን በበጎ መመልከት</u>

ሮሜ.8፡28 “እግዚአብሔርን ለሚወዱት እንደ ሐሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።”

<u>የዓላማ ፅናት</u>

- ኢያ.1፡7 “... ፅና፣ እጅግ በርታ ...”
- ሀጌ.1፡7 “... ልባችሁን <u>በመንገዳችሁ</u> ላይ አድርጉ።”
- 2ጴጥ.3፡17 “... በአመፀኞች ስህተት ተሰባችሁ ከራሳችሁ ፅናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ።”
- ምሳ.26፡4 “አንተ ደግሞ <u>እርሱ እንዳትመስል</u> ለሰነፍ እንደ ስንፍናው አትመልስለት።”

<u>ጠንካራ ሠራተኝነት</u>

- ሮሜ.12፡11 “ለስራ ከመትጋት አትለግሙ ...”
- 2ተሰ.3፡10 “... ሊሰራ የማይወድ አይብላ ...”
- ምሳ.12፡27 “... ለሰው የከበረ ሐብት ትጋት ነው።”
- ምሳ.19፡3 “የሰው ስንፍና መንገዱን ታጣምምበታለች ...”
- ምሳ.20፡4 “ታካች ሰው በብርድ ምክንያት አያርስም፤ ስለዚህ በመከር ይለምናል ...”
- መክ.4፡5 “ሰነፍ እጆቹን ኮርትሞ ይቀመጣል፤ የገዛ ስጋውንም ይበላል”

<u>ሰው ሲያቅድና ለስራ ሲነሳ የእግዚአብሔር አብሮነትም አብሮ እንደሚሆን</u>

- ፊልጵ.2፡13 “ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሰራ እግዚአብሔር ነው፡፡”
- ኢሳ.57፡19 “የከንፈሮችህን ፍሬ እፈጥራለሁ …”
- ነህ.2፡20 “… የሰማይ አምላክ ያከናውልናል፣ እኛም ባርያዎቹ ተነስተን እንሰራለን …”
- ምሳ.16፡9 “የሰው ልብ መንገዱን ያዘጋጃል፤ እግዚአብሔር ግን አካሄዱን ያቀናለታል፡፡”

<u>ጠንክሮ ከመስራትና በዓላማ ከመፅናት ባለፈ መጨነቅና መስገብገብ እንደማያስፈልግ</u>

- ማቴ.6፡27 “ከናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማነው?
- ዘሌ.23፡22 “የምድራችሁን መከር በሰበሰባችሁ ጊዜ የእርሻችሁን ድንበር ፈፅማችሁ አትጨዱ፣ የመከሩንም ቃርሚያ አትልቀሙ፣ ለድሆችና ለእንግዶች ተዉት፤”

<u>ሰው ሐብቱን ቀርቅሮ ከሚያስቀምጥ ለገብያ ማቅረብ እንዳለበት - በዘመናዊው ቋንቋ ኢንቬስት ማድረግ እንዳለበት</u>

ምሳ.11፡26 “እህልን የሚያስቀር ሰው በህዝብ ዘንድ ይረገማል፤ በረከት ግን በሚሸጠው ራስ ላይ ነው፡፡”

በዚህም ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱሱ በጋርዮሽ ዘመን በሰዎች እጅ ቢፃፍም ዛሬ ላይ አዲስ ተደርገው ሰዎችን ሆነ ጎብረተሰቡን በመልካም፣ በአሸናፊነት … ባህሪ እንዲቀረፁ ከሚያስተምሩት ከዘመናዊው የስነ ልቦናና የማኅበራዊ ሳይንሶች እኩል ሲያስተምር እንመለከተዋለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት መጽሐፍ ቅዱሱ ጥንታዊ መጽሐፍ ሆኖ ሳለ ነገር ግን ከዘመናዊው የተፈጥሮ ሳይንስ፣ ከቴክኖሎጂ፣ ከጤና ሳይንስ፣ ከአከባቢ ጥበቃ፣ ከሕግ፣ ከመሪነት፣ ከስነልቦናና ከማኅበራዊው ሳይንስ እኩል መናገሩ ምንም እንኳን መጽሐፉ በጋርዮሽ ዘመን ቢፃፍም ፀሀፊዎቹ ግን መጽሐፉን ያዘጋጁት ልዕለ ስብዕና ባለው አካል መሪነት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

1.4.2.3. <u>የትንቢቱ ተጨባጭነት ባለፈው፣ በአሁኑና በሚመጣው ዘመን መረጋገጥ አለመረጋገጡ</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ከሌሎች መጽሐፍት የሚለየው በተራማጅነቱ ነው፣ መጽሐፉ ከያዘው አጠቃላይ እውነታ በተጨማሪ በትንቢቶቹ በኩል ለየትውልዱ ለይቶ የሚናገረው መልዕክት ይዟል፣ ትንቢቶቹም በባለፈውና በዚህ ትውልድ የተረጋገጡ፣ ለመጪው ትውልድም ተጨባጭ የሆኑ መሆናቸውን ስንመለከት መጽሐፉ በሰዎች እጅ ይፃፍ እንጂ ያፃፈው ልዕለ አዕምሮአዊ አምላክ መሆኑን ያሳያል፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

1. በቀደመው ትውልድ የተረጋገጡ

በቀደመው ትውልድ የተረጋገጡትን በሙሉ መዘርዘር ባይቻልም ለምሳሌ ያህል የኢየሱስን የህይወት ታሪክ እንመልከት፣

ተቁ	የተነገረው ትንቢት	የተነገረበት		የተፈፀመበት ዘመን		የዘመን ልዩነት
		ስፍራ	ጊዜ (approx.)	ስፍራ	ጊዜ	
1	ከድንግል እንደሚወለድ	ኢሳ.7፡14	700ዓ.ዓ	ማቴ.1፡23	33 ዓዓ	667
2	አሳልፎ የሚሰጠው ሰው የሚከፈለው 30 ብር መሆኑ	ዘካ.11፡12	500 ዓ.ዓ	ማቴ.26፡15	000	500
3	ልብሱን ሰዎች እንደሚከፋፈሉ	መዝ.22፡ 18	1000ዓ.ዓ	ዮሐ.19፡23	000	1000
4	እጅና እግሩ እንደሚቸነከር	መዝ.22፡ 16	1000ዓ.ዓ	ዮሐ.20፡ 25	000	1000
5	ጎኑ እንደሚወጋ	ዘካ.12፡10	500ዓ.ዓ	ዮሐ19፡34	000	500
6	በሐብታሞች መቃብር እንደሚቀበር	ኢሳ.53፡9	700 ዓ.ዓ	ማቴ27፡57-60	000	700
7	ከሞት እንደሚነሳ	መዝ.16፡10	1000ዓ.ዓ	ሐስ.2፡31	000	1000

እነዚህ በጥንት ነብያት ስለመሲሁ ሲተነብዩ የነበሩት ትንቢቶች ጊዜያቸውን እየጠበቁ መፈፀማቸውን የአዲስ ኪዳን ዘመን ሐዋርያቶች በአዲስ ኪዳን መጽሐፎቻቸው ውስጥ ማረጋገጣቸው የትንቢቱን ትክክለኛነት ያረጋግጣል፡፡

2. በዚህ ትውልድ የተረጋገጡ

በአሁኑ ዘመን እየተፈፀሙ ያሉ ብዙ ትንቢቶች አሉ፣ ሁሉንም መዘርዘር ባይቻልም አንኳር እንዲሆንልን በሀገራት ደረጃ ያሉትን ክስተቶች ለይተን እንመለከታለን፣ በዚህም ከእስራኤል-ፍልስጥኤም ግጭት፣ ከሶርያ፣ ከቱርክ፣ ከኢትዮጵያንና ከተባበሩት መንግሥታት ጋር በተያያዘ የተነገሩትን ትንቢቶችና እየተከናወኑ ያሉትን ድርጊቶች እንመለከታለን፡፡

የእስራኤል-ፍልስጥኤም ግጭት

ጎረቤታሞቹ እስራኤልና ፍልስጥኤም ከተፈጠሩበት ጊዜ አንስቶ እርስ በርስ ሲጋጩ የኖሩ ህዝቦች ናቸው፣ ይህንን ታሪክ ከስር መሠረቱ ብንመለከት፣

> ዘፍ.25፡21-25 “ይስሐቅም ለሚስቱ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ፣ መካን ነበረችና እግዚአብሔርም ተለመነው፣ ርብቃ ሚስቱም ፀነሰች፡፡ ልጆችም በሆድ ውስጥ ይገፋፉ ነበር፤ እርሷም፡- እንዲህ ከሆነ ይህ ለእኔ ምኔ ነው? አለች፡፡ ከእግዚአብሔርም ትጠይቅ ዘንድ ሄደች፡፡ እግዚአብሔርም አላት፡- ሁለት ወገኖች በማህፀንሽ ናቸው፣

ሁለቱም ህዝቦች ከሆድሽ ይከፈላሉ፤ ህዝብም ከህዝብ ይበረታል፤ ታላቁም ለታናሹ ይገዛል፡፡ ትወልድ ዘንድ ዘመኗ በተፈፀመ ጊዜም እነሆ በማፀንዋ መንታ ነበሩ፣ በፊትም የወጣው … ዔሳው ተባለ፡፡ ከዚያም በኋላ ወንድሙ ወጣ፣ በእጁም የኤሳውን ተረከዝ ይዞ ነበረ፣ ስሙም ያዕቆብ ተባለ፡፡"

ዛሬ የእስራኤል ህዝብ የሚባለው የያዕቆብ ዘር ነው፣ ፍልስጥኤምን ስንመለከት፣ ፍልስጥኤም ከኖህ ዘመን ቀጥሎ በነበሩት ትውልዶች የካም ልጅ(የኩሽ ወንድም) የነበረው የምፅራይም ዘሮች መኖርያ ሀገር ነበረች(ዘፍ.10፡6-14)፣ ከነያዕቆብ ትውልድ ጀምሮ ግን ፍልስጥኤም የኤዶምያስ ህዝቦች መኖርያ እንደሆነችና ኤዶምያስ ደግሞ የዔሳው ዘር እንደሆነ ዘፍ.36፡1, አሞ.1፡11 እና ትንቢተ አብድዩ ምዕራፍ አንድ ላይ እንመለከታለን፡፡

በዚህም እስራኤልና ፍልስጥኤም የሚባሉት ዘሮች ከእናታቸው ከርብቃ ማህፀን ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ እየተጣሉ ያሉት የያዕቆብና የዔሳው ዘሮች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በዚህ ዘመን ያለውን ግጭትም ከስር መሠረቱ ብንመለከት፣ በመጀመርያ እግዚአብሔር፣ የእስራኤል ህዝብ በሰራው ጥፋት መቀጣጫነት በፍልስጤማውያን ከሀገራቸው እንደሚባረሩ ተናገረ፣

ኢሳ.9፡12 "ጠላቶቹን ሶርያውያንንም ከምስራቅ፣ ፍልስጥኤማውያንንም ከምዕራብ ያንቀሳቅስበታል፤ እስራኤልንም በተከፈተ አፍ ይበሉታል፡፡ በዚህም ሁሉ እንኳ ቁጣው አልተመለሰች …"

በዚህ ትንቢት መሠረትም እስራኤላውያኑ በፍልስጥኤማውያንና ሶርያውያን ተገፍተው ከሀገራቸው ተባረሩ፣ ፍልስጥኤማውያኑም የእስራኤልንም መሬት ተካፈሉ፡፡ የእግዚአብሔር ቅጣት ሲያልቅም እግዚአብሔር እስራኤላውያኑን ወደ ሀገራቸው ለመመለስ ተነሳ፣ በያዕቆብ ላይ እጁን ያነሳ መቀጣት ስላለበትም ፍልስጥኤማውያኑ በያዕቆብ ልጆች እንደሚቀጡ አስቀድሞ ተናገረ፣

- አብድ.1፡10-18 "በወንድምህ በያዕቆብ ላይ ስለ ተደረገ ግፍ እፍረት ይከድንህል… በፊቱ አንፃር በቆምህ ቀን፣ አህዛብ ጭፍራውን በማረኩበት፣ እንግዶችም በበሩ በገቡበት፣ በኢየሩሳሌምም እጣ በተጣጣሉበት ቀን አንተ ደግሞ ከእነርሱ እንደ አንዱ ነበርህ፡፡ ነገር ግን በመከራው ቀን ወንድምህን ትመለከት ዘንድ በጥፋታቸው ቀን በይሁዳ ልጆች ላይ ደስ ይልህ ዘንድ፣ በጭንቀት ቀን በትዕቢት ትናገር ዘንድ አይገባህም ነበር፡፡ በጥፋታቸውም ቀን በህዝቤ በር ትገባ ዘንድ፣ በጥፋታቸው ቀን መከራቸውን ትመለከት ዘንድ፣ በጥፋታቸው ቀን በሐብታቸው ላይ እጅህን ትዘረጋ ዘንድ አይገባህም ነበረ፡፡ የሸሹትንም ለመግደል በመንታ መንገድ ላይ ትቆም ዘንድ፣ በጭንቀትም ቀን ከእርሱ የቀሩትን አሳልፈህ ትሰጥ ዘንድ አይገባህም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ቀን በአህዛብ ሁሉ ላይ ቀርቧልና አንተ እንዳደረግኸው እንዲሁ ይደረግብሀል፣ ፍዳህም በራስህ ላይ ይመለሳል … የያዕቆብም ቤት ሰዎች ርስታቸውን

ይወርሳሉ፡፡ እግዚአብሔርም ተናግሮአልና የያዕቆብ ቤት እሳት … የዔሳው ቤት ገለባ ይሆናሉ፤ እነርሱንም ያቃጥሉአቸዋል ይበሉአቸውማል …"

- ኢዩ.3፡1-2 "እነሆም በዚህ ወራትና በዚህ ዘመን የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ … ስለ ህዝቤና ስለ ርስቴ ስለ እስራኤል በአህዛብ መካከል የበተኑአቸውን ምድሬንም የተካፈሉአት እፋረድባቸዋለሁ፡፡"

በዚህ ቃል መሠረት ዛሬ የእስራኤል ምርኮ ተመልሶ፣ እስራኤል እንደ ሀገር ተመልሳ ተመስርታና የእስራኤልን ምድር የተካፈሉት ደግሞ ተመልሰው ችግር ውስጥ ገብተዋል፣ ዛሬ ላይ ፍልስጥኤም የገባበት መከራም ከዚሁ የመነጨ ነው፡፡

ይህ በርብቃ ማህፀን ውስጥ የተጀመረው ግጭትም ቋሚ ሆኖ ለዘመናት ቀጥሏል፣ ዛሬ በሽምግልናቸው ታዋቂ የሆኑትና ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑት ኃያላን ሀገራት እንኳን ለዚህ በርብቃ ማህፀን ውስጥ ለተጀመረው ፀብ መፍትሄ ለማፈላለግ ላይ ታች ቢሉም መፍትሄ ማምጣት ግን አልቻሉም፡፡ ነብዩ አብድዩ(አባዲ) ደግሞ የሁለቱን ህዝቦች ፀብ የእግዚአብሔርና "ኮከቤን ከሁሉም በላይ ከፍ አደርጋታለሁ" የሚለው የዲያብሎስ ፀብ አድርጎ የተመለከተበትን መንገድን ስንመለከት ደግሞ የሁለቱ ህዝቦች ፀብ መቋጫ እንደማይኖረው እንመለከታለን፡፡

<u>ሶርያ</u>

ማርች 15, 2011 በሠላማዊ ሰልፍ የተጀመረው የሶርያ አብዮት በሂደት ከቁጥጥር ውጪ እየወጣ ብዙ ኃይላትን በተቃራኒ ቡድን እያሳለፈ በተለይ ከ2013 ጀምሮ በሀገሪቱና በህዝቦቿ ላይ ብዙ ውድመትን ይዞ መጣ፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ይህንን ውድመት ከነጊዜው ጭምር አስቀድሞ አስልቶ ተናግሯል፣

- ኢሳ.7፡8 "የሶርያ ራስ ደማስቆ ነው፣ የደማስቆም ራስ ረአሶን ነው፣ <u>በስድሳ አምስት ዓመት</u> ውስጥ ኤፍሬም ይሰባበራልና ሕዝብ አይሆንም፤"
- ኢሳ.17፡1-2 "ስለ ደማስቆ የተነገረ ሸክም፡፡ እነሆ ደማስቆ ከተማ ከመሆን ተቋርጣለች፤ ባድማና የፍርስራሽ ክምር ትሆናለች፡፡ <u>ከተሞቿ</u> ለዘላለም የተፈቱ ይሆናሉ …"

እነዚህ ነብዩ ኢሳያስ ከ2,700 አመታት በፊት ስለ የሶርያ(ደማስቆ) ውድመት የተናገራቸው ትንቢቶች ናቸው፣ ኢሳያስ ትንቢቱን "ስድሳ አምስት አመት ውስጥ" ያለው የእስራኤል ምሥረታን 1948ን መነሻ በማድረግ ነው፣ ከእስራኤል ምሥረታ በኋላ 65 አመታትን ስንቆጥር የሶርያ ነገር ከሶርያውያን እጅ ወጥቶ በውጪ ኃይላት እጅ የወደቀበትና ፍፁም ውድመት፣ እልቂት፣ ስደት … መከናወን የጀመረበት ጊዜ ነው፡፡

ቱርክ

ቱርክ ለእስራኤል ካላት ጂኦግራፊያዊ ቀረቤታ አንፃር ሐዋርያቱ ብዙ ጊዜ ጎብኝተዋታል፣ ቤተክርስቲያንም መስርተውላታል ነገር ግን በወቅቱ ሐዋርያቱ በተለያዩ አካባቢዎች ከመሠረቷቸው አብያተ ክርስቲያናት መካከል የተሳሳተ አሰራር በመከተላቸው ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ሰባቱ የኢሲያ አብያተ ክርስቲያናት መካከል አንዷ የቱርካ የኤፌሶን ቤተክርስትያን ነበረች፣ የተሰጣትም ማስጠንቀቂያ፣

> ራዕ.2፡1-5 "በኤፌሶን ወዳለው ቤተክርስቲያን … ንስሀም ባትገባ መቅረዝህን ከስፍራው እወስዳለሁ፡፡"

እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ "መቅረዝ" ማለት "ወንጌል" ማለት ነው፣ በዚህም እንደ ክርስትናው አገላለፅ ቤተክርስቲያኗ በተነገራት ማስጠንቀቂያ ባለመመለሷ መቅረዝዋ ከስፍራው ተወስዶባት የአውሮፓ ብቸኛዋ የሰለመች ሀገር ሆናለች፡፡

ኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ታያልና ትዕቢተኛ ሀገር ነበረች፣ በድሮው ዘመን ግዙፍ የጦር ሠራዊት ነበራት፣

> 2ዜና.14፡9-13 "ኢትዮጵያዊውም ዝሪ አንድ ሚሊዮን ሰዎችና ሦስት መቶ ሰረገሎች ይዞ ወጣባቸው፣ ወደ መሪሳም መጣ፣ አሳም ሊጋጠመው ወጣ፣ በመሪሳ አጠገብ ባለው በፅፋታ ሸለቆ ውስጥ ተሰለፉ፡፡ አሳም አቤቱ በብዙም ሆነ በጥቂቱ ማዳን አይሳንህም፣ አቤቱ አምላካችን ሆይ ባንተ ታምነናልና በስምህም <u>በዚህ ታላቅ ወገን ላይ</u> መጥተናልና እርዳን፣ አቤቱ አምላካችን አንተ ነህ፣ ሰውም አያሸንፍህ ብሎ ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ፡፡ <u>እግዚአብሔርም በአሳና በይሁዳ ፊት ኢትዮጵያውያንን መታ፣ ኢትዮጵያውያንም ሸሹ፡፡</u> አሳም ከእነሱ ጋር ያለው ህዝብ እስከ [22] ጌራራ ድረስ አሳደዱዋቸው፡፡"

ይህ የኢትዮጵያ የትዕቢተኝነት ታሪክ የጥንት ዘመን ታሪክ ብቻ አይደለም፣ መጽሐፍ ቅዱሱ በደርግ ጊዜ የነበረውን ትዕቢትም ቀድሞ ተናነሯል፣ ይህ ቃል የተነገረው ከቤተእስራኤላውያኑ ወደ ሀገራቸው የመመለስ ታሪክ ጋር በተያያዘ ነው፡፡

ለእስራኤል ቤተ እስራኤላውያንን ከዓለም የማሰባሰቡ ስራ ያን ያህል ከባድ ስራ አልነበረም ነገር ግን ምንም ጠላትነት ካልነበራት ኢትዮጵያ ውስጥ የማስወጣቱ ስራ ያልተጠበቀ ከባድ ስራ ነበረ፣ ደርግ ያለምንም ምክንያት ቤተእስራኤላውያኑ "ከኢትዮጵያ አይወጡም" አለ፡፡ በዚህም በወቅቱ በተለይ በ"ኦፐሬሽን ሞሰስ" ብዙዎቹ ከኢትዮጵያ

[22] ጌራራ ማለት የስዊዝ ካናል ሳይከፈት በፊት ኢትዮጵያውያን በእግር ወደ እሥራኤል የሚሄዱበት መንገድ ላይ የነበረች፣ ከእሥራኤል በአዜብ(በደቡብ ምዕራብ) አቅጣጫ፣ ጋዛ አካባቢ የምትገኝ ከተማ ናት፣ በዚህች ከተማ አብርሃምም ይስሐቅም ኖረዋል(ዘፍ.10፡19, ዘፍ.20፡1, ዘፍ.26፡6 …)

እንዲወጡ የተደረጉት በድብቅ በሱዳን በኩል በእግር ስለነበረና በሱዳን ከነበረው ማከማቻ ካምፕም ችግር የተነሳ ብዙ ሰዎች አለቁ፣ "ኦፐሬሽን ሰሎሞን" ደግሞ የተደረገው በአዲጋ ጥላ ስር ነበረ፣ ይህም የኢህአዴግ ሠራዊት አዲስ አበባን ከቦ በነበረበት፣ የደርግ ሠራዊት በቦሌ አውሮፕላን ጣብያ ላይ እገዳ በጣለበትና የወያኔ አየር መቃወሚያዎች የአዲስ አበባን ሰማይ ወጥረው በያዙበት ሁኔታ ውስጥ ነበረ።

ሁለቱም ኦፐሬሽኖች (Operation Moses & Operation Solomon) በጭንቅ ውስጥ የተሰሩ ውጤታማ ኦፐሬሽኖች ስለነበሩ የስለላ ድርጅቱ እነዚህን ኦፐሬሽኖችን ከድርጅቱ ተአምራዊ ኦፐሬሽኖች ውስጥ አስቀምጧቸዋል።

እስራኤላውያኑን ወደ ሀገራቸው የማሰባሰብ ስራ ውስጥ የእስራኤል ጠላት ካልሆነችው ከኢትዮጵያ የማስወጣቱ ስራ ከባድ እንደሚሆን ቀድሞ መጽሐፍ ቅዱሱ በኢሳ.43፡5 ላይ ጠቆም አድርጎ ነበረ፣

> ኢሳ.43፡5-6 "... ዘርህንም ከምስራቅ አመጣዋለሁ፣ ከምዕራብም አሰበስበዋለሁ፣ ሰሜንን መልሰህ አምጣ(እላለሁ)፣ ደቡብንም <u>አትከልክል</u>።"

መፅሐፍ ቅዱሱ ላይ በወቅቱ "ደቡብ" ተብላ የተገለፀችው ኢትዮጵያ ናት፣ ይህንንም ለመረዳት ሉቃ.11፡31 ላይ አማርኛው "ንግሥተ አዜብ" የሚላትን እንግሊዘኛው "The Queen of the South" ይላታል፣ [23]ጥንታዊያኑ የግብፆች የፓፒረስ ፅሁፎችም(ሂሮግሊፍ) ኢትዮጵያን "ደቡብ" ይሏታል እንደዚሁ እስራኤላውያኑ ከተበተኑባቸው ሀገራት ውስጥ ከእስራኤል አንፃር በደቡብ አቅጣጫ የምትገኘው ኢትዮጵያ ናት፣ በዚህም መጽሐፉ "ደቡብ" የሚላት ኢትዮጵያን መሆኑ ግልፅ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሱ ደቡብን ለይቶ "አትከልክል" ማለቱና ኢትዮጵያ ያለ ምንም ምክንያት እስራኤላውያኑ ከሀገር እንዳይወጡ የከለከለችበት ሁኔታ በዚህ ትንቢት ውስጥ ቀድሞ ተነግሮ እንመለከታለን።

<u>የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት</u>

ከኢየሱስ መወለድ ከ600 አመታት በፊት የተፃፈው መጽሐፈ ዳንኤል ምዕራፍ 2 ላይ ስለ ዓለማቀፋዊ መንግሥታት ታሪክ በወፍ በረር ዕይታ ፅፏል፣ ከነገሥታቱ ውስጥ የመጨረሻው በዓለም ላይ ስለሚነግሠው መንግሥት ሲናገር፣ ይህ መንግሥት ከሌሎቹ ነገሥታት በተለየ ጠንካራ እንደሚሆን ነገር ግን መንግሥቱ "የሸክላና ብረት ድብልቅ" እንደሚሆን ይናገራል፣ ይህ "ጠንካራ" ነገር ግን "የሸክላና ብረት ድብልቅ" የተባለው ደካማና ጠንካራ ሀገራት መንግሥታትን አደባልቆ እየመራ ያለው የተባበሩት መንግሥታት ነው።

[23] ተክለፃድቅ መኩሪያ(1965)፣ **የኢትዮጵያ ታሪክ - ኑቢያ**፣ ገፅ 1-2

የሚገርመው ደግሞ ይህ መንግሥት የሚወድቀው በእስራኤል ላይ ጦር በማዝመቱ ምክንያት መሆኑ፣ በዚህም አደገኛ ጦርነት ምክንያት የዓለም መንግሥት ፍፃሜ እንደሚመጣና የኢየሱስ መንግሥት ምሥረታ እንደሚጀመር ከታች(ዓለምና እስራኤል) በሚለው ርዕስ ስር በዝርዝር ቀርቧል፡፡

3. <u>ለወደፊቱም ተጨባጭ ትንቢቶች ማስቀመጡ</u>

ለወደፊቱ ዓለምና የሰው ልጅ ምን እንደሚሆኑ የሚናገሩትን ትንቢቶች በሙሉ መዘርዘር ባይቻልም፣ ከእነዚህ ውስጥ ለምሳሌ ያህል ሊከሰቱ የተዘጋጁና ዛሬ ምልክታቸውን እየተመለከትን ያለውን የአዲሱ የግብይት ቴክኖሎጂ፣ ወንጌል ለዓለም ሁሉ መሰበክ፣ የሰዎች ፍቅር መቀዝቀዝና በዓለምና እስራኤል መካከል እየተፈጠረ ያለውን ክፍተት እንመለከታለን፡-

<u>መጪው ዘመናዊ የግብይት ቴክኖሎጂ</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ በመጨረሻው ዘመን ግብይት በኢኮሜርስ እንደሚሆን ቀድሞ ተንብዮዋል፣ በ7.3 ክፍልም አሰራሩ ምን ያህል ተግባራዊ ሊሆን እንደተዘጋጀ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡

<u>ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል</u>

ክርስትና ከ2,000 አመት በፊት በአንዱ ኢየሱስ ተጀመረ፣ በመቀጠል 12ቱ ሐዋርያት እያለ ዛሬ ላይ ከ2 ቢሊየን በላይ ደርሷል፣ የዚህን እጥፍ የሚሆኑቱ ደግሞ በተለያየ መንገድ ወንጌሉን ሰምተዋል፡፡ ይህ ሁሉ ደግሞ እየሆነ ያለው መጽሐፍ ቅዱሱ “ከጊዜ በኋላ ይተዋል” እየተባለ ባለበትና እንዲተውም እየተሰራ ባለበት ሁኔታ ውስጥ ነው፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱ ይህንን ሳይሰማ፣ ተከታዮቹ አስር ሺ በማይሞሉበት ጊዜ በተነገረ “በመጨረሻ ዘመን ወንጌል ለዓለም ሁሉ ይሰበካል” ትንቢት መሠረት እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

> ማቴ.24፡14 “ለአህዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካ፣ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል፡፡”

ለዚህም ትንቢት ፍፃሜ መጽሐፍ ቅዱሱ ዛሬ ከየትኛውም ጊዜ በላይ በብዛትና በብዙ ሺዎች ቋንቋዎች እየተተረጎመ፣ እየታተመና እየተሰራጨ ይገኛል፡፡

<u>የሰዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ በመጨረሻው ዘመን የሰዎች ፍቅር እየቀዘቀዘ እንደሚሄድ ይናገራል፣

> ማቴ.24፡12 “ከአመፃም ብዛት የተነሳ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች፡፡”

ይህንን የመጽሐፍ ቅዱሱ ትንቢት በተግባር እየተመለከትነው ያለ እውነታ ነው፡፡

<u>የኤፍራጥስ ወንዝ ይደርቃል</u>

የኤፍራጥስ ወንዝ ከሜሶፖታሚያን ሥልጣኔ ጋር ስሙ ጎልቶ የሚነሳ ታሪካዊና ግዙፍ ወንዝ ነው፣ ወንዙ ከቱርክ የአርሜኒያ ከፍታ ቦታዎች ተነስቶ በሶርያና በኢራቅ አድርጎ ከቲግሪስ ወንዝ ጋር በመቀላቀል ወደ ፐርሺያ ገልፍ የሚፈስ ሲሆን ወንዙ ከ2,800 ኪሜ በላይ የሚረዝም የምዕራብ ኢሲያ ሀገራት ግዙፍ ወንዝ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ግዙፍ ወንዝ ከመጨረሻው ዘመን በፊት(ከሰባተኛው ጽዋ በፊት) እንደሚደርቅ መፅሐፍ ቅዱሱ ይናገራል(ራዕ.16፡12)፣ በአሁኑ ወቅትም እንደ ትንቢቱ የኤፍራጥስ ወንዝ እየደረቀ ይገኛል።

<u>ዓለምና እስራኤል</u>

የእስራኤል ጉዳይ ሲነሳ የዓለም ህዝብ ሁለት ፅንፎችን ይይዛል፣ ይህ በግለሰቦችም በመንግሥታትም ደረጃ ያለ እውነታ ነው፣ መነሻ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ የጥላቻው ጎራ ግን እየገዘፈ እንደሚሄድ መጽሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣ በዚህም ዛሬ ላይ አብዛኞቹ ሀገራት የእስራኤል ደጋፊዎች አይደሉም፣ አሜሪካ ድምፅን በድምፅ የመሻር መብቷን እየተጠቀመች እንጂ የተባበሩት መንግሥታት ብዙ ቦንብ የሆኑ ውሳኔዎችን በእስራኤል ላይ አስተላልፎ ነበረ፣ በአሁኑ ጊዜም አሜሪካ ውስጥ ከሪፐብሊካኖች በስተቀረ አብዛኛው ዲሞክራት ፀረ እስራኤል መንፈስ ውስጥ እየገባ ይገኛል።

ይህ ዓለም ከጊዜ ወደ ጊዜ በእስራኤል ላይ ያለው ጥላቻ እየጨመረ መሄድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው ነገር ግን በነዚህ ጥላቻዎች ውስጥ መጽሐፉ እስራኤልን "ከባድ ድንጋይ አደርጋታለሁ" እንዳለው የሁሉም ጥላቻ ውሀ ሲያነሳ አይታይም፣

> ዘካ.12፡2-3 "እነሆ ኢየሩሳሌምን የመንገድገድ ዋንጫ አደርጋታለሁ ... ለአህዛብ ሁሉ ከባድ ድንጋይ አደርጋታለሁ የሚሸከሙአት ሁሉ እጅግ ይቆስላሉ።"

እስራኤል ዛሬ ከስደት በመመለስና በምዕራፍ ሰባት ከምንመለከተው ቀጣዩ የመከራ ዘመኗ መካከል ትገኛለች፣ በዚህም ይህ ዘመን በአንባራዊነት የእስራኤል የእረፍት ዘመኗ ነው፣ በዚህም የሚነሱባት ሁሉ ይህ ነው የሚባል ጉዳት ሳያደርሱባት ራሳቸውን ጭንቅ ውስጥ ሲከቱ ነው የምንመለከተው። ግብፅ፣ ሶርያ፣ ዮርዳኖስ ... እስራኤልን ወግተው በጦርነቱ ከደረሰባቸው ሽንፈት በተጨማሪ ያተረፉት ግዛታቸውን ለእስራኤል አስረክቦ መቀመጥን ነው፣ ግብፅ የሲናይ በረሀን የተወሰነ ክፍል፣ ሶርያ የጎላን ኮረብታዎችን፣ ዮርዳኖስ የዮርዳኖስ ወንዝ አካካቢዎችን ለእስራኤል አስረክበው ቁጭ ብለዋል።

በግለሰቦች ደረጃም ቢሆን ተመሳሳይ ነገር ነው የምንመለከተው፣ ተራ ግለሰቦችን ትተን መሪዎችን እንኳን ብንመለከት፣ የሀገር መሪዎች በእስራኤል ላይ ከተነሱበት ቀን ጀምሮ የሚኖሩት ህይወት የሰቀቀን ህይወት ነው፣ እነዚህ መሪዎችም የፈሩት ነገር ሳይቀርላቸው ከሌሎች መሪዎች ተለይተው እድሜያቸው ሲያጥር ነው የምንመለከተው፣ ከዕድሜ ማጠር በላይ ደግሞ አያያዛቸውና አገዳደላቸው እንኳን በውርደት ነው ለምሳሌ ሙሐመድ ጋዳፊ፣ ሳዳም ሁሴን፣ ሙሐመድ ሙርሲን መመልከት ይቻላል፤ የሀማስና የሂዝቦላህ መሪ

እንደዚሁ የኢራን የኒውክለር ሳይንቲስት መሆን ደግሞ መች እንደሚገደል ያልተነገረውና በሰቀቀን የሚኖር የሞት ፍርደኛ መሆን ነው፡፡

እውነታው በእንዲህ እያለ ዘመኑ ወደ መጨረሻው ሲጠጋ ዓለም ለእስራኤል የሚኖረው ጥላቻና ቁጣ ከላይ በተመለከትነው መንገድ እየጨመረ እየሄደ በመጨረሻም ዓለም በአንድ ላይ ሆኖ "ማን እርሱን ሊዋጋ ይችላል" በሚባል ጦር(ራዕ.13፡4) በእስራኤል ላይ ያዘምታል፣

- ዘካ.2፡3 "የምድር አህዛብ ሁሉ በላይዋ ላይ ይከማቻሉ ..."
- ሉቃ.21፡20 "ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባ ስታዩ ..."

ይህ አደገኛ፣ ከዓለም የተውጣጣ ጦርም እስራኤልን ለሦስት አመት ከግማሽ አሸንፎ ከገዛ በኋላ(ራዕ.11፡2, ራዕ.13፡5)፣ እስራኤል እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ስታነሳ እግዚአብሔርም ለእስራኤል ይነሳል፣

ራዕ.11፡18 "አህዛብም ተቆጡ ቁጣህም መጣ ..."

እንደተባለው እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ በቁጣ ይገለጣል፣ የእስራኤልን ጠላቶች ይመታል(ራዕ.19፡15-21)፣ የአህዛብ ቁጣም በእግዚአብሔር ቁጣ ይደመደማል፡፡

በዚህም ዓለም ለእስራኤል ያለውን ጥላቻ እየጨመረ መሄድ ውስጥ የመጽሐፉን ትንቢት ተጨባጭነት እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ እነዚህን በቀድመው ትውልድና በአሁኑ ትውልድ የተረጋገጠ እና በቀጣዩ ትውልድ የሚሆኑና አሁንም ምልክታቸው እየታዩ ባሉት እውነተኛ ትንቢቶች የመጽሐፍ ቅዱሱን ልዕለ ስብዕናነት እንመለከታለን፡፡

1.4.3. <u>ቅዱሳን መጽሐፍቱ "እስራኤል ከሌላው ዓለም ትለያለች" ማለታቸው ልቦለድ ነው ወይስ በተግባር የሚታይ እውነታ ነው?</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ እስራኤልን ከሌሎቹ ሀገራት በተለየ የተለየ ስፍራ ይሰጣታል፣ ቁርአንም እንደዚሁ፣

> 45፡16 "ለእስራኤል ልጆች መጽሐፍንና ሕግን፤ ነቢይነትንም በርግጥ ሰጠናቸው፡፡ ከመልካም ሲሳዮችም በርግጥ ለገስናቸው፡፡ <u>በዓለማት ላይም አበለጥናቸው</u>፡፡"

መጽሐፍ ቅዱሱ እስራኤል ለእግዚአብሔር ከታዘዘች የተባረከች ሀገር እንደምትሆን ካልታዘዘች ደግሞ የመከራ ሀገር እንደምትሆን አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

በመጀመሪያ ፈጣሪ ለእስራኤላውያን ሕግን አወረደላቸው፣ ህጉንም ከጠበቁ እስራኤል የተባረከች ሀገር እንደምትሆን ተናገራቸው፣

> ዘሌ.26፡1-8 "እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝና ለእናንተ ጣኦት አታድርጉ ... ሰንበታቴን ጠብቁ ... በስርዓቴ ብትሄዱ፣ ትዕዛዜን ብትጠብቁ ... ዝናባችሁን በወቅቱ

አዘንባለሁ፣ ምድሪቱም እህልዋን ትሰጣለች ... በምድራችሁ ላይ በፀጥታ ትኖራላችሁ ... ሰይፍ በምድራችሁ አያልፍም፣ ጠላቶቻችሁንም ታሳድዳላችሁ ... ከእናንተም አምስቱ መቶውን ያሳድዳሉ፣ መቶውም አስሩን ሺ ያሳድዳሉ ...”

ይላል፣ እንደዚሁ ደግሞ እስራኤላውያኑ ህጉን ካልጠበቁ ችግር ውስጥ እንደሚገቡ ተናገራቸው፣

ዘሌ.26፡27-33 “... ባትሰሙኝ በትዕቢተኝት ብትሄዱብኝ ... እናንተንም በአህዛብ መካከል እበትናችኋለሁ ... በልባቸው ድንጋጤን እሰድዳለሁ፣ በነፋስም የምትንቀሳቀስ የቅጠል ድምፅ ታሸብራቸዋለች ... የልጆቻችሁን ስጋ ትበላላችሁ ... በአህዛብም መካከል ታልቃላችሁ ... ነገር ግን ... ልባቸው ቢዋረድ ... እኔ ለያዕቆብ የማልኩትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ።”

የእስራኤል ህዝብም ከነዚህ ሁለቱ ትዕዛዞች መካከል አንዱን እንዲመርጥ ተነግሮት ነበረ።

በዚህም መሠረት፣ እስራኤል ለእግዚአብሔር ሲታዘዝ በሠላምና በደስታ ሲኖር ነበረ፣ ሲያጠፋ ደግሞ በብዙ መከራ ውስጥ ሲያልፍ ነበረ፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ላይ ሆነ በታሪክ እንደምንመለከተው የእስራኤል ህዝብ ባጠፋ ቁጥር ለብዙ መከራ ተላልፎ ሲሰጥ ነበረ፣ ለ 400 አመታት በግብፃውያን እጅ(ዘፍ.15፡13, ሐስ.7፡6)፣ ለ 40 አመታት በፍልስጥኤማውያን እጅ(መሳ.13፡1)፣ ለ 70 አመታት በባቢሎን እጅ(ኤር.29፡4-10) ... የከፈሉትን መከራ መመልከት ይቻላል። የሚገርመው ደግሞ እስራኤላውያኑ ተላልፈው በሚሰጡበት ጊዜም ቅጣቱ ከእግዚአብሔር መሆኑን የሚያረጋግጥልን ህዝቡ የሚቀጣው ቅጣት የሰው ዘር አይቶት በማያውቀው ቅጣት መሆኑ ነው፣ ነብያቱ እንኳን የቅጣቱን ክብደት በራዕይ ተመልክተው፣

አሞ.7፡2 “... ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ይቅር እንድትል እለምንሀለሁ ያዕቆብ ታናሽ ነውና እንዴት ይቆማል?”

በማለት ከእግዚአብሔር ጋር ሲከራከሩ እንደነበረ መጽሐፉ ላይ እንመለከታለን።

በዘመናዊው ታሪክና በመጽሐፍ ቅዱሱ ታሪክ ላይ የተመዘገቡትን እነዚህን ቅጣቶች ብንመለከት፣

- ፈርኦን ለ400 አመታት በባርነት ሲገዛቸው ለስራ በማሰብ ሳይሆን “ሆን” ብሎ በብዙ ስራ ሲያስጨንቃቸው(ዘጸ.1፡11) እና የእስራኤል ዘር እንደይበዛ ወንድ ልጅ ሲወለድ እንዲገደል ሲያደርግ ነበረ(ዘጸ.1፡22)፣
- ኢየሱስን ሲገድሉት፣ ማቴ.27፡25 “... ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን” እንዳሉት የተናገሩት ቃል በባዕድ ምድር አግኝቷቸው ከ1933-1945 የነገሠው ሂትለር ከ6 ሚለየን በላይ የሚሆኑትን እስራኤላውያንን በአሰቃቂ ሁኔታ ፈጅቷቸው ነበረ፣

- በእስራኤላዊነታቸው ብቻ ከሌላው ህዝብ ተለይተው እንዲሸበሩ ሲደረጉ ነበረ፣
  - አሞናዊው ናዖስ በተነሳባቸው ጊዜ የእስራኤል ህዝብ በፍራቻ "እንገዛልሃለን" ብለው እንኳን ሽምግልና ሲልኩበት "ለመገዛት ከወሰናችሁ እንኳን ቀኝ አይናችሁን ከውስጣችሁ አውጥቼ ነው የምገዛችሁ" ሲላቸው ነበረ (1ሳሙ.11፡2)፣
  - ኢሳ.3፡12-13 "... ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ወዳሉ 127 ሀገሮች ... በአስራ ሁለተኛው ወር በአዳር በአስራ ሦስተኛው ቀን አይሁድን ሁሉ፣ ልጆችንና ሽማግሌዎችን፣ ህፃናቶችንና ሴቶችን፣ <u>በአንድ ቀን ይገድሉ ዘንድ</u>፣ ምርኮአቸውንም ይዘርፉ ዘንድ ደብዳቤዎች በመልዕክተኞች እጅ ወደ ንጉሡ አገሮች ሁሉ ተላኩ::"
- በአሸናፊነቱ የሚታወቀው የእስራኤል ጦር ወራዳ ሽንፈቶች እንዲከናነብ ተደርጓል፣
  - በቤተመቅደስ ውስጥ በተሰራ እርኩሰት ምክንያት በአንድ ቀን ውጊያ ብቻ 30,000 የእስራኤል ወታደሮች ተገድለዋል (1ሳሙ.4፡10)፣
  - እግዚአብሔር ያልፈቀደውን ጦርነት ጀምረው "ንብ እንዳሳደደችው" እስኪባል ድረስ የእስራኤል ጦር በጠላቶቹ ተመቷል(ዘዳ.1፡44)፣
  - እርኩስ ነገር በማድረጋቸው "ልባቸው ቀለጠ" እስኪባል በጦርነት ውስጥ እንዲሞቱ ተደርገዋል(ኢያ.7፡1-5)፣
- በተለያየ ጊዜ ከደረሰባቸው ረሃብ የተነሳ የእርግብ ኩስ(2ነገ.6፡25)፣ የአህያ ስጋ(2ነገ.6፡25)፣ የሰው ስጋ(ዘሌ.26፡29, 2ነገ6፡25-30) በልተዋል፣
- ወደ ኢትዮጵያ ተሰደው የነበሩት እንኳን "ፈላሻ(ርስት የሌለው)፣ ቀጥቃጭ፣ ቡዳ ..." እየተባሉ ከጎበረተሰቡ ተገልለውና ተወግዘው በብቸኝነት ሲኖሩ ነበሩ፣

እግዚአብሔር እስራኤላውያኑን "ካመፃችሁ እቀጣችኋለሁ" እንዳለው፣ እስራኤላውያኑ ሲያምፁ በተለያየ ጊዜ በአሰቃቂ ቅጣት ቀጥቷቸዋል፣ "እበትናችኋለሁ" እንዳለው ብዙ ጊዜ በትኗቸዋል፣ በተበተኑበትም ሀገርም "እረፍት አታገኙም"(ዘዳ.28፡65) እንደ ተባለው መዘርዘር እስኪያቅት ድረስ መከራቸው በልተዋል፣ "የቅጠል ኮሽታ ታስደነግጣችኋለች" እንደተባሉት (ዘሌ.26፡36) ከጭፍጨፋ የተረፉት እንኳን ከደረሰባቸው ሽብር የተነሳ ድንጉጦች ሆነው ነው ከቅጣቱ የወጡት::

ቅጣቱ ከፈጣሪ በመሆኑንም በየቅጣቶቹ ውስጥ ሁለት ቋሚ አሰራሮች እንመለከታለን፣ ለመበተን አደጋ ተላልፎ መሰጠትና ከተፈጥሮአዊው አሰራር ውጪ የህዝቡ ቋንቋ፣ ባህልና ኃይማኖት ሳይበረዝ፣ ከ12ቱ ጎሳ አንዱም ጎሳ ሳይጎድል የመሰብሰብ አሰራር:: በታሪክ እንደሚታወቀው ብዙ ህዝቦች ሀገራቸውን ለቀው ተበትነዋል ነገር ግን ተሰብስበው ተመልሰው ሀገራቸውን የመሠረቱ የሉም፣ ሁሉም በተበተኑበት ባህል፣ ቋንቋና ብሔር መካከል ተውጠው ቀርተዋል፣ የእስራኤል ግን ከዚህ የተለየ ነው፣ መበተን ብቻ ሳይሆን እስራኤላዊ ማንነት ሳይጎድል መልሶ የመሰብሰብ ቋሚ ሂደትን እንመለከትባቸዋለን::

ከነዚህ “የመበተንና የመሰብሰብ” ታሪኮች መካከል በቅርብ የነበረውንና ሁላችንም የምናውቀው የ1948 መሰብሰብና እንደ ሀገር መደራጀት ብንመለከት በውስጡ ብዙ ተአምራዊ ነገሮችን እንመለከትበታለን፡፡ እስራኤል ኢየሱስን ሲገድሉት “ደሙ በልጆቻችን” እንዳሉት(ማቴ.27፡25)፣

ኢሳ.9፡12 “ጠላቶቹን ሶርያውያንንም ከምስራቅ፣ ፍልስጥኤማውያንንም ከምዕራብ ያንቀሳቅስበታል፤ እስራኤልንም በተከፈተ አፍ ይበሉታል፡፡ <u>በዚህም ሁሉ እንኳ ቁጣው አልተመለሰች …</u>”

በዚህ ትንቢት መሠረትም እስራኤላውያኑ ከመሬታቸው ላይ ተባረሩ “<u>በዚህም ሁሉ እንኳ ቁጣው አልተመለሰች</u>” በሚለው መሠረት ደግሞ እግዚአብሔር የተበተኑትን እንኳን ለሂትለር አሳልፎ ሰጠ፡፡

ከሂትለር እለቂት በኋላ “ወደ ሀገራችሁ ትሰባሰባላችሁ” የተባለው የእግዚአብሔር ጊዜ ሲደርስ “ወደ ሀገራችን” እንመለስ ጥያቄዎች ከህዝቡ መካከል እየተጠናከረ መውጣት ጀመረ፣ ነገር ግን በወቅቱ ይህን ጥያቄ መመለስ የማይታሰብ ነገር ነበረ ምክንያቱም ሀገራቸው ላይ ሙሉ በሙሉ አረቦች ሰፍረውበት ስለነበረ፣ በዚህም ኃያላኑ ሀገራት አንድ መፍትሄ አቀረቡ ወደ ነበሩበት ሀገር ከመመለስ ይልቅ “አፍሪካ ውስጥ ሰው ከማይኖርባቸው ሰፋፊ ለም መሬቶች ውስጥ አንዱን ስፍራ በማካለል እስራኤል የምትባል ሀገር በመስራት እስራኤላውያኑ ወደዚህ ስፍራ በመሄድ የራሳቸውን ሀገር እንዲመሠርቱ፡፡”

ነገር ግን የፈጣሪ ቃል “ወደ ሀገራችሁ ትሰበሰባላችሁ” ስለነበረ እስራኤላውያኑ አውቀውም ይሁን ሳያውቁ ይህንን አማራጭ ሐሳብ ውድቅ አደረጉ፣ በአረቦች የተያዘውን መሬታቸውን በጦርነት በማስለቀቅ መልሰው መያዙ አማራጭ የሌለው ምርጫ አደረጉ፣ ነገር ግን በወቅቱ ይህን ማከናወኑ የማይታሰብ በሰውኛ አስተሳሰብ “የእብደት” ዕቅድ ነበረ፣ ምክንያቱም በእስራኤል መሬት ላይ አረቦች ሰፍረዋል፣ አካባቢውን የምትገዛው እንግሊዝም ሐሳቡን አልተቀበለችም፣ የእስራኤል መሬት የሚጎራበተው በአረቦች በመሆኑ ወታደራዊ ቤዝ ማግኘት አይቻልም፣ ከሂትር ጭፍጨፋ የተረፈውን ጥቂት ወጣት መልሶ ወደ ጦርነት መማገድ ሞራላዊ አልነበረም፣ ጦርነቱ የሚካሄደውም በግለሰብ ደረጃ በተሰበሰቡ ቡድኖች እንጂ ከጀርባቸው የተደራጀ ሀገራዊ ድጋፍ በሌለበት ሁኔታ ነበረ፡፡

በነዚህ ችግሮች መካከል ግን “የማይሳካ” የሚያስብል የጦርነት እቅዶች ተሰሩ፣ ጦርነቱም ተጀመረ ነገር ግን ከእስራኤላውያኑን እቅድ ጀርባ ልዕለ ስብዕና ያለው አካል እንዳለ ባስመሰከረ መልኩ እስራኤላውያኑ <u>ማሸነፍ የማይችሉትን ጦርነት</u> <u>በአጭር ጊዜ</u> ተአምራዊ በሆነ መንገድ አሸነፉ፣ ከዚያም እስራኤል የምትባለውን ሀገር በመመሥረት ከሂትለር የተረፉት ዜጎቻቸውን ወደ ሀገር በመመለስ በአጭር ጊዜ ውስጥ ስፍራውን “እስራኤል” “እስራኤል” እንዲሸት አደረጉት፡፡ የሚገርመው ደግሞ ይህ ተአምራዊ ፍጥነት አስቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበረ፣

ኢሳ.66፡8 “ከቶ እንዲህ ያለ ነገር ማን ሰምቶአል? እንዲህስ ያለ ነገር ማን አይቶአል? በውኑ አገር በአንድ ቀን ታምጣለችን? ወይስ በአንድ ጊዜ ህዝብ ይወለዳልን? ጽዮን እንዳማጠች ወዲያው ልጆችዋን ወልዳለችና፡፡”

በክስተቱም ሀገር የሚያክል ነገር በአንድ ጊዜ ሲወለድ ተመለከትን፣ በተለያዩ ነብያት ሲነገር የነበረው የእስራኤል ዳግም ምሥረታ ተፈፀመ፣

ሕዝ.38፡8-9 “ከብዙ ዘመን በኋላ ትፈለጋለህ፤ በኋለኛው ዘመን፣ የዘላለም ባድማ በነበሩ በእስራኤል ተራሮች ላይ ከብዙ ህዝብ ውስጥ ወደ ተሰበሰበች፣ ከሰይፍ ወደ ተመለሰች ምድር ትገባለህ፣ እርስዋም ከህዝብ ውስጥ ወጥታለች ሁሉም ሳይፈሩ ይቀመጡታል፡፡ አንተም ትወጣለህ እንደ ዐውሎ ነፋስም ትመጣለህ አንተና ጭፍሮችህ ሁሉ ከአንተም ጋር ብዙ ህዝብ ምድርን እንደ ደመና ትሸፍናላችሁ፡፡”

እስራኤልም በተሰጣት የተስፋ ቃል ከተመሠረተች በኋላ በተለያዩ ጊዜያት ከአረቦች በተነሱባቸው የመልሶ ማጥቃት ጦርነቶች አስከፊ ጦርነቶች ውስጥ ብታልፍም ጦርነቶች ግን እስራኤል ላይ ያን ያህል ጉዳት ሳያደርሱ ይባሱኑ ለእስራኤል ተጨማሪ መሬቶችን ሲያስገኙ ነበረ፡፡

አሁን እስራኤል በጠላቶቿ መካከል እየኖረች ያለችው በ“ከስደት ተመላሽ” መንፈስ ሳይሆን መጽሐፉ እንዳለው ለጠላቶችዋ “አለቃ” እና “የመንገድገድ ዋንጫ” ሆና ከወዳጆችዋ ጋር ደግሞ “እያቀማጠሏችሁ” በተባለው መንገድ ነው፣

- ሕዝ.38፡ “አንተና ወደ አንተ የተሰበሰቡ ወገኖችህ ሁሉ ተዘጋጁ፣ አንተም ራስህን አዘጋጅተህ አለቃ ሁናቸው፡፡”
- ዘካ.12፡2-3 “እነሆ ኢየሩሳሌምን የመንገድገድ ዋንጫ አደርጋታለሁ … ለአህዛብ ሁሉ ከባድ ድንጋይ አደርጋታለሁ የሚሸከሙአት ሁሉ እጅግ ይቆስላሉ፡፡”
- ኢሳ.66፡12 “እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፡- እነሆ ሠላምን እንደ ወንዝ፣ የአህዛብንም ክብር እንደሚነርፍ ፈሳሽ እመልስላታለሁ፤ ከዚያም ትጠባላችሁ፣ በጫንቃ ላይ ይሸከሙአችኋል በጉልበትም ላይ እያስቀመጡ ያቀማጥሉዋችኋል፡፡”

ዛሬ እስራኤል በጠላቶቿ መካከል እየኖረች ያለችበትን ይህንን ክብር በስጋዊው ዓይን ስንመለከተው ምንጩ በዘመናዊ መንገድ ከተደራጀው መከላከያ ሠራዊቷና ከደህንነት ተቋሟ ነው፣ የእነዚህ ተቋማቶቸዋንም ብንመለከት፣

- የእስራኤል የመከላከያ ተቋም ከትኖውም ኃያል ሀገር መከላከያ ሠራዊት እኩል የተደራጀ፣ “አሉ” የሚባሉ እስከ አቶሚክና ሃይድሮጂን ቦንቦች የታጠቀ፣ የምድርን ክበብነት ዞረው መምታት የሚችሉ የረዥም ርቀት ሚሳኤሎች የታጠቀ፣ ምድራዊዋ እስራኤል ሙሉ በሙሉ ብትጠፋ እንኳን በጠፋችበት ሁኔታ ውስጥ በከርሰ ምድርና በሳተላይቶች ላይ በተጠመዱ የኒውክለር አረሮች ጠላቶቻቸውን መልሰው አመድ

ማድረግ የሚችልበት አቅም ያለው፣ አዕምሮ ያለው በመደበኛ ጦርነት ሊገጥመው የማይችለው ሠራዊት ነው፣

- የእስራኤል የደህንነት ተቋም በዓለም ላይ "አሉ" ከሚባሉ ጥቂት የደህንነት ተቋማት ውስጥ ይመደባል፣ ከአወቃቀሩና ከአሰራሩ ምስጢራዊነት የተነሳም እጁ እስከየት እንደሚረዝም እንኳን አይታወቅም፣ በዚህም ተቋሙ የእስራኤልን ጥቅም ከማስከበር አልፎ ሀገራት እንኳን ችግር ሲገጥማቸው አልፎ ሲረዳቸው ይታያል፣ ብዙ ሀገራትም የደህንነት ስራቸውን ለማዘመን የዚህችን ሚጢጢ ሀገር ድጋፍ ሲጠይቁ ይታያል፡፡

ይህ የደህንነት ተቋም "ሞሳድ" ተብሎ በአዲስ መልክ ይደራጅ እንጂ የእስራኤል ህዝብ የደህንነት ተቋማት ጥቅም የገባው ግን ከጥንት ከነኢያሱ ዘመን (ዘኍ.13) ጀምሮ ነው፡፡

እስራኤል በተመሠረተች በዚህ አጭር እድሜ፣ በትንሽ ጂኦግራፊ ከልል፣ በባዶ የተፈጥሮ ሐብትና በጥቂት የህዝብ ብዛት ይህንን ሁሉ ጥንካሬ ይዛ ያለችው በኃይማኖት፣ በዘር፣ በቋንቋና በባህል አንድ በሆኑ፣ ጂሀድን መጠቀም በሚችሉ፣ በነዳጅ ዘይት ሐብት በተንበሸበሹ ከበርቴ ጠላቶቿ መካከል እንደ ሴንጢ ተሰንቅራ ባለችበትና እነዚህ ጎረቤቶቿም ይህቺን በመካከላቸው የተሰነቀረ ጩቤ መስላ የተቀመጠችውን ሀገር ከመካከላቸው ነቅለው ለማጥፋት የቻሉትን ሁሉ ጥረት በሚያደርጉበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ደግሞ የሁኔታውን ተአምራዊነት ያጎላል፡፡

የሚገርመው ደግሞ ሀገሪቱ በነዚህ ጠላት ጎረቤቶቿን መካከል እየኖረች ያለችው ታፍራና ተከብራ ይባሱኑም እነዚህን ሀገራት በተለያዩ ሜራዎች እያተራመሰቻቸው ነው፣ ለምሳሌ እንኳን ብንመለከት፣

- <u>ከ1980-1988 የቆየው ኢራንና ኢራቅ ጦርነት</u>፡- ሁለቱም ሀገራት ለእስራኤል ጠላቶች በመሆናቸው እስራኤል ለሁለቱም ተፋላሚ ሀገራት የተቃራኒያቸውን ትክክለኛ የስለላ መረጃዎችን ስትሸጥ ነበረ፤ በዚህም ሁለቱን ጠላቶችዋን ማጫረስ፣ መረጃዎችን በከፍተኛ ገንዘብ መሸጥ፣ በሀገራቱ ላይ ያላትን የደህንነት የበላይነት ማሳየት … የመሳሰሉ ጥቅሞችን ከጦርነቱ ስታገኝ ነበረ፡፡
- <u>IS(Isalamic State)</u> የሚባለው ድርጅት ካቋቋሙት ሀገራት ውስጥ አንዷ እስራኤል ናት፣ ሀገሪቱ ይህንን ድርጅት በማቋቋሟም ብዙ ጥቅሞችን አግኝታበታለች፣ "ጠላቶቼ" የምትላቸውን የእስልምና ሀገራት በዚህ ቡድን ሲተራመሱ ነበረ፣ ጠላቶችዋ የሆኑትን ሁለቱን የእስልምና ቡድኖች፣ ሺአና ሱኒ በዚህ እልህ አስጨራሽ ውጊያ ውስጥ እርስ በርስ ሲዋጉ ነበረ፣ እስራኤል በወቅቱ በጋዛ ላይ ፊፅማ የነበረችውን የአንድ ለመቶ እልቂት እንዲረሳ ያደረገችበት ክስተት ነበረ፣ በሊባኖስ ህዝብ መካከል ተደብቆ ለምት አልመች ያላት "ሂዝቦላህ" አይ ኤስን ለመዋጋት

በወጣበት በሶሪያ ሜዳ ላይ ያገኘችበትና የምትፈልጋቸውን አባሎቹን እየመረጠች ለመግደል ሁኔታዎች የተመቻቸላት ጊዜ ነበረ ...

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ እስራኤል ከገፀ ምድር እንድትጠፋ በሚመኙ ጠላቶቿ መካከል እየኖረች ያለችው በሉአላዊነት ይባሱኑም "የመንገድገድ ዋንጫ" እና የሰፈሩ አለቃ ሆና ነው::

እነዚህ የእስራኤል ታሪኮች ያላረጁና ከእስራኤል ምሥረታ ከ1948 ዓ.ም ወዲህ የተፈፀሙ ናቸው፣ ዛሬ ኤቲስቶች መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተነገሩትን የእስራኤልን ታሪኮች እንደ ልቦለድ እንደሚያዩት ሁሉ፣ ቀጣዩ ኤቲስት ትውልድም እነዚህን ታሪኮች "ልቦለድ ናቸው" እንደሚል እሙን ነው ነገር ግን "ውሾቹ ይጮሃሉ ግመሎቹ በመስመር ይጓዛሉ" እንደሚባለው ተረት ታሪኩ ሳይስተዋል የሚፈስ እውነታ ነው::

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ መጽሐፍ ቅዱሱ፣ እስራኤል ለእግዚአብሔር ቃል ከታዘዘች ተከብራ እንደምትኖር ካልታዘዘች ደግሞ እንደምትዋረድ የተናገራቸውን እውነታዎች በተግባር የተረጋገጠ እውነታ መሆኑን ስንመለከት የመጽሐፍ ቅዱሱን እውነተኛነትና ልዕለ ስብዕናነት እንመለከታለን::

1.4.4. በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ የተገለፀትን ታሪኮች በዘመናዊው የታሪክና የአርኪዎሎጂ ጥናቶች ማረጋገጥ ይቻላል? ወይስ ልቦወለዶች ናቸው?

ታሪክና አርኪዎሎጂ የፈጣሪን መኖር ከማይቀበሉት የትምህርት ክፍሎች ውስጥ ናቸው ይሁን እንጂ እነዚህ የሳይንስ ክፍሎች የመጽሐፍ ቅዱሱ ታሪኮች የተዘገቡበት መካከለኛው ምስራቅ ጋር ሲደርሱ ምርምራቸው ከመጽሐፍ ቅዱሱ ዘገባ ጋር አንድ ሆኖባቸዋል::

መጽሐፍ ቅዱሱ ልቦለድ ባለመሆኑ የሰዎችን ማንነትና የክስተቶችን መቼት ያስቀመጠው ከታዋቂ ሰዎችና ክስተቶች ጋር በማገናኘት ነው:: መጽሐፉ የሰዎችን ማንነት ሲናገር አያት ቅድመ አያታቸውን በመዘርዘር ነው፣ ለምሳሌ ያህል የኢየሱስን የዘር ሐረግ ብንመለከት፣

> ማቴ.1፡2-17 "አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፣ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፣ ያዕቆብም፣ ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፣ ይሁዳም ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፣ ፋሬስም ኤስሮምን ወለደ ... እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አስራ አራት ትውልድ፣ ከዳዊት እስከ ባቢሎን ምርኮ አስራ አራት ትውልድ፣ ከባቢሎን ምርኮ እስከ ክርስቶስ አስራ አራት ትውልድ::"
>
> በዚህ የዘር ሐረግ ቆጠራ ውስጥ 42 ትውልዶችን እንመለከታለን የሚገርመው ደግሞ እነዚህ 42 ሰዎችም ዝም ብለው የተዘረዘሩ ሰዎች ሳይሆኑ ብሉይ ኪዳኑ ውስጥ ደግሞ የሰሯቸው ስራዎችና ታሪኮችን በኖሩበት ዘመን ቅደም ተከተል ቀርቧል::

በተመሳሳይ መልኩ መጽሐፉ ከስተቶችንም የዘገበው የክስተቶቹን መቼት(ጊዜና ስፍራ) እንኳን በመግለፅ ነው፣ የሚገርመው ደግሞ የዘመን አቆጣጠር ባልነበረበት ከኢየሱስ በፊት በነበሩትን ዘመናት እንኳን የነበሩት ታሪኮች የተተረኩት ከሌሎች ታዋቂ ታሪኮች ጋር በማገናኘት ነበረ፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- 1ነገ.6፡1 "የእስራኤል ልጆች ከግብፅ ምድር ከወጡ አራት መቶ ሰማንያ አመት በሆነ ጊዜ፣ ሰሎሞን በእስራኤል ላይ በነገሠ በአራተኛው አመት፣ ዚፍ በሚባለው በሁለተኛው ወር የእግዚአብሔርን ቤት መስራት ተጀመረ።"
- 2ነገ.25፡27 "እንዲህም ሆነ፤ የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪን በተማረከ በሠላሳ ሰባተኛው አመት በአስራ ሁለተኛው ወር ከወሩም በሀያ ሰባተኛው ቀን የባቢሎን ንጉሥ ዮርማሮዴቅ በነገሠ በአንደኛው አመት የይሁዳ ንጉሥ ዮአኪንን ከወህኒ አወጣው።"
- አሞ.1፡1 "በቴቁሔ ከላም ጠባቂዎች መካከል የነበረ አሞፅ፣ በይሁዳ ንጉሥ በዖዝያን ዘመን፣ በእስራኤልም ንጉሥ በዮአስ ልጅ በኢዮርብዓም ዘመን፣ የምድር መናወጥ ከሆነበቱ ከሁለት አመት በፊት ..."

ይህ የመጽሐፍ ቅዱሱ የሰዎችን የዘር ሐረግ እያገናኘና ታሪክን ከስፍራና ጊዜ ጋር አስተሳስሮ የማስቀመጥ ባህል ለዚህ ዘመን የታሪክና የአርኪዎሎጂ ግኝቶች ትልቅ የማነፃፀርያ ግብአት እየሆነ ይገኛል። በዚህም በአብዛኛው በመካከለኛው ምስራቅ አካባቢ የተገኙ የታሪክና የአርኪዎሎጂ ግኝቶች ከመጽሐፍ ቅዱሱ ታሪኮች ጋር እየተሰናሰሉ ይገኛሉ፣ ይህም እውነታ የመጽሐፍ ቅዱሱ ትክክለኛነት እያረጋገጠ ይገኛል።

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ የአርኪዎሎጂ ግኝቶች የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪኮች በተግባር የሚያረጋግጡ ኢጋጮች ሆነዋል፣ ለምሳሌ ያህል የሰዶምና ገሞራ ቃጠሎ ታሪክ፣ ኔፊሊም ስለሚባሉ ቁመታቸው 3ሜትር ስለሆኑ ሰዎች ታሪክ፣ የዳይኖሰር ታሪክ፣ የፈርኦን ወታደሮች የቀይ ባህር ታሪክና የከተሞች ቅጥር ግንቦች ታሪኮች በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ የተገኙ የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ በተግባር ያረጋገጡ እውነታዎች ናቸው፣ ቀጥሎ በስፋት ቀርበዋል፣

- **<u>የሰዶምና ገሞራ ቃጠሎ ታሪክ</u>**

መጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት ምዕራፍ 18-19 ላይ የ"ሰዶምና ገሞራ" የሚባሉ ከተሞች ስለ ኃጢያታቸው ብዛት እግዚአብሔር ከሰማይ እሳትና ዲን አዝንቦባቸው እንዳቃጠላቸው የሚገልፅ ታሪክ እንመለከታለን።

አርኪዎሎጂስቶች በነዚህ በተጠቀሱት ስፍራዎች ላይ ባደረጉት ቁፋሮ መጽሐፍ ቅዱሱ እንደሚናገረው በእሳት ተቃጥሎ የተቀበረ ከተማ አግኝዋል።

አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ከተማዋ የተቃጠለችበትን ነገር ሲናገር በደፈናው "ከሰማይ በወረደ እሳት ዲን" ይላል እንግሊዘኛው ግን ከተማዋ የተቃጠለችው ከሰማይ በዘነበባት "Sulfur/brimstone" (የድኝ ድንጋይ) እንደሆነ ይናገራል፣ በስፍራው በቁፋሮና በወንዝ

በተቆረጡ ሸለቆ ግድግዳዎች(Sedimentary Strata) ላይ የሚታየው እውነታም ይኸው ነው፣ የሚገርመው ደግሞ ከእነዚህ ድንጋዮች ላይ አፈሩ ተጠርጎ ክብሪት ሲጫርበት ዛሬ እንኳን ይነዳል።

- **<u>ቁመታቸው 3 ሜትር የሆኑ ሰዎች</u>**

መጽሐፍ ቅዱሱ "ኔፊሊም" የሚባሉ ቁመታቸው ስድስት ክንድ የሚደርሱ ሰዎች በምድር ላይ እንደነበሩ ይናገራል(ዘፍ.6፡4, ዘኁ.13፡32-33, ዘዳ.3፡11...)። በአርኪዎሎጂ ጥናቶችም መጽሐፍ ቅዱሱ እንደተሚናገረው ቁመታቸው 3 ሜትር የሆኑ የሰዎች አጥንቶች ተገኝተዋል።

- **<u>ዳይኖሰር</u>**

ሳይንሱ በጥንት ጊዜ "ዳይኖሰር" የሚባሉ የተለያየ ዝርያ የነበራቸው እንስሳት እንደነበሩ ይነግረናል፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ስለዚህ ከምድረ ገፅ ስለጠፋ የአውሬ ዘር በቀጥታ ባይነግረንም፣ ከሕይወታዊ ፍጥረታት ውስጥ አንድ ማስተካከያ የተደረገበት አውሬ እንዳለ ግን ይነግረናል፣ ይህም አውሬ መጽሐፉ በደፈናው "እባብ" የሚለውና በዛሬ መልካቸው "ተሳቢ እንስሳት" ስር የምንመድባቸው እንደ እባብ፣ ዘንዶ፣ አናኮንዳ ... የመሳሰሉ ዝርያዎች ናቸው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ፣ እነዚህ ተሳቢ እንስሳት ቀድሞ የተፈጠሩት እንደ የትኞቹም የየብስ እንስሳት ከነእግር ነበረ ይሁን እንጂ ከሆነ ጊዜ በኋላ ፈጣሪ የዚህን ዝርያ እግር በማስወገድና በሆዳቸው እንዲሳቡ ሰውነታቸውን እንደ አዲስ አስተካክሎ ሰራ(ዘፍ.3፡14)። የዳይኖሰርን(የትንሹንም ሆነ የግዙፉን ዝርያ) እግሮች በማስወገድ፣ ምድር ላይ መሳብ በሚችልበት ቅርፅና መጠን ሲስተካከል የዛሬዎቹ የእባብ፣ አናኮንዳ፣ ዘንዶ ... እናገኛለን።

ይህ ሳይንሱ እግር የነበረው ዘንዶ (ዳይኖሰር) በጥንት ጊዜ ይኖር እንደነበረ ጥናት ማድረጉና የመጽሐፍ ቅዱሱ ከዘንዶና ዝርያው ላይ እግር እንደተወገደ የዘገበበት እውነታ አስገራሚ እውነታ ነው።

- **<u>የፈርኦን ወታደሮች የቀይ ባህር ታሪክ</u>**

መጽሐፍ ቅዱሱ ዘጸ.14 ላይ እግዚአብሔር እስራኤሎችን ከግብፅ ሀገር ባርነት ሲያወጣ እንዲሄዱ የፈለገው መንገድ ባልነበረበት በባህር ነበረ፣ ከዚያም እግዚአብሔር እስራኤላውያኑን በተአምር ባህሩን ካሻገራቸው በኋላ የፈርኦን ወታደሮች በዚያ መንገድ ሲሄዱ ባህሩን እንደመለሰባቸውና ወታደሮቹ በባህሩ ውስጥ እንደሰጠሙ እንመለከታለን። በዚሁ እስራላውያን በተሻገሩበት የቀይ ባህር ወለል ላይ በተደረገ የአርኪዎሎጂ ጥናትም በባህር ውስጥ ሊገኙ የማይችሉ ሰረገላዎች፣ የጦር መሣርያዎች፣ የሰውና የፈረሶች አፅሞችና የእግር ኮቴ ዱካዎች ተገኝተዋል፣ እነዚህ ግኝቶችም በወቅቱ በአካባቢው ከነበረው ታሪክ

ጋር ሲመሳከር የፈርኦን ወታደሮች የጦር መሣርያዎችና ሰረገላዎች መሆናቸው ተረጋግጧል።

- **<u>የከተሞች ቅጥር ግንቦች</u>**

በድሮ ጊዜ ነገሥታት ራሳቸውንና ህዝባቸውን ከጠላት ለመከላከል ግንቦችን ይሰሩ ነበረ፣ ዛሬም የነዚህን ግንቦች ቅሪቶችን በኢየሩሳሌም፣ ሐረርና በቻይና አካባቢ እንመለከታለን፣ እንደዚህ አይነት መጽሐፍ ቅዱሱ ታሪካቸውን የመዘገበላቸው ታዋቂ ግንቦች ነበሩ፣ እነዚህ ግንቦች በነበሩባቸው ስፍራዎችም በተደረጉ የአርኪሎጂ ጥናቶች ግንቦቹ በቁፋሮ ተገኝተዋል፣ በዚህም የኢያሪኮ ግንብ ቅሪትና የነህምያ ግንብ ቅሪቶች ተገኝተዋል።

ሌሎች ብዙ የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ በተግባር የሚያሳዩ ቅርሶች በእስራኤል ሙዚየሞች ውስጥ ተደርድረው ይገኛሉ፣ ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ምንም እንኳን እስራኤል "ኢየሱስ አልተወለደም ገና ይወለዳል" በማለት አዲሱን ኪዳኑን ባትቀበለውም በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተጠቀሱት የአዲሱ ኪዳን ቁሳቁሶችና ታሪካዊ ስፍራዎች ለምሳሌ፣ የኢየሱስ መቃብር፣ የቃና ዘገሊላ ወይን መጥመቂያ ጋኖች ... እያስጎበኘች ትገኛለች።

ከነዚህ የታሪክና የአርኪዎሎጂ ግኝቶች የምንረዳው የመጽሐፍ ቅዱሱን ትክክለኛነት ነው።

<u>ማጠቃለያ</u>

በዚህ ምዕራፍ በዝርዝር እንደተመለከትነው ኤቲስቶች "ፈጣሪ አምላክ የለም ፍጥረታት የተፈጠሩት በተፈጥሮአዊ የቢግ ባንግና ዝግመተ ለውጥ ሂደት ነው" ቢሉም ይህ አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና የፍጥረታትን ስነስርዓት፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ልዕለ ስብዕናነት፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ለየት አድርጎ የሚመለከታት እስራኤል ከሌሎች ሀገራት የተለየች መሆኗን በመመልከትና በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተፃፉት ታሪኮች በዘመናዊው ታሪክና አርኪዎሎጂ ጥናቶች ማረጋገጥ የሚቻል መሆኑን በመመልከት የአማኞች "ፈጣሪ አምላክ አለ" አስተምህሮ ትክክለኛ መሆኑን፣ በዚህም የኤቲዝም ፍልስፍና የስህተት ፍልስፍና መሆኑን ተመልክተናል።

ዛሬ ላይ ብዙዎች የኤቲዝም ፍልስፍናን አዲስ ፍልስፍና አድርገው ቢያደንቁትም ፍልስፍናው አሸናፊ ሆኖ መውጣት አቅቶት እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር እኩል እድሜ ያለው ፍልስፍና ነው (መዝ.14፡1)። ኤቲስቶች ፍልስፍናቸውን የእውቀት ጥግ አድርገው ቢያደንቁም ውስጡ ግን ባዶ መሆኑን ከላይ በስፋት ተመልክተናል፣ መጽሐፉም እንደዚህ አይነት አጉል ፍልስፍናዎችን ባዶ እንደሚያደርጋቸው አስቀድሞ ተናግሯል፣

> ነቆሮ.1፡19-20 "የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተፅፎአልና። ጥበበኛ የት አለ፣ ፀሀፊስ የት አለ፣ የዚች ዓለም መርማሪስ የት አለ፣ እግዚአብሔር የዚችን ዓለም ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን፣"

በዚህም “ዝግመተ ለውጥ” ዝግመተ አዕምሮ የሆነበትንና “ኤቲዝም” ኡቲዝም የሆነበትን ሁኔታ በግልፅ ተመልከተናል፡፡

ሰዎችም ይህንን ምንም መሠረት የሌለውን የኤቲስትነት አስተምህሮ ሊከተሉ የቻሉት፣ አማኞች እንደሚሉት፣ በተቃራኒ መናፍስታዊ ኃይል አሳሳችነት መሆኑን አሁን በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱም ሰዎች በራሳቸው ላይ በሚፈጥሩት ከፍተት ምክንያት ለተቃራኒው መናፍስታዊ ኃይልና ለማይረባ ፍልስፍና ተላልፈው እንደሚሰጡም አስቀድሞ ተናግሯል፣

> ሮሜ.1፡20-28 “... እግዚአብሔርን እያወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ መጠን ስላላከከበሩትና ስላላመሰገኑት ... እግዚአብሔር ለማይረባ አዕምሮ አሳልፎ ሰጣቸው...”

በዚህም ሰዎች “አወቅን” በማለት ለፈጣሪ ክብር ባለመስጠታቸው ምክንያት ለተረት ተረት መናፍስት ተላልፈው መሰጠታቸውን እንመለከታለን

መጽሐፍ ቅዱሱ ሰይጣንን “አውሬ” ይለዋል፣ ኤቲስቶችም የሰው ዘር የመጣው ከዝንጀሮ መሰል አውሬ እንደሆነ ይናገራሉ፣ የሰው ልጅ ከእንስሳቱ የሚለይበትን ማንነት ይህም ኃይማኖተኝቱን ጥሎ ሲሄድም ይህንኑ እንስሳዊ(አውሬያዊ) ባህሪ እየተላበሰ ይገኛል፣ በዚህ “ፈሪሀ እግዚአብሔር” እያጠፋ ባለው የኤቲስቶች አስተምህሮ ምክንያት በዓለም ላይ ብዙ ኢሰብአዊነትን ይህም ኢተፈጥሯዊነት (ግብረ ሰዶም፣ ጾታ መቀየር ...፣ ኢሞራላዊነት (የሰው ልጅ የሰውነት ክፍል ተሰርቆ የሚሸጥበት፣ ህፃናትና ባልቴቶችን እንኳን የሚደፈሩበት...)፣ ሰይጣናዊነት(ሰውን ከነነፍሱ የሚቃጠልበት፣ ቶርች የሚደረግበት ...)፣ በአጠቃላይ ኤቲስት እየሆነች ባለችው ዓለም ሰብአዊነት በእንስሳዊነት እየተተካ ሲሄድ እየተመለከትን ነው፡፡ በዚህም ኤቲዝም ካለበት መንፈሳዊ ችግር በተጨማሪ ሰዎችን ከሰብአዊነት እያወጣ ለማኅበራዊ ችግርም ምክንያት እየሆነ ይገኛል፡፡

በዚህም ይህንን በሰማይም በምድርም የማይጠቅመውን ኤቲዝምን ወደ ጎን በማድረግ፣ ፈጣሪን በየትኛው ኃይማኖት በኩል እንደሚገኝ ማጥናቱ ተገቢ ነው፡፡ በሚቀጥሉት ምዕራፎችም ይህንን ፈጣሪ የምናገኘው በየትኛው ኃይማኖት አስተምህሮ በኩል ነው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ገለልተኛ በሆነ መንገድ የየኃይማኖቶቹን ቅዱሳን መጽሐፍት አስተምህሮ እንፈትሻለን፡፡ በመቅድም ክፍልም በተመለከቱት ሁለቱ መስፈርቶች መሠረት በቀጣይ ምዕራፎች፣ የአብርሃም ኃይማኖቶችን (እስልምና፣ ኦርቶዶክስ፣ ፕሮቴስታንት...) እና ዋቄፈናን በስፋት እንመለከታለን፡፡

ምዕራፍ ሁለት

2. እስልምና

እስልምና “የአብርሃም ኃይማኖቶች” ከሚባሉት ኃይማኖቶች አንዱ ነው፣ ኃይማኖቱ በ6ኛው ክፍለ ዘመን በነብዩ ሙሐመድ የተመሠረተ ሲሆን የሚመራውም በቁርአንና ሀዲስ በሚባሉት መጽሐፍት ነው፡፡ በእስልምና ቁርአን በቀጥታ ከፈጣሪ ዘንድ የተወረደ መጽሐፍ እንደሆነ የሚታመን ሲሆን ሀዲስ የሚባሉት መጽሐፍት ደግሞ የነብዩን ውሎ፣ አስተምህሮና ልምምዶች የተዘገቡባቸው መጽሐፍት ናቸው፡፡

ቁርአን በ30 ጁዝ(ክፍል) የሚከፈል 114 ምዕራፎች ያሉት የእስልምና ቅዱስ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህቺ መጽሐፍ የተጠቀመችው አማርኛውን የቁርአን ትርጉም ሲሆን የአማርኛው ትርጉም የተሰራው ዋናው መልዕክት እንዳይዛነፍ ሲባል በአማርኛ ሰዋሰው ሳይሆን በዓረብኛው ሰዋሰው በመሆኑ ከቁርአኑ በቀጥታ ተወስደው በዚህች መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን የቁርአኑን ጥቅሶች ለመረዳት ቀስ ብሎ አስተውሎ ማንበብ አስፈላጊ ነው፡፡

ሀዲሳቱን በተመለከተ፣ [24] “የሀዲስ መጽሐፍት ብዛት ብዙ ሺ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶችም ተቀባይነት ያላቸው(Al Kutub al sittah) ስድስት መጽሐፍት ብቻ ናቸው፤ እነሱም፣ ሳሂህ ቡኻሪ፣ ሳሂህ ሙስሊም፣ ጃሚያ አት ቲርሚዲ፣ የአቡ ዳውድ ሱና፣ አቡ አብድር ረህማን እና አቡ አብደላ ሙሐመድ ናቸው፡፡” አንዳንድ የሱኒ ሙስሊሞች “የአቡ አብድር ረህማን” እና “የአቡ አብደላ ሙሐመድ” ሀዲሳት ፋንታ ሌላ ሀዲሳትን ሲያስገበቡ ይታያል፣ በዚህም ይህቺ መጽሐፍ የተጠቀመችው ዋነኞቹንና ለሁሉም የእስልምና ቡድኖች የጋራ የሆኑትን አራቱን ሀዲሳት ብቻ ነው፡፡

ከቁርአኑና ከሀዲሳቱ የተጠቀሱትን ጥቅሶች ከመጽሐፉቱ እያነፃፀራችሁ ማንበብ ለምትፈልጉም ጥቅሶቹ የተጠቀሱበት መንገድ ከታች በቀረበው ማስታወሻ ላይ ተመልክቷል፡፡

[24] ዳግማዊ ኃይለ ሥላሴ (2008)፣ **ኢስላም ምንድነው? ክርስትናስ?**፣ ገፅ 69

ማስታወሻ

ከቁርአኑ የተወሰዱ ጥቅሶች የተቀመጡት የምዕራፍ ቁጥርና የአንቀፅ ቁጥርን በማስቀመጥ ነው፣ ጥቅሶቹንም ከቁርአን ለማነፃፀር አባሪ-II(Annex-II) ይጠቀሙ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ከቁርአን ሲጠቅሱ ሱራ፣ ሱረቱል፣ ሱ.፣ ቁርአን ወይንም ቁ. የሚለውን ቃል ከምዕራፍና አንቀፅ ቁጥሮቹ ፊት ለፊት ያስቀምጣሉ፣ በዚህም የሌሎች ሰዎችን መጽሐፍት ስታነቡ ይህንን የጥቅስ አቀማመጥም ዘዴ እንግዳ ሊሆንባችሁ አይገባም፡፡ ከሀዲሳት የተወሰዱት ጥቅሶች የተጠቀሱት በየራሳቸው መንገድ ነው፣

- ሳሂህ ቡኻሪ በጣም ሰፊ መጽሐፍ በመሆኑ ከዚህ መጽሐፍ የተወሰዱት ጥቅሶች የቀረቡት "ሳሂህ ቡኻሪ፡II፡22፡33" መልክ ሲሆን ሦስቱ ተከታታይ ቁጥሮች የመጽሐፉ ቅፅ(Volume)፡ የመጽሐፉ ምዕራፍና የአንቀፅ ቁጥር ያመለክታሉ፡፡ አንዳንዶች ከዚህ መጽሐፍ ሲጠቅሱ ሳሂህ ቡኻሪ፡II፡22 ሀዲስ 33፣ በማለት ሀዲስ የሚለውን ቃል በመካከል ሲያስገቡ አንዳንዶች ደግሞ በ"ሳሂህ ቡኻሪ፡II፡33" መልክ የመጽሐፉን ምዕራፍ በመተው የመጽሐፉን ቅፅና የአንቀፅ ቁጥር ብቻ ያስቀምጣሉ፡፡
- ከሳሂህ ሙስሊም መጽሐፍ የተጠቀሱት "ሳሂህ ሙስሊም፡II፡22" መልክ ሲሆን ሁለቱ ተከታታይ ቁጥሮች የመጽሐፉ ምዕራፍና አንቀፅ ቁጥርን ያመለክታሉ፡፡ አንዳንዶች ከዚህ መጽሐፍ ሲጠቅሱ ሳሂህ ሙስሊም፡II ሀዲስ 22፣ በማለት ሀዲስ የሚለውን ቃል በመካከል ያስገባሉ፡፡
- ከሌሎቹ ቀሪዎቹ አራቱ ሀዲሳት የተወሰዱት ጥቅሶች በሙሉ የቀረቡት "የመጽሐፉ ስም፡II" መልክ ነው፣ ቁጥሩም የአንቀፅ ቁጥርን ያመለክታል፡፡

በዚህም በዚህ መጽሐፍ፣ ያለ መጽሐፍ ስም በቁጥሮች ብቻ የተቀመጡት ጥቅሶች የተወሰዱት ከቁርአን ሲሆን ከመጽሐፍ ስም ጋር የተቀመጡት ደግሞ ከሀዲሳት የተወሰዱ ናቸው፡፡

ትክለኛዋን ኃይማኖት ለመለየት ለምናደርገው ጥናትም በዚህ ምዕራፍ፡-

- የእስልምናና የአይሁድ/ክርስትና አንድነትና ልዩነት፣
- እስልምና ለማን እንደተላከና ማንን ደግሞ እንደማይመለከት፣
- የነብዩ ሙሐመድና የክርስትናው ኢሳ(ኢየሱስ) ተቃርኖ፣
- የእስልምና ቅዱሳን መጽሐፍት እና የመጽሐፍ ቅዱሱ ተቃርኖ፣
- የእስልምናና የአይሁድ/ክርስትና አምላክ ማንነት ተቃርኖ፣

በስፋት እንመለከታለን፡፡

2.1. <u>የእስልምናና የአይሁድ/ክርስትና አንድነትና ልዩነት</u>

ክርስትናና እስልምና የአብርሃም ኃይማኖቶች እንደመሆናቸው መጠን የሁለቱም መሠረት የአይሁድ ኃይማኖት ነው፣ ክርስትና በ0000 ዓ.ም በኢሳ(ኢየሱስ) ሲመሠረት እስልምና ደግሞ በ6ኛው ክፍለ ዘመን (በእስልምና/በሂጅራ ካሌንደር በ0000 አካባቢ) በነብዩ ሙሐመድ ተመሠረተ::

እስልምና የአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍትን፣ ነብያትን፣ መላዕክትን ... የሚቀበል ሲሆን (2:136, 2:285, 29:46 ...) ክርስትናው ግን የነብዩ ሙሐመድን ነቢይነትና የቁርአንን ቅዱስ መጽሐፍነት በአጠቃላይ በነብዩ ሙሐመድ የተሰራውን የእስልምናን መንገድ አይቀበልም::

አይሁድ/ክርስቲያኑ የእስልምናን መንገድ የማይቀበለው "ኢሳ ተመልሶ ይመጣል ስለዚህ ዘመኑ(ኪዳኑ) የነብዩ ኢሳና የኢንጅል(የወንጌል) ዘመን ነው፣ የነብዩ ሙሐመድ መንገድ ከኢሳ መንገድ ተቃራኒ ነው፣ ቁርአኑም ከመጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ ነው፣ የእስልምናው አምላክና የክርስትናው አምላክ ተቃራኒ ናቸው በሚሉ ምክንያቶች ነው::

የትኛው ትክክለኛ እንደሆነ በዝርዝር የምንመለከት ሲሆን ከዚያ በፊት ግን እስልምና ለማን እንደተላከ አስቀድመን እንመለከታለን::

2.2. <u>እስልምና ለማንስ ተላከ? ማንንስ አይመለከትም?</u>

እስልምና የአብርሃም ኃይማኖቶች ከሚባሉት ኃይማኖቶች ውስጥ እንደመሆኑ መጠን ኃይማኖቱ ከሱ በፊት ለነበሩት የአብርሃም ኃይማኖቶች ለአይሁድና ለክርስትና እውቅና ይሰጣል፣ በዚህም አይሁድ/ክርስቶያኖችን "የመጽሐፍቱ ባለቤቶች" (29:46)፣ "መጽሐፉን የሰጠናቸው" (13:36) "መጽሐፉን የሚያነቡ" (2:113)፣ "ቀድሞ እውቀት የተሰጣቸው"(17:107)፣ "ቀድሞ ያመኑት"(16:102) ... ሲላቸው፣ አይሁድ/ክርስቲያኑም ከቁርአን በፊት የተሰጣቸውን መጽሐፍት አጥብቀው እንዲይዙና በያዙት ኃይማኖት እንዲጠነክሩ ይመክራል (5:66-69, 7:145, 2:121 ...)::

ቁርአኑ ስለወረደበት ምክንያትም ሲናገር "ለአረጋጋጭነት" መሆኑን ብዙ ስፍራዎች ላይ ደጋግሞ ይናገራል(6:92, 2:41, 2:91, 2:97, 3:3 ...)፣ አረጋጋጭነት የሚያስፈልገው ቀደምት ቅዱሳን መጽሐፍት ከፈጣሪ መውረዳቸውን <u>ላላረጋገጡት</u> ማኅበረሰቦች ነው ነገር ግን አይሁድ/ክርስቲያኖች የተሰጣቸውን መጽሐፍት፣ ከቁርአኑ መምጣት በፊት፣ አረጋግጠው ኃይማኖታቸውን አቁመውበት የነበሩ በመሆኑ የቁርአኑ "አረጋጋጭነት" ብሎም እስልምና ለነዚህ አይሁድ/ክርስቲያን ማኅበረሰብ አለመሆኑን እንመለከታለን::

ይባሱኑ ደግሞ ቁርአኑ እንደሚናገረው ቀደምት ለአይሁድ/ክርስቲያኖች የወረዱት መጽሐፍት በጣም የተበራሩ(2:99, 37:117)፣ የተዘረዘሩ(6:98) እንዲሁም ግልፆች(45:17) መሆናቸው፣ ለነብዩ ሙሐመድም እንደ ቀደምት ነብያት ሙሉ እውቀት

ያልተወረደላቸው መሆኑ(40፡78) እና ሙስሊሞችም ከቁርአኑ ያልገባቸውን ነገር ቢኖር ቀድሞ መጽሐፍ የወረደላቸውን አይሁድ/ክርስቲያኖችን እንዲጠይቁ መነገሩ(21፡7) "አረጋጋጭ" የተባለው ቁርአን የተላከው ለአይሁድ/ክርስቲያን ማኅበረሰብ አለመሆኑን ዳግም እንመለከታለን፡፡

ቁርአኑ በአይሁድ/ክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ስላለው ሚና ሲናገር፣

> 16፡102 "እነዚያ ያመኑትን(አይሁድ/ክርስቲያኖች) ለማረጋጋት፣ ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር(ቁርአንን) ቅዱሱ መንፈስ(ጅብሪል) እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው፡፡"

በማለት ቁርአን የወረደው አይሁድ/ክርስቲያኑን በራሱ ኃይማኖት ለማረጋጋት ሙስሊሙን ደግሞ ለመምራት እንደሆነ ይነግረናል፡፡

ታድያ እንዲሰልም ቁርአን የተላከለት ህዝብ የትኛው ነው? ብለን ስንጠየቅ ቁርአኑ "<u>እንደ አይሁድ/ክርስቲያን ነቢይም መጽሐፍም ላልተላከላቸው ማኅበረሰቦች</u>" መሆኑን ደጋግሞ ይነግረናል፣

- 32፡3 "... በእርሱ(በቁርአኑ) ከአንተ በፊት <u>ከአስፈራሪ(ነቢይ) ያልመጣላቸውን ህዝቦች</u> ልታስፈራራበት (ያወረድንልህ) ነው፡፡ እነርሱ ሊመሩ ይከጀላልና(ይፈለጋልና)፡፡"
- 34፡44 "የሚያጠኑዋቸው የኾኑ መጽሐፍቶችን ምንም አልሰጠናቸውም፡፡ ከአንተ በፊትም አስፈራሪ ነቢይን ወደ እነርሱ አልላክንም፡፡"
- 43፡23 "... ከበፊትህ በማንኛይቱም ከተማ ውስጥ እሰፈራሪ አልላክንም..."

በማለት ነብዩ ሙሐመድ ቁርአን/እስልምና ይዘው የመጡት ቀድሞ ነቢይና መጽሐፍት ከተላኩላቸው ከአይሁድ/ክርስትና ውጪ ላሉት ነቢይም መጽሐፍም ላልተላከላቸው ህዝቦች መሆኑን ቁርአኑ ይነግረናል።

ታዲያ እስልምና ተለይቶ የተላከላቸው ህዝቦች የትኞቹ ናቸው? ብለን ስንመለከት፣ ቁርአን እስልምና የተላከላቸው ህዝቦች የትኞቹ እንደሆኑ ለይቶ ይናገራል፣ ይህንንም የሚናገረው ቁርአናዊውን የፈጣሪ አሰራር ጭምር በማስቀመጥ ነው፣ ይህም መልዕክተኛ የሚላከው ለወገኖቹና በወገኖቹ ቋንቋ ብቻ መሆኑ፣

- 14፡4 "ከመልክተኛ ማንኛውንም ለነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ <u>በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አላክንም</u>፣"
- 30፡47 "ከአንተ በፊት መልዕክተኞችን <u>ወደየህዝቦቻቸው</u> በእርግጥ ላክን፡፡"

በዚህም መሠረትም ቁርአንም/እስልምናም የተላከላቸው ህዝቦች፣

> 9፡128 "<u>ከነሳችሁ የሆነ</u> ችግራችሁ በእርሱ ላይ ፅኑ የሆነ፣ በእናንተ (እምነት) ላይ የሚጓጓ፣ በምዕመናን ላይ ሩኅሩኅ አዛኝ የሆነ መልዕክተኛ መጣላችሁ፡፡"

ለተባሉት ለሙሐመድ ጎሳ (ለዓረቦች) ብቻ ነው፣ ይህ እውነታም ቁርአኑ ላይ በግልፅ ቋንቋ ተነግሯል፣

- 44፡58 "(ቁርአኑን) በቋንቋህም ያገራነው (ህዝቦችህ) ይገነዘቡ ዘንድ **ብቻ** ነው።።"
- 42፡7 "እንደዚሁም የከተሞች እናት የሆነችውን (የመካን ሰዎች) እና በአካባቢዋ ያሉትንም ልታስፈራራ ... ልታስጠነቅቅ ዓረብኛ የኾነን ቁርአን ወዳንተ አወረድን።።"

በማለት ቁርአን/ነብዩ ሙሐመድ/እስልምና የተላኩት ለዓረቡ ማኅበረሰብ **ብቻ** መሆኑን ቁርአኑ ይገልፃል።።

ይህ እውነታም ቁርአኑ በደነገጋቸው ኃይማኖታዊ ስርዓቶች ውስጥም ተመልክቷል፣ በእስልምና የተደነገጉት ኃይማኖታዊ ስርዓቶች የታዘዙት ለዓረቡ ዓለም እንጂ አጠቃላይ ዓለምን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት አይደለም፣ በዚህም እስልምናን ለአጠቃላይ ዓለም ሲደረግ ሌላው ዓለም ከእስልምና ስርዓቶች ጋር ይፋለሳል፣ ለምሳሌ፡-

- የስግደት አቅጣጫ ወደ መካ መሆኑ ነገር ግን ይህ አባባል ትክክለኛ የሚሆነው ለዓረቡ አካባቢ እንጂ ሉል(Sphere) በሆነችው ዓለም ላይ ለሚኖሩ ህዝቦች አለመሆኑ፣ ምክንያቱም ሉል በሆነችው ዓለም ከዓረብ አካባቢ እየራቅን በሄድን ቁጥር የመካ አቅጣጫ በአንግል እየተገለበጠ ስለሚሄድ በመካ አቅጣጫ በፍፁም መስገድ የማይቻል መሆኑ፣ በዚህም ወደ መካ ዞሮ መስገድ የሚችለው የዓለም ህዝብ ሳይሆን የአረብ ህዝብ ብቻ መሆኑ፣
- የጨረቃ ለጋነት ለሀጅና ዑምራህ፣ ለጾም ... ምልክት እንደሆነ መነገሩ ነገር ግን የጨረቃን ለጋነት በምልክትነት ተጠቅሞ እነዚህን ኃይማኖታዊ ስርአቶች በትክክለኛ ጊዜው ማከናወን የሚችለው በአንድ በተወሰነ ክልል የሚኖሩ ህዝቦች እንጂ የዓለም ህዝቦች አለመሆኑ።። ለአንዱ ለጋ ጨረቃ፣ ለሌላው ደምቃ የምትታይ ወይንም ስታበራ ከርማ እየገባች ያለች ... መሆኗ፣ በዚህም "የጨረቃ ለጋነት" ምልክት የተሰጠው ለዓለም ህዝብ ሳይሆን ለአረብ ህዝብ ብቻ መሆኑ።።
- የሶላት ሰአቶች በፀሐይ እንቅስቃሴ የሚወሰኑ መሆኑ ነገር ግን የፀሀይ እንቅስቃሴን በምልክነት ተጠቅሞ ሶላት በትክክለኛው ሰአት ማከናወን የሚችለው በአንድ በተወሰነ ክልል የሚኖሩ ህዝቦች እንጂ የዓለም ህዝቦች አለመሆኑ፣ በዚህም በፀሐይ እንቅስቃሴ የሚወሰነውን ሶላት በትክክለኛ ጊዜ መፈፀም የሚችለው የዓለም ህዝብ ሳይሆን የአረብ ህዝብ ብቻ መሆኑ።።
- ሀጅና ዑምራህ ኃይማኖታዊ ግዴታዎች ቢሆኑም ቴክኖሎጂ ባልሰተስፋፋበት ዘመን ሰዎች ከአሜሪካ፣ ከአውስትራሊያ ... ከመሳሰሉ ስፍራዎች በዚህ ስነ ስርዓት ላይ መገኘት የማይችሉ መሆኑና በዚህ ዘመንም ቢሆን የዓለም ህዝብ ቢሰልም ስፍራው ማስተናገድ የማይችል መሆኑ፣ በዚህም የሀጅና ዑምራህን ኃይማኖታዊ ግዴታ መፈፀም የሚችለው የዓለም ህዝብ ሳይሆን የአረብ ህዝብ ብቻ መሆኑ፣

እነዚህና መሰል እውነታዎች እስልምና የተላከው ለዓረቡ ዓለም ብቻ መሆኑን ዳግም ያረጋግጡልናል፡፡ ቁርአኑ ይህ አለመናበብ እንዳይከሰትም ከላይ እንደተመለከትነው በጂአግራፊ ቋንቋ ጭምር "መካና አካባቢዋን" ያለው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡

እነዚህን ከላይ ከቀረቡትን እውነታዎችንም በአንድ ላይ ስንመለከት እስልምና የተላከው ቀድሞ ነቢይና መጽሐፍት ላልተላከላከላቸው ከአይሁድ/ክርስትና ውጪ ላሉና በመካና በአካባቢዋ ለሚኖሩ የዓረብ ህዝቦች ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም ከዓረብ ውጪ የሆኑ ሰዎች ቢሰልሙ እስልምናቸው የተሳሳተ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ሰዎች አልገባቸውም እንጂ ይህ ኃይማኖትን በየማኅበረሰቡና በየማኅበረሰቡ መሪዎች(ነብያት) የመከፋፈል አሰራር ታስቦበት የተደረገው መሆኑን ቁርአን ይናገራል፣

> 5፡48 "ከእናንተ ለሁሉም ሕግንና መንገድን አደረግን፡፡ አላህም በሻ ኖሮ አንድ ህዝብ ባደረጋችሁ ነበር፡፡ ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራች (ለያያችሁ)፡፡ በጎ ስራዎችን ለመስራት ተሽቀዳደሙ፤ መመለሻችሁ በጠቅላላ ወደ አላህ ነው፡፡"

ቁርአኑ ይህንን እውነታ ሲያብራራ፣ በሦስቱም የአብርሃም ኃይማኖቶች (እስልምና፣ አይሁድ፣ ክርስትና) መካከል ያለው ከፍፍል በአላህ ዘንድ እውቅና ያለውና የሦስቱም ኃይማኖት ተከታዮች ገነት እንደሚገቡ፣ ገነት የሚገቡትም በየመሪዎቻቸው መሪነት መሆኑና ለፍርድ የሚቀርቡትም በመሪዎቻቸው በኩል በወረዱት መንፈሳዊ መጽሐፍት መስፈርት መሆኑን ይናገራል፣

- በፍርድ ቀን ሰዎች የሚጠሩት በመሪያቸው መሪነት መሆኑ
  17፡71 "ሰዎችን ሁሉ በየመሪያቸው የምንጠራበት ቀን አስታውስ ..."
- ለአይሁድ(እስራኤል) ህዝብ መሪነት የተሾመው ሙሳ(ሙሴ) መሆኑና የሚዳኙበት መጽሐፍም ተውራት መሆኑ
  - 32፡23 "ሙሳን መጽሐፍን በርግጥ ሰጠነው ... ለእስራኤል ልጆችም መሪ አደረግነው፡፡"
  - 5፡44 "... ተውራት(ኦሪትን) አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነብያት በነዚያ አይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፡፡"
- ለክርስቲያኖች መሪነት የተሾመው ኢሳ(ኢየሱስ) መሆኑና የሚዳኙበት መጽሐፍም ኢንጅል መሆኑ
  - 57፡27"... የመርየም ልጅ ኢሳን አስከተልን፡፡ ኢንጅልንም ሰጠነው ..."
  - 5፡47 "የኢንጅልም ባለቤቶች(ክርስቲያኖች) በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፡፡"
- ለሙስሊሞች መሪነት የተሾመው ሙሐመድ መሆኑና የሚዳኙበት መጽሐፍም ቁርአን መሆኑ
  - 6፡163 "... እኔ የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ፡፡"

- 5፡48 “ወደ አንተ መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲኾን አወረድን፡፡ በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ …”

➢ ሁሉም የሚዳኘው በየራሱ ነቢይ በኩል በተላከለት መጽሐፍ መሆኑ

5፡44-48 “እኛ ተውራትን(ኦሪትን) በውስጧ መምርያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፡፡ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነብያት በእነዚህ አይሁዳውያን በሆኑት ላይ በእርሷ ይፈርዳሉ … ኢንጅልንም(ወንጌልንም) … (ለኢሳ) ሰጠነው፡፡ የኢንጅልም ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ፡፡ ወደ አንተም መጽሐፉን(ቁርአንን) … አወረድን … በመካከላቸውም አላህ ባወረደው ሕግ ፍረድ …”

➢ ገነት የሚገቡት ሦስቱም አይሁድ ክርስቲያንና ሙስሊሞች መሆኑ

- 2፡111-112 “ገነትንም አይሁድ ወይንም ክርስቲያኖች የኾነ ሰው እንጂ ሌላ አይገባትም” አሉ፡፡ ይህቺ ከንቱ ምኞታቸው ናት፡፡ እውነተኞች እንደሆናችሁ ማስረጃ አምጡ በላቸው፡፡ አይደለም (ሌላም ይገባባታል) …”
- 5፡66 “እነርሱም ተውራት(ኦሪት) እና ኢንጂል(ወንጌል) ከጌታቸውም ወደነሱ የተወረደውን መጽሐፍ ባቋቋሙ(በሰሩበት) ኖሮ ከበላያቸውና ከእግሮቻቸው ስራ በተመገቡ ነበረ፡፡ ከነርሱ ውስጥ ትክክለኞች ህዝቦች አልሉ፡፡”
- 5፡68 “እናንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራት(ኦሪት) እና ኢንጂል(ወንጌል) ከጌታችሁ ወደናንተ የተወረደውን እስኪታቆሙ(እስክትሰሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም፡፡”

እነዚህን ሐሳቦች በአንድ ላይ ስንመለከትም ሙሴ የአይሁድ፣ ኢየሱስ የክርስቲያን፣ ሙሐመድ የሙስሊሞች መሪዎች መሆናቸውንና ተከታዮቻቸውም የሚዳኙት ለመሪዎቹ በተሰጡት መጽሐፍት፣ ገነት የሚገቡትም በነዚህ መሪዎቻቸው መሪነት መሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይም፣ እንደ ቁርአን፣ የአይሁድና/የክርስትና ኃይማኖቶች በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የእስልምና እህት የኃይማኖት ድርጅቶች መሆናቸውንና ቁርአን/እስልምና የተላከው ለዓረቡ ማኅበረሰብ ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ በዚህም ከዓረብ ውጪ ያሉት ህዝቦች ቁርአን/እስልምና የማይመለከታቸው መሆኑንና ቢሰልሙ እንኳን እስልምናቸው ቁራናዊ አለመሆኑን ቁርአን ይነግረናል፡፡

ስለዚህ ከዓረብ ዘር ውጪ የሆኑ ሙስሊሞች የቁርአኑ/የእስልምና መንገድ የገነት መሄጃ መንገዳቸው አይደለም፣ በዚህም **እንደ ቁርአኑ** ከዓረብና ከአይሁድ ዘር ውጪ ላለ ማንኛውም ሰው ለገነት መግቢያነት የተቀመጠለት መንገድ በዘር ያልተወሰነውና በደፈናው “ተከታዮቹ፣ የኢንጅል ባለቤቶች …” በተባለው የኢሳን(ኢየሱስን) መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- 57፡27 “… የመርየም ልጅ ኢሳን … ኢንጅልንም ሰጠነው፡፡ በዚያም በተከተሉት (ሰዎች) ልቦች ውስጥ መለዘብንና እዝነትን … አደረግን፡፡”

- 5፡47 “<u>የኢንጅልም ባለቤቶች</u> በውስጡ አላህ ባወረደው ሕግ ይፍረዱ”

የኢሳን *መንገድ* የሚሰብከው ክርስትና የተላከው ለአጠቃላይ የዓለም ህዝብ እንጂ ለአንድ ዘር አለመሆኑ(ዮሐ.6፡33, ዮሐ.8፡26, ዮሐ.18፡20, ሮሜ.11፡15, ገላ.6፡14 …) እንደዚሁ በገነት የሚኖሩት ከሁሉም ዘሮች የሚሰበሰቡ ሰዎች መሆናቸውን(ራዕ.5፡9-10) መናገሩ ያለ ዘር ልዩነት የተከፈተው የገነት *መግቢያ መንገድ* የኢሳ የክርስትና *መንገድ* መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዘር ጉዳዮች በተጨማሪ እስልምና ከጾታ አንፃርም የተለየ አሰራርን ይከተላል ይህም በእስልምና *መንገድ* ወንዶች እንጂ ሴቶች ጀነተ/ገነት አይገቡም፣ ቁርአኑ ይህንን የሚናገረው ሴቶች ያለባቸውን “ችግር” ከመግለፅ አንስቶ በግልፅ ቋንቋ 17፡40 “**<u>ጌታችሁ በወንዶች ልጆች መረጣችሁ</u>** …” በማለት ነው፡፡

ሴቶች በእስልምና *መንገድ* ገነት የማይገቡበት እስልምናዊ ምክንያትም እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

- <u>“እርኩስ ናቸው”</u>
  - 4፡43 “… ከእናንተ አንዱ ከአይነ ምድር ቢመጣ ወይንም ሴቶች ብትነካኩና ውሀን ባታገኙ፣ ንፁህ የሆነ የምድር ገፅ አስቡ፡፡ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁንም (በራሱ) አብሱ፡፡ አላህ ይቅር ባይና *መሃሪ* ነውና፡፡”

  በዚህም ወንዱ ሳያውቅ ቢረክስ በመታጠቡ ይነፃል ነገር ግን ሴትዋ ሴትነትዋ ማንነቷ ነው፣ በዚህም ሴት በሴትነቷ ብቻ ቁርአናዊውን “የቅድስናውን ሕግ” ማለፍ አትችልም፣ “ያልተቀደሰ(እርኩስ)” ደግሞ ገነት አይገባም፡፡
  - ሳሂህ *ሙስሊም* 4፡1038 “ስትሰግዱ ውሻ፣ ሴትና ፈስ ቢያቋርጡ ስግደት ከንቱ ትሆናለች፡፡”

  የተመሳሳይ ሐሳብ ሳሂህ *ሙስሊም* 4፡1032, ሳሂህ ቡኻሪ 1፡9፡490 ላይ ቀርቧል፡፡ እንደ ቁርአኑ እነዚህ ሦስቱ ነገሮች የፀሎት አርካሽ እርኩስ ነገሮች ናቸው፣ “እርኩስ” ደግሞ ገነት አይገባም፡፡
- <u>“በተፈጥሮ ጠማማ ናቸው”</u>

  ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡548 “ሴቶች ከጎድን አጥንት የተፈጠሩ ናቸው፣ የጎድን አጥንት የተጣመመ ነው፣ ላቃናው ብትሉ ይሰበራል፣ ነገር ግን እንደ ጠማማነቱ ብትተዉት እንደተጣመመ ይቀመጣል፡፡”

  ጠማማ ደግሞ ገነት አይገባም፡፡
- <u>“ከምንም ነገር በላይ ጎጂ ናቸው”</u>

  ሳሂህ *ሙስሊም* 36፡6603 “ከሴት ይበልጥ ጎጂ ስቃይ ለወንድ አልተውኩም፡፡”

  የዚህ ተመሳሳይ ሐሳብ ሳሂህ *ሙስሊም* 36፡6604 ላይ ቀርቧል፣

- “የወንዶች ግማሽ ናቸው”
  - 4፡11 “አላህ በልጆቻችሁ (ውርስ በሚከተለው) ያዛችኋል። ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ብጤ አለው።”
  የዚህ ተመሳሳይ ሐሳብ በሳሂህ ሙስሊም 11፡3933 ላይም ቀርቧል።
  - 2፡282 “የሁለት ሴቶች ምስክርነት ከአንድ ወንድ እኩል ነው።”
  የዚህ የዚህ ተመሳሳይ ሐሳብ ሳሂህ ቡኻሪ 3፡48፡826 ላይም ቀርቧል።
- “አዕምሮ ጎዶሎ ናቸው”
  ሳሂህ ቡኻሪ 3፡48፡826 “... ኑብዩም፣ የሴት ምስክርነት የወንድ ምስክርነት ግማሽ አይደል፣” አሉ፣ ሴትየዋም “አዎን” አለች፣ ይህ የሆነው የሴቶች አዕምሮ ጎዶሎ(deficiency in intelligence) በመሆኑ ነው፣ አለ።”
  የዚህ ተመሳሳይ ሐሳብ በሳሂህ ቡኻሪ 1፡6፡301 ላይም ቀርቧል።

በርግጥ ገነት ቅድስና ያላት ስፍራ በመሆኗ እርኩስ፣ ጠማማ፣ ጎጂና ሙሉ ያልሆነ ሰው ሊገባባት አይችልም፣ በዚህም ሴቶች በእስልምና መንገድ ገነት መግባት አይችሉም።

በተቃራኒው ደግሞ ወንዶች በሴቶች ላይ በሚሰሩት ኃጢያት እንኳን ከገነት እንዳይገድሉ “ሴቶችን ከመጉዳት ከሚመጣ ኃጢያት” ተጠያቂነት ነፃ ተደርገዋል፣ በዚህም ወንዱ በህጋዊው እስከ አራት(4፡3) በምርኮ የያዛቸውን እስከ ፈለገው(4፡24) ማግባት፣ ያገባትንም ሲፈልግ መፍታት(2፡227, 33፡51)፣ የፈታትን መልሶ ማግባት(2፡228, 33፡51)፣ በሚስት ስፍራ ሚስት መለወጥ(4፡20)፣ ሚስቱን መደብደብ(4፡34, 38፡44, 70፡30-31)፣ ጊዜያዊ ጋብቻ መፈፀም እንደሚችል(ሳሂህ ሙስሊም 8፡3253፣ ሳሂህ ቡኻሪ 7፡62፡12)፣ ለሴት ገንዘብ ሰጥቶ(4፡24)፣ ሰዓት ሰጥቶ(ሳሂህ ሙስሊም 8፡3252)፣ ልብስ ሰጥቶ (ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡139) ዝሙት መፈፀም እንደሚችል፣ ለሴት የገባውን መሀላ ማፍረስ እንደሚችል(2፡226) ተነግሯል።

ነብዩ ሙሐመድ ደግሞ ከነዚህ በተጨማሪ አስራ አንድ ህጋዊ ጋብቻዎችን(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡5፡268)፣ ውሽሜዎችን መያዝ፣ የውሽሜዎቹን ልጆች ማግባት፣ የአጎት/የአክስት ሴቶች ልጆች ማግባት(33፡50-51)፣ ከባሮች ጋር መተኛት(33፡52)፣ ለአቅመ ሄዋን ያልደረሰች የ9 አመት ልጅ ማግባት(ሳሂህ ቡኻሪ 5፡58፡236) ተፈቅዶላቸዋል።

ወንዱ በገነት ከሚጠብቀው ሽልማቶች አንዱ “በገነት ውስጥ አይናቸው ጎላ ጎላ ያሉ ሴቶች ናቸው”(52፡20-25, 44፡54 ...) ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው በእስልምናው ሴቶች ገነት ስለማይገቡ ቁርአኑ ለሴቶቹ “አይናቸው ጎላ ጎላ ያሉ ወንዶች/ወንድ እንደሚጠብቃቸው” አይናገርም ወይ እነሱ ከባሎቻቸው ቀድመው ሞተው ገነት ገብተው አይኖቻቸው ጎላ ጎላ ተደርጎ ለባሎቻቸው እንደ ሽልማት እንደሚዘጋጁ አይናገርም፣ እንደውም አሁን የሞቱት ሙስሊም ወንዶች 83፡22 “እውነተኞቹ ምዕመናን በእርግጥ

በድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው።" በማለት አማኝ ወንዶች እንደሞቱ በዚህ ህይወት ውስጥ እንደሚገቡ ይናገራል።

ይባሱኑ ደግሞ ጃሚያ አት ትርሚዲ 2562 "... በገነት ዝቅተኛ ስፍራ ያለ ሰው 72 ሚስቶች ይኖሩታል።" ማለቱና ለአንድ ወንድ የሚሸለሙት ሚስቶች ብዛት ምጣኔን ስንመለከት የገነት ሴቶች ከዚህ ዓለም አለመሆናቸውን ያሳየናል፣ ታዲያ እነዚህ ሴቶች እነማን ናቸው? ብለን ስንመለከት፣

- ለወንዶቹ የሚዘጋጁት ሚስቶች ከመላዕክት መሆኑ፣
  ነ7:40 "**<u>ጌታችሁ በወንዶች ልጆች መረጣችሁና</u>** ከመላዕክት ሴቶች (ልጆች) ያዝን ..."
- ስማቸውም "Houri"(ሁሪ/ሁረል ኤይን) እንደሚባሉ፣
  ሳሂህ ቡኻሪ 4:55:544 "... ገነት የሚገቡት ሰዎች ሚስቶቻቸው ሁሪ/ሁረል ኤይን ናቸው።"

ስለነዚህ ሴት መላዕክት ውበትም ሲናገር፣

- ሳሂህ ቡኻሪ 4:52:53 "አንድ ሁሪ(ሁረል ኤይን) ወደ ምድር መጥታ ለሰዎች ብትታይ በሰማይና በምድር መካከል ያለውን ስፍራ በመልካም መዓዛ ትሞላዋለች።"
- ሳሂህ ቡኻሪ 4:54:476 "... ሁሪዎች(ሁረል ኤይኖች) አጥንትና ስጋቸው ብርሃን የሚያሳልፍ (እንደ መስታወት/transparent) በመሆኑ መቅኔያቸው ይታያል።"
- ሳሂህ ቡኻሪ 4:54:469 "... ገነት የሚገቡት ሰዎች ሚስቶች ቆንጆዎች ናቸው፣ በስጋቸው ውስጥ የአጥንታቸው መቅኔ የሚታይ (transparent flesh) ናቸው።"

በዚህም ሴቶች "እርኩስ ናቸው" ብሎ የጀመረውና በገነት ለሴቶች የሚሰጠውን ሽልማት የማይናገረው የእስልምና መንገድ፣ ለወንዶቹ የሚሸለሙት ሴቶች ከሰው ዘር ያልሆኑ "ሁሪ/ሁረል ኤይን" የሚባሉ መላዕክት መሆናቸውን ይገልፃል።

በዚህም ሴቶች በእስልምናው መንገድ የገነት መግቢያ እድል እንደሌላቸው እንመለከታለን፣ የሚገርመው ደግሞ ነብዩ እነዚህን ትምህርቶች ያስተማሩት ሁሉም ልጆቻቸው ሴቶች በሆኑበት(33:40) እና ለነሱ እንኳን ማዳላት በሚገባቸው ሁኔታ ውስጥ መሆኑን ስንመለከት በእርግጠኝነት ሴቶች በእስልምና መንገድ ገነት እንደማይገቡ እንመለከታለን። ስለዚህ በእስልምና ውስጥ ያሉ ሴቶች የገነት መግቢያ መንገድ ማግኘት የሚችሉት በጾታ ያልተገደበውና ቁርአኑ በደፈናው "ተከታዮቹ"(57:27)፣ የኢንጅልም ባለቤቶች(5:47) ... ባለው በኢሳ(ኢየሱስ) መንገድ በኩል ብቻ ነው።

የኢሳን መንገድ የሚከተለው ክርስትናው በጾታ ምክንያት ምንም መድልዎ እንደማይደርግ(ገላ.3:28) እንደዚሁ ወደ ገነት ሲገባም ሁሉም የሚሰጠው አካል እንደ መላዕክት ጾታ የሌለው ሰማያዊ አካል መሆኑን(ማቴ.22:30) ስንመለከት ለሁሉም ጾታ ገነት መግቢያ መንገድ ተደርጎ የተዘጋጀው የኢሳ መንገድ መሆኑን እንረዳለን።

በአጠቃላይም “እስልምና ለማን ተላከ? ማንንስ አይመለከትም?” የሚሉትን ጥያቄዎች ስንመለከት እስልምና የተላከው ለዓረብ ወንዶች ብቻ መሆኑን፣ ከዓረብ ዘር ውጪ ያሉትን የሰው ዘሮችና ሴቶችን የማይመለከት መሆኑን፣ ከዓረብ ዘር ውጪ ላሉት የሰው ዘሮች እና ለሴቶች ገነት እንዲገቡበት የተዘጋጀላቸው መንገድ የኢሳ የክርስትና መንገድ መሆኑን ከቁርአኑ እንረዳለን፡፡

በዚህም አልመሲህ ኢሳ በራዕ.2፡5 ላይ “እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ…” እንደሚለው በእስልምናው መንገድ ያልተጠቃለሉት ዓረብ ያልሆኑት ዘሮችና ሴቶች እስልምና እንደማይመለከታቸውና የሰለሙት እንኳን እስልምናቸው ቁርአናዊ ባለመሆኑ እነዚህ ሰዎች በዘርና በጾታ ወዳልተገደበው ወደ ኢየሱስ(ኢሳ) መመለስ ያለባቸው መሆኑን ነው የምንመለከተው፡፡

በቀጣይ ክፍሎችም ይህንን <u>ለዓረብ ወንዶች ብቻ ተለይቶ</u> የተወረደውን ኃይማኖት ከክርስትና ጋር የገጠመውን ተቃርኖ በስፋት በመመልከት ትክክለኛው መንገድ የትኛው እንደሆነ እንፈትሻለን፡፡

2.3. <u>ነብዩ ሙሐመድና የክርስትናው ኢሳ(ኢየሱስ) ተቃራኒ መሆናቸው</u>

ነብዩ ሙሐመድና አልመሲህ ኢሳ(ኢየሱስ ክርስቶስ) የሁለቱ ኃይማኖቶች የእስልምና እና የክርስትና ኃይማኖት መሪ ነብያት መሆናቸውን ከላይ ተመልከተናል፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከ33 ዓ.ዓ እስከ አሁን ድረስ በህይወት ያለና ተመልሶ የሚመጣ የክርስትና ኃይማኖት መስራችና መሪ ሲሆን [25] ነብዩ ሙሐመድ ደግሞ ከ570 እስከ ሰኔ 8, 632 ዓ.ም ድረስ በዓረቡ ዓለም የኖሩ የእስልምና ኃይማኖት መስራችና መሪ ነቢይ ናቸው፡፡

ነብዩ ሙሐመድ የአይሁድ/ክርስትና ነብያትን ነቢይነት የሚቀበሉ ሲሆኑ የሁሉንም ቀደምት ነብያት ታሪክ በበጎ ጎን አንስተዋል ኢድሪስ/ሄኖክ(ነ9፡56)፣ ኢብራሂም፣ ኢስማኢልና ኢስሐቅ(2፡127)፣ ያዕቁብ(2፡132)፣ አሮን/ሀሩን(2፡248)፣ ሳሙኤል(2፡246)፣ ሳኦል/ጧሉት(2፡247)፣ ዳዊት/ዳውድ(2፡251)፣ ኢየሱስ/ኢሳ(2፡253)፣ የህያ/ዮሐንስ(ነ9፡7) … <u>ነብዩ ሙሐመድም በዚህ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገኝበት የእስራኤል ነብያት መንገድ በነቢይነት መሾማቸውን ይናገራሉ</u>፣

- 33፡7 “ከነቢዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን <u>ከአንተም</u>፣ ከኑህም፣ ከኢብራሂምም፣ ከሙሳም ከመሪየም ልጅ ኢሳም በያዝን ጊዜ …”
- 6፡90 “እነዚህ(ነብያት)፤ እነዚያ አላህ የመራቸው ናቸው፡፡ <u>በመንገዳቸው ተከተል</u>፡፡”

በማለት ነብዩ ሙሐመድ በቀደመው የነብያት መንገድ በነቢይነት መላካቸውን ይናገራሉ፡፡ ይሁን እንጂ የኢየሱስ ክርስቶስንና የነብዩ ሙሐመድን መንገድ ስናነፃፅር መንገዳቸው

[25] https://en.m.Wikipedia>wiki>Muhammed in Islam

ፍፁም ተቃራኒ ሆኖ ነው የምንመለከተው፣ ይህንን እውነታ በደንብ ለመረዳት ሁለቱን ነብያት፣

- ከነቢይነት ሹመት አንፃር፣
- የቀደምቱ ነብያት መንገድ አንፃር፣
- ከኃይማኖት መሪ ስብዕና አንፃር፣

እያነፃፀርን እንመለከታቸዋለን፡፡

2.3.1. <u>ነብዩ ኢሳ እና ነብዩ ሙሐመድ ከነቢይነት ሹመት አንፃር</u>

ኢየሱስ በነቢይነት መሾሙን በመጽሐፍ ቅዱሱም ሆነ በቁርአኑ ላይ በግልፅ ተነግሯል(33፡7, 2፡253, 61፡6 ...) ነገር ግን የነብዩ ሙሐመድ ነቢይነት ላይ ብዙ አወዛጋቢ ነገሮችን ያሉበት ሲሆን በአካል በሚያውቃቸውና የአይሁድ/ክርስትና ነብያትን አነሳስ በሚያውቀው የዓረቡ ማኅበረሰብ ዘንድም በነብዩ ሙሐመድ ነቢይነት ላይ ብዙ ተቃውሞ ሲነሳ ነበረ፡፡

ነብዩ ሙሐመድ በነቢይነት የተነሱት በሂራ ዋሻ ውስጥ፣ ለራሳቸውም ባልጠበቁት መንገድ፣ “ቁርአን ከጅብሪል(ገብርኤል) ተቀበልኩ” ካሉ በኋላ ቢሆንም(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡3) ነብዩ ግን ነቢይነታቸው አስቀድሞ “በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ተተንብዮ ነበረ” አሉ፡-

- 61፡6 “የመርየም ልጅ ኢሳም፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ ... ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ <u>አሕመድ</u> በሆነው የማበስር ስኾን ወደናንተ (የተላክሁ) የአላህ መልእክተኛ ነኝ ...”
- 7፡157 “ለእነዚያ ያንን እነሱ ዘንድ በተውራት(ኦሪት)ና በኢንጅል(ወንጌል) ተፅፎ የሚያገኙትን <u>የማይፅፍና የማያነብ ነቢይ</u> የኾነውን መልክተኛ የሚከተሉት ለኾኑት (በእርግጥ እፅፍለታለሁ)፡፡”

ነብዩ ሙሐመድ “ስለኔ ነቢይነት በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ በዚህ መልክ ተተንብዮ ነበር” ቢሉም ይህ አባባል መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ባለመኖሩ ነቢይነታቸው መጽሐፍ ቅዱሱን በያዘው በአይሁድ/ክርስቲያን ማኅበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአይሁድ/ክርስትና ነብያት አነሳስ ታሪክ የሚያውቀው የዓረቡ ማኅበረሰብም ቢሆን ለነብዩ ሙሐመድ ነቢይነት እውቅና ለመስጠት “እንደ ቀድሞዎቹ ነብያት ተአምራት ያሳየን” ሲሉ ነበረ፣

- 21፡5 “የቀድሞዎቹም እንደተላኩ (መልእክተኛ ከሆነ) በተአምር ይምጣብን አሉ፡፡”
- 6፡37 “ከጌታውም በእርሱ ላይ ለምን ተአምር አልተወረደም” አሉ
- 13፡7 “... ከጌታው ተአምር ለምን አልተወረደለትም ...”
- 17፡90-93 “አሉም “ለኛ ከምድር ምንጭን እስከምታፈነዳ ... ወይም እንደምትለው ከሰማይ ቁራጮችን በኛ ላይ እስከምታወድቅ ወይም አላህንና መላዕክትን በግልፅ

እስከምታመጣ ... አናምንህም አሉ::" "ጌታዬ ጥራት ይገባው፤ እኔ ሰው መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው::"

ነብዩም በዚህ መልክ "ነቢይ ነኝ ነገር ግን ተአምራት አልተሰጠኝም" የሚል መልስ ሲሰጡ ከቆዩ በኋላ፣ ይህ መልስ አላዋጣ ሲላቸው ተአምራት መሞከር እንዳለባቸው ተገነዘቡ፣ በዚህም፣

> 21:37 "ሰው ችኳይ ሆኖ ተፈጠረ:: ተአምራቶቼን በርግጥ አሳያችሃለሁና አታቻኩሉኝ::"

ሲሉ ቆይተው በመቀጠልም "ተአምራት ሰሩ" የሚሉ መረጃዎች ተለቀቁ፣ እነዚህ ተአምራቶችም፣

- ውሀን ጠርተው ሰዎችን ማስታጠባቸውን(ሳሂህ ሙስሊም 30:5656)
- ጨረቃን ሰንጥቀው መከፈላቸውን (ሳሂህ ሙስሊም 39:6728)

የሚገልፀ ዘገባዎች ሲሆኑ ነገር ግን እነዚህ ዘገባዎች ከቁርአኑ "ተአምራት ያልያዘ ነቢይ" ከሚለው ሐሳብ ጋር የሚጋጭ መሆኑ፣ መረጃውም የሰዎች ዘገባዎች በሚፃፍበት በሀዲሱ እንጂ በዋናው ቁርአን ላይ አለመመልከቱና ማጎበረሰቡም ተአምራቱን በዘገባ እንጂ <u>በተግባር</u> ያልተመለከተው በመሆኑ ምክንያት የነብዩ ሙሐመድ ነቢይነት በወቅቱ በአረቡ ማጎበረሰብም ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት አልቻለም፣ በዚህም ምክንያት ነብዩ ቀድሞ "በእስራኤላውያኑ ነብያት መንገድ ነኝ" የሚሉትን ሐሳብ በመተው እስልምናን በራሳቸው መንገድ መሠረቱ፣ ቀጥሎ በስፋት ቀርቧል::

2.3.2. <u>ነብዩ ሙሐመድ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ከቀደምት ነብያት መንገድ አንፃር</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ነብዩ ሙሐመድ ተአምራት ባለመያዛቸው ተአምራት በተግባር እያሳዩ ህዝቡን መምራት አልቻሉም፣ በዚህም "በእስራኤላውያኑ ነብያት መንገድ ነኝ" የሚለው አካሄድ እንደማያስኬዳቸው ተገነዘቡ፣ <u>የእስራኤላውያኑ ነብያት መንገድ የሚያስኬደው ተአምራት ለያዘና ተአምራቶቹን ለህዝቡ በተግባር እያሳየ ህዝቡን መምራት ለሚችል ነቢይ ነው፣</u> በዚህም ነብዩ ሙሐመድ የአይሁድ/ክርስትናን መንገድ በመተው በራሳቸው መንገድ ኃይማኖታቸውን ለማቋቋም ተነሱ፣ በዚህም፡-

- የእስራኤል ነብያትን በመተው ብቸኛ ነቢይነታቸውን አወጁ፣
- የእስራኤል ቅዱሳን መጽሐፍትን በመተው ቁርአኑን ብቻ ተከተሉ፣
- ስለ አይሁድ/ክርስትናን ያስተማሩትን የአንድነት ትምህርት በመተው "ትክክለኛ ኃይማኖት እስልምና ብቻ ነው" አሉ፣
- አይሁድ/ክርስትና የተሳሳተ ኃይማኖት እንደሆነ አስተማሩ፣
- ከአይሁድ/ክርስትናው የተቃረነ ኃይማኖት ማስፋፍያ እስትራቴጂን ተከተሉ፣

ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን::

2.3.2.1. <u>የእስራኤል ነብያትን በሙተው ብቸኛ ነቢይነታቸውን አወጁ</u>

ነብዩ ሙሐመድ በሠላሙ ጊዜ የአይሁድ/እስራኤል ነብያትን ነቢይነት ተቀብለው ነበረ፣

- 33፡7 "ከነቢዮችም የጠበቀ ኪዳናቸውን <u>ከአንተም</u>፣ ከኑህም፣ ከኢብራሂምም፣ ከሙሳም ከመርየም ልጅ ኢሳም በያዝን ጊዜ አስታውስ፡፡ ከእነርሱም የከበደ ቃል ኪዳን ያዝን፡፡"
- 6፡90 "እነዚህ(ነብያት)፤ እነዚያ አላህ የመራቸው ናቸው፡፡ <u>በመንገዳቸው ተከተል</u>፡፡"
- 40፡78 "<u>ካንተ በፊት</u> መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡"
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡162 "... ከሌሎች ነብያት በላይ አድርጋችሁ አትመልከቱኝ..."

ይሁን እንጂ ነብዩ ሙሐመድ ነቢይነታቸው ላይ በተፈጠረው ጥያቄ ምክንያት ይህንን እውነታ በመተው "ነቢይ እኔ ብቻ ነኝ" የሚል መንገድን ተከተሉ፣

- 22፡52 "ከመልክተኛና ከነቢይም <u>ከአንተ በፊት አንድም አላክንም</u> ..."
- 6፡14 "... እኔ <u>መጀመሪያ</u> ትዕዛዝን ከተቀበለ ሰው ልሆን ታዘዝኩ ..."
- 6፡163 "... እኔ የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ፡፡"
- 39፡12 "የሙስሊሞች መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ፡፡"

አሉ፣ ይህ የነብዩ የአቋም ለውጥም እስልምና የመጣው ከፈጣሪ ነው ወይስ የነብዩ ሙሐመድ ፈጠራ ነው? የሚለውን ጥያቄ ያጭራል፡፡

2.3.2.2. <u>የእስራኤል ቅዱሳን መጽሐፍትን በመተው ቁርአኑን ብቻ ተከተሉ</u>

ነብዩ በሠላሙ ጊዜ የአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍትን ሙስሊሙ እንዲጠቀምባቸው ሲያስተምሩ ነበሩ፣

- 2፡136 "በአላህና ወደ እኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስሃቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳም በተሰጡት ከነርሱ <u>በአንድም መካከል የማንለይ</u> ስንሆን አመንን፡፡"
- 4፡136 "በዚያም ከበፊቱ ባወረድነው መጽሐፍ እመኑ፡፡"
- 29፡46 " ... (የመጽሐፉን ባለቤቶች) በዚህ ወደኛ በተወረደው ወደናንተም በተወረደው አመንን፡፡"

ከማለት አልፈው ቀድሞ ለአይሁድ/ክርስቲያኖች የወረዱት መጽሐፍት በጣም የተብራሩ(2፡99, 37፡117)፣ የተዘረዘሩ(6፡98) እንዲሁም ግልፆች(45፡17) መሆናቸውና ለነብዩ ሙሐመድ ደግሞ እንደ ቀደምት ነብያት ሙሉ እውቀት ያልተወረደላቸው መሆኑን፡-

> 40፡78 "ካንተ በፊት መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡ ከእነሱም ባንተ ላይ የተረከንልህ አልለ፡፡ ከእነርሱም ባንተ ላይ ያልተረከነው አልለ፡፡"

በመግለፅ ሙስሊሞችም ከቁርአኑ ያልገባቸውን ነገር ቢኖር እንኳን ቀድሞ መጽሐፍ የወረደላቸውን አይሁድ/ክርስቲያኖችን እንዲጠይቁ ተናግረው ነበረ(21፡7)።

ይሁን እንጂ ነብዩ ሙሐመድ በነብይነታቸው ላይ በተፈጠረው ፈተና ምክንያት እነዚህን አባባሎቻቸውን ሁሉ በመተው፣

21፡45 "የማስፈራችሁ በተወረደልኝ **ብቻ** ነው።"

በማለት የአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍትን ትተው ተነሱ። ፈጣሪም በሳቸው ላይ ለተወረደው ቁርአን **<u>ብቻ</u>** ለይቶ ጥበቃ እንደሚያደርግ(15፡9) እና ለሌሎቹ መጽሐፍቱ ጥበቃ እንደማያደርግ አስተማሩ። የእስልምና ኃይማኖት በሙሐመድ ላይ **<u>ብቻ</u>** የተወረደውን ቁርአኑን <u>በመለየት</u> በመጽሐፍ መልክ አሳትሞ ይጠቀምበታል።

መጽሐፍ ቅዱሱ ጋር ግን ይህ "መፈንቅለ ቀደምት መጽሐፍት" አሰራር ባለመኖሩ ምክንያት መጽሐፉ ሁሉንም ቀደምት መጽሐፍት በአንድ ላይ አሰባስቦ ይዟል፣ ይህ ደግሞ ማንም መጽሐፍ ቅዱሱን መነሻ እያደረገ ሰዎችን በተሳሳተ መንገድ ይዞ እንዳይሄድና የቀደመችው መንገድ እንዳትጠፋ ያደርጋል። ነብዩ ሙሐመድ ግን ቀድሞ ተደግፈው የተነሱትን የአይሁድ/ክርስትናን መጽሐፍትን፣ "አንለያቸውም፣ እናምንባቸዋለን ..." ያሉትን ቃል ሁሉ ትተው፣ ከታች በስፋት እንደምንመለከተው እነዚህን መፅሐፍት ተመልሰው በመተቸት፣ "ቁርአን ብቻ ብለዋል"።

<u>ይህ</u> አካሄድም ነብዩ እስልምናን በፈለጉት መንገድ እንዲያስኬዱ ረድቷቸዋል። ይህ የነብዩ "መፈንቅለ ቀደምት መጽሐፍት" አካሄድ እስልምና የመጣው ከፈጣሪ ነው ወይስ የነብዩ ሙሐመድ ፈጠራ ነው? የሚል ጥያቄን ያጭራል።

2.3.2.3. <u>ስለ አይሁድ/ክርስትናን ያስተማሩትን የአንድነት አስተምህሮ በመተው "ትክክለኛ ኃይማኖት እስልምና ብቻ ነው" አሉ</u>

ነብዩ በሠላሙ ጊዜ አይሁድ/ክርስትና ከእስልምና ጋር አንድ መሆናቸውን ሲያስተምሩ ነበረ፣

- <u>አምላካችን አንድ ነው</u>
  29፡46 "የመጽሐፉን ባለቤቶች ... አምላካችን አምላካችሁ አንድ ነው። እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን።"
- <u>የአይሁድ/ክርስትናን መሠረታዊ ዕሴቶች እንቀበላለን</u>
  2፡285 "... ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጽሐፍቱም፣ በመልዕክተኞቹም፣ ከመልዕክተኞቹም "በአንድም መካከል አንለይም" ... ሰማን ታዘዝንም ..."

- <u>ክርስቲያኖች ጥሩዎች ናቸው</u>
  5፡82 "... እነዚያን "እኛ ክርስቲያኖች ነን" ያሉትን ለእነዚያ ለአመኑት(ሙስሊሞች) በወዳጅነት በርግጥ ይበልጥ የቀረቧቸው ኾነው ታገኛለህ፡፡ ይህ ከእነሱ ውስጥ ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነርሱም <u>የማይኮሩ</u> በመሆናቸው ነው፡፡"
- <u>አይሁድ/ክርስቲያን ያረደውን ልንበላ፣ ሴቶቻቸውን ልናገባ የተፈቀደ ነው</u>
  5፡5 "... የእነዚያም መጽሐፍ የተሰጡት ሰዎች ምግብ(ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው ... ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡት ሴቶች... (ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)፡፡"
- <u>እስራኤሎች ፈጣሪ የመረጣቸው ህዝቦች ናቸው</u>
  45፡16 "ለእስራኤል ልጆች መጽሐፍንና ሕግን፣ ነቢይነትንም በርግጥ ሰጠናቸው፡፡ ከመልካም ሲሳዮችም በርግጥ ለገስናቸው፡፡ <u>በዓለማት ላይም አበለጥናቸው</u>፡፡"

ነገር ግን በነብዩ ነቢይነት ላይ በተፈጠረው ጥያቄ ምክንያት ነብዩ እነዚህን አስተምህሮዎቻቸውን በመተው፣

3፡19 "አላህ ዘንድ (የተወደደ) ኃይማኖት <u>ኢስላም</u> **ብቻ** ነው ..."

በማለት የአይሁድ/ክርስትናን መንገድ ወደ ጎን አደረጉ፣ በዚህም ቀድሞ የአይሁድ/ክርስትና ስርዓቶችን፣ ዕሴቶችን ... ዓረባዊ በሆነ መንገድ ቀየሩ፣

- <u>ከኢብራሂም-ኢስሀቅ-ያዕቁብ መስመር ወደ ኢብራሂም-ኢስማኤል መስመር ተቀየሱ</u>

ነብዩ ከያዕቁብ(ያዕቆብ) በሚወለዱት በእስራኤላውያን ነብያት መንገድ መሆናቸውን ሲናገሩ ቢቆዩም ከዚህ መንገድ ጋር መተሳሰር ባለመቻላቸው ምክንያት ወደ የዘር ሀረጋቸው መንገድ፣ ወደ ኢስማኢል መንገድ ተቀይሰዋል፡፡ በዚህም ፈጣሪ ለአብርሃም ቃል የገባለት ልጅ ኢስሀቅ ሳይሆን ኢስማኢል መሆኑን፣ ኢብራሂምም ለመስዋዕት እንዲያቀርብ የታዘዘውና ለመስዋዕት ያቀረበው ኢስሀቅን ሳይሆን እስማኢልን መሆኑን፣ ኢስማኢልም ነቢይ እንደነበረ፣ ኢስማኢልም ከኢብራሂም ጋር ሆኖ መካ ላይ ከአባን እንደገነባ አስተማሩ በዚህም አማኙም ወደ ኢየሩሳሌም የነበረውን የስግደት አቅጣጫ ወደ ከአባ እንዲለወጥ አዘዙ፡፡

- <u>ወደ እየሩሳሌም(እስራኤል) የነበረው የስግደት አቅጣጫ(ቂብላ) ወደ መካ (ሳዑዲ ዓረቢያ) አዞሩ</u>
  - ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡13 "ነብዩ ወደ ባይት ኡል መቅዲስ(ኢየሩሳሌም) ዞረው ለመጀመሪያዎቹ 16 ወይ 17 ወራት ሲሰግዱ ነበረ፣ <u>ነገር ግን ይህ የስግደት አቅጣጫ ወደ መካ ቢሆን ይመኙ ነበረ</u>፡፡ ከዚያ በኋላ ቂብላቸውን(የስግደት አቅጣጫ) ወደ ካዕባ አደረጉት፡፡"

- 2፡144-145 “የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በርግጥ እናያለን፡፡ ወደ ምትወዳት ቂብላ እናዞርሀለን፡፡ ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ (ወደ ካዕባ) አግጣጫ አዙር … እነዚያ መጽሐፍን የተሰጡትን በእስረጂ ሁሉ ብትመጣቸው ቂብላህን አይከተሉም፡፡ አንተም ቂብላቸውን ተከታይ አይደለህም፡፡”

- <u>የእረፍት ቀንን ከእሁድ ወደ አርብ ቀየሩ</u>
  62፡9 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ! <u>በአርብ ቀን</u> ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት ኺዱ፡፡ መሸጥንም ተው፡፡”

- <u>ካሌንደር ቀየሩ</u>
  ኢየሱስን መነሻ አድርጎ በፀሐይ እንቅስቃሴ ላይ ተመስርቶ የሚሰላውን የዘመን አቆጣጠር በጨረቃ እንቅስቃሴ ላይ ተመስርቶ በሚሰላው የሂጅራ አቆጣጠር ተተካ፡፡

- <u>ከአይሁድ/ክርስቲያን ጋር ያዘዙትን መልካም ግንኙነት መልሰው ከለከሉ</u>
  - 5፡51 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን <u>ረዳቶች</u> አድርጋችሁ አትያዙ፡፡”
  - 3፡118 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ ከእናንተ ሌላ <u>ምስጢረኛ</u> አትያዙ…”
  - 4፡144 “እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ ከምዕምናን ሌላ ከሃዲዎችን <u>ወዳጆች</u> አድርጋችሁ አትያዙ፡፡”

- <u>ከአይሁድ/ክርስቲያን ጋር መጋባትን መልሰው ከለከሉ</u>
  2፡221 “[26]አጋሪዎች(አይሁድ/ክርስቲያኖች) የሆኑ ሴቶች እስኪያምኑ (እስኪሰልሙ) ድረስ አታግቡአቸው፡፡”

- <u>አይሁድ/ክርስቲያን ያረደውን መብላት መልሰው ከለከሉ</u>
  - 9፡28 “… አጋሪዎች(አይሁድ/ክርስቲያኖች) <u>እርኩሶች</u> ብቻ ናቸው…”
  - 16፡115 “በእናንተም ላይ እርም ያደረገው … ያንንም(በመታረድ ጊዜ) በእርሱ ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ብቻ ነው፡፡”

- <u>በአይሁድ/ክርስትና “እርኩስ” የተባለውን ግመል የእስልምና ኃይማኖት ምልክት በማድረግ የግመል ስጋ እንዲበላ አዘዙ፣</u>
  22፡36 “ግመሎችን ለእናንተ ከአላህ ኃይማኖት <u>ምልክቶች</u> አደረግናቸው፡፡ ከርሷ ብሉ”

አሉ፣ በዚህም ነብዩ እስልምናን ከአይሁድ/ክርስትናው መንገድ ለዩ፣ ይህ የነብዩ የአቋም ለውጥ እስልምና የመጣው ከፈጣሪ ነው ወይስ የነብዩ ሙሐመድ ፈጠራ ነው? የሚል ጥያቄን ያጭራል፡፡

[26] በእስልምና “አጋሪ” ማለት ከአምላክ በተጨማሪ አምልኮን ለሌላ አካል የሚያጋራ ማለት ነው፣ ቁርአን ሁለቱንም አይሁድና ክርስትናን በአጋሪነት ይከሳቸዋል(9፡30, 5፡73)

2.3.2.4. <u>አይሁድ/ክርስትና የተሳሳተ ኃይማኖት እንደሆነ አስተማሩ</u>

ነብዩ ከአይሁድ/ክርስትና ጋር ያስተማሩትን የአንድነት ትምህርት ከመተው ባለፈም የአይሁድ/ክርስትና ኃይማኖት የተሳሳተ ኃይማኖት መሆኑን አስተማሩ፣ <u>አላህ ላወረዳቸው መጽሐፍት ጥበቃ እንደሚያደርግ የተናገረውን ቃል(15፡9) በመተውም</u> ቀድሞ በተወረዱት በአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍት ላይ ሂሶችን ሰነዘሩ፡፡

ነብዩ በነዚህ መጽሐፍት ላይ ሂስ እንዲሰጡ ያመቻቸው ደግሞ በክርስትና ውስጥ ያለው ለሰው ከባድ የሆኑት ጥልቅ መንፈሳዊ እውቀት የሚፈልጉት አስተምህሮዎች ነበሩ፡፡ በዚህም ነብዩ የክርስትና ከባድ አስተምሮችን "የክርስትና ስህተት" እንደሆኑ አስተማሩ ነገር ግን እነዚህ "ስህተት" የተባሉት የክርስትና አስተምህሮዎች ነብዩ ቀድሞ በሠላሙ ዘመን ሲደግፏቸው ስለነበረ አሁን ያቀረቡዋቸው ሂሶች ከመጀመርያው አስተህሮታቸው ጋር መልሶ ሲቃረን እንመለከታለን፣ እነዚህን ሂሶችና ተቃርኖዎችን ብንመለከት፡-

- "ኢሳ(ኢየሱስ) ሰው እንጂ አምላክነት የለውም፣
- አንድ አምላክ እንጂ የሥላሴ አስተምህሮ ስህተት ነው፣
- ፈጣሪ አይወልድም አይወለድም፣
- ኢሳ አልተገደለም፣
- የዓለም አምላክ እንጂ `የእስራኤል አምላክ` አባባል ስህተት ነው"

የሚሉትን ሲሆኑ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

2.3.2.4.1. <u>"ኢሳ(ኢየሱስ) ሰው እንጂ አምላክነት የለውም"</u>

ክርስትናው አልመሲህ ኢሳ(ኢየሱስ ክርስቶስ) የሰውና የአምላክ "ተዋህዶ" መሆኑን ይናገራል ነገር ግን ነብዩ በተፈጠረው ችግር ምክንያት ኢሳ ሰው ብቻ እንደሆነና አምላክነት እንደሌለበት አስተማሩ፣

- 3፡59 "አላህ ዘንድ የኢሳ ምሳሌ እንደ አዳም ብጤ ነው፣ ከአፈር ፈጠረው፣ ከዚያም ለርሱ(ሰው) ሁን አለው ሆነም፡፡"
- 5፡116 "አላህም፡- የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ - እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን፣ በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፡፡ "ጥራት ይገባህ፤ ለኔ ተገቢዬ ያልሆነ ነገር ማለት ለኔ አይባኝም..."

በማለት ነብዩ ሙሐመድ ኢሳ ሰው እንጂ አምላክነት እንደሌለበት አስተማሩ፣ ይሁን እንጂ ነብዩ ሙሐመድ በሠላሙ ጊዜ ኢሳ የሰው አምላክ ተዋህዶ መሆኑ አስተምረው ነበረ፣ ይህም ኢሳ ሰው ብቻ ሳይሆን ከሰው ማንነቱ በተጨማሪ ኢሳ እራሱ፣

- የአላህ መንፈስ መሆኑ
- የአላህ ቃል መሆኑ፣
- እንደ ፈጣሪ መፍጠሩን፣

- ሲወለድም አራስ ልጅ ብቻ አለመሆኑ፣
- በመጨረሻው ቀን ፈራጅ መሆኑን

አስተምረው ነበረ፣ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፣

1. <u>ኢሳ የአላህ መንፈስ መሆኑ</u>

ቁርአን ኢሳ ከሰው ማንነቱ በተጨማሪ "የአላህ መንፈስ" እንዳለበት ይናገራል፣

> 4፡171 "የመርየም ልጅ አልመሲህ ኢሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የጣላት "የኹን" ቃሉም <u>ከእርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው</u>።።"

ይህ ቃል በግልፅ ቋንቋ ኢሳ እንደ ሌላው ሰው ተራ ሰው ሳይሆን መንፈስ የሆነው አላህ ማንነት በውስጡ ያለበት ሰው መሆኑን ይነግረናል፣ "ብቻ" የሚለው ቃል ደግሞ የኢሳን ጊዜያዊውን ሰውኛ ማንነት እንኳን ወደ ጎን ያደረገ አገላለፅ ነው።።

ማንም ሰው ሆነ መልአክ "የፈጣሪ መንፈስ" አልተባለም፣ ቁርአን ላይ "ጂብሪል(የፈጣሪ መንፈስ)" የሚል ቃል በቅንፍ ተቀምጦ እንመለከታለን(16፡102)፣ በቅንፍ የሚቀመጠው አሰራር የሰዎች ቅጥያ እንጂ መቼም አላህ በቅንፍ ብሎ አይናገርም፣ ይሁን እንጂ ቁርአኑ ያለቅንፍ በቀጥታ "የአላህ መንፈስ" ያለው ኢሳን ብቻ ነው፣ ቁርአኑ ጅብሪልን ለምን በቀጥታ ያለቅንፍ "የአላህ መንፈስ" አላለውም? ኢሳስ "እንደኛ ስጋ ነው" ተብሎ በምኑ ነው "የፈጣሪ መንፈስ" የሚባለው የሚለውን ስንመለከት፣ የኢሳን ትክክለኛ ማንነት እንገነዘባለን።።

በቅንፍ ያለቅንፍ የሚለው እንዳለ ሆኖ፣ የአላህ መንፈስ የተባሉትን ሁለቱ ጂብሪልና ኢሳ ብቻ መሆናቸውን ስንመለከት ኢሳ ከሰው በላይ ከጅብሪል እኩል የሚያደርገው ማንነት እንዳለው እንመለከታለን፣ ሌሎች ኢሳ ከጅብሪል በላይ የሚያደርጉ ተጨማሪ ቁርአናዊ መገለጫዎቹን ደግሞ ቀጥለን እንመለከታለን።።

2. <u>ኢሳ የአላህ ቃል መሆኑ</u>

ኢሳ ከሰውኛ ማንነቱና የአላህ መንፈስነቱ በተጨማሪ "እውነተኛ ቃል" ሲባል እንመለከታለን፣

> 19፡34 "ይህ የመሪየም ልጅ ኢሳ ነው።። ያ በርሱ የሚጠራጠሩበት <u>እውነተኛ ቃል</u> ነው።።"

እዚህ ጋር ደግሞ ቁርአኑ ኢሳን "እውነተኛ ቃል" ሲለው እንመለከታለን፣ የትኛውም ሰው ይሁን መልአክ "ቃል ነው" አልተባለም መጽሐፍ ቅዱሱም ኢሳን "የፈጣሪ ቃል ነው" ይለዋል(ዮሐ.1፡1)።።

የፈጣሪ ቃልና የሰው ቃል ይለያያል፣ በሰውኛ "ቃል" ማለት "ድምፅ" ማለት ሲሆን የፈጣሪ ቃል ግን ከ"ድምፅ" ትርጉም በተጨማሪ ሌላ ትልቅ ትርጉም አለው፣ ፈጣሪ ፍጥረታትን <u>የፈጠረው</u> "በቃሉ" ነው(2፡117)፣ ስለዚህ የፈጣሪ ቃል እንደ ሰው ቃል "ድምፅ"

ማለት ብቻ ሳይሆን ከፈጣሪ የሚወጣ የፈጣሪ "የመፍጠር ማንነት" ማለት ነው፣ ኢሳ ደግሞ "የፈጣሪ ቃል" በመሆኑ ኢሳ ሰሪ የሆነው የአምላክ ማንነት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ይህ እውነታም ሌላ ስፍራ ላይ ቀርቧል፣

> 4፡171 "የመርየም ልጅ አልመሲህ ኢሳ የአላህ መልእክተኛ ወደ መርየም የጣላት "የኹን" ቃሉም ከእርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው፡፡"

ፈጣሪ ፍጥረታትን የሚፈጥረው "ኹን" ብሎ ነው፣ በዚህም ኢሳ "የኹን ቃል ነው" ሲባል ኢሳ የፈጣሪ የመፍጠር ማንነት ማለት ነው፡፡

ይህንን እውነታም ኢሳ በምድራዊ ህይወቱ ወቅት አረጋግጧል፣ 3፡49 እና 5፡110 ላይ እንደምንመለከተው ኢሳ በምድር በነበረበት ወቅት ከጭቃ የወፍ ቅርፅ እየሰራ በትንፋሹን ሲተነፍስበት ህይወትን ያለው ሆኖ ይበርር ነበረ፣ ልክ ፈጣሪ አዳምን ሲፈጥር ጭቃ በሰው ቅርፅ ሰርቶ እፍ ብሎ ሰውን እንደፈጠረው(ሳሂህ ቡኻሪ 8፡76፡570)፡፡

ከፈጣሪ በቀር ማንም ሰውም ሆነ መልአክ የመፍጠር ችሎታ የለውም፣ ሁሉም ተፈጣሪ ናቸውና፣ ኢሳ ግን "ቃል" የሚባለው "የፈጣሪ የመፍጠር" ማንነት በመሆኑ ይህንን ማንነቱን በተግባር ሲያሳይ ነበረ፡፡

3. ኢሳ ሲወለድ አራስ ብቻ አለመሆኑ

ቁርአን "የሰው ልጅ ሲወለድ ምንም እንደማያውቅ" ይናገራል፣

> 16፡78 "አላህ ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ፡፡"

ሰዎች በመሆናችን የዚህን ቃል ትክክለኛነት እናውቃለን ነገር ግን ኢሳ ከሰው ማንነት በተጨማሪ ከላይ የተመለከትናቸውን የፈጣሪን ማንነቶች ስላለው ሲወለድ እንደ ማንኛውም ሰው ያለ እውቀት አይደለም፣

> 19፡22-30 "(መርየም) ወዲያውኑ አረገዘችው፡፡ በእርሱም (በሆዷ ይዛው) ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች፡፡ ምጡም ወደ ዘንባባው አስጠጋት "ዋ ምኞቴ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩ፡፡ ተረስቼም የቀረሁ በሆንኩ" አለች፡፡ ከበታቿም እንዲህ ሲል ጠራት "አትዘኚ፡፡ ጌታሽ ከበታችሽ ትንሽ ወንዝ በርግጥ አድርጓል፡፡ የዘንባባይቱንም ግንድ ወዳንቺ ወዝውዢያት ባንቺ ላይ የበሰለን የቴምር እሸት ታረግፍልሻለችና፡፡ ብይም ጠጪም፣ ተደሰቺ፡፡ እኔ ለአልረህማን ዝምታን ተስያለሁ፣ ዛሬ ፍፁም ሰውን አላናግርም" በይ፡፡ በእርሱም የተሸከመቺው ሆና ወደ ዘመዶቿ መጣች፡፡ "መርየም ሆይ! ከባድ ነገር በርግጥ ሰራሽ" አሏት፡፡ "የሀሩን እህት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም፡፡ እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም" አሏት፡፡ ወደርሱም ጠቀሰች፡፡ "በአንቀልባ ያለን ህፃን እንዴት እናናግራለን!" አሉ፡፡ (ህፃኑም) አለ "እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ፡፡ መጽሐፍን ሰጥቶኛል ነቢይም አድርጎኛል፡፡ በየትም ስፍራ ብሆን ብሩክ

አድርጎኛል፡፡ በህይወትም እስካለሁ ሶላት በመስገድ ዘካንም በመስጠት አዞኛል፡፡ ለናቴም ታዛዥ አድርጎኛል፡፡ ትዕቢተኛ እምቢተኛም አላደረገኝም፡፡"

በመጀመርያ መርየም በምጡና በብቸኝነቷ ምክንያት ስትማረር ይህ ገና የተወለደ ልጅ የመርያምን ቋንቋ ተረድቶ፣ ፍላጎትዋን አስተውሎ፣ መርየም ያልተመለከተችው የሚጠጣ ውሃና የሚበላ ቴምር ተመልክቶ በማርያም ቋንቋ ነው የተናገረው፣ ከዚያም ስለ "ለአልረህማን ስለት መሳል"፣ ሰዎች ብዙ ጥያቄ ይዘው እንደሚጠብቋትና ለነሱም ምን አይነት መልስ መመለስ እንዳለባት መከራት፡፡ ሰዎችም መርየምን የትዝብት ጥያቄ ሲጠይቋት ለርሷ ጠበቃ በመሆን ስለራሱ አስረዳ፡፡

እነዚህ ኢሳ እንደተወለደ የተናገራቸው ንግግሮችም ኢሳ ሲወለድ ከስጋ ማንነቱ በተጨማሪ ሁሉን አዋቂ ማንነት ይህም መለኮትነት እንደነበረው እንመለከታለን፡፡ ኢሳ በዚሁ መለኮታዊ ማንነቱ ምክንያትም ከየትኛውም ሰው በተለየ ሲወለድ በሰይጣን አልተነካም"፣

ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡506 "ማንኛውም ሰው ሲወለድ ሰውነቱን በሁለቱም በኩል ሰይጣን በሁለት ጣቱ ይነካዋል፣ ከኢየሱስ በስተቀር ሁሉም ሰው ሲወለድ እንደዚሁ ነው፣ ሰይጣን ኢየሱስን እንደሌላው ሰው ለመንካት ሞክሮ አልተሳካለትም፡፡"

በዚህ ኢሳ ሲወለድ ሰው ብቻ እንዳልነበረና ከሰው ማንነት በተጨማሪ ሁሉን አዋቂነትንና መለኮታዊነትን ይዞ እንደተወለደ እንመለከታለን፡፡

4. ኢሳ በመጨረሻው ቀን ፈራጅ መሆኑ

በእስልምናው የትኛው ሰው ገነት እንደሚገባ የትኛው ደግሞ ሲኦል እንደሚገባ በአላህ ዘንድ ቀድሞ የተወሰነ ነገር ነው(ሳሂህ ሙስሊም 33፡6393, ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡549, 4፡54፡430, 8፡77፡593, 9፡93፡540...) ነገር ግን አላህ በፍርዱ ማንንም ስለማያጋራ(18፡26)፣ የፈጣሪን ፍርድ ከፍርድ ቀን በፊት ማንም ሊያውቅ አይችልም፣ ኢሳ ግን የአምላክ ማንነት በውስጡ ስለያዘ ዛሬ ላይ ሆኖ ማን ገነት እንደሚገባ ይባሱኑም ከዚያ አልፎ በገነት ውስጥ ሰዎች ስለሚኖራቸው ደረጃ እንኳን ያውቃል፣

ሳሂህ ሙስሊም 41፡7015 "... (ደጃል የተባለው ሰይጣን በሚገለጥበት ዘመን) የመርየም ልጅ ኢሳም ይመጣና (ያለቀሱትን ሰዎች) እንባ ያብስና በገነት ውስጥ የሚኖራቸውን ደረጃ ይነግራቸዋል ..."

ይህም የኢሳ እውቀት የፈራጅ አምላክ ማንነት በውስጡ እንዳለ ያሳየናል፣ ይህንን እውነታ በመመልከት ነው ነብዩ ሙሐመድ "ህይወቴ በእጁ በሆነች በኢሳ" ያለው (ሳሂህ ሙስሊም 1፡0287)፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ኢሳ የትኛውም ሰውና መልአክ ያልሆነውን የአላህ መንፈስ መሆኑ፣ የአላህ ቃል መሆኑ፣ ሲወለድም አራስ ልጅ ብቻ አለመሆኑና በመጨረሻው ቀንም

ፈራጅ መሆኑን ስንመለከት፣ ኢሳ እንደኛ አይነት ሰው ብቻ ሳይሆን ከሰውኛ ማንነቱ በተጨማሪ የፈጣሪ ማንነት የተዋሀደው መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም ነብዩ ሙሐመድ በነቢይነቱ ላይ በተፈጠረው ችግር ምክንያት የኢሳን ማንነት አውርዶ የተናገበት ንግግር ስህተት መሆኑና ከራሱም አስተምህሮ ጋር ተመልሶ የሚጋጭ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

2.3.2.4.2. <u>"አንድ አምላክ እንጂ ኢጋሪነት "የሥላሴ ትምህርት" ስህተት ነው"</u>

ነብዩ ሙሐመድ ያወገዙት ሁለተኛው የክርስትና አስተምህሮ የ"ሥላሴ" አስተምህሮ ነው፣

- 5፡73 "እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው ያሉ በርግጥ ካዱ፡፡ ከአምላክም አንድ አምለክ እንጂ ሌላ የለም፡፡"
- 4፡171 " ... (አማልክት) ሦስት ናቸው አትበሉ ... አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው፡፡"
- 5፡116 "አላህም፡- የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ አንተ ለሰዎቹ - እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን፣ በሚለው ጊዜ አስታውስ፡፡"

ነብዩ የሥላሴ አስተምህሮ ያወገዙት ከተሳሳተ መረጃ ተነስተው ነው፣ በ5፡116 ላይ የቀረበውን ስንመለከት ነብዩ "ሥላሴ" ብለው የወሰዱት ፈጣሪ፣ ኢሳና መርየምን ነው፣ ነገር ግን ክርስትናው ሥላሴ የሚለው "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የሚባለውን የፈጣሪ ማንነቶች ነው፣ በዚህም ነብዩ ሥላሴን አስመልክተው የሰጡት ወቀሳ ከመነሻው በተሳሳተ መረጃ ላይ የተመሠረተ ወቀሳ ነው፡፡

በመቀጠል የክርስትናው የሥላሴ አስተምህሮ የተለያየ ሦስትነት ሳይሆን ፀሐይ ላይ የምንመለከተው አይነት ሦስትነት ነው፣ ፀሐይ የምንላት ሰማዩ ላይ የምናያት ክብ አካል፣ ከእርሷ ወጥተው ስራ የሚሰሩት ብርሃንና ሙቀት የተመለከቱበት፣ የአንድነትና ሦስትነት አሰራር ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ወልድን(ኢሳን) ብርሃን ሲለው መንፈስ ቅዱስን ደግሞ በዋናነት በእግዚአብሔር ኃይልነት ይገልፀዋል፤ የዚህ ተመሳሳይ ምሳሌም በሰው ልጅ ተፈጥሮ ላይ እናገኛለን፣ በአስልምና ሰው ስጋና ነፍስ ነው፣ በፍርድ ቀንም የሰውነት አካሎች(ስጋ) በነፍስ ላይ መስካሪ ሆና ትቀርባለች፣ በዚህም አንድ በሆነው ሰው ውስጥ ሁለት ማንነቶችን እንመለከታለን፡፡ እነዚህ ምሳሌዎች "ሥላሴ" የሚለው ቃል ምን እንደሚመስል ለማሳየት የቀረቡ አስረጂ ምሳሌዎች እንጂ ከሰው አዕምሮ በላይ የሆነው የፈጣሪ ማንነት በፀሐይና በሰው ማንነት አይወሰንም፣ ፈጣሪ ልዕለ ስብዕና ማንነት ያለው ስለሆነ(ዝርዝሩ በ5.1.2.3 ክፍል ቀርቧል)፡፡

ነብዩ ይህንን ለሰው የሚከብደውን እውቀት መልሰው ለሌላ ዓላማ ይጠቀሙበት እንጂ ይህንን የፈጣሪ የሥላሴነት አስተምህሮ እራሳቸውም በሥላሙ ጊዜ በተወሰነ መጠን አስተምረውት ነበረ፡፡ የሚገርመው ደግሞ በሥላሙ ጊዜ ነብዩ በራሳቸው አላህን በብዙ ቁጥር ሲጠሩ ነበረ፡-

- 3፡47 “አላህ የሚሻለውን ይፈጥራል “**<u>እንዳችን</u>**” ባሻ ጊዜ ሁን ይለዋል፣ ወዲያውም ይሆናል፣”
  እዚህ *ጋር* “እንዳችን” የሚለው የሚያሳየው ሰሜቲካዊውን የአክብሮት አጠራር ሳይሆን “ከኛ ውስጥ” “አንዱ” ማለትን ነው፡፡
- 20፡41 “(አላህ ለሙሳ) <u>ለነፍሴም</u> (በመልእክቴ) መረጥኩህ፡፡”
  እዚህ *ጋር* አላህ “ነፍሴ” ስለሚላት የራሱን ማንነት ሲናገር እንመለከታለን
- 19፡17 “*<u>መንፈሳችንንም</u>* ወደ እርስዋ (መርየም) <u>ላከን</u>፡፡ ለእርስዋም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰላት፡፡”
  “*መንፈሳችንንም*” እና “ላከን” የሚሉት ቃላትም ተመሳሳይ ነገርን ያሳያሉ

በነዚህ የቁርአን ክፍሎች “እንዳችን”፣ “ነፍሴ”፣ “*መንፈሳችንን*” “ላከን” የሚሉት ቃላት የአላህን *ሥላሴነት* ያሳያሉ፡፡

አንዳንዶች የአላህ *መንፈስ* የሚለውን የክርስቲያኖቹ “*ሥላሴ*” አስተምህሮ *ጋር* እንዳይሄድብን በማለት “የአላህ *መንፈስ*” የሚለው ላይ በቅንፍ “ጅብሪል” የሚለውን ቃል በመጨመር “የአላህ *መንፈስ* ጅብሪል ነው” ይላሉ ነገር ግን <u>መልአኩ</u> ጅብሪልና የአላህ *መንፈስ* የተለያዩ መሆናቸውን በቁርአኑ ሌሎች ክፍሎች ላይ ተመልክቷል፣

- <u>ጅብሪል የአላህ *መልአክ መሆኑ*</u>
  - 2፡98 “ለአላህና ለመላዕክቱ ለመልዕክተኞቹም ለጅብሪልም ለሚካልም(ሚካኤል) ጠላት የሆነ ሰው …”
  - 19፡19 “(ጅብሪልም) እኔ ንፁህን ልጅ ለአንቺ ልሰጥሽ <u>የጌታሽ *መልዕክተኛ*</u> ነኝ አላት፡፡”
  - 19፡64 “(ጂብሪል አለ) <u>በጌታህ ትዕዛዝ እንጂ አንወርድም</u>፡፡ በፊታችን ያለው በኋላችንም ያለው በዚህም መካከል ያለው ሁሉ የእርሱ ነው፡፡ ጌታህም ረሺ አይደለም፡፡”
- <u>የአላህ *መልአክና የአላህ መንፈስ የተለያዩ መሆኑን*</u>
  - 70፡4 “… *መላዕክቱና መንፈሱ* …”
  - 97፡3-4 “*መወሰኛይቱ* ለሊት ከሺ ወር በላጭ ናት፣ በርሷ ውስጥ <u>*መላዕክትና መንፈሱ*</u> በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ላይ ይወርዳሉ፡፡”
  - 38፡71-74 “ጌታህ <u>ለመላዕክት</u> “እኔ ሰውን ከጭቃ ፈጣሪ ነኝ” ባለ ጊዜ (አስታውስ)፡፡ “ፍጥረቱን ባስተካከልኩና <u>ከመንፈሴ በነፋሁበት</u> ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ሆናችሁ ውደቁ” (አልኩ)፡፡ <u>*መላዕክትም* መላው ባንድነት</u> ሰገዱ፡፡ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር …”

በዚህም ጅብሪል የአላህ *መልአክ መሆኑንና* የአላህ *መልአክና* የአላህ *መንፈስ* ደግሞ የተለያዩ አካላት መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

አላህ ብቸኛ ፈጣሪ በመሆኑ ፍጥረታትን የሚፈጥረው ያለ ብጤ(2፡117)፣ ራሱን ችሎ (6፡101) ነው፣ በዚህም አላህ ለመፍጠር የመልአክን(ጅብሪልን) እገዛ አይፈልግም፣ አዳምን

ሲፈጥረው ከመንፈሱ ነፍቶበት ነው(15፡28-29)፣ መርየምም ስታረግዝም እንደዚሁ ነበረ(66፡12)፣ "ከመንፈሴ በነፋሁበት" የሚለው ቃል ውስጥ አድራጊውና ድርጊቱን ስንመለከት ደግሞ ከውስጥ መውጣትን እንጂ ከአላህ ውጪ ያለን መልአክ አያመለክትም፡፡

በዚህም የአላህ መንፈስና ጅብሪል የተለያዩ መሆናቸውን፣ የአላህ ልዕለ ስብዕና ባይገባን እንኳን "የአላህ መንፈስ" የሚባለው ከአላህ ውስጥ እየወጣ የሚሰራ የአላህ ማንነት መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም አላህና የአላህ መንፈስ የሚባሉ ሁለት የአላህን ማንነቶች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ከላይ እንዳየነው ኢሳ ውስጥ የአምላክ ማንነት ተመልክተናል፣ የሚገርመው ደግሞ ነፍስን እፍ ብሎ የማስገባት ስራ የሰሩት ልክ እንደ ፀሐይ አንድም ሦስትም የሆኑት አላህ፣ የአላህ መንፈስ(19፡21) እና ኢሳ(3፡49, 5፡110 ...) <u>ብቻ</u> መሆናቸውን ስንመለከት አምላክ ሦስት ማንነት እንዲሁም የሥላሴን አስተምህሮ ትክክለኛነት እናረጋግጣለን፡፡ ለዚህም ነው አላህ አንዴ "እኔ"(32፡7, 15፡28, 39፡7 ...) ሌላ ጊዜ ደግሞ "እኛ"(19፡20, 51፡47-48 ...) እያለ በተለያየ አነጋገር የሚናገረው፡፡

በርግጥ ይህ ከባድ እውቀት ነው ምክንያቱም ፈጣሪ ከሰው ልጅ አዕምሮ በላይ በመሆኑ ነገር ግን ነብዩ ይህ ሰዎች ሊረዱት የማይችሉትን ነገር ግን እራሳቸው እንኳን ቀድሞ ያስተማሩትን አስተምህሮ ተመልሰው በስህተትነት ማስተማራቸው ስህተት ነው፡፡

2.3.2.4.3. "<u>ፈጣሪ አይወልድም አይወለድም፣ ለሱ ብጤም የለውም</u>"

ይህንን አስመልክቶ ነብዩ ሲያስተምሩ፣

- 9፡30 "... ክርስቲያኖችም አልመሲህ ኢሳ የአላህ ልጅ ነው አሉ ... አላህ ያጥፋቸው ከእውነታ እንዴት ይመለሳሉ!"
- 6፡101 "... ለእርሱ(ለአላህ) ሚስት የሌለችው ሲኾን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል ነገርን ሁሉ ፈጠረ፡፡"

ብለዋል፣ እዚህ ጋር የተፈጠረው ስህተት "ልጅ" የሚለውን ቃል በስነተዋልዶ ዓይን ብቻ በመመልከት የመጣ ስህተት ነው ነገር ግን "ልጅ" የሚለው ቃል የግድ በስነተዋልዶ መወለድን ብቻ አያመለክትም ለምሳሌ ቁርአኑ ላይ፣

- 111፡1 ላይ አቡ ለሐብ(የእሳት ልጅ) - ሲል የዚህ ሰው አባት እሳት ነው ማለት አይደለም፣
- 42፡7 ላይ "መካ የከተሞች እናት" ሲል መካ ከተሞችን የወለደች ሴት ከተማ ማለት አይደለም፡፡

ይህ ምሳሌአዊ አነጋገር ነው፣ እንደዚሁ በተለምዶ የዘመኑ ልጅ፣ የአዲስ አበባ ልጅ፣ የስለት ልጅ ... በማለት ሲገለፅ ዘመን ወይ አዲስ አበባ ወይ ስለት... የሚባል እናት ወይ

አባት ኖሮ አለመሆኑ ግልፅ ነው፣ ሁሉም የተነገረበት አውድ አለው፣ እንደዚሁም የኢሳም የአላህ ልጅነት የተነገረበትን የራሱ አውድ አለው::

እንደ እስልምና የሰው ልጅ ሁለት ማንነቶች አሉት ስጋና ነፍስ(74:38)፣ እንደዚሁ ኢሳ ውስጥም ካሉት(ከተዋሃዱት) ማንነቶች ውስጥ አንዱ ከመርየም ይዞ የተወለደው ስጋዊ ማንነቱ ሲሆን ሌላው ደግሞ ከላይ የተመለከትነው አምላካዊ ማንነቱ ነው፣ በዚህም ኢሳ በስጋ የሰው ልጅነት አለው በመንፈስ ደግሞ አምላክነት አለው፤ ይህ የአምላክ ማንነት ደግሞ ራሱን ዝቅ አድርጎ፣ ስጋን [27] ተዋህዶ መወለዱና ብዙ ስቃዮችን እስኪመለከት ድረስ መታዘዙ "የአላህ ልጅ" አስባለው፣ መጽሐፍ ቅዱሱም የኢሳን ልጅነት የተመለከተው በዚሁ መልክ ነው፣

> ፊልጵ.2:7-8 "... በሰው ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፣ በምስሉም እንደ ሰው ተገኘ፡ ራሱን አዋረደ፤ ለሞትም ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳን የታዘዘ ሆነ::"

በዚህም የኢሳ "የአላህ ልጅነት" በዚህ ራስን ዝቅ የማድረግና የመታዘዝ አውድ የሚፈታ እንጂ በስነተዋልዶ ልጅነት አይደለም፣ ኢሳ እንደዚህ መሆን ያስገደደው ደግሞ ከታች በ2.3.2.4.4 ክፍል በቀረበው ቁርአናዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት ነው:: መጽሐፍ ቅዱሱ በኢሳ ውስጥ ስለ ተዋህደው አምላካዊ ማንነት ሲናገርም፣

> ዕብ.7:3 "አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍፃሜ የለውም፣ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል::"

ይላል፣ በዚህም በኢሳ ውስጥ የተዋህደው አምላካዊ ማንነት አልተወለደም፣ እናትም አባትም የሉትም፣ ዘላለማዊ በመሆኑ መጀመርያም ፍፃሜም የሉትም::

እዚህ ጋር ለአብዛኛው ሙስሊም ጥያቄ የሚፈጥረው "አምላክ እንዴት የሰውን ስጋ ተዋህዶ ሊወለድ ይችላል" የሚለው ነው፣ ይህ አምላክ ሁሉን ነገር ማድረግና ሁሉን ነገር መሆን መቻሉን ካለማወቅ የሚመጣ ስህተት ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት እንኳን 19:17 "መንፈሳችንንም ወደ እርስዋ (መርየም) ላክን:: ለእርስዋም ትክክለኛ ሰው ሆኖ ተመሰላት::" የሚለውን መመልከት ይቻላል፣ የአላህ መንፈስ እንዴት ሰው ሊመሰል እና እንደ ሰው ዓይን አፍንጫው ... ኖሮት ሊታይ ይችላል? አይባልም፣ እሱ ሁሉን መሆን ስለሚችል እንዳለ እንቀበለዋለን፣ በዚህም "ፈጣሪ እንደዚህ መሆን አይችልም" የሚለው አነጋገር ስህተት ነው::

---

[27] "ተዋህዶ" የሚለው ቃል ለመረዳት ለምሳሌ ያህል በተቃራኒው መንፈሳዊ ጎራ ያለውን አሰራር እንመልከት፣ ሰዎች ላይ ሰይጣን ሲቀመጥ ይህ መንፈስ ከዚያ ሰው ጋር የሚፈጥረው ጥምረት የተዋህዶ ጥምረት ነው:: ይህንን ከእዕምሯችን የመረዳት አቅም በላይ የሆነውን አሰራር ሙሉ በሙሉ ማወቅ ባንችልም ተዋህዶ ማለት ስጋና መንፈስ የሚጣመሩበት አሰራር መሆኑን ግን በቀላሉ መረዳት እንችላለን::

2.3.2.4.4. “ኢሳ አልተገደለም”

ይህንን አስመልክቶ ቁርአኑ፣

> 4፡157-158 “እኛ የአላህ መልዕክተኛ የመርየምን ልጅ አልመሲህ ኢሳን ገደልን፣ በማለታቸው (ረገምናቸው)፣ አልገደሉትም አልሰቀሉትምም … ይልቁንስ አላህ ወደ እሱ አስነሳው።”

ይላል፣ ይሁን እንጂ ኢሳ አልተገደለም ከሆነ ከፈጣሪ አሰራር አንፃር በእስልምናው ላይ አንድ ትልቅ ክፍተት ይፈጠራል። በቁርአኑ ላይ የተገለፀው አንድ ቋሚ የፈጣሪ አሰራር አለ፣ ይህም ኃጢያት የሚሰረየው በመስዋዕት ብቻ መሆኑን፣

> 22፡34 “<u>ለአህዛብ ሁሉ</u> (ወደ አላህ) መስዋዕት ማቅረብን <u>ደነገግን</u>።”

ይህ የአላህ የማይሻረው ዘላለማዊ ህጉ ነው። የአብርሃም ልጅም መስዋዕት ለመሆን የዳነው በዚህ አሰራር መሆኑን ቁርአን ይነግረናል፣

> 37፡107 “(የኢብራሂምን ልጅ) በታላቅ ዕርድም (መስዋዕት) ተቤዠነው።”

ይህ የሆነው “ኃጢያት ያለ መስዋዕት ስለማይነፃ ነው”። ለእስልምናና ለክርስትና አባት የሆነው የአይሁድ ኃይማኖት ዛሬም ድረስ ኃጢያትን ለማስተሰረይ የሚጠቀመው ይህንኑ መስዋዕት የማቅረብ ስርአት ነው።

በዚሁ ፈጣሪ ከነአብርሃም ዘመን ጀምሮ ሲሰራበት በነበረው መርህም ክርስትናው ኃጢያት የሚነፃው በኢየሱስ መስዋዕትነት እንደሆነ ያስተምራል። እንደ ክርስትና አስተምህሮ፣ ኢየሱስ በእንስሳት መስዋዕት ፋንታ መስዋዕት ሆኖ የሰው ልጆች ኃጢያት ማስተሰረያ እንዲሆን የተፈለገው የሰው ልጅ ኃጢያት በአይነትና በመጠን እየበዛ በእንስሳት ደም መንፃት ስላልቻለ ነው፣ በዚህም ለሁሉም ኃጢያት ጠቅልሎ መስዋዕት ማቅረብ የሚችል እንስሳ፣ ሰው፣ መልአክ … ባለመኖሩ ለዚህ ሁሉ ኃጢያት ተመጣጣኝ መስዋዕት ማቅረብ የሚችለው እራሱ ዋናው አምላክ በመሆኑ፣ ወልድ(አንዱ የፈጣሪ የሥላሴ ማንነት የሆነውና የኢሳ አምላካዊ ማንነት) ለራሱ የሰው ስጋ ለብሶ፣ በዚሁ ስጋው እንደሻማ ቀልጦ ለሌሎች አበራ።

<u>እስልምናው ጋር ስንመጣ ግን ስለኃጢያት ስርየት ከተደነገገው የፈጣሪ መርህ ወይ እንደ አይሁዱ የእንስሳት መስዋዕት በማቅረብ ወይ እንደ ክርስቲያኑ በኢየሱስ መስዋዕትነት በማመን አልተከበረም፣ በዚህም የእስልምናው አስተምህሮ መሀል ሜዳ ላይ የቀረ አስተምህሮ ሆኗል።</u>

<u>እስልምና በዚህ አካሄዱም ኢስማኤልን ለማዳን ተብሎ ስለቀረበው መስዋዕት ብሎ የሚያከብረው የታላቁን የአረፋ በዓል መንገድ መከተል አልቻለም፣ በዚህም የአረፋ በዓል ትርጉም አልባ ሆኖበታል።</u>

ሌላው ከኢሳ መሞት ጋር በተያያዘ ኢሳ አምላክ ከሆነ አምላክ እንዴት ይገደላል? የሚለውን ጥያቄ ሲነሳ ይታያል፣ ይህ አንድ መሠረታዊ እውነታን ያላስተዋለ አባባል ነው፣ አንድ ሰው ተደብድቦ ሲገደል የሚደበደበውም ሆነ የሚሞተው ስጋዊ ማንነቱ እንጂ ነፍሳዊ/መንፈሳዊ ማንነቱ አይደለም፣ ስጋውያን የሚነዱት ስጋዊ ማንነትን ነው፣ ኢሳም ለሰዎች ኃጢያት ስርየት መስዋዕትነትን የከፈለው በስጋዊ ማንነቱ ነው።

2.3.2.4.5. <u>"የዓለም አምላክ እንጂ "የእስራኤል አምላክ" አስተምህሮ ስህተት ነው"</u>

ይህ ሐሳብ የሚነሳው በመጽሐፍ ቅዱሱ ብዙ ስፍራዎች ላይ ያለውን "የእስራኤል አምላክ" የሚለውን አባባል በመቃወም ነው። በርግጥ ቁርአኑም ለእስራኤል ከሌላኛው ዓለም ነጥሎ ትልቅ ስፍራ ይሰጣታል፣

> 45፡16 "ለእስራኤል ልጆች መጽሐፍንና ሕግን፤ ነቢይነትንም በርግጥ ሰጠናቸው። ከመልካም ሲሳዮችም በርግጥ ለገስናቸው። <u>በዓለማት ላይም አበለጥናቸው</u>።"

በዚህም እስራኤል ለፈጣሪ የተለየች ሀገር መሆንዋን የማይታበይ ሀቅ ነው። ይሁን እንጂ "የእስራኤል አምላክ" የሚለውን አጥርቶ ለማለፍ ያህል፣ መጽሐፉ ላይ በመጀመርያ "እስራኤል" የተባለው ያዕቁብ(ያዕቆብ) ሲሆን ከዚያም ይህ ስም የአስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ዘሮች ሆነ፣ ከዚያ ቀጥሎም እነኚህ ዘሮች የሚኖሩበት ሀገር መጠርያ ሆነ ነገር ግን "እስራኤል" የሚለው ቃል በመጀመርያ የቀረበው "አማኝ" በሚል ትርጉሙ ነበረ፣ ፈጣሪ የያቆብን እምነት ተመልክቶ "ከእንግዲህ ወዲያ ስምህ ያዕቆብ አይባል እስራኤል ይባል" አለ።

መጽሐፍ ቅዱሱ ይህ የእስራኤል "አማኝ" ትርጉምና የእስራኤል "ሀገር" ትርጉም የተለያየ መሆኑን በሮሜ.9፡6-8, ገላ.4፡22-31 ... ስፍራዎች ላይ በግልፅ ይገራል። በዚህም <u>በአዲሱ ኪዳን</u> "እስራኤላዊነት" በስጋ ከእስራኤል ዘር መወለድ ሳይሆን "አማኝነት" ይህም "የክርቶስን ተከታይነትን" ማለት ነው፣ ይህም በተግባር የተረጋገጠ እውነታ ነው፣ በስጋ የዘር ሀረጋቸው እስራኤል የሆኑት ኢየሱስን የገደሉበት፣ ላለፉት 2,000 አመታት በኢየሱስ በኩል የመጣውን ክርስትና ያላገኙበትና በራዕይ መጽሐፍም ላይ በገነት የሚኖሩት ከሁሉም ዘሮች መሆናቸው የተነገረበት እውነታ ውስጥ(ኤፌ.3፡5-6, ራዕ.5፡9-10 ...)፣ መጽሐፍ ቅዱስ "እስራኤል" ብሎ የሚጠራው ማንን እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል።

በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ "የእስራኤል አምላክ" በሚልበት አገላለፁ ኢሳም "ለእስራኤል እነጂ አልተላከሁም፣ ከእስራኤል ቤት ለጠፉ በጎች፣ የእስራኤል አምላክ ..." ብሎ ያስተማራቸው እውነታዎች በሙሉ የተነገሩት ቁርአኑ "ተከታዮቹ"(57፡27) ለሚላቸው ለክርስቲያኖች እንጂ ለእስራኤል ሀገር አይደለም።

በተመሳሳይ መንፈስም አንዳንድ የእስልምና ምሁራን መጽሐፍ ቅደሱን ሲተቹ ይታያል ይሁን እንጂ የአብዛኞቹ ትችቶች፣ ከላይ እንደተመለከተው "እስራኤል" የሚለውን ቃል

ትርጉም በማምታታት፣ የአይሁድ ኃይማኖት ስርአቶችን ከክርስትና ኃይማኖት ስርአቶች ጋር በማምታታት፣ የብሉይ ኪዳኑን የቤተመቅደስ ስርአት ከአዲስ ኪዳኑ የቤተክርስቲያን ስርአት ጋር በማምታታት፣ የሰውና የአምላክ ተዋህዶ የሆነውን የኢሳን(ኢየሱስን) አምላካዊ ማንነትና ሰውኛ ማንነት በማምታታት፣ የሥላሴን የሦስትነትና የአንድነት እውነታ የማምታታት በአጠቃላይ በሁለት ነገሮች መካከል የማምታታት አካሄድ እንጂ ሚዛን የሚያነሱ መሠረታዊ የሆኑ ትችቶች አይደሉም።

በአጠቃላይ ስንመለከት "የክርስትና ስህተቶች" ተደርገው በነብዩ ሙሐመድ የቀረቡት ነጥቦች እንደ ነብዩ ቀደምት አስተምህሮ ስህተት አለመሆናቸውን ይባሱኑም ነብዩ ከቀደመው መንገድ ያደረጉትን የአቅጣጫ ለውጥ አጉልተው የሚያሳዩ ሆነው ነው የምንመለከታቸው፣ ይህ እውነታም እስልምና የነብዩ ሙሐመድ የፈጠራ ስራ እንጂ የቀደመው መንገድ አለመሆኑን ያሳያል።

2.3.2.5. ከአይሁድ/ክርስትናው የተቃረነ ኃይማኖት ማስፋፍያ እስትራቴጂን ተከተሉ

ነብዩ በእስራኤሎቹ ነብያት መንገድ፣ ለህዝቡ ተአምራት እያሳዩ፣ ህዝቡን የሚያሳምኑበት መንገድ ሲያጡ ለኃይማኖታቸው ማስፋፍያነት የተጠቀሙት በግልፅ የማጭበርበር፣ የማስፈራራት፣ የሽብርተኝነትና በጂሀድ በጉልበት የማስለም ዘዴዎችን ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

1. **ማጭበርበር**

ነብዩ "ከክርስትና ጋር አንድ ነን" ብለው ያሰባሰቡት የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ወደ ክርስትና እንዳይሳቡባቸው እስልምና ከክርስትና ኃይማኖት እንደሚበልጥ ለማሳየት ግልፅ የማጭበርበር አስተምህሮዎችን ሲያስተምሩ ነበረ፣ ለምሳሌ፣

- አይሁዶች/ክርስቲያኖች ቁርአን ሲነበብላቸው ያለቅሳሉ
  5፡83 "(አይሁዶችና ክርስቲያኖች) ወደ መልክተኛውም የተወረደውን (ቁርአን) በሰሙ ጊዜ እውነቱን ከማወቃቸው የተነሳ ዓይኖቻቸው እንባን ሲያፈሱ ታያለህ። "ጌታችን ሆይ አመንን ከመስካሪዎቹም ጋር ፃፈን" ይላሉ።"
- አይሁዶች/ክርስቲያኖች በቁርአን ደስ ይላቸዋል
  13፡36 "እነዚያ መጽሐፉን የሰጠናቸው ወዳንተ በተወረደው ይደሰታሉ።"
- አይሁዶች/ክርስቲያኖች ቁርአን ሲሰሙ ይሰግዳሉ
  17፡107 "(ቁርአን) በእርሱ እመኑ ወይ አትመኑ በላቸው፣ እነዚያ ከእርሱ በፊት እውቀትን የተሰጡት በእነርሱ ላይ በተነበበ ጊዜ ሰጋጆች ኾነው በሸንጎበቶቻቸው ላይ ይወድቃሉ፤"

- <u>አይሁዶች/ክርስቲያኖች ሙሐመድን እንደ ወንድ ልጃቸው ያውቁታል</u>
  2፡146 “እነዚያ መጽሐፍ የሰጠናቸው ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ (ሙሐመድን) ያውቁታል። ከነሱም የተለዩ ክፍሎች እነርሱ የሚያውቁ ሲኾኑ እውነቱን በርግጥ ይደብቃሉ። ይህ ከጌታህ የሆነ እውነት ነው ከተጠራጣሪዎቹም አትሁን።”
- <u>ነብዩ ሙሐመድ እንደሚመጡ በመጽሐፍ ቅዱሱ ተነግሮ ነበረ</u>
  61፡6 “የመርየም ልጅ ኢሳም፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ እኔ ከተውራቱ በፊቴ ያለውን የማረጋግጥና ከኔ በኋላ በሚመጣው መልክተኛ ስሙ አሕመድ በሆነው የማበስር ስኾን ወደናንተ (የተላከሁ) የአላህ መልእክተኛ ነኝ ...”
- <u>ቁርአን እንደሚወርድ በመጽሐፍ ቅዱሱ ተተንብዮ ነበረ</u>
  26፡196 “እርሱም (ቁርአን) በቀድሞዎቹ መጽሐፍት ውስጥ የተወሳ ነው።”
- <u>አይሁዶች/ክርስቲያኖች ቀድሞውኑ ሙስሊሞች ነበሩ</u>
  28፡52-53 “እነዚያ ከእርሱ በፊት መጽሐፍን የሰጠናቸው እነርሱ በእርሱ ያምናሉ። በእነሱም ላይ በሚነበብላቸው ጊዜ፣ በእርሱ አምነናል። እርሱ ከጌታችን የሆነ እውነት ነው። እኛ ከርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን፣ ይላሉ።”
- <u>“ከኔ በፊት የነበሩት የእስራኤል ነብያት አይሁድ/ክርስቲያን ሳይሆኑ ሙስሊሞች ነበሩ”</u>
  ነብዩ፣ 6፡163 “... እኔ የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ።”፣ 39፡12 “የሙስሊሞች መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ።” ያሉትን ትተው፣
  - 3:67 “ኢብራሂም አይሁዳዊም ክርስቲያንም አልነበረም ግን ወደ ቀጥተኛ ኃይማኖት ተዘነበለ፣ ሙስሊም ነበረ ...”
  - 61፡7 “ኢየሱስ ወደ ኢስላም የሚጠራ ሲኾን ...”
  - 22፡78 “... የአባታችሁን የኢብራሂምን ኃይማኖት ተከተሉ። እርሱ ከዚህ በፊት ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል።”
  - 2፡139-140 “... በአላህ (ኃይማኖት) ትከራከሩናላችሁን ... ወይም ኢብራሂም ኢስማኢል ኢስሃቅም ያዕቁብም ነገዶቹም አይሁዶች ወይም ክርስቲያኖች ነበሩ ትላላችሁን፣ “እናንተ ታውቃላችሁ ወይንስ አላህ ...”

ነብዩ ለነዚህ ማጭበርበርያ ትምህርቶቹ ሲልም በየመልዕክቶቹ ውስጥ መሀላን ሲያበዛ ነበረ፣ ለምሳሌ፣

> 52፡1-6 “በጡር (ጋራ) እምላለሁ። በተፃፈው መጽሐፍም። በተዘረጋ ብራና ላይ፤ (በተፃፈው)። በደመቀው ቤትም። ከፍ በተደረገው ጣራም። በተመላው ባህርም እምላለሁ።”

ተመሳሳይ መሀላዎቹንም በብዙ ስፍራዎች ላይ እንመለከታለን 75፡1, 77፡1-6, 81፡1-15, 85፡1-3, 86፡1-11 ...፤ እንደዚሁ የነብዩ ጓደኞችም ነብዩን በመሀላዎች ሲያግዙ ነበረ፣ ለምሳሌ፣

> 53፡1-11 "በኮከብ እምላለሁ በወደቀ (በገባ) ጊዜ፡፡ ነቢያችሁ *ሙሐመድ* አልተሳሳተም፤ አልጠ*መመ*ምም፡፡ ከልብ ወለድ አይናገርም ... *ኃ*ይሎቹ ብርቱ (መልአክ) አስተማረው፡፡ እውቀት ባለቤት የሆነው (አስተማረው በተፈጥሮ ቅርፁ ሆኖ በአየር ላይ) ተደላደለም፡፡ እርሱ በላይኛው አድማስ ሆኖ፡፡ ከዚያ ቀረበ፤ ወረደም ... ወደ ባሪያውም (አላህ) ያወረደውን አወረደ፡፡ (ነብዩም በአይኑ) ያየውን በልቡ አልዋሸም፡፡"

ነገር ግን በወቅቱ የነበሩት ሰዎችም ይህንን የነብዩን አጭበርባሪነት በ*መመ*ልከት 16፡101 "... አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም፡፡" ሲሉት ነበረ፡፡

2. <u>ማስፈራራት</u>

ከማጭበርበሩ ጎን ለጎን ነብዩ የሚነሱበትን ጥያቄዎች ማለፍ የሞከረበት አንዱ መንገድ አስፈራሪ ትምህርቶች በመስጠት ነው፣ አስፈራሪ ትምህርቶች ሰዎችን በፍራቻ መንፈስ ውስጥ በማስገባት የጥያቄና የፍልስፍና መንፈስን ይይዛሉ፡፡ ቁርአኑም ነብዩ *ሙ*ሐመድ አስፈራሪ ነቢይ እንደሆነ ይናገራል(21፡45, 13፡7...)፣ ከአስፈሪ ትምህርቶቹ ለምሳሌ ያህል አንዱን ብንመልከት፣

> ሳሂህ ሙስሊም 41፡7005 - 41፡7019 "... ደጃል ወጣት ሰው ነው፣ ፀጉሩ ወፍራም፣ የተጠቀለለ፣ ቂጪጫ፤ አንድ አይኑ የማያይ፣ አይኑም የሚንሳፈፍ ወይን ይመስላል፣ በአይኖቹ መ*ከ*ከል "*ቃ*ፊር/ከሀዲ" የሚል ፅሁፍ ተፅፏል ... የሚሄድበት ፍጥነት በንፋስ እንደ ሚነዳ ዳመና ነው፤ እሳትና ውሀ ይዞ ይሄዳል፣ እሳቱ እንደ ቀዝቃዛ ውሀ ነው፣ ውሀው እንደ እሳት ነው፤ እሳትና ጫካ አለው እሳቱ ጫካ ነው፣ ጫካው እሳት ነው ... ደጃልም ሰውየውን ለሁለተኛ ጊዜ ሊገድለው ሲፈልግ የሰውየው አንገት ወደ መዳብነት ተቀየረ፣ በዚህም የሚገድልበትን መንገድ ስላጣ፣ ሰውየውን <u>ወደ ላይ ወረወረው</u>፣ ሰዎችም ወደ ሲኦል እሳት የወረወረው ይመስላቸዋል፣ <u>ነገር ግን ወደ ገነት ነው የወረወረው</u>፡፡"

ነብዩ ይህንን እና መሰል አስፈራሪ ታሪኮችን ሲያወራ የነበረው ለማስፈራራት እንጂ እንደዚህ አይነት ሰው ኖሮ፣ ከምድር ወደ ሲኦል ወይ ወደ ገነት ሰውን መወርወር የሚቻል ... ሆኖ አይደለም የሚገርመው ደግሞ የተረት ነገር ተመልሶ በትክክል ደግሞ መናገር እንደማይቻለው ሁሉ፣ ተረቱ በሌላ ጊዜ ሲደገም፣ የጠፋው ዓይን ግራ ይሁን ቀኝ ተምታቶበታል፣ ሳሂህ ሙስሊም 41፡7010 "... ደጃል ግራ ዓይኑ የጠፋ ነው ..." ሲል ሳሂህ ሙስሊም 41፡7005 "ደጃል ቀኝ ዓይኑ የጠፋ ነው ..." ይላል፡፡

አስፈራሪ ትምህርቶች ሰዎችን በፍራቻ መንፈስ ውስጥ በማስገባት የጥያቄና ፍልስፍና መንፈስን ስለሚይዝ ነብዩ በነቢይነቱ ላይ የተነሳውን ጥያቄ በእንደዚህ አይነት አስፈራሪ ትምህርቶች ሸፍኖ ሲሄድ ነበረ፡፡

3. <u>ሽብር</u>

ነብዩ የተነሳበትን የነቢይነት ጥያቄ በመሸፈን አዲስ የመሠረተውን ኃይማኖት ለማስፋፋት የሽብር ስራን ስራዬ ብሎ ሲያካሂድ ነበረ፣ ስለራሱ አሸባሪነት ሲናገርም ሳሂህ ቡኻሪ 4፡52፡220 "... እኔ በሽብር አሸናፊ ተደርጌያለሁ፡፡" ይላል፣ ተመሳሳይ ሐሳብም ሳሂህ ሙስሊም 4፡1066, ሳሂህ ሙስሊም 4፡1067 ... ላይ ቀርቧል፣ ነብዩ ከራሱ የሽብር ስራ ባለፈ ተከታዮቹም ለኃይማኖት ማስፋፍያነት የሽብርን መንገድ እዲከተሉ አስተምሯል(8፡60)፡፡

በዚህም ነብዩ በዘመኑ ጭካኔ የተሞላባቸውን ብዙ የሽብር እርምጃዎችን በመውሰድና በማስወሰድ አካባቢውን ሲያስሸብር ነበረ፣ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- ሳሂህ ቡኻሪ 7፡71፡590 "... ሰዎቹም ተይዘው ሲቀርቡ ነብዩ የሰዎቹን <u>እጆችና እግሮች ቆራረጠ</u>፣ አይናቸውንም <u>በጋለ ብረት ተኮሳቸው</u>፡፡"
- ለጦርነት በተሰማሩበትም በውጊያ ወንዶቹን ካሸነፉ በኋላ እናቶችንና ህፃናትን ሲገድሉ እንደ ነበረ ሳሂህ ሙስሊም 19፡4321 - 4323 ላይ እንመለከታለን፣
- ሳሂህ ቡኻሪ 4፡52፡264፣ ነብዩ ሙሐመድ አቡ ራፊን እንዲገድሉ የአንሳሪ ሰዎችን ላከ፣ ከገዳዮቹም አንዱ ሲናገር "... (ጨልሞ ነበረ) በጎረሮ ውስጥ አገኘሁት ... ከዚያ ጎራዴዬን መዝዤ በሆዱ ውስጥ ሰገሰኩኝ፣ አጥንቱን እስኪነካ ... ከዚያ ጥዋት ሞቱን ጥሩንባ ለፋፊው እስኪያበስረኝ ጠበቁ ከዚያ መጥቼ ለነብዩ አበሰርኩት፡፡"

  ተመሳሳይ የግድያ ትዕዛዝ ነብዩ በከአብ ቢን አል አሽራፍ ላይ ሲሰጥና ተከታዮቹም ሄደው ሲፈፅሙ ሳሂህ ቡኻሪ 5፡59፡369 ላይ እንመለከታለን፡፡

የነብዩ አሸባሪነት በወቅቱ በአካባቢው የናኘ ሲሆን የሚገርመው እሱ ሳይደርስባቸው ቀድሞ "ነመን በጤና" በማለት ለሱ ግብር ሲገብሩ የነበሩ ነገሥታት እንኳን ነበሩ፣ በዚህም የባህሬኑ መንግሥት(ሳሂህ ቡኻሪ 5፡59፡351) እና በወቅቱ አጠራር አይላ(Aila) የምትባል ሀገር(ሳሂህ ቡኻሪ 2፡24፡559) ነገሥታትን መመልከት ይቻላል፡፡

5. <u>ጂሀድ</u>

ጂሀድ ማለት ቅዱስ ጦርነት ማለት ነው፣ ይህ ጦርነትም የሚታወጀው ሰዎች እስልምናን በኃይል እንዲቀበሉ ለማድረግ ሲሆን የመጨረሻ ግቡም የዓለምን ህዝብ ማስለም ነው(8፡39, 48፡16, 13፡15 ...)፡፡

በዚህም ነብዩ ተከታዮቹን ለጂሀድ ውጊያ ሲያደፋፍር ነበረ(2፡65, 8፡65, 4፡84, 22፡78...)፣ ሰፊ የጂሀድ ትምህርቶችንም ሲሰጥ ነበረ፣ ይህም፡-

- በጂሀድ መሳተፍ በአላህ ዘንድ መወደድ መሆኑን(61፡4)፣
- አንድ ሰው በጂሀድ ቢሞት ገነት የሚገባ መሆኑን (ሳሂህ ቡኻሪ 4፡52፡48, 4፡74, 29፡6...)፣
- በህይወት ከተረፈም በጦርነቱ ከዘረፋ የሚገኘውን ሐብትና ምርኮኛ የራሱን ድርሻ የሚከፋፈል መሆኑን(ሳሂህ ቡኻሪ 4፡53፡366, 4፡53፡352, 4፡53፡358, 4፡53፡359
- በጂሀድ ባይሳተፍ ደግሞ ገሀነም የሚገባ መሆኑን(8፡16)፣
- በጂሀድ መለገም ኃጢያት መሆኑን(9፡38-39)፣
- ከጂሀድ መመለስ ኃጢያት መሆኑን(9፡84)፣
- ከጂሀድ መሸሽ ኃጢያት መሆኑን(33፡16, 8፡15-16)፣
- ከጂሀድ የሸሸን ፈጣሪም በምድር እንደሚቀጣው(9፡39, 48፡17)

አስተማረ፡፡

በዚህም ነብዩ አንድ ሙስሊም በጂሀድ ተዋጊነት መሳተፉ ጥቅም እንጂ ጉዳት የማያመጣበትና አለመሳተፉ ግን በሰማይም በምድርም ተጎጂ እንደሚያደርገው አስተማረ፡፡ በዚህም ነብዩ በወቅቱ አብዛኛው ሙስሊም ጂሀዲስት እንዲሆንና የትኛውም ጂሀዲስትም ከየትኛው ወታደር በላይ በወኔና በድፍረት እንዲዋጋ አደረገ፣ እስልምናንም ለመስፋፋት ይህንን እስትራቴጂ አጠንክሮ ገፋበት፣ እራሱም ብዙ የጂሀድ ጦርነቶችን መራ የመካ ወረራ(ሳሂህ ቡኻሪ 5፡58፡122፣ ሳሂህ ሙስሊም 8፡3253 ...)፣ የአል ካነዳቅ ጦርነት(the battle of the trench)(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡8፡452)፣ የባድር ጦርነት(ሳሂህ ቡኻሪ 5፡59፡358)፣ የአል-ሃራ ጦርነት(ሳሂህ ቡኻሪ 5፡59፡358) ...

ነብዩ በዚህ የጂሀድ ዘዴም ኃይማኖቱን በቀላሉ ማስፋፋት እንደሚችል ተገነዘበ፣ በራሱም ላይ ከባድ ጉዳት እንኳን እስኪደርስበት በጂሀድ ሲሳተፍ ነበረ፣

> ሳሂህ ቡኻሪ 7፡71፡618 "በኡሁዱ ጦርነት ... ሄልሜቱ በነብዩ እራስ ላይ ተሰበረ፣ የነብዩ ፊትም በደም ተሸፈነ፣ ጥርሱም ተሰበረ፡፡"

ነብዩ በዚህ ለኃይማኖት ማስፋፍያነት በዘየደው አዲስ ስልትም እስልምና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከቁሬሽ መንደር ተነስቶ ዓረብን፣ ከዚያም ሰሜን አፍሪካንና አብዛኛውን ኢሲያ አዳረሰ፡ ኃይማኖቱ ወደ ሀገራችን የተስፋፋውም በዚህ መንገድ ነበረ፣ ይህንንም ሁኔታ፣ በግልፅ በመናገራቸው የሚታወቁት ሐረሮች አንድ መታሰቢያ ስነ ግጥም ቋጥረውለት ነበረ፣

> [28]"Salaata Orfoo
> Sodaa qottoo
> Allaahuu Akibar``

ሲተረጎምም፣

[28] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 32

“የአርፎ ስግደት
መጥረብያ ፍራቻ
አላሁ አክበር”

“አርፎ” የሚባለው በወቅቱ ሐረር አካባቢ በግድ እንዲያሰልም በስፍራው የተሾመ ሰው ነበረ፣ ይህ ሰው የስግደት ሰዓትን ጠብቀው የማይሰግዱትን ሰዎች አንገታቸውን በመጥረብያ ሲቆርጥ ስለነበረ ህዝቡ “ንመን በጤና” በማለት በየስግደት ሰአቱ መዝጊድ እየተገኘ ይሰግድ ነበረ፣ ህዝቡም ምንም እንኳን ባላመነበት ነገር በግድ እየሰገደ የነበረ ቢሆንም ለሁኔታው ግን ይህንን መታሰብያ ግጥም ቋጥሮለት ነበረ፡፡

ዛሬ ላይ እያንዳንዱ ሙስሊም እስልምና እንዴት ወደ ዘሩ እንደገባ ማወቅ ቢችል ብዙ ተመሳሳይ ታሪኮች እንደሚያገኙ ግልፅ ነው ይሁን እንጂ ዛሬ ላይ የትኛውም ሙስሊም ነብዩ ስለ ሲኦል ያስተማሩዋቸውን አስፈራሪ ትምህርቶችን ሰምቶ እውነተኛውንና የተሳሳተውን መንገድ የመመርመር አቅም የለውም፡፡

[29] የነብዩ ሙሐመድ የዘር ሐረግ፣ የአረብ የዘር ሐረግ ከሆነው ከኢስማኢል የዘር ሐረግ እንደሚመዘዝ ይነገራል፣ ነብዩ ኃይማኖቱን በእስራኤላውያኑ ኢብራሂም-ኢስሀቅ-ያዕቁብ መስመር ጀምሮ ወደ አረቦቹ የኢብራሂም-ኢስማኢል መስመር ቀየረ፣ ስለሚመጣው ነገር አስቀድሞ የሚናገረው መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለዚህ የዘር ሐረግና ኃይማኖት ሲናገር፣

ዘፍ.16፡12 “እስማኤል ... እጁን በሁሉም ላይ ያነሳል ሁሉም እጁን ያነሳበታል...”

ሙስሊሞችም “ዓለም እስኪሰልም ድረስ ተጋደል” ትዕዛዝ ለማስፈፀም በተለያየ የጂሀድ ስልት እየታገሉ ይገኛል እንደዚሁ ደግሞ የዓለም ህዝብም የርዕዮተ ዓለም ልዩነት እንኳን ሳይገድበው አንድ ሆኖ እየተዋጋ ያለው ይህንኑ ሽብርተኝነትን ነው፣ ይህ እውነታ ግን አስቀድሞ በመጽሐፍ ቅዱሱ ተተንብዮ ነበረ፡፡

ከላይ የቀረቡት የነብዩ ኃይማኖት ማስፋፍያ ዘዴዎች፣ አጭበርባሪነት፣ አስፈራሪነት፣ ሽብርተኝነትና ጂሃዲስትነት ለእስልምና መስፋፋት የጀርባ አጥንት የነበሩ ቢሆኑም ከሙሐመድ በፊት በነበሩት የአይሁድ/ክርስትና ነብያት ግን ኃይማኖታቸውን ሲያስፋፉ የነበሩት ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ብቻ መሆኑን ስንመለከት የነብዩ ሙሐመድ እስልምና በነአብርሃም፣ ኢስሐቅ፣ ያዕቁብ፣ ሙሳ፣ ኢሳ ... መንገድ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይም ስንመለከት ነብዩ ሙሐመድ “በአይሁድ/ክርስትና መንገድ ነኝ” በማለት ተነስቶ የአቅጣጫ ለውጥ አደረገ፣ በዚህም “በነብያቱ መንገድ ነኝ” ያለውን ትቶ “ነቢይ እኔ ብቻ ነኝ” በማለት፣ “ቀደምት መጽሐፍትን እንቀበላለን” ብሎ “ቁርአን ብቻ” በማለት፣

[29] https://en.m.Wikipedia>wiki>Ishmaelites

“አንድ ነን” ሲል ከርሞ “ትክክለኛው እስልምና ብቻ ነው” በማለት፣ ከዚያም አይሁድ/እስልምና ላይ የተሳሳቱ ሂሶች በማቅረብና ከአይሁድ/ክርስትና ኃይማኖት ማስፋፍያ መንገድ በተቃራኒ የራሱን ኃይማኖት ያስፋፋበትን ሁኔታ ስንመለከት ነብዩ ሙሐመድ ህዝቡ ላይ ትልቅ የሽወዳ ስራ መስራቱን እንመለከታለን፣ ነብዩ ይህን ደግሞ ለምን እንዳደረገ በማጠቃለያው ክፍል እንመለከታለን።

2.3.3. ነብዩ ሙሐመድ እና ኢየሱስ ክርስቶስ ከኃይማኖት መሪ ስብዕና አንፃር

በባሌም ይሁን በቦሌ ዛሬ ላይ ሙሐመድና ኢየሱስ በዓለማችን ወደር የሌላቸው የኃይማኖት መሪዎች ሆነው ይታያሉ፣ ሌላውን ትውልድ ትተን በዛሬው ትውልድ እንኳን ብንመዝናቸው እያንዳንዳቸው ከየትኛውም ታዋቂ ሰው በላይ ከ1.5 ቢሊየን በላይ ተከታይ አሏቸው።

እነዚህ ሁለቱ መሪዎች የሁለቱ ዓለማቀፍ ኃይማኖቶች፣ የእስልምናና ክርስትና መስራችና መሪዎች ሲሆኑ ሁለቱም መሪዎች እነሱን መከተልና አለመከተል የሲኦልና የገነት ልዩነት አድርገው ይገልፃሉ፣ ስለዚህ የትኛውም ሰው የየትኛውን ኃይማኖት መሪ መንገድ መከተል እንዳለበት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት።

በዚህም የሁለቱንም ኃይማኖት መሪዎችን መንገድ ስናነፃፅር፡-

- የፈጣሪን ባህሪ ከመምሰል አንፃር፣
- ከመንፈሳዊነት ይልቅ ለስጋዊ ድሎት ከመሮጥ አንፃር፣
- ካላቸው እውቀት አንፃር፣
- ገነት ለመግባት እርግጠኛ ከመሆናቸው አንፃር፣

እያነፃፀርን የትኛው መሪ ትክክለኛ መሪ እንደሆነና ሰዉ ማንን መከተል እንዳለበት እንመለከታለን።

2.3.3.1. የፈጣሪ ባህሪን ከመምሰል አንፃር

ሁለቱን መሪዎች ከፈጣሪ መንገድ አንፃር ለማነፃፀር ሁለቱንም በተመሳሳይ መንገድ ከገለፀት ከፈጣሪ ባህሪ አንፃር እንመለከታቸዋለን፣ ሁለቱም መሪዎች ፈጣሪን ከሞላ ጎደል በአንድ መልክ ገልፀውታል፣ አብዛኛቹ የቁርአን ምዕራፎች የሚጀምሩት “በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው” በሚል ቃል ነው፣ ኢየሱስም ፈጣሪን በዚሁ መልክ ይገልፀዋል።

በዚህም ይህን በሁለቱም ኃይማኖቶች ወጥ የሆነው የፈጣሪ ማንነት ይዘን ኢየሱስና ሙሐመድ ጋር በመሄድ የትኛው በፈጣሪ መንፈስ ውስጥ ሲሰራ እንደ ነበረ፣ የትኛው ደግሞ በተቃራኒ መንፈስ ሲሰራ እንደነበረ እንመለከታለን፣

- **<u>የኢየሱስ መንገድ</u>**

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ሰዎችን በፍቅር ጠራ፣ ተከታዮችን ያፈራው ገድሎ ሳይሆን ሞቶላቸው ነው፣ በጨለማ ለነበረው ህዝብም ያበራው እራሱ እንደ ሻማ ቀልጦ ነው፣ ጠላቶች በተነሱበት ጊዜም አልተዋጋቸውም ምክንያቱም "ሩህሩህ፣ አዛኝ ..." መንፈስ ውስጥ የሚኖር በመሆኑ፣ ይህ እውነታም ቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበረ፣

> ማቴ.12፡18-20 "እነሆ የመረጥሁት ብላቴናዬ፣ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ወዳጄ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ ... አይከራከርም አይጮህም፣ ድምፁ በአደባባይ የሚሰማ የለም ... የተቀጠቀጠን ሸንበቆ አይሰብርም የሚጤስን የጥዋፍ ክር አያጠፋም።"

ኢየሱስ ተከታዮቹ ክርስቲያኖችንም በዚህ የፍቅር መንገድ እንዲጓዙ አስተማረ "ሰዎችን ይቅር ባትሉ ፈጣሪ ይቅር አይላችሁም አለ"፣ ጥላቻን፣ ስድብን፣ በቀልን ከለከለ፣ ይባሱኑ "ባልንጀራውን እንደራሱ የማይወድ ሊከተለኝ አይገባም" አለ(ማቴ.19፡19)፣ ይህ ለወዳጅ ብቻ ሳይሆን ለጠላትም መደረግ እንዳለበት አስተማረ፣ በዚህም ክርስቲያኖች አጋፔ(ጠላትን መውደድ) እስከሚባለው ከባድ የፍቅር ደረጃ እንዲጓዙ አዘዘ፣ በዚህም ከባባድ የፍቅር ትዕዛዞችን ሰጠ፡-

- ማቴ.5፡44-45 "ጠላቶቻችሁን ውደዱ፣ የሚረግሙአችሁን መርቁ ..."
- ማቴ.5፡39-41 "... ክፉውን አትቃወሙ፣ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፣ እንዲከስህም እጅ ጠባብህን እንዲወስድ ለሚወድ መጎናፀፊያህን ደግሞ ተውለት፣ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ፣ ለሚለምንህ ስጥ፣ ከአንተም ይበደር ዘንድ ለሚወደው ፈቀቅ አትበል።"

በዚህ አንድ የክርስቶስ ተከታይ ሰዎች ክፉ ቢሰሩበት እንኳን የመጨረሻ እርምጃው "ሲያሳድዳችሁ ፀልዩ" ብቻ ሆነ ይህም በአማኙ ላይ ለሚደርስ ለማንኛውም ነገር መልስ የሚሰጠው ፈጣሪ በመሆኑና በዚህም አማኙ ራሱን በፈጣሪ ኃይል ላይ ብቻ እንዲጥልና ከሰው ጋር ሠላም እንዲያወርድ አዘዘ።

በዚህም "ሩህሩህ፣ አዛኝ ..." የተባለውን መንፈስ በኢየሱስ ህይወትና አስተምህሮ ውስጥ እንመለከታለን።

- **<u>የሙሐመድ መንገድ</u>**

ሙሐመድ ከላይ እንደተመለከትነው "ሩህሩህ፣ አዛኝ ..." መንገድ ትቶ የማጭበርበር፣ የማስፈራራት፣ የሽብርተኝነትና የጂሀድን መንገድ መረጠ፣ በዚህም ብዙ ሰዎች ተጭበረበሩ፣ ተሸበሩ፣ ተገደሉ ... ነብዩም ይህ መንገድ ውጤታማ መሆኑን በመመልከት ተከታዮቻቸው በዚህ መንገድ እንዲሄዱ አስተማረ፣ በዚህም ዛሬ ድረስ የሱን ዓላማ ይዘው

በተነሱ ከግለሰብ አንስቶ እንደ አይኤስ፣ ቦኮሀራም … በመሳሰሉ ድርጅቶች ብዙዎች ተጭበረበሩ፣ ተሸበሩ፣ ተገደሉ …

በዚህም ከፈጣሪ "ሩህሩህ፣ አዛኝ …" ባህሪ አንፃር ከኢየሱስና ከሙሐመድ የትኛው በፈጣሪ መንገድ እንዳለ በግልፅ መመልከት ይቻላል፣ ከዚህ እውነታም በመነሳት ማን በፈጣሪ መንገድ ላይ እንዳለና ሊከተሉት የሚገባው የትኛው እንደሆነ መለየት አያዳግትም::

2.3.3.2. <u>ከመንፈሳዊነት ይልቅ ለስጋዊ ድሎት ከመሮጥ አንፃር</u>

የቅዱሳን ምድራዊ/ስጋዊ አኗኗር ምን መምሰል እንዳለበት በሁለቱም የእስልምናና የክርስትና ቅዱሳን መጽሐፍት ላይ በተመሳሳይ ቃል ተገልጿል፣ የእስልምናውን ብንወስድ፡-

- ሳሂህ ቡኻሪ 8፡76፡456 "… አብዛኞቹ የገነት ነዋሪዎች እዚህ ደሀ የነበሩት ናቸው::"
- ሳሂህ ቡኻሪ 8፡76፡555 "የገነት መግቢያ ላይ ሆኜ ስመለከት ሐብታሞች ገነት እንዳይገቡ ሲከለከሉ አብዛኞቹ ድሆች እንዲገቡ ሲፈቀድላቸው አየሁ::"
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡435 "እነሱ በዚህኛው ዓለም ይደሰታሉ፣ እኛ ደግሞ በሚቀጥለው::"

ከዚህ ሐሳብ አንፃር የሁለቱን መሪዎች ኑሮ እነፃፅረን ስንመለከት፣

- <u>**የኢየሱስ መንገድ**</u>

ኢየሱስ በምድር ላይ በኖረባቸው ዘመኖቹ ምድራዊ ሐብት የማከማቸትና ምድራዊ ደስታን የመከተል ሐሳብ አልነበረውም፣ በዘመኑም "ይህ ነው" የሚባል ምድራዊ ንብረት አልነበረውም፣ የሐብት መነሻ የሆነውን የራሴ የሚለው ቤት እንኳን አልነበረው(ማቴ፡8፡19-20)፣ ይባሱኑም ሐብታሞቹን "ሰማያዊ መዝገብ እንድታገኙ ምድራዊው ሐብታችሁን ሽጣችሁ ለደሀ ስጡ" ሲል ነበረ(ሉቃ.12፡33)::

ኢየሱስ የሚታወቀውም ምንም ምድራዊ ሐብት የሌለው ነገር ግን በመምህርነቱ፣ በሚሰራው ተአምራት፣ በፈዋሽነቱ … በአጠቃላይ በላዩ ላይ በነበረው መንፈሳዊ ኃይልና አገልግሎት ብቻ ነበረ::

- <u>**የሙሐመድ መንገድ**</u>

ነብዩ ሙሐመድ ከላይ ካየነው ቁርአናዊ አስተምህሮ በተቃራኒ ለምድራዊ ሐብትና "ደስታ" ትልቅ አትኩሮት ሰጥቶ ሲንቀሳቀስ ነበረ፣ በዚህም ነብዩ ብዙ ሐብትን የማጋበስና ብዙ ሚስቶችን የመሰብሰብ ጉዳይ ትልቅ ፈተና ሆኖበት ነበረ፣ በዚህ ፈተናም የግል ጥቅሙን እንኳን ዘላለማዊ በሆነው የፈጣሪ ቃል ውስጥ እስከማስገባት ደርሶ ነበረ፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፣

- 8፡1 "... <u>የዘረፋ</u> ገንዘቦች የአላህና የመልክተኛው ናቸው፣ ስለዚህ አላህን ፍሩ::"
- 8፡41 "ከማንኛውም ነገር በጦር (ከከሃዲዎች) <u>የዘረፋችሁትም</u> አንድ አምስተኛ ለአላህና ለመልክተኛው ..."
- 58፡12 "እናንተ ያመናችሁ ሆይ፣ መልክተኛውን በተወያያችሁ ጊዜ ከመወያየታችሁ በፊት ምፅዋትን አስቀድሙ::"

በዚህም የሙሐመድን የሐብት ብዛት መገመት ይቻላል፣ የሚገርመው በመጀመሪያ ለሱ እንዲሰጠው በቁርአኑ በኩል ያዘዘው ሙሉውን የዘረፋ ገንዘብ ነበረ ነገር ግን በዚህ መንገድ የሚፈጠረው ሐብት እየበዛ በመሄዱና የተዋጊዎቹንም ሞራል ለመጠበቅ ሲል በመጀመርያ ያዘዘውን በመተው ቁርአኑን "አንድ አምስተኛ" በሚለው አስተካከለው::

በተመሳሳይ መንገድም ቁርአኑ 6፡51 "... ከአላህ <u>ሌላ</u> አማላጅ የለም ..." እያለ፣ ነብዩ ለገንዘብ በመሳሳት 9፡103 "ከገንዘቦቻቸው ስትሆን በርስዋ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የሆነችን ምፅዋት ያዝ <u>ለነሱም ፀልይላቸው</u>፤ ፀሎትህ ለነሱ እርካት ነውና አላህም ሰሚ አዋቂ ነው::" በማለት ቁርአኑን ለራሱ ጥቅም አስተካከለው::

በሚስቶች በኩልም እንደዚሁ ብዙ ሚስቶች ሲያሰባስብ ነበረ፣ በመጀመሪያ እስከ አራት(4፡3) ቢልም ከጊዜ በኋላ በዚህ የቁርአን ሕግ መገዛት አቅቶት እስከ አስራ አንድ ሚስቶች ያገባ ሲሆን(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡5፡268)፣ ከነዚህ በተጨማሪ ቁጥራቸው የማይታወቅ ውሽማዎች(33፡50-51) እና ባሮች(33፡52) ጋር ሲተኛ ነበረ::

በዚህም ሙሐመድ በብዙ ምድራዊ "ደስታ" እና ምድራዊ ሐብታምነት ሲኖር እንደነበረ፣ ኢየሱስ ደግሞ በተቃራኒው ሲኖር እንደነበረ እንመለከታለን፣ በዚህም የእነዚህን የሁለቱ ኃይማኖት መሪዎች ኑሮ ከላይ ካየነው ቃል ጋር ስናስተያይ፣ የኢየሱስ ህይወት በፈጣሪ መንገድ የተመራ ሲሆን፣ ሙሐመድ ግን በሐብታምነትና "በደስታ" ያሳለፈ በቅርቢቱ ህይወት "ቀረኝ" የሚለው ነገር የሌለውና የአላህ ቃል ተቃራኒ ሆኖ ያለፈ ሰው መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም አንድ ሰው ከፈጣሪ ፍርድ ለማምለጥ የየትኛውን መሪ መንገድ መከተል እንዳለበት በግልፅ እንመለከታለን::

2.3.3.3. <u>ከእውቀት አንፃር</u>

አንድ መሪ ያውም የዘላለማዊው ህይወት መንገድ መሪ፣ ተመሪውን ወዴት ይዞ እንደሚሄድ ሙሉ እውቀት ሊኖረው ይገባል፣ በዚህም መስፈርት እነዚህን ሁለቱን መሪዎች ስናነፃፅር::

ቁርአን "አላህ ኢሳን ጥበብን፣ መጽሐፍን፣ ስነፅሁፍን ... አስተማረው" ይላል(3፡48, 5፡110)፣ በዚህም ኢየሱስ በቀጥታ የአላህ ተማሪ በመሆኑ ምክንያት እውቀቱ እስከ ጥግ እንደሚሆን ግልፅ ነው::

ነገር ግን ሙሐመድ ይህን እድል አላገኘም፣ በራሱም አልተማረም(62፡2, 7፡157-158...)፣ እስራኤላዊም ባለመሆኑ ከቀደሙት ቅዱሳን መጽሐፍት አልተማረም፣ በዚህ ላይ

ደግሞ ቁርአኑ 40፡78 “ካንተ በፊት መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡ ከእነሱም ባንተ ላይ የተረክንልህ አልለ፡፡ ከእነርሱም ባንተ ላይ **ያልተረክነው አልለ**፡፡” ማለቱ ሙሐመድ የእውቀት ዕጥረት እንደሚኖርበት ግልፅ ነው፡፡

ይህንን እውነታም ብዙ ስፍራዎች ላይ ታዝበናል፣ በ2.4.3.2 ክፍል የቀረበውን የሳይንስ እውቀት ዕጥረቱን ትተን የመንፈሳዊ እውቀት ዕጥረቱን እንኳን በምሳሌ ብንመለከት፣

- <u>በዓለም ላይ ስላሉት ኃይማኖቶች በቂ እውቀት አልነበረውም</u>

ነብዩ ከክርስትናና አይሁድ እምነት ዉጪ ያሉትን ኃይማኖቶች ፈፅሞ አያውቃቸውም፣ ስለ ኃይማኖቶች ትምህርት ካስተማረ የሚያስተምረው ስለ እስልምና፣ አይሁድና ክርስትና ኃይማኖቶች ብቻ ነው፣ ከነዚህ ኃይማኖቶች ውጪ ሌላ ኃይማኖት እንዳለ አያውቅም ነበረ፣

> ሳሂህ ቡኻሪ 8፡77፡597፣ “… <u>ማንኛውም ህፃን</u> ሲወለድ እስላም ሆኖ ነው፣ ነገር ግን ወላጆቹ ወደ ይሁዲነት ወይ ወደ ክርስትና ይቀይሩታል፡፡”

በዚህም ነብዩ ሙሐመድ የኃይማኖት መሪ ሆኖ ትልቅ የኃይማኖቶች የእውቀት ክፍተት እንዳለበት እንመለከታለን፣ ቁርአን በወቅቱ ግዙፍ የነበሩትን የሂንዱይዝም፣ ሺንቶይዝምን … ኃይማኖቶችን አለማወቁ የነብዩ “ከአላህ ቁርአንን ተቀበልኩ” አባባልን ከመፈታተን አልፎ የነብዩን የእውቀት ዕጥረት ያሳብቃል፡፡

- <u>የክርስትና እውቀቱም የተምታታ ነበረ</u>

ነብዩ ክርስትናን የሚነቅፍበት አንዱ መስፈርት “ኢጋሪነት” በሚለው የሥላሴ አስተምህሮ ነው ነገር ግን ነብዩ ኢጋሪነትን(የሥላሴን ትምህርት) የተመለከተው የማርያም፣ የኢሳና የእግዚአብሔር ጥምረት አድርጎ ነበረ፣

> 5፡116 “አላህም፡- “የመርየም ልጅ ኢሳ ሆይ! አንተ ለሰዎቹ፡- እኔንና እናቴን ከአላህ ሌላ ሁለት አምላኮች አድርጋችሁ ያዙ ብለሃልን” በሚለው ጊዜ (አስታውስ)፡፡”

ይህም ክርስቲያኖች ሥላሴ የሚሉት “አብ፣ ወልድ መንፈስ ቅዱስ” የሚለውን ካለመረዳት የመጣ ስህተት ነው፡፡

- <u>ስለ ይሁዲ እምነት የነበረው እውቀት የተምታታ ነበረ</u>

ነብዩ እንደ ክርስቲያኖችም ባይሆን ይሁዲዎችንም አንዳንዴ በኢጋሪነት ይከሳቸዋል፣

> 9፡30 “አይሁድ ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው አለች …”

ሙሐመድ “ዑዘይር” የሚለው አይሁዶቹ “ዕዝራ” የሚሉትን ሰው ነው ነገር ግን በየትኛውም የአይሁድ መጽሐፍ ላይ “ዕዝራ የእግዚአብሔር ልጅ ነው” የሚል ቃል

አልተፃፈም፣ የአይሁድ መጽሐፍት “ዕዝራ” የሰው ልጅ ያውም “የአሮን ዘርና የሥራያ ልጅ”(ዕዝ.7፡1-5) መሆኑን ነው የሚነግሩን፡፡

በዚህም “አይሁድ ዕዝራ የአላህ ልጅ ነው” አሉ የሚለው ስህተት ነው፡፡

- <u>የሁለቱን መርየም(ማርያም) ታሪኮችን መቀላቀል</u>

ነብዩ ኢየሱስን በድንግልና የወለድችውን የማርያምን ታሪክ ከሞከሼዋ ከነሀሩን(አሮን) እህት ማርያም ታሪክ ጋር ተቀላቅሎበታል፣

> 19፡27 “… “መርየም ሆይ! ከባድ ነገርን በእርግጥ ሰራሽ” አሏት፡፡ “የሃሩን እህት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም፡፡ እናትሽም አመንዝራ አልነበረችም” አሏት፡፡”

የሃሩን(አሮን) እህት የሆነችው ማሪያም እና ኢየሱስን የወለደችው ማርያም ታሪኮች የተለያዩ ናቸው፣ በሁለቱ ማርያሞች መሃከል ከአንድ ሺ አመት በላይ ልዩነት አለ ነገር ግን ነብዩ የሁለቱ ሴቶች ስም ተመሳስሎበት ሁለቱን ታሪክ ቀላቅሏል፡፡

- <u>የማሪያምንና የኢጋርን ታሪክ ማቀላቀል</u>

ማርያም ኢየሱስን የወለደችበት ሁኔታ ከአጋር ኢስማኤል ታሪክ ጋር ተቀላቅሎበታል፣

> 19፡22-27 “(መርየም) ወዲያውኑ አረገዘችው፡፡ በእርሱም (በሆዷ ይዛው) ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች፡፡ ምጡም ወደ ዘንባባው አስጠጋት … ከበታቿም እንዲህ ሲል ጠራት “አትዘኚ፡፡ ጌታሽ ከበታችሽ ትንሽ ወንዝ በርግጥ አድርጓል …”

ይህ ታሪክ የሚጀምረው 19፡16 ላይ ነው፣ ሲጀምርም “በመጽሐፉ ውስጥ” በማለት ታሪኩ የተወሰደው ከመጽሐፍ ቅዱሱ እንደሆነ ይናገራል፣ ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ማርያም ኢየሱስን የወለደችው ዮሴፍና ብዙ እረኞች ባሉበት፣ በቤቴልሔም፣ በከብቶች ግርግም ውስጥ እንጂ ብቻዋን ወደ በረሀ ተሰዳ አይደለም፡፡ ህፃን ልጇን ይዛ የተሰደደችውና በበረሀ በውሀ ጥም ልትሞት ስትል ፈጣሪ የውሀ ምንጭ ያመላከታት፣ እስማኤልን ይዛ የተሰደደችውን ኢጋር(ዘፍ.21፡15-19) እንጂ ማርያም አይደለችም፡፡

- <u>የሎጥና የኖህ ዘመን ቅጣቶችን ማቀላቀል</u>

> 11፡40 “ትዕዛዝ በመጣና እቶኑ በገነፈለ ጊዜ … ልጁም ከውሀው ወደ ሚጠበቀኝ ተራራ እጠጋለሁ አለ … ማዕበሉም ከመካከላቸው ጋረደ፣ ከሰጣሚዎች ሆነ፡፡”

የእቶን እሳት ጥፋት የሆነው በሎጥ ዘመን ነው፣ የጥፋት ውሀ የሆነው ደግሞ በኖህ ዘመን፣ ነብዩ እነዚህ ሁለቱ ታሪኮች ተቀላቅለውበታል፣ በዚህ የታሪክ መቀላቀልም እርስ በርስ የሚጠፋፉት እሳትና ውሀ በመቀላቀሉ፣ ተቀጪዎቹ ምንም ቅጣት ያልወረደባቸው መሆኑ እንኳን አላስተዋለም፡፡

እነዚህን እውነታዎችም ነብዩ *ሙሐመድ* ትልቅ የእውቀት ክፍተት እንደነበረበት ያሳያሉ፣ ይህ እውነታም ነብዩ *ሙሐመድ* እምነት የሚጣልበት *መ*ንፈሳዊ *መ*ሪ አለመሆኑና የሱን አስተምህሮ ተከትሎ *መ*ሄድ የማይቻል *መ*ሆኑን ነው፡፡

2.3.3.4. <u>ገነት ለመግባት ካላቸው እርግጠኝነት አንፃር</u>

አንድ የኃይማኖት *መ*ሪ የተከተለው *መ*ንገድ ገነት እንደሚያደርሰው እርግጠኛ *መ*ሆን አለበት፣ ቁርአኑም፣ 17፡71 "ሰዎችን ሁሉ በመሪያቸው የምንጠራበትን ቀን (አስታውስ)" በማለት *መ*ሪ ግንባር ቀደም እንደሆነ ይናገራል፡፡ ቁርአን ኢየሱስ ምንም ኃጢያት ባለመስራቱ(19፡19) ገነት እንደሚገባ ይመሰክራል፣

> 3፡45 "... *መ*ርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በሆነ ቃል ስሙ አልመሲህ ኢሳ የመርየም ልጅ <u>በዚህ ዓለምና</u> **<u>በመጨረሻውም ዓለም</u>** <u>በተከበረ</u> ከባለሟሎችም በሆነ (ልጅ) ያበስርሻል፡፡"

በዚህም በመጨረሻ ቀን ኢየሱስ ፍርድ የሚጠብቅ ሳይሆን፣ 4፡159 "... (ኢሳ) በትንሳኤ ቀን በነሱ(በመጽሐፉ ሰዎች) መስካሪ ይሆናል፡፡" እንደሚለው በትንሳኤ ቀን የኢየሱስ ስራ የሚሆነው የመስካሪነት ስራ ነው፡፡ ስለ ነብዩ *ሙሐመድ* ስንመለከት ግን የነብዩ ገነት የመግባት ዕድል ላይ ብዙ አወዛጋቢ ነገሮችን እንመለከታለን፡፡ በመጀመርያ ነብዩ እንደ ማንኛውም ሰው፡-

- <u>ኃጢያት ሲሰራ ነበረ</u>
  - ቁርአን እስከ አራት ሚስት አግቡ(4፡3) የሚለውን ተላልፎ ፲ ሚስቶች ማግባቱ (ሳሂህ ቡኻሪ ፡5፡268)
  - ሚስቶቻችሁን አታበላልጡ (4፡3) እያለ ነብዩ ግን አይሻን ከሁሉም ሚስቶቹ አስበልጦ የሚወዳት *መ*ሆኑ(ሳሂህ ቡኻሪ 7፡65፡330)
  - ከላይ የተመለከትነው የነብዩ የአቅጣጫ ለውጥ፣ የማጭበርበር፣ የሸብርና የግድያ ኃጢያቶች፣
  - ከታች በ2.4.3 ክፍል የተመለከተው ነብዩ ለግል ጥቅሙ ሲል ቁርአኑን ማስተካከሉና ቁርአኑ እርስ በርሱ እንዲሁም ከእውነታ ጋር እንዲጋጭ ማድረጉ፣
- <u>አላህም *መ*ሳሳቱን ሲነገረው ነበረ</u>
  - 47፡19 "... ስለ <u>ስህተትህም</u> ... ምህረትን ለምን፡፡"
  - 4፡105-106 "እኛ በሰዎች *መ*ካከል አላህ ባሳወቀህ ልትፈርድ ወደ አንተ በርግጥ *መ*ጽሐፉን አወረድን፡፡ <u>አላህን ምህረትን ለምን</u>፡፡ አላህ *መ*ሀሪና አዛኝ ነውና፡፡"
- <u>ለስህተቱም ምህረትን ሲለምን ነበረ</u>
  ሳሂህ ቡኻሪ 8፡75፡319 "... እኔ በአንድ ቀን ውስጥ <u>70 ጊዜ አላህን ይቅርታ እጠይቃለሁ ንሰሀም እገባለሁ</u>፡፡"

ነብዩ ከአላህ ምህረትን ይለምን እንጂ

- ሳሂህ ቡኻሪ 9፡93፡473 “ሰዎችን የማይምሩትን አላህ አይምራቸውም።”
- ሳሂህ ቡኻሪ 8፡73፡26 “ሌሎችን የማይምር ምህረትን አያገኝም።”
- ሳሂህ ቡኻሪ 3፡34፡335 “በከፉ ፋንታ ከፉ አትመልሱ …”

የሚሉትን ትዕዛዛትን ተላልፎ በሽብርና በጂሀድ ብዙ ሰዎችን ማስገደሉን ስንመለከት ነብዩ ምህረት የማግኘትና ገነት የመግባት ዕድል አጠራጣሪ እንደሆነ እንመለከታለን። ነብዩም በራሱ ገነት ለመግባቱ እርግጠኛ አልነበረም፣

- ሳሂህ ቡኻሪ 8፡76፡470 “… ሰውን ስራው ከሲኦል አያድነውም … <u>እኔም እራሴ የአላህ ምህረት በኔ ላይ ካልሆነ</u> መዳን አልችልም …”
- 46፡9 “… በእኔም በእናንተም ምን እንደሚሰራ <u>አላውቅም</u>።”

<u>በዚህም ሙሐመድ በተከተለው መንገድ ገነት ይግባ አይግባ እርግጠኛ አይደለም</u> ይባሱኑ ደግሞ ነብዩ ሙሐመድ “ተአምራት አልተሰጠኝም” ቢልም ቁርአኑ ግን ተአምራት ያልያዘ <u>መሪ ነቢይ</u> እንደሌለና እውነተኛ ነቢይም ሳይገደል ወደ ሰማይ የሚነሳ መሆኑን ያመለክተናል፣

- 40፡49-50 “እነዚያም በእሳት ውስጥ ያሉት ለገሀነም ዘበኞች “ጌታችሁን ለምኑልን፤ ከእኛ ከቅጣቱ አንድን ቃል ያቃልልን” ይላሉ። (ዘበኞቹም) <u>መልእክተኞቻችሁ በተአምራቶች ይመጡላችሁ አልነበሩምን</u>” ይላሉ።”
- 19፡56 “በመጽሐፉ ኢድሪስንም(ሄኖክን) አውሳ። <u>እርሱ እውነተኛ ነቢይ ነበርና። ወደ ከፍተኛ ስፍራ አነሳነው</u>።”

ነብዩ ግን ከነዚህ ሁለቱ መስፈርቶች በተቃራኒ ተአምራት ሳይዝ “ነቢይ ነኝ” ማለቱና እንደ ኢድሪስና ኢሳ(4፡158) ወደ ሰማይ ሳይወሰድም በሰዎች ተገድሎ መቀበሩን ስንመለከት ነብዩ ሙሐመድ የገነት መሪ ነቢይ እንዳልሆነ እንመለከታለን። መሪው መግባት ካልቻለ ደግሞ ተመሪው ህዝብም የሚገባበት መንገድ የለም(17፡71)፣ በዚህም የነብዩ ሙሐመድ ተከታዮች(ሙስሊሞች) ገነት መግባት እንደማይችሉ እንረዳለን።

<u>ማጠቃለያ (የነብዩ ሙሐመድ እና የኢየሱስ ክርስቶስ መንገድ ንፅፅር)</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ሁለቱ የዓለማችን ወደር የለሽ መሪዎች ፍፁም ተቃራኒ ሆነው አግኝተናቸዋል፣ ተቃርኖውም የመጣው ሁለቱም የሚመሩት በተቃራኒ መንፈስ በመሆኑ ምክንያት ነው፣ በርግጥ ይህ ግልፅ ተቃርኖ ትክክለኛውን መሪ እንድንመርጥ ያስችለናል።

ነብዩ ሙሐመድ ከኢየሱስ ጋር ፍፁም ተቃራኒ እንደሆነው ሁሉ ከፈጣሪ ቃል ሆነ ከመሪነት ስነምግባር ጋርም ፍፁም ተቃራኒ ነው፣ በዚህም ማንም ሰው፣ ከሌላ ሰውኛ ተፅዕኖዎች ነፃ ሆኖ እውነታውን በነፃ አዕምሮ ከተመለከተ ከሙሐመድና ከኢየሱስ መንገድ የኢየሱስን የክርስትና መንገድ እንደሚመርጥ ግልፅ ነው።

ይህ እውነታ በመንፈሳዊው ብቻ ሳይሆን በስጋዊው ህይወትም የተመለከተ እውነታ ነው፣ አንድ "ኢየሱስን እከተለዋለሁ" የሚል ሰው እንደ ኢየሱስ በመልካም ባህሪ ቢኖር በሰውም በመንግሥትም ተወዳጅ ይሆናል ነገር ግን አንድ ሰው "የሙሐመድን መንገድ ጠብቄ እሄዳለሁ" ቢል ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል፣ እንደ ሙሐመድ ሰዎችን እንዲሰልሙ ቢያስገድድ፣ አልሰልም ያሉትን ቢያጭበረብር፣ ቢያሸብር፣ ቢገድል፣ ቢያስገድል፣ የጂሀድ ጦርነት ቢያውጅ፣ የአይሻ አይነት የ9 አመት ልጅ ቢያገባ፣ ፲፩ ሚስቶች ቢያገባ ... ከባድ ቅጣት ይጠብቀዋል፣ በዚህም ዛሬ ላይ ያሉት ሙስሊሞች የሙሐመድን መንገድ ሙሉ በሙሉ አይከተሉም፣ ከነዚህ ተግባራት አንዱን ልፈፅም ቢሉ የሚጠብቃቸው እስር ቤት ነው፣ ነብዩም በዚህ ዘመን ኖረው ቢሆን ኖሮ ...

በዚህም የኢየሱስ መንገድ ለስጋዊውም ሆነ ለመንፈሳዊው ህይወት ትክክለኛ መንገድ መሆኑን እና የኢሳ ተቃራኒ የሆነው የሙሐመድ መንገድ በሰማይም በምድርም የኪሳራ መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

2.4. <u>የእስልምና ቅዱሳን መጽሐፍት እና መጽሐፍ ቅዱሱ ተቃራኒ መሆናቸው</u>

እስልምና የአብርሃም ኃይማኖቶች መካከል እንደመሆኑ መጠን ከርሱ ቀድሞ ለወረዱት የአብርሃም ኃይማኖቶች መጽሐፍት ከፈጣሪ ለመውረዳቸው ዕውቅና ይሰጣል፣ ቁርአኑም በዚሁ መንገድ ከፈጣሪ እንደወረደ ይናገራል፣

> 2፡136 "በአላህና ወደ እኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስሃቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳም በተሰጡት ከነርሱ <u>በአንድም መካከል የማንለይ</u> ስንሆን አመንን፡፡"

በዚህም ቁርአኑ ከሱ በፊት የወረዱት መጽሐፍት(መጽሐፍ ቅዱስ) የፈጣሪ ቃል መሆኑን ይመሰክራል፣ በ1.4 ክፍልም እንደቀረበው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመለከተው ልዕለ ስብዕናነት የመጽሐፉ ትክክለኛ የፈጣሪ ቃልነት ያረጋግጣል፣ በዚህም የከርስትው መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ የፈጣሪ ቃል መሆኑ ምንም ጥርጣሬ የለውም፡፡

በእስልምና፣ ቁርአን ከፈጣሪ ዘንድ በቀጥታ የወረደና በፈጣሪ ጥበቃ የሚደረግለት መጽሐፍ በመሆኑ(15፡9, 6፡19 ...) ያለምንም እንከን፣ መዛነፍ፣ መጉደልና መጨመር እንደወረደ የተቀመጠ መጽሐፍ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቁርአኑን በዝርዝር ስንመለከት መጽሐፉ እንደ ሙሐመድ ነቢይነት ብዙ ችግሮች ያሉበት መጽሐፍ ነው፣ ይህም ቁርአኑ፣

- "ወረደ" የተባለበት መንገድ የተምታታ መሆኑ፣
- የተሰባሰበው በተወዛገበ መንገድ መሆኑ፣
- አምላካዊ ቃልነቱን በሚያፈርስ መልኩ መስተካከሉን፣ ከእውነታና እርስ በራሱ የሚጋጭ መሆኑን

ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፣

2.4.1. <u>ቁርአን “ወረደ” የተባለበት መንገድ የተምታታ መሆኑ</u>

ቁርአን ከፈጣሪ(ከአላህ) ዘንድ በቀጥታ በሙሐመድ ላይ እንደተወረደ ቁርአኑ በራሱ ይናገራል፣

- 26፡194 “ከአስፈራዎቹ (ነብያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)።”
- 32፡2 “የመጽሐፉ መወረድ ጥርጥር የለበትም። ከዓለማት ጌታ ነው።”
- 25፡6 “ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለን ምስጢር የሚያውቀው አወረደው።”

የዚህ ተመሳሳይ ሐሳብም በብዙ ስፍራዎች ላይ ቀርቧል 21፡2, 39፡1-2,39፡41 ...

ነገር ግን ሙሐመድ ቁርአኑን “ተቀበለ” የተባለበትን መንገድ ስንመለከት ብዙ የተምታታ ነገር እንመለከታለን፣

- አላህ ሙሐመድን አስተማረው(53፡6-18)፣
- አላህ በሙሐመድ ልቦና ላይ አወረደው(26፡194)፣
- ሙሐመድ በህልም ተቀበለ(ሳሂህ ቡኻሪ 9፡87፡111)፣
- በደወል ድምፅ ከሰማይ ይገለጥለታል(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡2)
- ገብርኤል ተገልጦ ሙሐመድን አስተማረው(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡2)

በዚህም ቁርአኑ “ወረደ” የተባለበት መንገድ የተምታታ መሆኑን እንመለከታለን።

የቁርአኑን ይዘት በዝርዝር ስንመለከት ደግሞ ቁርአን ከፈጣሪ ወይ ከገብርኤል የወረደ ሳይሆን ከ60-70% መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮቸን ኮፒ በማድረግና ከሌሎች ነገሮች ጋር በማቀናበር የተሰራ መጽሐፍ ነው፣ የተቀናበሩትም ነገሮች ነብዩ “ጅብሪል ተናገረኝ” በሚሉት የግል ፍልስፍና፣ ሰዎች ሙሐመድን የመከሩት ምክር፣ ሙሐመድ ሰዎችን የመከረው ምክር፣ ሰዎች ሙሐመድን ለሚጠይቁት ጥያቄ የተሰጡ መልሶች፣ ሙሐመድ ሰዎችን የመከረው ምክር፣ የግለሰቦች አስተያየት፣ የሙሐመድ የግል ጉዳይ፣ ፀሎት፣ መሀላ፣ ተረቶችና የመሳሰሉትን ነገሮች በአንድ ላይ በማጠራቀም ነው፣ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡-

1. <u>መጽሐፍ ቅዱሱን ኮፒ በማድረግ</u>

ሙሐመድ አዲስ አድርገው የሚተርኩት ቁርአን ከ60-70% የሚሆነው ፅሑፉ አዲስ ሐሳብ ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አስቀድሞ የተዘገበ ታሪክ ነው፣ ይህ አሰራርም የመጽሐፍ ቅዱሱን የኮፒ ራይት መብት የጣሰ አሰራር ነው።

ዛሬ ላይ ብዙ ሙስሊሞች “ነብዩ ቁርአንን ሲያወርዱ የአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍትን ስለማያውቁ ከነዚህ መጽሐፍት ኮፒ የሚያደርጉበት መንገድ አልነበረም” ቢሉም ነብዩ ሙሐመድ ግን በወቅቱ ለአይሁድ/ክርስትና አስተምህሮ እንግዳ ሰው እንዳልነበሩ ብዙ ማሳያዎች አሉ፣ የነብዩ የቅርብ ሰው የነበሩትና የመጀመርያ ባለቤታቸው የኪድጃ የአጎት ልጅ “ወረቃ” ከእስልምና መምጣት በፊት ክርስቲያን የነበሩ፣ <u>ወንጌልን በሂብሩ ቋንቋ ሲተረጉሙ የነበሩ ሰው ነበሩ</u> (ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡3)። ነብዩ ሙሐመድም፣

- 2፡136 “በአላህና ወደ እኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስሃቅም ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳም በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን፡፡”
- 5፡68 “እናንተ የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ተውራት(ኦሪት) እና ኢንጂል(ወንጌል) ከጌታችሁ ወደናንተ የተወረደውን እስከታቆሙ(እስከትሰሩባቸው) ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም፡፡”

ሲል የነበረው መጽሐፍ ቅዱሱን አስቀድሞ ያውቅ ስለነበረ ነው፡፡

ነብዩ ብዙ ስፍራዎች ላይ የአይሁድ/ክርስትና ኃይማኖትን ሲያወግዙ የነበሩትም የኃይማኖቶቹን አስተምህሮ “ተመልከተው” ነው፣ ነብዩ ሙሐመድን የመሰለ የኃይማኖት መሪ ይቅርና በወቅቱ ነብዩ አካባቢ የነበረው ተራው ህዝብ እንኳን ነብዩን “እንደ ቀደምት ነብያት ከሆነ በተአምራት ይምጣብን” ያሉት የአይሁድ/ክርስትናን ኃይማኖት ስለሚያውቁ ነበረ፡፡ እነዚህ እውነታዎችም የሚያሳዩን ነብዩ ሙሐመድ ቁርአንን ከማምጣታቸው በፊት የአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍትን ያውቁ እንደነበረ ነው፡፡

በዚህም ነብዩ አስቀድሞ በአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍት ላይ የተፃፉ ሐሳቦችን በሳቸው ላይ የወረደ አዲስ ነገር አድርገው ማቅረባቸው የመጽሐፍ ቅዱሱን የኮፒ ራይት መብትም የጣሰ አሰራር ነው፡፡

2. “ጅብሪል ተናገረኝ” በሚሉት ዘዴ

ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡546፣ አናስ እንደዘገበው፣ ነብዩ መዲና መምጣታቸውን አብዱላ ቢን ሠላማ እንደሰሙ ወደ ነብዩ መጡና፣ ከእጉ በቀር ማንም ሊመልሰው የማይችል ሦስት ጥያቄ እጠይቅሀለሁ አንደኛ ...፣ ሁለተኛ ...፣ ሦስተኛ “ለምንድነው ልጅ አባቱን እና የእናቱን ወንድም የሚመስለው፣ ነብዩም “መልሱን ጅብሪል/ገብርኤል አሁን ነገረኝ ... በግንኙነት ወቅት አባት ቀድሞ ስሜቱን ከጨረሰ የሚወለደው እሱን ይመስላል፣ እናት ቀድማ ከጨረሰች እስዋን ይመስላል ...”

ይህ ውሸት መሆኑንና የልጅ መልክ የሚወሰነው በስሜት ሳይሆን የአባትና የእናት ዘረመሎች የሚጣመሩበት መንገድ መሆኑን ስንመለከት ነብዩ የራሳቸውን ፍልስፍና “ገብርኤል ተናገረኝ” ብለው ሲናገሩ እንደነበረ እንመለከታለን፡፡

በርግጥ በ2.3.3.3 ክፍል እንደተመለከትነው የነብዩ ሙሐመድ አስተምህሮ ሁሉን ከሚያውቀው ፈጣሪ አለመሆኑ፣ በ2.3.2 ክፍል እንደተመለከትነው ነብዩ ከአይሁድ/ክርስትና ኃይማኖት የአቅጣጫ ለውጥ ማድረጋቸው እንዲሁም ከታች በ2.4.3 ስር እንደተመለከተው ቁርአኑ ለሙሐመድ ድክመት ተብሎ መከለሱ፣ ከእውነታ ጋር እንዲሁም እርስ በርስ መጋጨቱን ስንመለከት ቁርአን ከፈጣሪ የወረደ መፅሐፍ ሳይሆን የሙሐመድ የአእምሮ ውጤት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

3. ሰዎች ሙሐመድን የመከሩት ምክር

በምሳሌ ብንመለከት፣

> ሳሂህ ቡኻሪ ፡8፡395፡ ኡመር ቢን አል ካታብ እንደተረከው፡ ጌታዬ በሦስት ነገር ከኔ ጋር ተስማማ ... አንደኛው ...፣ ሁለተኛው የሴቶችን መሸፋፈን የሚመለከተውን አንቀፅ አስመልክቶ፣ ለአላህ ነቢይ "ሚስቶችህ ሰውነታቸውን ቢሸፍኑ መልካም ነው ምክንያቱም ጥሩም መጥፎም ሰው ይናገራቸዋልና" አልኩት፣ በዚህም ስለሴቶች መሸፋፈን የሚያዘው አንቀፅ ተገለጠ፡፡ ሦስተኛ የነብዩ ሚስቶች በነብዩ ላይ አንድ ሆነው በተነሱበት ጊዜ እኔም፣ "ነብዩ ሁላችሁንም ቢፈታ አላህ ከናንተ የበለጠ ሚስቶች ይሰጠዋል፡፡" አልኩዋቸው፣ በዚህ እኔ የተናገርኩት አንቀፅ ወረደ፡፡"

ተመሳሳይ ሐሳብ ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡10 ላይም ቀርቧል፡፡

እነዚህ የሰው ምክሮች የአላህ ቃል ተደርገው ቁርአኑ 33፡59 እና 66፡5 ላይ መቅረባቸው፣ ቁርአን የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን ያሳያል፡፡

4. ሰዎች ሙሐመድን ለሚጠይቁት ጥያቄ የተሰጡ መልሶች

ሰዎች ነብዩ ሙሐመድን ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ፣ ነብዩ ለሰዎቹ የሚመልሱት መልስ እንደ አላህ ቃል እንዲፃፍ ሲያዙ ነበረ፣ በዚህም መልሶቻቸው በቁርአኑ ላይ የአላህ ቃል ተደርገው እንመለከታለን፣ ለምሳሌ፣

> ሳሂህ ሙስሊም 26፡5395 "አይሻ እንተረከችው፣ ሰአዳ ልትፀዳዳ ሜዳ ወጣች፣ ከሴቶች ሁሉ ረኽርምና ጠብደል በመሆኗ ከሚያውቃት ሰው መደበቅ አትችልም፣ ዑመር ከታብ ተመለከታት "ሰአዳ፣ ኧረ በአላህ ልትደበቂ አትችይም፣ ስትወጪ ጠንቀቅ አለ"፣ ወደ ቤትም ተመለሰች፣ በወቅቱ የአላህ መልዕክተኛ እኔ ቤት እየተመገበ ነበረ፣ አጥንት በእጁ ይዞ ነበረ፣ ሰአዳም "ዑመር እንዲህ እንዲህ አለኝ" ብላ ተናገረች፣ በዚህ ጊዜ መገለጥ መጣ፣ አጥንቱን በእጁ እንደያዘ "ስትፈልጊ መውጣት ተፈቀደ" አለ፡፡"

እንደዚህ አይነት ብዙ ተመሳሳይ የቁርአን ቃል አወራረዶችን ብዙ ስፍራዎች ላይ ተመልክቷል፣

- ሳሂህ ቡኻሪ6፡60፡44 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 2፡198
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡51 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 2፡223
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡52 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 2፡232
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡209 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 11፡114
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡203 ላይ ለተጠየቀው ጥያቄ የሰጠው መልስ 11፡5

እነዚህ የሙሐመድ ምክሮች የፈጣሪ ቃል ተደርገው በቁርአኑ ላይ መፃፋቸው ቁርአን የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን ያሳያል፡፡

5. <u>ሙሐመድ ሰዎችን የመከረው ምክር</u>

በምሳሌ ብንመለከት፣

- ዘዳ11፡34 “ለናንተ ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደሆነ ምክሬ አይጠቅማችሁ።።”
- ዘዳ10፡3-5 “ጌታችሁ ያ ሰማያንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው ... ከእርሱ ፈቃድ በኋላ ... እነሆ አላህ ጌታችሁ ነውና ተገዙት፣ አትገሰፁም ... መመለሻችሁ ወደ እርሱ ነው ... እርሱ ያ ...”
- ዘዳ6፡2-3 “እርሱ ያ ከጭቃ የፈጠራችሁ ከዚያም (የሞት) ጊዜን የወሰነ ጊዜ አለ... እርሱም ያ በሰማያትና በምድር (ሊግገዙት የሚገባው) አላህ ነው... የምትሰሩትንም ሁሉ ያውቃል።።”

እነዚህን ቀጥተኛ የሙሐመድን ምክሮች በቁርአን ውስጥ መመልከቱ “ቁርአን ከፈጣሪ የወረደ ነው” የሚለውን ሐሳብ ያፈርሳል።።

6. <u>የግለሰቦች አስተያየት</u>

እነዚህ አስተያየቶች በድጋፍና በተቃውሞ የተሰጡ ሲሆኑ ከሁለቱም አይነት በአንዳንድ ምሳሌ እንመልከት፣

- በድጋፍ የተሰጠ አስተያየት
  53፡1-11 “በኮከብ እምላለሁ በወደቀ (በገባ) ጊዜ።። ነቢያችሁ ሙሐመድ አልተሳሳተም፤ አልጠመመምም።። ከልብ ወለድ አይናገርም ... ኃይሎቹ ብርቱ (መልአክ) አስተማረው።። የእውቀት ባለቤት የሆነው (አስተማረው በተፈጥሮ ቅርፁ ሆኖ በአየር ላይ) ተደላደለም።። እርሱ በላይኛው አድማስ ሆኖ።። ከዚያ ቀረበ፤ ወረደም።። ... ወደ ባሪያውም (አላህ) ያወረደውን አወረደ።። (ነብዩም በአይኑ) ያየውን በልቡ አልዋሸም።።”
- በተቃውሞ የተሰጠ አስተያየት
  21፡5 “በእውነቱ (ቁርአኑ) የሕልሞች ቅዠቶች ነው።። ይልቁንም ቀጠፈው እንዲያውም እርሱ ቅኔን ገጣሚ ነው።። ቀድሞዎቹም እንደተላኩ (መልእክተኛ ከሆነ) በተአምር ይምጣብን አሉ።።”

እነዚህ የፈጣሪ ቃላት አይደሉም።።

7. <u>የሙሐመድ መሀላ</u>

52፡1-7 “በጡር (ጋራ) እምላለሁ።። በተፃፈው መጽሐፍም።። በተዘረጋ ብራና ላይ፤ (በተፃፈው)።። በደመቀው ቤትም።። ከፍ በተደረገው ጣራም።። በተመላው ባህርም እምላለሁ።። የጌታህ ቅጣት በእርግጥ ወዳቂ ነው(የማይቀር ነው)።።”

8. <u>የሙሐመድ ፀሎት</u>

ፀሎት ከሰው ወደ ፈጣሪ የሚቀርብ ልመና እንጂ የፈጣሪ ቃል አይደለም ይሁን እንጂ ቁርአን ላይ የሰዎችን ፀሎት እንመለከታለን፣ ለምሳሌ፣

> ፣፡1-7 "... ምስጋና ለአላህ ይግባው የዓለማት ጌታ ለኾነው፤ እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው የፍርዱ ቀን ባለቤት ለኾነው፡፡ አንተን ብቻ እንገዛለን፤ አንተንም ብቻ እርዳታ እንለምናለን፡፡ ቀጥተኛውን መንገድ ምራን..."

ይህ ፀሎት የሰው ፀሎት እንጂ የፈጣሪ ቃል አይደለም፣ ይህም እውነታ የሚያሳየን ቁርአን ከሰማይ የወረደ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን ነው፡፡

9. <u>ሙሐመድ የግል ጉዳዩን የፈጣሪ ቃል አድርጎ የፃፈበት</u>

ነብዩ የራሳቸውን የግል ጉዳዮች የፈጣሪ ቃል አስመስለው ቁርአን ላይ አስገብተዋል፣ ለምሳሌ፣

- 33፡30-33 "የነብዩ ሴቶች ሆይ ... <u>ያ በልቡ ውስጥ በሽታ ያለበት እንዳይከጅል</u> በንግግር አትለስልሱ ..."
- 33፡53 "እናንተ ያመናችሁ ሆይ ... ወደ ምግብ ካልተፈቀደላችሁ በስተቀር የነብዩን ቤቶች (በምንም ጊዜ) አትግቡ ... <u>በተመገባችሁ ጊዜ ወዲያውኑ ተበተኑ</u>፡፡ ለወግ የምትጫወቱ ኾናችሁ (አትቆዩ) ... <u>ዕቃን (ለመዋስ) በጠየቃቸኋቸው ጊዜ ከመጋረጃ ኋላ ሆናችሁ ጠይቋቸው</u> ..."
- 49፡1-2 "እናንተ ያመናችሁ ሆይ ... ድመፆቻችሁን ከነብዩ ድምፅ በላይ ከፍ አታድርጉ..."

መቼም ሰማይና ምድርን የሰራው ፈጣሪ ስለ ሙሐመድ ሴቶች፣ ስለ ሙሐመድ ጓዳ፣ ሙሐመድ ጋር ስለሚመጡ ወሬኞች ለትውልድ በሚተላለፍ ቅዱስ መጽሐፉ አያወራም፣ ይህ ሙሐመድ የግል ጉዳዩን በቁርአን በኩል የተናገረበት ንግግር ነው፡፡

10. <u>ተረቶች</u>

ቁርአን "የፈጣሪ ቃል" ቢባልም በውስጡ ግን ብዙ ተረቶችን ይዟል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- <u>በነሃስ ግድብ የተገደቡ የእጁጅ መጁጅ ህዝቦች</u>

  ፣፰፡93-97 "ከዚያ (ወደ ሰሜን አቅጣጫ) መንገድን ቀጠለ፡፡ በሁለቱ ጋራዎች መካከል በደረሰ ጊዜ በአቅራቢያቸው ንግግርን ለማወቅ የማይቃረቡ ህዝቦች አገኘ፡፡ "ዙርቀርነይን ሆይ! የእጁጅና መጁጅ በምድር ላይ አበላሺዎች ናቸውና በእኛና በእነሱ መካከል ግድብን ታደርግ ዘንድ ግብርን እናደርግልህን" አሉ ... (እሱም)በጉልበት እገዙኝ፡፡ በእናንተና በእነርሱ መካከል ብርቱ ግድብ አደርጋለሁና፡፡ "የብረት ታላላቅ ቁራጮች ስጡኝ (አላቸው) ... (ብረቱን) እሳት

ባደረገው ጊዜ "የቀለጠውን ነሐስ ስጡኝ፤ በእርሱ ላይ አፈስበታለሁና" አላቸው፡፡ (የእጁድና መእጁድ) ሊወጡት አልቻሉም፡፡ ለእርሱ መሸንቆርንም አልቻሉም፡፡ "ይህ (ግድብ) የጌታዬ ችሮታ ነው፡፡"

እነዚህ የእጁድና መዕጁድ ህዝቦችና በሁለት ተራሮች መሃከል የተሰራው የነሃስ ግንብ፣ በየትኛው የምድር ክፍል ላይ ይገኛል? ከተባለ፣ መልስ የለም፣ እነሱ የሚገኙት በመሬት ላይ ሳይሆን በተረቶች ውስጥ ብቻ ነው፡፡

ይህ በፈረንጆቹም ዘንድ የታወቀ ተረት ነው፣ አሌክሳንደር ዘግሬት የተባለው ሰው በተረት ውስጥ እንደዚህ እንዳደረገ ይነገራል፣ የዚህን የአሌክሳንደር ዘግሬት የተባለው ሰው ተረት ነብዩ ሌላ ስፍራም ላይ አቀናብሮ ተጠቅሞታል፣ አሌክሳንደር ዘግሬት ንስር አሞራና ፈረስ አዳቅሎ የሚበር ፈረስ ሰርቶ በዚህ አውሬ በርሮ ገነት እንደገባ ይነገራል፣ ሙሐመድም በዚህ የተረት ፈረስ(ቡራቅ) ወደ ገነት (ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡429) እና ሩቁ መዝጊድ(17፡1) መሄዱን ተናግሯል፡፡

- <u>ፀሐይ የምትገባበት ጉድጓድ</u>

  18፡86 "ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት፡፡"

- <u>ከሰው የተለዩ ከፀሐይ መከለያ የሌላቸው ህዝቦች</u>

  18፡89-90 "ከዚያም መንገድ ወደ ምስራቅ ቀጠለ፣ <u>ወደ ፀሐይ **መውጫ** በደረሰ ጊዜ</u> ለእነሱ ከበታቸዋ መከለያን ባላደረግንላቸው ሕዝቦች ላይ ስትወጣ አገኘናት፡፡"

እነዚህ ፀሐይ የምትወጣበት ጉድጓድ አጠገብ ያሉ መከለያ የሌላቸው ህዝቦች የትኞቹ ህዝቦች/ሀገር እንደሆኑ ብናውቅ ጥሩ ነበረ፡፡

- <u>ነሐስ የሚፈልቅበት ምንጭ</u>

  34፡12 "... (ለሱሌይማን) የነሐስንም ምንጭ ለእርሱ አፈሰስንለት፡፡"

ምንጩ የሱሌይማን ሀገር በሆነችው እስራኤል የት እንደሚገኝ ቢጠቁሙን መልካም ነበረ፣ ምንጩ ደርቆ ቢሆን እንኳን ቢያንስ ዛሬ ቅሪቱ ይገኝ ነበረ፡፡

- <u>ሰንበትን ስላላከበሩ ዝንጀሮ የተደረጉ ሰዎች፡-</u>

  7፡163-166 "ከእርሱም ከተከለከሉት ነገር(ሰንበትን እንዳይሰሩ) በኮሩ ጊዜ ለእነሱ "ወረዶች ዝንጀሮች ሁኑ አልን፤" (ኾኑም)፡፡"

ሰንበትን የማያከብሩትን እንደዚህ ይሆናሉ ከሆነ ሙስሊሙን ማኅበረሰብ ጨምሮ ሰንበትን የማያከብር ህዝብ ጉድ በሆነ ነበረ፡፡

- <u>ጉንዳኖች ሰዎችን በስም ያውቃሉ ወቅታዊውን ፖለቲካም ይከታተላሉ</u>

  27፡18 “(እነ ሱለይማን) በጉንዳንም ሸለቆ በመጡ ጊዜ አንዲት ጉንዳን፡- እናንተ ጉንዳኖች ሆይ! ወደ መኖሪያችሁ ግቡ፤ ሱለይማንና ሰራዊቱ እነርሱ የማያውቁ ሲሆኑ አይሰባብሩአችሁም አለች፡፡”

እዚህ ጋር ሱለይማን(ሰሎሞን) በተሰጠው ጥበብ የበራሪን ቋንቋ ያውቃል ተብሏል(27፡16)፣ ታዲያ ጉንዳንዋስ ሱለይማንን የሚባል ሰው መኖሩን፣ ሱለይማንን ከሰው መለየትን፣ ሱለይማን ወታደሮች እንዳሉት፣ የሱለይማን ወታደሮች በዚያ እንደሚያልፉ የዘመቻቸውን ፕሮግራም … እውቀቶችን ከየት አገኘች? ይህ ስህተት የመጣው “የሱለይማን ጥበብ ወሰን የለውም” ብሎ አስፍቶ ከማሰብ የስፋቱ ብዛት ጉንዳንዋም ስላጠቃለለ እንጂ የጉንዳን ሰሎሞን ወይ የጉንዳን ነብይ ኖሮ አይደለም፡፡

በወቅቱ የነበሩት ህዝቦችም ይህንን የሙሐመድን ተረት ተረት ተገንዝበው፣ ቁርአኑ 25፡5 “አሉም “የመጀመሪያ ሰዎች ተረቶች ናት፣ አስፃፋትም፣ እርሷም በእርሱ ላይ ጧትና ማታ ትነበብለታለች፡፡” ብለው ነበረ፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ቁርአኑ ከፈጣሪ ቃልነት ይልቅ በሰሚ ሰሚ ከመጽሐፍ ቅዱሱ የተቀዱ እውቀቶች፣ ነብዩ “ገብርኤል ተናገረኝ” በሚሉት ውሸት፣ የሰዎችና የሙሐመድ ምክሮች፣ የሰዎች አስተያየቶች፣ የሙሐመድ የግል ጉዳዮች፣ ፀሎት፣ መሀላ፣ ተረቶች … ጥርቅም መሆኑን እንመለከታለን፡፡ በዚህም ቁርአንና ፈጣሪን የሚያገናኛቸው ነገር እንደሌለና ቁርአኑ የሙሐመድ የአዕምሮ ስራ ብቻ መሆኑን በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል፡፡

2.4.2. <u>ቁርአኑ የተሰባሰበው በተወዛገበ መንገድ መሆኑ</u>

በእስልምና ቁርአን ከፈጣሪ በቀጥታ የወረደ፣ በፈጣሪ ጥበቃ የሚደረግለትና እንደወረደ በሰው ምንም ሳይነካካ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ያለ ቅዱስ መጽሐፍ ተደርጎ ይታመን እንጂ ታሪኩን ስንመለከተው እውነታው ሌላ ነው፡፡

ከመነሻው ብንመለከት፣ ነብዩ ሙሐመድ ባለመማሩ(7፡158) ምክንያት ቁርአኑን አልፃፈውም፣ በዚህም የተወሰኑ የቁርአን ክፍሎችን በተማሩት ሰዎች(25፡5) በፓፒረስ ቅጠልና በቀጫጭን ነጭ ድንጋዮች(ሳሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509) ላይ አፃፈ ሌሎቹን ክፍሎች ደግሞ ሰዎች በሸምደዳ እንዲይዙ አደረገ(ሳሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509)፡፡

ቁርአኑም በእንዲህ ሁኔታ እያለ ነብዩ ተገደሉ፣ ከዚያም ተከታዮቻቸው ኃይማኖቱን በጂሀድ ማስፋፋት ቀጠሉ ይሁን እንጂ በአሰቃቂው የያማማ ጦርነት ብዙ ቁርአንን በቃላቸው የያዙት ሰዎች በማለቃቸው ምክንያት በቃል የተያዘው የቁርአን ክፍል ፈፅሞውኑ እንዳይጠፋ፣ በአዕምሮ የተያዘው የቁርአኑ ክፍል ቶሎ በፅሁፍ እንዲቀመጥ የኃይማኖቱ መሪዎች መከሩ፣ በዚህም አቡ በከር አስ-ሲዲቅ ለዛይድ ቢን ታቢት ቁርአኑን በአንድ መጽሐፍ እንዲያሰባስቡ አዘዙዋቸው(ሳሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509)፡፡

ዛይድ ቢን ታቢት ግን ይህንን ተልዕኮ መፈፀም እንደማይችሉና "የአላህ ነቢይ ያልሰሩትን እንዴት ችለህ ትሰራለህ ... ቁርአን በአንድ መጽሐፍ አሰባስብ ከምትለኝ <u>አንድን ተራራ ነቅለህ ስፍራውን ቀይረው ብትለኝ ይቀለኛል</u>" በማለት የተሰጣቸውን ግዳጅ ቢቃወሙም ስራው የግዴታ ስለነበረ ቁርአኑን የማሰባሰብ ስራ ጀመሩ(ሳሂህ ቡኻሪ 6፡61፡509)፡፡ በዚህ ሁኔታ ውስጥ የተጀመረው ስራ በብዙ ጉድለቶች ውስጥ ቀጠለ፣ ጉድለቶቹም፡-

- ነብዩ ግልፅ ያላደረገው የቁርአን ክፍል መኖሩ፣
  አቡ ዳውድ ሱና፡787 "... የአላህ መልዕክተኛ ከኛ ጋር ተወስዷል፣ ይሄ ክፍል የዚያ አካል መሆኑን ግልፅ አላደረጉልንም፡፡"
- ነብዩ "የተቀበሉትን" ሙሉ በሙሉ ለመያዝ ሲቸገሩ የነበረ መሆኑ፣
  ነብዩ ቁርአኑን ሙሉ በሙሉ በቃል መያዝ እንዳቃታቸው ሲናገሩ ነበረ (ከታች በ2.4.3.3/25 እና በ2.4.3.3/26 ክፍል በስፋት ቀርቧል)፣ ይህም እውነታ ነብዩ የወረደላቸውን ቁርአን ሙሉ በሙሉ ማስተላለፍ እንዳልቻሉና በዚህም ሳይተላለፉ የቀሩ የቁርአን ሐሳቦች እንዳሉ እንመለከታለን፡፡
- ነብዩ ካወረዱት ውስጥ የጠፋ የቁርአን ክፍል መኖሩ፣
  ሳሂህ ቡኻሪ 6፡61፡510፣ ኡትማንም ለሃፍሳ(ለነብዩ ሚስት) "ቁርአኑን በመጽሐፍ እየሰራን ስለሆነ፣ አንቺ ጋር ያሉትን የቁርአን ፅሁፎችን ላኪልን" ሲላትና እስዋም ያገኘችውን ስትልክለት ጉዳት የደረሰባቸው የፓፒረስ ቅጠሎች መኖራቸውን ተናግራለች፣ [30] በፓፒረስ ላይ የተፃፈን ቁርአን፣ በነብዩ ሞት ሀዘን ወቅት ፍየል ቤት ገብታ የፓፒረሱን ቅጠል በመብላትዋ የተወሰኑ የቁርአን ክፍሎች ጠፍቷል በማለት ተናግራ ነበረ (የኢብን ማጃህ ሱናን 3፡1944)፡፡
- ሰብሳቢዎቹ መካከል አለመግባባት የነበረ መሆኑን፣
  - አቡ ዳውድ ሱና 786፡ ያዚድ አል ፋሪሲ እንደዘገበው፣ ኢብን አባስ ሲናገር እንደሰማሁት "አትማን ቢን አፋንን ጠየኩት "ለምንድነው የአል-ተውባህና የአል-አንፋልን ክፍሎች ወደ "ረኅሾሞቹ ሰባቱ ምዕራፎች" በመካከላቸው "ቢስሚላሂ ራህማኒ ረሂም" ሳትፅፍ የቀላቀልከው" አሉት፣ ኡትማንም "... ይዘቱን ሳየው ... የዚህ አካል ነው ብዬ ስለገመትኩኝ ነው..." ሲል እንመለከታለን፤ ይህ ንትርክም በጃሚ አት ቲረሚዝ 5፡3086 ላይም ተመልክቷል፡፡
  - ሳሂህ ቡኻሪ 6፡61፡510፣ ውስጥ እንደተመለከተው ቁርአኑ በአንድ ሲሰባሰብ፣ "ኡስማንም ለሦስቱ ቁረይሻዊ ሰዎች "ምናልባትም ከዛይድ ቢን ታቢት ጋር በአንዳች ባትስማሙ ቁርአን በቁረይሽ ዘዬ ስለወረደ ዝም ብላችሁ በቁረይሽ አነጋገር ፃፉት፡፡" ሲል እንመለከታለን፡፡

[30] ሳሂህ ኢማን(2007)፣ **ድብቁ እውነት ሲገለጥ**፣ ሦስተኛ እትም፣ ገፅ 30

በነዚህ ችግሮች ውስጥም ቁርአኑ ተፅፎ ካለቀ በኋላ በወቅቱ የነበረው ከሊፋ ኡስማን፣ አንድ አይነት ቁርአን ብቻ እንዲኖር በማሰብ ቁርአኑ በመጀመርያ የተፃፉበትን የፓፒረስ ቅጠሎች፣ ድንጋዮች … እና ሌሎቹ አይነት ቁርአኖች በሙሉ ሰብስቦ አቃጠለ(ሳሂህ ቡኻሪ 6፡61፡510)፣ የሚገርመው ግን ከሊፋው እንዳሰበው ሳይሆን በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ የቁርአን ኮፒዊች ይገኛሉ፣ [31]"ከከሊፋ ኡስማን ሞት በኋላ ቁርአን የተለያዩ ቅጂዎች እንዳሉት በታሪክ መዛግብት ተመልክቷል፣ በዚህ ዘመን አራት ቅጆዎች እንዳሉት ይነገራል፣ እኔ ሦስቱን ማግኘት ችያለሁ … አራቱ ቅጂዎችም፣ የዋርሽ ቁርአን፣ የቃሉን ቁርአን፣ የአል ዱሪ ቁርአን፣ የሃፍስ ቁርአን፣ ሲሆኑ በመካከልቸውም ብዙ ልዩነት አላቸው።።"

ከላይ በተመለከቱት ቁርአንን የማሰባሰብ ችግሮች ምክንያት ዛሬ አብዛኛው ሙስሊም የሚጠቀመዉ ቁርአን ላይ ብዙ ችግሮች ተፈጥረውበታል፣ ይህም፣

ቁርአኑን ነብዩ ሙሐመድ በሚያውቁበት መንገድ ማስቀመጥ አልተቻለም፣ የቁርአኑ ምዕራፎቹ የተቀመጡት በአወራረዳቸው ቅደም ተከተል ሳይሆን በርዝመታቸውና እጥረታቸው ቅደም ተከተል ነው፣ ከመግቢያው ምዕራፍ "አል ፋቲሃ" በስተቀር ሌሎቹ ከሞላ ጎደል የቀረቡት በምዕራፎቻቸው እርዝማኔ እንጂ በተወረዱበት ቅደም ተከተል አይደለም፣ ለምሳሌ አል ተውባህ የወረደው በመጨረሻው ላይ ነው(አቡ ዳውድ ሱና 785) ነገር ግን ቁርአኑ ላይ የምናየው በዘጠነኛው ምዕራፍ ላይ ነው።።

በመቀጠል ቁርአኑን የስነፅሁፍ ስነምባር የጎደለው መጽሐፍ እንዲሆን አድርጎታል፣ እነዚህም ችግሮች የክሮኖሎጂ(የጊዜ ቅደም ተከተልነት) ችግር፣ አሰልቺ ድግግሞሽ፣ ግራ መጋባት፣ ታሪኮች መቀላቀል፣ ያልተዘገቡ ታሪኮችና የተቆረጡ ታሪኮችን እንመለከትበታለን፣

- <u>የክሮኖሎጂ ችግር(የጊዜ ቅደም ተከተልነት)</u>
  በቁርአኑ ምዕራፎች ውስጥ የምንመለከተው ታሪክ የጊዜ ፍሰት ጠብቆ የተፃፈ አይደለም፣ ይህንን ለመረዳት ክሮኖሎጂውን ጠብቆ የተፃፈ መጽሐፍ ለምሳሌ መጽሐፍ ቅዱሱን ብንለከት ሲጀምር "በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ" በማለት ከመጀመሪያው ሲጀምር፣ በመካከሉም የቀረቡት ታሪኮች የከስተታቸውን ጊዜ ጠብቀው የተፃፉ ሲሆን፣ ሲጨርስም "በመጨረሻ" በማለት የቁሳዊው ዓለም መጨረሻ እንዴት እንደሚሆን በማሳየት ይቋጫል፣ ቁርአኑን ስንመለከት ግን እንደዚህ ከመጀመሪያው ታሪክ አይነሳም፣ አጨራረሱም መጨረሻ ባልሆነ መልኩ ነው የሚጠናቀቀው።።
- <u>አሰልቺ ድግግሞሽ</u>
  በምሳሌ ብንመለከት ፈርኦንና ሙሴ ስለ <u>እስራኤል ህዝብ መለቀቅ</u> የተነጋገሩት ንግግር ብቻ በተመሳሳይ ቃላት ከ23 በላይ ስፍራዎች ላይ ተደጋግሟል፣ 2፡5-51,

[31] ሳሂህ ኢማን(2007)፣ **ድብቁ እውነት ሲገለጥ**፣ ሦስተኛ እትም፣ ገፅ 19-22

7፡127, 8፡54, 10፡75, 11፡96, 14፡6, 17፡101, 20፡49, 20፡77-78, 23፡45-48, 26፡16-53, 27፡12, 28፡3, 29፡39, 40፡23-24, 40፡37, 43፡46, 44፡17, 51፡38, 69፡9, 73፡16, 79፡15-17, 85፡18 ... የሚገርመው ደግሞ እንደዚህ በመደጋገሙ ውስጥ አንድ ተጨማሪ አዲስ ነገር አናገኝበትም፣ ሁሉም አጠር አጠር ተደርገው በተመሳሳይ ቃላት የተደጋገሙ ተመሳሳይ ታሪኮች ናቸው፣ ይህ ችግርም የቁርአንን ንባብ አሰልቺ አድርጎታል።

- <u>ግራ መጋባት</u>

  ግራ የተጋቡ አንቀፆች ለምሳሌ ያህል ብንመለከት፡-

  - 49፡14 "የዓረብ ዘላኖች "አምነናል" አሉ። "<u>አላመናችሁም፤ ግን ሰልመናል በሉ</u>። "እምነቱ በልቦቻችሁ ውስጥ ገና (ጠልቆ) አልገባም።"
    "የሰለመ" ማለት "ያላመነ" ማለት ነው እንዴ?
  - 57፡27 "... (ኢየሱስን) በተከተሉት (ሰዎች) ልቦች ውስጥ መለዘብንና እዝነትን፣ አዲስ የፈጠሩትን ምንኩስና <u>**አደረግን**</u>። <u>በእነርሱ ላይ ምንኩስና አልፃፍናትም</u>። <u>ግን የአላህን ውዴታ ለመፈፀም ፈጠሩዋት</u>።"
    የፈጠሩትን "አደረግን" ይላል ተመልሶ ደግሞ "አልፃፍናትም" ይላል
  - የአላህ አሸናፊነትና ጥበበኝነት እንዴት ይገለፃሉ?
    5፡38 "ሰራቂውንና ሰራቂቱንም በሰሩት ነገር ለቅጣት ከአላህ የሆነ መቀጣጫ እጆቻቸውን ቁረጡ። አላህም <u>አሸናፊ ጥበበኛ</u> ነው።"
  - 29፡61 "ሰማያትን ምድርን የፈጠረ ፀሐይና ጨረቃን የገራ ማን እንደሆነ በርግጥ ብትጠይቃቸው በርግጥ <u>አላህ ነው ይሉሃል</u>። <u>ታዲያ እንዴት ይመለሳሉ</u>።"
  - 23፡84-90 "... የሰባቱ ሰማያት ጌታና የአርሹ ባለቤት ማን ነው በላቸው፣ <u>በርግጥ የአላህ ነው ይሉሃል</u> ... ይልቁንም እውነት አመጣንላቸው። እነርሱም (በመካዳቸው) <u>ውሸታሞች</u> ናቸው።"
  - ተራራውን ነቅሎ ከበላያቸው ያስኬድ ነበረ
    2፡93 "የጡርን ጋራ ከበላያችሁ ያነሳን ስንኾን(በኦሪት ሕግ እንድትሰሩ) ኪዳናችሁን በያዝን ጊዜ (አስታውሱ)። "የሰጠናችሁን በኃይል ያዙ ስሙም" (አልን)። ሰማንም አመፅንም አሉ።"
    ነገር ግን እኚህ ሰዎች አምፀዋል፣ ተራራውን ያነሳው ለወከባ ነበር እንዴ?
  - አብረው የማይሄዱ ሐሳቦች
    44፡25-30 "(እስራኤሎች ከግብፅ ሲወጡ) ከአተክልቶችና ከምንጮች ብዙ ነገሮችን ተው። ከአዝመራዎችም ከመልካም መቀመጫዎችም። <u>በርስዋ ተደሳቾች ከነበሩባት ድሎት (ብዙ ነገር ተው)</u> ... የእስራኤልንም ልጆች <u>አዋራጅ ከሆነ ስቃይ</u> በእርግጥ አዳንናቸው።"

- ከሰው ልጅ *መሳሳትና* ከምድር *መፈጠር* የቱ ይቀድማል? በአላህ ስም ለማስፈራራት ካልሆነ በቀር?
  50፡7 “ምድርን ዘረጋናት፡፡ በርስዋም ውስጥ *ጋራዎችን* ጣልንባት፡፡ በውስጥዋም ከሚያስደስት አይነት ሁሉ አበቀልን፡፡ (ይህንን ያደረግነው) <u>ተመላሽ</u> ለኾነ ባሪያ ሁሉ ለማሳየትና ለማስገንዘብ ነው፡፡”
- 5፡64 “አይሁዶች የአላህ እጅ የታሰረች ናት አሉ፡፡ እጆቻቸው ይታሰሩ…”
  አይሁዶች ዓለምን እንደዚህ ማሽከርከራቸው እጆቻቸው በደንብ ሳይታሰር ቀርቶ ይሆን?

- <u>ያልተዘገቡ ታሪኮች</u>

  የነብዩ ቁርአኑን በቃል *መያዝ* አለመቻል፣ ያልተናገሩት ክፍል *መኖር*ና ተናግረው የጠፉ ክፍሎች *መኖር* ምክንያት *መሠረታዊ* ነገሮች በቁርአን ላይ ሳይዘገቡ ቀርተዋል፡፡

  ለምሳሌ *ሀዲስ* ላይ የምንመለከተው ደጃል የተባለው ሰው *ታሪክ*፣ ኢብራሂም ሊሰዋው የነበረው የትኛውን ልጅ እንደሆነ (ኢስማኤልና ኢስሀቅ *መካከል* ሰፊ *መንፈሳዊ* ትርጉም አለና)፣ የአዳም ሚስት ስም፣ *ሙስለሊሞች* ከቁርአኑ እኩል ስልጣን ያለው *ሀዲስ* የተባለ የ*ሙስሊም መመ*ርያ *መጽሐፍ* ይኑር አይኑር … የ*መሳሰሉ መሠረታዊ* ነገሮች ቁርአኑ ላይ ሳይዘገቡ ቀርተዋል፡፡

- <u>የታሪኮች መቆረጥ፣</u>

  ለምሳሌ፣ አንድ “አቡ ለሐብ” የሚባል ሰው *ታሪክ* ምዕራፍ ፩፩ ላይ እናገኛለን፣ የዚህ ሰው *ታሪክ* የተፃፈው በዚህ ምዕራፍ ላይ ብቻ ሲሆን፣ ምዕራፉ አጭር በመሆኑ *ሙሉ* ምዕራፉን እንመልከት፣

  ፩፩፡1-5 “የአቡ ለሐብ ሁለት እጆች ከሰሩ(ጠፉ እርሱ) ከሰረም፡፡ ከእርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም፡፡ የ*መንቀልቀል* ባለቤት የሆነች እሳት በእርግጥ ይገባል፡፡ ሚስቱም (ትገባለች)፤ እንጨት ተሸካሚ ስትሆን፡፡ በአንገትዋ ላይ ከጭረት የኾነ ገመድ ያለባት ስትኾን፡፡”

  እዚህ *ጋ*ር የምንመለከተው የተቆረጠ *ታሪክ* ነው፣ አቡ ለሐብ የተባለው ግለሰብ እዚህ *ጋ*ር የተጠቀሰው ጥፋት በ*ማጥፋቱ* እንደሆነ ይገባናል ነገር ግን እዚህ *ጋ*ር ሰዎች እንዲ*ማሩ* የተፈለገው ዋናው ነጥብ፣ የዚህ ሰው ጥፋት ምን እንደሆነ አልተጠቀሰም፣ በዚህ ሊተላለፍ የተፈለገው ዋናው *ሐሳብ* ተቆርጦ ቀርቷል፡፡

- <u>የታሪኮች *መቀላቀል*፣</u>

  ቁርአን *መጽሐፍ* ቅዱሱን ቢቀበልም አንዳንድ ስፍራዎች ላይ ከ*መጽሐፍ* ቅዱሱ የተወሰዱ *ታሪኮች* ከሌሎች *ታሪኮች* *ጋ*ር ተቀላቅለዋል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- 38፡48 “ኢስማዒልን፣ <u>አልየሰዕንም፣ ዙልኪፍንም</u> አውሳ፡፡”
- 40፡23-24 “*ሙሳን* … ወደ ፈርአን <u>ወደ ሃማን፣ ወደ ቃሩንም</u> ላክነው፡፡”
- 50፡12-14 “ከእነርሱ በፊት የኑህ(ኖህ) ህዝቦችና <u>የረሰስ ሰዎች፤ ሰሙድም</u> አስተባበሉ፡፡ <u>ዓድም</u> ፈርዖንም፤ የሉጥ(ሎጥ) ወንድሞችም፤ <u>የአይከት ሰዎችም የቱበበዕ ህዝቦችም</u> ሁሉ መልክተኞቹን ሁሉ አስተባበሉ፡፡ ዛቻዬም ተረጋገጠባቸው፡፡”

እነዚህ ከታወቂ የመጽሐፍ ቅዱሱ ፃድቃን ስሞች ጋር የገቡት አልየሰዕ፣ ዙልኪፍ፣ ሃማን፣ ቃሩን፣ ሰሙድ፣ ዓድ፣ የረሰስ ሰዎች፣ የአይከት ሰዎች፣ የቱበበዕ ህዝቦች የሚባሉት ታሪኮች በአይሁድ/እስራኤል መጽሐፍት ላይ የሉም፣ እነዚህ ታሪኮች የተቀላቀሉት ከሌላ በታ ነው፣ በዚህም ቁርአኑ ላይ የታሪክ መቀላቀል ተፈጥሮበታል፡፡

እነዚህ ከላይ የተመለከቱት፣ ነብዩ ግልፅ ያላደረገው የቁርአን ክፍል መኖሩ፣ ነብዩ ቁርአኑን እየረሳ መቸገሩ፣ ተፅፈው የጠፉ የቁርአን ክፍል መኖሩ፣ ሰብሳቢዎቹ ያልተግባቡባቸው የቁርአን ክፍሎች መኖሩ፣ ቁርአንን ነብዩ ባስተማሩት ቅደም ተከተል ማስቀመጥ አለመቻሉ፣ ክሮኖሎጂውን ጠብቆ ማስቀመጥ አለመቻሉ፣ አሰልቺ ድግግሞሽ መፈጠሩ፣ ግራ የመጋባት፣ ታሪኮችን ያለመዘገብ፣ የመቆራረጥና የታሪክ መቀላቀል ችግሮችን በአንድ ላይ ስንመለከት “ቁርአን ከፈጣሪ በቀጥታ የወረደና በፈጣሪ ጥበቃ የሚደረግለትና እንደወረደ የሚገኝ ቅዱስ መጽሐፍ ነው” የሚባለው አባባል ስህተት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

2.4.3. <u>አምላካዊ ቃልነቱን በሚያፈርስ መልኩ መስተካከሉ፣ ከእውነታና እርስ በራሱ መጋጨቱ</u>

ፈጣሪ ሁሉን አዋቂ በመሆኑ በሌላ ጊዜ ሌላ እውቀት ተገልጦለት የተናገረውን አይቀይርም፣ ቃሉም አይምታታበትምም አይዋሸምም ነገር ግን ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን በሚያሳይ መልኩ ለሙሐመድ ስንፍና ሲከለስ፣ እርስ በርስ እንዲሁም ከእውነታ ጋር ሲጋጭ እንመለከታለን፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፣

2.4.3.1. <u>ለሙሐመድ ስንፍናና ጥቅም ተብሎ በየጊዜው መከለሱ</u>

ነብዩ በመጀመርያ “የአላህ ቃል ነው” ብሎ ያስተማራቸውን አንዳንድ ትዕዛዞችን፣ በተለይ ከሴት ጋር በተያያዘ ያወረደው ቃል፣ ለራሱም መፈፀም ከብዶት ነበረ፡፡ ይህ የሆነውም ነብዩ ከነበረበት ሐብት፣ ዝና፣ ስልጣን … ከፍ እያለ ሲመጣ በብዙ አማራጮች በመከበቡ ምክንያት ነው ነገር ግን ለነብዩ ምን ችግር አለው በምትኩ ሌላ ቃል አወረደ፣

በመጀመሪያ 4፡3 “… ከሴቶች ለናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት ሦስት ሦስት አራት አራትም አግቡ፣ <u>አለማስተከከልን ብትፈሩ</u> አንዲትን ብቻ ወይንም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን ያዙ” አለ፡፡ ነብዩ ይህንን “አለማስተካከል ብትፈሩ” የሚለውን ሕግ በመተላለፍ

አይሻን ከሚስቶቹ ሁሉ አስበልጦ ስለሚወዳት(ሳሂህ ቡኻሪ 7፡65፡330) ቁርአኑን መልሶ አስተካክለው፣

> 33፡51 "ከእነርሱ የምትሻትን ታቆያለህ፡፡ የምትሻትን ወዳንተ ታስጠጋለህ፡፡ (በመፍታት) ካራቅሃትም የፈለግሃትን (በመመለስ ብታስጠጋ) <u>በአንተ ላይ ኃጢያት የለብህም</u>፡፡"

በመቀጠል ይህንን እስከ አራት የሚፈቅደውን ተላልፎ ሚስቶቹን ወደ ዘጠኝ(ሳሂህ ቡኻሪ 7፡62፡69) ከዚያም ወደ ፲፩ አሳደገ(ሳሂህ ቡኻሪ ፡5፡268) ነገር ግን ይህ ድርጊቱ "ኃጢያት" እንዳይሆንበት ይህን ስንፍናውን ሽፋን የሚሰጠውና ከዚህ በላይ ገደብ ማለፍ እንደሌለበት የሚገልፅለትን ሌላ ቃል አወረደ፣

> 33፡52 "ከእነዚህ በኋላ እጅህ ከጨበጠቻቸው(ባሮች) <u>በስተቀር</u> ሴቶች ላንተ አይፈቀዱልህም፡፡ ከሚስቶችም መልካቸው ቢደንቅህም እንኳ እነርሱ ልታላውጥ (አይፈቀድልህም)፡፡"

የሚመጣው ስለማይታወቅም ነብዩ በሚስት ብዛት በቁጥር እንዳይገደብ ሌላም መከራከርያ ቃል አውርዷል፣

> 33፡50 "... የአመነች ሴት ነፍሷን(ራሷን) ለነብዩ ብትሰጥ ነብዩ ሊያገባት የፈለገ እንደሆነ <u>ከምዕመናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትሆን (ፈቀድንልህ)</u>፡፡

የሚገርመው ደግሞ "ማንም የጣለውን ሲያነሱበት አይወድም" እንደሚባለው አባባል ነብዩ ይህንን ሁሉ ሚስት ይዞ፣

> 33፡53 "... ሚስቶቹንም ከእርሱ በኋላ <u>ምን ጊዜም</u> ልታገቡ ለእናንተ አይገባችሁም፡፡ ይህ አላህ ዘንድ ከባድ ኃጢያት ነው፡፡"

በማለት እሱ የፈታቸውን ሌሎች ሰዎች እንዳያገቧቸው ሲከለክል እንመለከተዋለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በማኅበረሰቡ የሚወዛወዙትን ነገሮች ለሁሉም መፍቀድ ሲያቅተው ለራሱ ብቻ ለይቶ ቃል ሲያወርድ እንመለከተዋለን፣

> 33፡50 "አንተ ነብዩ ሆይ እኛ እነዚያን ... የአጎትህን ሴቶች ልጆች፣ የአክስቶችንም ሴቶች ልጆች፣ የየውሽማህን ሴቶች ልጆች፣ የየሹሜህንም ሴቶች ልጆች (ማግባት) <u>ላንተ ፈቅደንልሀል</u>፡፡ የአመነች ሴት ነፍሷን(ራሷን) ለነብዩ ብትሰጥ ነብዩ ሊያገባት የፈለገ እንደሆነ <u>ከምዕመናን ሌላ ላንተ ብቻ የጠራች ስትሆን (ፈቀድንልህ)</u>፡፡

ነብዩ ቁርአኑን በየጊዜው እንደዚህ ማስተካከሉ ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል ሳይሆን የሙሐመድ የአዕምሮ ውጤት መሆኑን ያሳያል፣ በወቅቱ የነበሩት ሰዎችም ሙሐመድን "አንተ ... በርግጥ እብድ ነህ" (37፡36, 44፡14, 15፡6) ሲሉት ነበረ፡፡

2.4.3.2. ከእውነታ ጋር መጋጨቱ

ፈጣሪ ሁሉን አዋቂና ቅዱስ በመሆኑ አይዋሸም፣ በዚህም ዘመን ተሻጋሪ እውነታን ይናገራል ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ "የፈጣሪ ቃል ነው" በተባለው ቁርአን ውስጥ ብዙ ውሸቶችን እንመለከታለን፣ ቀጥሎ ቀርቧል፣

1. **"ፀሐይ የምትገባበት ጉድጓድ"**

ፀሐይ ጠዋት ላይ ከመሬት ውስጥ የምትወጣና ማታ ደግሞ መሬት ውስጥ የምትገባ ስለምትመስል፣ ቁርአኑ ፀሐይ ስለምትገባበት ጉድጓድ ያስተምረናል፣

> 18፡85-93 "መንገድን (ወደ ምዕራብ) ተከተለ። ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት።"

2. **"ፀሐይ ገብታ ትተኛለች፣ እንድትበራ የምትነሳውም ተቀስቅሳ ነው"**

እዚህ ጋር ደግሞ ፀሐይ ጉድጉዋዷ ውስጥ እንደምትገባ ብቻ ሳይሆን ገብታም እንደምትተኛና ተቀስቅሳ እድነደምትነሳ እንማራለን፤

- ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡421 አቡ ዳር እንደተረከው፡ ነብዩ በፀሐይ መጥለቂያ ጊዜ "ፀሐይ የት እንደምትጠልቅ ታውቃለህ" አለኝ እኔም "ይህን በደንብ የሚያውቁት አላህና ነብዩ ናቸው" አልኩት፣ እሱም "የአላህ ዙፋን ስር ገብታ እስክትተኛ ትሄዳለች፣ ከዚያም እንደገና ለመውጣት ፍቃድ ትቀበላለች፣ ነገር ግን ተመልሳ መተኛት ትፈልጋለች ግን ትከለከላለች፣ በመጣችበት መንገድ መመለስም ትፈልጋለች ነገር ግን ትከለከላለች፣ በዚህም በተወሰነላት መንገድ ብቻ እንድትሄድ የአላህ ትዕዛዝ ነው፤" አለኝ።"
- ሳሂህ ሙስሊም 1፡297 አቡ ዳር እንደተረከው፡ "... የአላህ ዙፋን ስር ገብታ እስክትተኛ ትሄዳለች፣ ከዚያ ተነሺና ወደ መጣሺበት ስፍራ ተመልሰሽና ውጪ ትባላለች ..."

በሳይንስ እውቀቱ ከነብዩ ሙሐመድ ለሚበልጠው የዛሬው ሙስሊም ይህ ቃል ማፈሪያ ቃል ነው።

3. **"ምድር "ሉል"(Sphere) ሳትሆን ጠፍጣፋ መሆኗ"**

"ምድር የተዘረጋች ናት"

- 13፡3 "እርሱ ያ ምድርን የዘረጋ..."
- 51፡48 "ምድርን ዘረጋናት።"

ተመሳሳይ ሐሳቦችን 15፡19, 50፡7 ... ስፍራዎች ላይ ቀርቧል።

"ምድር የተነጠፈች ምንጣፍ ናት"

- 71፡19 "አላህም ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ አደረጋት።"
- 78፡6 "ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣"
- 20፡53 "(እርሱ) ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ ..."

“ተራሮች ስለሚከልሉን እንጂ አጠቃላይ ምድር ግልፅ ሆና ትታየን ነበረ”

- 18፡47 “ተራራዎችን የምናስኬድበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ምድር ግልፅ ሆና ታያታለህ፡፡”
- 20፡105-107 “ከጋራዎችም ይጠይቁሃል፤ በላቸው “ጌታዬ መበተንን ይበትናቸዋል፡፡ (ምድርንም) ትክክል ሜዳ ሆና ይተዋታል፡፡”

ቁርአኑ በዚህ መልክ የምድርን ጠፍጣፋነት እርግጠኛ ሆኖ በተለያየ ቃላት ደጋግሞ ይነግረናል፣ ይህ ፈፅሞ ስህተት ነው፣ 51፡48 “ምድርን ዘረጋናት፡፡ ምን ያማርን ዘርጊዎች (ነን)” የሚለው የአላህ መመፃደቂያ ዛሬ መሬት ሉል(Sphere) መሆንዋን ለተገነዘበው ሙስሊም ማፈሪያ ነው፡፡ የሚገርመው ደግሞ በዚህ በተሳሳተው የ“ምድር የጠፍጣፋነት” አስተምህሮ፣ ሌሎች እውነታዎችም ተዛብተዋል፣ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

4. **“ምድር ጠፍጣፋ በመሆኗ ወርድና ስፋት አላት”**

57፡21 “ከጌታችሁ ወደ ኾነች ምሕረት፣ ወርዷ እንደ ሰማይና ምድር ወርድ ወደ ሆነች ገነት ተሽቀዳደሙ፡፡”

ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ ሰዎች የምድርን ጠርዝ ለማየት በተሽቀዳደሙ ነበረ፣ መንግሥታትም ሰዎችና እንስሳቱ ከጠርዝዋ እንዳይወድቁ በመሬት ጠርዝ ዙሪያ ትልቅ አጥር በሰሩ ነበረ¡

5. **“ምድር ጠፍጣፋ በመሆኗ ምዕራብና ምስራቅ የሚባሉ ቋሚ ስፍራዎች አሏት”**

55፡17 “የሁለቱ ምስራቆች ጌታ፤ የሁለቱ ምዕራቦችም ጌታ ነው፡፡”

መሬት ጠፍጣፋ ከሆች ይህ አባባል ትክክል ነው ነገር ግን መሬት ሉል በመሆንዋ ምዕራብ ወይ ምስራቅ የሚባል ስፍራን ማግኘት አንችልም፣ እንፈልግ ብንልም መሬት ክብ በመሆኗ ስንዞር እንቀራለን እንጂ ይህንን ስፍራ ፈፅሞ አናገኘውም፡፡

6. **“መሬት እንዳትነቃነቅ በተራሮች መቸከልዋ”**

“መሬት ጠፍጣፋ” በመሆኗ እንዳታረገርግ አላህ በተራሮች ችካል እንዳዋቀራት ቁርአን ይናገራል፣

- 78፡6-7 “ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣ ጋራዎችን ችካሎች አላደረግንምን፣”
- 16፡15 “በምድር ውስጥ በናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለባት፤”
- 31፡10“... በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለ፡፡”
- ጃሚያ አት ቲርሚዲ 6፡44፡3369 “... አላህ መሬትን ሲፈጥር መንቀጠቀጥ ጀመረች፣ ስለዚህ ተራሮችን ፈጠረና “በላይዋ ላይ ሁኑ” አላቸው፣ ከዚያ መሬት ከመናወጥ <u>ተረጋጋች</u>፡፡”

“መሬት ከመናወጥ ተረጋጋች” ተብሎ የመሬት መንቀጥቀጥ ከየት እንደሚመጣ ቢነግሩን መልካም ነበረ ወይስ ችካሉን በደንብ አልቸከለም? እውነታው ግን ተራራ የመሬት ችካል ሳይሆን እንደየትኛውም ደረቁ የመሬት ገፅ በቀለጠው የመሬት አካል ላይ የተንሳፈፈ ነው፣ የትኛውም ተራራ የማንትልን የቀለጠ ከፍል አልፎ አይሄድም፡፡ የችካሉ ነገር እውነት ሊሆን

የሚችለው እንኳን መሬት የተዘረጋች፣ ጠፍጣፋ ሙሉ በሙሉ ጠጣር አካል ብትሆን ነበረ፣ መሬት ግን ሉል ሆና በራስዋ ዛቢያ ላይና በፀሐይ ዙርያ የምትሽከረከር እንደዚሁ ውስጥዋ በቀለጠ ዓለት የተሞላች አካል በመሆኗ የችካሉ ነገር የጋርዮሽ ሰዎች ዕይታ ብቻ ነው።።

የተራሮችን የድንጋይ ተፈጥሮም ስንመለከት ተራሮች ከሌላ ስፍራ የተጣሉ፣ ለአከባቢው እንግዳ በሆኑ ድንጋዮች የተዋቀሩ ሳይሆን አብዛኞቻቸው በየአካባቢያቸው ካለው የመሬት ንጣፍ ጋር ተመሳሳይ ሲሆኑ ሌሎቹ ደግሞ በተፈጥሮአዊ ሂደት ከመሬት ውስጥ የወጡ ናቸው።።

የሚገርመው ደግሞ ተራሮች ለዘላለም እንደቆሙ የነበሩና የሚኖሩ ሳይሆን በመሬት ውስጣዊና ዉጫዊ ሂደት አንዳንዶች በሂደት እየጠፉ ሌሎች ደግሞ በሂደት እየተፈጠሩ የሚሄዱ ናቸው፣ ለምሳሌ የሂማልያ ተራራ በአመት በአንድ ኢንች ያድጋል።።

7. <u>“ሰማይ በጠንካራ ግንባታ የተሰራ መሆኑና ሸንቁር የሌለበት መሆኑ”</u>

ነብዩ የቀደመው የጋርዮሽ ትውልድ ሰማይን በሚመለከትበት እይታ በመመልከት ሰማይ በጠንካራ ግንባታ የተሰራና ሸንቁር የሌለበት አድርጎ ሲያስተምር ነበረ፣

<u>“ሰማይ ሊታለፍ በማይቻል ግንባታ የተሰራ ነው”</u>

- 50፡6 “ወደ ሰማይ ከበላያቸው ስትሆን ለእርስዋ <u>ምንም ቀዳዳዎች የሌሉአት ኾና እንዴት እንደገነባናትና</u> (በከዋክብት)እንዳጌጥናት አልተመለከቱምን።።”
- 51፡47 “ሰማይንም በኃይል <u>ገነባናት</u>።።”
- 67፡3-5 “ያ ሰባት ሰማያትን የተነባበሩ ሆነው የፈጠረ ነው … <u>ከስንጥቆቹ አንዳች ታያለህን</u>፣ ከዚያም ብዙ ጊዜ ዓይንህን መላልስ።። ዓይንህ ተዋርዶ እሱም የደከመ ሆኖ ወዳንተ ይመለሳል።።”

<u>“የሰማይ ግንባታ ሊሰበር፣ ሊቀደድ፣ሊሰባበርና ሊወድቅ የሚችል ቁስ ነው”</u>

- 34፡9“… በእነርሱ ላይ ከሰማይ ቁራጭን እንጥልባቸዋለን…”
- 81፡11 “ሰማይም በተገሸጠች ጊዜ፤”
- 84፡1 “ሰማይ በተቀደደች ጊዜ፤”
- 42፡5 “(ከአላህ ፍራቻ) ሰማያት ከበላያቸው ሊቀደዱ ይቀርባሉ።።”
- 25፡25 “ሰማይም በደመና የምትቀደድበትን … ቀን (አስታውስ)።።”
- 82፡1 “ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ፤”
- 73፡18 “ሰማዩ በርሱ (በዚያ ቀን) ተሰንጣቂ ነው።።

<u>የተገነባውም ሰማይ ከጨረቃ በታች መሆኑ</u>

- 71፡15-16 “አላህ ሰባት ሰማያት አንዱን ካንዱ በላይ ሲኾን እንዴት እንደ ፈጠረ አታዩምን፣ <u>በውስጣቸው ጨረቃን አብሪ አደረገ</u>።።”
- 37፡6 “እኛ ቅርቢቱን ሰማይ በከዋክብት ጌጥ አጌጥናት።።”
- 67፡5 “ቅርቢቱን ሰማይም በእርግጥ በመብራቶች (በከዋክብት) አጌጥናት

ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ጨረቃ የተጓዙት ሳይንቲስቶች ቁርአንን አንብበው ቢሆን ኖሮ ጉድ ሆነን ነበረ፣ ዛሬ ሳይንቲስቶች በቴሌስኮፓቸውና መንኮራኩሮቻቸው ከጨረቃም አልፈው ሌሎች ፕላኔቶች ጋር መድረሳቸውን ስንመለከት የቁርአኑ የሰማይ ግንባታ ታሪክ ውሸት ሆኖ እናገኘዋለን::

8. <u>የተቀያየረው እውነታ "ጨረቃ አብሪ ፀሐይ አንፀባራቂ"</u>

እንደሚታወቀው ፀሐይ ቋሚ የብርሃን ምንጭ ናት፣ ጨረቃ ደግሞ ከፀሐይ ተቀብላ ታንፀባርቃለች ነገር ግን ቁርአኑ የሁለቱን አሰራር አቀያይሯል፣

- 25፡16 "ያ በሰማይ ቡርጆችን ያደረገና በእርስዋም አንፀባራቂ(ፀሐይ) አብሪ ጨረቃንም ያደረገ ጌታ ከብሩ በጣም ላቀ::"
- 10፡5 "እርሱ ያ ፀሐይን አንፀባራቂ ጨረቃንም አብሪ ያደረገው ነው::"

እውነታው ግን ፀሐይ አብሪ ጨረቃ ደግሞ አንፀባራቂ ናት::

9. <u>"የፀሐይ ግርዶሽ የሚከሰተው አማኞችን ለማስፈራራት ነው"</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 2፡18፡158፣ "ፀሐይና ጨረቃ ግርዶሽ የሚፈጥሩት ... አላህ አማኞችን ሊያስፈራራበት ነው::"

የፀሐይ ግርዶሽ የተፈጥሮ ሂደት በመሆኑ እንዴትና መቼ እንደሚከሰት ይታወቃል፣ በዚህም ለዚህ ትውልድ ይህንን ክስተት "የአላህ ማስፈራሪያ ነው" ማለት አስቂኝ ነው::

10. <u>"የፀሐይና ጨረቃ የማይዛነፍ ተራ"</u>

ቁርአን ፀሐይና ጨረቃ ተራ እንዳላቸው ይነግረናል፣

- 36፡40 "ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስባት አይገባትም:: ሌሊትም ቀንን (ያለጊዜው) ቀዳሚ አይሆንም:: ሁሉም በመዞሪያቸው ውስጥ ይዋኛሉ::"
- 31፡29 "አላህ ለሊትን በቀን ውስጥ የሚያስገባ፣ ቀንንም በለሊት ውስጥ የሚያስገባ፣ ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ መሆኑን አታይምን፣"

ጨረቃ መሬትን ስትዞር መሬት ደግሞ ፀሐይን ትዞራለች፣ በዚህም ፀሐይና ጨረቃ የእርስ በርስ አንፃራዊ እንቅስቃሴ የላቸውም፣ ሁለቱም በአንዴ የሚወጡበትና በአንዴው የሚጠፉበት አንዳንዴም ትይዩ ሆነው ለመሬት ግርዶሽ የሚፈጥሩበት አጋጣሚዎች አሉ:: በዚህም በመካከላቸው ምንም አንፃራዊ የእንቅስቃሴ ሕግ የለም፣ ስለዚህ የቁርአን "የፀሐይና የጨረቃን የማይዛነፍ ተራ" አስተምህሮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን::

11. <u>"መብረቅ ከሃዲዎችን ለመቅጣት ነው የሚወርደው"</u>

13፡13 "ነጎድጓድ ... እነርሱም (ከሃዲዎች) በአላህ የሚከራከሩ ሲሆኑ በእርስዋ የሚሻውን ይመታል:: እርሱም ኃይለ ብርቱ ነው::"

ተመሳሳይ ሐሳብ ጃሚ አል ቲርሚዲ 5፡44፡3117 ላይም እንመለከታለን፣ ነገር ግን ከሃዲዎች በከረምት እንጂ በበጋ የሉም እንዴ?

12. <u>“ደመና የሚነዳበት እሳት”</u>

ጃሚያ አት ቲርሚዲ 3117 “ከመላዕክት መሃከል ለደመናት ተጠያቂ የሆነው መልአክ ደመናትን የሚነዳበት ትንሽ እሳት አለው … የነጎድጓድ ድምፁም የሚወጣው መልአኩ ደመናውን ለመንዳት በሚመታው ግዜ ነው …”

የበጋውን ደመና የሚነዳው መልአክ የእሳት መግረፊያ ስለሌለው ይሆን እንዴ ደመናውን ሲነዳ ድምፅ የማይሰማው?

13. <u>“ከዋክብት ሰማይ ውስጥ ይጠልቃሉ”</u>

56፡75-76 “በከዋክብትም መጥለቂያዎች እምላለሁ፡፡ እርሱ ብታውቁ ታላቅ መሀላ ነው፡፡”

“እርሱን ብታውቁ” ብሏል ነገር ግን ይህንን ያላወቀው ሳይንስ¡ ከዋክብት “መጥለቂያ የላቸውም፣ የቅርቢቷ ኮከብ(የፀሐይ) ብርሃን ሲደምቅ የኮከቦቹ ድምቀት ስለሚጠፋ የጠለቁ ይመስለናል” ይለናል፡፡

14. <u>“ከዋክብት ሰማይ ላይ የሚሄዱበት መንገድ አላቸው”</u>

ቁርአን ሰማይ ጠባር ግንባታ አድርጎ በመነሳቱ ከዋክብት ሰማዩ ላይ የሚንቀሳቀሱበት የራሳቸው መንገድ እንዳላቸው ይናገራል፣

51፡7 “የ(ከዋክብት) መንገዶች ባለቤት በኾነችው ሰማይ እምላለሁ፡፡”

ይህ እውነት የሚሆነው “የሰማይ ግንባታ” አስተምህሮ ባይፈርስብን ነበረ ነገር ግን እሱ በመፍረሱ “የከዋክብት መንገድ” የተባለውም ፈርሷል፡፡

15. <u>“ዝናብና በረዶ የሚመጣው ከሰማይ ውስጥ ነው”</u>

ቁርአኑ “ሰማይ ማለት በከዋክብት የተጌጠ፣ ጠባርና ሽንቁር የሌለበት አካል” መሆኑን ነግሮን የነበረ ቢሆንም ተመልሶ ደግሞ፣

- 24፡43 “… ከሰማይም <u>በውስጧ ካሉት ጋራዎች</u> በረዶን ያወርዳል፡፡”
- 16፡65 “አላህም ከሰማይ ውሀን አወረደ፡፡”
- 43፡11 “ያም ከሰማይ ውሀን በልክ ያወረደላችሁ ነው፡፡”

ችግር የለውም “ለነዚህ መውረጃ የተዘጋጁ ቀዳዳዎች ሊኖሩ ይችላሉ” ብለን እንለፍ ነገር ግን ይህ “ከሰማይ ውስጥ የሚፈስ ውሀ ፅንሰ ሐሳብ “የውሀ ዑደትን” በማያውቁ የጋርዮሽ ሰዎች አስተሳሰብ እንጂ እውነታ አይደለም፡፡

16. <u>“ፀሐይ ድቡልቡል(Sphere) ሳትሆን ሰማዩ ላይ የተለጠፈች ክብ ነገር መሆኗ”</u>

ይህንን ሐሳብ ቁርአኑ ሲያስረዳ፣

- 81፡1 “ፀሐይ በተጠቀለለች ጊዜ፣”
- ሰሂህ ቡኻሪ 4፡54፡422 “… በትንሳኤ ቀን ፀሐይና ጨረቃ እጥፍጥፍ(folded) ይደረጋሉ፡፡”

ይህ ጋርዮሹ ማኅበረሰብ፣ ሰማዩ ላይ የተለጠፈች ፀሐይ ምስል እንጂ እውነታ አይደለም፣ ሳይንሱ ፀሐይ ጠጣር ልጥፍ ነገር ሳትሆን በሀይድሮጂንና ሂሊየም ጋዞች የተሰራች እንደ መሬት ሉል (Sphere) የሆነች ኮከብ መሆኗን ነው የሚነግረን፡፡

17. <u>"ከዋክብትን እንደ ተለጠፈ ጌጥ አሳንሶ መመልከት"</u>

- 15፡16 "... (ሰማይን) ለተመልካቾችም (በከዋክብት) አጊጠናታል፡፡"
- 41፡12 "... ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን፡፡"

ከዋክብቱ ሰማይ ላይ የተቀመጡ ጌጦች ሳይሆኑ አንዳንዶቹ ከዋክብት መሬትን፣ ፀሐይንና ጨረቃን እንኳን የሚበልጡ ናቸው፣ አንዳንዶቹ መካከል ያለው ርቀት መሬትና ጨረቃ መካከል ካለው ርቀት እጅጉን ይበልጣል፣ በዚህም የቁርአኑ ቃል ከእውነታው ምን ያህል እንደራቀ እንመለከታለን፡፡

18. <u>"ሰው የሚኖረው ዳስ በሚመስል ዓለም ውስጥ ነው"</u>

እንደ ቁርአኑ እይታ፣ አሁን ሰው እየኖረ ያለው ከላይ እንደኮርኒስ በተዘረጋ ሰማይ ስር፣ ተራሮች እንደ ቋሚ እንጨት ጣል ጣል በተደረገባትና እንደ ምንጣፍ በተዘረጋች ምድር፣ በአጠቃላይ ዳስ በምትመስል መኖርያ ስር ነው፡፡

<u>"የሰማይ ጣርያነት"</u>

- 40፡64 "... (አላህ) ሰማይን ጣርያ ያደረገላችሁ ነው፡፡"
- 21፡32 "ሰማይንም (ከመውደቅ) የተጠበቀ ጣራ አደረግን፡፡"

<u>"የምድር ምንጣፍነት"</u>

- 71፡19 "አላህም ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ አደረጋት፡፡"
- 78፡6 "ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣"
- 20፡53 "(እርሱ) ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ ..."

<u>"ተራሮች እንደ ቋሚ እንጨት በምድር ላይ መቸከላቸው"</u>

- 78፡6-7 "ምድርን ምንጣፍ አላደረግንም፣ ጋራዎችን ችካሎች አላደረግንምን፣"
- 16፡15 "በምድርውስጥ በናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለባት፤"
- 31፡10 "... በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለ፡፡"
- 88፡17-19 "(ከሃዲዎች) አይመለከቱምን ... ወደ ተራራዎች እንዴት እንደ ተቸከሉ፡፡"

<u>የዳሱ ምስል</u>

- 2፡22 "(እርሱ) ያ ለናንተ ምድርን ምንጣፍ ሰማይን ጣሪያ ያደረገው ..."
- 55፡33 "የጋኔንና የሰው ጭፍሮች ሆይ! <u>ከሰማያትና ከምድር ቀበሌዎች</u> መውጣት ብትችሉ ውጡ፡፡ በስልጣን እንጂ አትወጡም፡፡ (ግን ስልጣን የላችሁም)፡፡"
- 32፡4 "አላህ ሰማያትንና ምድርን <u>በመካከላቸውም ያለውን</u> በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ከዚያም በአርሹ ላይ(ስልጣኑ) የተደላደለ ነው፡፡"

ከነዚህ ቃላት የዳሱን ምስል መመልከት ይቻላል፣ ከላይ የሰማይ ጣርያ፣ ከስር አልፎ አልፎ ተራራ እንደ ቋሚ እንጨት ጣል ጣል የተደረገባት የተነጠፈች ምድር፣ ይህ ጥንታዊው

የጋርዮሽ ዘመን የነበረው ህዝብ ሰማይና ምድርን የሚመለከትበት እይታ እንጂ እውነታ አይደለም፡፡

19. <u>“ሰይጣናቱም የሚኖሩት በዚህ ዳስ ውስጥ መሆኑ”</u>

- 55፡33 “የጋኔንና የሰው ጭፍሮች ሆይ! <u>ከሰማያትና ከምድር ቀበሌዎች</u> መውጣት ብትችሉ ውጡ፡፡ በስልጣን እንጂ አትወጡም፡፡ (ግን ስልጣን የላችሁም)፡፡”
- 72፡8-10 “(ጂኒዎችም) እኛ ሰማያትን (ለመድረስ) ፈለግን፡፡ ብርቱ ጠባቂዎችንና ችቦዎችንም ተሞልታ አገኘናት፡፡ ወደ እርስዋም (ወሬን) ለማዳመጥ በመቀመጫዎች እንቀመጥ ነበር፡፡ አሁን ግን የሚያዳምጥ ሰው ለእርሱ ተጠባባቂ ችቦን ያገኛል፡፡”
- 37፡6-10 “እኛ ቅርቢቱን ሰማይ በከዋክብት ጌጥ አጌጥናት፡፡ አመፀኛም ከሆነ ሰይጣን ሁሉ መጠበቅን ጠበቅናት፡፡ ወደ ላይኛው ሰማይ አያዳምጡም፡፡ ከየወገኑም ሁሉ ችቦ ይጣልባቸዋል፡፡ የሚባረሩ ሲሆኑ(ይጣልባቸዋል)፡፡ ለእነሱም ዘውታሪ ቅጣት አለባቸው፡፡ ንጥቂያ የነጠቀ ወዲያውም አብሪ ኮከብ የተከተለው ሲቀር፤”

ተመሳሳይ ሐሳብም ሀዲስ ሳሂህ ሙስሊም 26፡5538 ላይ ቀርቧል፡፡ ይሁን እንጂ ከላይ የተመለከትነው “የሰማይ ግንባታ” ትርክት ስለፈረሰ ሰይጣናቱ ተጠግተው የሚያዳምጡት የሰማይ ጣርያ የለም፡፡

20. <u>“ዩኒቨርስ የተደራረበ 14 አንባሻ የምትመስል መሆኑ”</u>

ቁርአን መሬትን ጨምሮ የአጠቃላይ ዩኒቨርስ ምስል ይነግረናል፣

- 65፡12 “አላህ ያ ሰባት ሰማያት የፈጠረ ነው፡፡ ከምድርም መሰላቸውን (ፈጥሮአል)፡፡” ተመሳሳይ ሐሳብ ሳሂህ ቡሃሪ 3፡43፡634, 4፡54፡418 … ላይም ቀርቧል
- 71፡15-16 “አላህ ሰባት ሰማያት አንዱን ካንዱ በላይ ሲኾን እንዴት እንደ ፈጠረ አታዩምን፣ በውስጣቸው ጨረቃን አብሪ አደረገ፡፡”
- ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡418 “ቁራጭ መሬት ያለአግባብ የሚወስድ ሰው፣ በትንሳኤ ቀን ሰባት መሬቶች ድረስ ይሰምጣል፡፡”

በዚህም በቁርአኑ ቴልስኮፕ ዩኒቨርሳችንን ስንመለከት፣ ከላይ ያየነው የዳስ ምስሉ ላይ ወደላይና ወደታች ስድስት ስድስት ሰማያትንና ምድራትን በመጨመር፣ ልክ በመካከላቸው ክፍተት ኖሯቸው የተደረደሩ 14 አምባሻዎች ምስል ነው፡፡

አንዳንድ ሙስሊሞች ይህንን “ሰባት ሰማያት” የሚለውን “ስለ ፕላኔቶች ነው” የተፃፈው በማለት የቁርአኑን አገላለፅ እውነት ለማስመሰል ሲጥሩ እንመለከታለን ነገር ግን “ሰባት መሬት ድረስ ይሰምጣል” ማለት አንዱ ባንዱ ላይ ማለት እንጂ እንደ ፕላኔቶች አጠገብ ለአጠገብ ያለ ሁኔታን አያሳይም፣ ፕላኔቶችም ሰባት ሳይሆኑ በዚህ ሶላር ሲስተማችን ውስጥ ብቻ ስምንት መደበኛ ፕላኔቶችና አራት ድንክ ፕላኔቶች ናቸው ያሉት፣ በሌሎቹ ሶላር ሲስተሞች ያሉት ደግሞ በሺዎች የሚቆጠሩ ፕላኔቶች ናቸው፣ ውሸትን “ውሸት” ማለት ሲገባቸው ወደ እውነት በማጠጋጋት እውነት ለማስመሰል መልፋታቸው ተጨማሪ ስህተት ነው፡፡

21. <u>"መንገዶች የተሰሩት በአላህ ነው"</u>

43፡10 "(እርሱ) ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ በርስዋም ውስጥ ትመሩ ዘንድ ለእናንተ መንገዶችን ያደረገላችሁ ነው፡፡"

ፈጣሪ ሁሉን ነገር መስራት ይችላል ነገር ግን ፈጣሪ ሰዎች እንዲሰሩት የሰጣቸው ስራዎች አሉ፣ ከነዚህ ውስጥ አንዱ የመንገድ ስራ ነው፣ በዚህም መንገድ ሲሰራ ምናየው በሰው እንጂ በአላህ አይደለም፣ ፈጣሪ ቀድሞውኑ መንገዶች የሚሰራ ቢሆን ኖሮ ሰው የሌለበት ጫካዎችና በረሀዎች መንገድ በኖራቸውና የመንገዶች ባለስልጣን መስሪያ ቤትም ባላስፈለገ ነበረ፡፡

22. <u>"በፅንስ ውስጥ ያለውን ማንም አያውቅም"</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 2፡17፡149 "... በፅንስ ውስጥ ያለውን ማንም ሊያውቅ አይችልም..."

ይህ ቃል የትክክለኛው ፈጣሪ ቃል ባለመሆኑ ዛሬ በአልትራሳውንድና በመሳሰሉት ቴክኖሎጂ በፅንስ ውስጥ ያለው ነገር ማወቅ ይቻላል፡፡

23. <u>"በልጅ ውስጥ የእናት የዘር ተዋፅዖ የለም"</u>

ቁርአን የሰው ልጅ የሚፈጠረው ከወንድ ዘር ብቻ እንደሆነና ሴትም፣ ልክ እንደ መሬት፣ ከወንድ የመጣውን ዘር ማብቀያ ቦታ ብቻ እንደሆነች ይነግረናል፣

<u>"ዘር ከወንድ ብቻ መሆኑ"</u>

- 53፡46 "ከፍትወት ጠብታ (በማህፀን ውስጥ) <u>በምትፈስስ ጊዜ</u>፡፡"
- 86፡5-7 "ሰውም ከምን እንደ ተፈጠረ ይመልከት፡፡ ከተስፈንጣሪ ውሀ ተፈጠረ፡፡ ከጀርባና ከእርግብግብቶች መካከል የሚወጣ ከኾነ (ውሀ)፡፡"
- 80፡17-19 "... ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው፤ መጠነውም፡፡"
- 30፡54 "አላህ ያ ከደካማ(ፍትወት ጠብታ) የፈጠራችሁ ነው፡፡ ከዚያ ደካማነት በኋላ ኃይልን አደረገ፡፡"

ተመሳሳይ ሐሳቦችም 16፡4, 36፡77 ... ስፍራዎች ላይ እንመለከታለን

<u>"ዘር መሬት ውስጥ እንደሚዘራና እንደሚበቅል የሰውም ዘር ከወንድ ወጥቶ በሴት ውስጥ የሚያድግ መሆኑ"</u>

- 2፡223 "ሴቶቻችሁ ለእናንተ እርሻ ናቸው፡፡ እርሻችሁንም በፈለጋችሁት ኹነታ ድረሱ..."
- 4፡4 "ሴቶችም መህሮቻቸውን በደስታ ስጡ፡፡"
- 21፡77 "በተጠበቀ መርጊያ ውስጥም (በማህፀን) አደረግነው፡፡"
- 23፡12-14 "በርግጥ ሰውን ... በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፡፡"

ነገር ግን ሴቶች ዘር የሚበቅልበት "የተጠበቀ መርጊያ" ስፍራ ሳይሆኑ እነሱም በልጆቻቸው ውስጥ ከወንዱ እኩል የራሳቸው የዘር አስትዋፅዖ ያላቸው መሆኑ ነው ሳይንሱ የሚነግረን፡፡

ሴቶች የዘር አስትዋፅዖ ባይኖር ኖሮ እናቱን/እናቷን የሚመስል/የምትመስል ልጅ ባልኖረ/ች ነበረ፡፡

24. <u>“የሰው ልጅ በማህፀን ውስጥ የረጋ ደም ከዚያ ቁራጭ ስጋ ነበረ“</u>

- 23፡13-14 “... የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፡፡”
- ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡549 "... ሁላችንም ስንፈጠር በናታችን ሆድ ውስጥ ለመጀመሪያው 40 ቀናት እንሰበሰባለን፣ በቀጣይ አርባ ቀናት ደግሞ የረጋ ደም እንሆናለን፣ ቀጥሎ ባሉት 40 ቀናት ደግሞ ቁራጭ ስጋ ...”

እንደዚህ አይነት የፅንስ የእድገት ደረጃ የለም፣ የሰው ልጅ ከተፀነሰበት ጊዜ አንስቶ ይብዛም ይነስም እንጂ አካል፣ ህይወት፣ ቅርፅ ... ያለው እንጂ የረጋ ደም፣ ቁራጭ ስጋ የሚሆንበት የፅንስ እድገት ደረጃ የለም፡፡

25. <u>“የሰው ልጅ ህይወት የሚፈጠርበት አጥንት ካበቀለ ከ120 ቀናት በኋላ ነው”</u>

- 23፡12-14 “በርግጥ ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፡፡ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፡፡ ቁራጭዋም ስጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፡፡ አጥንቶቹንም ስጋ አለበስናቸው፡፡ <u>ከዚያም</u> (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረት አድርገን አስገኘነው፡፡”
- ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡549፣ “... ሰው በናቱ ማህፀን ውስጥ (ከ120 ቀናት በኋላ) አላህ አራት ነገር እንዲፅፍ መልአክ ይልካል እነሱም፣ የሚሰራውን ስራዎቹን፣ የሚሞትበትን ቀን፣ የሚኖርበትን አኗኗርና በጎይማኖቱ የተባረከ ይሁን የተረገመ ይሁን ይፅፋል፣ ከዚያ ነፍስን ወደ ፅንሱ ያስገባል ...”

ነገር ግን ህይወት የሚገኘው በመጀመርያው ቀን እንጂ አጥንት ካወጣ በኋላ አይደለም፣ ፅንስ ይቅርና እያንዳንድዋ የወንድ አስፐርም ሴል እንዲሁም የሴቷ እንቁላል እራሳቸው ህይወት አላቸው፡፡

26. <u>“የህፃን ጾታ የሚወሰነው አካሉ ከተሰራ በኋላ ነው”</u>

- 75፡36-39 “ሰው ስድ ሆኖ መትተውን ይጠረጥራልን፣ የሚፈስስ የኾነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን፣ ከዚያ የረጋ ደም ሆነ (አላህ ሰው አድርጎ) ፈጠረውም፡፡ አስተካከለውም፡፡ <u>ከእርሱም</u> ሁለት አይነቶችን ወንድና ሴት አደረገ፡፡”
- ሳሂህ ሙስሊም 33፡6397 እና ሳሂህ ቡኻሪ 8፡77፡594 “... አላህ ለፅንስ ጥበቃ መልአክ ይመድባል፣ እሱም፣ አምላኬ አሁን የዘር ጠብታ ነው፣ አምላኬ አሁን የረጋ ደም ነው፣ አምላኬ አሁን ስጋ ሆኖአል ይላል፣ ከዚያ አላህ የመጨረሻውን ቅርፅ ሊሰጠው ሲወስን፣ <u>መልአኩም ወንድ ነው ሴት ይሁን</u>፣ ጥሩ ወይስ መጥፎ ሰው ይሁን ... ብሎ ይጠይቃል ...”

ጾታ የሚወሰነው በእርግዝና ጊዜ የወንዱና የሴቷ ዘር በሚገናኝበት ጊዜ በሚፈጠረው የዘረመል ጥምርታ እንጂ ከቆይታ በኋላ አይደለም::

27. <u>የህፃን መልክ የሚወሰነው በግንኙነት ወቅት ነው</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 4:55:546 "... በግንኙነት ወቅት አባት ቀድሞ ስሜቱን ከጨረሰ የሚወለደው እሱን ይመስላል፣ እናት ቀድማ ከጨረሰች እስዋን ይመስላል ..."

የልጅ መልክ የሚወሰነው በስሜት ሳይሆን የአባትና የእናት ዘረመሎች የሚጣመሩበት መንገድ ነው::

28. <u>"ሰው የሚያስበው በደረቱ ነው"</u>

- 6:125 "አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ደረቱን ለኢስላም ይከፍታል:: ሊያጠመው የሚሻውን ሰው ደረቱን ጠባብ ቸጋራ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል::"
- 3:29 "በደረቶቻችሁ ውስጥ ያለውን ብትደብቁ ወይም ብትገልፁት አላህ ያውቀዋል::"
- 39:22 "አላህ ደረቱን ለእስልምና ያስፋለትና ..."

ደረት ማሰቢያ አካል አይደለም፣ ይህንን ስህተት የወለደው፣ "ሰው የሚያስበው በልቡ ነው" የሚለውን ተለምዶአዊ አነጋገርን በስፋት ለማብራራት በመሞከር ነው፣ ሰው የሚያስበው በአዕምሮው እንጂ በደረቱ አይደለም፣ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ቀጫጭን ሰዎች ጉድ ሆነው ነበረ::

29. <u>"ሙስሊም በአንድ አንጀቱ ሲመገብ ሙስሊም ያልሆነ ሰው በሰባት አንጀቱ ይመገባል"</u>

- ሳሂህ ሙስሊም 23:5113 "ሙስሊም ያልሆነ ሰው በሰባት አንጀት ይበላል ሙስሊሙ ግን የበሚላው በአንድ አንጀቱ ነው::"
  ይህ ሐሳብ በተደጋጋሚ እስከ 23:5118 ድረስ ተብራርቷል፣
- ሳሂህ ሙስሊም 23:5120 "... አማኝ በአንድ አንጀቱ ሲጠጣ ያላመኑት በሰባት አንጀት ይጠጣሉ::"

እዚህ ጋር ሙስሊም የህክምና ባለሙያዎች ብታስረዱን መልካም ነው፣ ቁርአኑ እውነት ወይ ውሸት ነው የሚናገረው? ሰው ሲሰልም ስድስቱ አንጀትስ የት ይገባል?

30. <u>"አንድ ሙስሊም አስር ያልሰለሙ ሰዎችን ያሸንፋል"</u>

8:65 "አንተ ነብዩ ሆይ! ምእመናንን በመዋጋት አደፋፍራቸው:: ከእናንተ ውስጥ ሀያ ታጋሾች ቢኖሩ ሁለት መቶን ያሸንፋሉ:: ከእናንተ መቶ ቢኖሩ <u>ከእነዚያ ከካዱት እነሱ የማያውቁ ህዝቦች ስለሆኑ</u> ሺህን ያሸንፋሉ::"

ሙስሊሞች ቴኳንዶ ቤት የሚበዙት ይህ የቁርአኑ ስሌት አልመጣላቸው ብሎ ይሆን እንዴ?

31. **“<u>የአማኞች መቃብር ይሰፋል የትምክህተኞች በአንድ ላይ ይጨመቃል</u>”**

ሰዎች እስከ ፍርድ ቀን በመቃብራቸው ውስጥ እንደሚቆዩ ቁርአን ይናገራል (83፡4-6, 19፡66-67, 30፡19 ...)፣ ሀዲስ ስለዚህ ቆይታ ሲናገር፣

> ጃሚያ አት ቲርሚዲ 1071 “... የአማኝ መቃብር ሰባ በሰባ ድረስ ይለጠጣል ብርሃናማም ይደረጋል ... ትምክህተኛ የነበረ ሰው መቃብር ግን በአንድ ላይ ይጨመቃል፣ የጎድን አጥንቶቹ እስኪጣበቁ ድረስ ይጨፈለቃል ...”

ምንም እንኩዋን ጉዳዩ ስለ ድህረ ሞት ጉዳይ ቢሆንም ተመልሶ ግን በአካባቢያችን ስለምንመለከተው መቃብር የሚያወራ በመሆኑ እውነታውን በቀላሉ ማወቅ እንችላለን፣ የየትኛውም መቃብር ስፋት ሲያንስ፣ ሲሰፋ፣ መብራት ሲገባለት... አልተመለከትንም፡፡

32. **<u>“የውሀ ብክለት የሚባል ነገር የለም”</u>**

> ሱናን አቡ ዳውድ 66፣ የሆነ ሰው መጥቶ የአላህን መልዕክተኛን “ቡዳህ ከሚባለውና የሞቱ ውሾች፣ የወር አበባ ጨርቆጭና ቆሻሻ ከሚጣልበት የውሀ ጉድጓድ ውሀ ቀድተን መታጠብ እንችላለን?” ብሎ ጠየቀ፣ የአላህ መልዕክተኛም “በርግጥ ውሀ ንፁህ ነው፣ ምንም ነገር እሱን አያቆሽሽም አሉ፡፡”

33. **<u>“ተላላፊ በሽታ የሚባል ነገር የለም”</u>**

> ሳሂህ ሙስሊም 26፡5508 “... ተላላፊ በሽታ የሚባል ነገር የለም፡፡”
> ተመሳሳይ ሐሳብም ጃሚ አል ቲርሚዲ 2143 ላይ እንመለከታለን፡፡

34. **<u>“የሰውነት ማተኮስ ከሲኦል ሙቀት ነው”</u>**

> ሳሂህ ቡኻሪ 7፡71፡621 “... ትኩሳት ከሲኦል ሙቀት ስለሆነ ትኩሳቱን በውሀ አጥፉት፡፡” የዚህን ተመሳሳይ ሐሳብ በተጨማሪ በሳሂህ ቡኻሪ 7፡71፡619 - 7፡71፡622፣ ተብራርቷል፡፡

ትኩሳቱ ከሲኦል ሙቀት ከሆነ ለምን ታማሚውን ብቻ ከሌላው ሰው ለይቶ ያተኩሰዋል? ከሲኦል ትይይዩ ስለተቀመጠ ይሆን? እንደዚያ ከሆነ ከውሀው ይልቅ የሚሻለው ስፍራውን መቀየር ነው¡

35. **<u>“የቀትር ወበቅ መነሻው የሲኦል ሙቀት ነው”</u>**

> ሳሂህ ቡኻሪ 1፡10፡513 “ዙሁር የምትሰግዱት ወበቁ ቀዝቀዝ ሲል ነው፣ ወበቁ የሚመጣው ከሲኦል እሳት ነው፡፡”

ወበቅ የሚመጣው ከፀሐይ እንጂ ከሲኦል እሳት አይደለም፣ ታድያ ፀሐይ ስትጠፋ ወበቁ ለምን ይጠፋል?

36. **<u>“የዝንብ ክንፍ መድኃኒት ይዟል”</u>**

> ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡537 “እንዳችሁ በምትጠጡት ውስጥ ዝንብ ቢገባባችሁ፣ በመጠጡ ውስጥ ንከሩት፣ አንዱ ክንፉ በሽታ እንደያዘው ሌላኛው ክንፉ ደግሞ ለበሽታው መድኃኒት ይይዛል፡፡”

37. <u>“ጥቁር አዝሙድ ሁሉንም በሽታ ይፈውሳል”</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 7፡71፡592 “ጥቁር አዝሙድ ከሞት በስተቀር ሁሉንም በሽታ ይፈውሳል።”

መቼም ከዚህ በኋላ ለህክምና ወጪ አናወጣም እንደማትሉ ተስፋ አደርጋለሁ¡

38. <u>“የግመል ሽንት ከበሽታ ይፈውሳል”</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 8፡82፡796 “... ነብዩም እንደነገሩዋቸው ... ሄደው የግመሎችን ወተትና ሽንት ለመድኃኒትነት ጠጡ ከዚያ ጤናማና ወፍራም ሆኑ።”

የዚህን ተመሳሳይ ሐሳብ ሳሂህ ቡኻሪ 7፡71፡590 እና ሳሂህ ሙስሊም 16፡4130 ላይ ቀርቧል።

ሐሳቡ ትክክል ቢሆን ኖሮ ዛሬ የግመል ሽንት እየታሸገ በተሸጠልን ነበረ ነገር ግን አልሆነም ሌላው ማኅበረሰብ ይቅርና ሙስሊሙ ማኅበረሰብም እንኳን ይህንን ቃል አይሰማም።

እነዚህ ከላይ ከተራ ቁጥር 22 ጀምሮ የምንመለከታቸው የእስልምና የጤና አስተምህሮዎች የተሳሳቱ ይባሱኑ አንዳንዶቹ በሽታን የሚፈጥሩ ናቸው፣ “ቦኮ ሀራም” ን ጨምሮ ብዙ አሸባሪ ቡድኖች ዘመናዊውን ህክምናን የሚቃወሙት ይህ እስላማዊው የህክምና ትምህርት “በቂ ነው” በማለት ነው።

39. <u>“ጦጣዎች ዝሙት የፈፀመ ጦጣን ይወግራሉ”</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 5፡58፡188 “ከእስልምና ዘመን በፊት አንድ ሴት ጦጣ በማመንዘሯ ምክንያት በብዙ ጦጣዎች በድንጋይ ሰትወገር ተመለከትኩኝ፣ እኔም ከነሱ ጋር ሆኜ በድንጋይ ወገርኳት።”

ይህ ታሪክ በእስልምና ዘመን ቢሆን ኖሮ ንግግሩን “መንፈሳዊ እውቀት” ሊሆን ይችላል በሚል “ባላወቀ” እናልፍ ነበረ ይሁን እንጂ ድርጊቱ ተፈፀመ የተባለው ነብዩ እንደ ማንኛውም ሰው በነበረ ጊዜ በመሆኑ ይህ ወሬ ውሸት ብቻ መሆኑን እንመለከታለን።

40. <u>ምግብ አላህን ያመሰግናል</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 4፡56፡779 “... ምግቡ እየተበላ አላህን ሲያመሰግን ሰማነው።”

41. <u>“ነብዩ ካልነኩኝ” ብሎ የጮኸው ዛፍ</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 2፡13፡41 “... የቴምር ዛፍ ግንድ፣ ነብዩ እጃቸውን እስኪጭኑበት ድረስ እንደ እርጉዝ ግመል ሲጮህ ሰማን።”

42. <u>አውራ ዶሮ የሚጮኸው መልአክ ሲመለከት ነው</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 4:54፡522 “አውራ ዶሮ ሲጮህ አላህን በረከት ለምኑ ምክንያቱም አውራ ዶሮ የሚጮኸው መልአክ ሲመለከት ነው።”

43. <u>አህያ የሚጮኸው ሰይጣን ሲመለከት ነው</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 4:54፡522 “አህያ ሲጮህ አላህን ምህረት ለምኑ ምክንያቱም አህያ የሚጮኸው ሰይጣን ሲመለከት ነው።”

44. <u>“ጥቁር ውሻ ሰይጣን ነው”</u>

ሳሂህ ሙስሊም 4፡1032 - አቡ ዳር እንደዘገቡት፡ የአላህ መልዕክተኛ “... ፀሎት የሚቋረጠው በፊስ፣ በሴትና ጥቁር ውሻ ማለፍ ነው” ... ጥቁር ውሻ ደግሞ ከሌሎቹ አይነት ውሾች በምን ይለያል አልኩት እሱም “ጥቁር ውሻ ሰይጣን ነው” አለኝ፡፡”

ከመላሹ በላይ ተንኮለኛው ጠያቂው ነው፣ የጥቁር ውሻ ፊት እንደሚስፈራ እያወቀ¡

45. <u>“ሰይጣን የወደቀ ምግብ ይበላል”</u>

ሳሂህ ሙስሊም 23፡5043 እና 23፡5044 “(ከተመገባችሁ በኋላ) ጣታችሁንና ሳህናችሁን ላሱ ምክንያቱም በረከታችሁ የቱ ጋር እንዳለ አታውቁምና፣ ልትነርሱት ያላችሁት ከእጃችሁ ቢወድቅ አንስታችሁ ቆሻሻውን ጠርጋችሁ ብሉት፣ ለሰይጣን ልትተውት አይገባምና፡፡”

እስቲ የወደቀውን ምግብ እዚያው ተውትና ሰይጣን መጥቶ ሲበላው ተመልከቱት፣ ከላይ ያየነው ጥቁር ውሻ መጥቶ መብላት ግን ግምት ውስጥ ሊገባ አይገባም፣ ሰይጣንን ነው መጠበቅ ያለባችሁ፡፡

46. <u>“ማፋሸግ ከሰይጣን ነው”</u>

በእስልምና ማፋሸግ የተከለከለ ነው፣ ምክንያቱም፣

- ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡509 “ማፋሸግ ከሰይጣን ነው፡፡”
- ሳሂህ ቡኻሪ 8፡73፡.245 “አላህ ማንጠስ ወደደ፣ ማፋሸግ ግን ጠላ ... ማፋሸግ ከሰይጣን ነው፣ ቶሎ አቋርጡ፣ ሰይጣን ይስቅባችኋል፡፡”
- ሳሂህ ሙስሊም 42፡7130 “... ስታፋሽጉ ሰይጣን እንዳይገባ በእጃችሁ አቃርጡ፡፡”

ሰው የሚያፋሽገው ሰውነቱ እረፍት፣ እንቅልፍና የለመደው ማነቃቂያ ... በሚፈልግበት ጊዜ እንጂ በሰይጣን አይደለም፣ ሰውየው ሰውነቱ የፈለገውን ነገር ሲያገኝ ማፋሸጉን ያቆማል፡፡

<u>ማጠቃለያ(ከእውነታ ጋር መጋጨት)</u>

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው በሙሉ የዋነኞቹ የእስልምና ቅዱሳን መጽሐፍት ውሸቶች ናቸው፣ የሚገርመው ደግሞ የውሸት ነገር መጋለጡ ስለማይቀር ሙሐመድ የተናገራቸው ቃላት ውሸትነት ሲረጋገጥበት በተለያየ ዘዴ ፈተናውን ሲያልፍ ነበረ፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- አንድ ሰው ነብዩ ባዘዙት መድኃኒት ወንድሙ አለመፈወሱን ሲናገር፣
  ሰሂህ ቡኻሪ 7፡71፡614 “አንድ ሰውም ወደ ነብዩ ቀርቦ `ወንድሜ (በተቅማጥ ምክንያት) ለመንቀሳቀስ አቅም አጥቷል` አለ፣ ነብዩም `ማር አጠጣው` አሉት፣ ሰውየውም ተመልሶ `ማር አጠጣሁት ነገር ግን አባሰበት` አለ፣ ነብዩም `አላህ ትክክለኛውን ተናግሯል፣ የወንድምህ ሆድ ውሸት ተናገረ` አሉት፡፡”
- “መሬት እንዳትንቀሳቀስ በተራራ ተዋቅራለች” መባሉና በአካባቢያቸው ስለሚበዛው መሬት መንቀጥቀጥ ሲጠይቅ በማይጨበጥ መንገድ ፈተናውን ሲወጣ፣

ሰሂህ ቡኻሪ 9፡88፡214 “... እዛ (ናጂድ በተባለው ስፍራ) የመሬት መንቀጥቀጥና የመቅሰፍት ስፍራ፣የሰይጣን ራስ ጎን የሚወጣበት ስፍራ ነው”

- ነብዩ “ተላላፊ በሽታ የለም” በማለታቸው ጥያቄ የተፈጠረባቸውን በደዊኖች ለማሳመን፣

ጃሚ አል ቲርሚዲ 2143 “... አንድ ነገር ሌላውን አይበክልም(ተላላፊ በሽታ የለም) ... እንደዚያ ካልሆነ የመጀመሪያው ታማሚ በሽታውን ከየት አመጣው? ... አላህ ሁሉንም ነፍስ ፈጠረ፣ ህይወቱን ፃፈ፣ የሚቀሰፍበትን ጊዜ ፃፈ ...”

በማለት በደዊኑን ከባድ ጥያቄ በመጠየቅ ፈተናውን ተወጥተውታል፡፡

ይህንን የሙሐመድን አካሄድ ያስተዋሉ በወቅቱ የነበሩት ሰዎች፣ የሙሐመድን ቁርአን “ውሸት ነው” ሲሉ ነበረ፣

- 25፡4“... (ቁርአን ሙሃመድ) የቀጠፈው... ውሸት እንጂ ሌላ አይደለም...”
- 34፡43 “... ይህም ቁርአን የተቀጣጠፈ ውሸት ነው እንጂ ሌላ አይደለም...”
- 38፡7 “... ይህ ውሸት መፍጠር እንጂ ሌላ አይደለም ...”

ሲሉ ነበረ፣ እነዚህ አስተያየቶች ዛሬ ላይ ትክክለኛ ሆነው ነው የምንመለከተው፡፡ ለዚህ ትውልድ፣ ቁርአን ስለራሱ የተናገረው፣ 59፡21 “ይህንን ቁርአን በተራራ ላይ ባወረድነው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ የተነሳ ተዋራጅ ተሰንጣቂ ሆኖ ባየኸው ነበር፤” የሚለው አሁን አስቂኝ ማስፈራርያ ብቻ ነው፡፡

ፈጣሪ ቅዱስና ሁሉን አዋቂ ስለሆነ አይዋሸም በዚህም ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑንን እንመለከታለን፡፡

2.4.3.3. <u>ቁርአን እርስ በርስ እንዲሁም ከሀዲሳት ጋር መጋጨቱ</u>

ፈጣሪ ቅዱስና ሁሉን አዋቂ በመሆኑ ከመነሻው ሲናገር አንዱን እውነት ይናገራል በዚህም ከጊዜ በኋላ ሌላ እውነት ተገልጦለት መጀመርያ ከተናገረው ጋር እርስ በርስ አይጋጭበትም ነገር ግን ቁርአን ስንመለከት የሚናገረው ነገር እርስ በርስ እንዲሁም ከሀዲሳት ጋር ይጋጫል፣ ይህ ደግሞ ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑን ያሳያል፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

2.4.3.3.1. <u>እርስ በርስ የሚጋጨው የአላህ የመጨረሻ ዘመን ፍርድ</u>

ቁርአን፣ አላህ በፍርዱ ፃድቅ እንደሆነና ሰውን ሁሉ በአግባቡ እንደሚዳኝ ይናገራል(4፡40, 21፡47 ...)፣ ፍርድም የሚሰጠው በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ(58፡22)፣ በመልከተኛው ያመነና ዘካ የሰጠ(2፡43)፣ ሰጋጅ(2፡43)፣ መልካም የሰራ(2፡25)፣ በአላህ መንገድ የተጋደለ(61፡4)፣ ቤቱን (ካዕባን) በሀጅ ወይ በዑምራህ የጎበኘ(2፡158) በሚሉ መስፈርቶች ነው፡፡ በነዚህም መስፈርቶች የሰዎች ስራ በትክክለኛ ሚዛን ተመዝኖ ዋጋቸው እንደሚሰጣቸው ቁርአኑ ይናገራል፣

21፡47 “በትንሳኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን፡፡ ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም፡፡ (ስራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርስዋን እናመጣታለን፡፡”

ይሁን እንጂ ፍርድ ተዛብቶባቸው ሲኦል ገብተው የሚወጡ ሰዎች ደግሞ እንደሚኖሩ ሀዲሱ ላይ ተመልክቷል፣

ሳሂህ ቡኻሪ 8፡76፡564 “...አንዳንድ ሰዎች የእሳት ወላፈን ከነካቸው፣ ቀለማቸው ከተቀየረ በኋላ፣ ከእሳቱ ወጥተው ገነት እንዲገቡ ይደረጋሉ፣ የገነት ሰዎችም እነዚህን ሰዎች “አል-ጀሃናሚን”፣ (የሲኦል) እሳት ሰዎች ይሏቸዋል፡፡”

በሌላ ስፍራ ደግሞ ቁርአኑ “... (አላህ) የፈለገውን ይምራል የፈለገውን ይቀጣል፡፡”(3፡129, 5፡18, 5፡20 ...) በማለት ከላይ የተጠቀሰውን የፍርድ ሚዛንና የፍርድ መስፈርቶችን ትርጉም ሲያሳጣ እንመለከታለን፡፡ ከዚህ በባሰ ደግሞ ቁርአኑ አንድ ሰው ገነት ወይን ሲኦል መግባት አለመግባቱ በራሱ የተወሰነው ሰውየው ሳይወለድ፣ የራሱ ምንም አስትዋፅዖ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ ይናገራል፣

- <u>አላህ ቀድሞውኑ ለገሀነም የፈጠራቸው ሰዎች መኖራቸው</u>
  - ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡549 “... ሰው በናቱ ማህፀን ውስጥ (ከ120 ቀናት በኋላ) አላህ አራት ነገር እንዲፅፍ መልአክ ይልካል እነሱም፣ የሚሰራውን ስራዎቹን፣ የሚሞትበትን ቀን፣ የሚኖርበትን አኗኗርና በኃይማኖቱ <u>የተባረከ</u> ይሁን <u>የተረገመ</u> ይሁን ይፅፋል፣ ከዚያ ነፍስን ወደ ፅንሱ ያስገባል...” ተመሳሳይ ሐሳብም ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡430, 8፡77፡593, 9፡93፡540 ... ላይ ቀርቧል
  - ሳሂህ ሙስሊም 33፡6393 “... ክፉ ማለት በናቱ ሆድ ውስጥ ክፉ እንዲሆን ... የአላህ መልአክ በዚያ ይቀርፀዋል፡፡”
  - 7፡179 “ኪጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን በርግጥ ለገሀነም ፈጠርን፡፡”
  - 32፡13 “በሻን ኖሮ ነፍስን ሁሉ እምነቱዋን በሰጠናት ነበረ፣ ግን ገሀነምን ከኢጋንንትና ከሰዎች የተሰበሰቡ ሆነው በእርግጥ እሞላለሁ፡፡”
  - 16፡9 እና 11፡118 “ጌታህም በሻ ኖሮ ሰዎችን ሁሉ አንድ ህዝብ ባደረጋቸው ነበረ ... የጌታህም ቃል ገሀነምን ከኢጋንንትና ከሰዎች ከሁሉም በእርግጥ እሞላታለሁ በማለት ተፈፀመች፡፡”
- <u>አላህ እምነት እንዳይኖራቸው የሚያደርጋቸው ሰዎች መኖሩ</u>
  32፡13 “በሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ ቅንነቷን (እምነቷን) በሰጠናት ነበር፡፡”
- <u>አላህ የሚያሳስታቸው መኖራቸው</u>
  4፡88 “... አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን <u>አላህም ያሳሳተውን ሰው</u> ለእርሱ መንገድ ፈፅሞ አታገኝለትም፡፡”

- <u>አላህ የሚያጣምማቸው መኖራቸው</u>
  - 4፡88 "... አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን ..."
  - 35፡8"... አላህ የሚሻውን ሰው ያጠምማል፣ የሚሻውንም ያቀናል።"

  ተመሳሳይ ሐሳቦችም በ7፡186, 39፡36, 74፡31 ... ስፍራዎች ላይ እናገኛለን።
- <u>አላህ እንዳያስታውሱ የሚያዘናጋቸው መኖራቸው</u>

  18፡28 "ልቡን እኛን ከማስታወስ ያዘነጋነውን ..."
- <u>አላህ ልቦናቸው እንዳያስተውል የሚዘጋባቸው መኖራቸው</u>
  - 18፡57 "... በልቦቻቸው ላይ እንዳያውቁት ሽፋኖችን፣ በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን <u>አደረግን</u>፣ ወደ መምራትም ብትጠራቸው ፈፅመው አይመሩም።"
  - 47፡23-24 "እነዚህ እነዚያ አላህ የረገማቸው፣ ያደነቆራቸውም፣ አይኖቻቸውንም ያወራቸው ናቸው።"
  - 2፡6 "እነዚያ የካዱት (ሰዎች) ብታስፈራራቸውም ባታስፈራራቸውም በነርሱ ላይ እኩል ነው፤ አያምኑትም። አላህ በልቦቻቸው ላይ በመስሚያቸውም ላይ <u>አትሞባቸዋል</u> ..."
  - 17፡46 "(ቁርአንን) እንዳያውቁት በልቦቻቸው ላይ ሽፋንን በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን <u>አደረግን</u>።"
  - 6፡25 "ከእነርሱ ወደአንተ (ወደ ሙሐመድ) የሚያዳምጥ ሰው አልለ። በልቦቻቸው ላይ እንዳያውቁት ሺፋኖችን በጆሮዎቻቸውም ላይ ድንቁርናን <u>አደረግን</u>።"

የሚገርመው ደግሞ ሰውየው ለማመንና ነፍት ለመግባት ቢጣጣር እንኳን ጥረቱ ዋጋ የለውም።

11፡34 "ለናንተ ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደሆነ ምክሬ አይጠቅማችሁ።"

አላህም ይህን ሁሉ አድርጎ ተመልሶ ደግሞ፣

43፡74-76 "አመፀኞች በገሀነም ስቃይ ውስጥ ናቸው ... <u>አልበደልናቸውምም፤ ግን በዳዮቹ እነርሱው ነበሩ</u>።" ይላል።

በዚህም ቁርአን ስለ ፈጣሪ ፍርድ አሰጣጥ የሰጠው አስተምህሮ ምን ያህል እርስ በርሱ እንደሚጋጭ እንመለከታለን።

2.4.3.3.2. <u>የሰይጣን የገሀነም ፍርድ</u>

የሰው ልጅ ገሀነም ሆነ ጀነት ለመግባት የራሱ አስትዋፅዖ እንደሌለው ሁሉ ጋኔኖችም የተቀመጠላቸው እድል ተመሳሳይ ነው ነገር ግን የእነሱን ከሰው ለየት ለማድረግ የተሞከረው "ኢብሊስ ከመጀመሪያው ስህተቱ የራሱ ነበረ" ለማለት ተሞክሯል፣

2፡34 “ለመላዕክትም፣ ለአዳም ስገዱ ባልን ጊዜ(አስታውስ)፡፡ ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፤ ኢብሊስ(ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር እምቢ አለ፤ ኮራም ከከሃዲዎቹ ሆነ፡፡”

ኢብሊስ ግን ለሰው አለመስገዱ ቁርአናዊ ነበረ ምክንያቱም አምላክ አላህ ብቻ በመሆኑ(3፡2, 47፡19)፣ ስግደትም ለአላህ ብቻ በመሆኑ(6፡162)፣ አላህ የማጋራትን ኃጢያት ስለማይምር(4፡116, 6፡11-19) … ወዘተ፣ በዚህም ኢብሊስ “ከአላህ ውጪ ለማንም አልሰግድም” ማለቱ ትክክል ነበረ፡፡ በዚህም ኢብሊስ እንዲሳሳት ምክንያት የሆነው አላህ ቃሉን ተላልፎ ኢብሊስን “ለአዳም ስገድ” ማለቱ እንጂ የኢብሊስ የአላህን ቃል መተላለፍ አልነበረም፡፡

ይህ የኢብሊስን “ትክክለኛነት” ለማሳየት ቀረበ እንጂ፣ ጉዳዩ ያለቀው በኢብሊስ ድርጊት ሳይሆን ከፍጥረት መጀመሪያ ነው፣ 7፡179 “ከጋኔንም ከሰዎችም ብዙዎችን በርግጥ ለገሀነም ፈጠርን፡፡” በሚለው ቃል፣ በዚህም አላህ ኢብሊስ ሲፈጥረው ለሲኦል እንዲሆን አጣሞ ነው፣

15፡39 “(ኢብሊስ) አለ “ጌታዬ ሆይ! እኔን በማጥመምህ …”

ስለዚህ ኢብሊስን ያሳሳተው አላህ መሆኑና ለኢብሊስ መሳሳት ተጠያቂውም አላህ መሆኑን እንመለከታለን፣ ይህም እላይ ካየነው በሰው ልጆች ላይ ከሚፈረደው የተምታታ የፍርድ ሂደት ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡

2.4.3.3.3. <u>በስጋዊ ዓይን የተተረከው ገነትና ገሀነም</u>

ቁርአን በገነት ውስጥ ስለሚኖረው ደስታና በገሀነም ስለሚኖረው ቅጣት ሰፊ ትንታኔዎችን ይሰጣል ነገር ግን ትንታኔዎቹ በሙሉ የቀረቡት በስጋዊ ዓይን እንጂ ለፍርድ ስለምትቀርበው ነፍስ አይደለም፣ በስጋዊ ዓይን የተሰጡት ትንታኔዎችም ቢሆኑ እንደ ፈጣሪ ዕይታ ሳይሆኑ ሙሐመድ በወቅቱ “አሪፍ” በሚለው የኑሮ ዘይቤ ልኬት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

- <u>**መብላትና መጠጣት በገነት**</u>

ቁርአኑ በገነት ውስጥ ሰፊ የመብላትና መጠጣት ዘመን እንደተዘጋጀ ይናገራል ነገር ግን እነዚህ የገነት ምግብና መጠጦቹ የተሳሉት በስጋዊ እይታና በነሙሐመድ ዘመን በነበረው የቅንጦት ምግቦችና አመጋገብ ስነ ስርዓቶች እንጂ ወደ ፈጣሪ በምትሄደው ነፍስና የሁሉንም ትውልድ አኗኗር ዘይቤ ባገናዘበ መልኩ አይደለም፣

- 56፡18 “ከጠጅ ምንጭም በብርጭቆዎችና በኩስኩሶች በፅዋም (በእነሱ ላይ ይዞራሉ) … ከሚመጡትም አይነት በእሸቶች፡፡ ከሚሹትም በኾነ በራሪ ስጋ (ይዞሩባቸዋል)፡፡
- 52፡22-23 “ከሚሹት ሁላ እሸትንና ስጋን <u>እንጨምርላቸዋለን</u>፡፡ በውስጥዋ መጠጥን ይጠጣሉ፡፡”

- ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡469 "... የገነት ኗሪዎች የሚጠቀሙበት ዕቃ የተሰራው በወርቅና በሲልቨር ነው፣ ማበጠሪያቸውም የተሰራው ከወርቅ ነው፣ ለእሳትነትም የሚጠቀሙት በጣም የሚነደውን የቃጫ መሰል ዛፍ(aleo) እንጨት ነው ..."
- 2፡25 እና 3፡15 "እነዚያ ያመኑትንና መልካሞችንም የሰሩትን ... ከርስዋ ከፍሬ (ኣይነት) ሲሳይን በተመገቡ ቁጥር (ፍሬዎችዋ ስለሚመሳሰሉ) ይህ ያ ከአሁን በፊት የተመገብነው ነው ይላሉ:: እርሱንም ተመሳሳይ ሆኖ ተሰጡ::"
- 83፡23-27 "በባለ ኣንበር ኣልጋዎች ላይ ኾነው ይመለከታሉ:: በፊቶቻቸው ላይ የድሎትን ውበት ታውቃለህ:: ተጣርቶ ከታተመ ጠጅ ይጠጣሉ:: ማተሚያውም ምስክ ከሆነ፤ በዚህም ተሸቀዳዳሚዎች ይሸቀዳደሙ:: መበረዣውም ከተስኒም ነው::"
- 76፡17 "በእርስዋም መበረዣዋ ዘንጀቢል የሆነች ጠጅ ይጠጣሉ::"
- 43፡71-73 "ከወርቅ የኾኑ ሰፋፊ ዝርግ ሳሕኖችና ኩባያዎች በነርሱ ላይ ይዝዞራሉ:: በእርስዋም ውስጥ ነፍሶች የሚከጅሉት፣ ዓይኖችም የሚደሰቱበት ሁሉ አልለ ... ለእናንተም በውስጥዋ ብዙ ፍሬዎች በርግጥ ዘውታሪዎች ናችሁ::"

ይሁን እንጂ መብላትና መጠጣት ካለ መፀዳዳትም ሊኖር ነው፣ ገነት ደግሞ ሽንት ቤት የለም፣ በዚህም ነብዩ ሙሐመድ "ሰዎች የሚበሉትና የሚጠጡት ሁሉ የሚወጣው በላብና በግሳት ነው" ብሏል (ሳሂህ ሙስሊም 4፡6798, ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡544)፣ ይህም ኣያስኬድም እንደዛ ከሆነ ሙሐመድ የተመለከተው በላብና በግሳት የተሞላ ግማታም ገሀነም እንጂ ገነት ኣይደለም፣ ይህ ስህተት የመጣው ገነትን በስጋዊ ዓይን ከመመልከት ነው::

ሙሐመድ ጀነትን ያሰባት በስጋዊ ሁኔታና በዘመኑ በነበረ የቅንጦት ኑሮ ምስል እንጂ ወደ ፈጣሪ በምትሄደው የነፍስ ማንነትና ፍላጎት ኣይደለም፣ ስጋዊ እይታውም ቢሆን የሁሉም ትውልድ እውነታ ኣይደለም፣ ያንን ትውልድ የሚያጓጓ እነኚህ ጠግቦ መብላት፣ መጠጣት፣ መስባት፣ በደንብ የሚነዱ እንጨቶችን መሞቅ፣ በወርቅ ማበጠሪያ፣ በወርቅና የሲልቨር እቃዎች መጠቀም ነበረ፣ ለዚህ ትውልድ ደግሞ እነዚህ ትርጉም የላቸውም ይባሱኑም የዚህ ትውልድ ፍላጎት ኣለመስባት፣ "ሼፕ/ቅርፅ" እንዳይበላሽበት ምግብ በመቀነስና ጤናማው የቪጂቴሪያን ኣመጋገብ ስልት ነው::

ይሁን እንጂ ወደ ፈጣሪ ሄዳ ገነት ትግባ ሲኦል ትግባ ፍርድ የምትቀበለውም ነፍስ ናት(ከታች በዝርዝር ቀርቧል)፣ በዚህም በስጋ እይታ የቀረበው የቁርኣኑ የጀነት ኣስተምህሮ እውነታውን በመሳቱ ምን ያህል እርስ በራሱ እንደተምታታ እንመለከታለን::

- **<u>ሴክስ በጀነት</u>**

እስልምና በጀነት ሴክስ እንዳለ ያስተምራል፡-

> 52፡20-25 "በተደረደሩ አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ኾነው (በገነት ይኖራሉ)፡፡ ዓይናማዎች በኾኑ ነጫጭ ሴቶች <u>እናጠናዳቸዋለን</u> … ለነርሱም የኾኑ ወጣቶች ልክ የተሸፈነ ሉል መስለው በእነርሱ ላይ (ለማሳለፍ) ይዘዋወራሉ፡፡ ሚጠያየቁ ኾነው ከፊላቸው በከፊሉ ላይ ይዞራል፡፡"
>
> ተመሳሳይ ሐሳብ 44፡54, 56፡22 … ስፍራዎች ላይ እናገኛለን፡፡

በርግጥ ይህ በ2.2 ክፍል ስር እንደቀረበው ምድራዊዎቹ ሴቶች የእስልምና ገነት ስለማይገቡ ይህ ጉዳይ የሚመለከተው ወንዶችን ብቻ ነው፣ ለወንዶቹ የሚዘጋጁት ሴቶች ምድራዊ ሳይሆኑ "ሁሪ/ሁረል ኤይን" የሚባሉ መላዕክት መሆናቸውን በዚሁ ክፍል ተመልክተናል፡፡ ይሁን እንጂ በገነት "አለ" የተባለው የሴክስ ጉዳይ ግን እንግዳ ነገር ነው፣

- ጃሚያ አት ትርሚዲ 2562 "… በገነት ዝቅተኛ ስፍራ ያለ ሰው <u>72 ሚስቶች</u> ኖሩታል፡፡"
- ጃሚ አት ቲርሚዲ 2536 "በገነት ውስጥ ወንዶች <u>የአንድ መቶ ሰዎች</u> የሴክስ ችሎታ ይሰጣቸዋል፡፡"
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡402 "በገነት ውስጥ አንድ ትልቅ 60 ማይል ስፋት ያለው አዳራሽ አለ፣ በየኮርነሩ ሌሎቹን ሚስቶችን የማያዩ ሚስቶች ተቀምጠዋል፣ እና አማኞችም እየሄዱ እየነበኙዋቸው ይደሰቱባቸዋል፡፡"

በዚህም ሙስሊም ወንድ ጀነትን የሚያስበው እንትኑ ቆሞበት ነው፡፡

ነገር ግን ይህ በገነት የተነገረው የሴክስ ጉዳይ ስጋዊ እንጂ ነፍሳዊ/መንፈሳዊ ካለመሆንም አልፎ ከቁርአኑም ጋር ይጋጫል፡-

1. በመጀመሪያ ቁርአኑ እንደሚለው አደምና ሀዋ ሴክስ የጀመሩት በሰይጣን ከተታለሉ በኋላ ነው፣

> 7፡20 "ሰይጣንም ከሀፍረተ ገላቸው የተሸሸገውን ለእነርሱ ሊገልፅባቸው በድብቅ ንግግር ጎተጎታቸው … ከዛፉቱም በቀመሱ ጊዜ ሀፍረተ ገላቸው ለሁለቱም ተገለፀላቸው፡፡"

በዚህም በቁርአኑ መሠረት የሴክስ ነገር የተገለፀው በሰይጣን ምክንያት መሆኑንና የመባረራቸው ምክንያትም እሱ ሆኖ እያለ አሁንም ወደ ገነት ሲመለሱ ወደዚህ ሰይጣን ወደ ገለጠውና ለመባረራቸው ምክንያት ወደሆነው ነገር ይመለሳሉ ማለቱ ስህተት ነው፡፡

2. አደም በገነት በነበረበት ጊዜ አንዲት ሀዋ እንጂ 72 ሀዋዎች አልነበሩትም፣ ይህ የአደምና ሃዋ ታሪክ ብቻ ሳይሆን ቋሚ የፈጣሪ አሰራር በመሆኑም በሁሉም ትውልድ

ውስጥ ያለው የወንድና የሴት ምጣኔ አንድ ለአንድ ነው፣ በዚህም "ሚስቶች" የሚለውም ሐሳብ ከፈጣሪ አለራር መርህ አንፃር ስህተት ነው።።

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ የቁርአን "የገነት ሴክስ" አስተምህሮ ወደ ፈጣሪ ሄዳ ፍርድን ስለምትቀበለው ነፍስ ፍላጎት ሳይሆን በስጋዊው የሴክስ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ትንታኔ ነው፣ "ሚስቶች" የሚለው አገላለፅ ደግሞ ከፈጣሪ አለራር ጋር የሚጋጭ አስተምህሮ ነው።።

- **<u>ገሀነም በእስልምና</u>**

እንደ ገነት ሁሉ ሙሐመድ ገሀነምን የተመለከተው በስጋዊ ዓይን ነው ነገር ግን ነብዩ ገሀነምን ለመሳል የሞከረው ከገነት በተቃራኒ ምስሉን በማበላሸት ነው፣ በዚህም ስለ ገሀነም አመጋገብ ከላይ ካየናቸው ጥራቶች በተቃራኒው በሚያስጠሉ ምስሎች ቀርበዋል፣

- 56፡51-55 "... እናንተ ጠማሞች አስተባባዮች ሆይ! ከዘቁም ዛፍ በርግጥ በይዎች ናቸሁ።። ከርስዋም ሆዶቻችሁን ሞይዎች ናችሁ።። በርሱ ላይም ከፈላ ውሀ ጠጪዎች ናችሁ።። የተጠሙንም ግመሎች አጠጣጥ ብጤ ጠጪዎች ናችሁ።።"
- 88፡4-7 "ተኳሳን እሳት ይገባሉ።። በጣም ከፈላች ምንጭ ይጋታሉ።። ለእነርሱ ዶሪዕ ከሚባል (እሾሃም) ዛፍ እንጂ ሌላ ምግብ የላቸውም።። <u>የማያሰባ</u> ከረሃብም የማያብቃቃ ከኾነው።።"
- 37፡64-66 "(የዘቁም ዛፍ) እርስዋ በገሀነም አዘቅት ውስጥ የምትወጣ ዛፍ ናት፣ <u>እንቡጧ ልክ የሰይጣን ራሶች</u> ይመስላል፣ እነርሱ ከርሷ በይዎች ናቸው፣ ሆዶችን ከእርሷ ሞይዎች ናቸው።።"
- 47፡15 "... ሞቃትን ውሀ እንደተጋቱ፣ አንጀቶቻቸውንም ወዲያውኑ እንደቆራረጠው ..."
- 56፡41-44 "የግራ ጓደኞችም ምንኛ(የተዋረዱ) የግራ ጓዶች ናቸው፣ በመርዛ ንፋስ በጣም በፈላ ውሀ ውስጥ ናቸው፣ ከጥቁርም ጭስ በሆነ ጥላ ውስጥ፣ ቀዝቃዛ መልካምም ያልሆነ ..."
- 69፡36 "ምግብም ከእሳት ሰዎች እጣቢ (እዥ) በስተቀር የለውም።።"

እነኚህ ሁሉ ትንታኔዎች የነፍስ ጉዳይ ሳይሆኑ ስጋዊ ጉዳዮች ናቸው፣ በተጨማሪም እነዚህ ስጋዊ ጉዳዮች የተቃኙትም በነሙሐመድ ዘመን ባለው የችግር ምስሎች እንጂ አጠቃላይ እውነታ አይደለም፣ "የሰይጣን ራሶች የመሰለ ምግብ" የሚለው ደግሞ አስቂኝ ነው።።

ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ከገሀነም ጋር በተያያዘ ስለሚኖረው ሴክስ ቁርአኑ ምንም አይናገርም፣ ትክክለኛ ያልሆኑት ጾታዊ ግንኙነቶችን ገነት ውስጥ ስላስገባ በገሀነም ውስጥ ጾታዊ ግንኙነት ጥላሸት የሚቀባበትን ምንም መንገድ አላገኘም፣ በገሀነም ሴክስ መኖሩን

አለመናገሩ አንዳንድ ሰዎች ገሀነምን መልካም ስፍራ አድርገው እንዳይመለከቱ ያደረገው ጥንቃቄ ሊሆን ይችላል ¡

በአጠቃላይ ስንመለከት እነዚህ በቁርአኑ የተሰጡት የገነት-ገሀነም ትንታኔዎች የቀረቡት በስጋዊ እይታ እንጂ ከነፍስ ማንነት አንፃር አይደለም፣ ነገር ግን ወደ ፈጣሪ ሄዳ ፍርድዋን የምትቀበለው ነፍሳዊ ማንነት እንጂ ስጋዊ ማንነት እንዳልሆነች ቁርአኑ በሌላ ስፍራ ላይ ደግሞ ይናገራል፣

- 9፡27-30 “(ለአመነች ነፍስም) “አንቺ የረካሺው ነፍስ ሆይ! “ወዳጅ ተወዳጅ ሆነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ:: በባሮቼ ውስጥ ግቢ:: ገነቴንም ግቢ፤” (ትባላለች)::”
- 74፡38 “ነፍስ ሁሉ በሰራችው ስራ ተያዥ ናት::”
- 50፡21 “ነፍስም ሁሉ ከእርስዋ ጋር ነጂና መስካሪ ያለባት ኾና ትመጣለች::”
- 75፡14 “በርግጥ ሰው በነብሱ ላይ አስረጅ ነው (አካሎቹ ይመሰክሩበታል)::”
- 73፡20 “... ከመልካም ስራም ለነፍሶቻችሁ የምታስቀድሙትን ሁሉ እርሱ የተሻለና በምንዳ ታላቅ ሆኖ አላህ ዘንድ ታገኙታላችሁ::”

ዛሬም እንደምንመለከተው ሰው ሲሞት ስጋው እዚህ ቀርቶ ነው ነፍሱ ወደ ፈጣሪ የምትሄደው፣ ይህንንም በሞቱት ሰዎች ላይ መመልከት እንችላለን፣ ቁርአኑም ስለሞቱትና ስጋቸው ተቀብሮ ነፍሳቸው ወደ ፈጣሪ ስለሄዱት ሰዎች ይናገራል፣

- 83፡22 “እውነተኞቹ ምዕመናን በእርግጥ በድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው::”
- 3፡169 “እነዚያ በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሙታን አድርገህ አትገምታቸው:: በእርግጥ እነሱ እጌታቸው ዘንድ ህያዋን ናቸው፤”
- 43፡74-76 “አመፀኞች በገሀነም ስቃይ ውስጥ ናቸው ... አልበደልናቸውምም፤ ግን በዳዮቹ እነርሱው ነበሩ::”

በዚህም ምንም እንኳን ሰዎች ሲሞቱ ስጋቸው እዚህ ቢቀርም በነፍሳቸው(በመንፈሳዊው ማንነታቸው) ግን ገነት ወይንም ገሀነም ውስጥ እንዳሉ እንመለከታለን::

በዚህም ሰው ሲሞት ወደ ገነት/ገሀነም የምትሄደው ነፍስ መሆኗ ግንዛቤ ውስጥ ሳይገባ፣ ስለገነት ተድላና ስለ ገሀነም ጭንቅ፣ በስጋ አዕምሮ ገምቶ ትንታኔ መስጠቱ ስህተት መሆኑንና ቁርአኑም ላይ እርስ በርስ ግጭቶች እንደፈጠረ እንመለከለታለን:: ከሁሉ በላይ ደግሞ ቁርአኑ ነፍሳዊ ሽልማቶችና ቅጣቶችን አለማወቁ በራሱ ቁርአኑ ሰውኛ ፈጠራ መሆኑን በራሱ ላይ የመሰከረበትን እውነታ ነው የተመለከትነው::

ከላይ በሰፊ ትንታኔ የቀረበው፣ ቁርአን ምን ያህል እርስ በርሱ እንደሚጋጭ ለማሳየት ነው ነገር ግን በዚህ መልክ እየተነተኑ መሄዱ በጣም ስለሚሰፋ ሌሎቹን እርስ በርስ ግጭቶቹን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን::

1. <u>የአላህ ዙፋን የት ነው?</u>

<u>ካዕባ</u>

2፡158 "... ቤቱን(ካዕባን) በሐጅ ወይም በዑምራህ ስራ ለጎበኘ ሰው..."

<u>በምድር ላይ የፀሐይ መግቢያ ጉድጓድ አጠገብ</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡421 አቡ ዳር እንደተረከው፡ ነብዩ በፀሐይ መጥለቂያ ጊዜ "ፀሐይ ስትጠልቅ የት እንደምትሄድ ታውቃለህ" አለኝ እኔም "ይህን በደንብ የሚያውቁት አላህና ነብዩ ናቸው" አልኩት፣ እሱም "የአላህ ዙፋን ስር ገብታ <u>እስከትተኛ</u> ትሄዳለች ..."

<u>በመንግሥተ ሰማይ በፍየሎች ጀርባ ላይ</u>

አቡ ዳውድ 4723 "በመንግሥተ ሰማይ(heaven) እና በመሬት መካከል ያለው ርቀት 71 <u>ወይ</u> 72 <u>ወይ</u> 73 <u>አመታት</u> ነው፣ በሰባቱም መንግሥተ ሰማያት መካከል ያለው የእርስ በርስ ርቀትም እንደዚሁ ነው፣ ከሰባተኛው መንግሥተ ሰማይ በላይ ውቅያኖስ አለ፣ የውቅያኖሱ ጠለልና ወለል በሁለት መንግሥተ ሰማያት መካከል ያለ ርቀት ያክላል፣ ከዚያ በላይ ስምንት የተራራ ፍየሎች አሉ፣ የፍየሎቹ ኮቴና ጉልበት መካከል ያለው ርቀትም በሁለት መንግሥተ ሰማያት መካከል ያለ ርቀት ያክላል፣ በጀርባቸውም ላይ ዙፋን አለ፣ የዙፋኑ ቁመት የሁለት መንግሥተ ሰማያት መካከል ያለ ርቀት ነው፣ አላህም ያለው በዚያ ላይ ነው።"

2. <u>የአላህን ዙፋን የሚሸከሙት እነማን ናቸው?</u>

<u>ፍየሎች</u>

አቡ ዳውድ 4723 "... ስምንት የተራራ ፍየሎች አሉ ... በጀርባቸውም ላይ ዙፋን አለ ... አላህም ያለው በዚያ ላይ ነው።"

<u>መላዕክት</u>

አቡ ዳውድ 4727 "... የአላህን ዙፋን ከተሸከሙት <u>መላዕክት</u> ከአንዱ ጋር እንድነጋገር ፍቃድ ተሰጠኝ፣ የመልአኩ ጆሮና ትከሻው መካከል ያለው ርቀት 700 አመታት ያህል ይርቃል።"

69፡17 "መላዕክትም በየጫፎቸዋ ላይ ይሆናሉ። የጌታህንም ዐርሽ በዚያን ቀን ስምንት መላዕክት ከበላያቸው ይሸከማሉ።"

<u>እነ ሙሴ</u>

ሳሂህ ሙስሊም 30፡5853፣ ሳሂህ ሙስሊም 30፡5854 "... በዚያን ቀን ሙሴ የዙፋኑን ጠርዝ ይይዛል ..."

3. <u>አላህ ሊታይ ይችላል?</u>

<u>ሊታይ ይችላል</u>

53፡11-13 "(ነብዩ በዓይኑ) ያየውን ልቡ አልዋሸም። ታዲያ በሚያየው ላይ ትከራከሩታላችሁን፣ በሌላይቱ መውረድ ጊዜ በእርግጥ አይቶታል።"

ሊታይ አይቻልም

6፡103 “(አላህን) ዓይኖች አያገኙትም፤ (አያዩትም)።”

4. <u>አላህ ለሰዎች በቀጥታ ይናገራል?</u>

<u>አዎን ይናገራል</u>

- 4፡164 “... አላህም ሙሳን ማነጋገር አነጋገረው።”
- 2፡253 “እነዚህን መልዕክተኞች ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ አበለጥን፣ ከነርሱ ውስጥ አላህ ያነጋገረው አለ።”

<u>አይናገርም</u>

42፡51 “ለሰውም አላህ በራዕይ ወይም ከግርዶ ወዲያ፣ ወይም መልዕክተኛ (መልአክን) የሚልከና በፈቃዱ የሚሻውን ነገር የሚያወርድለት ቢኾን እንጂ (በገሀድ) ሊናግረው ተገቢ አይደለም።”

5. <u>አላህ ቃሉን ይለውጣል ወይስ አይለውጥም?</u>

<u>አይለውጥም</u>

10፡64 “... የአላህ ቃላት መለወጥ የላትም፤”

<u>ይለውጣል</u>

2፡106 “ከአንቀፅ <u>ብንለውጥ</u> ወይም እርሷን ብናስረሳህ <u>ከርሷ የሚበልጥ ወይም ብጤዋን</u> <u>እናመጣልሀለን</u>።”

6. <u>አላህ የሽርክ (የማጋራት) ኃጢያትን ይቅር ይላል?</u>

<u>ይቅር አይልም</u>

4፡116 “አላህ በርሱ የማጋት ወንጀልን አይምርም።”

<u>ይቅር ይላል</u>

4፡153 “(የመጽሐፉ ሰዎች) ... ከዚያም ተአምራቶች ከመጡላቸው በኋላ ወይፈኑን (አምላክ አድርገው) ያዙ። ከዚያም ይቅር አልን።”

7. <u>አላህ ፍርድ የሚሰጠው ምን ላይ ተመርኩዞ ነው?</u>

<u>“አላህ ሁሉን አዋቂ” በመሆኑ በራሱ እውቀት</u>

10፡18 “... አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን...”

<u>የሰውን ስራ በሚዛን ሰፍሮ</u>

21፡47 “በትንሳኤም ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን። ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም። (ስራው) የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢኾንም እርስዋን እናመጣታለን። ተቆጣጣሪዎችም በኛ በቃ።”

ተመሳሳይ ሐሳቦችንም በ7፡8-9, 7፡13, 18፡49, 21፡47, 17፡71, 23፡101-103, 99፡7 ... ስፍራዎች ላይ ተመልከቷል።

<u>በኢሳ ምስክርነት</u>

4፡159 “... (ኢሳ) በትንሳኤ ቀን በነሱ(በመጽሐፉ ሰዎች) መስካሪ ይሆናል።”

በሰውየው የአካል ክፍሎች ምስክርነት

41፡22 “ጆሮዎቻችሁ ዓይኖቻችሁና ቆዳዎቻችሁም በእናንተ ላይ ከመመስከራቸው የምትደበቁ አልነበራችሁም፡፡”

ታድያ ምስክር የሚሆነው የትኛው ነው? ሁሉም እንዳንል ተጨማሪ ምስክር የሚጠራው የአንዱ ምስክርነት ብቻውን አስተማማኝነት ከሌለው ነው ይባሱኑ ደግሞ “ሁሉን አዋቂው” ጋር የምስክር አስፈላጊነት ደግሞ የበለጠ ግራ አጋቢ ነገር ነው፡፡

8. ፍርድ የሚሰጠው ሰዎች እንደሞቱ ነው ወይስ በፍርድ ቀን?

እንደሞቱ

83፡22 “እውነተኞቹ ምዕመናን በእርግጥ በድሎት (ገነት) ውስጥ ናቸው፡፡”

43፡74-76 “አመፀኞች በገሀነም ስቃይ ውስጥ ናቸው … አልበደልናቸውምምን፤ ግን በዳዮቹ እነርሱው ነበሩ፡፡”

በፍርድ ቀን

83፡4-6 “እነዚያ እነርሱ ተቀስቃሾች መኾናቸውን አታውቁምን? በታላቁ ቀን፡፡ ሰዎች ሁሉ ለዓለማት ጌታ(ፍርድ) በሚቆሙበት ቀን(ተቀስቃሾች መሆናቸውን)፡፡”

19፡66-67 “ሰውም “በሞትሁ ጊዜ ወደፊት ሕያው ሆኜ(ከመቃብር) እወጣለሁን” ይላል፡፡ ሰው ከአሁን በፊት ምንም ነገር ያልነበረ ሲሆን እኛ የፈጠርነው መሆኑን አያስታውስምን?”

30፡19 “ሕያውን ከሙት ያወጣል፡፡ሙታንም ከሕያው ያወጣል፡፡ ምድርንም ከሞተች በኋላ ሕያው ያደርጋታል፡፡ እንደዚሁ (ከመቃብር) ትወጣላችሁ፡፡”

9. አማላጅ ማነው?

አላህ ብቻ ነው ሌላ አያስፈልግም

- 6፡51 “… ከአላህ **ሌላ** አማላጅ የለም …”
  ተመሳሳይ ሐሳብም 6፡70, 32፡4, 39፡44 ላይ ቀርቧል፣
- 10፡18 “… እነዚህም አላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ፤ አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን በላቸው …”
- 39፡43 “ይልቁንም (ቁረይሾች) ከአላህ ሌላ አማላጆችን ያዙ … ምልጃ መላውም የአላህ ብቻ ነው፡፡”
- 39፡7 “… ማንኛይቱም ኃጢያት ተሸካሚ ነፍስ የሌላይቱን ኃጢያት አትሸከምም፡፡”
  ተመሳሳይ ሐሳብም 53፡38, 17፡15, 6፡164 ላይም ቀርቧል፣

ሰዎች

- 9፡103 “ከገንዘቦቻቸው ስትሆን በርስዋ የምታጠራቸውና የምታፋፋቸው የሆነችን ምፅዋት ያዝ ለነሱም ፀልይላቸው፤ ፀሎትህ ለነሱ እርካት ነውና አላህም ሰሚ አዋቂ ነው፡፡”
- 60፡4 “(ኢብራሂም ለአባቱ) ደህና ሁን፡፡ ወደፊት ከጌታዬ ምሕረትን እለምንልሃለሁ፡፡ እርሱም ለኔ በጣም ሩህሩህ ነውና፣ አለ፡፡”

ተመሳሳይ ሐሳብም በ9፡114 እና 19፡47 … ላይ ቀርቧል፡፡

- 7፡155-156 ላይ ሙሳ ስለ ህዝቡ የምልጃ ፀሎት ሲያቀርብና አላህም ይቅርታ ሲያደርግ እንመለከታለን፡፡

<u>አርሹን የሚሸከሙት</u>

40፡7 “እነዚያ አርሹን የሚሸከሙት … ለተፀፀቱት መንገድህንም ለተከተሉት ምህረት አድርግላቸው … እያሉ ለእነዚያ ላመኑት ምህረትን ይለምናሉ፡፡”

<u>መላዕክት</u>

53፡26 “በሰማያት ውስጥ ካለ መልአክም ብዙዎች (ሊማለዱለት) ለሚሻውና ለሚወደው ሰው ከፈቀደ በኋላ ቢኾን እንጂ ምልጃቸው ምንም አትጠቅምም፡፡”

10. <u>ሰዎች ገሀነም እንዲገቡ ምክንያት የሆነው ማነው?</u>

<u>አላህ</u>

35፡8 “… አላህ የሚሻውን ሰው ያጠማል …”

<u>ሰይጣን</u>

15፡39 “(ኢብሊስም) … ለነርሱ በምድር ላይ (ኃጢያትን) እሸልምላቸዋለሁ፣ ሁሉንም አጠማቸዋለሁ፡፡

<u>ሰዎች እራሳቸው</u>

30፡9 “… መልዕክተኞቻቸውም በተአምራት መጡባቸው (አስተባበሉምና ጠፉ)፣ አላህም የሚበድላቸው አልነበረም፣ ግን ነፍሶቻቸውን ይበድሉ ነበረ፡፡”

11. <u>በፍርድ ቀን ሰዎች ኃጢያተኞች መዘገባቸው ምኑ ጋር ይደረግላቸዋል?</u>

<u>በጀርባቸው</u>

84፡10 “መጽሐፉን በጀርባው ኋላ የተሰጠውማ፤ (ዋ ጥፋቴ በማለት) ጥፋትን በርግጥ ይጠራል፡፡”

<u>በግራ እጃቸው</u>

69፡25 “መጽሐፉን በግራ የተሰጠውማ (ዋ ጥፋቴ) ምነው መጽሐፌን ባልተሰጠሁ ይላል፡፡”

12. <u>የገሀነም ሰዎች ምግብ ምንድነው?</u>

<u>ዶሪዕ ብቻ</u>

88፡6 “… ለእነርሱ ዶሪዕ ከሚባል (እሾሃም) ዛፍ <u>እንጂ ሌላ ምግብ የላቸውም</u>፡፡”

<u>የቁስል እጣቢ ብቻ</u>

69፡36 “ምግብም ከእሳት ሰዎች እጣቢ (እኸር) <u>በስተቀር የለውም</u>፡፡”

<u>ዘቁም ነው</u>

37፡64-66 “እርስዋ በገሀነም አዘቅት ውስጥ የምትወጣ ዛፍ ናት፡፡ እንቡጣ ልክ የሰይጣናት ራሶች ይመስላል፡፡ እነርሱም ከርስዋ በይዎች ናቸው፤ ሆዶችንም ከእርስዋ ሞይዎች ናቸው፡፡”

13. <u>ተራሮች በቂያማ ቀን(በመጨረሻው ቀን) ምን ይሆናሉ?</u>

<u>እንደ ተነከረ ሱፍ ይሆናሉ</u>

70፡9 “ጋራዎችም በተለያዩ ቀለማት እንደ ተነከረ ሱፍ (ነፋስ እንደ ሚያበረው) በሚኾኑበት ቀን፡፡”

<u>ነደው ይጠፋሉ</u>

78፡20 “ጋራዎች በሚነዱበት(እንደ) ሲሪብዱም በሚኾኑበት (ቀን) …”

14. <u>ስንት ገነቶች አሉ?</u>

<u>አንድ</u>

57፡21 “ከጌታችሁ ወደ ኾነች ምሕረት፣ ወርዷ እንደ ሰማይና ምድር ወርድ ወደ ሆነች ገነት ተሸቀዳደሙ፡፡”

<u>ሁለት</u>

55፡46 “በጌታው ፊት መቆምን ለፈራ ሰው ሁለት ገነቶች አሉት፡፡”

<u>አራት</u>

55፡62 “ከሁለቱ ገነቶችም ሌላ ሁለት ገነቶችም አሉ፡፡”

15. <u>የአላህ አንድ ቀን በሰው ስንት ቀን ነው?</u>

<u>አንድ ሺ</u>

22፡47 “… እጌታህም ዘንድ አንዱ ቀን ከምትቆጥሩት (ቀን) አንድ ሺ አመት ነው፡፡”

<u>ሀምሳ ሺ</u>

70፡4 “መላዕክቱና መንፈሱም <u>ልኩ</u> አምሳ ሺ <u>በሆነ ቀን</u> ውስጥ ወደ እርሱ ያርጋሉ(ይወጣሉ)፡፡”

16. <u>ፍጥረታት በምን ያህል ጊዜ ተፈጠሩ?</u>

<u>በስድስት ቀን</u>

25፡59, 50፡38, 57፡4 … “ያ ሰማያትን ምድርን በመካከላቸው ያለውን ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ፣”

<u>ከስድት ቀን በላይ</u>

41፡9-12 “በላቸው፣ እናንተ በዚያ ምድርን በሁለት ቀኖች ውስጥ በፈጠረው አምላክ በርግጥ ትክዳላችሁን … በውስጥዋም ምግቦችዋን(ካለፉት ሁለት ቀኖች ጋር) በአራት ቀናት ውስጥ ለጠያቂዎች ትክክል ሲሆኑ ወሰነ፡፡ ከዚያም ወደ ሰማይ <u>ጭስ ሆና ሳለች</u> አሰበ፡፡ ለእርስዋም ለምድርም “ወዳችሁም ሆነ ጠልታችሁ <u>ኑ</u>” አላቸው፡፡ “<u>ታዛዦች ሆነን መጣን</u>” <u>አሉ</u>፡፡ በሁለት ቀኖች ውስጥ ሰባት ሰማያት አደረጋቸው፡፡”

እዚህ ጋር ስድስት የፍጥረታት ቀኖችን በግልፅ እንመለከታለን ነገር ግን በ5ኛውና በ6ኛው ቀን ሰማይን ሲዘረዝር በመጀመሪያ ጭስ መስላ ተፈጥራ የነበረችውና ሲጠሩም “ታዛዦች ሆነን መጣን”፣ “አሉ” የተባሉትና ቀድሞውኑ ተፈጥረው የነበሩትን የፍጥረት ጊዜ ስናስብ የፍጥረት ቀናት ከ6ቀናት በላይ መሆኑን እንረዳለን፡፡

17. <u>ከሰማይና ከምድር ቀድሞ የተፈጠረው የትኛው ነው?</u>

<u>ምድር</u>

2፡29 “እርሱ ያ በምድር ያለውን ሁሉ ለእናንተ የፈጠረ ነው፡፡ ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ፤ ሰባት ሰማያትም አደረጋቸው …”

<u>ሰማይ</u>

79፡27-30 “ባፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይንስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት፣ ከፍታዋን አጓነ፤ አስተካከላትም፡፡ ሌሊንም አጨለመ፡፡ ቀንዋንም ገለፀ፡፡ ምድርንም ከዚያ በኋላ ዘረጋት፡፡”

18. <u>ሰው ከምን ተፈጠረ?</u>

<u>ከጭቃ</u>

- 15፡26 “ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው፡፡”
- 55፡14 “ሰውን እንደ ሸክላ ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ ፈጠርነው፡፡”

<u>ከውሀ</u>

25፡54 “እርሱም ያ ከውሀ ሰውን የፈጠረ፣”

ተመሳሳይ ሐሳቦችም በ21፡30 እና 24፡45 ላይ ቀርቧል፡፡

<u>ከአፈር</u>

30፡20 “እናንተንም ከአፈር መፍጠሩ …”

<u>ከፍትወት ጠብታ</u>

16፡4 “ሰውን ከፍትወት ጠብታ ፈጠርነው፡፡”

ተመሳሳይ ሐሳቦች 30፡54 እና 36፡77 ላይ ቀርቧል፡፡

<u>ከረጋ ደም</u>

96፡2 “ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)፡፡”

<u>ከተለያዩ ነገሮች</u>

- 23፡12-14 “በርግጥ ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው፡፡ ከዚያም በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፡፡ ቁራጭዋም ስጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፡፡ አጥንቶቹንም ስጋ አለበስናቸው፡፡ ከዚያም (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረት አድርገን አስገኘነው፡፡”
- 32፡7-9 “ያ የፈጠረውን ነገር ሁሉ ያሳመረው የሰውንም ፍጥረት ከጭቃ የጀመረው ነው፡፡ ከዚያም ዘሮቹን ከተንጣለለ፣ ከደካማ ውሀ ያደረገ ነው፡፡ ከዚያም (ቅርፁን) አስተካከለው፡፡ በርሱም ውስጥ ከመንፈሱ ነፋበት፤ (ነፍስ ዘራበት)፡፡
- 40፡67 “እርሱ ያ ከአፈር ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደም የፈጠራችሁ ነው፡፡”

19. <u>ልጅ በእናቱ ሆድ ውስጥ እውቀት አለው ወይስ የለውም?</u>

<u>የለውም</u>

16፡78 “አላህ ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ፡፡”

<u>አለው</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 8፡77፡597 “... የአላህ መልእክተኛ እንዳለው “ማንኛውም ህፃን ሲወለድ እስላም ሆኖ ነው፣ ነገር ግን ወላጆቹ ወደ ይሁዲነት ወይ ወደ ክርስትና ይቀይሩታል፡፡”

20. <u>ኑብያት እኩል ናቸው ወይስ ይበላለጣሉ?</u>

<u>እኩል ናቸው</u>

2፡285“... በመልዕክተኞቹም ከመልዕክተኞቹ በአንድም መካከል አንለይም፡፡”

<u>ይበላለጣሉ</u>

2፡253 “እነዚህን መልዕክተኞች ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ አበለጥን፣ ከነርሱ ውስጥ አላህ ያነጋገረው አለ፡፡”

21. <u>ቁርአን በሙሐመድ ላይ ተወረደ? ወይስ ሙሐመድ ላይ አልተወረደም?</u>

<u>ሙሐመድ ላይ የተወረደ ነው</u>

26፡194 “ከአስፈራዎቹ (ኑብያት) ትኾን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)፡፡”

የዚህን ተመሳሳይ ሐሳብ 21፡2, 39፡1-2, 39፡41 ... ስፍራዎች ላይ ቀርቧል፡፡

<u>አልተወረደም</u>

16፡64 “ባንተ ላይ መጽሐፉን አላወረድንም ...”

22. <u>ቁርአን በምን ያህል የጊዜ ርዝማኔ ወረደ?</u>

<u>በአንድ ለሊት</u>

- 44፡3 “እኛ (ቁርአኑን) በተባረከች ለሊት ውስጥ አወረድነው፡፡”
- 97፡1 “እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ለሊት አወረድነው፡፡”

<u>በረዥም የጊዜ ሂደት ተከፋፍሎ</u>

- 25፡32 “እነዚያ የካዱት “ቁርአን በእርሱ ላይ ለምን በጠቅላላ አንድ ጊዜ አልተወረደም” አሉ፡፡ እንደዚሁ በእርሱ ልብህን ልናረጋ (ከፋፍለን አወረድነው) ቀስ በቀስ መለያየትንም ለየነው፡፡”
- 17፡106 “ቁርአንንም በሰዎች ላይ በዝግታ ላይ ሆነህ ታነበው ዘንድ ከፋፈልነው፡፡ ቀስ በቀስ ማውረድም አወረድነው፡፡”
- 3፡3 “ከዕርሱ በፊት ያሉትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ ሲኾን መጽሐፉን(ቁርአንን) ባንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደ ...”

23. <u>ያለ መፅሐፍ ቅዱስ በቁርአን ብቻ ህዝብን መምራት ይችላል?</u>

<u>ይችላል</u>

21፡45 “የማስፈራችሁ በተወረደልኝ **ብቻ** ነው፡፡”

<u>አይቻልም</u>

ቁርአኑ ከመነሻው በአይሁድ/ክርስትና መጽሐፍትን ተደግፎ መነሳቱና ብዙ ታሪኮችንም የወሰደው ከመጽሐፍ ቅዱሱ ቀነጫጭቦ መሆኑ፣ ሌሎቹን ታሪኮች ደግሞ በቀጥታ ከአይሁድ/ክርስቲያን መጽሐፍት እንዲነበብ "አውሳ" (38፡48፣ 19፡16 ...)፣ "አስታውስ" (7፡171, 8፡32, 15፡28 ...) እያለ ማዘዙና ለሙሐመድም፣

> 40፡78 "ካንተ በፊት መልክተኞችን በርግጥ ልከናል፡፡ ከእነሱም ባንተ ላይ የተረከንልህ አልለ፡፡ ከእነርሱም ባንተ ላይ **ያልተረከነው አልለ**፡፡"

ማለቱና ሙሐመድም ሙስሊሞች ከቁርአኑ ያልገባቸውን ነገር ቢኖር ቀድሞ መጽሐፍ የወረደላቸውን አይሁድ/ክርስቲያኖችን ጠይቁ ማለቱ(21፡7) እስልምና መጽሐፍ ቅዱስን ጥሎ በቁርአን ብቻ መሄድ እንደማይችል እንመለከታለን፡፡

24. <u>ሙሐመድ መካ የቆየው ለምን ያል ጊዜ ነው?</u>

<u>ለ10 ዓመት</u> - ሳሂህ ቡኻሪ 7፡72፡787 "... መካ ለ10 አመት ሲቆዩ ..."

<u>ለ13 ዓመት</u> - ሳሂህ ቡኻሪ 5፡58፡242 "... ከዚያ መካ ለ13 አመታታ ቆየ ..."

<u>ለ15 ዓመት</u> - ሳሂህ ሙስሊም 30፡5809 "ሙሐመድ እንደ ነቢይ ከተገለጠ ቦሃለ በመካ 15 አመታት ቆየ"

25. <u>ሙሐመድ ቁርአንን ሙሉ በሙሉ በቃሉ ያውቃል?</u>

<u>አዎን ያውቃል</u>

87፡6 "(ቁርአንን)በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ አትረሳምም፡፡"

<u>ሙሉ በሙሉ አያውቅም፣ አንዳንዶቹን ሲረሳ ነበረ</u>

- ሳሂህ ቡኻሪ 1፡8፡394 "... እኔ እንደናንተው የሰው ልጅ ነኝና ልረሳ እችላለሁ፣ ስለዚህ እኔ ከረሳሁኝ አስታውሱኝ ..."
- ሳሂህ ሙስሊም 4፡1179፡ "... የአላህ መልዕክተኛም ... እኔኮ የሰው ልጅ ነኝ፣ እናንተ እንደምትረሱት እኔም እረሳለሁ ..."
- አቡ ዳዉድ 3970፣ አይሻ እንደተረከችው "አንድ ሰው ቂያማ እየሰገደና ድምፁንም ከፍ አድርጎ ቁርአን በቃሉ ይቀራ ነበረ፡፡ በነጋታው የአላህ መልዕክተኛ "አላህ ምህረቱን ያብዛልኝ ... ትላንት ማታ ስንትና ስንት አንቀፆችን አስታወሰኝ፣ ረስቻቸው ነበረ" አሉ"
- ሳሂህ ቡኻሪ 3፡48፡823፣ አይሻ እንደተረከችው "ነብዩ መዝጊድ ውስጥ ሆነው ቁርአን በቃሉ ይቀራ የነበረን ሰው ሰሙ፣ ከዚያ "አላህ ምህረቱ በኔ ላይ ይሁን... የረሳሁትን የቁርአን ብዙ ክፍሎች አስታወሰኝ" አሉ፡፡
- ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡449-450፣ እዚህ ስፍራ ላይ የምንመለከተው ለሙሐመድ ቁርአን ሲገለጥለት አላህ "እንዳትረሳ የምነግርህን ብቻ አዳምጥ፣ ስነግርህ ምላስህን አታንቀሳቅስ፣ ምላስህን ካንቀሳቀስክ የምትረሳው ክፍል ይኖራል" ማለቱና ሙሐመድ

ግን ቁርአኑን ሲቀበል ሳያውቅ ምላሱን ማንቀሳቀሱን እንመለከታለን፣ በዚህም የተረሱ የቁርአን ክፍሎች እንዳሉ ሀዲስ ምስክር ነው።።

26. <u>ሙሐመድ ከቁርአኑ መርሳቱ ቁርአናዊ ነው?</u>

<u>አይደለም</u>

87፡6 “(ቁርአንን)በእርግጥ እናስነብሃለን፤ <u>አትረሳምም</u>።።”

<u>አዎን</u>

2፡106 “ከአንቀፅ ብንለውጥ ወይም እርሷን <u>ብናስረሳህ</u> ከርሷ የሚበልጥ ወይም ብጤዋን እናመጣልሀለን።።”

27. <u>ከሙሐመድ በፊት እስልምና ነበረ?</u>

<u>አልነበረም</u>

- 22፡52 “ከመልክተኛና ከነቢይም <u>ከአንተ በፊት</u> አንድም አላክንም …”
- 6፡14 “… እኔ <u>መጀመሪያ</u> ትዕዛዝን ከተቀበለ ሰው ልሆን ታዘዝኩ …”
- 6፡163 “… እኔ የሙስሊሞች *መጀመሪያ* ነኝ።።”
- 39፡12 “የሙስሊሞች *መጀመሪያ* እንድሆን ታዘዝኩ።።”
- ሀዲሳት “እስልምና ከመምጣቱ በፊት” እያሉ መዘገባቸው ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡3, ሳሂህ ቡኻሪ 2፡26፡725, ሳሂህ ቡኻሪ 2፡15፡70, ሳሂህ ቡኻሪ 4፡52፡155, ሳሂህ ቡኻሪ 5፡57፡76, ሳሂህ ቡኻሪ 9፡88፡232 …

<u>ነበረ</u>

- 3፡67 “ኢብራሂም አይሁዳዊም ክርስቲያንም አልነበረም ግን ወደ ቀጥተኛ ኃይማኖት ተዘነበለ *ሙስሊም* ነበረ …”
- 61፡7 “ኢየሱስ ወደ ኢስላም የሚጠራ ሲኾን …”
- 22፡78 “… የአባታችሁን የኢብራሂምን ኃይማኖት ተከተሉ።። እርሱ ከዚህ በፊት *ሙስሊሞች* ብሎ ሰይሟችኋል።።”

28. <u>ከሙሐመድ በኋላ የሚመጣ ነቢይ አለ? ወይስ የለም?</u>

<u>የለም</u>

33፡40 “*ሙሃመድ* … የአላህ *መልክተኛና* የነቢዮች *መደምደሚያ* ነው።።”

<u>አለ</u>

“ማህዲ” የሚባለው ነቢይ(የአቡ ዳውድ ሱና 4285) እና ወደ ፈጣሪ የተወሰደው ነብዩ ኢሳ (ሳሂህ *ሙስሊም* 41፡6924, ሳሂህ *ሙስሊም* 1፡0289) ከ*ሙሐመድ* በኋላ ይመጣሉ።።

29. <u>ሳያበላልጡ በመያዝ ብዙ ሚስቶችን ማግባት ይቻላል?</u>

<u>ይቻላል</u>

4፡3 “… ከሴቶች ለእናንተ የተዋበላችሁን ሁለት ሁለት ሦስት ሦስትም አራት አራትም አግቡ።። <u>አለማስተካከልንም ብትፈሩ</u> አንዲትን ብቻ ወይም እጆቻችሁ ንብረት ያደረጉትን (ባሮችና ምርኮኞች) ያዙ …”

አይቻልም

4፡129 "... በሴቶችም መካከል ምንም እንኩዋ ብትጓጉ (በፍቅር) ለማስተካከል አትችሉም፡፡"

30. ዝሙት የተፈቀደ ነው?

የተፈቀደ ነው

4፡24 "ከሴቶችም (በባል) ጥብቆቹ እጆቻችሁ (በምርኮ) የያዙዋቸው ሲቀሩ በእናንተ ላይ እርም ናቸው ... ከዚያችሁም (ከተከለከሉት) ወዲያ ጥብቆች ሆናችሁ ዝሙተኛ ሳታሆኑ በገንዘቦቻችሁ ልትፈልጉ ለናንተ ተፈቀደ፡፡ ከእነሱም በርሱ(በመገናኘት) የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች ..."

ሀዲስም ሰዓት ሰጥቶ(ሳሂህ ሙስሊም 8፡3252)፣ ልብስ ሰጥቶ (ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡139) ዝሙት መፈፀም እንደሚቻል ይናገራል፡፡

የተከለከለ ነው

17፡32 "ዝሙትን አትቅረቡ፡፡ እሱ በርግጥ መጥፎ ስራ ነውና፡፡ መንገድነቱም ከፋ፡፡"

31. ያልሰለሙትን ሴቶች ማግባት ይቻላል?

አዎን

5፡5 "... ከምእመናት ጥብቆቹም ከእነዚያ ከእናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡ("ክርስቲያኖች") ሴቶች ጥብቆቹም፤ ዘማዊዎችና (ዝሙተኞች) የምስጢር ወዳጅ ያገርዎች ሳትሆኑ ጥብቆች ኾናችሁ መጎሮቻቻን በሰጣችኋቸው ጊዜ (ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው)፡፡"

አይቻልም

2፡221 "አጋሪዎች("ክርስቲያኖች") የሆኑ ሴቶች እስኪያምኑ ድረስ አታግቡአቸው፡፡"

32. ሙስሊም ክርስቲያን/አይሁድ ያረደውን መብላት ይፈቀድለታል?

ይፈቀዳል

5፡5 "... እነዚያም መጽሐፍን የተሰጡ ሰዎች(አይሁድ/ክርስቲያን) ምግብ(ያረዱት) ለእናንተ የተፈቀደ ነው፡፡"

አይፈቀድም - ክርስቲያን የሚያርደው "በስመ አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ብሎ ስለሆነ

2፡173 "በእናንተ ላይ እርም ያደረገው ... በእርሱም (ማረድ) ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ነገር ብቻ ነው፡፡"

6፡121 "በእርሱም ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ፡፡"

33. ከአይሁድ/ከክርስቲያን ከሲኦል የሚድኑ አሉ?

አዎን

2፡111-112 "ገነትንም አይሁድን ወይም ክርስቲያኖችን የሆነ እንጂ ሌላ አይገበባትም አሉ፣ ይህቺ (ከንቱ) ምኞታቸው ናት ... አይደለም ሌላውም ይገባባታል ..."

አያመልጡም

3፡85 “ከኢስላም ሌላ ኃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ፈፅሞ ከርሱ ተቀባይ የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ ነው፡፡”

34. ፍርድ ተላልፎበት ሲኦል የገባ ሰው የሚወጣበት መንገድ አለው

የለውም

ሲኦል የገባ አይወጣም 2፡167, 5፡36-37, 32፡14, 35፡36-37, 41፡28 …

አለው

የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት ያለው ከሲኦል እንዲወጣ ይደረጋል፣ ሳሂህ ቡኻሪ 8፡76፡564, ሳሂህ ቡኻሪ 8፡76፡565 …

35. በኃይኖማት ማስገደድ ይቻላል?

አይቻልም

2፡256 “በኃይማኖት ማስገደድ የለም፡፡”

ይቻላል

- 13፡15 “በሰማያትና በምድር ያሉት ሁሉ በውድም ሆነ በግድ ለአላህ ይሰግዳሉ፡፡”
- 48፡16 “… ትጋደሉዋላችሁ ወይም ይሰልማሉ፡፡”

36. ቅዱሳን መላዕክት በየትኛው ጾታ ይጠራሉ?

በሴት

3፡39 “(ዘከሪያ) በፀሎት ማድረሻ ክፍል ሆኖ ሲፀልይ መላዕክት ጠራችው “አላህ በየሕያ(በዮሐንስ) ከአላህ በሆነ ቃል የሚያረጋግጥ ጌታም ድንግልም ከደጋጎቹ ነቢይ ሲኾን ያበስርሀል” በማለት …”

በወንድ

53፡27 “እነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት መላዕክትን በሴት አጠራር ይጠራሉ፡፡”

37. መላዕክት ለቅጣት ብቻ ነው የሚወርዱት?

አዎን

15፡7-8 “ከእውነተኞች እንደሆንክ ለምን በመላዕክት(መስካሪ) ለምን አትመጣም(አሉ)፡፡ መላዕክትን በእውነት በቅጣት እንጂ አናወርድም፡፡”

አይደለም ለሌላ ስራም ይወርዳሉ

- 16፡2 “ከባሮቹ በሚሻውሰው ላይ መላዕክትን ከራዕይ ጋር ያወርዳል …”
- 53፡5 “(ሙሐመድን) ኃይሎቹ ብርቱው (መልአክ) አስተማረው፡፡”

38. ደመና የሚነዳው አላህ፣ መልአክ ወይስ ንፋስ?

- 24፡43 “አላህ ደመናን የሚነዳ መኾኑን አላየህምን…”
- ጃሚያ አት ቲርሚዲ 3117 “ከመላዕክት መሃከል ለደመናት ተጠያቂ የሆነው መልአክ ደመናትን የሚነዳበት ትንሽ እሳት አለው … የነጎድጓድ ድምፁም የሚወጣው መልአኩ ደመናውን ለመንዳት በሚመታው ግዜ ነው …”

39. ጂሃድ በተቀደሱ ወራት ይደረጋል?

አዎን

9፡36 “የወሮች ቁጥር አላህ ዘንድ … አስራ ሁለት ወር ነው፣ ከእነሱም አራቱ የተከበሩ ናቸው … በነሱ ውስጥም … ኣጋሪዎች በአንድ ላይ ሆነው እንደሚዋጉዋችሁ በአንድ ላይ ሆናችሁ ተዋጉዋቸው …”

አይፈቀድም

9፡5 “የተከበሩት ወሮችም ባለቁ ጊዜ ኣጋሪዎቹን(የሥላሴ አማኞችን) ባገኛችሁ ስፍራ ግደሉዋቸው፡፡”

40. ሰይጣን ከሰው ልጅ ሲነፃፀር በመጠን ምን ያክላል?

ረቂቅ

ሳሂህ ሙስሊም 26፡5404 “ደም ሰውነታችን ውስጥ እንደሚዘዋወረው፣ ሰይጣንም በሰውነታችን ውስጥ ይዘዋወራል፡፡”

በጣም ትንሽ

- ሳሂህ ሙስሊም 4፡7132 “… ስታፋሽጉ ሰይጣን እንዳይገባ በእጃችሁ ኣቃርጡ፡፡”
- ሳሂህ ሙስሊም 2፡462 “… ሰይጣን የለሊቱን ጊዜ ኣፍንጫችን ውስጥ ያሳልፋል፡፡”
- ሳሂህ ቡኻሪ 2፡21፡245 - አብዱላህ እንደተረኩት የሆነ ሰው ነብዩ ጋር ቀረበና እስከሚነጋ ድረስ እንደሚተኙና ለፀሎት እንኳን መነሳት እንደሚያቅተው ነገራቸው፣ ነብዩም “ሰይጣን በጆሮው ውስጥ ሸንቶበት ነው” አሉ፡፡

ትንሽ

37፡64-66 “እርስዋ በገሀነም አዘቅት ውስጥ የምትወጣ ዛፍ ናት፡፡ እንቡጧ ልክ የሰይጣናት ራሶች ይመስላል፡፡ እነርሱም ከርስዋ በይዎች ናቸው፤ ሆዶችንም ከእርስዋ ሞይዎች ናቸው፡፡”

መካከለኛ (እንደ ሰው)

- ሳሂህ ቡኻሪ 3፡38፡505 “… አቡ ሁራይራ ሰይጣንን ሲሰርቅ ያዙት…”
- 55፡56 “በውስጣቸው ከበፊታቸው (ከባሎቻቸው በፊት) ሰውም ጀንም ያልገሰሳቸው (ሴቶች) …”

በጣም ግዙፍ

ሰሂህ ቡኻሪ 9፡214 “… እዛ (ናጂድ በተባለው ስፍራ) የመሬት መንቀጥቀጥና የመቅሰፍት ስፍራ የሰይጣን ራስ ጎን የሚወጣበት ስፍራ ነው፡፡”

41. ሰይጣን ለገነት የተመረጡ ሰዎችን ማሳሳት ይችላል?

አይችልም

38፡82-83 “(ኢብሊስም) አለ “በአሸናፊነትህ ይሁንብኝ፤ በመላ አሳስታቸዋለሁ፡፡ ከእነርሱ ምርጥ ባሮችህ ሲቀሩ፡፡”

ይችላል (አማኞችን ማሳሳት ስለሚችሉ ለገሀነም ከታሰበው በላይ ሰዎችን ማስገባታቸው::) 6:128 "ኢጋንንት ጭፍሮች ሆይ! ከሰዎች(ጭፍራን በማጥመም) በርግጥ አበዛችሁ (ይባላሉ)::"

42. <u>የኑሕ(የኖህ) ልጅ ከጥፋት ውሀ(ጎርፍ) አምልጧል?</u>

<u>አዎን</u>

- 37:76-77 "እርሱንም (ኑሕን) ቤተሰቦቹንም ከከባድ ጭንቅ አዳንን:: ዘሮቹንም እነርሱን ብቻ ቀሪዎች አደረግን::
- 21:76 "ኑሕንም ከዚያ በፊት (ጌታውን) በጠራ ጊዜ (አስታውስ):: ለእርሱም (ጥሪውን ተቀበልነው:: እርሱንም ቤተሰቦቹንም ከከባድ ጭንቅ አዳን::"

<u>አላመለጠም</u>

11:42-43 "... ኑሕም ልጁን ከመርከቢቱ የራቀ ሆኖ ሳለ "ልጄ ሆይ ከኛ ጋር ተሳፈር ከከሃዲዎች አትሁን" ሲል ጠራው:: (ልጁም) "ከውሀው ወደ ሚጠብቀኝ ተራራ እጠጋለሁ አለ" ... ማዕበሉም በመካከላቸው ወረደ:: ከሰጣሚዎቹም ሆነ::"

43. <u>ፈርኦን ህፃናቱ እንዲገደሉ ያዘዘው መች ነው?</u>

<u>ሙሳ ነቢይ በነበረበት ጊዜ</u>

40:25 "(ሙሳ) ከእኛ ዘንድ እውነትን ይዞ በመጣላቸው ጊዜ "የእነዚያ ከእርሱ ጋር ያመኑትን ሰዎች ወንዶች ልጆች ግደሉ ... አሉ::"

<u>ሙሳ ህፃን በነበረበት ጊዜ፣ በዚህም እናቱ በሳጥን በባህር ላይ በሳጥን ጣለችው</u>

20:39-40 "(ህፃኑን) በሳጥን ውስጥ ጣይው፣ እርሱንም (ሳጥኑን) በባህር ላይ ጣይው:: ለእኔ ጠላት ለእርሱ ጠላት የሆነ ሰው ይይዘዋልና ... ከጭንቅም አዳንንህ..."

44. <u>በጉባዔ የሚደረገው ፀሎት በግል ከሚደረገው ፀሎት በስንት እጥፍ ይበልጣል?</u>

<u>ሀያ አምስት ጊዜ</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 1:11:619 "በጉባዔ የሚደረግ ፀሎት በግል ከሚደረገው ፀሎት 25 እጥፍ ይበልጣል::

<u>ሀያ ሰባት ጊዜ</u>

ሳሂህ ቡኻሪ 1:11:618 "በጉባዔ የሚደረግ ፀሎት በግል ከሚደረግ ፀሎት 27 እጥፍ ይበልጣል::

45. <u>ዉዱ(ለፀሎት የሚደረግ እጥበት) ስንት ጊዜ ይደረጋል?</u>

<u>አንድ ጊዜ</u> - ሳሂህ ቡኻሪ 1:4:159

<u>ሁለት ጊዜ</u> - ሳሂህ ቡኻሪ 1:4:160

<u>ሦስት ጊዜ</u> - ሳሂህ ቡኻሪ 1:4:161

46. <u>ቆሞ መጠጣት ይፈቀዳል?</u>

<u>አይፈቀድም</u>

ሳሂህ ሙስሊም 23:5017 "ነብዩ ሰዎች ቆመው መጠጣት እንደሌለባቸው አዘዋል::"

ይፈቀዳል

ሳሂህ ሙስሊም 23፡5023 “ለኑብዩ ውህ ስሰጣቸው እንደ ቆሙ ጠጥተዋል።”

ቁርአን ስለራሱ ሲናገር 4፡82 “ቁርአንን በጥንቃቄ አይመረምሩም፣ ከአላህ ሳይሆን ከሌላ ቢሆን ብዙ ልዩነት ባኙበት ነበር።” ይላል፣ ይህን የቁርአን ቃል ከላይ ካየነው እውነታ ጋር ስናነፃፅር ቁርአኑ እራሱ ከፈጣሪ አለመሆኑን በራሱ ላይ እየመሰከረ እየተመለከትነው ነው።

እነዚህን እርስ በርስ ግጭቶች ቁርአን ላይ መመልከታችን፣ ቁርአኑ የፈጣሪ ቃል መሆን ይቅርና በጠንቃቃ ሰው እንኳን አለመፃፉን ያሳያል፣ በርግጥ ለዚህ ችግር ዋናውን ድርሻ የሚይዘው የሙሐመድ አለመማርና በአዕምሮው ሽምድዶ ያለመያዝ ችግር ነው፣ በነዚህ ችግሮቹ ምክንያትም ቀድሞ ያስተማረውን እየረሳ ከሱ የሚጋጭ ነገር እያስተማረ ሲቸገር ነበረ፣ መጀመርያ ያዘዘውን በፅሁፍ ቢያስቀምጥና በአግባቡ ቢያጠና ኖሮ አድሮ ሌላ ቃል ባላወረደ ነበረ።

በአጠቃላይ ስንመለከት ቁርአኑ የወረደበት መንገድ የተምታታ መሆኑ፣ የተሰበሰበው በተወዛገበ መንገድ መሆኑ፣ ውስጡም የተለያዩ ነገሮች ጥርቅም መሆኑ፣ አምላካዊ ቃልነቱን በሚያፈርስ መንገድ ለሙሐመድ የግል ጉዳይ ተብሎ በየጊዜው መከለሱ፣ ከእውነታ ጋርና እርስ በርስ መጋጨቱን ስንመለከት ቁርአን የሙሐመድ የፈጠራ ስራ እንጂ ከፈጣሪ የወረደ መጽሐፍ አለመሆኑን እንመለከታለን።

2.5. አላህ እና የአይሁድ/ክርስትና አምላክ ተቃራኒ ኃይላት መሆናቸው

በእስልምና “አላህ” ማለት ሁሉን የፈጠረ፣ ሁሉን የሚያውቅ፣ ሁሉን የሚችል፣ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ(2፡115)፣ ለሰውም ከደም ጋኑ ጅማት ይልቅ የቀረበ(50፡16) አምላክ ነው፣ ቁርአን አላህና የክርስትናው እግዚአብሔር አንድ እንደሆኑ ይናገራል፣

29፡46 “... (የመጽሐፉን ባለቤቶች) አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው።”

እንደዚሁ ብዙ ክርስቲያኖችም የቁርአኑ አላህና የመጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር አንድ መሆናቸውንና የስም ልዩነቱም በቋንቋ ልዩነት የመጣ እንደሆነ ያምናሉ፣ ይህቺ መጽሐፍም እስከዚህ ክፍል ድረስ በዚሁ መልክ ስትመለከት ነበረ።

ነገር ግን የሁለቱን ማንነት በጥልቀት ስንመለከት አላህና እግዚአብሔር የተለያዩ እንደውም ተቃራኒ ኃይላት ናቸው፣ ይህንንም ዕውነታ ከባህሪ፣ አላህ ከሰይጣናት ጋር ባለው ትስስር፣ ለሙሐመድ ቁርአን ሲገለጡላቸው በነበሩት ጊዜ፣ ስፍራና ሁኔታዎች ውስጥ በምንመለከተው እውነታ፣ ከአላህ ቅድመ እስልምና ማንነትና ከካዕባ ታሪክ አንፃር ስንመለከት አላህና እግዚአብሔር ተቃራኒ ኃይላት ሆነው እናገኛቸዋለን፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

2.5.1. ከባህሪ አንፃር

ትክክለኛው ፈጣሪ በመልካምነት ፅንፍ ላይ ሲገኝ ሰይጣን ደግሞ በክፋት ፅንፍ ላይ ይገኛል፣ ሰዎችም በዚህ መካከል ባለው ስፍራ ላይ ተበትነው ይገኛሉ፣ በዚህ የማንነት ልኬት ላይ የአላህን ማንነት በመመልከት አላህ የሚመደበው ወደ እግዚአብሔር ነው ወይስ ወደ ሌላው የሚለውን ብንመልከት፡-

1. **አሳሳችነት**

አሳሳችነት የሰይጣን ባህሪ ነው፣ ይህንንም ባህሪውን በቁርአን 38፡82, 7፡20, 20፡120 ... ላይ እንመለከታለን፣ አላህም እንደ ሰይጣን አሳሳች መሆኑን ቁርአኑ ላይ ተመልክቷል፣

> 4፡88 "... አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን አላህም ያሳሳተውን ሰው ለእርሱ መንገድ ፈፅሞ አታገኝለትም፡፡"

በዚህም ሁለቱም አሳሳች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

2. **አጥማሚነት**

አጥማሚነት የሰይጣን ባህሪ ነው ፲፭፡39 "(ኢብሊስ አለ) ... ሁሉንም አጠማቸዋለሁ፡፡" አላህም እንደ ሰይጣን አጥማሚ መሆኑን ቁርአኑ ላይ ተመልክቷል፣

- ፲፡34 "ለናንተ ልመክራችሁ ብሻ አላህ ሊያጠማችሁ ሽቶ እንደሆነ ምክሬ አይጠቅማችሁ፡፡"
- 4፡88 "... አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን አላህም ያሳሳተውን ሰው ለእርሱ መንገድ ፈፅሞ አታገኝለትም፡፡"
- 35፡8 "... አላህ የሚሻውን ሰው ያጠምማል፡፡"

ተመሳሳይ ሐሳቦችን በ7፡186, 39፡36, 74፡31 ... ስፍራዎች ላይ ቀርቧል፡፡

በዚህም ሁለቱም አጥማሚ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

3. **አታላይነት**

አታላይነት የሰይጣን ባህሪ ነው፣ አላህም እንደ ሰይጣን አታላይ መሆኑን ቁርአኑ ላይ ተመልክቷል፣

> 4፡142 "መናፍቃን አላህን ያታልላሉ፡፡ እርሱም አታላያቸው ነው፡፡"

በዚህም ሁለቱም አታላይ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

4. **ፈታኝነት**

ሰይጣን በሰዎች ላይ ፈተና(ችግር) እንደሚያመጣ የታወቀ ነው፣ አላህም እንደ ሰይጣን ፈታኝ መሆኑን ቁርአኑ ላይ ተመልክቷል፣

- 21፡35 "... ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን፡፡"
- 2፡155 "ከፍርሃትና ከረሀብም በጥቂት ነገር፣ ከገንዘቦችና ከነፍሶችም፣ ከፍራፍሬዎችም በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን፡፡"
- 18፡7 "እኛ ... ልንፈትናቸው ..."

በዚህም ሁለቱም ፈታኝ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

5. <u>ከማስተዋል ማዘናጋት</u>

ሰይጣን ልቦናን ያዘናጋል 18፡63 "... ማስታወሱን ሰይጣን እንጂ ሌላ አላስረሳኝም::"፣ አላህም እንደ ሰይጣን ከማስተዋል የሚያዘናጋ መሆኑን ቁርአኑ ላይ ተመልክቷል፣

- 18፡28 "ልቡን እኛን ከማስተዋል ያዘነጋነውን ..."
- 17፡46 "(ቁርአንን) እንዳያውቁት በልቦቻቸው ላይ ሽፋንን በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን አደረግን::"

ተመሳሳይ ሐሳቦችም በ18፡57, 47፡23-24, 2፡6, 6፡25 ላይ ቀርቧል፣
በዚህም ሁለቱም አዘናጊ መሆናቸውን እንመለከታለን::

6. <u>ማስረሳት</u>

ሰይጣን ሰው እንዲረሳ ያደርጋል(18፡63, 58፡19 ...)፣ አላህም እንደ ሰይጣን ሰውን የሚያስረሳ መሆኑን ቁርአኑ ላይ ተመልክቷል::፣

- 2፡106 "ከአንቀፅ ብንለውጥ ወይም እርስዋን <u>ብናስረሳህ</u> ..."
- 18፡28 "ልቡን እኛን <u>ከማስታወስ</u> ያዘነጋነውን ..."

በዚህም ሁለቱም የሚያስረሱ መሆናቸውን እንመለከታለን::

በአጠቃላይ ስንመለከት አላህና ሰይጣን በአሳሳችነት፣ በአጥማሚነት፣ በአታላይነት፣ በፈታኝነት፣ ልቦናን በመዝጋትና በማስረሳት አንድ መሆናቸውን፣ በዚህም አላህ እግዚአብሔር ሳይሆን ተቃራኒ ኃይል እንደሆነ እንመለከታለን::

2.5.2. <u>ከሰይጣን ጋር ባለው ትስስር</u>

ጂኒ፣ የሞት መናፍስትና ጋኔን በስልጣንና በስራ ድርሻ የሚለያዩ የሰይጣን(ኢብሊስ) አይነቶች ናቸው፣ ቁርአኑ ላይ አላህና የእስልምና ቅዱሳን ከነዚህ አካላት ጋር አብረው እንደሚሰሩ ደግሞ በግልፅ ተመልክቷል፣

1. <u>ጂኒዎች</u>

ቁርአኑ ጂኒዎች ሙስሊሞች መሆናቸውን ይነግረናል፣

> 72፡1-2 "... እነሆ ከጂን የሆኑ ጭፍሮች (ቁርአንን) አዳመጡ:: እኛ አስደናቂ ... ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን (ቁርአን ሰማን):: በእርሱ አመንን፣ አሉ::"
>
> ተመሳሳይ ሐሳብም ሳሂህ ቡኻሪ 5፡58፡199 ላይ ቀርቧል::

ሙሐመድም ሙስሊሞች ጂኒዎችን የሚጎዳ ስራ እንዲያቆሙ ሲያዝ ነበረ፣

> ጃሚያ አት ትርሚዚ 18 "... የአላህ መልዕክተኛ እንደተናገሩት፣ በኩበትም ሆነ በአጥንት እስቲንጃ አታድርጉ <u>የወንድሞቻችሁ</u> የጅኖች ምግብ ነውና::"

እዚህ ጋር "ከሰል፣ ኩበትና አጥንት" የሚሉት ቃላት የቀረቡት በመንፈሳዊ ትርጉም ነው ምክንያቱም ጅኒዎች መንፈሳዊ ፍጡራን ስለሆኑ ቁሳዊውን ምግብ አይመገቡም ነገር

ግን ነብዩ ማስተላለፍ የፈለጉት መልዕክት ሙስሊሞችን ጅኒዎችን ከሚነዳ ስራ እንዲታቀቡ ነው።።

2. <u>የሞት መናፍስት</u>

ዋናው ፈጣሪ ሰው በተሰጠው እድሜው በህይወት እንዲኖር ፈጠረው ነገር ግን የዚህ ፈጣሪ ተቃራኒ የሆነው ሰይጣን ደግሞ የሰው ልጆች በተሰጣቸው እድሜ እንዳይኖሩ ቀድሞ ይቀጥፏቸዋል፣ በዚህም መሠረት የአላህን ጎራ ብንመለከት፣

- <u>የሞት መላዕክት የሚሰሩት ለአላህ መሆኑ</u>
  6፡100 "ለአላህ ኢጋንንትን የፈጠራቸው ሲሆን ... ወንዶች ልጆችንና ሴቶች ልጆችንም ... <u>ለዕርሱ ቀጠፉ</u>።።"
- <u>አላህ ከነፍሰ ገዳይ ሰዎች ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑ</u>
  በ2.3.2.5 ክፍል እንደተመለከተው የአላህ ቃል የሆነው ቁርአን ሰዎች በጂሀድ እንዲጋደሉ ያዛል፣ ከማዘዝም አልፎ ደግሞ በዚህ መጋደል ውስጥ ስለሚገደሉት ሰዎች ኃላፊነቱን አላህ እራሱ እንደሚወስድ ይናገራል፣
  > 8፡17 "አልገደላችሃቸውም ግን አላህ ገደላቸው።። (ጭብጥ አፈር) በወረወርክ ጊዜ አንተ አልወረወርክም።። ግን አላህ ወረወረ (ወደ አይኖቻቸውም አደረሰው)።።"
- <u>አላህም በራሱ የሞት መናፍስቱን ስራ እንደሚሰራ</u>
  - 17፡16-17 "<u>ከተማን ለማጥፋት **በፈለግን** ጊዜ ባለጸጋዎች እናበዛለን።። በውስጧም ያምፃሉ።። በእርስዋ ላይ ቃሉ(ቅጣቱ) ይፈፀምባታል።። ማጥፋትንም እናጠፋታለን ... ከክፍለ ዘመናት ሰዎች ያጠፋናቸው ብዎች ናቸው</u>።።"
  - 32፡26 "(አላህም) ከክፍለ ዘመናት ሰዎች <u>ብዙዎችን ያጠፋን መሆናቸንን</u> ..."
  - 38፡3 "ከእነርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦችን <u>ብዙን አጥፍተናል</u>።።"

በአጠቃላይ ስንመለከት አላህ ከሞት መናፍስትና ከነፍሰ ገዳይ ሰዎች ጋር አብሮ እንደሚሰራና እራሱም ይህንን የሰው ነፍስ ማጥፋት ስራ እንደሚሰራ እንመለከታለን፣ ይህም እውነታ አላህ የፈጣሪ ይሁን የሰይጣን ጎራ እንደሆነ እንድንለይ ይረዳናል።።

3. <u>አጠቃላይ ሰይጣናት/ጋኔኖች</u>፡-

አላህ ከጂኒዎችና ከሞት መናፍስቱ በተጨማሪ ከአጠቃላይ የሰይጣን ዘሮች(ጋኔን፣ ኢጋንንት ...) ጋር አብሮ እንደሚሰራ ቁርአኑ ይናገራል፡-

- <u>የአላህ መልዕክተኞች መሆናቸው</u>
  - 2፡102 "... ሰይጣናት ሰዎችን ድግምት የሚያስተምሩ ሲሆኑ ካዱ:: ያንን በባቢል <u>በሁለቱ መላዕክት</u> በሃሩትና በማሩት ላይ የተወረደውን ነገር(ያስተምሯቸዋል)::"
    እዚህ ጋር ቁርአኑ ሰይጣናትም መላዕክትም ስራቸው አንድ እንደሆነ ቢናገርም የፈጣሪ መላዕክት ግን ድግምት የማይሰሩ በመሆናቸው "መላዕክት" ተብለው የቀረቡት ሰይጣናት መሆናቸውን መላዕክትነታቸውም ለአላህ መሆኑን እንመለከታለን::
  - 19፡83 "እኛ ሰይጣናትን በከሀዲዎች ላይ (በመጥፎ ስራ) ማወባራትን(ለክፉ ማነሳሳት) የሚያወባሩዋቸው ሲኾኑ <u>የላከን</u> መሆናችንን አላየህምን::"
- <u>ከነብዩ ጋር አብረው የሚሰሩ መሆኑን</u>
  - 72፡19 "እነሆም የአላህ ባሪያ (ሙሀመድ አላህን) የሚጠራ ሆኖ በተነሳ ጊዜ (ጋኔኖች) <u>በእርሱ ላይ ድርብርቦች ሊኾኑ</u> ቀረቡ::"
  - ሳሂህ ቡኻሪ 2፡19፡177 "... ነብዩ እንዳሉት፣ አነጂም ሳነብላቸው ተኛሁኝ፣ <u>ከሱም ጋር የተኙት</u> ሙስሊሞች፣ እምነት የለሾች(pagans)፣ <u>ጂኒዎችና</u> የሰው ልጆች በሙሉ ናቸው::"
- [32] <u>"የእስልምና ቅዱሳኑን" ሲረዱ የነበረ መሆኑ</u>
  - 34፡12 "... (ለሱሌይማንም) ... <u>ከጋኔኖችም</u> በጌታው ፍቃድ በፊቱ የሚሰሩትን (አደረግንለት)::"
  - 21፡82 "<u>ከሰይጣናትም</u> ለርሱ(ለሱለይማን) (ሉልን ለማውጣት) የሚጠልሙንና ከዚያም ሌላ ያለን ስራ የሚሰሩትን (ገራንለት)፣ ለእነሱም ተጠባባቂዎች ነበርን::"
  - 27፡15-17 "ለዳውድና ለሱለይማን እውቀትን በርግጥ ሰጠናቸው... ሱለይማንም ሰራዊቶቹ <u>ከጋኔን</u>፣ ከሰውም፣ ከበራሪ የሆኑትም ተሰበሰቡ:: እነሱም ይከመከማሉ::"

በአጠቃላይ በእስልምና ጂኒዎች አማኞች እንደሆኑ መነገሩ፣ ሙስሊሞችም የወንድሞቻውን ጅኒዎችን እንዳይነዱ መከልከሉ፣ ነብዩ ሙሐመድ ከጅኒዎች ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑን፣ አላህ ከነፍሰ ገዳዮች ጋር የሚሰራ መሆኑ፣ አላህ በራሱ ነፍሰ ገዳይ መሆኑ፣ የእስልምና ቅዱሳንም ከጅኒዎች በተጨማሪም ከአጠቃላይ ጋኔኖች፣ ኢጋንንት፣

[32] እዚህ ጋር "የእስልምና ቅዱሳን" የተባለበት ምክንያት፣ ምንም እንኳን ሱሌይማን የመጽሐፍ ቅዱሱ ሰለሞን እንደሆነ፣ ዳውድ ደግሞ ዳዊት እንደሆነ ቢነገርም መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ሰለሞንና ዳዊት ከጋኔናችና ከሰይጣናት ጋር አብሮ መሥራታቸውን የሚናገር ቃል ስለሌለ ነው::

የሞት መናፍስትና ሰይጣናት ጋር አብረው የሚሰሩ መሆናቸውን ስንመለከት ጂኒ፣ የሞት መናፍስት፣ ጋኔን፣ ኢጋንንት፣ ሰይጣን እና አላህ አንድ ወገን መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

2.5.3. <u>ለሙሐመድ ቁርአን ሲገለጡላቸው በነበሩት መንገዶች፣ ጊዜና ስፍራዎች ውስጥ የምንመለከተው እውነታ</u>

ጊዜ፣ ስፍራና ሁኔታ የአንድን ነገር ማንነት ለማጥናትና ለማወቅ የሚረዱን ዋነኛ መስፈርቶች ናቸው፣ በዚህም አላህ ሲገለጥበት የነበረበትን ጊዜ ስፍራና ሁኔታ በመመልከት የአላህን ማንነት ስንመለከት፣

- **<u>ጊዜ</u>**

ቁርአን የወረደበትን ጊዜ ስንመለከት፣

> 97፡1 “እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ <u>ሌሊት</u> አወረድነው፡፡ መወሰኛይቱም ሌሊት ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ፣ መወሰኛይቱ <u>ሌሊት</u> ከሺ ወር በላጭ ናት፡፡ በርስዋ ውስጥ መላዕክትና መንፈሱ በጌታቸው ፈቃድ በነገሩ ሁሉ ይወርዳሉ፡፡ <u>እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሠላም ብቻ ናት</u>፡፡”

እዚህ ጋር “ሌሊት” የሚለው ቃል የተተረጎመው በቀጥተኛ ትርጉም ሳይሆን በመንፈሳዊ ትርጉሙ ነው ምክንያቱም ቁርአኑ የወረደው በአንድ ሌሊት ሳይሆን በረዥም የጊዜ ሂደት ስለሆነ(25፡32, 17፡106, 3፡3)፡፡

በመንፈሳዊው አተረጓጎም ሌሊትና ቀን የተለያየ ትርጉም አላቸው፣ በቀን የሚሰራው “ማንንም የማይፈራው” ማለት ነው፣ በሌሊት የሚሰራው ደግሞ “ተደብቆ የሚሰራ” ማለት ነው፣ በዚህም ቁርአኑ የወረደው በመንፈሳዊ ሌሊት መሆኑ ቁርአኑ ከዋናው አምላክ ሳይሆን በድብቅ ከሚሰራው የዋናው አምላክ ተቃራኒ መንፈሳዊ ኃይል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በእስልምና ውስጥ ዋና ዋናዎች ክስተቶችና ስነ ስርዓቶች ከሌሊት ጋር የተያያዙ ናቸው፣ እስልምናው ለጊዜ መቁጠርያ፣ ለጾም መያዣና መፍቻ እንዲሁም ለኃይማኖቱ አርማነት የሚጠቀሙት ሌሊት የምትነግሰው ጨረቃን ነው፣ ይባሱኑ እውነታውን በመቃረንም ጨረቃ አብሪ፣ ፀሐይ አንፀባራቂ(10፡5) ይላል፣ ነብዩ ሦስቱን መላዕክት የተገናኙት በሌሊት ነው(ሳሂህ ሙስሊም 1፡312)፣ “ቡራቅ” የተባለውን አውሬም የሚጋልቡት በሌሊት ነው(ሳሂህ ቡኻሪ 5፡57፡22, ሳሂህ ሙስሊም 1፡309) ...

በዚህ የእስልምናና የሌሊት ጥብቅ ግንኙነት ውስጥ የአላህን ማንነት እንመለከታለን፡፡

- **<u>ስፍራ</u>**

ፈጣሪ ለሙሳ ተውራት(ኦሪትን) የሰጠው በተራራ ላይ ነበረ(ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡162)፣ ሙሐመድ ቁርአንን የተቀበለው “ሂራ” በሚባል ዋሻ ውስጥ ነው(ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡3)፣ ይህም አሰራር የመንፈስ ተቃርኖን ያሳያል፡፡

አላህ የት እንደሚኖር ስንመለከትም ሳሂህ ቡኻሪ 4፡54፡421 "... ፀሐይ ስትጠልቅ የአላህ ዙፋን ስር ገብታ እስክትተኛ ትሄዳለች ..." ማለቱና 18፡85-93 "... ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃ ባላት ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት፡፡" በሚለው አነጋገር ውስጥ የፀሐይን ነገር ትተን (ምክንያቱም ፀሐይ ዓለምን ትዞራለች እንጂ የምትገባበት ጉድጓድ የላትምና) ሁለቱን ቃላት በአንድ ላይ ስንመለከት አላህ የሚኖረው መንፈሳዊ ስሙ "የጥቁር ጭቃ ምንጭ" በተባለው ስፍራ ነው፡፡

- **ሁኔታ**

ነብዩ ሙሐመድ የቁርአን እንዴት ሲገለጥላቸው እንደነበረ ሲናገሩ

ሳሂህ ቡኻሪ 1፡1፡2 "... ዋናዎቹ መልዕክቶች የሚመጡልኝ በደወል ድምፅ ነው..." ሀዲሳቱ የደወልን ድምፅ የሚገናኘው ከሰይጣን ጋር እንደሆነ ይናገራሉ፣

ሳሂህ ሙስሊም 24፡5277-5279 "... ደወል የሰይጣን የሙዚቃ መሣርያ ነው" በዚህም በደወል ድምፅ የሚናገረው ማን እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

እነዚህን ቁርአን የወረደበት ጊዜና ስፍራና ሁኔታ በአንድ ላይ ስንመለከት አላህ ማለት ዋናው ፈጣሪ ሳይሆን የዚህ የዋናው ፈጣሪ ተቃራኒ መንፈስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

2.5.4. ከአላህ ቅድመ እስልምና ማንነት

[33] "አላህ" የሚለው ስም የመጣው "አል-ኢላህ" የሚለውን የጣኦት ስም በማሳጠር ነው፣ በአረቡ አካባቢ "ኢላህ" የሚባል ጣኦት ሲመለክ እንደነበረ የአቡ ዳውድ ሱና 4272 እና 4273 ላይ እንመለከታለን፡፡

ዛሬም በእስልምና "ኢላህ" የሚለው አሪጂናሉ የጣኦት ስም "እርኩስ" ተብሎ አለመተውና ይባሱኑ "ቅዱስ" ተደርጎ ትርጉሙ "አምላክ ማለት ነው" በማለት፣ "ላ ኢላህ ኢል አላህ" እያለ ሙስሊሙ ለአላህ ያለውን እምነት በየጊዜው እየደጋገመ የሚናገርበት ቃል መሆኑን ስንመለከት አላህና ኢላህ አንድ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

[34] "በአካባቢው የተጠኑትን የአርኪዎሎጂ ግኝቶችንና ሙሐመድ በመካ የተመለከታቸው ሦስቱን ሴት አማልክት "አል-ለት፣ ዑዛ እና መናት"(53፡19-20)፣ የ"አል-ኢላህ" (በአሁኑ አጠራር "አላህ") የሚባለው አምላክ ልጆች ነበሩ፡፡"

በዚህም አላህ ማለት ኢላህ የተባለውና ዓረብ አካባቢ ሲመለክ የነበረ ጣኦት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

[33] https://en.m.wikipedia>wiki>Allah

[34] ዳግማዊ ኃይለ ሥላሴ(2008)፣ **ኢስላም ምንድነው? ክርስትናስ?**፣ ገፅ 74

2.5.5. ከ"ካዕባ" ግንባታና አምልኮ ታሪክ

እንደ እስልምና ካዕባ የመጀመሪያው መዝጊድ ነው(3፡96)፣ ያሰራውም አብርሃም(ኢብራሂም) እንደሆነ ይነገራል(2፡127, ሳሂህ ቡኻሪ 4፡55፡583 ...)፣ እውነታውን ስንመለከት ግን ካዕባ ከኢብራሂም ጋር የሚገናኝ ታሪክ አይደለም፣

1. *ሙሐመድ የሙስሊሞች መጀመሪያ መሆኑ*(22፡52, 6፡163, 39፡12, 6፡14...)፣ በዚህም ከሙሐመድ ከብዙ ዘመናት በፊት ይኖር የነበረው ኢብራሂም ከእስልምና(መዝጊድ) ጋር የሚገናኝበት መንገድ የሌለ መሆኑ፣
2. *ሙሐመድ የተላከው ነብይ* ላልተላከበት ቦታ (43፡23) እንጂ እንደ ኢብራሂም ያሉ ነብያት ለተላኩበት ቦታ አለመሆኑ፣
3. *ሙሐመድ የተላከው ፈፅሞውኑ መልዕክተኛ* ላልተላከላቸው ህዝቦች (28፡46, 32፡3, 34፡44, 36፡ 2-6 ...) እንጂ እንደ ኢብራሂም ያሉ ነብያት ለተላኩለት ህዝብ አለመሆኑ፣

ስንመለከት ኢብራሂም ከእስልምና *ኃይማኖት*(ከመዝጊድ)፣ ከሳዑዲ ሀገር እና ከአረብ ህዝቦች ጋር እንደማይገናኝና ካዕባንም እንዳላስነሳው አንመለከታለን።

ሙሐመድ የካዕባን ታሪክ በአብርሃም ታሪክ ጋር ከሸኖ ያቀረበውም ሰዎችን ከእግዚአብሔር አምላኪነት ወደ ቁርየሽ ጣኦት አምላኪነት ለመመለስ በማሰብ ነው። በዚህ ምክንያትም ነው *ሙሐመድ* በመጀመርያ ለማስመሰል "የእግዚአብሔር ቤት" ተብሎ ወደሚጠራው ኢየሩሳሌም(Bait-ul-maqdi) ሲሰግድ ቆይቶ ከዚያ አቅጣጫውን ወደ ካዕባ በመቀየር (2፡144-145, ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡13 ...)፣ ካዕባን "የአላህ ቤት" ብሎ የሰየመው(2፡158, 106፡1-4)።

ካዕባ የተሰራው በኢብራሂም ሳይሆን በቁረይሽ ሰው መሆኑና የተሰራውም ደግሞ በቅድመ እስልምና ለነበረው የጣኦት አምልኮ መሆኑን የሚያመላክቱ ሐሳቦችን እዚያው ቁርአኑና ሀዲስ ላይ እናገኛለን፣

- 106፡1-4 "ቁረይሽን ለማለመድ(ባለዝሆኖቹ አጠፉ)። የብርድና የቢጋን ወራት ጉዞ ሊያላምዳቸው ይህንን ሰራ። ስለዚህ የዚህን ቤት (የካዕባን) ጌታ ይገዙ። ያንን ከረሃብ ያበላቸውን ከፍርሀትም ያረካቸውን (ጌታ ያምልኩ)።"
- ሳሂህ ሙስሊም 43፡7179፡ "በቅድመ እስልምና ሴቶች ካዕባን የሚዞሩት ራቁታቸውን ነበረ ..."

በዚህም ካዕባ የሚገናኘው ከአብርሃምና ከነባሩ የአይሁዳውያን እምነት ጋር ሳይሆን ከቁረይሾች ታሪክ ጋር መሆኑን እንመለከታለን። ካዕባ አካባቢ የጣዖት አምልኮ እንደነበረና *ሙሐመድም* ይህንን አምልኮ የእስልምና አካል እንዳደረጉ የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎችንም መመልከት ይቻላል፡-

- ነባሩን ካዕባን የመዞር የጣኦት አምልኮ ማስቀጠሉ (ሳሂህ ሙስሊም 43፡7179)፣
- ነባሩን በካዕባ "ሶፋና መርዋ" መካከል የነበረውን የጣኦት አምልኮ ስነ ስርዓት፣ ጎብረተሰቡ በእስልምና መምጣት ለመተው ሲወያይ እንኳን ሙሐመድ ጎብረተሰቡ ይህንን አምልኮ እንዳይተዉት ማዘዙ (ሳሂህ ቡኻሪ 6፡60፡22– 6፡60፡23, 2፡158)፣
- ነብዩ ካዕባ ውስጥ የሚመለከውን ዋናውን ጣኦት "ጥቁር ድንጋይ" መሳለሙና ሌሎችም እንዲሳለሙት ማዘዙ(ሳሂህ ቡኻሪ 2፡26፡667)

እነዚህን እውነታዎች ስንመለከት ነብዩ ሙሐመድ በአይሁድ/ክርስርትና ኃይማኖት ስም ትልቅ ሽወዳ መስራቱን እንመለከታለን፣ በዚህም ነብዩ በካዕባ የሚኖረውን(2፡158) እና በጂአግራፊ(በአካባቢ) የተወሰነው "የዚህች ሀገር ጌታ" የተባለው(27፡91) የቁረየሽ አምላክ "አላህ" ዋናው ፈጣሪ አምላክ ተደርጎ እንዲመለክ አድርጓል።

በአጠቃላይ ስንመለከት ከላይ የተመለከትናቸው የአላህ ባህሪ ከሰይጣን ባህሪ ጋር አንድ መሆን፤ አላህ ከጂኒ፣ አጋንንት፣ ሰይጣን፣ ጋኔን፣ የሞት መናፍስት ጋር አብሮ የሚሰራ መሆኑ፤ ቁርአኑ ለሙሐመድ የተገለጠበት ጊዜ፣ ስፍራና ሁኔታ ሰይጣናዊ መሆኑና ከአላህ ቅድመ እስልምና ታሪክና ከካዕባ የግንባታ ታሪክ እንደምንመለከተው "አላህ" ፈጣሪ አምላክ ሳይሆን ዓረቡ አካባቢ የሚኖር ቁረይሾች የሚያመልኩት ሰይጣን መሆኑን እንረዳለን።

<u>ማጠቃለያ(እስልምና)</u>

ቆም ብሎ ላስተዋለ ሰው <u>አንድ እውነታ ከመጀመርያው ጀምሮ በቋሚነት እየተደጋገመ ይገኛል</u>፣ ነብዩ ሙሐመድ በእስራኤል ነብያት መንገድ ነኝ ብሎ በተቃራኒ መንገድ መሄዱ፣ ቁርአን "የፈጣሪ ቃል" ተብሎ ውስጡ የፈጣሪ ቃል አለመሆኑ እንዲሁም "አላህ እግዚአብሔር ነው" ተብሎ የእግዚአብሔር ተቃራኒ ኃይል መሆኑን። መቸም ዋናው ፈጣሪ እንደዚህ አይነት ድብብቆሽ እንደማይሰራ እሙን ነው፣ እንደዚህ አይነት ድብብቆሽ የሚሰራው ተደብቆ እንደ ፈጣሪ መመለክ የሚፈልገው መንፈስ ነው፣ እሱም ከላይ ከነፀባዩና ማንነቱ የተመለከትነው የቁረይሾቹ ጣኦት/ሰይጣን መሆኑ ግልፅ ነው።

በዚህም ሙስሊሙ ማህረሰብ፣ ሙሐመድ የሰራውን ህገወጥ ቅጥያ በቁረጥ ወደ ቀደመው እውነተኛው መንገድ መመለስ ይገባዋል፣ ይህም እውነተኛ መንገድ ነብዩ፣ ቁርአኑና አላህ ተመሳስለው የተነሱበት በስሙ የነገዱበት የክርስትናው መንገድ ነው።

በክርስትና ስር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም ትክክኛዋ ቤተክርስቲያን የትኛዋ ናት? የሚለውን ከምዕራፍ አራት ጀምሮ የምንመለከት ሲሆን ከዚያ በፊት ግን ከክርስትና በመውጣት ሌላ ኃይማኖት የመሠረቱትን ኃይማኖቶች ምሥረታ ታሪኮችን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን።

ምዕራፍ ሦስት

3. በተለያየ ምክንያት ከክርስትና የወጡ ኃይማኖቶች

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው በክርስትና ስር የነበሩ ነገር ግን እንደ እስልምና ከክርስትና በመውጣት ሌላ መንገድ የተከተሉትን ኃይማኖታዊ ድርጅቶችን ነው፣ በዚህም፣

- በፖለቲካ ምክንያት ከክርስትና የወጡ፣
  - "እስልምና ለዓረብ፣ ክርስትና ለእስራኤል፣ ዋቄፈና ለኦሮሞ" ብሎ የተደራጀውን "ዘመናዊ ዋቄፈና"
  - ክርስትናን በራሳቸው ማኅበረሰብ እሴት የቀረፁትን ራስ ተፈሪያንን፣
- እንደ እስልምና በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የራሳቸውን አስተምህሮ ጨምረው ከክርስትና የወጡ - ባኢ፣ ሞርሞን፣ የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒስት፣ ሂውማኒዝምና የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ

ሲሆኑ ሁሉንም በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

3.1. በፖለቲካ ምክንያት ከክርስትና የወጡ

ነብዩ ሙሐመድ ኃይማኖትን ከማኅበረሰብ ጋር በማያያዝ ለዓረቡ ማኅበረሰብ የተላከው እስልምና እንደሆነ አስተምረዋል፣ በተመሳሳይ መንፈስም አንዳንዶች ክርስትናን ከዘር ጋር በማገናኘት ከክርስትና ወደ ራሳቸው ማኅበረሰባዊ ኃይማኖት ተመልሰዋል፣ ከነዚህ ማኅበረሰባዊ ኃይማኖቶች መካከል ለምሳሌ ያህል ዘመናዊውን ዋቄፈናንና የራስ ተፈሪያንን ኃይማኖት እንመለከታለን፡፡

3.1.1. ዘመናዊው [35]ዋቄፈና

የኦሮሞ ህዝብ ከረዥም ዘመናት በኋላ ብሔራዊ ማንነቱ ሲከበርለት የብሔሩን ማንነት፣ ይህም፣ ቋንቋውን፣ ባህሉን፣ አስተዳደርዊ ስርዓቱን … መልሶ እየገነባ ይገኛል ይሁን እንጂ በዚህ ሂደት ውስጥ አንዳንዶች ኃይማኖትን የብሔር ማንነት በማድረግ የዋቄፈና ኃይማኖትንም መልሶ በመገንባትና በዘመናዊ መንገድ በማደራጀት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህም [36] በ1996 ዓ.ም በአቶ ድርቢ ደምሴ መሪነት ዋቄፈና በፍትህ ሚኒስቴር እንደ አንድ ኃይማኖት “የዋቄፈታ እምነት ተከታዮች ማኅበር” በሚል እውቅናና የምስክር ወረቀት አግኝቷል፣ ከዚህ ጊዜም ጀምሮ ዋቄፈና እንደ ኃይማኖት በዘመናዊ መልክ ተደራጅቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡

ምንም እንኳን የቀድሞው ዋቄፈና እንደ የትኞቹም ኋላ ቀር ባህላዊ ኃይማኖቶች ዓለማቀፋዊ ዕይታ ያለመያዝ ውሱንነቶች የነበሩበት ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በዘመናዊ መልክ የተደራጀው ዘመናዊው ዋቄፈና ግን ከባህላዊ ኃይማኖቶች በተለየ፣ እንደሌሎቹ ዓለማቀፍ ኃይማኖቶች ራሱን በዓለማቀፋዊ ፍልስፍና አደራጅቷል፣ ይህም፣

> “ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ ነው፣ አይሁድ፣ ዓረብ … ይህንን አምላክ በራሳቸው ማኅበረሰብ ዕሴት እንደሚያመልኩት ኦሮሞም ይህን አምላክ በራሱ እሴት ያመልካል፡፡”

በማለት ብዙ ክርስቲያኖችን ወደ ራሱ መመለስ የቻለ ሲሆን ብዙዎችን ደግሞ ግራ በማጋባት በክርስትናና በዋቄፈናነት፣ በሁለት ኃይማኖት መካከል እንዲዋልሉ አድርጓል፡፡ በዚህ ምዕራፍም፣

- የዘመናዊውን ዋቄፈና ኃይማኖታዊ ቁመና፣
- ኃይማኖቱ ለመስፋፍያነት የተጠቀመው ዘዴዎች፣
- ኃይማኖቱ ከክርስትና ጋር ያለውን ሽኩቻ፣

በስፋት እንመለከታለን፡፡

---

[35] ብዙ ሰዎች “ዋቄፈና” እና ”ዋቄፈታ” የሚባሉት ቃላት ትርጉም ላይ ሲምታቱ ይታያል፣ “ዋቄፈና” ኃይማኖት ሲሆን “ዋቄፈታ” ደግሞ የዋቄፈና ኃይማኖት ተከታይ ግለሰብ ነው፡፡ Maatii Sabaa (6400 ALW/206 ALA), **DAANIYAA**, fuula 52, Waldaa Aadaafi Dudhaa Oromoo(WADO)

[36] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 50-54

3.1.1.1. <u>የዘመናዊው ዋቄፈና ኃይማኖታዊ ቁመና</u>

ማንኛውም የኃይማኖት ተቋም "የኃይማኖት ተቋም" ለመሆን ከመንግሥት ከሚሰጥ ሰርተፊኬት ባለፈ ኃይማኖታዊ ቁመና ሊኖረው ይገባል፣ በዚህ መሠረት ዘመናዊውን ዋቄፈናን፣ በኃይማኖታዊ መስፈርቶች፣ ይህም ኃይማኖቱ የሚመራበት መዋቅር፣ ኃይማኖቱን የሚመሩ የኃይማኖት መሪዎች፣ የአምልኮ ስፍራ፣ የአምልኮ ፕሮግራም እና ኃይማኖቱ የሚመራበት ቅዱስ መጽሐፍ መያዝ አለመያዙን ስንመለከት ዘመናዊው ዋቄፈና በኃይማኖት ስም መንግሥታዊ ፍቃድ ይያዝ እንጂ ኃይማኖታዊ መስፈርት የሚያሟላ ኃይማኖት ሆኖ አናገኘውም::

ዋቄፈና እንደ አንድ ኃይማኖታዊ ድርጅት ፍቃድ ይሰጠው እንጂ ኃይማኖቱ እንደ ኃይማኖት ድርጅት የሚመራበት ኃይማኖታዊ መዋቅር የለውም፣ የዋቄፈና ኃይማኖት ፕሬዚዳንት ማን ነው? አይታወቅም፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በቀበሌ ደረጃ ያለው የኃይማኖቱ መዋቅርም አይታወቅም፣ የሚከተለው የአመራር አይነትም አይታወቅም:: እንደዚሁ አንድ ኃይማኖት ለኃይማኖታዊ ስነ ስርዓት ማስኬጃ ራሳቸውን የቻሉ የኃይማኖት መሪዎችና የመሪዎች ማፍለቂያ ማዕከላት ሊኖሩት ይገባል ይሁን እንጂ የዋቄፈና ኃይማኖት ራሳቸውን ለኃይማኖታዊ አገልግሎት የለዩ መንፈሳዊ ሰዎችም ሆነ እነዚህን ሰዎች የሚያፈልቁ ማዕከላት የሉትም::

ኃይማኖቱ በነዚህ ከፍተቶቹ ላይ ደግሞ እንደ አንድ የኃይማኖት ተቋም የኢሬቻ በዓል ከሚከናወንበት ስፍራ ውጪ ቋሚ ማምለኪያ ስፍራም ሆነ የአምልኮ ፕሮግራም የለውም፣ በዚህም በተለይ ታች ላለው ለብዙሀኑ ጎብረተሰብ ተደራሽ አይደለም፣ የኃይማኖቱ ተከታዮቹ በሞት፣ በውልደት ... የሚፈልጉትን ኃይማኖታዊ አገልግሎት የሚሰጣቸው አካል የለም፣ በኃይማኖቱም ወጥ ሳምንታዊ ወይ ወርሀዊ የአምልኮ ፕሮግራም የለም፣ ኃይማኖቱ በኢሬቻ ክብረ በአላቶቹ ጊዜያት ካለው ፕሮግራም ውጪ እንደ ኃይማኖት ምዕመኑን የሚያገለግልበት አምላኩንም የሚያመልክበት ቋሚ ፕሮግራም የለውም፣ በዚህም የዋቄፈና "ኃይማኖት" ኃይማኖት ሳይሆን የኢሬቻ በዓል አስፈፃሚ ኮሚቴ ብቻ የሆነበት እውነታ ነው የምንመለከተው::

ከመንፈሳዊ መጽሐፍም ጋር በተያያዘ ዋቄፈና እንደ ክርስትና፣ እስልምና፣ ሂንዱ ... ኃይማኖቶች ወጥ በሆነ መንገድ የሚመራበት የራሱ ቅዱስ መጽሐፍ የለውም ይባሱኑም የኃይማኖቱ ምሁራን እንደዚህ አይነት መጽሐፍ ሊኖር እንደማይገባ ይናገራሉ [37] "ፈጣሪና ሰው አይነጋገሩም ... እንደዚህ ማለትም ነውር ነው ... ፈጣሪ ሰዎች የሚያስቡበትን አዕምሮና "አያንቱማ"(መንፈሳዊ ኃይል) ይሰጣል እንጂ ... ከፈጣሪ በቃልም በመጽሐፍም መቀበል የሚባል አሰራር የለም::" ይላሉ::

[37] Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa**, fuula 25

ይሁን እንጂ ሌሎቹ ኃይማኖቶች ጋር የምንመለከታቸው መንፈሳዊ መጽሐፍት በፈጣሪ ተፅፈው የወረዱ ሳይሆኑ ሰዎች በተሰጣቸው መንፈሳዊ ኃይል/መገለጥ የፃፏቸው መጽሐፍት ናቸው፣ በዚህም ዋቄፈና "መጽሐፍ አያስፈልግም" ከሚል "አያንቱ" የሚላቸው ሰዎች ጋር ያለውን መንፈሳዊ እውቀት በመጽሐፍ አለማዘጋጀቱን በድክመት መቀበል ነበረበት፡፡

ኃይማኖቱ ቅዱስ መጽሐፍ በማጣቱና በሰዎች አሉታ ላይ ተመስርቶ በመመራቱ የኃይማኖቱ ጀማሪዎች ዘንድ የነበረው እውቀት በአዕምሮ እየተያዘ ለሁሉም ትውልዶች መተላለፍ እንደማይችል ግልፅ ነው፣ በዚህ ላይ ደግሞ ኃይማኖቱ ለዘመናት በክርስትናና በእስልምና ኃይማቶች ተፅዕኖ ስር ወድቆ በነበረበት እውነታ ውስጥ ኃይማኖቱ ሙሉ ሆኖ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወርድ ሲዋረድ እንዳልመጣ ግልፅ ነው፡፡

በዚህም በኃይማኖቱ ላይ ብዙ የእውቀት ክፍተቶች ተፈጥረውበታል፣ በቀላል ምሳሌ እንኩዋን ብንመለከት፣ ዛሬ በኃይማኖቱ ላይ ብዙ ጥናትና ምርምር ያደረጉ፣ ለኃይማኖቱ ሰርተፊኬት ያስገኙትን፣ የኃይማኖቱን መሪዎች ኃይማኖታዊ እውቀት ብንመለከት ብዙ የእውቀት ክፍተቶችን እናስተውላለን፣ ለምሳሌ፡-

- [38] "ሰይጣን የሚባል መኖሩን አናውቅም"
- [39] "ፈጣሪ ሰውን ይምሰል አይምሰል አናውቅም"
- [40] "ከሞት በኋላ ህይወት ይኑር አይኑር አናውቅም"

ሲሉ እንመለከታለን፣ የኃይማኖት መሪ ሆኖ "አናውቅም" ያመጣው ደግሞ ይኸው የመንፈሳዊ መጽሐፍ እጥረት ነው፡፡

ኃይማኖቱ ቅዱስ መጽሐፍ በማጣቱ ምክንያትም በቤተ እምነቱ ውስጥ አከራካሪ ነገር ሲነሳ መዳኘት እስከማይቻልበት ደረጃ እየተደረሰ ይገኛል፣ ለምሳሌ በኢሬቻ በዓል አከባበር ዙሪያ እርድ፣ ደም/አራቁ ሃይቅ/ወንዝ ውስጥ ማፍሰስ፣ ዛፍ ቅቤ መቀባት፣ የወንድ ብልት ቅርፅ በጭንቅላት ላይ ማሰር ... ብዙ አከራካሪ ጉዳዮችን መመልከት ይቻላል፤ ለዚህ ስርዓት የሸማግሌዎቹ ጎራ ለትክክኝነቱ ሲሟገቱ ዘመነኞቹ ደግሞ ከክርስትና እውቀታቸው በመነሳት "ተው ይሄ ሰይጣናዊ አሰራር ነው" በማለት ሲያወግዙና ፖሊስ መካከላቸው እስኪገባ ድረስ ሲሻኮቱ እየተመለከትን ነው፣ የትኛው ነው ትክክለኛው? መፍረድ አይቻልም ምክንያቱም ኃይማኖቱ ቅዱስ መጽሐፍ ስለሌለው፡፡

[38] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 31, 68
[39] Ibid, fuula, 172
[40] Ibid, fuula 35,40,68, 172

በአጠቃላይ ስንመለከት ምንም እንኳን የዋቄፈና ኃይማኖት በመንግሥት እንደ አንድ የኃይማኖት ተቋም ቢመዘገብም፣ ኃይማኖቱ ኃይማኖታዊ መዋቅር፣ የኃይማኖት መሪዎች፣ ተደራሽ ማምለኪያ ስፍራዎች፣ ኃይማኖታዊ ፕሮግራሞችና ቅዱስ መጽሐፍ የሌለው በአጠቃላይ የዋቄፈና ኃይማኖት ከመንግሥት ከወሰደው ሰርቲፊኬት ውጪ "ኃይማኖት" የሚያስብለው ኃይማኖታዊ ቁመና እንደሌለው እንመለከታለን::

3.1.1.2. <u>ዘመናዊው ዋቄፈና ለመስፋፍያነት የተጠቀመው ዘዴዎች</u>

ከላይ እንደተመለከተው ዋቄፈና ምንም አይነት ኃይማኖታዊ ቁመና ባይኖረውም ኃይማኖቱ ግን አጭር ጊዜ ውስጥ ብዙ ተከታዮችን ከክርስትናው መውሰድ ችሏል፣ ኃይማኖቱም ይህንን ማድረግ የቻለው ጊዜያዊ አጭበርባሪ የሆኑ እስትራቴጂዎችን በመጠቀም ነው፣ እነዚህ እስትራቴጂዎቹም:-

- "ዋቄፈታነት ኦሮሞነት፣ ኦሮሞነት ዋቄፈናነት" ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ፣
- ዋቄፈና የገዳ አስተዳደራዊ ስርዓት አካል ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ፣
- ዋቄፈና የኦሮሞ ባህል አካል ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ፣
- የኢሬቻ በዓልን የኦሮሞ ባህላዊ የምስጋና ቀን "Thanks giving Day" በማስመሰል ነው፣

ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን::

1. <u>**"ዋቄፈታነት ኦሮሞነት፣ ኦሮሞነት ዋቄፈናነት" ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ፣**</u>

ዋቄፈና የአይሁድና የእስልምናን መጽሐፍትን በመጥቀስ [41] "የአይሁድና የዓረብ ህዝቦች የራሳቸው ኃይማኖት አላቸው ኦሮሞም የራሱ ኃይማኖት ዋቄፈናን አለው፣ ስለዚህ ኦሮሞ ሆኖ የራሱን ትቶ እነዚህን የባዕድ ኃይማኖቶች መከተል ማለት ራስን አለማወቅ ነው::" የሚል አስተምህሮን ይከተላል፣ በዚህም በኦሮሞነትና በዋቄፈታነት መሃከል ምንም ልዩነት እንደሌለና ወደ ዋቄፈና ያልመጣ ኦሮሞ የኦሮሞ ብሔርተኝነት (sabbonummaa) በውስጡ የሌለ፣ የአስተሳሰብ ባሪያ ሰው እንደሆነ ያስምራል::

በርግጥ በ2.2 ክፍል እንደተመለከትነው በሙሐመድ በኩል የወረደው እስልምና የተላከው ለዓረብ ህዝብ ነው እንደዚሁ በሙሴ በኩል የወረደው የአይሁድ ኃይማኖት የተላከው በስጋ የዘር ሀረጋቸው እስራኤላውያን ለሆኑት ብቻ ነው ነገር ግን ከክርስትና ጋር በተያያዘ "ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች፣ የእስራኤል አምላክ ..." የሚሉትን ቃላት በመውሰድ ብቻ "ክርስትናም ለእስራኤል ብቻ ነው የተላከው" የሚለው አባባል ስህተት ነው::

[41] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 18-19

ይህም ስህተት የመጣው “እስራኤል” የሚለውን ቃል ከስር መሠረቱ ካለመረዳት ነው፣ በመጀመሪያ “እስራኤል” የተባለው ያዕቆብ ነው፣ ከዚያም በሂደት ይህ ስም የአስራ ሁለቱ የያዕቆብ ልጆች ዘሮች ስም ሆነ፣ ከዚያ በሂደት እነኚህ ዘሮች የሚኖሩባት ሀገር መጠርያ ሆነ ነገር ግን ከመጀመሪያው “እስራኤል” የሚለው ስም ለያዕቆብ የወጣው “አማኝ” በሚለው ትርጉሙ ነው።።

መጽሐፍ ቅዱሱ፣ በአዲስ ኪዳን ክፍል፣ ይህን የእስራኤላዊነት “አማኝ” ትርጉምና “ሀገር” ትርጉም የተለያየ መሆንና ሰዎችም በዚህ የተለያየ ትርጉም እንዳይምታቱ አስቀድሞ አስተምሯል(ሮሜ.9፡6-8, ገላ.4፡22-31 ...)፣ ይህንኑ እውነታም በተግባር ማረጋገጥ ይቻላል፣ በሀገር እስራኤላዊ የሆኑት እስራኤላውያን የአይሁድ እምነት ተከታዮች እንጂ በኢየሱስ በኩል የወረደውን የክርስትና እምነት ተከታዮች አይደሉም፤ በመጽሐፍ ቅዱሱ የራዕይ መጽሐፍም በገነት የሚኖሩት ሰዎች ከሁሉም ዘሮች የተውጣጡ ሰዎች እንደሚሆኑ ይናገራል(ኤፌ.3፡5-6, ራዕ.5፡9-10 ...)፣ እነዚህ እውነታዎችም ክርስትና የወረደው ለሁሉም ዘሮች መሆኑን ያሳያሉ።።

በዚህም ኃይማኖቶችን በብሔር የመከፋፈል አሰራር የሚሰራው ለክርስትና ሳይሆን ለአይሁድና ለእስልምና ኃይማኖቶች ነው፣ በዚህም አንድ ኦሮሞ በብሔር-ኃይማኖት ስሌት ከእስልምና ወይ ከአይሁድ ኃይማኖት ወደ ዋቄፈታነት ቢመለስ ምክንያታዊ ቢሆንም በኃይማኖት-ብሔር ስሌት ካልተሰራው ከክርስትና ወደ ዋቄፈታነት መመለሱ ግን ስህተት ነው።።

በሌላ በኩል ደግሞ ኦሮሞነትንና ዋቄፈታነትን በዚህ መልክ በማያያዝ ዋቄፈታ ያልሆነውን ኦሮሞ የአስተሳሰብ ባርያ አድርጎ መመልከቱ መሠረታዊውን የግለሰቦችን የኃይማኖት ነፃነት መብትን የሚጎዳ አሰራር ነው፣ አንድ ኦሮሞ ሙስሊም፣ ክርስቲያን፣ ኤቲስት ... መሆኑ “የአስተሳሰብ ባርያ” አድርጎ መተርጎም በሕግ የሚያስጠይቅ የሰብአዊ መብት ጥሰት ነው፣ ኃይማኖት የግል ብሔር/ሀገር ደግሞ የጋራ ማንነት ነው።።

ለኃይማኖት ማስፋፊያት ብሎ የኃይማኖት-ብሔር ጥምረት እስትራቴጂን መጠቀሙም ለኃይማኖቱ ይጥቀመው እንጂ የብሔሩን ማንነት ግን የሚጎዳ አካሄድ ነው፣ ምክንያቱም፣

- በዋቄፈታ እምነት ላይ የሚታዩት ድክመቶች(ቅዱስ መጽሐፍ ማጣት፣ ኃይማታዊ መዋቅር ማጣት ...) የኦሮሞ ድክመት ተደርጎ እንዲወሰድ ያደርጋል፣
- ኃይማኖትን በብሔር ከከፋፈልን ኦሮሞ ከመቶ አመታት በላይ ተሸንፎ የነበረው “አምላኩ ተሸንፎበት ነበር” የሚል እንድምታን ይፈጥራል፣ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ የኦሮሞ አምላክ የሚባለው ዋናው ፈጣሪ አምላክ ሳይሆን ሊሸነፍ የሚችል አከባቢያዊ ጣኦት ሊሆን ነው።።

በዚህም ዋቄፈና “የኃይማኖት ብሔር ጥምርታ” እስትራቴጂን ዋነኛ የኃይማኖት ማስፋፊያ እስትራቴጂ አድርጎ ይጠቀምበት እንጂ አካሄዱ የተሳሳተ ይባሉኑም የግለሰቦች

መብትና የብሔሩ ማንነት የሚጎዳ እስትራቴጂ በመሆኑ ይህ የዋቄፈና እስትራቴጂ እየተባነነበት ሲሄድ ኃይማኖቱ ባዶውን የሚቀርበት እድል ሰፊ ነው፡፡

2. <u>ዋቄፈና የገዳ አስተዳደራዊ ስርዓት አካል ተደርጎ እንዲወሰድ በማረግ</u>

ሌላው ለዋቄፈና ኃይማኖት መስፋፋት ትልቁን አስትዋፅዖ እያበረከተ ያለው ኃይማኖቱ ራሱን የገዳ አስተዳደራዊ ስርዓት አካል አድርጎ ማቅረቡ ነው፣ በዚህ የኃይማኖቱ እስትራቴጂም ብዙዎች የገዳ ስርዓትን ለመደገፍ ሲሉ ዋቄፈታኑትን እንዲደግፉና እንዲቀበሉ፣ የገዳ አባቶችም የዋቄፈና ኃይማኖትን በባለቤትነት እንዲይዙ ሲደረግ እየተመለከትን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ዛሬ ላይ የገዳ ስርዓትና የዋቄፈና ጥምረት ትክክለኛ የሚሆነው ሁሉም ኦሮሞ የዋቄፈና ኃይማኖት ተከታይ ቢሆን ነበረ፣ ዛሬ አብዛኛው ኦሮሞ የሌላ እምነት ተከታይ ነው፣ በዚህም ዛሬ ላይ የተሰራው የገዳ አስተዳደራዊ ስርዓትና የዋቄፈና ኃይማኖት ጥምረት አግባብ አይደለም፡፡ ጥምረቱም የገዳ ስርዓትን የሚጎዳ ጥምረት ነው ምክንያቱም ጥምረቱ የገዳ ስርዓት የብሔሩን የሌላው እምነት ተከታዮችን የማይወክልና በዚህም እነዚህ ሰዎች ከገዳ ስርዓት ደጋፊነት ዞር እንዲሉ የሚያደርግ እንደዚሁ ዋቄፈና እንደ ኃይማኖት ያሉበት ጉድለቶች(ቅዱስ መጽሐፍ፣ የኃይማኖት መዋቅር … ማጣቱ) የገዳ ስርዓት ጉድለት የሚሆንበትን ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

በዚህም የገዳ የአስተዳደር ስርዓት በሁሉም ኦሮሞ ዘንድ ተቀባይነትና ድጋፍ ለማግኘት ሲል እንዲሁም በዋቄፈና ምክንያት ደካማ ስርዓት ከመሆን ለመዳን ራሱን በኃይማኖታዊ ጉዳዮች ጣልቃ ከመግባት ነፃ ማድረግ ሲጀምር ዘመናዊው ዋቄፈና ባዶ የሚሆንበት እድል ሰፊ ነው፡፡

3. <u>ዋቄፈና የኦሮሞ ባህል አካል ተደርጎ እንዲወሰድ በማድረግ</u>

ዋቄፈና በኃይማኖት ተቋምነት ቢመዘገብም እየተንቀሳቀሰ ያለው ግን በዋናነት እንደ ኃይማኖት ተቋም ሳይሆን ራሱን የኦሮሞ ባህል አካል በማስመሰል ነው፡፡ ዋቄፈና ይህንን እስትራቴጂ የተከተለው ባህል ሁሉንም የብሔሩን አባላትና መንግሥትን የሚመለከት ጉዳይ በመሆኑና አይነኬ የማንነት ጉዳይ በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡

ዋቄፈና በዚህ እስትራቴጂውም ከመንግሥት፣ ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች፣ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ ከመረዳጃ ማኅበሮች … ሰፊ እገዛ እንዲያገኝ አድርጎታል፤ እነዚህ ድርጅቶችም ህዝቡን ለዋቄፈናነት ሲቀሰቅሱ፣ በፖለቲካ ሲደግፉ፣ ኃይማኖቱን ሲያስተዋውቁ፣ ሲያደራጁ፣ በበጀት ሲደጉሙ፣ የማምለኪያ ስፍራና ፕሮግራም ሲያዘጋጁ፣ ለኢሬቻን በዓል ዝግጅትና ድምቀት ሲንቀሳቀሱ … እየተመለከትን ነው፡፡

ይሁን እንጂ እነዚህ መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ከተደራጁለት ዓላማ ውጪ፣ በኃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ በመግባት፣ አንድን በኃይማኖት

ተቋምነት የተመዘገበን ኃይማኖታዊ ድርጅት ከሌላው ኃይማኖት ለይተው እያደረጉለት ያለው ድጋፍ ወንጀል ነው፣ ኢ-ህገ መንግሥታዊም ነው::

ለምሳሌ ጨምበላላ፣ ጊፋታ፣ አሸንዳን/ሶሎል ... በዓላት በመንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት ድጋፍ ቢያደርጉላቸው ችግር የለውም ምክንያቱም እነዚህ በዓላት ኃይማኖታዊ በዓላት ሳይሆኑ ባህላዊ በዓላት ናቸውና ነገር ግን በኃይማኖትነቱ ለሚታወቀውና በኃይማኖትነት ለተመዘገበው ለዋቄፈና ብሎም ለዋቄፈና ኃይማኖታዊ በዓል ለኢሬቻ የሚደረገው ድጋፍ ስህተት ነው::

በዚህም እነዚህ መንግሥታዊም ሆኑ መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ህጉንና ህገ መንግሥቱን ማክበር ሲጀምሩ፣ ኃይማኖቶችን በእኩል ዓይን መመልከት ሲጀምሩና ከተደራጁለት ዓላማ ውጪ በመውጣት በኃይማኖቶች መካከል ልዩነት መፍጠር ስህተት እንደሆነ መረዳት ሲጀምሩ ዋቄፈና ባዶውን የሚቀርበት እድል ሰፊ ነው::

4. <u>የኢሬቻ በዓልን የኦሮሞ ባህላዊ "የምስጋና ቀን" በማስመሰል</u>

የዋቄፈና ኃይማኖት ዋነኛ የህዝብ መሰብሰቢያ ዘዴ የኢሬቻ በዓል ነው፣ ዋቄፈና የኢሬቻ በዓል በክርስቲያኑ ኦሮሞ ህዝብ ዘንድ እንዲከበር እያደረገ ያለው ቀኑ የኦሮሞ ባህላዊ የምስጋና ቀን(Thanks giving Day) በማስመሰል ነው:: በዚህ ዘዴም ዋቄፈና የራሱን ኃይማኖታዊ በዓል ክርስቲያኖች እንደዲያከብሩለት እያደረገና በዓሉንም ለኃይማኖት ማስፋፍያነት እየተጠቀመ ይገኛል::

ይሁን እንጂ እነዚህ በ "የምስጋና ቀን" ስም በኢሬቻ መንፈስ እየተያዙ ያሉት ክርስቲያኖች፣ ከፈጣሪ ጋር የሚኖራቸውን ግንኙነት የሚመሩበት፣ <u>በየብሔሩ የመጨመርና የመቀነስ</u> ስራ የማይሰራበት ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው መሆኑና በዚህ መጽሐፋቸውም ላይ የኢሬቻ የምስጋና ቀን(Thanks giving Day) ያልታዘዘ መሆኑን እያስተዋሉ ሲሄዱ በ "የምስጋና ቀን" ስም የኢሬቻን በዓል የሚያከብሩበትና ሳያስተውሉ ጥቁሩን የዋቄፈናን አምላክ የሚያመልኩበትበት አሰራር እንደሚዳከም ግለፅ ነው::

በአጠቃላይ ስንመለከት ዋቄፈና የኃይማኖት አቋም ሳይኖረው በኦሮሞ ህዝብ ዘንድ እንደዚህ በአጭር ጊዜ ሊስፋፋ የቻለው ራሱን በማንነት ፖለቲካ፣ በገዳ ስርዓትና በባህል በመሸፈን እና ኃይማኖታዊ በዓሉን ባህላዊ የምስጋና በዓል በማስመሰል በሰራው የማጭበርበር ስራ እንጂ በኃይማኖታዊ ቁመናው አይደለም፣ ይህ የማጭበርበር አካሄዱ ደግሞ እየተነቃበት ሲሄድ ኃይማኖቱ ባዶውን እንደሚቀር ግልፅ ነው::

3.1.1.3. <u>የዋቄፈናና የክርስትና ሽኩቻ</u>

ዘመናዊው ዋቄፈና እንደ አዲስ ሲደራጅ ብዙ ሰዎችን መውሰድ የቻለው ከክርስትና ኃይማኖት ነው፣ የዋቄፈና ዋነኛ አትኩሮትም የክርስትና ኃይማኖቶች ላይ ሲሆን ራሱንም የክርስትና *መሠረት* አድርጎ ያስተምራል፣ እንደዚሁ ደግሞ ክርስትናውም ዋቄፈናንን "ቅድስና የጎደለው የሰይጣን አምልኮ" አድርጎ ይመለከተዋል፣ እነዚህን ሽኩቻዎች ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡፡

3.1.1.3.1. <u>የዋቄፈና አስተምህሮ - "የክርስትና *መሠረት* ዋቄፈና ነው"</u>

የዘመናዊው ዋቄፈና ምሁራን [42] "ዋቄፈና ከጥንት የሰው ልጅ *መፈጠር* ጀምሮ የነበረ ኃይማኖት ነው"፣ [43] "የክርስትና *መሠረትም* ዋቄፈና ነው" ይላሉ፣ ይህንንም ሲያስረዱ፣

- [44] "በኑቢያ ዘመን ዋቄፈና "ኦሲሪስ" በመባል ይታወቃል፣ ኦሲሪስ ከ6,500 አመታት በፊት ኑቢያኖች ሲከተሉት የነበረ ኃይማኖት ነው፣ የኩሽ ህዝቦችም ተገንጥለው ወጥተው የሞርሞር ሀይቅ፣ በጥቁር አባይ፣ አካባቢ ሰፍረው ሲኖሩ በነበረበት ወቅት በአንድ አምላክ በዋቄፈና ሲኖሩ ነበረ፣ ስለዚህ የሁሉም ኃይማኖቶች *መሠረት* ዋቄፈና ነው፡፡"
- [45] "*ሙሴና ኢየሱስ* ዋቄፈታ ነበሩ፣ የዋቄፈናን እምነት ከግብፅ ይዘው ወደ ሀገራቸው በመመለስ ክርስትናን ፈጠሩ፡፡"

ይሁን እንጂ እነዚህ የዘመናዊው ዋቄፈና ምሁራን የሚናገሩት ታሪኮች ለባህላዊው የዋቄፈና የኃይማኖት አባቶችም ሆነ ከሺ ዘመናት በፊት ለተቋቋሙት የአብርሃም ኃይማኖቶች ሆነ ለዘመናዊው ታሪክ እንግዳ የሆኑ፣ በኃይማኖት ሽኩቻ ምክንያት የማይገናኙ ታሪኮች የተገናኙበት ልቦወለዶች ናቸው፡፡

እውነታን ግን ከዚህ በተቃራኒ ነው፣ ዘመናዊው ዋቄፈና ራሱን "የክርስትና *መሠረት* ነኝ" ይበል እንጂ እውነታውን ስንመለከት ግን ክርስትናን ተደግፎ የቆመው ዋቄፈና ነው፤ ይህም ከቀላል "የኢሬቻ በዓል የሚከበረው የኦሮቶዶክሱን መስቀል ቀጥሎ ባለው እሁድ ነው" ከሚለው አባባል አንስቶ የሰው ልጅ ትልቁ ጥያቄ የሆነውን "ዓለም እንዴት

---

[42] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 19-20

[43] Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa**, fuula 16

[44] Maatii Sabaa (6400 ALW/206 ALA), **DAANIYAA**, fuula 56-57, Waldaa Aadaafi Dudhaa Oromoo(WADO)

[45] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 59, 91 fi
Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa**, fuula 17

ተፈጠረች፣ የሰው ልጅ እንዴት ተፈጠረ ...” ጥያቄዎችን የሚመልሰው በክርስትናው ላይ ተንተርሶ ቃላቱን ወደ ኦሮምኛና ኦሮሚያ በማስጠጋት ነው፣ ለምሳሌ [46]

- የዓለም ስነፍጥረት
  ክርስትና - በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ፣
  ዋቄፈና- በመጀመሪያ ዋቃ ኦሎና ጀሎን ፈጠረ፣
- የሰው ልጅ ስነ ፍጥረት
  ክርስትና - እግዚአብሔር አዳምን ከአፈር አበጀው፣ ከአዳምም ሄዋንን ሰራ
  ዋቄፈና - “ዋቃ” በመጀመሪያ አንድ ሰው ፈጠረ፣ ከዚያም ይህን ሰው ለሁለት በመክፈል ወንድና ሴት አደረጋቸው፣
- በመጀመሪያ የተፈጠሩት ሰዎች ስም
  ክርስትና - አዳምና ሄዋን ይባላሉ፣
  ዋቄፈና - አስዴምና ሀዌ ይባላሉ፣
- የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ሲኖሩ የነበረበት ስፍራ
  ክርስትና - ኤደን ገነት፣
  ዋቄፈና - ኤደደ ገናሌ፣

በመጀመሪያ ላይ ያለው “ሰማይና ምድር” የሚለውን በተመሳሳይ የኦሮሚኛ ቃል “ኦሎና ጀሎ” በሚል ተቀየሩ፣ “ኦሎ” ማለት የላይኛው ማለት ሲሆን “ጀሎ” ማለት ደግሞ የታችኛው ማለት ነው፡፡ በሁለተኛው ላይ ያለው ታሪክ ትንሽ ቅንብር ተደርጎለት ኮፒ የተደረገ ታሪክ ነው፡፡ ሦስተኛ ላይ የተመለከተው “አዳምና ሄዋን” የሚለው ሊተረጎም ስለማይችል፣ ቃሉን ወደ አቅራቢያ ተመሳሳይ የኦሮምኛ ቃል በማስጠጋት አዳምን “አስዴም”(ወደዚህ ና)፣ ሄዋንን “ሀዌ”(ስመኝ) በሚለው ቃል ተለውጧል፡፡ በአራተኛ ላይም የምንመለከተው ቀረብ ወዳለ የኦሮሚኛ ቃል የማጠጋጋት ስራ ነው፣ በዚህም “ኤደን ገነት” የነበረው “የኦሮሞ መነሻ ነው” ወደሚባለው “መደ ወላቡ” እና ገናሌ ወንዝ በማጠጋጋት “ኤደደ ገናሌ” በሚለው ቃል ተለውጧል፡፡

በዚህም ዋቄፈና የክርስትናውን ታሪክ እንዳለ በመውሰድና ኦሮሚኛ በማድረግ የስነፍጥረት ታሪኩን ጉድለት ለሚሟላት ሞክሯል፣ በነዚህ የታሪክ ሽሚያ ውስጥ የሚያስገርመው ነገር ዋቄፈና በመጀመርያ የተፈጠሩት ሁለቱ ሰዎች የሚናገሩት ቋንቋ ኦሮምኛ እንደሆነ ይነግረናል ¡

ዘመናዊው ዋቄፈና ከመጽሐፍ ቅዱሱ ሁሉንም ታሪክ እንዳለ ለመልገበጥ ሀፍረት ስለያዘው ሌሎች ነገሮችን በዝምታ ነው ማለፍ የፈለገው፣ በጀመረው የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪኮች ኦሮምኛ በማድረግ መንገድ መግፋት አልደፈረም፣ የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ ምን

[46] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 21-23

ይሆናል? የቁሳዊው ዓለም የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምንድነው? የፈጣሪ የወደፊት እቅድ ምንድነው? … ለሚሉት ጥያቄዎች ዋቄፈና ምንም መልስ የለውም፡፡ የስነ ፍጥረቱ ታሪክ ላይም ከአዳምና ሄዋን ታሪክ በቀጥታ ወደ ኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ነው የሚወርደው፣ በዚህ መካከል ስላለው የሰው ዘር በዝምታ ነው የሚያልፈው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ግን ከአዳም ታሪክ ቀጥታ ወደ እስራኤል ታሪክ አልወረደም፣ በዚያ መካከል ስላለው ሌሎች ዘሮች አመጣጥም ይዘረዝራል፣ ኦሮሞ ያለበትን የኩሽቲክ ዘር እንኩዋን እንዴት እንደመጣና የኩሽ ልጆች እነማን እንደሆኑ እንኳን ያስተምራል፡፡

በዚህ የታሪክ ሽሚያ ውስጥ አብዛኞቹ የዋቄፈና ኃይማኖት መጽሐፍት እየተምታቱ የተቸገሩበት ነገር አንዴ [47]“ዋቄፈና ከሰው ልጅ መፈጠር አንስቶ የነበረ ኃይማኖት ነው” እያሉ ተመልሰው ደግሞ [48]“ዋቄፈና የኩሽ ህዝቦች ባህል፣ ፍልስፍና፣ ዕውቀትና ጥበብ ነው” እያሉ ያለበት ሁኔታ ነው፡፡

ዘመናዊው ዋቄፈና ራሱን “ከፍጥረት ጊዜ ጀምሮ የነበረ ኃይማኖት” በማድረግ የስነ ፍጥረት ታሪክ ጋር በመሄድ ከክርስትናው ጋር የታሪክ ሽሚያ ውስጥ ይግባ እንጂ ዋቄፈና ከኦሮሞ ውጪ በሌሎች ክርስትናና እስልምናን ባልተቀበሉ ህዝቦች ዘንድ ቢያንስ በሌሎች የኩሽቲክ ብሔሮች እንኳን አለመታወቁ፣ በዋቄፈና ውስጥም ከኦሮሞ ብሔር ማንነት፣ እሴቶች … ውጪ ስለሌሎች ኩሽቲክ ስለሆኑ እንደ ሱማሌ፣ አፋር፣ ሲዳማ … ብሔረሰቦች ማንነት፣ ዕሴት … ምንም አለመነገሩ፣ ዋቄፈናን የፍጥረት መጀመሪያ ይቅርና ኩሽቲክ ጋር እንኳን ማድረስ እንዳንችል ያደርገናል፡፡

በዚህም በዋቄፈና ራሱን የክርስትና መሠረት ያደረገበት ሁኔታ ተጨባጭነት የሌለው ተራ ፉክክር ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

3.1.1.3.2. <u>የክርስትና ትችት በዋቄፈና ላይ</u>

ክርስትናው ጋር ስንመጣ ክርስትና ዋቄፈናን የሚተቸው፣

- “ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ አይደለም”
- “ዋቄፈና የሚያመልከው ብዙ አማልክትን ነው”
- “ዋቄፈና ጣኦታዊ/ሰይጣናዊ ነው”

በሚሉ ሂሶች ሲሆን ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡-

[47] Maatii Sabaa (6400 ALW/206 ALA), **DAANIYAA**, fuula 55, Waldaa Aadaafi Dudhaa Oromoo(WADO)

[48] Maatii Sabaa (6400 ALW/206 ALA), **DAANIYAA**, fuula 51, Waldaa Aadaafi Dudhaa Oromoo(WADO)

- **“ዋቄፈና የሚያመልከው ዋናውን አምላክ አይደለም”**

ዋቄፈና ራሱን ከዋናው ፈጣሪ ጋር ቢያገናኝም ኃይማኖቱ በአንድ ሀገር፣ ያውም በአንድ ብሔር፣ ያውም በተወሰኑ የብሔሩ ተወላጆች፣ ያውም በተጭበረበረ እስትራቴጂ፣ ያውም ባለው የፖለቲካ ይሁኝታነት ተወስኖ የሚሄድ መሆኑ ዋቄፈና የዋናውን አምላክ ተከታይ ሳይሆን በብዙ ነገሮች የሚወሰን አነስተኛ አምላክን የሚከተል ኃይማኖት መሆኑን ያሳያል። ይህንንም አምላክ ደግሞ ዋቄፈናም በራሱ “የኦሮሞ አምላክ”፣ “ጥቁር የሆነው የጥቁሮች አምላክ” … ማለቱ የዋቄፈና አምላክ ዋናው አምላክ ሳይሆን በብሔር ወይ በቀለም የተገደበ አነስተኛ አምላክ መሆኑን ያመላክታል።

- **“ዋቄፈና የሚያመልከው ብዙ አማልክትን ነው”**

ዋቄፈና ራሱን የዋናው አንድ አምላክ ተከታይ ኃይማኖት ቢያደርግም በውስጡ ግን ብዙ የሚሰገድላቸውና መስዋዕት የሚቀርብላቸው አማልክትን አሉት፣ ለምሳሌ ያህል፡-

1. “አያና”(ውቃቢ) የሚባለው ስግደት የሚደረግለት መንፈስ፣ [49] “እያንዳንዱ ሰው ለራሱ፣ ለአባቱ(ቦረንቲቻ)፣ ለእናቱ(አቴቴ) እና ለሀገሩ አያና መስገድ ይገባዋል።”
2. [50] ቃልቻ(Raaga/”ነቢይ”)፣ [51] አያንቱ/አያና ለሚባሉት በገልማ/ጊምቢ ስግደት የሚደረግላቸው አማልክትን ይመለካሉ፣
3. [52] አቴቴ፣ ስሟ ከማሪያም ጋር የሚመሳሰል “ማረም” የምትባለው “የወሊድ መንፈስ” የምትመለከበት ስነ ስርዓት፣ ለዚህች አምላክም በሀገር ደረጃ በኢሬቻ ሳምንት በቡራዩ መልካ አቴቴ ታላቅ ክብረ በዓል የሚደረግላት ሲሆን በቤተሰብ ደረጃም እናቶች በራሳቸው ፕሮግራም መሠረት “Atetee facaafachu” የሚባል የአምልኮ ስነ ስርዓት ያደርጋሉ።
4. [53]“ቦረንቲቻ”፣ ይህ ለታላቅነት/ለቦረናነነት ውቃቢ የሚደረግ የአምልኮ ስነ ስርአት ነው፣ ፕሮግራሙም የሚጀመረው ጥቁር በሬ በማረድና ሞራውን በማንበብ ወይ ቤት ውስጥ በመለጠፍ ነው።

እነዚህን እውነታዎችም ዋቄፈና ከአንድ አምላክ አምላኪነት ይልቅ የብዙ አማልክት አምላኪነቱን ያሳያል።

---

[49] Tarruu Unguree(LLB)(2015)፣ **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa,** fuula 43-50

[50] ibid, fuula, 42-43

[51] ibid, 64, 90

[52] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**, fuula 121

[53] Maatii Sabaa (6400 ALW/206 ALA), **DAANIYAA**, fuula 263-265, Waldaa Aadaafi Dudhaa Oromoo(WADO)

➢ **<u>“ዋቄፈና ጣኦታዊ/ሰይጣናዊ ነው”</u>**

ዋቄፈና ብዙ አማልክትን የሚያመልክ ኃይማኖት በመሆኑ በውስጡ ጣኦታዊ/ሰይጣናዊ እሴቶችን ይዟል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- ዋቄፈና እንደ ቅዱስ የሚመለከታቸው [54]“የኮከብ ቆጣሪነት፣ የሙት መንፈስ ሳቢነት፣ ማሊማ/ጫምሲቱ(ዝናብ ላይ ስልጣን ያለው መንፈስ)፣ ራግዱ(“ነቢይ”)፣ ሞራ ገላጭ፣ ጨሌ/ጠጠር የሚቆጥሩ፣ መዳፍ፣ ጀበናና የዕጣን ጢስ የሚያነቡ … የኃይማኖቱ እሴቶች መሆናቸው፣
- [55] መካደም፣ [56] የመስዋዕት ዕርድ፣ [57] የምግብ መስዋዕት “ደደርባ/daddarbaa (ከመብላትና መጠጣት በፊት የተወሰነውን መጣል/ማፍሰስ) እና ዲባዩ/Dhibaayyuu (መስዋዕቱ በተወሰነ ስፍራ ብቻ የሚቀርብበት የአምልኮ ስነ ስርዓት)፣
- በኢሬቻ በዓል አከባበር ላይ የአካባቢው ሰዎች በዚያን ቀን በስፍራው የሚያካሂዱት እርድ፣ ዛፍ እንጨት መቀባት፣ አረቄ ሀይቁ ውስጥ መጣል…

እነዚህ ኃይማኖታዊ ስነ ስርዓቶችም የሚያሳዩት ኃይማኖቱ እንደየትኛውም ኋላ ቀር ኃይማኖት ኢጋንንታዊ መሆኑን ነው፡፡

ከነዚህ አከባቢያዊ ጉዳዮች በተጨማሪም ዋቄፈና ስለሚያመልከው አምላክም ሲናገር [58]ፈጣሪ ጥቁር ነው፣ [59]ጥቁርነት የኃያላን ኃያልነት፣ ቅድስና፣ አምላክነት ማለት ነው” ማለቱና በክርስትናው የሚመለከው ፈጣሪ ደግሞ በነጭና ብርሃናማ አገላለፆች መገለፁ፣ እነዚህ ሁለቱ ኃይማኖቶች በተቃራኒ ኃይላት እንደሚመሩ ያሳያል፡፡ ሁለቱም ጋር የተጠቀሰው ቀለም ደግሞ የቀለም ጉዳይ ሳይሆን ምሳሌያዊ አገላለፅ ነው ምክንያቱም ክርስትናው “አምላክ መንፈስ በመሆኑ እንደ ሰው ስጋና ደም የለውም” ስለሚል ዋቄፈናም [60] “ፈጣሪ በዓይን አይታይም” ስለሚል፡፡

በምሳሌያዊ አነጋገሩም ክርስትናው ፈጣሪን “ነጭና ብርሃናማ” በማለት መግለፅ የፈለገው ቅድስናውን ለማመልከት መሆኑና ነገር ግን ዋቄፈና “ዋቃ ጉራቻ/ጥቁር አምላክ”

---

[54] Tarruu Unguree(LLB)(2015), **Waaqefannaa, amantii duudhaa ganamaa,** fuula 64-65

[55] ibid, 90-91

[56] ibid, 117

[57] ibid, 76

[58] Dirribii Damusee Bokkuu(2016) - Pirezidaantii Maccaaf Tulamaa, **Ilaalcha Oromoo**,fuula, 124

[59] Maatii Sabaa (6400 ALW/206 ALA), **DAANIYAA**, fuula 50, Waldaa Aadaafi Dudhaa Oromoo(WADO)

[60] Maatii Sabaa (6400 ALW/206 ALA), **DAANIYAA**, fuula 48, Waldaa Aadaafi Dudhaa Oromoo(WADO)

የሚለው ውስጥ “ጉራቻ” የሚለው ቃል ምሳሌነት የሚነሳው በመጥፎ ጎን መሆኑ፣ ለምሳሌ በኦሮምኛ እንኳን “Baga Gurraacha gannaatii baga booqa birraatti dabarte - እንኳን ከጥቁሩ ከረምት ወደ ብርሃናማው ፀደይ አሸጋገረህ” እንደሚባለው፣ እንደዚሁ የአንድ ሰውን ቀናተኝነት ለመናገር “ለምን ፊትህ ጠቆረ”፣ መቆሸሸን ለማመልከት “እንደ ጥላሸት የጠቆረ” … መባሉ፣ የዋቄፈናና የጥቁር አምላክ ጥምረት የዋቄፈናን ኢጋንንታዊነት ያረጋግጣል።

በአጠቃላይ ስንመለከት ዘመናዊው ዋቄፈና ራሱን በዘመናዊ ፍልስፍና አደራጅቶ ይቅረብ እንጂ ኃይማኖቱ እንደየትኛውም ኋላ ቀር ኃይማኖት ጣኦታዊ/ሰይጣናዊ ኃይማኖት እንጂ ዋናውን አምላክ የሚከተል ኃይማኖት አለመሆኑን እና ዘመናዊው ዋቄፈናም ጥንታዊውን ዋቄፈና በአዲስ ፍልስፍና አደራጅቶ ከዓለማቀፋዊ ኃይማኖቶች እኩል ለማድረግ ያዘጋጀው ፍልስፍና ባዶ መሆኑን እንመለከታለን።

ከሁሉ በላይ ሊስተዋል የሚገባው ነገር ደግሞ በዋቄፈና ውስጥ ያሉት ኃይማኖታዊ እሴቶች በሙሉ በሁሉም ኋላ ቀር ኃይማኖቶች ውስጥ የምንመለከታቸው ሰይጣናዊ እሴቶች(Values specific to satan) እንጂ የኦሮሞ እሴቶች(Values specific to Oromo) አለመሆናቸውን ነው፣ በዚህም በሁሉም ኋላ ቀር ኃይማኖቶች የምናገኛቸውን ዕሴቶችን የኦሮሞ ማንነቶች አድርጎ በፖለቲካው አስደግፎ እየተሄደ ያለው የዘመናዊው ዋቄፈና አካሄድ ሰይጣናዊ ሜራ ብቻ ነው፣ በዚህም ማንም በብሔር ስም በጭፍን ከመነዳት በየትኛው መናፍስታዊ ጎራ እየተሰለፈ እንዳለ ሊያስተውል ይገባል።

የስህተት አሰራሮችን አስቀድሞ የሚያስጠነቅቀው መጽሐፍ ቅዱስ፣ ከክርስትና ወደ መሰል ኋላ ቀር ኃይማኖቶች ለሚመለሱት አስቀድሞ የራሱ መልዕክት አስቀምጧል፣

> Isa.1:28-29 “… Warri waaqayyo irraa debi`anis hin badu; Qilxuu jalatti hirreefattanii itti gammaddan sanaaf yeella`uuf jirtu, iddoo dhaaba isa fo`attan sanaafis salphachuuf jirtu;”

3.1.2. ራስ ተፈሪያን

[61] የራስ ተፈሪያን ኃይማኖት ከ1930 ጀምሮ በሂደት የተመሠረተ ኃይማኖት ሲሆን ኃይማኖቱ በአሁኑ ጊዜ ከአንድ ሚሊየን በላይ ተከታዮች አሉት፡፡ የራስ ተፈሪያን እምነት ተከታዮችም በብዛት የሚገኙት በካሪቢያን አካባቢ በተለይ በጃማይካ ሀገር ሲሆን በኢትዮጵያ ሻሸመኔ አካባቢ እንዲሁም በአሜሪካና በእንግሊዝ በተወሰነ መጠን ይገኛሉ፡፡

የራስ ተፈሪያን ኃይማኖት ተከታዮች “የምናመልከው አንዱን ሰማይና ምድርን የፈጠረውን አምላክ ነው” ይላሉ፣ ይህንንም አምላክ “ጃህ” ብለው ይጠሩታል፣ ይህም ስም “እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የተጠራበት “ጄሆቫ” ከሚለው ስም የተወሰደ ነው” ይላሉ፡፡ ኃይማኖቱ ከሌሎች የክርስትና ኃይማኖቶች የሚለየው በዋናነት ንጉሥ ኃ/ሥላሴን “መሲህ” ማድረጉ፣ የኢትዮጵያ ምድር “የተስፋይቱ ምድር/ጽዮን” ማለቱ፣ የእግዚአብሔር ምርጥ ህዝቦች “ጥቁር ህዝቦች ናቸው” ማለቱና ከነዚህ ጋር በተያያዙ አስተምህሮዎቹ ነው፡፡

የኃይማኖቱ አመሠራረት ታሪክም ከቅኝ ግዛት ዘመን ፖለቲካ ጋር የተያያዘ ነው፣ በቅኝ ግዛት ዘመን የአፍሪካ ጥቁር ህዝቦች በአውሮፓውያኑ ነጭ ወራሪዎች መጠን የለሽ ግፍ ሲፈፀምባቸው ቆይቷል፣ ከነዚህ ውስጥ ዋነኛው ግፍ የተፈፀመባቸው በነጮች የባርያ ንግድ ከአፍሪካ ተሸጠው በአውሮፓ፣ በካሪቢያን፣ በላቲንና በሰሜን አሜሪካ በባርነት በጉልበት ስራ እንዲሰማሩ የተደረጉት ጥቁር አፍሪካውያን ዋነኞቹ ናቸው፡፡

[62] በ1833 አብርሃም ሊንከን የባርያ ንግድ እንዲቆምና በባርነት የተያዙ ሰዎች ነፃ እንዲወጡ ሲያውጁ በአብዛኛው ባርያዎች በነበሩ ነዋሪዎቿ የምትታወቀው ጃማይካ የጥቁሮች ሀገር ሆና ተመሠረተች፣ በወቅቱም የነዚህ ጥቁር ህዝቦች መሪ፣ አክቲቪስትና “ወደ አፍሪካ እንመለስ” እንቅስቃሴ መሪ የነበረው ማርከስ ጋረቬይ በውስጡ ያለውን ራዕይ(በሂደት ትንቢት የተባለ ንግግር) ተናገረ “አፍሪካ ላይ ጥቁር ሰው ሲነግሥ ነፃነታችን እንደቀረበ እወቁ” አለ፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ ኃ/ሥላሴ በ1930 እኤአ ኢትዮጵያ ላይ ንጉሥ ሆነው ተሾሙ፣ ሹመታቸውም ዓለማቀፍ ዜና ሆነ፣ በንግሥናቸው ፕሮግራም ላይም ከዓለም ዙርያ ብዙ ልዑላንና የመንግሥት ተወካዮች የተገኙ ሲሆን በወቅቱ ኒውዮርክ ታየምስ ስለ ንግሥናቸው ሰፊ ሽፋን በመስጠት ዘገበ፣ በዚህ ጊዜ የማርከስ ጋርቬይ ተከታዮች የመሪያቸው ትንቢት ፍፃሜ እንደደረሰ አወጁ፡፡

በዚህ ላይ ደግሞ አፄ ኃ/ሥላሴ ራሳቸውን፣ ኢየሱስ በተጠራበት ስም፣ “ሞአ አንበሳ ዘእምነ ነገደ ዘ ይሁዳ”(ራዕ5፡5) ብለው መጥራታቸው እንዲሁም በኢየሱስ ሹመት

[61] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Rastafari
[62] www.bbc.co.uk.guides

“የነገሥታት ንጉሥ”(ራዕ.17፡14, ራዕ.19፡16) ብለው ራሳቸውን መሾማቸው፣ አፄውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አገናኝቶ “የጥቁሮች መሲህ” ለማለት ተጨማሪ አስትዋፅዖ አበረከተ።።

[63] እንደነ ሊኦናርድ ሆዌል ያሉ የክርስትና ቀሳውስት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስለ ኢትዮጵያ የተነገሩትን ቃላት (ዘፍ.2፡13, መዝ.68፡31, አሞ.9፡7, ራዕ.5፡5 …) በማገናኘት የንጉሡን “መሲህነት”ና የኢትዮጵያ ምድር “ተስፋይቷ ምድር/ጽዮን” መሆን መሰከሩ።።

ከዚያም ከጥቂት አመታት በኋላ የኢጣልያን ወረራ ተፈፀመ ኃ/ሥላሴም ከሀገር ሸሹ፣ ከዚያም ኢትዮጵያ ነፃነቷን ካገኘች በኋላ ንጉሡ በ1966 እኤአ ወደ ጃማይካ ተጓዙ፣ በዚህ ጊዜም የአፄውን መሲህነት የተቀበለው የጃማይካ ህዝብ ትልቅ አቀባበል አደረገላቸው።።

ከዚህ የንጉሡ ጉብኝትና የህዝቡ ታላቅ አቀባበል በኋላም ኃይማኖቱ በተለያዩ ፍልስፍናዎች እየጠነከረ መጣ፣ ራሱንም በቀኝ ገዢ ነጮች ከሚመራው “የነጮች ክርስትና” ተፅዕኖ ነፃ በሚያደርግ፣ በጥቁር ህዝቦች ላይ የነበረው የባርነት የስነልቦና ጫና “በሚጠግን”ና የጥቁር ህዝቦችን ማንነት በሚያንፀባርቅ መንገድን ራሱን አደራጅ።። በዚህም ኃይማኖቱ፣ በራሱ ጥቁር የኃይማኖት መሪዎች የሚመራበትና ከዚያም ባለፈ በክርስትና ውስጥ የነበሩትን “ነጭ ተኮር” አስተምህሮዎችን ወደ ጥቁርነት የመቀየር ሰፊ ስራዎች መስራት ጀመረ፣ ከነዚህ ውስጥም፣

- “ፈጣሪ በመጀመሪያ ጥቁር ህዝቦችን ፈጠረ፣ ከዚያም ሰዎች ኃጢያትን ሲሰሩ ኃጢያት የሰሩ ሰዎችን ከለር ከላያቸው ላይ አጠፋ፣ በዚህም ኃጢያተኞቹ ነጭ ሲሆኑ የፈጣሪ ምርጥ ህዝቦች ደግሞ ጥቁሮች ናቸው፣ የቀደምት እስራኤላውያን ጥቁሮች ነበሩ፣ ኢየሱስም ጥቁር ነበረ፣
- መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፃፈው በአፍሪካ ቋንቋ በአማርኛ ነው።።”

የሚሉት ይገኙባቸዋል።።

በዚህም እስትራቴጂ ቤተክርስቲያኗ ከጅማሮው በጥቁሩ ማኅበረሰብ ዘንድ የመስፋፋት ሁኔታ ብታሳይም ይህ የመስፋፋት ታሪካ ግን የጥቂት ጊዜ ታሪክ ብቻ ነበረ፣ ይህም ለጥቁሮች ስነልቦና ተብለው የገቡት ልቦለዶች በሂደት በገጠማቸው ፈተና ነው፣

- “መሲህ” የተባሉት ኃ/ሥላሴ መገደልና እንደ መሲሁ ኢየሱስ ከሞት መነሳት አለመቻል፣
- የተስፋይቱ ምድር(ኢትዮጵያ) ህዝቦች በረሀብና እርስ በርስ ጦርነት መርገፍ፣
- መጽሐፍ ቅዱስ ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ አለመፃፉና አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም መሆኑ እየታወቀ መምጣቱ፣

[63] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Rastafari

- ጥቁርና ነጭም የሚለዩት በኃጢያት መስራት አለመስራት ሳይሆን በጂኦግራፊ ክልል ሰዎች ለአየር ፀሐይ ባላቸው ተጋላጭነት የሚወሰን መሆኑ

... የመሳሰሉት ትርክቶች ረጋ ተብሎ ሲታይ ሁሉም ውሸት መሆናቸው እየተስተዋለ መጣ። ኃይማኖቱም ምንም እንኳን በሙሐመድ ነቢይነት ስም ከክርስትናው በተገነጠለው እስልምና መንገድ፣ በአፄ ኃ/ሥላሴ መሲህነት ስም ከክርስትና ቢገነጠልም ኃይማኖቱ እንደ እስልምና ጂሀድን የመሳሰሉ ጠንካራ ኃይማኖት ማስፋፍያ እስትራቴጂዎች ባለመቀየሱ ምክንያት በሂደት የመዳከም ምዕራፍ ውስጥ ገባ። ነገር ግን በዚህ የመዳከም ሂደት ውስጥ በ1970ዎቹ የተነሳው "የሬጌው ንጉሥ" ቦብ ማርሊይ በጃማይካው የሬጌ ሙዚቃ ስልት ባገኘው ዓለማቀፋዊ ታዋቂነት፣ ኃይማኖቱም ዳግም የማንሰራራት ዕድል መልሶ አገኘ።

"ቦብ ራስ ተፈሪያን ነው" ይባል እንጂ ዘፈኖቹ ውስጥ ግን የምንመለከተው የኃይማኖት ፍልስፍና ራስ ተፈሪያንነትን አይደለም፣ እስቲ ለምሳሌ "Get up, stand up" ዘፈኑ ውስጥ ጥቂት ስንኞችን እንመለከት፡-

"Most people think Great God will come from the skies

Take away everything and make everybody fill high

...

Almighty God is a living man ..."

እነዚህን ስንኞች "ከሰማይ የሚመጣ አምላክ የለም፣ ሰው እራሱ አምላክ ነው" የሚል ፍቺ የሚሰጡን ሲሆን ይህም የሚያሳየው ቦብ ሲከተል የነበረው "ሰው እግዚአብሔር ነው" የሚለውን በቀጣይ ምዕራፍ የምንመለከተው የሂውማኒዝም አስተምህሮ እንጂ የአንድ አምላክ የራስ ተፈሪያን አስተምህሮ አይደለም።

በርግጥ መጽሐፍ ቅዱሱ የሚያወግዘው የ"ዘፋኝነት" ህይወት ውስጥ ያለ ሰው የኃይማኖት የጀርባ አጥንት መሆን እንደማይችል ስንመለከት እንደዚሁ የአብዛኞቹን የኃይማኖቱ ተከታዮች ህይወት የዘፋኝነትና ሱሰኝነት ህይወት መሆኑን ስንመለከት ኃይማኖቱ ከትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱስ መንገድ አለመሆኑንና ኃይማኖቱ የጥቁሮችን ሞራል ለመገንባት ሲባል ብቻ የተቋቋመ ኃይማኖት እንጂ በመንፈሳዊ እውነታ ላይ ተመስርቶ የተጀመረ ኃይማኖት አለመሆኑን እንረዳለን።

የሚያሳዝነው ነገር የዚህ ማኅበረሰብ የኃይማኖት መሪዎች ህዝቡን በውሸት ትርክት ሞራሉን ለመጠገን ከመልፋት ይልቅ፣ እነዚህ ህዝቦች በስጋዊ ህይወታቸው የተጎዱትን ጉዳት ትክክለኛውን መንፈሳዊ መንገድ በማሳየት በመንፈሳዊው ዓለም እንዲካሱ በረዱ ኖሮ መልካም ነበረ፣ የምድሩ ሞራላዊ ጉዳት ለመጠገን ተብሎ የምድሩም በአግባቡ ሳይጠገን ሰማያዊውን ጉዳትን ማምጣት፣ ህዝቡን ከባሪያ ነጋዴዎቹ በላይ መጉዳት ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ሌላው አሳዛኝ ነገረ አሁን ያለው የጃማይካውያን ትውልድ እንደ ቀደምቱ ትውልድ በባርነት ህይወት ውስጥ አላለፈም፣ ሁሉም በነፃነት ተወልዶ በነፃነት ያደገ ሆኖ ሳለ አሁንም የጃማይካ ህዝብ እንደ ህዝብ ሌላው ዓለም ያለበት ስነ ልቦና ላይ የለም፣ በዚህም የአንድ ወቅት ክስተት ትውልዱ ላይ ተለጥፎ በህዝቡ ላይ መቆሚያ የሌለው ጉዳት ሲያመጣ ይታያል፣ በዚህም አብዛኞቹ ጃማይካውያን የስነ ልቦና ጉዳተኞች መሸሸጊያ በሆነው ሱሰኝነት፣ ዘፋኝነት፣ ግዴለሽነት፣ ሰካራምነት … ህይወት ውስጥ ይገኛሉ፣ ይህም የአንድ ወቅት ክስተት የዘር መለያ ሆኖ ይገኛል፣ ይህ ደግሞ መርገምት ነው::

በባርነት ህይወት ውስጥ ማለፍ ከባድ ነገር ነው፣ እንዲህ ላደረጉት እግዚአብሔር የስራቸውን ሰፍሮ የሚሰጣቸው ሲሆን የራስ ተፈሪያን ኃይማኖት ተከታዮች ሊያውቁት የሚገባው ዋነኛ ነገር ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱሱ አምላክ ለተበደሉ የሚፈርድ(መዝ.103፡6)፣ በዳዮችን የሚቀጣ(ቆላ.3፡25)፣ ከሐብታሞች በላይ ድሆችን የሚወድ(ሉቃ.16፡19-25)፣ ዝቅ ያሉትን ከፍ የሚያደርግ እንዲሁ ከፍ ከፍ ያሉትን የሚያዋርድ(ማቴ.23፡12) … በአጠቃላይ የምስኪኑ ወዳጅ የተጎዳ ጥቁር ህዝብ ረዳት መሆኑን ነው::

በዚህም ህዝቡ ለሞራል ግንባታ ተብሎ በሐሰተኛ ትርክት በክርስትናው ላይ የተሰራውን ህገወጥ ቅጥያ በመቁረጥ፣ እንደ ሀገር የተፈጠረውን መርገምት በማንሳት፣ የዘላለም ህይወት የሆነውን የነፍስን ጉዳይ በመመልከት፣ ጥለው ወደ ወጡበት ክርስትናቸው መመለስ እንዳለባቸው እንመለከታለን::

ማጠቃለያ (ከክርስትና ወደ ማጎበረሰባዊ ኃይማኖት የተመለሱ)

እስልምና፣ ዋቄፈናና የራስ ተፈሪያን ኃይማኖቶች አንድ የሚጋሩት እውነታ አለ፣ በ2.2 ክፍል እንደቀረበው እስልምና ለዓረቡ ማጎበረሰብ "የተላከ" ኃይማኖት ነው እንደዚሁ ዋቄፈና በኦሮሞ፣ ራስ ተፈሪያን ደግሞ በጃማይካውያን የተወሰኑ ኃይማኖቶች ናቸው::

የነዚህ ኃይማኖቶች የጀርባ አጥንት ከኃይማኖታዊ ጉዳይ በላይ ፖለቲካዊው አመክንዮ ነው፣ "የማጎበረሰብን ማንነት መገንባት" ነብዩ ሙሐመድ ከጠላቶቻቸው እስራኤሎች በኃይማኖት ለመለየት እስልምናን ለዓረብ አመጡ፣ ዘመናዊው ዋቄፈናም "ከሰሜኖቹ ክርስትና"፣ ራስ ተፈሪያንም "ከነጮች ክርስትና" ለመለየት ተመሳሳይ መንገድን ተከተሉ::

በዚህም ሳይሰተዋል፣ በፖለቲካ ምክንያት፣ "ከገጠሮች/ጠላቶች" ጋር አብሮ ላለመጓዝ፣ ብዙዎች ከተቃራኒው መናፍስታዊ ኃይል ኋላ እየተሰለፉ፣ ከምድራዊው ጉዳት በባሰ ራሳቸውን ለዘለማዊ ህይወት ጥፋት በሚጋብዘው ጎራ ውስጥ እየተጠቃለሉ ይገኛሉ::

ስለዚህም እነዚህ ወገኖች መንፈሳዊው እውነታ ከጊዜያዊው ፖለቲካ በላይ መሆኑ በመረዳት፣ በፖለቲካ ምክንያት ከሄዱበት የተሳሳተ መንፈሳዊ መንገድ በመመለስ ወደ ተዉት ክርስትና መመለስ እንዳለባቸው እንመለከታለን::

3.2. መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የራሳቸውን አስተምህሮ ጨምረው ከክርስትና የወጡ (ባኢ፣ የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ፣ ሞርሞን፣ ክርስቲያን ሳይንስ፣ የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን፣ ሺንቼኦንጂ፣ ሂውማኒዝምና አማኝ ኢቮሉሽኒስት)

እነዚህ ኃይማኖቶች በዋናነት የሚመሩት ከመጽሐፍ ቅዱሱ በኋላ "በወረደላቸው" መጽሐፍ ሲሆን መጽሐፍቱም እንደ ቁርአን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታን ከመስራቹን አስተምህሮ ጋር በአንድ ላይ አጣምረው የያዙ መጽሐፍት ናቸው፡፡

ከነዚህ ኃይማኖቶች ውስጥ ባኢ፣ ሞርሞንና ሺንቼኦንጂ የሚባሉት በሀገራችን ውስጥ በግልፅ እየሰሩ ሲሆኑ ሌሎቹ ክርስቲያን ሳይንስ፣ አማኝ ኢቮሉሽኒስት፣ ሂውማኒዝም እና የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ የሚባሉት ደግሞ በግልፅ በተቋም ደረጃ ባይደራጁም በግል የእነሱን አስተምህሮ የሚከተሉ ሰዎች እንዳሉ ይታወቃል ነገር ግን እስካሁን የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን ተከታይ ሀገራችን ውስጥ ይኑር አይኑር እምብዛም አይታወቅም፡፡

በዚህ ምዕራፍም የነዚህ ኃይማኖቶች አስተምህሮ በዝርዝር በመመልከት የሁሉንም ማጠቃለያ ሐሳብ በአንድ ላይ እንመለከታለን፡፡

3.2.1. ባኢ(ባሀ'ኡላህ) – Baha'i (Baha' Ullah)

[64] ይህ ኃይማኖት የተመሠረተው በ1844 ዓ.ም ራሱን "ባብ"(the gate) ብሎ በሚጠራው ሚርዛ አሊ ሙሐመድ በሚባል የሺአ እስልምና ተከታይ በነበረ ኢራናዊ ሰው ነው፣ ይህም ሰው ራሱን "ሙሐመድ ከዘሬ ይመጣል ያለው ማህዲ"(የአቡ ዳውድ ሱና 4285) እንደሆነ ይናገራል፡፡

[65] "የባኢ ኃይማኖት ከምሥረታው አንስቶ ብዙ ስደቶችን ያስተናገደ ኃይማኖት ሲሆን መሪውም እስኪገደል ድረስ ኦቶማን "ሶሪያ" ብሎ በሚጠራው ግዛቱ (የዛሬይቱ እስራኤል) ላይ ለ10 አመት ያህል ታስሯል፡፡ ምንም እንኳን ባብ በብዙ ስቃይ ውስጥ አልፎ ቢገደልም የሱ መገደል ግን ኃይማኖቱን ከመስፋፋት አላቆመም፣ በአሁኑ ጊዜም ኃይማኖቷ በዓለም ላይ ከ7.3 ሚሊየን በላይ ተከታዮች አሏት፡፡"

"ባብ" ይህን ኃይማኖት ለመመሥረት ምክንያት የሆነውም "ኃይማኖቶች በሙሉ መነሻቸው መለኮታዊ ነው፣ የሚለያዩትም አላስፈላጊ በሆኑ ጥቃቅን ነገሮች ነው" በሚል እምነቱ ነበረ፡፡ በዚህም ባብ በዋና ዋናዎቹ "ነብያት" (አብርሃም፣ ሙሴ፣ ቡድሃ፣ ክሪሺና፣ ኢየሱስ፣ ሙሐመድ) ነቢይነት የሚያምን ሲሆን ራሱንም በዚህ ዝርዝር ውስጥ ያካትታል፡፡

የባኢ ኃይማኖት የሚመራው ባብ ከመጽሐፍ ቅዱስና ከሌሎች ኃይማኖቶች መጽሐፍት አውጣጥቶ በራሱ መንገድ ባዘጋጀው "አል ኪታብ አል አቅዳስ" (ከሁሉ የበለጠ

[64] **Mankinds search for God**, Watch Tower Bible and Tract Societyof Pennsylvania(1990), page 304

[65] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Baha'i Faith

የተቀደሰ መጽሐፍ) በሚባለው መጽሐፉ ነው፡፡" መጽሐፉም የየኃይማኖቶችን አስተምህሮ በአንድ ላይ በመጨፍለቅ የተዘጋጀ መጽሐፍ ሲሆን በአንድ ላይ መደባለቅ የማይችሉትን አስተምህሮዎችን ደግሞ ትቷቸዋል፣ ለምሳሌ፣

- በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የተከፈለውን ቤዛነት፣
- የሥላሴ አስተምህሮ፣
- የሂንዱይዝምን ደጋግሞ መወለድ (reincarnation) አስተምህሮ

በመጽሐፉ ውስጥ አላካተታቸውም፡፡

3.2.2. <u>የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ (The new age movement)</u>

[66] ይህ እንቅስቃሴ በ1970 ዓ.ም አካባቢ በምዕራባውያኑ ሀገራት የተጀመረ ሲሆን [67] ኃይማኖቱም አንድ ወጥ ኃይማኖት ሳይሆን በውስጡ ክርስትና፣ የዮጋ፣ የተመስጦ፣ የኮከብ ቆጠራ ... የመሳሰሉ እምነቶችን ሰብስቦ የያዘ ሲሆን ለዚህም የሚያቀርበው ምክንያትም "አንድ ፍፁማዊ መንፈሳዊ መንገድ የለም" የሚል ነው፡፡ የኃይማኖቱ ዋነኛ አስተምህሮም "ሰዎች መንፈሳዊ ማንነታቸውን (እግዚአብሔር የሆነውን ማንነት) በማሳደግ እግዚአብሔርነት ጋር እንዲደርሱ መርዳት ነው፡፡" በዚህም የኃይማኖቱ ዋነኛ አትኩሮት የግለሰቦችን መንፈሳዊ ኃይል ማበረታታት ላይ ነው፡፡

ኃይማኖቱ በዋናነት የህንዳውያን አስተምህሮ የሚያነላ በመሆኑ ራስን በተመስጦ ውስጥ አስገብቶ አዕምሮን ፍፁም ባዶ በማድረግ ከአማልክት ምሪትን የመቀበል፣ ዮጋ፣ በተመስጦ ውስጣዊ ስሜቶችን በማዳመጥና በመከተል ወደ ደህንነት ማደግና "ደጋግሞ መወለድ" (reincarnation) አስተምህሮን ይከተላል፡፡

የባኢ ኃይማኖት ኃይማኖቶችን አንድ ለማድረግ የሚሞክረው በእስልምና መሠረት ላይ እንደሆነው የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ ደግሞ ኃይማኖቶችን አንድ ለማድረግ እየሰራ ያለው በህንዶችን ኃይማኖት መሠረት ላይ ነው፡፡ የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ ክርስቲያናዊ ቃላትን በሽፋን እየተጠቀመ ብዙ ክርስቲያኖችን መውሰድ ይቻል እንጂ ውስጡን ስንመለከት ግን ብዙ ኢ-ክርስቲያናዊ አስተምህሮዎችን ይዟል፣ ለምሳሌ፡-

- "ሰው እግዚአብሔር ነው፣
- ሰው "እግዚአብሔር" ስለሆነ ደህንነቱ በራሱ እጅ ነው፣ ሌላ አዳኝ አያስፈልገውም፣
- ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን ትልቅ መምህርና ለሰዎች ምሳሌ የሚሆን የህይወት መርህ የነበረው ሰው ነበረ፡፡"

የሚሉ መሠረታዊውን የክርስትና አስተምሮ የሚጥሱ አስተምህሮዎችን ይዟል፡፡

---

[66] https://en.m.wikipedia>wiki>new age

[67] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 109

3.2.3. ሞርሞን (Mormon/The Church of Jesus Christ Latterday Saints)

[68] "የሞርሞን ቤተክርስቲያን ጆሴፍ እስሚዝ በሚባል ሰው በኒውዮርክ ከተማ በ1830 የተመሠረተች ሲሆን ቤተክርቲያኗ በአሁኑ ጊዜ ከ15 ሚሊየን በላይ አባላት እንዳሏት ይነገራል፡፡"

[69] እንደ ቤተክርስቲያኗ እምነት ሞሮኒ የተባለው መልአክ በ1820 ዓ.ም ለጆሴፍ ተገልጦለት፣ ጆሴፍ የተሰወረን የወርቅ ሳህን አግኝቶ በላዩ ላይ የተፃፈውን መልዕክት እንዲተረጉም ነገረው፣ ጆሴፍም መልአኩ የነገረውን የወርቅ ሳህን "ኩሞራ" በተባለው ተራራ ስር በ1827 ዓ.ም አገኘው፣ መልአኩም ለጆሴፍ በሳህኑ ላይ የተፃፈውን ምልክት ማንበብ የሚችልበት "ዑሪምና ቱሚም" የተባለውን ትልቅ መነፅር ሰጠው፣ ጆሴፍም በዚያ መነፅር ፅሁፉን ተርጉሞ ከጨረሰ በኋላ በ1830 ዓ.ም ኃይማኖቱ የሚመራበትን "The book of mormon" መጽሐፍ አሳተመ፡፡

ይህ መጽሐፍ እንደ ቁርአኑ "አዲስ" ተብሎ ይቅረብ እንጂ መጽሐፉ በአብዛኛው የተዘጋጀው መጽሐፍ ቅዱሱን ቃል በቃል በመገልበጥ እና የራስን ፍልስፍናዎች በመጨመር ነው፣ መጽሐፉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን ይያዝ እንጂ በውስጡ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሱን የሚቃረኑ አስተምህሮዎችን ይዟል ለምሳሌ፡-

- "እግዚአብሔር እንደኛው ሰው ነበረ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆችን አስቀድሞ በመረዳቱና በነዚህ መርሆች በመመራቱ ወደ እግዚአብሔርነት አደገ፣ በዚህም ማንም ሰው የሞርሞን መጽሐፍ በሚያስተምረው መልክ የመጽሐፍ ቅዱሱን መመርያ ከተከተለ ወደ እግዚአብሔርነት ማደግ ይችላል፣
- የአዳም በኃጢያት መውደቅ አስፈላጊና መልካም ነበረ፣
- ሥላሴ ስራቸውን በጎበረት የሚሰሩ ሦስት የተለያዩ አማልክት ናቸው፣
- ኢየሱስ የሉሲፈር የመንፈስ ወንድም ነው፣ ስሙም ሚካኤል ወይንም አዳም ይባላል፣
- የክርስቶስ ሞት ያለፈውን ኃጢያታችንን እንጂ የአሁኑንና የወደፊቱን አያጠፋም፡፡"

የሚሉ ኢክርስቲያናዊ አስተምህሮዎች ይገኙበታል፡፡

[68] https://en.m.wikipedia>wiki>mormons

[69] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 49-51

3.2.4. ክርስቲያን ሳይንስ (Christian Science)

[70] "ክርስቲያን ሳይንስ በ1879 ዓ.ም ሜሪ ቤከር በተባለች ሴት መሪነት በአሜሪካ ሀገር ተመሠረተ፣ ሜሪ ብዙ ታዋቂነት አግኝታ ኃይማኖት እንድትመሠርት ያበቃት "ሳይንስና ጤንነት" በሚለው መጽሐፏ ታዋቂነት ምክንያት ነው።"

ሜሪ መጽሐፉን ያዘጋጀችው መጽሐፍ ቅዱሱን ከራሷ ፍልስፍና ጋር አቀናጅታ በመፃፍ ሲሆን ሜሪ መጽሐፏ ከመጽሐፍ ቅዱስ በላይ ስልጣን ያለው መጽሐፍ እንደሆነ ታስተምራለች፣ ተከታዮቿም [71] "ሜሪ ሳይንስና ጤንነት የሚባለውን መጽሐፍ ያዘጋጀችው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመሆኑ መጽሐፉ ከስህተት ሁሉ ነፃ የሆነ ትክክለኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ነው" ብለው ያምናሉ።

መጽሐፏ የመጽሐፍ ቅዱስ ቃላትን ይያዝ እንጂ መሠረታዊ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮዎች አይቀበልም፣ ከነዚህ ውስጥ፦

- "እግዚአብሔር ሰብአዊነት ያለው አካል ሳይሆን፣ አዕምሮ፣ ህይወት፣ እውነት፣ ፍቅር፣ ፕሪንሲፕል ... ማለት ነው፣
- ድንግል ማርያም መንፈሳዊ የሆነ ሐሳብ አርግዛ ወለደች፣ ሐሳቧንም "ኢየሱስ" አለችው፣
- ሰው "የፍቅር ሐሳብ" ምስል እንጂ ቁስ አካል አይደለም፣
- ኃጢያት፣ በሽታና ሞት የተሳሳተ አስተሳሰብ ውጤቶች ብቻ ናቸው፣ ኢየሱስም የመጣው "ኃጢያት አለ" የሚለውን የተሳሳተ እምነት ለማጥፋት ነው፣
- በሽተኞች የሚፈወሱት "በሽታ የለም" ብለው በመካድ ሳይሆን በሽታ አለመኖሩን ሲያውቁ ብቻ ነው፣
- የኃጢያተኛው ሲኦል ሌላ ነገር ሳይሆን ክፉ ማድረጉ ነው፣ ቅዱሱም ትክክል የሆነውን ነገር በማድረግ የራሱን መንግሥተ ሰማያት ይፈጥራል፣
- ፀሎት አስፈላጊ ነገር ሲሆን የሚፀለየው ግን ወደ ሰብአዊው አምላክ ሳይሆን "መለኮታዊ ሐሳብ" ወደ ሆነው አምላክ ነው፣
- የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የጌታቸውን ኃይልና ስልጣን አላወቁም ነበረ፣ ከተሰቀለ በኋላ ያልሞተ መሆኑን እስከሚረዱበት ጊዜ ምንም አይነት ተአምርና አስደናቂ ስራዎች አልሰራም ... በመቃብሩ ውስጥ ኢየሱስ የተደበቀ መሆኑን ስላላወቁ ኢየሱስ ሞቷል ብለው አመኑ።"

የመሳሰሉ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን ይዟል።

---

[70] https://en.m.wikipedia>wiki>Christian Science

[71] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 63

3.2.5. <u>የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን (Unification church/ Unification movement)</u>

[72] "የዩኒፊኬሽን ቤተክርስቲያን በ1950 ስሙ ሰን ማየንግ ሙን በተባለ በደቡብ ኮሪያ በሚኖር የሰሜን ኮሪያ ሰው ተመሠረተ፣ ሙን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ደቡብ ኮሪያ ውስጥ የተማረ ሲሆን የከፍተኛ ደረጃ ትምህርቱን ደግሞ በኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ጃፓን ውስጥ ተማረ፡፡" እንደ "ቤተክርስቲያኗ" እምነት [73] ሙን የ16 አመት ልጅ ሳለ በአፕሪል 17, 1935 ዓ.ም፣ በፋሲካ ጠዋት ላይ ኢየሱስ ተገልጦለት "በመሰቀሌ ምክንያት ያልጨረስካቸውን ስራዎች ትጨርሳለህ" በማለት ተናገረው ይላሉ፡፡

ሙንም ራሱን "ሦስተኛው አዳም" እንደሆነ፣ ከአንደኛውና ከሁለተኛው አዳም(ኢየሱስ) እንደሚበልጥና "በእግዚአብሔር ከተላኩ ቅዱሳን መካከል በጣም የተሳካልኝ እኔ ነኝ፣ ስለ ህይወትና ስለ ዓለም ኢየሱስን ጨምሮ ከብዙዎች ጋር ተከራክሬ ሁሉንም ካሸነፍኩ በኋላ ራሳቸውን ለኔ አስገዝተዋል" ይላል፡፡

ሙን "ለቤተክርስቲያኗ" መመሪያነት "መለኮታዊ መመሪያ"(The devine Principle) የሚል ቅዱስ መጽሐፍ ከመጽሐፍ ቅዱሱና ከራሱ ፍልስፍና በማቀናጀት ያዘጋጀ ሲሆን ይህም መጽሐፍ በቤተክርስቲያኗ ከመጽሐፍ ቅዱሱ እንኳን ቅድሚያ የሚሰጠው መጽሐፍ ነው፡፡

መጽሐፉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትን ይያዝ እንጂ በውስጡ ግን ብዙ መጽሐፍ ቅዱሱን የሚቃረኑ አስተምህሮዎችን ይዟል፣ ለምሳሌ፡-

- "ሰው ስጋ የለበሰ እግዚአብሔር ነው፣
- ኢየሱስ ሰው እንጂ አምላክ አይደለም፣
- ሰው በኃጢያት የወደቀው እንዳይበላው የተከለከለውን ፍሬ በመብላቱ ሳይሆን ሄዋን በስጋዋ አዳምን ስለፈተነችው ነው፣
- ሄዋን ከሉሲፈር ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት አድርጋ ቃየል ተወለደ ይህም <u>የኮምኒዝም ስርዓት</u> ነው፣ ሄዋን ከአዳም አርግዛ አቤል ተወለደ ይህም <u>የዲሞክራሲ ስርዓት</u> ነው፣
- ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞቱ የእግዚአብሔር እቅድ አልነበረም፣ የክርስቶስ ትንሳኤና ምፅአት የሚባሉት አስተምህሮዎች የስህተት ትምህርት ናቸው፡፡"

የመሳሰሉ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶችን ይዟል፡፡

[72] ከመለሰ ወጉ(1987) - Ethipian Outreach ministry፣ **ከእውነት መሳይ እምነቶች ተጠንቀቁ**፣ ገፅ 103

[73] http://en.m.wikipedia.org>wiki>unification church

3.2.6. ሺንቼኦንጂ (Shincheonji Church of Jesus the Temple of the Tabernacle of the Testimony, SCJ)

[74] "የሺንቼኦንጂ ኃይማኖት በማርች 14, 1984 ሊ ማን-ሂ(Lee Manhee) በሚባል ሰው በደቡብ ኮርያ ውስጥ ተመሠረተች፣ እንደ ኃይማኖቷ አስተምህሮ ሊ ዳግም የሚመጣው ክርስቶስ ሲሆን መጽሐፍ ቅደሱ በዘይቤያዊ አነጋገር የተፃፈ በመሆኑም መጽሐፉን እንዲተረጉም ስልጣን የተሰጠው ሰው ሊ ብቻ እንደሆነ ታስተምራለች፡፡ ቤተክርስቲያኗ በአሁኑ ጊዜ ከ120,000 በላይ አባላት አሏት፡፡"

[75] ቤተክርስቲያኗ በክርስትና ስም ትምጣ እንጂ በውስጧ ግን የግብረ ሰድምና የዮጋ አስተምህሮዎችን ይዛለች፡፡ ኢየሱስ 12 ደቀ መዛሙርትን መርጦ ወደ ዓለም እንደላከው መስራቹም በተመሳሳይ መንገድ 12 ደቀ መዛሙርትን መርጦ እየሰራ ያለ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ የመጣው ጴጥሮስ የተባለው ክንፍ ቅርንጫፍ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኗ አዱስ አበባ ውስጥም የአምልኮ ቦታዎች ያሎት ሲሆን ሰዎችንም ወደ ቤተክርስቲያኗ የሚጋበዙትም በድርጅቱ ስም ሺንቼኦንጂ ሳይሆን "የኮሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እናጥና" በሚል ቀላሌ ዘዴ ነው፡፡"

3.2.7. ሂውማኒዝም (Humanism)

የሂውማኒዝም እምነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት ተከሽኖ የቀረበ ኤቲስታዊ አስተምህሮ ነው፡፡ ሂውማኒዝም በመጀመሪያ "ፈጣሪ አለ" ይላል ቀጥሎም "የሰው ልጅ ችሎታውን አልተጠቀመበትም እንጂ የመፍጠር ችሎታ አለው" ይላል፣ በመጨረሻም "የሰው ልጅ ፈጣሪ ነው" በማለት ፈጣሪ የሰው ልጅ መሆኑን ያስተምራል፡፡ ሂውማኒዝም "የሰው ልጅ ራሱን በማከበር፣ በማድነቅ፣ በማሞገስ፣ በማመስገን... (በአጠቃላይ ራስን በማምለክ) ፈጣሪነት ደረጃ የሚያደርሰውን ችሎታውን ማጎልበት ይችላል" ይላል፡፡

በሂውማኒዝም እግዚአብሔር፣ ሰይጣን፣ ገነት፣ ሲኦል ... የመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት ቢኖሩም ትርጉማቸው ግን ከመንፈሳዊው አተረጓጎም የተለየ ነው፣ በሂውማኒዝም አተረጓጎም "እግዚአብሔር ማለት መልካም ሐሳብ ማለት ነው፣ ገነት ማለት ደግሞ በመልካም ሐሳባችን የምንኖረው መልካም ህይወታችን ነው፣ ሰይጣን ማለት ክፉ ሐሳብ ማለት ነው፣ ሲኦል ማለት ደግሞ በዚህ ክፉ ሐሳባችን ምክንያት የምንኖረው መጥፎ

[74] https://en.m.wikipedia>wiki>Shincheonji Church of Jesus the Temple of the Tabernacle of the Testimony

[75] https://mbasic.facebook.com.YeChristian Tube (Christian Tube - ክርስቲያን ቲዩብ), posted on sep.21, 2019

ህይወታችን ነው ..." በማለት ይተረጉሟቸዋል፣ በዚህም ሂውማኒዝም "ሰው የዓለሙ ፈጣሪ ነው፣ ዓለሙንም የሚፈጥረው በአስተሳሰቡ ነው" ይላል::

ይህ አስተምህሮ በምዕራፍ አንድ የተሳሳተ አስተምህሮ እንደሆነ የተመለከትነው የ"እግዚአብሔር አምላክ የለም" አስተምህሮ አዲስ Version ነው::

3.2.8. አማኝ ኢቮሉሽኒስት (Theistic Evolutionism/God-Guided Evolution)

[76] እነዚህ ቡድኖች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱንና የኢቮሉሽንን(የዝግመተ ለውጥን) ሳይንስ በማጣመር አዲስ እምነትን የፈጠሩ ሲሆን የዚህ እምነት ተከታዮችም እግዚአብሔር ፍጥረታትን ለመፍጠር የኢቮሉሽንን(የዝግመተ ለውጥ ሕግ) እንደተጠቀመ ያምናሉ::

[77] እምነቱ የሚመራው፣ ፍራነሲስ ኮሊንስ የተባለው ሰው በ2006 ዓ.ም መጽሐፍ ቅዱሱና የኢቮሉሽን ሐሳቦችን በአንድ ላይ በመቀየጥ "The Language of God" ብሎ ባሳተመው መጽሐፍ ነው፣ መጽሐፉም የሳይንስና መጽሐፍ ቅዱስ ቅይጥ ሲሆን ዋነኛ አስተምህሮዎቹም፣

- "እግዚአብሔር ከ14 ቢሊየን አመታት በፊት ዩኒቨርስን ፈጠረ፣
- ዩኒቨርስም ህይወትን እንድታወጣ አስተካከለ፣
- ህይወት የምትባለዋ ነገር ከተጀመረች በኋላ ፈጣሪ ሌላ ተጨማሪ ጣልቃ ገብነት አላደረገም፣
- ከዚህችም የህይወት መጀመሪያ ፍጥረታት በዝግመተ ለውጥ ህጉ መጡ..."

በማለት አማኝ ኢቮሉሽኒስት "መጽሐፍ ቅዱሱንና የኢቮሉሽን ፅንሰ ሐሳቦችን በአንድ ላይ አስታርቀናል" ይበል እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሱና የኢቮሉሽን ሐሳቦች ከተጋጩ ግን ቅድሚያ የሚሰጠው ለኢቮሉሽኑ ሐሳቦች ነው::

[76] ዘለቀ በጎይሉ (2010)፣ **ሉሲ ምን ያህል እውነት ነች**፣ ገፅ 99
[77] https://en.m.wikipedia>wiki>The language of God

ማጠቃለያ

(መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ በመጨመር በራሳቸው መንገድ የተደራጁ ኃይማኖቶች)

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ስምንቱ ኃይማኖቶችና ፍልስፍናዎች መጽሐፍ ቅዱሱን ተተግነው ባዘጋጇቸው "ቅዱስ" መጽሐፍና ፍልስፍና የሚመሩ ሲሆን ኃይማኖቶቹ እንደ እስልምና መጽሐፍ ቅዱሱን ለመተዋወቂያነት ተጠቅመው በዚያ ላይ የራሳቸውን ፍልስፍና "ከሸነው" የራሳቸውን አስተምህሮ በማዘጋጀት ብዙዎችን ከመጽሐፍ ቅዱሱ መንገድ አስወጥተዋል።

ይሁን እንጂ የእነዚህ ኃይማኖቶች መሪዎች በሙሐመድ ተምሳሌት ቢነሱም ቢያንስ እንኳን፣

- እንደ ሙሐመድ "መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አህመድ የሚባል ነቢይ እንደሚመጣ ተተንብዮ ነበር" የሚል የሐሰት መንጠልጠያ አለመስራታቸው፣
- ሰዎችም ትምህርታቸውን እንዳይጠራጠሩ በአስፈሪ ልበ ወለዶች አስፈራርተው መያዝ አለመቻላቸው፣
- እስልምናው እንደ ተጠቀመው እንደ ጂሃድ አይነት ፍቱን መስፋፍያ እስትራቴጂ አለመጠቀማቸው፣

የእስልምናን ያህል ክርስትናን መገዳደር እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

መጽሐፍ ቅዱሱ ግን ማንም መንደርደሪያ እያደረገው የራሱን ፍልስፍና እየጨመረ ሰዎችን በተሳሳተ መንገድ ይዞ እንዳይሄድ ቀድሞውኑ ራሱን የሚከላከልበትና አጭበርባሪዎች የሚጋለጡበትን መንገድ አስቀምጧል፣ ይህም፣

- በመጽሐፍ ቅዱሱ አዳዲስ መሠረታዊ ነገሮች ከመምጣታቸው አስቀድሞ በነብያት አፍ እየተተነበየ የሚሰራበት መርህ፣

  > አሞ.3፡7 "በእውነት ጌታ እግዚአብሔር ምስጢሩን ለባሪያዎቹ ለነብያት ካልነገረ በቀር ምንም አያደርግም።

  በዚህ መርህም አዲስ ኪዳን፣ ኢየሱስ ክርስቶስ ... ሳይመጡ በፊት በነቢያቱ ቀድሞውኑ በትንቢት ሲነገር ነበረ፣ ለወደፊት የሚመጡት እንኳን ለምሳሌ፣ ኢ-ኮሜርስ፣ የአርማጌዶን ጦርነት፣ ሐሰተኛው ክርስቶስ ... ቀድመው ተተንብየዋል። ይህ የመጽሐፍ ቅዱሱ ክስተቶች አስቀድሞ በትንቢት የሚናገርበት አሰራር በሰበር የሚገባ እንግዳ ነገር እንዳይኖር አድርጓል።

- መጽሐፍ ቅዱሱ የተዘጋና አዲስ መጽሐፍ መቀበል የማይችል መጽሐፍ መሆኑ።

  መጽሐፍ ቅዱስ "በመጀመሪያ"(ዘፍ.1፡1) በማለት የቁሳዊውን ዓለም ፍጥረት አጀማመር በማስረዳት የጀመረ መጽሐፍ ሲሆን ከ1,500 አመታት በኋላ ተፅፎ ሲያልቅ ደግሞ የቁሳዊውን ፍጥረት መጨረሻ ምን እንደሚሆን በማስረዳት "በዚህ

ላይ <u>ማንም እንዳይጨምርበት</u>" (ራዕ.22፡18-19) ብሎ አሰጠንቅቆ መዝጋቱ ተጨማሪ አዲስ መጽሐፍ የሚጨመርበት አሰራር እንዳይኖር አድርጓል፣

- ኢየሱስም የመጣበትን ዓላማ ጨርሶ ከዚያም "እኔ መንገድ ነኝ በዚህ መንገድ ሂዱ" በማለት በመሄዱ ሐዋርያቱም ይህንኑ አስረግጠው ገላ.1፡8 "ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።" ማለታቸውን ሌላ መንገድ የተዘጋ መሆኑን፣ ከዚህ ወንጌል መንገድ ላይ ሌላ አስተምህሮ ማስኬድ እንዳይቻል አድርጓል፣

ይህ የመጽሐፍ ቅዱሱ አካሄድ የአጭበርባሪዎችን መንገድ የሚዘጋና የትክክለኛ ተከታዮቹን እምነት ከግራ መጋባት የሚታደግ አካሄድ ነው። ከነዚህ ቴክኒካል ጉዳዮች ባለፈም መጽሐፍቱ መጽሐፍ ቅዱሱ በተፃፈበት መንፈስ አለመፃፋቸውና ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የመጋጨታቸው እውነታ የመጽሐፍቱን አጭበርባሪነት አጉልቶ ያሳያል።

እነዚህ እውነታዎችም በአንድ ላይ የሚያሳዩን መጽሐፍ ቅዱሱን መነሻ አድርጎ ሰውን ከመጽሐፍ ቅዱሱ አንስቶ በሌላ መንገድ መቀየስ ለሚፈልጉ አጭበርባሪዎች መንገዱ ዝግ መሆኑን ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ እስልምናም ሆነ እነዚህ ስምንቱ ኃይማኖቶች መጽሐፍ ቅዱሱን መንደርደሪያ አድርገው ተነስተው ተመልሰው መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የመነሳታቸው እውነታ የመጽሐፍ ቅዱሱን እውነተኛ የፈጣሪ ቃልነትና የሰይጣንን የመጽሐፍ ቅዱሱን የማራከስ ሰፊ ሙከራዎችን እንድናስተውል አድርጓል።

በዚህም በአጭበርባሪዎች ተታለው ከትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መንገድ የወጡት በሙሉ ወደ ክርስትናቸው መመለስ እንዳለባቸው እንመለከታለን።

በክርስትና ስር ብዙ አብያተ ክርስቲያናት ቢኖሩም ትክክኛዋ ቤተክርስቲያን የትኛዋ ናት? የሚለውን በቀጣይ ምዕራፎች ውስጥ በሰፊው እንመለከታለን።

ምዕራፍ አራት

4. <u>ኦርቶዶክስ እና ካቶሊክ</u>

የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፣ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ቀድሞ "የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን" ከሚባለው ወጥ አሰራር በኋላ፣ መከፋፈሎች መምጣት ሲጀምሩ፣ እንደተፈጠሩ ይታመናል፡፡ የሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ልዩነትም ከሥላሴ(አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) ውጪ ባሉት ከማርያም፣ ታቦት፣ መላዕክት፣ ፃድቃን፣ ሰማዕታት ... ጋር በተያያዘ የሚከተሉት የተለያየ የአሰራርና የአክራሪነት ደረጃ ነው፣ የዚህች መጽሐፍ አትኩሮት ደግሞ በመሠረታዊው የእምነት አስተምህሮ ላይ በመሆኑ ይህንን የሁለቱን ኃይማኖቶች ልዩነት በመተው ሁለቱንም ኃይማኖቶች በአንድ ላይ እንመለከታለን፡፡

ብዙዎች የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ከጥንት የመጡ አብያተ ክርስቲያናት በመሆናቸው ምንም ችግር እንደሌለባቸው ሲናገሩ ይሰማል ነገር ግን "ጥንትነት" ማለት "ትክክለኛት" ማለት እንዳልሆነ ከሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ልዩነት እንኳን መረዳት ይቻላል፡፡ እነሱ ይቅርና ዋናዎቹ የመሠረቷቸው አብያተ ክርስቲያናት እንኳን በሰይጣን ሤራ ከነበሩበት ትክክለኛ መንገድ ሲወጡ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፡፡ ኢየሱስ ካረገ 100 አመት እንኳን ሳይሞላው ነበረ አዳዲስ የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ከስህተታቸው እንዲመለሱ ሲመክር የነበረው(ራዕ.2፡14, ራዕ.3፡2...)፣ ጳውሎስም ከመሠረታቸው ጥቂት አመታት እንኳን ያላስቆጠሩ አብያተ ክርስቲያናትን ነበረ ከስህተታቸው እንዲመለሱ ሲወቅስ የነበረው(1ቆሮ.1፡12)፣ እንደዚሁ እግዚአብሔርም ቅዱሳኑን ተጠቅሞ በቤተመቅደሱ ውስጥ ብዙ የተሐድሶ ስራዎች ሲሰራ ነበረ(ዘጸ.32፡20, መሳ.6፡25-30, 2ነገ.10፡26-28, 2ነገ.23፡4, 2ዜና.29፡5, 2ዜና.34 ...)፡፡

ይህም የሆነው ሰዎች በትክክለኛው መንገድ እንዳይሄዱ የሚፈልገው ሰይጣን በመኖሩ ምክንያት ነው፣ የሰይጣን ሰርጎ ገብነትና እግዚአብሔር ደግሞ ቅዱሳኑን ተጠቅሞ ቤቱን የሚያድስበት አሰራር የተመለደ ተደጋጋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ነው፡፡ በዚህም ከ"ስህተት ነፃ" አባባል ትክክል የሚሆነው ሰይጣን በህይወት ከሌለ ብቻ ነው፣ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናትም ብዙ ዘመናትን አልፈው እንደመጡት መጠን ለብዙ የሰይጣን ሤራዎች እንደሚጋለጡ ግልፅ ነው፡፡ በነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የገቡትን መሠረታዊ ስህተቶችም በዋናነት በአራት ክፍሎች ይመደባሉ፣ ይህም፣

- ማርያም፣ መላዕክትና ቅዱሳን ኢየሱስን እንዲተኩ የተደረገበትና ከዚያም አልፈው እንደ እግዚአብሔርም እንዲመለኩ የተደረገበት አሰራር፣
- ብሉይ ኪዳን እያለ አዲስ ኪዳን የመጣበትን ምስጢር አለማግኘት፣
- ያልተቀደሱ "ቅዱሳን መጽሐፍት"፣
- ከዋናው መጽሐፍ ቅዱስ የሚጋጩ ትውፊቶች ናቸው፣ ቀጥሎ በስፋት ቀርቧል፣

4.1. <u>ማርያም፣ መላዕክትና ቅዱሳን ኢየሱስን እንዲተኩ የተደረጉበትና ከዚያም አልፈው እንደ እግዚአብሔር እንዲመለኩ የተደረገበት</u>

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ማርያም፣ ቅዱሳንና መላዕክት የገዘፈ ስፍራ ይሰጣቸዋል፣ ይህ አሰራርም የእነዚህ አካላት ስፍራ ከኢየሱስና ከእግዚአብሔር ወሰን ጋር እንዲቀላቀል አድርጓል፣ በዚህም የአማላጅነት ስራ፣ የሰው ልጆችን ከሲኦል የማዳን ስራ እንዲሁም መመለክ ያለበት ማን መሆን እንዳለበት/እንዳለባቸው በቤተክርስቲያኗ ተደበላልቋል፣ በዚህም፡-

- ሰማያዊ አማላጅ ማነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሦስቱ ወይስ ሁለቱ?
- የሰው ልጆችን ከሲኦል የሚያድነው ማን ነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሦስቱ ወይስ ሁለቱ?
- መመለክ ያለበት ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ እግዚአብሔር፣ ወይስ አራቱም?

የሚሉትን ጥያቄዎች በመመልከት ቤተክርስቲያኒቷ ምንአይነት ስህተት ውስጥ እንደገባች እንመለከታለን፡፡

4.1.1. <u>ሰማያዊ አማላጅ ማነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሦስቱ ወይስ ሁለቱ?</u>

“አማላጅ” የሚለው ቃል በዋናነት ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሞች አሉት፣ በመጀመሪያ ደረጃ ያለው “ተጣልተው የተለያዩ አካላትን የሚያስታርቅ” ማለት ሲሆን ሁለተኛው የምልጃ ትርጉም በብዙ ሰዎች ዘንድ የማይታወቀው በሮሜ.8፡26 ላይ የምንመለከተው “ጉድለትን በመሙላት ብቁ ማድረግ” ትርጉም ነው፣ በሁለተኛው የምልጃ ትርጉም ላይ ሁሉም ጋር ያለው አስተሳሰብ ተመሳሳይ በመሆኑ ልዩነት የተፈጠረበትን የመጀመርያውን አተረጓጎም በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

የማስታረቅ ምልጃ በሁለት ይከፈላል፣ ምድራዊና ሰማያዊ ምልጃ፣ ምድራዊው ምልጃ ቅዱሳን በአፀደ ስጋ እያሉ ስለሌሎች የሚያደርጉት ፀሎት ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ቅዱሳን በምድራዊው ህይወታቸው ስለ ሌሎች ሰዎች እንዲማልዱ ያዛል(1ጢሞ.2፡1-2)፣ እዚህም ላይ ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ሐሳብ ስላለው እዚህ ውስጥም አንገባም፡፡

ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ትልቅ ችግር የተፈጠረው በሰማይ(በመንፈሳዊው ዓለም) ስለሚደረገው ቋሚ የምልጃ አይነት ነው፣ በዚህም በሰማያዊው ስፍራ በአማላጅነት ለሰው ልጆች በቋሚነት የሚቆመው ማነው? የሚለውን በሰፊው እንመለከታለን፡፡

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በድሮው ጊዜ ማርያም፣ ቅዱሳንና መላዕክት በሙሉ ሰማያዊ አማላጅ እንደሆኑ ሲነገር ነበረ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በተለይ ከ“ማኅበረ

ቅዱሳን" እና ዘመናዊ የመንፈሳዊ ትምህርት ቤቶች መስፋፋት ጋር በተያያዘ ከማርያም ውጪ ስላሉት አማላጅነት የሚሰማው ድምፅ እየቀነሰ መጥቷል፣ አሁን ላይ ያለው ትልቅ ድምፅ "ማርያም - አማላጅ"፣ "መላዕከት - ተራዳኢ"፣ "ፃድቃን/ሰማእታት - መታሰቢያ የሚደረግላቸው" የሚለው ነው።።

ይህ የስራ ክፍፍል በአሰራር ደረጃ የተሻለ ነው ምክንያቱም ማርያም፣ መላዕከትና ቅዱሳን የተለያየ ተፈጥሮ፣ ማንነት፣ ችሎታ፣ ስልጣን ... ስላላቸው ሁሉንም እኩል አድርጎ አንድ ስራ ላይ መመደብ አሳማኝ አልነበረም ይባሱኑም "ሁሉም አማላጆች ናቸው" ሲባልም ብዙ ጥያቄን ይፈጥራል፣ አንዱ ብቻውን ሙሉ ምልጃ ማድረግ አለመቻል ነው? ወይስ አንዱ ባያማልደኝ ወይ ቢረሳኝ ሌላው አልፎበት ይሰራል ከሚል ነው? ወይስ አማላጆቹ መካከል ተቀናጅቶ የመስራት ችግር ስላለ ነው? ወይስ ፈጣሪ ዘንድ መግባት ላይ ልዩነት ስላለ ነው? የሚሉ ግራ መጋባቶችን ይፈጥር ነበረ።።

ስለዚህም ከነዚህ ግራ አጋቢ አሰራር ወጥቶ አንድ ቋሚ ለምልጃ ሙሉ ብቃት ያለውና ለዚህ አገልግሎት የተለየ አማላጅ መምረጡ በአሰራር ደረጃ ትክክል ነው፣ በዚህም ይመስላል በአሁኑ ጊዜ "ማርያም" ከሁሉ በላቀ የአማላጅነትን ማዕረግ ይዛ ነጥራ ወጥታለች፣ በዚህም "ያለ ማርያም አማላጅነት ዓለም አይድንም" እስከማለት ተደርሷል።።

በርግጥ በነፍስ አፀድ ያሉቱ ቅዱሳንና መላዕከቱ በነበሩበት በብሉይ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር አማላጅ አጣሁ(ኢሳ.59፡16, ሕዝ.22፡30-31 ...) ማለቱና በዚህ ላይ ደግሞ መላዕከቱና ቅዱሳኑ እልፍ አእላፍ መሆናቸውና እነሱም በኃይልና በስልጣን መለያየታቸውን ስንመለከት ሰማያዊውን የምልጃ አገልግሎትን ከቅዱሳኑና ከመላዕከቱ ላይ አንስቶ ለማርያም ብቻ መስጠቱ አግባብነት አለው።። ነገር ግን ይህንን የምልጃ አገልግሎትን ከቅዱሳኑ አንስቶ ለማርያም ብቻ መስጠቱ ደግሞ ሌላ ከፍተት ይፈጥራል፣ ይህም የምልጃቸው ልዕቀታቸውን መጽሐፍ ቅዱሱ የሚመሰክርላቸው ሙሴና ሳሙኤል(ኤር.15፡1) እያሉ ማርያምን ከነሱ በላይ ማስኬዱ አሳማኝ አይደለም እንደዚሁም በስጋው ወራት ስለ እስራኤል ዘር መዳን ያማለደው ሙሴ(ዘጸ.14፡11-20) እያለ ወይን ጠጅ ስለማስሞላት የማለደችውን ማርያምን ማስበለጥ አሳማኝ አይሆንም።።

በነዚህ ግራ አጋቢ ነገሮች ላይ ደግሞ ማርያም፣ መላዕከትና ቅዱሳን ሰዎች ከምድር የሚፀልዩትን ፀሎት ለመቀበል እንደ እግዚአብሔር "በሁሉም ስፍራ የመገኘት" ችሎታ አላቸው? ብለን ስንመለከት ደግሞ የሦስቱም አማላጅነት ላይ ሌላ ጥያቄ ይፈጠራል።።

ይህ የማርያም/መላዕከት/ቅዱሳን አማላጅነት ሐሳቦች እንደዚህ መምታታቱ የሰማያዊው የአማላጅነት ስራ የእነሱ ስራ ባለመሆኑ ይሆን እንዴ? የሚለውንም መመልከቱ ተገቢ ነው፣ ስለዚህ የማርያም፣ መላዕከት፣ ቅዱሳንና የኢየሱስን አገልግሎቶችና ማንነቶችን በዝርዝር በመመልከት ትክክለኛው ሰማያዊ አማላጅ ማነው? የሚለውን ጥያቄ በስፋት እንመለከታለን።።

4.1.1.1. <u>የማርያም አማላጅነት</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ ማርያም ብፅዕት እንደሆነችና ኢየሱስን በድንግልና አርግዛው በድንግልና እንደወለደችው ይናገራል፣ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ለማርያም የሚሰጠው ስፍራ ግን ከዚህ ባለፈ ማርያም ሰማያዊ አማላጅ እንደሆነች ይነገራል፡፡

ለዚህ ሐሳብ በዋናነት የሚቀርበው መከራከሪያም "የማርያም የቃና ዘገሊላ ምልጃ የሰማያዊው ምልጃዋ ተምሳሌት ነው" የሚልና ከመጽሐፍ ቅዱሱ ውጪ በሌሎች መጽሐፍት ላይ ስለ ማርያም የተገለፁት "ማርያም ስለሰው ልጆች ታጢያት ሞተች በሦስተኛው ቀን ተነሳች፣ በአብ ቀኝ ትገኛለች…" በሚሉ አስተምህሮዎች መሠረት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

4.1.1.1.1. <u>"የማርያም የቃና ዘገሊላ ምልጃ የሰማያዊው ምልጃዋ ተምሳሌት ነው"</u>

የቃና ዘገሊላን ታሪክ የምናገኘው በዮሐ.2፡1-11 ላይ ነው፣ ይህ ቃል የሚናገረው ማርያምና ኢየሱስ ቃና ዘገሊላ በተባለ ስፍራ ሠርግ ላይ ተገኝተው በነበረ ጊዜ የወይን ጠጅ በማለቁ ምክንያት ማርያም ኢየሱስን ለምና ኢየሱስም በተአምራዊው መንገድ ውሀን ወደ ወይን ጠጅ የቀየረበት ታሪክ ነው፡፡ ቤተክርስቲያኗም ከዚህ ታሪክ በመነሳት "ማርያም በቃና ዘገሊላው ሰርግ ላይ አማልዳለች" ከማለት አልፋ "የቃና ዘገሊላው ምልጃ የማርያምን ሰማያዊ ምልጃ ምሳሌ ነው" ትላለች፡፡

እዚህ ጋር ምድራዊውን የምልጃ ስራ ወደ ሰማያዊው ተምሳሌትነት ከመውሰዳችን በፊት፣ የምድራዊው ምልጃዋ ላይ የነበረውን ክፍተት መመልከቱ ጠቃሚ ነው፣ ይህም ማርያም ኢየሱስን ስትለምን፣ ኢየሱስ ልመናዋን በቀጥታ ከመፈፀም፣

- "አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ" ማለቱ የማርያም የአማላጅነት ብቃት ግምት ውስጥ ያስገባል፣
- "ጊዜዬ ገና አልደረሰም" ማለቱ ደግሞ የማርያም የእግዚአብሔር ጊዜን ያለማወቅ ችግር ያሳያል፣

እነዚህን ችግሮች በማርያም ምልጃ ውስጥ ብቻ መመልከታችን፣ ከማርያም ውጪ ደግሞ የትኛውም አማላጅ እንደዚህ አለመባሉንና ማርያምንም ከቃና ዘገሊላ በኋላም በሌላ የምልጃ ስራ ውስጥ አለመመልከታችን፣ ማርያምን የሰማዩ የምልጃ ስራ ጋር ማድረስ ይቅርና በምድር ላይ የሞከረችው አንዱ ምልጃዋ ላይ እንኳን ጥያቄ ተፈጥሮ እንመለከታለን፡፡

እነዚህ በማርያምና በኢየሱስ መካከል የነበሩት አወዛጋቢ ንግግሮች እንዳሉ ሆነው፣ ውሀው ወደ ወይን ጠጅ መቀየሩን ብቻ በመመልከት "ማርያም በቃና ዘገሊላ ላይ አማልዳለች" ቢባል እንኳን ሌላ ችግር ደግሞ ከፊታችን ይጠብቀናል፣

- “ምድራዊ አማላጆች ሰማያዊ አማላጆች ናቸው” የሚል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለም፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ስለ ማርያም ድህረ ሲጋዊ የምልጃ አገልግሎት ምንም አለመናገሩና ከወንጌላትና ከ“ሐዋርያት ስራ መጽሐፍ” በኋላ በተፃፉት ሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንድም ስፍራ ላይ “ማርያም” የሚል ቃል አለመመልከቱ ማርያም በድህረ ሲጋዊ ህይወቷ የምትሰራው የምልጃ ስራ አለመኖሩን ያሳያል፡፡
- ማርያም አሁን በምድር ላይ የለችም፣ በዚህም ሰማያዊ አማላጅ ለመሆን ፀሎት ከምድር መቀበል መቻል አለባት ነገር ግን ማርያም እንደ እግዚአብሔር “በሁሉም ስፍራ መገኘት” የሚቻልበትን አምላካዊ ማንነት የላትም፣ በዚህም ሰዎች ወደ ማርያም የሚያደርጉት የ“አማልጅኝ” ጩኸትን ማርያም መቀበል አትችልም፣ በዚህም ወደ ማርያም የሚደረገው ፀሎት “እሪ በከንቱ” ብቻ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት የማርያምን ምድራዊ ምልጃ በቃና ዘገሊላ ተሞክሮ ብዙ ግራ አጋቢ ጥያቄዎችን የተፈጠረበት፣ እስዋም ከዚህ ውጪ ሌላ ምልጃ ሳትሞክር የተወችበት፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ከወንጌሉና ከሐዋርያት ስራ መጽሐፍ በኋላ በተፃፉት መጽሐፍት ውስጥ ስሟን ሳያነሳ ያለፈበትና ማርያምም “በሁሉም ስፍራ በመገኘት ፀሎትን መቀበል” አምላካዊ ማንነት የሌላት መሆኑን ስንመለከት፣ በማርያም የቃና ዘገሊላ ታሪክ ላይ ተንተርሶ “በሰማዩም ታማልዳለች” የሚለው ሐሳብ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

4.1.1.1.2. “<u>ማርያም ለሰው ልጆች ኃጢያት ሞተች</u>”

አንድ አማላጅ ኃጢያት ለማስተሰረይ ስለዚያ ኃጢያት መስዋዕት ማቅረብ አለበት(ዕብ.5፡1)፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት ሊቀካህናት እንስሳትን ለመስዋዕትነት ያቀርቡ ነበረ፣ በአዲሱ ኪዳን ኢየሱስ እራሱን መስዋዕት አደረገ፣ ማርያምም አማላጅ ለመሆን ስለ ኃጢያት የሚሰዋ መስዋዕት ልታቀርብ ይገባል፣ ይህንም ክፍተት ለመዝጋት ቤተክርስቲያኗ ማርያም ለሰው ልጆች መስዋዕት መሆኗን ትናገራለች፡-

> [78] “ፀሀየ ፅድቅ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እመቤታችን ማሪያም 64 ዓመት በሆናት ጊዜ … ሙቺ አላት፡፡ እርስዋም አንተን ወልጄ ያንተ እናት ሆኜ እንዴት ልሙት ብትለው እመቤታችን በፈቃድዋ እንዳልሞተችለት ዐውቆ 9,999 ነፍሳት በአንድ ቀን ተኮንነው ገሀነመ እሳት ሲወርዱ አሳያት፡፡ እነዚህም ነፍሳት እመቤታችንን ማሪያምን ባዩ ጊዜ፣ እመቤታችን ሆይ ለዘመዱ የማያዝን አንጀት ራሱን የማይሸከም አንባት አንጀቱም አንጀት አንባቱም አንባት አይደለምና ከልጅሽ አስታርቂን፣ ከገሀነም እሳት አውጪን፣ መንግሥተ ሰማያት አግቢን” ብለው ቢያለቅሱባት እርሷም እመቤታችን ማሪያም ልጄ ሆይ ወዳጄ ሆይ እባክህ ማርልኝ አለችው፡፡ እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔ ደቂቀ አዳምን (የአዳም ልጆችን) ከገሀነመ እሳት አውጥቼ መንግሥተ

[78] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን ዘሀገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም** ፣ ሁለተኛ እትም፣ ገፅ.154

ሰማያት ያገባሁት ተገፍፌ፣ ተገርፌ፣ ተሰቃይቼ፣ ተቸንክሬ፣ ሞቼ፣ ተነስቼ አይደለም? <u>አንቺም ስለነዚህ ነፍሳት ኃጢያታቸው ካልሞትሽላቸው ዘለዓለም በገሀነም እሳት ወርደው ይቀራሉ አላት።። እርሷም እመቤታችን እንኳን አንድ ጊዜ ሰባት ጊዜ ልሙት ብላ ሞታለች</u>።። (*መጽሐፈ ፀሎት ወመዝገበ ፀሎት* በአማርኛ፣ ነገረ ማርያም ገፅ 638-640፡ ተስፋ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፡ አዲስ አበባ፡ 1989 ዓ.ም።።)"

በዚህም መሠረት ማርያም ስለሰው ልጆች ኃጢያት መስዋዕት በመሆኗ ማርያም አማላጅ መሆንዋን ቤተክርስቲያኗ ትናገራለች።።

ነገር ግን ይህንን ታሪክ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አናገኝም ይባሱኑም መጽሐፍ ቅዱሱ፣ ክርስቶስ በመስቀሉ ላይ አንድ ጊዜ የከፈለው ዋጋ "ለደቂቀ አዳም" ብቻ ሳይሆን ለሰው ዘር በሙሉ መሆኑን፣ ሌላም አጋዥ ሳያፈልገው ሰዎችን ከኃጢያት ሁሉ ማንፃት የሚችል ጉድለት የሌለበት መስዋዕት መሆኑን ነው የሚናገረው(1ዮሐ.1፡7, ዕብ.10፡12, ዕብ.7፡26-27, ቆላ.1፡21-22, ዕብ.10፡11-14, ዕብ.7፡22-27, ዕብ.9፡25-28 ...)።።

በዚህም ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሆኖ "ተፈፀመ" እንዳለው፣ አንዴ የሰራው ስራ ሙሉ ያለቀለት ስራ እንጂ እሱ ሳይጨርሰው ማሪያም መስዋዕት ሆና የምታሟላው ቀሪ ስራዎች የለም፣ በዚህም የ"ማርያም ለሰው ልጆች ኃጢያት ስርየት ሞተች" በሚል መነሻ ማርያምን ሰማያዊ አማላጅ ለማድረግ የታሰበው ሐሳብም ስህተት መሆኑን እንመለከታለን።።

4.1.1.1.3. <u>"ማርያም በአብ ቀኝ ትገኛለች"</u>

ሰማያዊ አማላጅ ለመሆን ሌላው መስፈርት ኃጢያትን ይቅር ከሚለው አብ ቀኝ መገኘት ነው፣ ለዚህም ቤተክርስቲያኗ፣ ማርያም በአብ ቀኝ እንደምትገኝ ታስተምራለች፣ [79]"(ማርያምም ስትሞት) ሐዋርያትም ወስደው ቀበሩዋት፣ በሦስተኛውም ቀን ከሞት ተነሳች ... ወደ ሰማይም አረገች <u>በቀኝም ተቀመጠች</u>።። (የኢ.ኦ.ተ.ቤ/ክ፤ ውዳሴ ማርያም ንባቡና ትርጓሜው፡ ገፅ.207-209፤ ትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፤ አዲስ አበባ፤ 1983 ዓ.ም)"

ይህ "በአብ ቀኝ" የመገኘት ታሪክ የኢየሱስ ታሪክ ነው፣ ይህም በትንቢት የተተነበየ(መዝ.110፡1) በወንጌላቱም የተገለፀ(ማር.16፡19) በራዕይ የተረጋገጠ(ሐስ.7፡55) እውነታ ነው፣ ስለማሪያም በአብ ቀኝ መገኘት መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የትም ስፍራ ላይ አናገኝም፣ ደግነቱ "ቀበሩዋት" የተባሉት "ሐዋርያት ናቸው" መባሉና ሐዋርያቱ ደግሞ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ስለዚህ ጉዳይ አንድም ስፍራ ላይ አለመናገራቸው፣ የማርያም በአብ ቀኝ መገኘት ታሪክ ውሸት መሆኑና ይህንንም ተተግኖ ማርያምን ሰማያዊ አማላጅ ያደረገው አስተምህሮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን።።

---

[79] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን ዘሀገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም**፣ ሁለተኛ እትም፣ገፅ.154-155

በአጠቃላይ ስንመለከት በመጽሐፍ ቅዱሱ አንድም ስፍራ ላይ "ማርያም ታማልዳለች" የሚል ቃል ወይ በሌላ ተቀራራቢ አባባል ይህም "ማርያም ለሰው ልጆች መንገድ፣ ጠቢቃ፣ መካከለኛ፣ ሊቀካህን ... ናት" ተብሎ አለመነገሩ፣ ማርያም ስለ ሰው ልጆች ኃጢያት የሞተች አለመሆኑ፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የምንመለከታቸውም ቅዱሳን ማርያም እንድታማልዳቸው ወደ እርሷ ፀሎት አለማድረጋቸው፣ ማርያምም እንደ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ተገኝታ ፀሎት መቀበል የማትችል መሆኗን ስንመለከት ማርያም በሰማያዊ(መንፈሳዊ) ስፍራ በአማላጅነት አገልግሎት እንዳልተሾመች እንመለከታለን::

4.1.1.2. የመላዕክት አማላጅነት

ቤተክርስቲያኗ የመላዕክትን አማላጅነት ለማስረዳት በዋናነት የምታቀርበው ቃል:-

> ዘካ.1:12 "... የእግዚአብሔርም መልአክ መልሶ፣ አቤቱ የሠራዊት ጌታ ሆይ እነዚህን ሰባ አመት የተቆጣሃቸውን የኢየሩሳሌምና የይሁዳ ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው? አለ::"

የሚለውን ነው፣ ይህንን ክፍል ስናጠና ይሄ መልአክ የተንቀሳቀሰው ጥናት እንዲያደርግ እንጂ እንደ አማላጅ የሰዎች የ"አማልደኝ" ፀሎት ቀርቦለት አይደለም፣ በዚህም ይህ ቃል ለመላዕክት ከሚቀርበው የ"አማልደኝ" ፀሎት ጋር አይያያዝም ነገር ግን ከመላዕክቱ የስራ ድርሻ፣ ባህሪና ተፈጥሮ አንፃር ስንመለከት መላዕክቱ እንደማያማልዱ እንመለከታለን:-

- **ከመልአክ የስራ ድርሻ አንፃር**

መላዕክቱ የተፈጠሩት ለእግዚአብሔር ለመላክ እንጂ ለሰው ለመላክ አይደለም፣ በዚህም መላዕክቱ ከሰዎች ወደ እግዚአብሔር እንዲላኩ የተቀመጠ አሰራር የለም፣ በሰው የሚሰጣቸውም ተደራቢ የስራ ድርሻም የለም፣ በዚህም የእግዚአብሔርን መልአክን "ለምንልኝ ልላከህ" ማለት የመላዕክቱንና የእግዚአብሔርን ክብር የሚጋፋ የድፍረት አነጋገር ነው::

- **"የምልጃ ስራ ይሰራሉ" የተባሉት መላዕክት ተለይቶ አለመታወቅ**

ቤተክርስቲያኗ "መላዕክት አማላጆቻችን ናቸው" ትበል እንጂ አንድ ግልፅ ያላደረገችውና በደፈናው ያለፈችው ነገር አለ ይህም፣ መላዕክቱ እልፍ አእላፍ ከመሆናቸውና በስራ ድርሻ፣ በስልጣን ... ከመለያየቱ አንፃር የሚያማልዱት መላዕክት ሁሉም ናቸው? ወይስ የተወሰኑቱ ብቻ ናቸው? የሚለውን ግልፅ አላደረገችም፣ ለምሳሌ የገብርኤልና የሚካኤል የስራ ድርሻ የተለያየ ነው፣ ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል(ሉቃ.1:19)፣ ሚካኤል የጦር መሪ ነው(ራዕ.12:7) ...

መጽሐፍ ቅዱሱም የሁሉንም መላዕክት ስምና የስራ ድርሻ አልነገረንም፣ ሊነግረንም አይችልም፣ ምክንያቱም መላዕክቱ እልፍ አዕላፍ ስለሆኑና ለምልጃ አገልግሎት ተለይተው የተሾሙ መላዕክት ስለሌሉ፣ ዳንኤል እንኳን ስለሚካኤል ሲናገር ከዋነኞቹ አለቆች

አንዱ(ዳን.10፡13) ይላል እንጂ ሌሎቹ እንደሚካኤል የ"አለቅነት" ስልጣን ላይ ያሉት ብዛት፣ ስምና የስራ ድርሻ አልነገረንም።

➢ ከመላዕክቱ ባህሪ አንፃር

መላዕክቱ የሕግን ፍፅምና እንደሚያከሩና እንደ እግዚአብሔር "ይቅር" የሚባል ነገር እንደማያውቁ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ በተዘገቡ ታሪኮች ውስጥ መመልከት ይቻላል፣ ይህንንም እውነታ እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡበት ታሪክ ውስጥ እንደዚሁ ዘካሪያስና መልአኩ ገብርኤ መካከል በነበረው ሁኔታ ውስጥ መመልከት ይቻላል፣ እስራኤል ከግብፅ የወጡበትን ታሪክ ቅድሚያ ብንመለከት፣

> ዘጸ.23፡20-21 "በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ። በፊቱ ተጠንቀቁ፣ ቃሉን አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢያት ብትሰሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት።"

እዚህ ጋር እስራኤላውያኑን የእግዚአብሔርን ምህረት ተለማምደው የሚያደርጉትን መጨማለቅ በመልአኩ ፊት እንዳያደርጉ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያስጠነቀቀበት ቃል ነው። በአዲስ ኪዳኑም በገብርኤልና በዘካሪያስ መካከል የነበረው እውነታ ይህንኑ ያረጋግጥልናል፣

> ሉቃ.1፡20 "(መልአኩ ገብርኤልም ዘካርያስን) እነሆም በጊዜው የሚፈፀመውን ቃሌን ስላላመንህ፣ ይህ ቀን እስከሚሆን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው።"

ገብርኤልም በዘካርያስ አለማመን የዘካርያስን አፍ ዘግቶ ሄደ፣ እግዚአብሔር ሰዎች ቃሉን አለማመን አይደለም "አንፈልግህም"፣ "አንሰማህም" ... ብለው ሲሄዱ እንኳን ሲራራላቸው ብዙ ስፍራዎች ላይ ተመልክተናል፣ መልአክ ጋር ግን ምህረትን አንመለከትም፣ ቅድስና ከነደለ መቅጣት ብቻ ነው።

በዚህም መልአክ ስለ ሰዎች ኃጢያት አግዚአብሔርን መለመን ይቅርና ስለተሰራው ኃጢያት እዚያው ነው ዋጋን የሚሰጠው፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ምን ያህል በተቃርኖ መንገድ እየሄደች እንዳለ እንመለከታለን።

➢ ሌላው "እሪ በከንቱ"

ከላይ እንደተመለከትነው ማርያም እንደ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ መገኘት እንደማትችልና በዚህም ወደ ማርያም የሚደረገውን ፀሎት "እሪ በከንቱ" ብቻ እንደሆነ ተመልክተናል፣ እንደዚሁም መላዕክቱም ይህን የእግዚአብሔርን "በሁሉም ስፍራ የመገኘት" ችሎታ የላቸውም፣ በዚህም በአጠገብ ላልታዩ መላዕክት የሚደረግ ፀሎት "እሪ በከንቱ" ብቻ ነው።

በዚህም የምልጃ ስራ የመላዕክቱ የስራ ድርሻ አለመሆኑን እንመለከታለን። መላዕክቱ የሚያማልዱ ቢሆን ኖሮ በብሉይ ኪዳን ዘመን መላዕክቱ ባሉበት እግዚአብሔር "ወደኔ

የሚማልድ አጣሁ" አይልም ነበረ(ኢሳ.59፡16, ሕዝ.22፡30-31...)፣ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥም መላዕክትን አንድም ስፍራ ላይ "አማላጅ" ወይንም አማላጅነታቸውን የሚያሳዩ እንደ "መካከለኛ፣ አስታራቂ፣ ጠበቃ፣ ሊቀካህን ..." በሚሉ ቃላት አለመጠራታቸው፣ እንዲሁም ቅዱሳኑም መላዕክትን "አማልዱኝ" ብለው ወደነሱ ሲፀልዩ አለመመልከታችን፣ መላዕክት በ"አማላጅነት" አገልግሎት ላይ እንዳልተሾሙ እንመለከታለን፡፡

በዚህም የመላዕክት አማላጅነት አስተምህሮ ክርስቲያናዊ አይደለም ነገር ግን ይህ አስተምህሮ ከየት እንደመጣ ስንመለከተው ቁርአኑ(53፡26) ላይ እናገኘዋለን ስለዚህ የዚህ አሳሳች ትምህርት ምንጭ ከየት እንደመጣ ግልፅ ነው፣ ስለዚህ ይህን አስተምህሮ የምትከተሉ ተቀደሱ፡፡

4.1.1.3. <u>የቅዱሳን አማላጅነት</u>

ሰማዕታት፣ ፃድቃንና ቅዱሳን የሚባሉት ቃላት ተቀረራቢ ትርጉም ያላቸው ቃላት ናቸው፣ "ሰማዕታት" የሚባሉት ስለ እምነታቸው ብለው የተሰዉ ሰዎች ሲሆኑ፣ ፃድቃንና ቅዱሳን መካከል ግን የጎላ ልዩነት አንመለከትም፣ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ምሁራንም ዘንድ በአብዛኛው [80] ቅዱሳን የሚለው ሰፋ ያለና ፃድቃኑና ሰማዕታቱንም የሚያጠቃልል ቃል በመሆኑ፣ ሦስቱንም(ሰማዕታት፣ ፃድቃንና ቅዱሳን) በአንድ ላይ "ቅዱሳን" በሚለው ቃል እንጠራቸዋለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱን ስንመለከት ቅዱሳን በምድራዊው ህይወታቸው እንዲሰሩት ከተሰጣቸው ስራዎች ውስጥ አንዱ የማማለድ ስራ ነው (1ጢሞ.2፡1-2, 2ቆሮ.5፡19...) ቅዱሳኑም በዚህ በተሰጣቸው ትዕዛዝ መሠረት በአፀደ ስጋ በነበሩበት ወቅት ሲያማልዱ ነበረ አሁንም በአፀደ ስጋ ያሉት ቅዱሳን እያማለዱ ይገኛሉ፡፡

ነገር ግን ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህንን የቅዱሳን አፀደ ስጋዊ የማማለድ አገልግሎት በመለጠጥ ቅዱሳኑ ከሞቱ በኋላም በሰማይም የምልጃ አገልግሎታቸው እንደሚቀጥሉ ትናገራለች፤ ለዚህም ድጋፍ ብዙ ጥቅሶችን ሲያቀርቡ ይታያል [81]"2ነገ.13፡20-21, ራዕ.14፡13, ሉቃ.16፡22, ራዕ.6፡9-11, ማቴ.17፡2..."፡፡ ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ ከ2ነገ.13፡20-21 ውጪ ያሉት ጥቅሶች በሙሉ የሚናገሩት የቅዱሳን ትንሳኤ መኖሩንና በትንሳኤም ህይወትና እንቅስቃሴ መኖሩን እንጂ አንዱም ጥቅስ በአፀደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን የምልጃ አገልግሎት እንደሚሰሩ አይናገርም፡፡

ከነዚህ ውስጥ ለየት የሚለው 2ነገ.13፡20-21 ነው፣ እዚህ ጋር የቀረበው ታሪክ አስከሬን የኤልሳዕን አፅም በመንካቱ ከሞት የተነሳበት ታሪክ ነው ነገር ግን በሰማይ

---

[80] መ/ር ዐሥራት ደስታ et.al(1998)፣ **ነገረ ቅዱሳን - ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ገፅ መግቢያ ክፍል

[81] ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣ **ነገረ ቅዱሳን - ፩**፣ በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ/ በሰንበት ተ/ቤ/ማ/መ ማ/ቅ/ት/ሐ/አገ/ዋና ክፍል፣ ገፅ.82

በመገኘት ኃጢያት ማማለድና በጉድጓድ ውስጥ የተመለከተው ተአምራት በጣም የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ በጉድጓድ ውስጥ የተመለከተው ተአምራት እግዚአብሔር በቅዱሳኑ የሚሰራው ተአምራዊ አሰራር እንጂ ቅዱሳኑ በእግዚአብሔር ፊት የሚሰሩት ስራ አይደለም፣ ተአምራቱም የተሰራው በምድር ነው፣ ታሪኩ መረጃ ተደርጎ የቀረበው ግን በሰማይ ያለውን ምልጃ ለማስረዳት ነው፣ በዚህም ሁለቱ ምንም የማይገናኙ ታሪኮች ናቸው፡፡

በዚህም ስለ ቅዱሳን አማላጅነት የቀረቡት ታሪኮች የማይገናኙ ታሪኮችን የመቀጣጠል አሰራር እንጂ እውነታ አይደለም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱን ስንመለከት ቅዱሳን በአፀደ ነፍስ የማማለድ ስራ እንደማይሰሩ እንረዳለን፡-

- **<u>በአፀደ ነፍስ ያሉት በአፀደ ስጋ ያሉትን መርዳት የማይችሉ መሆኑን</u>**

መጽሐፍ ቅዱሱ በአፀደ ነፍስ ያሉት ሰዎች በአፀደ ስጋ ያሉትን ሰዎች መርዳት እንደማይችሉ ይናገራል፣

- መክ.94-6 “… ሙታን ግን አንዳች አያውቁም … <u>ከፀሐይ በታችም</u> በሚሰራው ነገር ለዘላለም እድል ፈንታ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም፡፡”
- ዕብ.7፡23-25 “እነርሱ <u>እንዳይኖሩ</u> ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፣ <u>እርሱ(ኢየሱስ) ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ</u> የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነሱ ሊያማልድ ዘወትር ይኖራልና…”

እነዚህ እውነታዎችም በተግባር የተረጋገጡባቸው ብዙ ኢጋጣሚዎች አሉ፣

- እነ ሄኖክ፣ ኤልያስ፣ አብርሃም … በነፍስ አፀድ ባሉበት ሁኔታ ውስጥ፣ ኢሳ.59፡15-16 “… እግዚአብሔርም አየ … ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ …” መባሉ፣ እንደዚሁም ሕዝ.22፡30-31 ላይ ቅዱሳኑ በነፍስ አፀድ እያሉ የሚማልድ በመጥፋቱ ህዝቡ በኃጢያቱ መቀጣቱን፣
- ሉቃ.16፡19-31 ላይም የአብርሃም፣ አልአዛርና ሐብታሙ ሰው በአፀደ ነፍስ የሚያደርጉትን ንግግር ውስጥ ሐብታሙ ሰው በሲኦል እንደተሰቃየና ቤተሰቦቹ ወደ ሲኦል እንዳይወርዱ በጭንቀት አብርሃምን ሲለምነውና በገነት ያለው አብርሃም በሲኦል ያሉትንም ሆነ በምድር ያሉትን ሰዎች ምንም ሊረዳ እንደማይችልና ይባሱኑ በአፀደ ስጋ ላሉት መፍትሄ የሚሰጡት እዚያው በአፀደ ስጋ ያሉት ነብያት እንጂ የነሱ ጉዳይ በአፀደ ነፍስ ካሉት ጋር የማይነካካ መሆኑን የነገረው መሆኑ፣
- ሐዋርያው ጳውሎስም ፊሊጵ.1፡23-24 ላይ “ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ … ነገር ግን በስጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው፡፡” በማለት ቅዱሳን የሚጠቃቀሙት በስጋ እያሉ መሆኑን ማሳየቱና 2ጢሞ.4፡7 ላይም “መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፣ ሩጫውን ጨርሻለሁ …” በማለት ፈጣሪ ከሱ የሚጠብቀውን ስራ መጨረሱን ሲናገር እንመለከታለን፡፡

እነዚህን እውነታዎች የሚያሳዩን በአፀደ ነፍስ ያሉት በአፀደ ስጋ ላሉት የምልጃ አገልግሎት መስጠት የማይችሉ መሆኑን ነው::

- **<u>በአፀደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን ያሉበት መንፈስ የፈራጅነት እንጂ የአማላጅነት አለመሆኑ</u>**

በአፀደ ነፍስ ያሉ ቅዱሳን ከፍርድ ቀን በፊት ያላቸው ፍላጎት በኃጢያተኞች ላይ ፍርድ እንዲፈጥን የሚጠይቁ እንጂ ፍርድ እንዳይፈረድ የሚማልዱ አይደሉም፣

> ራዕ.6፡9-11 "አምስተኛውንም ማህተም በፈታ ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሰዊያ በታች አየሁ:: በታላቅ ድምፅ እየጮሁ፣ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፣ <u>እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም? ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከመቼ አትበቀልም?</u> አሉ ... እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቁጥር እስኪፈፀም ድረስ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው::"

በፍርድ ቀንም ቅዱሳኑ ፍርድ በሰዎች ላይ እንዳይፈረድ የሚማልዱ ሳይሆን እራሳቸውም ከክርስቶስ ጋር በፈራጅነት የሚገለጡ መሆኑ፣

- ነቆሮ.6፡2 "ቅዱሳን በዓለም ላይ <u>እንዲፈርዱ</u> አታውቁምን?"
- ማቴ.19፡28 "እየሱስም እንዲህ አላቸው፣ እውነት እላችኋለሁ፣ እናንተስ የተከተላችሁኝ፣ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ <u>እናንተ ደግሞ በአስራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ስትፈርዱ</u> በአስራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ::"

በዚህም "በአፀደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን አማላጅ ናቸው" የሚለው አስተምህሮ ምን ያህል ከእውነታው የተቃረነ አስተምህሮ እንደሆነ እንመለከታለን::

- **<u>ሌላው "እሪ በከንቱ"</u>**

ከላይ በማሪያምና መላዕክት አማላጅነት ርዕስ ስር እንደተመለከትነው፣ ቅዱሳኑም እንደ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ መገኘት ስለማይችሉ፣ ወደ ቅዱሳኑም "አማልዱኝ" ተብሎ የሚደረገው ፀሎት "እሪ በከንቱ" ብቻ ነው::

በዚህም ቅዱሳኑ በሰማያዊው ስፍራ ላለው የምልጃ ስራ አለመሾማቸውን እንመለከታለን፣ ይህ የቅዱሳን ሰማያዊ አማላጅነት አስተምህሮ ክርስቲያናዊ ሳይሆን እንደ መላዕክት አማላጅነት ቁርአናዊ ነው(40፡7) ስለዚህ ይህንን አስተምህሮ የምትከተሉ ተቀደሱ::

በአጠቃላይም ስንመለከት ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ሰማያዊውን የምልጃ አገልግሎት የማይሰጡ መሆኑን ነው::

4.1.1.4. <u>የኢየሱስ አማላጅነት</u>

ከላይ እንደቀረበው ቤተክርስቲያኗ "አማላጅ" ብላ የያዘቻቸው ማርያምን፣ መላዕክትና ቅዱሳን ሰማያዊውን የምልጃ አገልግሎት እንደማይሰጡ ተመልክተናል፣ በዚህም ትክክለኛውን ሰማያዊ አማላጅ ማን እንደሆነ በግልፅ ሊታወቅ ይገባል፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ሰማያዊው አማላጅ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ በብዙ ስፍራዎች ላይ በተለያየ መንገድ ይናገራል(ከታች በስፋት ቀርቧል)።

የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግን እነዚህን የኢየሱስ ክርስቶስን አማላጅነት የሚገልፁትን የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍሎች አትቀበልም፣ የቤተክርስቲያኗ ምሁራኖችም እነዚህን የኢየሱስን አማላጅነት የሚገልፁትን የመጽሐፍ ቅዱሱን አስተምህሮዎች በተለያየ መንገድ ይቃወማሉ፣ ይህም፡-

1. "ኢየሱስ ፈፅሞ አማላጅ አይደለም፣
2. "የኢየሱስ ምልጃ ከውርስ ኃጢያት እንጂ ከድረጊት ኃጢያት አይደለም"
3. "ኢየሱስ ከትንሳኤው በኋላ ወደ አምላካዊ ማንነቱ ተመልሷል፣ ከዕርገቱ በኋላ አይለምንም፣ አሁን እሱ ፈራጅ ነው።"

የሚሉ ሲሆኑ መጽሐፍ ቅዱሱ ግን በሚያስገርም መልኩ ለሁሉም በቂ መልስ አስቀምጧል።

4.1.1.4.1. <u>"ኢየሱስ ፈፅሞ አማላጅ አይደለም"</u>

እነዚህ ቡድኖች በደፈናው "ኢየሱስ የማማለድ ስራ አይሰራም፣ እሱ ሙሉ አምላክ ነው፣ ማን ማንን ይለምናል? 'ኢየሱስ አማላጅ ነው' ማለት በራሱ የእሱን ክብር መንካት ነው" ይላሉ።

የዚህ ሐሳብ ዋነኛው ስህተት የሚነሳው ኢየሱስ ለሰው ልጆች መዳን ሲል ራሱን ዝቅ አድርጎ "ተዋህዶ" ሆኖ የመጣበትን ማንነት ካለመረዳት ነው፣ አይሁዶችም ኢየሱስን የሰቀሉት ይህንኑ ራሱን ዝቅ ያደረገበትን አሰራር ባለመረዳት ነበረ።

የኢየሱስ አማላጅነት ግን በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ በተለያዩ መንገዶች ተነግሯል፣

1. <u>በስሙ ትርጓሜ ተመልክቷል</u>

ኢየሱስ ሲወለድ ስሙ "ኢየሱስ" ተብሎ እንዲጠራ ያዘዘው እግዚአብሔር ነው፣ ያዘዘውም የስሙን ትርጉም ተናግሮ ነው፣

ማቴ.1፡21 "... እርሱ ህዝቡን ከኃጢያታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።"

አማላጅ የሚያስፈልገው ለኃጢያት ስርየት ነው፣ ኢየሱስ ማለት "ከኃጢያት የሚያድን" ማለት በመሆኑ <u>የኃጢያት ስርየት ጉዳይ የሚመለከተው ኢየሱስንና ኢየሱስን ብቻ መሆኑን እንመለከታለን</u>።

2. <u>የኃጢያት ማስተሰረያ/ማስወገጃ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ ተነግሯል</u>

- ዮሐ.2፡2 “እርሱም የኃጢታችን ማስተሰረያ ነው፣”
- ነዮሐ.3፡5 “እርሱም ኃጢያትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ…”
- ራዕ.1፡4-5 “… ለወደደን ከኃጢያታችንም በደሙ ላጠበን፣”
- ነጢሞ. 1፡15 “ኃጢያተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ…”

3. <u>የሰው ልጆችን ኃጢያት/እርግማን እንዲሸከም ተደርጓል</u>

- 2ቆሮ.5፡21 “እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢያት ያላወቀውን እርሱን <u>ስለ እኛ ኃጢያት አደረገው</u>፡፡”
- ገላ.3፡13 “በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተፅፏልና ክርስቶስ <u>ስለ እኛ እርግማን</u> ሆኖ ከህግ እርግማን ዋጀን፡፡”

4. <u>በሊቀ ካህንነት ሹመቱ ስለ ኃጢያት ስርየት የሚያስፈልገውን መስዋዕት አቅርቧል</u>

አንድ አካል ኃጢያትን የሚያሰርየው በሊቀ ካህነት ሲሾም እና ለኃጢያት ስርየት ደምና መስዋዕት ሲያቀርብ ነው፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን በሊቀ ካህንነት የተሾሙ አገልጋዮች የእንስሳትን መስዋዕት በማቅረብ የምልጃ አገልግሎትን ሲፈፅሙ ነበረ፣ የአዲስ ኪዳኑ አማላጅ ግን ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ ኢየሱስ እነዚህ ለኃጢያት ስርየት የሚያስፈልጉትን ሦስቱን ግብአቶችን በራሱ አሟልቶ እንመለከተዋለን፣

➢ <u>የሊቀካህንነት ሹመት</u>

"ሊቀካህን" ማለት በሰዎችና በእግዚአብሔር መካከል በመገኘት መስዋዕት በማቅረብ የሰዎችን ኃጢያት የሚያስተሰረይ ማለት ነው(ዕብ.8፡3, ዕብ.5፡1, ዕብ.7፡27 …)፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን ይህንን ስራ ሲሰሩ የነበሩት እንደነ አሮን የመሳሰሉ በሊቀ ካህንነት የተሾሙ አገልጋዮች ነበሩ፤ በአዲስ ኪዳን ዘመን መጽሐፍ ቅዱስ የሾመው ብቸኛ ሊቀካህን ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ(መዝ.110፡1-4, ዕብ.3፡1, ዕብ.5፡6, ዕብ.6፡20, ዕብ.7፡1-3, ዕብ.7፡23-26)፣ የአዲስ ኪዳን አማላጅ ኢየሱስ ብቻ ሆኖ እንመለከታለን፡፡

➢ <u>ለኃጢያት ስርየት የሚፈስ ደምና የሚቀርብ መስዋዕት</u>

ለኃጢያት ስርየት አማላጁ ከሊቀካህንነቱ ሹመት በተጨማሪ ስለኃጢያት ስርየት የሚሆን ደም ማፍሰስ እንዲሁም መስዋዕት ማቅረብ አለበት፣ ይህ የሆነው በሁለት ምክንያት ነው፣

- “ኃጢያት ያለ ደም አይነፃም” (ዕብ.9፡22)
- “የኃጢያት ደሞዝ ሞት ነው”(ሮሜ.6፡23)

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊቀካህናቱ ይህንን የኃጢያት ማንፃት ስራ ሲከውኑ የነበሩት የእንስሳቱን ደም በማፍሰስና በኃጢያተኛው ሰው ፋንታ እንስሳቱን መስዋዕት በማድረግ ነበረ፣ ነገር ግን በአዲስ ኪዳኑ ዘመን ለሰው ልጆች ኃጢያት ስርየት የራሱን ደም

በማፍሰስ(1ጴጥ.1፡18-19, ቆላ.1፡19-20 ...) እና በመስቀል ላይ መስዋዕት በመሆን(ዕብ.9፡26, ዕብ.10፡12 ...) ለሰው ልጆች ኃጢያት ዋጋ የከፈለው ኢየሱስ ብቻ ነው፡፡

ኢሳ.53፡10-11 "... ነፍሱን ስለ ኃጢያት መስዋዕት ካደረገ በኋላ ... ከነፍሱ ድካም ብርሃን ያያል ... ብዙ ሰዎችን ያፀድቃል፣ ኃጢያታቸውን ይሸከማል፡፡"

በዚህም ኢየሱስ በሊቀካህንነቱ ሹመት እና የራሱን ደም በማፍሰስና ህይወቱን በመስቀል ላይ መስዋዕት በማድረግ፣ የማስታረቅ ስራውን አከናወነ፣ በዚህም በአዲስ ኪዳኑ ዘመን አማላጅ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

5. <u>አማላጅነቱ በትንቢት ተነግሯል</u>

በብሉይ ኪዳን አማላጆች ሊቀካህናቱ ነበሩ ነገር ግን በአዲስ ኪዳን ዘመን አማላጅ ኢየሱስ እንደሚሆን ቀድሞ በትንቢት ተነግሮ ነበረ፣

ኢሳ.53፡5-12 "... እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቆሰለ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ የደህንነታችንም ተግሳፅ በሱ ላይ ነበረ፣ <u>በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን</u> ... <u>እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ</u> ... ስለ ህዝቤ ኃጢያት ተመትቶ ከህያዋን ምድር እንደተወገደ ከትውልዱ ማን አስተዋለ፡፡ ከክፉዎች ጋር መቃብሩን አደረጉ ... <u>ነፍሱን ስለኃጢያት መስዋዕት ካደረገ በኋላ</u> ... ከነፍሱ ድካም ብርሃንን ያያል፣ ፃድቅ ባርያዬም <u>በእውቀቱ ብዙ ሰዎችን ያፀድቃል፣ ኃጢያታቸውን ይሸከማል</u>፡፡ ስለዚህም እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፣ ከኃያልንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፤ ከአመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና እርሱ ግን <u>የብዙ ሰዎችን ኃጢያት ተሸከመ፣ **ስለ አመፀኞችም ማለደ**</u>፡፡"

ይህ አስቀድሞ በትንቢት የተነገረ እውነታ በትክክል መፈፀሙን ደግሞ በቀጣይ ክፍሎች እንመለከታለን፡፡

6. <u>እንደ አማላጅነቱም አማልዷል</u>

ኢየሱስ እንደ አማላጅነቱ በተግባር አማልዶ አሳይቷል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- ሉቃ.22፡31-32 "እነሆ ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ <u>አማለድሁ</u>..."
- ሉቃ.23፡34 "ኢየሱስም፡፡ አባት ሆይ፣ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ፡፡"
- ዮሐ.17፡1-17 "ከክፉ እንድትጠብቃቸው ... በእውነትህ ቀድሳቸው"

7. <u>በአማላጅነቱም የሰው ልጅንና ፈጣሪን አስታርቋል</u>

"አማላጅ" ማለት የተጣሉ አካላት የሚያስታርቅ "አስታራቂ" ማለት ነው፣ ኢየሱስ አማላጅ በመሆኑ በኃጢያት ምክንያት የተለያዩትን ሰውንና እግዚአብሔርን የማስታረቅ ስራ በብቃት ተወጥቷል፣

- ሮሜ.5፡10-11 "... ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር <u>በልጁ ሞት ከታረቅን</u> በኋላ በህይወቱ እንድናለን፤ ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን አሁን <u>መታረቁን ባገኘንበት</u> <u>በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ</u> በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን፡፡"
- ቆላ.1፡19-22 "... በመስቀሉ ደም ሠላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና እናንተንም ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፤ በፊት የተለያችሁትን ክፉ ስራችሁንም በማድረግ በሃሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን <u>በስጋው ሰውነት በሞቱ በኩል</u> <u>አስታረቃችሁ</u>፡፡"
- ኢፌ.2፡16 "ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ... ያስታርቅ ዘንድ ነው"

በአጠቃላይ ስንመለከት እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ በአንድነት የኢየሱስን አማላጅነት የሚነግሩን እውነታዎች ናቸው፤ በዚህም "ኢየሱስ አማላጅ አይደለም" የሚለው አባባል ክርስቲያናዊ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

4.1.1.4.2. <u>"ኢየሱስ ከውርስ ኃጢያት እንጂ ከድረጊት ኃጢያት አያማልድም"</u>

አንዳንዶች ከላይ የተመለከተው ዘዴ አላዋጣ ሲላቸው፣ ኃጢያትን በሁለት በመክፈል የውርስና የድርጊት ኃጢያት በማለት፣ "ኢየሱስ አማላጅ የሆነው ለውርስ ኃጢያት(ከአዳም ለሚወረሰው ኃጢያት) እንጂ ለድርጊት ኃጢያት(አንድ ሰው ለሚፈፀመው ኃጢያት) አይደለም፣ የድርጊት ኃጢያት አማላጆች ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ናቸው" ይላሉ፡፡ ነገር ግን ኢየሱስ የከፈለው የኃጢያት ዋጋ በኃጢያት አይነት የማይገደብና ሁሉንም አይነት ኃጢያት የማስተሰረይ አቅም እንዳለው መጽሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣

1. <u>ኢየሱስ ዋጋ የከፈለው ለሁሉም አይነት ኃጢያት መሆኑና በዚህም አማላጅነቱ ከሁሉም አይነት ኃጢያት መሆኑ</u>

   1ዮሐ.1፡7 "የልጁም የኢየሱስ ክርስቶስ ደም <u>ከኃጢያት ሁሉ</u> ያነፃናል፣"

   እዚህ ጋር "<u>**ከኃጢያት ሁሉ**</u>" የሚለው ቃል "ኃጢያት ሳይከፋፈል" ማለት ነው፣ ይህም የኢየሱስ የደም ጉልበት በተለያየ አይነት ኃጢያት እንደማይገደብና ኃጢያትን ሁሉ የማንፃት አቅም ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡

2. <u>"ለኃጢያታችንን፣ ለበደላችንን፣ ለመተላለፋችንን፣ ለአለመታዘዛችንን ..." በአጠቃላይ ለድርጊት ኃጢያታችን ተቀጪው ኢየሱስ መሆኑ</u>

   1ጴጥ.2፡22-24 "... እርሱም ኃጢያትን አላደረገም ... በስጋው ኃጢያ<u>ታችንን</u> በእንጨት ላይ ተሸከመ ..."

   ኢሳ.53፡6 "... እግዚአብሔርም <u>የሁላችንን</u> በደል በእርሱ ላይ አኖረ፡፡"

   ዕብ.2፡2 "... <u>መተላለፍና አለመታዘዝ ሁሉ</u> የጽድቅን ብድራት ከተቀበለ፣ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል ብንለው እንዴት እናመልጣለን?"

3. <u>ኢየሱስ አንዴ የከፈለው ክፍያ ሙሉ መሆኑና ሳይጨርስ ወይንም ከአቅም በላይ ሆኖበት ለሌላ አካል የስተላለፈው ስራ አለመኖሩ</u>

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ "ተፈፀመ" እንዳለው፣ የከፈለው ዋጋ ሙሉ የኃጢያት ዋጋ መሆኑና ይህም አንዴውኑ በመስቀል ላይ የተጨረሰ መሆኑ፣

- ዕብ.10፡11-14 "ሊቀካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢያትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መስዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሟል፤ እርሱ(ኢየሱስ) ግን ስለ ኃጢያት <u>አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ</u> በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ... <u>አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍፁማን አድርጎአቸዋልና</u>፡፡"
- ዕብ.7፡22-27 "... እርሱም እንደነዚያ ሊቀካህናት አስቀድሞ ስለራሱ ኃጢያት በኋላም ስለ ህዝቡ ኃጢያት ዕለት ዕለት መስዋዕት ሊያቀርብ አያስፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህንን <u>አንድ ጊዜ ፈፅሞ</u> አድርጎአልና፡፡"
- ዕብ.9፡25-28 "ሊቀካህናት በየአመቱ የሌላውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ፣ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም፣ እንዲህ ቢሆንስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፣ አሁን ግን በዓለም ፍፃሜ <u>ራሱን በመሰዋት ኃጢያትን ሊሸር አንድ ጊዜ ተገልጦአል</u>፡፡ ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት ተመደበባቸው፣ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ የብዙዎችን ኃጢያት ሊሸከም <u>አንድ ጊዜ ከተሰዋ</u> በኋላ <u>ያድናቸው</u> ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢያት ይታይላቸዋል፡፡"

ከዚህም የምንረዳው ኢየሱስ አንዴው የከፈለው ዋጋ ሙሉ መሆኑና ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የሚሸፍኑለት ጉድለት አለመኖሩን ነው፡፡

4. <u>የሰው ልጅ ኢየሱስ አንዴ በከፈለው ዋጋ ብቻ ከኃጢያት ነፅቶ የሚፀድቅ መሆኑ</u>

በአዲስ ኪዳን ፅድቅ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው፣ በዚህም <u>አንድ ሰው በኢየሱስ ሲያምን የውርስ ኃጢያቱ ተሰርዮለት የድርጊት ኃጢያቱ አይቀርበትም</u>፣ በዚህም አንድ ሰው በኢየሱስ እንዳመነ የውርስ፣ የድርጊትና ሌላም አይነት ኃጢያት ካለ ከሁሉም በአንዴው ነፅቶ "ፃድቅ" ይሆናል፣

- ሮሜ.3፡22 "እርሱም፣ ለሚያምኑት ሁሉ የሆነ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር <u>ፅድቅ</u> ነው፡፡"
- ሮሜ.5፡9-11 "ይልቁንስ እንግዲህ አሁን <u>በደሙ ከፀደቅን</u> በእርሱ ከቁጣው እንድናለን፡፡ ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን በኋላ በህይወቱ እንድናለን፤ ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን፡፡"
- ሮሜ 5፡17- "በአንዱ በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ ይልቁን የጸጋን ብዛትና <u>የፅድቅን ስጦታ</u> ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በህይወት ይነግሣሉ፡፡"

“መፅደቅ” ማለት ከኃጢያት መንፃት ማለት ነው፣ “የኢየሱስ ደም ያፀድቃል” ማለት ያፀድቃል ማለት ነው፣ በዚህም የኢየሱስ ደም ከአዳም የመጣውን የውርስ ኃጢያትን አሰርዮ የድርጊት ኃጢያትን ማንፃት የማይችል አድርጎ የደሙን ጉልበት በአንድ ጉዳይ ብቻ በመገደብ ለድርጊት ኃጢያት ሌላ አማላጅ መፈለጉ ስህተት ነው።።

5. <u>አዳኝ ኢየሱስ ብቻ መሆኑ</u>

አዳም በሰራው ኃጢያት ምክንያት የሰው ልጆች በሙሉ ሲወድቁ ለሰው ልጆች <u>ኃጢያት በሙሉ</u> ዋጋ በመክፈል የሰውን ልጅ ከሲኦል ፍርድ ያዳነው ኢየሱስ ብቻ ነው፣ በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ ለይቶ “አዳኝ” የሚለው ኢየሱስን ብቻ ነው፣

ሐስ.4፡12 “መዳንም በሌላ በማንም የለም፣ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና።።”

ኢየሱስ የሰራው ስራ የውርስን ኃጢያት አሰርዮ ለድርጊት ኃጢያት ሌላ አዳኝ የሚያስፈልግ ባለመሆኑ ነው መጽሐፉ አስረግጦ “መዳን በሌላ በማንም የለም ...” ያለው።።

በዚህም ማሪያም/ፃድቃን/መላዕክትን በማሸጋሸግ በምልጃ ስራ ላይ የምናስገባበት መንገድ የለም፣ <u>የኢየሱስ ስራ የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን አጋዥነት ሳይፈልግ ብቻውን ማፅደቅ ይችላልና</u>።።

በአጠቃላይም “የኢየሱስ አማላጅነት ለውርስ ኃጢያት እንጂ ለድርጊት ኃጢያት አይሰራም” የሚለው አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና በዚህም የኢየሱስን አማላጅነት መሸፈን የማይቻል መሆኑን እንመለከታለን።።

4.1.1.4.3. <u>“የኢየሱስ አማላጅነት በምድራዊ ህይወቱ ብቻ ነው፣ ኢየሱስ ከዕርገቱ በኋላ አብን አይለምንም፣ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም”</u>

በመጀመሪያ የተመለከትነው “ኢየሱስ ፈፅሞ አማላጅ አይደለም” የሚሉትን ቡድኖችን ነው፣ በመቀጠል የተመለከትነው ደግሞ ይህ ሐሳብ አላስኬድ ያላቸውና ኃጢያትን በሁለት በመክፈል፣ የውርስና የድርጊት በማለት፣ ለድርጊት ኃጢያት የምልጃ ስራ ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ለመስጠት የሞከሩትን ነው፣ ሦስተኛው ቡድን ደግሞ የእነዚህን ሁለቱን ቡድኖች ስህተት በማስተዋል ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በምልጃ ስራ ላይ አሸጋሽን ለማስገባት ሲሉ ሌላ ሦስተኛ መንገድ የቀየሱትን ነው።።

እነዚህ ወገኖችም የኢየሱስን ህይወት “ቅድመ ዕርገትና ድህረ ዕርገት” በማለት በሁለት ምዕራፍ በመክፈል፣ የተወሰነ የምልጃ ክፍልን ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ለመስጠት ሲሰሩ እንመለከታለን።። በዚህም “ኢየሱስን ከእርገቱ በፊት ሲያማልድ ነበረ አሁን ግን ኢየሱስ አብን አይለምንም፣ አሁን ከዕርገቱ በኋላ ፈራጅ ነው” በማለት ከዕርገቱ በኋላ ያለውን የምልጃ አገልግሎት ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ይሰጣሉ፣ ሁለቱንም ሐሳቦች ቀጥለን እንመለከታለን፡-

- **<u>“ኢየሱስ ከዕርገቱ በኋላ አብን አይለምንም”</u>**

እነዚህ ቡድኖች ለዚህ የሚያቀርቡት መከራከሪያ፣

> ዮሐ.16፡26 “በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤”

የሚለውን ቃል ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ቃል የሚናገረው ስለ ሁለት የተተካኩ ነገሮች፣ ይህም ኢየሱስ በምድር በነበረበት ወቅት ለሰዎች በቀጥታ ወደ አብ ሲያደርግ የነበረው የልመና አገልግሎት ከእርገት በኋላ ሰዎች “በኢየሱስ ስም” በመፀለይ ማግኘት የሚችሉ መሆኑን ለማመልከት እንጂ በኢየሱስ በኩል የነበረው የምልጃ ስራ ከዕርገት በኋላ ይቆማል የሚል አይደለም፡፡

ኢየሱስ ከዕርገቱ በፊት ለሰዎች ኃጢያት ስርየት በቀጥታ አብን ሲለምን ነበረ ነገር ግን ከዕርገቱ በኋላ ሰዎች በኢየሱስ በኩል የኃጢያት ስርየት ማግኘት የሚችሉት በስሙ በኩል ነው፡-

- ዮሐ.16፡23 “በዚያን ቀን ከእኔ አንዳች አትለምኑም፣ እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ <u>በስሜ</u> የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል፡፡”
- ሐስ.10፡43 “በእርሱ የሚያምን ሁሉ <u>በስሙ</u> የኃጢያቱን ስርየት እንዲቀበል ነብያት ሁሉ ይመሰክሩለታል፡፡”
- ሉቃ.24፡47 “<u>በስሙም</u> ንሰሀና የኃጢያት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአህዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተፅፎአል፡፡”
- 1ዮሐ.2፡12 “ልጆች ሆይ ኃጢያታችሁ <u>ስለ ስሙ</u> ተሰርዮላችኋል ...”

ይህም የሚያሳየው ዛሬ ሰዎች ኢየሱስን በአካል አግኝተው እንዲያማልዳቸው መጠየቅ ባይችሉም፣ ሰዎች የኢየሱስን የምልጃ አገልግሎት የሚያገኙት “በኢየሱስ ስም” በሚያደርጉት ፀሎት በኩል ነው፡፡ ይህ የሆነው ደግሞ ኢየሱስና ስሙ አንድ በመሆናቸው ነው፣ ይህ እውነታም መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ በብዙ መንገድ ተመልክቷል፣

- በኢየሱስ እመኑ እንደተባለው(ዮሐ.20፡31)፣ ሰዎች በኢየሱስ ስም እንዲያምኑ መነገሩ(1ዮሐ.3፡23, ሐስ.3፡16, ዮሐ.2፡23, ዮሐ.1፡12 ...)፣
- ኢየሱስ በቀጥታ ለሰው ልጆች ሲሰጣቸው የነበሩት አገልግሎቶችን ከዕርገቱ በኋላ ሰዎች በስሙ በኩል እንዲያገኙ መደረጉ፣ እነሱም፣ የኃጢያት ስርየት(1ዮሐ.2፡12)፣ የዘላለም ህይወት(1ዮሐ.5፡13)፣ የእግዚአብሔር ልጅነት(ዮሐ.1፡12)፣ መዳን(ሐስ.4፡12)፣ ተስፋ(ማቴ.12፡21)፣ ኢጋንንት ማውጣት(ማር.16፡17)፣ ተአምራት መስራት(ማር.9፡39)፣ ፈውስ(ሐስ.3፡16) ...

እነዚህ እውነታዎችም የሚያሳዩን ኢየሱስና ስሙ አንድ መሆናቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይም ስንመለከት ከዕርገት በፊትም ሆነ በኋላ የምልጃ ጉዳይ የሚመለከተው ኢየሱስን ብቻ መሆኑን ነው፡፡

- **<u>"ኢየሱስ ከዕርገቱ በኋላ ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም"</u>**

እነዚህ ወገኖች ደግሞ "ኢየሱስ በምድር በነበረበት ወቅት ሰውንና ፈጣሪን የማስታረቅ የምልጃ ስራውን ሰርቷል በአሁኑ ጊዜ ግን የሚሰራው የፈራጅነት ስራ ነው" ይላሉ፣ ለዚህም የሚያቀርቡት መከራከርያ፣

> ዮሐ.5፡22-23 "ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድንም ያከብሩት ዘንድ፣ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በአንድ ሰው እንኳን አይፈርድም፡፡"

በርግጥ የኢየሱስ ፈራጅነት የሚያከራክር አይደለም ነገር ግን ግልፅ ሊሆን የሚገባው ኢየሱስ በፈራጅነት የሚገለጠው በፍርድ ቀን ነው፣ የፍርድ ቀን ደግሞ ገና ነው፣ ከፍርድ ቀን በፊት ኢየሱስ በምልጃ በማገልገል፣ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ በመገለጥ የአርማጌዶንን ጦርነት በመምራት፣ የ666 መንፈስን በመቅጣት፣ ለሺ አመታት ምድርን በመግዛትና በመሳሰሉት አገልግሎቶቹን ከፈፀመ በኋላ ነው፡፡ በዚህም መታወቅ ያለበት ቁም ነገር የእግዚአብሔር ፕሮግራም ነው፣ ፈራጁ ኢየሱስ ቢሆንም ኢየሱስ በፈራጅነት የሚገለጠው ግን አሁን ሳይሆን በፍርድ ቀን ነው፡፡

> ዕብ.9፡24 "ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰራች፣ እውነተኛይቱ ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት <u>አልገባምና</u>፣ ነገር ግን <u>በእግዚአብሔር</u> ፊት ስለእኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ እርስዋ ወደ ሰማይ ገባ፡፡"

በትንሳኤና በፍርድ ቀን መካከል ካሉት የኢየሱስ አገልግሎቶች አንዱ አምነው <u>የፀደቁት ፃድቃን</u>፣ ከፀደቁ በኋላ በሚሰሩት ኃጢያት እንዳይፈረድባቸው ከፍርድ የማስመለጥ የምልጃ ስራ ነው፣ አንድ ሰው በኢየሱስ ሲያምን ከአዳም የሚመጣውም ሆነ በራሱ የሰራቸው ኃጢያቶች(የድርጊት ኃጢያቶች) ይሰረዩለትና ፃድቅ ይሆናል፣ ይሁን እንጂ ይህ ሰው ከፀደቀ በኋላ ኃጢያት ቢሰራ ይህ ኃጢያት የሚሰረየው በሰውየው ንስሀና በኢየሱስ የምልጃ አገልግሎት ነው፡፡

ሐዋርያቱ የኢየሱስ ድህረ ትንሳኤ የምልጃ አገልግሎት ከዕርገቱ በኋላ በፃፏቸው መልዕክቶቻቸው ውስጥ በተለያዩ አባባሎች "አማላጅ፣ መካከለኛ፣ ጠበቃ፣ ሊቀካህን ... በማለት በተለያየ መንገድ ገልፀዋል፣

1. **<u>አማላጅ</u>**

የኢየሱስን አማላጅነት ኢየሱስ ካረገ በኋላ በተፃፉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ቃል በቃል ተነግሯል፣

> ሮሜ.8፡34 "የሞተው፣ ይልቁን ከሙታን የተነሳው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፣ ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡"

ይህ ቃል “ስለእኛ የማለደው” ሳይሆን ስለእኛ “የሚማልደው” ነው የሚለው እንደዚሁ ኢየሱስ ይህንን የሚሰራው የት ሆኖ እንደሆነ በማመልከት “በአብ ቀኝ” ይላል፣ በዚህም ኢየሱስ ከርስቶስ የአሁን አገልግሎት ሰማያዊ የምልጃ አገልግሎት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

> ዕብ.7፡22-27 “እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል፡፡ እነርሱ እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤ ስለ እነርሱም **ሊያማልድ** ዘወትር በህይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈፅሞ ሊያድናቸው ይችላል፡፡”

እዚህ ጋር እያወዳደረ ያለው የቅዱሳኑን ምልጃና የኢየሱስን ምልጃ ልዩነት ነው፣ በዚህም የኢየሱስ ምልጃ ዘላቂ፣ በሞት የማይገደብና ከዕርገቱም በኋላ የማይቆም መሆኑን ነው፡፡

2. <u>መካከለኛ</u>

ኢየሱስ በፈራጅነቱ ከመገለጡ በፊት አሁን የሚገኘው በሰውና በእግዚአብሔር መካከል በሚገኘው የአማላጅነት ስፍራ ነው፣ በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ካረገ በኋላም “መካከለኛ” ይለዋል፣

- ፩ጢሞ.2፡5 “አንድ እግዚአብሔር አለና፣ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው <u>መካከለኛ</u> ደግሞ አንድ አለ፣ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፡፡”
- ዕብ.9፡15 “ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲፀና ሕግን የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለሆነ፣ የተጠሩት የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ <u>እርሱ የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ነው</u>፡፡”
- ዕብ. 12፡24 “<u>የአዲስ ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን ወደ ኢየሱስ</u>፣ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደ ሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል፡፡”

ይህ የኢየሱስ መካከለኝነት “እኔ ወደ አብ የሚወስደው መንገድ ነኝ”(ዮሐ.14፡6)፣ “እኔ ወደ አብ የሚያስገባው በር ነኝ”(ዮሐ.10፡7)፣ “በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን”(ዕብ.7፡25) … በመሳሰሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላትም ላይ ተመልክቷል፣ ፩ጢሞ.2፡5 ላይ የተገለፀው “የሰው ልጅ” የሚለው ቃል ደግሞ ኢየሱስ ከትንሳኤውና ከዕርገቱ በኋላ እንኳን ያለው በፍፁማዊ አምላካዊ ማንነቱ ሳይሆን ራሱን ዝቅ ባደረገበት የተዋህዶው “የሰው ልጅ” ማንነቱን መሆኑን ያሳያል፡፡

3. <u>ጠበቃ</u>

ኢየሱስን ወደ ፈራጅነቱ ከመሄዱ በፊት አሁን እየሰጠ ያለው አገልግሎት ስለ ሰው ልጆች ኃጢያት ስርየት የጠበቃነት አገልግሎት ነው፣ መጽሐፉ ይህንን የተናገረው ኢየሱስ ካረገ በኋላ ነው፡-

1ዮሐ.2፡1 “ልጆቼ ሆይ፣ ኃጢያትን እንዳታደርጉ ይህን እፅፍላችኋለሁ፡፡ ማንም ኃጢያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ፃድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡”

በዚህም ኢየሱስ ቅዱሳን ላይ ፍርድ እንዳይተላለፍ ስለነሱ የቆመ ጠበቃ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ካረገም በኋላም “አማላጅ፣ መካከለኛ፣ ጠበቃ” እያለ መጥራቱ ኢየሱስ ዛሬ ከእርገቱም በኋላ የሰው ልጆች አማላጅነት ስራ እየሰራ መሆኑን ያሳያል፡፡

4.1.1.4.4. ከኢየሱስ ውጪ ሰማያውን የምልጃ አገልግሎት ማንም መስራት የማይችል ስራ መሆኑ

ከላይ የቀረቡት እውነታዎች “ኢየሱስ አማላጅ አይደለም” የሚሉት ክርክሮች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆናቸውን ለማሳየት የቀረቡ እንጂ ዋናውን እውነታ ስንመለከት በአዲስ ኪዳን ዘመን ሰማያዊውን የምልጃ አገልግሎት ከኢየሱስ በስተቀር ሌላ አካል ሊሰራው የማይችለው ስራ ነው፡፡

አንድ አካል በሰማያዊው የምልጃ አገልግሎት ለመሾም ሰማያዊ መስፈርቶች፣ ቅድመ ሁኔታዎችና ማንነቶች ያስፈልጉታል፣ እነዚህን የሚያሟላ ብቸኛው አካል ደግሞ ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ፣ ኢየሱስ ብቸኛው የአዲስ ኪዳን ዘመን ሰማያዊ አማላጅ መሆኑን ያሳያል፣

1. ኢየሱስ የሰማያዊው ቤተመቅደስ ብቸኛ ሊቀካህን መሆኑ፣
   በብሉይ ኪዳን ዘመን የኃጢያት ስርየት ሲደረግ የነበረው በሰው ሊቀ ካህን በምድራዊዋ ቤተ መቅደስ ነበረ፣ አሁን ኢየሱስ የቃል ኪዳንዋ ታቦት ባለችበት በሰማያዊቷ ቤተ መቅደስ(ራዕ.11፡19) ብቸኛው ሊቀ ካህን በመሆኑ(ዕብ.8፡1)፣ ሰማያዊ አማላጅ ኢየሱስ ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፣
   - ዕብ.8፡1-7“... በሰማያት በግርማው ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፣ እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳዋን አገልጋይ ነው፣ እርስዋም በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት ...”
   - ዕብ.9፡1-12 “ፊተኛይቱም ደግሞ የአገልግሎት ስርዓትና የዚህ ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት ... ይህም ለአሁኑ ጊዜ ምሳሌ ነው ... ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሰራች ማለትም ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈፅሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም ...”
   - ዕብ.6፡20 “በዚያም ኢየሱስ እንደ መልከ ፄዲቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው፣ ስለኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ፡፡”

እነዚህ እውነታዎችም በሰማያዊዋ ቤተ መቅደስ የተሾመው ብቸኛው ሊቀካህን(አማላጅ) ኢየሱስ ብቻ መሆኑን ያሳያሉ::

2. በሰማያዊው ቤተመቅደስ መስዋዕት ያቀረበው ኢየሱስ ብቻ መሆኑ፣
   ኃጢያት የሚሰረየው በመስዋዕትና በደም ነው፣ በዚህም አንድ አካል በሰማያዊው ቤተመቅደስ አማላጅ ለመሆን በሰማያዊዋ ቤተመቅደስ መስዋዕት ማቅረብ መቻል አለበት፣

   > ዕብ.9፡11-12 "ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው መልካም ነገር ሊቀካህናት ሆኖ በምትበልጠውና በምትሻለው በእጆችም ባልተሰራች ማለት ለዚህ ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን የዘላለም ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈፅሞ ወደ ቅድስት <u>በገዛ ደሙ ገባ እንጂ</u> በፍየሎችና በጥጆች አይደለም::"

   በሰማያዊዋ ቤተ መቅደስ ለኃጢያት ስርየት መስዋዕት ያቀረበው ኢየሱስ ብቻ መሆኑ ኢየሱስ ብቸኛ ሰማያዊ አማጅ መሆኑን ያሳያል::
3. የኃጢያት ማስተሰረያ/ማስወገጃ ኢየሱስ ብቻ መሆኑ፣
   - 1ዮሐ.2፡2 "እርሱም የኃጢታችን ማስተሰረያ ነው፣"
   - 1ዮሐ.3፡5 "እርሱም ኃጢያትን ሊያስወግድ እንደተገለጠ ታውቃላችሁ..."
   - 1ጢሞ. 1፡15 "ኃጢያተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ ..."
4. የሰው ልጆችን ኃጢያት/እርግማን እንዲሸከም የተደረገው ኢየሱስ ብቻ መሆኑ፣
   - 2ቆሮ.5፡21 "እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ፅድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢያት ያላወቀውን እርሱን <u>ስለ እኛ ኃጢያት አደረገው</u>::"
   - ገላ.3፡13 "በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ ተፅፏልና ክርስቶስ <u>ስለ እኛ እርግማን</u> ሆኖ ከህግ እርግማን ዋጀን::"
5. ኢየሱስ በተዋህዶነቱ ውስጥ ባለው <u>በፈጣሪ ማንነቱ ስለ ፅድቅ የሚሟገት በመሆኑ፣ በሰውኛ ማንነቱ ደግሞ የሰውን ድካምና የሰይጣንን ፈተና ግምት ውስጥ የሚያስገባ(ዕብ.4፡15)</u> በመሆኑ በሰውና በፈጣሪ መካከል ትክክለኛውን የምልጃ ሚዛን መጠበቅ የሚችል ኢየሱስ ብቻ መሆኑ፣
6. ኢየሱስ በተዋህዶነቱ ውስጥ ባለው አምላክነት በሁሉም ስፍራ በመገኘት የሰዎችን የንስሀ ፀሎት መቀበል መቻሉ ከላይ የተመለከትነው የ"እሪ በከንቱ ችግር" ችግር የሌለበት መሆኑና በእግዚአብሔር አብ ቀኝ በመገኘቱ ምክንያት ደግሞ የሰዎችን የምልጃ ፀሎት ማድረስ የሚችል መሆኑ፣
7. ስሙ "ኢየሱስ" በመሆኑና "ኢየሱስ" ማለት ደግሞ "ከኃጢያት የሚያድን"(ማቴ.1፡21) ማለት መሆኑ እንዲሁም እየሱስ የተገለጠው ኃጢያትን ሊያስወግድ መሆኑ(1ዮሐ.3፡5) ስንመለከት የኃጢያት ስርየት ጉዳዮች ከኢየሱስ በቀር ማንንም የማይመለከት መሆኑን እንመለከታለን::

እነዚህን እውነታዎችም በአንድ ላይ ስንመለከት እኔ መንገድ ነኝ(ዮሐ.14፡6)፣ በር ነኝ(ዮሐ.10፡9) … ካለው ከኢየሱስ በቀር ማንም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሊቆም እንደማይችልና ኢየሱስም ምንም **ምትክ የሌለው ብቸኛው ሰማያዊ አማላጅ** መሆኑን እንመለከታለን፡፡ የሚገርመው ደግሞ ለምድራዊው አማላጅነት እንኳን ቅዱሳን ፀሎታቸውን ማድረግ ያለባቸው "በኢየሱስ ስም" በመሆኑ(ዮሐ.14፡13-14, ዮሐ.15፡16, ዮሐ.16፡24 …)፣ የምልጃ ጉዳይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚመለከተው ኢየሱስና ኢየሱን ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

የኢየሱስን አማላጅነት የሚያሳዩ እነዚህን ህልቆ መሳፍርት እውነታዎች በአንድ ላይ ስንመለከት የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ምን ያህል ከእውነታ እንደራቀች ነው፡፡ በቤተክርስቲያኗ የኢየሱስን አማላጅነት ለመሸፈን እነዚህ ሁሉ ጥረቶች የተደረጉት ደግሞ ዓላማቸው አንድ ነው፣ ሰዎች በኢየሱስ አማላጅነት የኃጢያት ስርየት አግኝተው ገነት እንዳይፀድቁ ነው፣ ይህንን ስራ የሚሰራው ደግሞ ከመነሻውም ሰዎች ከገነት እንዲባረሩ ምክንያት የነበረው ዲያብሎስ ነው፣ አሁንም ደግሞ ሰዎች የኢየሱስን ምልጃ ተጠቅመው ወደ ገነት እንዲገቡ የቀረበውን መንገድ እንዳይታይ በሌሎች አካላት እንዲሸፈኑ እያደረገ ይገኛል፣ በዚህም እያንዳንዱ ሰው በዚህ ሜራ ሊነቃና በኢየሱስ በኩል የተዘጋጀውን የምልጃ አገልግሎት በአግባቡ ሊጠቀምበት ይገባል፡፡

4.1.2. <u>የሰው ልጆችን ከሲኦል የሚያድነው ማን ነው? ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ ኢየሱስ፣ አራቱም፣ ሦስቱ ወይስ ሁለቱ?</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ያለ አግባብ በኢየሱስ የምልጃ ስራ ላይ እንዲገቡ ተደርገው ሰው የኢየሱስን የምልጃ አገልግሎት እንዳያገኝ ተደርጓል ነገር ግን ይህ ኢየሱስን በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የመጋረድ ስራ በዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም፣ ዋናውን ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣለትን ተልዕኮ፣ ይህም የሰው ልጆችን የማዳኑን ስራ የመጋረድና የማጠልሸት ስራ ተሰርቷል፣ ቀጥሎ በስፋት ቀርቧል፡፡

ከመነሻው ስንመለከት "አዳኝ" የሚለው ቃል ሰፋ ያለ ትርጉም አለው፣ ይህም ማስታረቅ፣ ማማለድ፣ ቤዛነት፣ መድኃኒትነት … በአጠቃላይ ከሲኦል አስመልጦ ለመንግሥተ ሰማይ ብቁ የማድረግን ስራ ያመለክታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ሰዎች የሚድኑት በኢየሱስ ብቻ መሆኑን ይናገራል፣

- ሐስ.4፡12 "መዳንም በሌላ በማንም የለም፣ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና፡፡"
- ነጢሞ. 1፡15 "ኃጢያተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ …"
- ዘካ.9፡9 "አንቺ የጽዮን ልጅ ሆይ፣ እጅግ ደስ ይበልሽ፤ አንቺ የኢየሩሳሌም ልጅ ሆይ፣ እልል በዪ፤ እነሆ፣ ንጉሥሽ ጻድቅና አዳኝ ነው፤ ትሁትም ሆኖ በአህያም፣ በአህያይቱም ግልገል በውርጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል፡፡"

እዚህ ጋር መጽሐፍ ቅዱሱ "ሌላ የለም" የሚለውን ቃል የጨመረው ከኢየሱስ ሌላ ወደ ማንም እንዳንመለከት በሚል ነው ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ይህ ቃል ሰሚ አጥቶ የሰው ልጆችን የማዳን ስራ የሚሰሩት ማርያም፣ መላዕክትና ቅዱሳን እንደሆኑ ነው የሚነገረው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

4.1.2.1. <u>"ማርያም የሰው ልጆችን ከሲኦል ታድናች"</u>

ማርያም "አማላጅ ናት" በማለት ሰዎች በክርስቶስ አማላጅነት እንዳይድኑ የተሰራውን ስራ ከላይ ተመልክተናል፣ ይህ ክርስቶስን በማርያም ስም የመጋረድ ስራ በዚህ አያበቃም፣ ዋናውን ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣለትን ተልዕኮ እንኳን እስከመጋረድ ይሄዳል፡፡ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን "የሰው ዘር ከሲኦል የሚድነው በማርያም አማካኝነት ነው" በማለት ማርያምን "ኪዳነ ምህረት፣ የዓለም መድኃኒት፣ ቤዛዊት ዓለም፣ ምዕራገ ፀሎት ..." ትላታለች፣

- **<u>"ኪዳነ ምህረት/ሰአሊተ ምህረት"</u>**

መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት በሙሴ በኩል በወረደው ኪዳን ሰዎች መዳን ስላልቻሉ ኪዳኑ ተሽሮ አዲሱ ኪዳን በኢየሱስ በኩል ወረደ፣ ኪዳን የሚፀናው በደም በመሆኑ ሙሴ ብሉይ ኪዳንን በኮርማዎች ደም እንዳፀናው(ዘጸ.24፡7-8) ኢየሱስ ደግሞ አዲሱን ኪዳን በመስቀል ላይ ባፈሰሰው በራሱ ደም አፀና፣

ማቴ.26፡28 "(ኢየሱስም) ስለ ብዙዎች ኃጢያት ይቅርታ የሚፈስ <u>የአዲስ ኪዳን ደሜ</u> ይህ ነው፡፡"

በዚህም የአዲስ ኪዳኑ ባለቤት ስለኪዳኑ ደሙን ያፈሰሰው ኢየሱስ ነው፣ ይህ ኪዳንም እንደ ሙሴው ብሉይ ኪዳን፣ ደካማ ሆኖ፣ ተሽሮ በማርያም በኩል ሌላ ኪዳን አልተደረገም፣ በኢየሱስ በኩል ከተደረገው ኪዳን በኋላ በሞተችው ማርያም በኩል የወረደ ሌላ ኪዳን የለም፣ በዚህም በማርያም በኩል ሌላ ኪዳን እንደወረደ ተደርጎ ማርያም "ኪዳነ ምህረት/ሰአሊተ ምህረት" የተባለችበት አሰራር የኢየሱስን ኪዳን ለመሸፈን የተሰራ ድርሰት ነው፡፡

- **<u>"የዓለም መድኃኒት"</u>**

መጽሐፍ ቅዱሱ "የዓለም መድኃኒት" የሚለው ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፣

1ዮሐ.4፡14 "እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደላከው እንመሰክራለን፡፡"

መድኃኒቱ ከአብ የተላከው ኢየሱስ በመሆኑ ጉድለት የሌለበት መድኃኒት መሆኑ እሙን ነው ነገር ግን በማርያም ስም የኢየሱስ መድኃኒትነት እንዳይታይና ሰዎች እንዳይድኑበት በሚሰራው ሤራ ምክንያት በቤተክርስቲያኒቷ "የዓለም መድኃኒት" የምትባለው ማርያም ናት፣

[82] "... እመቤታችንን <u>የዓለም ሁሉ መድኃኒት አድርጎ እንደፈጠራት</u> ልብ አድርገችሁ እወቁ፡፡ የኢ.አ.ተ.ቤ/ክ፣ ተአምረ ማርያም 3ኛ እትም ፣ ምዕ.12፡1-62፣ ገፅ 43-62፣ ትንሳኤ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣ 1989 ዓ.ም፡፡"

- **<u>"ቤዛዊት ዓለም"</u>**

መጽሐፍ ቅዱሱ የሰው ልጆች ቤዛ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ይነግረናል፣ ሮሜ 3፡23-24 "ሁሉም ኃጢያትን ሰርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፣ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይፀድቃሉ፡፡"

የኢየሱስ ቤዛነት ሙሉ በመሆኑ ሰዎችን የማፅደቅ ችሎታ እንዳለው ይህ ቃል ይነግረናል ነገር ግን ሰዎች በዚህ ሙሉ በሆነው በኢየሱስ ቤዛነት እንዳይድኑ በሚፈልገው አካል የሰው ልጆች ቤዛ ማርያም እንደሆነች ይነገራል፣

[83] "... ማርያም በሲኦል ላሉ ነፍሳትና ለሰው ልጆች ሁሉ ሞታ በሦስተኛ ቀን ከሞት ተነስታ አርጋ በቀኝ በመቀመጧ የከፈለችው ዋጋ እርሷን <u>ቤዛዊት ዓለም</u> አሰኝቷታል፡፡ (መጽሐፈ ፀሎት ወመዝገብ ፀሎት በአማርኛ፣ ነገረ ማርያም ገፅ 638-640፣ ተሰፈ ገብረ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ 1989 ዓ.ም)"

- **<u>"ምዕራገ ፀሎት"</u>**

እንደ ቤተክርስቲያኗ አገላለፅ "ምዕራገ ፀሎት" ማለት የፀሎት ማሳረጊያ ማለት ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ የፀሎት ማሳረጊያ ኢየሱስ እንደሆነና ማንም ሰው ፀሎቱን "በኢየሱስ ስም" ካሳረገ ለፀሎቱ መልስ እንደሚያገኝ ይናገራል (ዮሐ.14፡13፣ ዮሐ.14፡14፣ ዮሐ.16፡24 ...)፤ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ባለው ኢየሱስን በማርያም የመጋረድ ስራዎች ምክንያት "ምዕራገ ፀሎት" በማርያም ስም እንደሆነ ይነገራል፣

[84]"ድንግል ሆይ ... የፀሎት ማሳረጊያ አንቺ ነሽ፡፡" (አባ ፅጌ ድንግል፣ ማኅሌት ፅጌ፣ ገፅ 613)

እነዚህ "ማርያም ለሰው ልጆች ኃጢያት በመሞት ለሰው ልጆች ኪዳነ ምህረት፣ የኃጢያት መድኃኒት፣ ቤዛ፣ ምዕራገ ፀሎት ናት" የሚሉት ለማርያም የተሰጡት አገልግሎቶችና ማንነቶች በሙሉ የኢየሱስ አገልግሎቶችና ማንነቶች ነበሩ፡፡

ኢየሱስ የሰራው ስራ ሙሉ በመሆኑም ማርያም በነዚህ መስኮች ኢየሱስን የምታግዝበት አሰራርም የለም፣ <u>ማርያም የሰው ልጆችን ከሲኦል ማዳን የምትችል ቢሆን</u>

---

[82] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን/ቀሲስ/ ዘሀገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም**፣ 2ኛ ዕትም፣ ገፅ 83

[83] Ibid, ገፅ 88

[84] መጋቤ ጥበብ ሰለሞን/ቀሲስ/ ዘሀገረ ጊሸን ደብረ ከርቤ ማርያም አምባሰል(2004)፣ **በእንተ ማርያም**፣ 2ኛ ዕትም፣ ገፅ 90

ኖሮ የኢየሱስ መምጣት ባላስፈለገ ነበረ፣ ኢየሱስ የመጣው ማርያም ይህን ስራ መስራት ስለማትችል ነው።።

በርግጥ ትክክለኛዋ ማርያም በልጅዋ ላይ እንደዚህ አይነት ፉክክርና መፈንቅለ ስልጣን እንደማታደርግ ይታወቃል ነገር ግን ይህ የኢየሱስን ታሪክ እየተከታተለ በማርያም የሚሸፍነው አካል እንዲህ እያደረገ ያለው የኢየሱስ አዳኝነት እንዳይታ በማሰብ ነው፣ ይህም ሰዎች ከገነት እንዲባረሩ ምክንያት የሆነውና ዛሬም ወደገነት እንዳይመለሱ የሚፈልገው ዲያብሎስ ነው።።

4.1.2.2. “መላዕክት የሰው ልጆችን ከሲኦል ያድናሉ”

መላዕክት “አማላጅ ናቸው” በማለት ሰዎች በክርስቶስ አማላጅነት እንዳይድኑ የተሰራውን ስራ ከላይ ተመልክተናል፣ ይህ ክርስቶስን በመላዕክት ስም የመጋረድ ስራ በዚህ የሚያበቃ አይደለም፣ ዋናውን ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣበትን ተልዕኮውን እስከመጋረድ ድረስ ይሄዳል፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ የሰው ልጆችን ከሲኦል የማዳን ስራ የሚሰሩት መላዕክት እንደሆኑ ትናገራለች፣በምሳሌ ብንመለከት

> [85] “ሚካኤል ዘወትር በ12(ወር በገባ በ12ኛው ቀን) እልፍ አእላፍ ነፍሳትን ከሲኦል በክንፎቹ ይዞ ይወጣል፣ (ድርሳነ ሚካኤል ገፅ 32-40)፣ ይህ ድርጊት የሚካኤል ብቻ ሳይሆን ሁሉም መላዕክት በሚዘከሩበት ቀናቸው የሚያደርጉት የዘወትር ተግባር ነው።።”

በዚህ ስሌት ከሄድን ሲኦል ባዶ በቀረች ነበረ፣ ይህ የኢየሱስን አዳኝነት ለመጋረድ በመላዕከቱም ስም የተሰራ ድርሰት ነው፣ የድርሰቱ ምንጭም ሰዎች በኢየሱስ አምነው ገነት እንዳይገቡ የሚሰራው ቀድሞም ሰዎች ከገነት እንዲባረሩ ምክንያት የሆነው ዲያብሎስ ነው፣ መላዕክቱ የሰው ልጆችን ከሲኦል የማዳን ስራ መስራት የሚችሉ ቢሆን ኖሮ የኢየሱስ መምጣት ባላስፈለገ ነበረ።።

4.1.2.3. “ቅዱሳን የሰው ልጆችን ከሲኦል ያድናሉ”

ቅዱሳን “አማላጅ ናቸው” በማለት ሰዎች በክርስቶስ አማላጅነት እንዳይድኑ የተሰራውን ስራ ከላይ ተመልክተናል፣ ይህ በቅዱሳን ስም ክርስቶስን የመጋረድ ስራ በዚህ አይቆምም ዋናውን ኢየሱስ ወደ ምድር የወረደበትን ተልዕኮ እንኳን እስከመጋረድ ይሄዳል፣ ከዚህ በባሰ ደግሞ አንዳንድ ስፍራዎች ላይ ቅዱሳኑን የሰው ልጆችን ለማዳን ከኢየሱስ በላይ የሆነ ስራ መስራታቸውን ይነገራል፣ ይህም የኢየሱስን ስራ በማሳነስ ሰዎች የኢየሱስን አዳኝነት እንዳይመለከቱ ለማድረግ ታስቦ የተሰራ ልቦለድ ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

---

[85] መሪጌታ ጽጌ ፅጌ ስጦታውና መሪ ጌታ ሙሴ መንበሩ፣ **አርቶዶክስ መልስ ካላት እኛም ጥያቄ አለን (VCD)**

- "ከኢየሱስ `የላቀ` ስር ነቀል ስራ ሊሰሩ የነበሩ"

[86] "ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ፣ ቅዱስ ሚካኤል ነጥቆ ሄሮድስ ካስፈጃቸው 14 እልፍ ህፃናት ደምሮታል። እስዋንም በክንፉ ተሸክሞ ከጣና ሀይቅ አድርሷታል፣ በዚያም ከመከራዋ ብዛት ከገድሏ ፅናት ሰውነቷ ተበሳስቶ የአሳ መመላለሻ እስኪሆን ድረስ ከባህሩ ጉበታ ወደ ግራና ወደ ቀኝ ሳትል አስራ ሁለት አመት ፀልያለች፣ በመጨረሻም ጌታ ምን አደርግልሽ ዘንድ ትሻለሽ አላት እሷም "... ውሉደ አዳም እንዳይስቱ ዲያብሎስን ማርልኝ አለችው፣ ከሆነልሽ ጠርተሽ አምጪው አላት ... ከዚያም(ከሲኦል) ስትወጣ ነፍሳትን ማርካ ወጥታለች።"

ድርሰቱ በመጀመሪያ ክርስቶስ የተባለውን ለኢየሱስ ብቻ የተሰጠውን ስም በመጋራት "ክርስቶስ ሠምራ" ተብሎ ተጀመረ፣ ቀጥሎ በሐሳብ ደረጃ እንደ ክርስቶስ በማስታረቅ አገልግሎት ተስተካከለች፣ ቀጥሎ እንደ ክርስቶስ ነፍሳትን ከሲኦል ወደ ገነት አስመለጠች፣ በመጨረሻም ኢየሱስ የሰራውን የሰው ልጅና እግዚአብሔርን የማስታረቅ ስራ `አልፋ` "የኃጢያት መሠረቱን፣ የሰው ልጆች አሳሳቹ ዲያብሎስ ምህረትን እንዲያገኝ እግዚአብሔርን ለመነች"።

ይህ ያልተሳካ፣ ሊሳካ የማይችል የራሱ ዓላማ ያለው ልቦለድ ነው፣ ዓላማውም ሰዎች "ኢየሱስ ለሰይጣን መዳን ቢሰራ ኖሮ ስር ነቀል መፍትሄ ይገኛል" ብለው እንዲያስቡ ለማድረግና ኢየሱስ የከፈለውን ዋጋ ለማሳነስ የተሰራ ልቦለድ ነው፣ ነገር ግን የሰው ልጅና የዲያብሎስ ተፈጥሮና ስህተት የተለያየ በመሆኑ በፈጣሪ ፊት ምህረት የሚሰጠውና የማይሰጠው አለ፣ ዋናው ነገር ደግሞ ምህረት ጸጋ እንጂ እንደ መብት የሚታይ ነገር አይደለም፣ በኃጢያት ውስጥ ያለ አካል ምህረትን እንደ መብት አድርጎ ማውራት አይችልም፣ ስለጥፋቱ የሚገባው ሲኦል ነበረ፣ የመሃሪው ርህራሄ በዝቶ እንጂ።

ይህ ሰዎች ያለአግባብ እንዲያስቡ በማድረግ የመጣላቸውን የምህረት ዕድል እንዲያጣጥሉ የሚሰራው የዲያብሎስ ሴራ ነው።

- "ከክርስቶስ በላይ ስለ ኃጢያት ስርየት ዋጋ የከፈሉ"

[87] "አንድ ቀን ጌታችን ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ በአካል በቤተመቅደስ ተገልፆለት፣ ወዳጄ ልጄ ነአኩቶ ለአብ ሆይ ... እኔ ለሰው ልጆች ስል ደሜን ያፈሰስኩት መከራውን የተቀበልኩት አንድ ቀን ነው፣ አንተ ግን አርባ አመት ሙሉ ደምህን፣ እንባህን እያፈሰስክ ..."

---

[86] መ/ር ዐሥራት ደስታ et.al(1998)፣ **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ (የግቢ ጉባዔያት) ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ ገፅ 69

[87] መ/ር ዐሥራት ደስታ et.al(1998)፣ **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ (የግቢጉባዔያት) ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ገፅ 58

- “ከኢየሱስ በላይ የጸሙ”
  ማቴ.4፡2 “(ኢየሱስ) አርባ ቀንና ሌሊት ከጦመ ቦኋላ ተራበ፡፡”
  [88] “አባ ጳንጠሌዎን እህል ውሀ ሳይቀምሱ በጾም በፀሎት በስግደት አርባ አምስት አመት ኖረዋል፡፡”
- “ሐዋርያቱ የተደነቁበት የክርስቶስን ተአምር “የበለጠ” ተአምር”
  ማቴ.21፡19-20 “(ኢየሱስም) በመንገድ አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝበሽ አላት፣ በለሲቱም ያን ጊዜውን ደረቀች፣ ደቀ መዛሙርቱም ይህንን አይተው፣ በለሲቱ ያንጊዜውን እንዴት ደረቀች? ብለው ተደነቁ፡፡”
  [89] “አባ ጳንጠሌዎን ዛፍ ተክለው ዕለቱኑ አሳድገውና አድርቀው ፈልጠውና አክስለው ለማዕጠንት የሚሆን ፍሕም በማፋም በልብሳቸው አፍነው ወስደው ቤተክርስቲያን አጥነዋል፡፡”
- “አንዴ ይቅርና ሦስቴም ሞቶ መነሳት እንደሚቻል”
  መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ከሚታዩ ልዕቀት ያላቸው ስራዎች አንዱ የክርስቶስ ለሰው ልጆች ኃጢያት ሞቶ መነሳት ነው ነገር ግን ይህንን እንዳናደንቅ በቤተክርስቲያኗ “ሦስት ጊዜ ሞቶ የመነሳት” ልቦለድ እንመለከታለን፣
  [90] “ቅዱስ ጊዮርጊስ ሦስት ጊዜ ሞቶ ሦስት ጊዜ ተነስቷል፡፡”
- በደማቸው ይቅርና በቅዘናቸውና በመቃብር ቦታቸው እንኳን ሰውን ከሲኦል ማዳን የሚችሉ “ቅዱሳን”፣
  ለሰው ልጆች ድነት የፈሰሰው የክርስቶስ ደም መተኪያ የሌለው ክቡርና ቅዱስ ደም ነው ይሁን እንጂ ይህንን ደም ለማዋረድ ከታች በ4.3 ክፍል ከገድለ ተክለኃይማኖት መጽሐፍ ላይ በ “Screen shot” እንደቀረበው የተክለኃይማኖት ቅዘን ከኢየሱስ ደም ጋር እንደሚተካከል፣ በተክለኃይማት ቤተክርስቲያን መቀበር ከሲኦል እንደሚያድን ተተርኳል፡፡
- በስማቸው ለትውልድ እንኳን የሚተርፍ የኃጢያት ስርየት የሚደረግባቸው፣
  መጽሐፍ ቅዱሱ በኢየሱስ ስም የኃጢያት ስርየት እንደሚገኝ ይናገራል(ሉቃ.24፡47) ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ቅዱሳንም ከላይ እንደተመለከትነው “ስለሰው ልጆች ኃጢያት ዋጋ ከፍለዋል” ስለሚባል በስማቸው “የኃጢያት ስርየት” እንደሚደረግ፣

[88] ነገረ ቅዱሳን 2፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ መ/ር አሥራት ደስታ et.al , ገፅ 35
[89] ነገረ ቅዱሳን 2፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት(የግቢ ጉባኤያት) ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ መ/ር አሥራት ደስታ et.al , ገፅ 35
[90] አሉላ ጥላሁንና ዲ/ን ያረጋል አበጋዝ(1997)፣ **ነገረ ቅዱሳን-ቮ**፣ ገፅ 80

ስርየቱም ከኢየሱስ በበለጠ ከአማኙ ግለሰብ ባለፈ እስከ ብዙ ትውልድ እንኳን እንደሚዘረጋ ታስተምራለች፣

- [91] "አምላክ ፍቅርተ ክርስቶስ ብሎ ባንቺ ስም የተማፀነ ... እስከ አስራ አራት ትውልድ ይማርልሻል፡፡"
- [92] "አቡነ እስትንፋስ ክርስቶስ ከፈጣሪያቸው እስከ አስራ ሰባት ትውልድ ድረስ ዓስራተ ምህረት(የምህረት ቃል ኪዳን) ተቀብለው..."
- [93] "... ስሟን(ክርስቶስ ሠምራ) የጠራውን እስከ አስር ትውልድ እንዲምርላት ተስፋዋን ነግሯት ..."

ቅዱሳኑ የተቀደሱት በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው ነው፣ በዚህም የኢየሱስ ተፎካካሪ አይደሉም፣ ኢየሱስም ቅዱሳኑን "ከኔ በላይ ተአምራትን ታደርጋላችሁ" አለ እንጂ "ከኔ በላይ ትሆናላችሁ" አላለም ነገር ግን ስሙን ከክርስቶስ ጋር አመሳስሎ በኢየሱስ ስራ ፉክክር ውስጥ የገባው ሰዎች በክርስቶስ አምነው እንዳይድኑ የሚሰራው ተፎካካሪ እሱም ዲያብሎስ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የቀረቡት ልቦለዶች የተዘጋጁለት የራሳቸው ዓላማ አላቸው፣ ዓላማቸውም የኢየሱስን አዳኝነት *መጋረድ* ነው፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን *መጽሐፍት መመርያ* ያደረጉች ቤተክርስቲያንና በነዚህ አስተምህሮች የሚያምኑት ምዕመናኖቿ ከባድ አደጋ ውስጥ እንዳሉ *መጽሐፍ* ቅዱሱ ይነግረናል፡፡

> ዕብ.10፡28-29 "የሙሴን ህግ የናቀ ሰው ሁለት ወይንም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርህራሄ ይሞታል፡፡ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ እርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም *መንፈስ* ያከፋፋ፣ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?"

በአጠቃላይ ስንመለከት *ማርያም*፣ ቅዱሳን፣ *መላዕክትና* ክርስቶስ የተለያየ አፈጣጠር፣ ችሎታ፣ ጸጋ ... አላቸው፣ በዚህም አራቱም በእግዚአብሔር *መንግሥት* ውስጥ እግዚአብሔርን የሚያገለግሉት እንደየልዩነታቶቻቸው በተሰጣቸው የስራ ድርሻና ኃላፊነት ነው፡፡ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ እነዚህን አራቱንም አካላት እኩል በማድረግ፣ ማርያም፣ *መላዕክታትንና* ቅዱሳኑን ከአቅማቸው በላይ በክርስቶስ ወንበር ላይ በማስቀመጥ፣ ከዚህም አልፎ ክርስቶስን "በማስበለጥ"፣ ክርስቶስ የሰራው የሰው ልጆች የማዳን ስራ በሰፊው የመጋረድ ስራዎች እየተሰሩ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

---

[91] *መ/ር ዐሥራት ደስታ* et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ት/ም/ተቋ/(የግቢ ጉባዔያት) ተማሪዎች *መማሪያ መጽሐፍ*፣ *ገፅ* 80

[92] Ibid, *ገፅ* 96

[93] Ibid, *ገፅ* 69

መጽሐፍ ቅዱሱ ግን እነዚህ አራቱ አካላት ከኢየሱስ ጋር እኩል መሆን ይቅርና "መዳን በሌላ በማንም የለም"(ሐስ.4፡12) በማለት በኢየሱስ ላይ ሌላ ተደራቢ አካል መያዝ እንደማይቻል ይናገራል፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተሰራ ባለው ሜራ ላይ በመንቃት፣ በነሱ ስም በክርስቶስ ላይ የተጋረደውን መጋረጃ በማውረድ፣ እነሱንም ወደየስፍራቸው በመመለስ፣ በነሱ ስም የሚነግደውን ዲያብሎስን ባዶ በማስቀረት በኢየሱስ በኩል የመጣውን ድነት ሊጠቀምበት ይገባዋል፡፡

4.1.3. <u>መመለክ ያለበት ማርያም፣ ቅዱሳን፣ መላዕክት፣ እግዚአብሔር፣ ወይስ አራቱም?</u>

ከላይ እንደተመለከትነው በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የኢየሱስ አማላጅነት ቀጥሎም ጠቅላላ የኢየሱስ አዳኝነት ተሸፍኗል፣ ይህ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ቅዱሱን መጋፋት በዚህ አያቆምም ወደ እግዚአብሔር የመመለክ ክልልም ይዘልቃል፡፡ በቤተክርስቲያኗ ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን እንደ እግዚአብሔር ሙሉ የአምልኮ ስነ ስርዓቶች ይፈፀምላቸዋል፣ ስግደት፣ ዝማሬ፣ መስዋዕት … ይቀርብላቸዋል፣ የሚገርመው ደግሞ እነዚህ አካላት የሚመለኩት እግዚአብሔር እንዲመለክበት ለራሱ የለያቸውን መመለኪያ ነገሮቹን ለነሱም በማካፈል ነው፣ ይህም በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ቤተ ክርስቲያን በመሰየም፣ ታቦት/ፅላት በመሰየም፣ በወር ውስጥ ሰንበት የሆነ ቀን በመስጠት … ነው፡፡

ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን በዚህ ክልል ውስጥ እንዲገቡ የተደረገው በተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም ለማርያም የተሰጡት ምክንያቶች ግን ሰፋ ያሉ በመሆናቸው ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆኑትን ምክንያቶች በቅድሚያ በመመልከት በመቀጠል ደግሞ እንዴት ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን እየተመለኩ እንደሚገኙ እንመለከታለን፡፡

4.1.3.1. <u>ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆኑ ምክንያቶች</u>

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለማርያም የሚሰጠው የልዕለ ስብዕናነት አስተምህሮ ማርያምን የእግዚአብሔር የ"መመለክ" ግዛት ውስጥ አስገብቷታል፣ ለዚህ አምልኮተ ማርያም መነሻ የሆኑት አስተምህሮዎችም "ማርያም እመ አምላክ፣ እግዝእትነ፣ እናታችን/እመቤታችን ናት፣ ዘላለማዊ ድንግል ናት፣ "ጽዮን" ተብሎ በትንቢት ስለሷ ተነግሮ ነበረ" የመሳሰሉት ሲሆኑ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡፡

4.1.3.1.1. <u>"እመ አምላክ፣ እግዝእትነ፣ እናታችን/ እመቤታችን"</u>

በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለማርያም በሚሰጠው ልዕለ ስብዕናነት ምክንያት ማርያም "እመ አምላክ" ትባላለች፣ ከእግዚአብሔር አቻ ተደርጋ በግዕዙ "እግዝእትነ" ትባላለች፣ እግዚአብሔር "አባታችን" እንደሚባለው ማርያምም "እናታችን/እመቤታችን" ትባላለች፣ ኢየሱስ ስለ ፀሎት ካስተማረው "የአባታችን" ፀሎት(ማቴ.6፡9-13) ጋርም ለማርያም "እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ…"

የሚል ፀሎት ይደረግላታል፣ በዚህም ማርያም ከእግዚአብሔር አቻ ስትደረግ እንመለከታለን ይሁን እንጂ እነዚህ በሙሉ ለ"አምልኮተ ማርያም" የተሰሩ ልቦለዶች እንጂ እውነታዎች አይደሉም፡፡

"እመ አምላክ" ከሚለው ብንነሳ፣ ኢየሱስ የአምላክና የሰው ተዋህዶ በመሆኑ የእግዚአብሔርም የሰውም ልጅ ነው፣ የእግዚአብሔር ልጅ የተባለው እራሱ እግዚአብሔር ሆኖ ራሱን ዝቅ አድርጎ በመምጣቱ ምክንያት ሲሆን የሰው ልጅ የተባለው ደግሞ የሰውን ስጋ ለብሶ በማርያም በኩል በመወለዱ ምክንያት ነው፡፡ ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ፣ በኢየሱስ ተዋህዶ ማንነት ውስጥ ያለውን አምላክነትን ማርያም የወለደችው በማድረግ፣ ማርያምን "የአምላክ እናት/እመ አምላክ" በማለት ለማርያም ልዕለ ስብዕናነትን ሲሰጣት ይታያል ነገር ግን ኢየሱስ ከማርያም ስጋ ሳይዋሃድ በፊት በአምላክነቱ ነበረ፣

> ዕብ.7፡3 "<u>አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም</u>፣ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍፃሜ የለውም፣ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ላህን ሆኖ ይኖራል፡፡"

ስለዚህ ማርያም በኢየሱስ ተዋህዶነት ውስጥ ያለውን አምላካዊ ማንነት አልወለደችም፣ እናትነትዋ በተዋህደው ማንነት ውስጥ ላለው ስጋ ሰውነቱ ብቻ ነው፣ በዚህም ማርያምን "የአምላክ እናት/እመ አምላክ" የሚለው ጋር ማድረሱ ስህተት ነው፣ አምላክ አይወለድም፣ አልተወለደምም፡፡

ሌላው "እግዚአብሔር" እንደሚባለው ማርያም "እግዝእትነ" የተባለችበት፣ እግዚአብሔር "አባታችን" ሲባል ማርያም "እናታችን/እመቤታችን" የተባለችበት አሰራር ማርያምን ከእግዚአብሔር ጋር ለማተካከል የተሰሩት ባዶ ስራዎች እንጂ በምንም ሁኔታ ማርያም ከእግዚአብሔር ጋር ተስተካክላ አይደለም፣ ማርያም ፈጣሪ አይደለችም፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ "እናታችን፣ እመቤታችን ..." እያለ የሚጠራው በብሉይ ትርጉም እስራኤልን ሲሆን በአዲሱ ኪዳን ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንጂ ማርያምን አይደለም፣

- 2ዮሐ.1፡1-2 "በእኛ ስለሚኖርና ከእኛ ጋር ለዘላለም ስለሚሆን እውነት፣ እኔ ሽማግሌው በእውነት ለምወዳቸውና እኔ ብቻ ሳልሆን እውነት የሚያውቁ ሁሉ ደግሞ ለሚወዷቸው ለተመረጠች <u>እመቤትና</u> ለልጆችዋ፡፡"
- 2ዮሐ.1፡5 "አሁንም፣ <u>እመቤት</u> ሆይ፣ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እለምንሻለሁ፣ ይህቺ ከመጀመርያ በእኛ ዘንድ የነበረች ትእዛዝ ናት እንጂ አዲስ ትእዛዝን እንደምፅፍልሽ አይደለም፡፡"
- ገላ.4፡26 "ላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን በነፃነት የምትኖር ናት እርስዋም <u>እናታችን</u> ናት፡፡"

በአጠቃላይም ማርያምን ከሰው ማንነት አሳልፎ ከእግዚአብሔር አስተካክሎ "እመ አምላክ፣ እግዝእትነ፣ እናታችን/እመቤታችን ..." የተባለችበት ሁኔታ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ኢየሱስ ሰዎች ማርያምን ከስጋዊ እናትነት አስበልጠው ልዕለ ስብዕና ማንነት በመስጠት ሰዎች እንዳያመልኳት በሚል በአስተምሮዎቹ ውስጥ ብዙ ጥንቃቄ ሲያደርግ ነበረ፣ ይህንንም ከማርያም ጋር በነበሩት ንግግሮቹ፣ ግንኙነቶቹ እንዲሁም ሰዎች ስለ እናቱ የሚሰጡትን ልዕለ ስብዕና አስተያየቶች ላይ በሰጣቸው ትምህርቶች ውስጥ መመልከት ይቻላል፣

- ዮሐ.2፡4 "ኢየሱስም አንቺ ሴት፣ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ ... አላት፡፡"
- ሉቃ.2፡41-50 ላይ ማርያም ዮሴፍና ኢየሱስ የፋሲካን በዓል ለማክበር ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው በሚመለሱበት ጊዜ፣ የአንድ ቀን መንገድ ሙሉ ሲጓዙ ኢየሱስ ከነሱ መቅረቱን አላስተዋሉም ነበረ፣ ማርያምም ኢየሱስን ዘንግታዋለች እሱም ስጋዊ ወላጆቹን ትቶ ወደ መንፈሳዊ ነገሩ አዘንብሎ ነበረ፡፡
- ሉቃ.11፡27-28 "... ከህዝቡ አንዲት ሴት ድምፅዋን ከፍ አድርጋ፣ የተሸከመችህ ማህፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁአን ናቸው አለችው፣ <u>አዎን ብፁአንስ</u> የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት ናቸው አለ፡፡"
- ማር.3፡31-35 "እናቱና ወንድሞቹ መጡ በውጪም ቆመው ወደ እርሱ ልከው አስጠሩት፡፡ ብዙ ሰዎችም በዙሪያው ተቀምጠው ነበረና እነሆ እናትህና ወንድሞች በውጪ ቆመው ይጠብቁሃል አሉት፡፡ መልሶም <u>እናቴ ማን ናት</u>? <u>ወንድሞቼስ እነማን ናቸው</u>? አላቸው፣ እነሆ እናትና ወንድሞቼም፡፡ <u>የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ ነው እህቴም እናቴም አለ፡፡</u>"

በዚህም ኢየሱስ ሰዎች ለማርያም ልዕለ ስብዕናነት በመስጠት "አምልኮተ ማርያም" ውስጥ እንዳይገቡ ጥንቃቄ ሲያደርግ እንደነበረ እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆነው "እመ አምላክ፣ እግእነትነ፣ እናታችን/ እመቢታችን" የሚባሉት አስተምህሮዎች ስህተት መሆናቸውንና በዚህ አስተምህሮ ላይ የተመሠረተው የአምልኮተ ማርያም አስተምህሮም ስህተት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

4.1.3.1.2. <u>በትንቢት "ጽዮን" ተብሎ ስለሰዋ መነገሩ</u>

የማርያምን ልዕለ ስብዕናነትን ለማሳየት የሚቀርበው ሌላው ሐሳብ "መጽሐፍ ቅዱሱ "ጽዮን" የሚለው ማርያምን ነው" የሚለው ነው፣ ለዚህም ማሳያነት የኢሳያስ ትንቢት ላይ ያለው ቃል በብዛት ሲጠቀስ ይታያል፡-

> ኢሳ.60፡12-14 "ለአንቺ የማይገዛ ህዝብና መንግሥት ይጠፋል ... የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ"

ይህ ቃል ከ"ማርያም ስእል" አጠገብ ተፅፎ ብዙ ጊዜ ተመልክተናል ነገር ግን ይህ ኢሳ.60፡12-14 ሙሉው ቃል አይፃፍም እንጂ ሙሉው ቢፃፍ ኖሮ በሰከንድ ውስጥ "ነገሩ ሌላ ነው፣ ለምን ቃሉን በመቁረጥ በስእል በማስደገፍ ያጭበረብሩናል" ያስብላል፣ እስቲ ቃሉን ትንሽ ሰፋ አድርገን እንመልከት፣

> ኢሳ.60፡12-14 "ለአንቺ የማይገዛ ህዝብና *መንግሥት* ይጠፋል፣ እነዚያ አህዛብም ፈፅመው ይጠፋሉ፡፡ የመቅደሴን ስፍራ ያስጌጡ ዘንድ የሊባኖስ ክብር፣ ጥዱና አስታው ባርሰነቱም፣ ወደ አንቺ ይመጣሉ፣ የእግሬንም ስፍራ አከብራለሁ፡፡ አስጨናቂዎቸሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ፣ የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ፤ የእግዚአብሔር ከተማ፣ የእስራኤል ቅዱስ የሆንሽ ጽዮን ይሉሻል፡፡ ከሰውም ማንም እስከ ማያልፍብሽ ድረስ የተተውሽና የተጠላሽ ነበርሽ፤ ነገር ግን የዘላለም ትምክህትና **የልጅ ልጅ** ደስታ አደርግሻለሁ ... ከዚያ በኋላ በምርድሽ ውስጥ ግፍ፣ በዳርቻሽም ውስጥ ጉስቁልናና ቅጥቃጤ አይሰማም፤ ቅጥርሽን *መዳን* በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያለሽ፡፡"

ይህንን ቃል ስንመለከት "ጽዮን" ተብሎ የተነገረው ስለ ማርያም ሳይሆን "ጽዮን" ስለተባለችው ከተማ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ሌሎቹንም ቤተክርስቲያኗ "ጽዮን ማርያም ናት" ለማለት የምታቀርባቸውን ማስረጃዎችንም ስንመለከት እንደዚሁ "ጽዮን" የምትባለው ከላይ እንደተመለከትነው ህዝቦች የሚኖሩበት የከተማ ስም ሆኖ እናገኘዋለን፡-

- መዝ.86(87)፡1-7 – እዚህ ጋር ቃሉ ግልፅ አድርጎ የሚናገረው ሀገር ስለሆነችው ጽዮን ነው፣ ይህቺ ሀገርም የተመሠረተችው በተራሮች ላይ ስለሆነች "መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው" ይላል፣ ሀገሪቱንም ያነፃፀረው ከረዓብ፣ ባቢሎን፣ ፍልስጥኤም፣ ጢሮስና ኢትዮጵያ ሀገሮችና ህዝቦች ጋር ነው፣ ከተማ በመሆኗም "በውስጥዋ ለተወለዱ አለቆችዋ" ይላል፡፡
- መዝ.131(132)፡13-18 - ሙሉ ምዕራፉን ስናነብ ጽዮን ተብላ የተገለፀችው በቀጥታ ዳዊት የመሠረታት ጽዮን ከተማ ናት፣ ይህም ዳዊት በከተማይቱ ለእግዚአብሔር ቤተመቅደስ፣ ለታቦቱም ማረፊያ እስከሚሰራባት ያለውን ጉጉት የተናገረበት መዝሙር ነው፣ ማርያም ላለመሆንዋም "አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ፣ ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ፣ ካህናቶችዋንም ደህንነት አለብሳቸዋለሁ፣ ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል" ይላል፡፡
- መዝ.44(45)፡9-17 - ሙሉውን ምዕራፍ ስናነበው ምዕራፉ ድንግል ስለሆነች ሴትና ስለ ታጨችለት ንጉሥ የሚናገር ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፣ ይህንን በጥበብ የተነገረን ቃል በቀጥታ በመተርጎም "ቃሉ የሚናገረው ስለማርያምና ስለ እግዚአብሔር ነው" ማለቱ መቅሰፍት ነው፣ "ስለ ማርያምና ኢየሱስ ነው" ማለቱም እንዲሁ ሌላ መቅሰፍት ነው፣ በማያውቁት ገብቶ ከመቀሰፍ "አልገባኝም" ብሎ መተዉ ብልህነት ነው፡፡

ነገር ግን ይህንን የታጨችው ሴትና የንጉሡን ማንነት ለመረዳት እስቲ በተመሳሳይ መንፈስ የተፃፉ ሌሎች ቃላትን እንመልከት፣

- ኤፌ.5፡25-26 "ባሎች ሆይ፣ ክርስቶስ ደግሞ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳት ሚስቶቻችሁን ውደዱ ..."
- ራዕ.21፡2 "ቅድስቲቱም ከተማ ኢየሩሳሌም ለባሏ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ፡፡"
- ራዕ.21፡9 "... ከሰባቱ መላዕክት አንዱ መጥቶ፡- ወደዚህ ና የበጉን ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሀለሁ ብሎ ተናገረኝ፡፡"

በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ በሚስትነት እንዲሁም በሙሽራነት በአጠቃላይ በሴትነት የሚመስላት በክርስቶስ የተወደደችውና ክርስቶስ ለሷ ብሎም ደሙን ያፈሰሰላት "ጽዮን" ቤተክርስቲያን/እስራኤል/አዲሲቷን ኢየሩሳሌም እንጂ ማርያምን አለመሆኑን በግልፅ እንመለከታለን፣ ይህም ከላይ ከተለመከትነው "እናታችን፣ እመቤታችን ..." የመጽሐፍ ቅዱሱ አገላለፆች ጋር ተመሳሳይ የሆነ አገላለፅ ነው፡፡

"ጽዮን የማርያም ናት" ለሚሉ ሰዎች እነዚህን ለምድራዊዋ ጽዮን ከተማ የተነገሩ ቃላትን እንዴት እንደሚፈቱት ቢነግሩን መልካም ነበረ፣

- ኢሳ.52፡1 "ጽዮን ሆይ ... ያልተገረዘና ርኩስ ከእንግዲህ ወዲህ አይገባብሽም..."
- ሰቆ.ኤር.4፡22 "... ጽዮን ሆይ የበደልሽ ቅጣት ተፈፀመ፣ ከእንግዲህ ወዲህ አያስማርክሽም..."
- ሰቆ.ኤር.4፡11 "... እግዚአብሔር መአቱን ፈፅሞአል፣ ፅኑ ቁጣውን አፍስሷል፣ እሳትን በጽዮን ውስጥ አቃጠለ፣ መሠረትዋንም በላች፡፡"

እነዚህን ቃላት ስንመለከት ጽዮንና ማርያም ፈፅሞ የማይገናኙ ታሪኮች መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡ በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ "ጽዮን የሚለው ማርያምን ነው" በማለት አምልኮተ ማርያም ውስጥ የተገባበት አሰራር ስህተት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

4.1.3.1.3. "ዘላለማዊ ድንግልና"

በቤተክርስቲያኗ ሌላው ለአምልኮተ ማርያም ምክንያት የሆነው [94] "ማርያም ዘላለማዊ ድንግል ናት" በማለት ለማርያም ልዕለ ሰብዕናነት የተሰጠበት አስተምህሮ ነው፣ ለዚህ የማርያም "ዘላለማዊ ድንግልና" በዋናነት የሚቀርቡት ማስረጃዎች በመኃ.4፡12 እና በሕዝ.44፡1-3 የተነገሩት ምሳሌያዊ አነጋገሮች ናቸው ነገር ግን እነዚህ ምሳሌዎች

[94] **ቅድስት ድንግል ማርያም በኦርቶዶክሳውያን አስተምህሮ**፣ 2ኛ እትም፣ አዘጋጅ ታድሮስ ያዕቆብ ማላቲ፣ ትርጉም በኤራቅሲስ ዘተዋህዶ፣ አሳታሚና አከፋፋይ፣ በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ /በሰ/ት/ቤቶች ማደራጃ መምሪያ፣ ማኅበረ ቅዱሳን፣ 2008 ዓ.ም፣ ገፅ.15-19

በማስተዋል ከተመለከትናቸው እነዚህ ቃላት የተነገሩት ለሌላ አካላት እንጂ ለማርያም አይደሉም፣

መኃ.4፡12 “እህቴ ሙሽራ የተቆለፈ ገነት፣ የተዘጋ ምንጭ የታተመ ፈሳሽ ናት፡፡”

በመኃልየ መህልይ መጽሐፍ ላይ በሴት ጾታ የተገለፀችውን ማንነት ማርያም መሆን አትችልም ምክንያቱም ማርያም ጥቁር አይደለችም (*መኃ.1፡5*)፣ እረኛ አልነበረችም (*መኃ.1፡8*)፣ አልተደበደበችም (*መኃ.5፡7*)፣ አልቆሰለችም(*መኃ.5፡7*)፣ አልተዘረፈችምም (*መኃ.5፡7*) … ወዘተ፡፡ በዚህም በሴት ጾታ ስለተገለፀ ብቻ “የማርያም ታሪክ” ነው ማለቱ ስህተት ነው፡፡

> *ሕዝ.44፡1-3* “ወደ ምስራቅም ወደሚመለከተው በስተውጭ ወዳለው ወደ መቅደሱ በር አመጣኝ ተዘግቶም ነበረ፡፡ እግዚአብሔርም ይህ በር ተዘግቶ ይኖራል እንጂ አይከፈትም፣ ሰውም አይገባበትም የእስራኤል አምላክ ገብቶታልና ተዘግቶ ይኖራል(አለ)፡፡”

ይህ ቃል የሚናገረው በቤተ መቅደስ ውስጥ ስለነበረው ጉዞ እንጂ በማርያም ሆድ ውስጥ ስለተደረገ ምናባዊ ጉዞ አይደለም፣ እንደዚያ ከተባለ ደግሞ ቁጥር 4 ላይ የተገለፀው “የሰሜኑ በር” ምንዋ ሊሆን ነው? የዚሁ ተመሳሳይ ቃል ሕዝ.11፡1 “መንፈስ አነሳኝ ወደ ፀሐይ መውጫ ወደሚመለከተው ወደ እግዚአብሔር ቤትም ወደ ምስራቁ በር አመጣኝ፡፡ እነሆም በበሩ መግቢያ ሀያ አምስት ሰዎች ነበሩ፣ በመካከላቸውም የህዝቡን አለቆች የዓዙርን ልጅ ያዕዛንያን የበነያስ ልጅ ፈላጥያን አየሁ፡፡” የሚለውንስ ቃል ምን ልንለው ነው?

በዚህም እነዚህ ቃላት ስለ ማርያምን የተነገሩ ባለመሆናቸው፣ ለማርያም ዘላለማዊ ድንግልና በድጋፍነት ማቅረብ አይቻልም፡፡

ስለ ማርያም ድንግልና ስንመለከት፣ ማርያም ኢየሱስን የፀነሰችውና የወለደችው በድንግልናዋ ነው ነገር ግን ከዚህ እውነታ በመነሳት ድንግልናዋን ዘላለማዊ ማድረጉ ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው፡፡

ከመነሻው “ዘላለማዊ ድንግልና” የሚለው ሐሳብ ውስጥ “ዘላለማዊነት” የሚያያዘው ከበስባሽ ስጋ ጋር ሳይሆን ዘላለማዊነት ካለው መንፈሳዊው አካል ጋር ነው፣ በዚህም የማርያምን ምድራዊውን ስጋ ወስዶ ዘላለማዊ ማድረግ የመጀመሪያው ስህተት ነው፡፡ ከሞት ወይ ከመነጠቅ በኋላ ባለው መንፈሳዊ ህይወት ደግሞ ሰው የሚለብሰው ዘላለማዊውን መንፈሳዊ አካል ነው(*1ቆሮ.15፡40-50*)፣ ይህ አካል ደግሞ እንደ መላዕክቱ ጾታ የለውም(*ማቴ.22፡30*)፣ በዚህም ማርያም የነበራትን ስጋዊ ድንግልና ወደ መንፈሳዊው ዓለም ወስዶ ዘላለማዊ የሚደረግበት አሰራር የለም፡፡

በመቀጠል ማርያም ኢየሱስን በድንግልና አርግዛው በድንግልና ብትወልደውም የማርያም ድንግልና እስከመች እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱሱ በግልፅ ይነግረናል፡፡ ከመጀመርያ ታሪኩ ብንነሳ፣ ማርያም በድንግልናዋ ለዮሴፍ ለሚስትነት የታጨችበት ጊዜ፣ ኢየሱስ ሲጋ ለብሶ የሚወለድበት ጊዜ ነበረ፣ እግዚአብሔርም ማርያምን ለዚህ አገልግሎት ከሴቶች ሁሉ መርጧት ስለነበረ፣ በመንፈሳዊ አሰራር ኢየሱስ በማርያም ማህፀን ውስጥ እንዲረገዝ ተደረገ፡፡

ነገር ግን ማርያም ለዚህ አገልግሎት መታጨቷን ያልተረዳው ዮሴፍ፣ ማርያም እጮኛው ሆና እሱ ሳይገናኛት ስላረገዘች፣ ካሰበው ትዳር በስውር ሊተዋት አሰበ ነገር ግን እግዚአብሔር ዓለም ለማዳን በያዘው እቅድ ምክንያት የማርያምና የዮሴፍ ትዳር መበጥበጥ ስላልነበረበት መልአኩን ልኮ እውነታውን ለዮሴፍ በማስረዳት ዮሴፍ የማርያምን እጮኝነት እንዳይተው ተናገረው፡-

> ማቴ.1፡20-24 “የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፣ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ከመውሰድ አትፍራ፣ አለው … ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፣ እጮኛውንም ወሰደ፡፡”

አንዳንዶች “የዮሴፍን እጮኝነት በጠባቂነት እንጂ እኛ በምናስበው በትዳር መንገድ አይደለም” ቢሉም የዮሴፍ እጮኝነት ግን በትዳር እንጂ በሌላ መንገድ ባለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሱ የኢየሱስን የዘር ሐረግ የሚቆጥረው በአብርሃም - ዳዊት - ዮሴፍ የዘር ሐረግ በኩል ነው፣

- ማቴ.1፡1-16 “የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ መጽሐፍ፣ አብርሃም ይስሐቅን ወለደ … ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን ዕጮኛ ዮሴፍን ወለደ፡፡
- ዮሐ.1፡46 “ፊሊጶስ ናትኤልን አግኝቶ፡፡ ሙሴ በሕግ ነብያትም ስለ እርሱ የፃፉትን <u>የዮሴፍ ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስ</u> አግኝተነዋል አለው፡፡”
- ዮሐ.6፡42 “አባቱና እናቱ የምናውቃቸው ይህ <u>የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ</u> አይደለም?

በዚህም ኢየሱስ የተፀነሰው በመንፈሳዊው አሰራር ቢሆንም ዮሴፍ በኢየሱስ አባትነት መጠራቱ የዮሴፍና የማርያም ግንኙነት የትዳር ግንኙነት መሆኑን ያሳያል፡፡

አንዳንዶች ደግሞ “ዮሐንስ ማርያምን ወሰዳት” (ዮሐ.19፡27) የሚለውን መሠረት በማድረግ “ማርያም ኢየሱስን በድንግልናዋ ከወለደችው በኋላ ከሐዋርያቱ ጋር ወደ አገልግሎት ሄደች እንጂ ወደ ዮሴፍ ትዳር አልሄደችም” ቢሉም ዮሐንስ ማርያምን የወሰዳት ከክርስቶስ ሞት በኋላና ማርያምም ከ48 አመት በላይ ከሆናት በኋላ ነው ስለዚህ እነዚህ ሁለቱ ታሪኮች የማይገናኙ ታሪኮች ናቸው፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ ግን የማርያም ድንግልና እስከመቼ እንደቆየ በግልፅ ይነግረናል፣

> ማቴ.1፡25 “(ዮሴፍም)የበኩር ልጅዋን <u>እስከትወልድ ድረስ</u> አላወቃትም፡፡”

ይህም ቃል ክርስቶስ እስኪወለድ ድረስ ዮሴፍ ከማርምያም ጋር እንዳልተኛ ያሳየናል ነገር ግን ከኢየሱስ መወለድ በኋላ ማርያምና ዮሴፍ በትዳር ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምዖንና ይሁዳ የሚባሉ ወንዶች ልጆችና ስማቸው ያልተነገሩ ሴቶች ልጆች ወልደው አብረው በትዳር ሲኖሩ እንደነበረ መጽሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል፡፡

- ማቴ.13፡55 “ይህ የፀራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ <u>ያዕቆብና ዮሳ፣ ስምኦንና ይሁዳም</u> አይደሉምን? <u>እህቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን?</u>”
- ማር.3፡31-35 “እናቱና ወንድሞቹ መጡ በውጪም ቆመው ወደ እርሱ ልከው አስጠሩት፡፡ ብዙ ሰዎችም በዙሪያው ተቀምጠው ነበረና እነሆ እናትህና ወንድሞች በውጪ ቆመው ይጠብቁሃል አሉት፡፡ መልሶም እናቴ ማን ናት፣ ወንድሞቼስ እነማን ናቸው አላቸው፣ እነሆ እናትና ወንድሞቼም፡፡ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ወንድሜ ነው እህቴም እናቴም አለ፡፡”

እዚህ ጋር ኢየሱስ ያነፃፀረው ስጋዊ ቤተሰቡንና መንፈሳዊ ቤተሰቡን ነው፡፡

በዚህም ከላይ እንደተጠቀሰው ማርያም ከኢየሱስ ውልደት በኋላ ለዮሴፍ ያዕቆብ፣ ዮሳ፣ ስምኦንና ይሁዳ የሚባሉ ወንዶች ልጆችንና በእስራኤል ባህል ሴቶች ተፅዕኖ ስለሚደረግባቸው ስማቸው ያልተገለፀ ሴቶች ልጆችን እንደ ወለደችለት እንመለከታለን፡፡ በዚህም ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆነው የ“ዘላለማዊ ድንግልና” ሐሳብ ስህተት እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ለአምልኮተ ማርያም መነሻ የሆኑት “እመ አምላክ፣ እግዝእትነ፣ እናታችን/እመቤታችን፣ ጽዮን፣ ዘላለማዊ ድንግል” አስተምህሮዎች ስህተት እንደሆኑና በዚህም ማርያምን እንደ እግዚአብሔር ማምለክ የጣኦት አምልኮ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

4.1.3.2. <u>በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ከእግዚአብሔር አምልኮ የተካከለ ሙሉ አምልኮ</u>

“አምልኮ” ማለት ስግደት፣ ፀሎት፣ ምስጋና፣ ዝማሬ፣ ውዳሴ እና መሰል መንፈሳዊ ድርጊቶች ናቸው፣ በቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን እንደ እግዚአብሔር እየተመለኩ ስለሆነ እነዚህ የአምልኮ ድርጊቶች በነሱ ስምም እየተደረገ ይገኛል፣ የሚገርመው ደግሞ አምልኮ ማድረግ ብቻ ሳይሆን አምልኮው የሚደረገው የእግዚአብሔር መመለኪያ ብቻ የነበሩት ቤተመቅደሱን/ቤተክርስቲያኑን፣ ታቦቱን፣ ሰንበታቱን … ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንም በማካፈል ነው፣ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፣

4.1.3.2.1. በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የሚደረግ ስግደት

ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ስግደት እየተደረገ ይገኛል፣ ይህ ድርጊትም "ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ብቻ ስገድ" ከሚለው ቃል ጋር እንዳይጋጭም ቤተክርስቲያኗ ስግደትን በሁለት በመክፈል "ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የሚደርገውን ስግደት "የጸጋ ስግደት" ስትል ለእግዚአብሔር የሚደርገውን ደግሞ "የባህሪ ስግደት" ትላለች፡፡

ነገር ግን በሁለቱ ስግደቶች መካከል የተግባርና የይዘት ልዩነት አለመኖሩን ስንመለከት "ስግደት በሁለት ይከፈላል" የሚለው አባባል የይምሰል አባባል እንጂ "ስግደት" ስግደት መሆኑን ነው የምንመለከተው፡፡

በቤተክርስቲያኗ ለመላዕክትና ለቅዱሳን ለሚደረገው ስግደት ድጋፍ የተወሰኑ <u>የብሉይ ኪዳን</u> ጥቅሶች ቢቀርቡም(ከታች በዝርዝር እንመለከታለን)፣ ለማርያም ለሚደረገው ስግደት ግን ምንም መነሻ እየቀረበ አይደለም፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ለመላዕክትና ለቅዱሳን የተደረገው አይነት ስግደት እንኳን ለማርያም ሲደረግላት አንመለከትም፣ የሰብአ ሰገል ሰዎች ማርያም ኢየሱስ አጠገብ እያለች እንኳን ለይተው የሰገዱት ስግደት ለሚገባው ለኢየሱስ ብቻ ነበረ(ማቴ.2፡1-11)፣ እነዚህ እውነታዎችም የሚያሳዩት ስግደት ለማርያም የማይደረግ መሆኑን ነው፡፡

ለቅዱሳንና ለመላዕክት የሚደረገውን ስግደት አስመልክቶ ቤተክርስቲያኗ <u>ከብሉይ ኪዳን</u> ጥቅሶችን ስታቀርብ ይታያል ነገር ግን እነዚህን ጥቅሶች አስተውለን ስንመለከት "ስግደት" የተባለው የቀረበበት አውድ <u>በመንፈስ የተደረገ የአምልኮ</u> ስግደት ሳይሆን <u>ፊት ለፊት ለተመለከቱት</u> ቅዱስ/መልአክ የቀረበ <u>የአክብሮት ሥላምታ</u> ነው፣ ቀጥሎ በስፋት ቀርቧል፡፡

4.1.3.2.1.1. በቅዱሳን ስም የሚደረግ ስግደት

ቤተክርስቲያኗ ለቅዱሳን ስግደት መደረግ እንዳለበት ትናገራለች፣ ለዚህም በማስረጃነት የምታቀርበው ሰዎች በብሉይ ኪዳን ዘመን ለቅዱሳን ያደረጉትን ስግደት ነው (ዘፍ.23፡7, ዘፍ.33፡3, ዘጸ.18፡7, ዳን.2፡46, ነሳሙ.20፡41, ነሳሙ.25፡23 ...)፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቤተክርስቲያኗ "ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ"(ዘጸ.20፡4-5) የሚለውን በመመልከት ስግደትን [95] "የባህሪ ስግደትና የጸጋ ስግደት" በማለት በሁለት በመክፈል ለእግዚአብሔር የሚደረገውን ስግደት "የባህሪ ስግደት" ስትል ለቅዱሳን የሚደረገውን ስግደት ደግሞ "የጸጋ ስግደት" ትላለች፡፡ ለእግዚአብሔር የሚደረገው ስግደት

[95]ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣ **ነገረ ቅዱሳን - ፩**፣ በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ/ በሰንበት ተ/ቤ/ማ/መ ማ/ቅ ት/ሐ/አገ/ዋና ክፍል፣ ገፅ.67

ሁሉንም ስለሚያግባባ ለቅዱሳን ይደረጋል ስለሚባለው "የጸጋ ስግደት" ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ከመነሻ "የጸጋ ስግደት" የሚለው ስያሜ የተሳሳተ ስያሜ ነው፣ ሰው ለቅዱሳኑ የሚያደርገውን "ጸጋ" ማለት አንችልም "ጸጋ" ማለት እግዚአብሔር ለሰዎች እንዲያው በነፃ የሚሰጠው ስጦታ ማለት እንጂ ሰዎች ለቅዱሳን የሚሰጡት ስጦታ አይደለም፣ በዚህም "የጸጋ ስግደት" የሚለው ስያሜ የተሳሳተ ስያሜ ነው፡፡ በመቀጠል ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳን በሚደረጉት ሁለቱ አይነት ስግደቶች መካከል የተግባርም ሆነ የይዘት ልዩነት ባለመኖሩ ሁለት አይነት ስግደት አለመኖሩና ስግደት አንድ አይነት ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

የዚህ ስህተት መነሻ ከላይ የቀረበው በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ለሰዎች ያደረጉትን ስግደት ነው ነገር ግን እነዚህን ስግደቶች በየአውዱ ብንመለከት ስግደቱ የአክብሮት ሥላምታ እንጂ ፊት ለፊታቸው ለማይታየው በመንፈስ ያደረጉት ስግደት አይደለም፣ እነዚህ ስግደቶች በየአውዱ በምሳሌ ብንመለከት፡-

- <u>አማኝ ለአማኝ ያደረገው ስግደት</u>
  - ነሳሙ.25፡23 "አቢግያ ዳዊትን ባየችው ጊዜ ከአህያዋ ላይ ፈጥና ወረደች፣ በዳዊት ፊት <u>በግምባርዋ ወደቀች፣ በምድርም ላይ እጅ ነሳች</u>፡፡"
  - ዘጸ.18፡7 "ሙሴም አማቱን ሊገናኝ ወጣ፣ <u>ሰገደም</u>፣ ሳመውም፤ እርስ በርሳቸው ደህንነታቸውን ተጠያየቁ፣ ወደ ድንኳኑም ገቡ፡፡"
  - ነሳሙ.20፡41 "ብላቴናውም በሄደ ጊዜ ዳዊት ከስፍራው በደቡብ አጠገብ ተነሳ፣ በምድርም ላይ በግምባሩ ተደፋ፣ ሦስት ጊዜም <u>ለሠላምታ ሰገደ</u> ..."
- <u>አማኝ ላላመነው ያደረገው ስግደት</u>
  - ዘፍ.23፡7 "አብርሃም ተነሳ፣ ለምድሩ ህዝብም፣ ለኬጢ ልጆች <u>ሰገደ</u>"
  - ዘፍ.33፡3 "... (ያዕቆብም) ወደ ወንድሙም(ዔሳው) እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ <u>ሰገደ</u>፡፡"
- <u>ያላመነው ለአማኝ ያደረገው ስግደት</u>
  ዳን.2፡46 "የዚያን ጊዜ ንጉሥ ናቡከደነፆር በግምባሩ ተደፍቶ ለዳንኤል <u>ሰገደለት</u>፣ የእህሉንም ቁርባን ዕጣኑንም ያቀርቡለት ዘንድ አዘዘ፡፡"

እዚህ ጋር "ያላመነው ለአማኝ" እንደዚሁም "አማኝ ላላመነው" ያደረጉትንም ስግደቶች በመልካም ተምሳሌትነት አንወስደውም፣ "አማኞች ለቅዱሳን" ለሚያደርጉት ስግደት "በተምሳሌትነቱ" መውሰድ የምንችለው "አማኝ ለአማኝ" ያደረገውን ስግደትን ነው፡፡

አማኝ ለአማኝ ያደረገውን ስግደት ስንመለከት በውስጡ የምንመለከተው አምልኮን ሳይሆን <u>በፊት ለፊት ለተመለከቱት ሰው</u> በባህላዊ አክብሮታዊ የሥላምታ አሰጣጥ ዘዴ

ሠላም ማለትን ነው፣ ይህም የድሮ ሰዎች አክብሮታቸውን ለመግለፅ በመጎንበስ ወይንም በግምባር በመውደቅ ለሚያከብሩት ሰው የሚሰጡት የሠላምታ አሰጣጥ አይነት ነው፣ ይህንን ዛሬም በቻይናና በጃፓን ባህላዊ ፊልሞች ላይ መመልከት ይቻላል፣ ለዚህ አይነት ሠላምታ ሌላ ቃል ባለመኖሩ ቅዱሳኑ በወቅቱ "ሰገደ" የሚለውን ቃል ተጠቀሙለት::

በዚህ የብሉይ ኪዳን "ስግደት" የሚለው ቃል አሻሚ አገላለፅ ምክንያት የብሉይ ኪዳን ዘመን "ስግደት" በሁለት እንደሚከፈል እንመለከታለን፣

1. <u>የአክብሮት ሠላምታ ስግደት</u>፣ ይህም <u>በስጋ ላሉትና ፊት ለፊት</u> ለሚታዩ ቅዱሳን የሚደረግ የድሮ ሰዎች ለአክብሮት በማለት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ወይንም በግንባር በመውደቅ ሠላምታ የሚሰጡበት አሰራር፣
2. <u>የአምልኮ ስግደት</u>፣ ይህም "በሁሉም ስፍራ ይገኛል" ተብሎ ለሚታመነው <u>በፊት ለፊት በአካል ሳይመለከቱ በመንፈስ</u> የሚደረግ መንፈሳዊ ስግደት፣

ዛሬ በቤተክርስቲያኗ ለቅዱሳኑ የሚደረገውን ስግደት ስንመለከት ከብሉይ ኪዳኑ ስግደት የሚለይበት መሠረታዊ ልዩነት አለው፣ በብሉይ ኪዳን አማኞች የሰገዱት ስግደት በፊት ለፊታቸው ለተመለከቷቸው ቅዱሳን ነው ነገር ግን ዛሬ በቤተክርስቲያኗ የሚደረገው ስግደት <u>በህይወት ለሌሉ፣ በአካል ለማይታዩ፣ እንደ እግዚአብሔር "በሁሉም ስፍራ ይገኛሉ" በማለት በመንፈስ የሚደረግ ስግደት ነው፣ ይህ ደግሞ የአምልኮ ስግደት ነው::</u>

በብሉይ ኪዳኑ የተመለከተው ይህ አሻሚ የስግደት አተረጓጎም በአዲስ ኪዳኑ ግልፅ ተደርጎ እንመለከታለን፣ በአዲሱ ኪዳን ስግደት የተደረገላቸው ቅዱሳን ኢየሱስና ጴጥሮስ ናቸው፣ ኢየሱስ የአምላክ ተዋህዶ ስለሆነ የተደረጉለትን ስግደቶች አልተቃወመም፣ ነገር ግን ጴጥሮስ ሰው በመሆኑ ስግደት ሲደረግለት ፈፅሞ ተቃወመ(ሐሰ.10፡25-26)፣ ምክንያቱም ጴጥሮስ "ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ብቻ ስገድ" የሚለውን ቃል ስለሚያውቅ፣ በዚህም ጴጥሮስ ስግደት ለሰዎች መደረግ እንደሌለበት በግልፅ ቋንቋ ለእኛ <u>ለአዲስ ኪዳን</u> አማኞች አሳይቶን አለፈ::

በዚህም በቤተክርስቲያኗ "የጸጋ ስግደት" በሚል ሽፋን በህይወት ለሌሉና ፊት ለፊት ለማይመለከቷቸው ቅዱሳን በመንፈስ የሚከናወነው ስግደት ስህተት መሆኑንና ስግደቱም የአምልኮ ስግደት እንደሆነ እንመለከታለን::

4.1.3.2.1.2. <u>በመላዕክት ስም የሚደረግ ስግደት</u>

መላዕክት እንደ ሰው ፍጡራን ናቸው፣ ስራቸውም እግዚአብሔርን ማምለክ(ኢሳ.6፡3)፣ እግዚአብሔርን ማገልገልና በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ሰዎችን መርዳት ነው፣ በዚህም መላዕክቱ <u>በእግዚአብሔር ትዕዛዝ</u> የሰው ልጆችን ከክፉ ያድናሉ(መዝ.34፡7)፣ ይጠብቃሉ(መዝ.91፡10-12)፣ ክፉውን ይዋጋሉ(ኢሳ.37፡36)፣ ቅዱሳንን ያፅናናሉ(ዳን.10፡21)፣ ይመግባሉ(1ነገ.19፡1-8)፣ የፀሎትን መልስ ያመጣሉ(ሐዋ.12፡5)፣ ነፍስን ያሳርጋሉ(ሉቃ.16፡22) ...

ቤተክርስቲያኗ ለመላዕክትም ስግደት እንዲደረግ ታስተምራለች፣ ለዚህም የምታቀርበው መከራከርያ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ፊት ለፊታቸው ለተመለከቱት መላዕክት(ለሰማይ ሠራዊት) ያደረጉትን የአክብሮት ስግደት ነው(ዘፍ.19፡1-2, ዘጉ.22፡31, ኢያ.5፡14, 1ዜና.21፡16, ዳን.8፡15-17, መሳ.13፡20 ...)።

በሌላ በኩል ደግሞ እዚያው ብሉይ ኪዳን ላይ ለመላዕክት ስግደት ሊደረግ እንደማይገባና ስግደት ለእግዚአብሔር ብቻ መደረግ እንዳለበት ሲናገር እንመለከታለን፣

- ሶፎ.1፡5-6 "... ለሰማይ ሠራዊት የሚሰግዱትን ... አጠፋለሁ"
- ዘዳ.4፡19 "... የሰማይ ሠራዊትን ባየህ ጊዜ፣ ሰግደህላቸው አምልከሃቸውም እንዳትስት ተጠንቀቅ።"

ተመሳሳይ ቃላትም 2ነገ.21፡5-6, 2ዜና.33፡5-6, ኤር.19፡13 ... ላይ ቀርቧል

በዚህም ቤተክርስቲያኗ ለመላዕክት የሚደረገውን ስግደት ለእግዚአብሔር ከሚደረገው ስግደት ለመለየት ከላይ እንደተመለከትነው፣ ስግደትን በሁለት በመከፈል [96] "የባህሪ ስግደትና የጸጋ ስግደት" በማለት፣ ለእግዚአብሔር የሚደረገውን ስግደት የባህሪ ስግደት ስትል፣ ለመላዕክት የሚደረገውን ደግሞ የጸጋ ስግደት።" በማለት ለእግዚአብሔርም ለመላዕክትም ስግደትን ታከናውናለች።

ነገር ግን ከላይ እንደተመለከትነው የጸጋ ስግደት የተባለውና ቤተክርስቲያኗ ለመላዕክቱ እንዲደረግ ያዘዘችው የስግደት አይነት ከስያሜው ጀምሮ የተሳሳተ መሆኑን፣ ሁለቱ ስግደቶች መካከልም በተግባርም በይዘትም ምንም ልዩነት የሌለ መሆኑንና ቤተክርስቲያኒቷ "ለመላዕክት ሊሰገድ ይገባል" በማለት ከብሉይ ኪዳን የምታቀርባቸው ጥቅሶችና ዛሬ የሚደረገው ስግደት መካከልም ሰፊ ልዩነት መኖሩን፣ ይህም፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች ለመላዕክት የሰገዱት ፊት ለፊታቸው በአካል ቆሞ ላዩት መልአክ በመጎንበስ አክብሮታቸውን በማሳየት መሆኑንና ዛሬ የሚደረገው ስግደት ግን መልአኩን በአካል ባላዩበት እንደ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የመገኘት ማንነት በመስጠት፣ በመንፈስ የሚደረግ የአምልኮ ስግደት መሆኑን እንመለከታለን።

ከላይ የተመለከትነው ይህ በብሉይ ኪዳኑ የተወሳሰበው አገላለፅ በአዲሱ ኪዳን ግልፅ ተደርጎ እንመለከታለን፣ ይህንንም እውነታ ለመረዳት በዮሐንስና ገብርኤል መካከል የነበረውን ነገር እስቲ እንመልከት፡-

- ራዕ.19፡10 "ልሰግድለት በእግሩ ስር ተደፋሁ። እርሱም። እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ ... አለኝ።"

[96] ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣**ነገረ ቅዱሳን-ፎ**፣በኢ/አ/ተ/ቤ/ክ/በሰንበት ተ/ቤ/ማ/መ ማ/ቅ ት/ሐ/አገ/ዋና ክፍል፣ገፅ.105-106

- ራዕ.22፡8-9 “ይህንን ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ፡፡ በሰማሁትና ባየሁት ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ፡፡ እርሱም፡፡ እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነብያት ጋር የዚህን መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ፡፡”

ከዚህ ከዮሐንስና ከገብርኤል ንግግር ሰዎች ለመላዕክት መስገድ እንደሌለባቸው እንመለከታለን፣ ሁለቱም ስፍራ ላይ “ተጠንቀቅ” የሚለው ኃይለ ቃል ደግሞ ለሚያስተውል ሰው የራሱ ትርጉም አለው፡፡

እንደ ስልጣኑና ለእግዚአብሔር ባለው ቀረቤታው(ሉቃ.1፡19) ቢሆን ኖሮ ለመላዕክት ለመስገድ አንደኛ ተመራጭ የነበረው ገብርኤል ነበረ “አትስገዱልኝ” ብሎ ከለከለን እንጂ፣ መልአክ ያዩ ብዙ <u>የአዲስ ኪዳን</u> ፃድቃን አሉ ኢየሱስ፣ ማርያም፣ ዘካሪያስ፣ ቆርኔሌዎስ … ነገር ግን አንዳቸውም ለመላዕክቱ ሲሰግዱ አልተመለከትንም፣ እንድንሰግድም አላዘዙም፡፡

<u>በዚህም ዛሬ በቤተክርስቲያኗ እንደ ብሉይ ኪዳኑ ቅዱሳኑ እንኳን መልአክን በአካል ሳያዩ፣ መላዕክት እንደ እግዚአብሔር “በሁሉም ስፍራ ይገኛሉ” በማለት ለመላዕክት በመንፈስ የሚደረገው የአምልኮ ስግደት ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡</u>

መጽሐፍ ቅዱሱን ጠንቅቆ ላነበበ ሰው በመላዕክቱ ዓለም ሁለት ጎራዎች አሉ፣ ቅዱስና እርኩስ፣ በቅዱሱ ጎራ ያሉት በሙሉ የሚሰግዱለትም ሆነ እንዲሰገድለት የሚፈልጉት ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፣ በእርኩሱ መንገድ ያሉት መንፈሳዊ ኃይላት ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ስግደትን ይፈልጋሉ፣ በዚህም በሁለቱም የመላዕክት ጎራ መካከል ሰፊ የአስተሳሰብ ልዩነት እንመለከታለን፣ ይህንንም እውነታ ሁለቱ መላዕክቶችን (ቅዱሳኑና እርኩሳኑ) ሲናገሩ እስቲ እንመልከት፣

ራዕ.19፡10 መልአኩ ገብርኤል “እንዳትሰግድልኝ ተጠንቀቅ” ሲል

በሌላ በኩል ደግሞ፣

ማቴ.4፡9 ላይ ዲያብሎስ “ወድቀህ ብትሰግድልኝ”

ሲል እንመለከተዋለን፣ በዚህም ቅዱሱ መልአክ ስግደትን አልቀበልም ሲል ዲያብሎስ ደግሞ “ለኔ ስገድ” አለ፣ በዚህም እንዲሰገድላቸው የሚፈልጉት እርኩሳኑ መላዕክት ብቻ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በዚህ ላይ ደግሞ ዲያብሎስ ራሱን ቅዱሳን መላዕክት አስመስሎ እንደሚያጭበረብር መጽሐፍ ቅዱሱ መናገሩን(2ቆሮ.11፡14) እንደዚሁ በ4.3.4.7 ክፍል እንደተመከተው ዲያብሎስ በቤተክርስቲያኗ ሌሎች መጽሐፍት በኩል ራሱን ቅዱስ መልአክ አስመስሎ እንደሚተውን ስንመለከት፣ በቅዱሳኑ መላዕክት ስም እያጭበረበረ ያለው ዲያብሎስ መሆኑን እንረዳለን፣ በዚህም በአጭበርባሪው ተጭበርብረው ከእግዚአብሔር ውጪ በተለያየ ስም ስግደት እየፈፀሙ ያሉ ሰዎች አደጋ ውስጥ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

4.1.3.2.2. <u>ከስግደት በተጨማሪ ወደ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የሚደረጉ አምልኮዎች</u>

በመግቢያው ላይ እንደተመለከትነው "አምልኮ" ብዙ ክፍሎች አሉት፣ ስግደት፣ ፀሎት፣ ምስጋና፣ ውዳሴ ... ከነዚህ ውስጥ ስግደትን ከላይ በስፋት የተመለከትን ሲሆን ሁሉንም የአምልኮ ክፍሎች በዚህ መልኩ መዘርዘሩ ሰፊ ስለሆነ ሌሎቹን የአምልኮ ክፍሎች ቀጥለን አጠር አጠር አድርገን እንመለከታለን፡-

1. <u>**ፀሎት**</u>፡- መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ፀሎት የሚደረገው ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነበረ ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ፀሎት እየተደረገ ይገኛል፡፡

   ዋናው አምልኮም የሚደረገው በማርያም ስም በመሆኑም ከ"አባታችን ሆይ" ፀሎት(ማቴ.6፡9-13) ቀጥሎ ለማርያምም "እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ ..." የሚል ፀሎት ተዘጋጅቶላታል፤ ከወሊድም ጋር በተያያዘ ፀሎት የሚደረገው ለማርያም ብቻ ነው "እመቤቴ በሠላም ትገላግልሽ፣ ማርያም በሽልም ታውጣሽ ..." ይባላል፣ የሚገርመው ደግሞ ከወሊድ ጉዳይ የተገለሉት መላዕክትና ቅዱሳን ብቻ አይደሉም፣ እግዚአብሔርም ጭምር ነው፣ ወሊድ ላይ ከማርያም ስም ውጪ ማንም አይጠራም፣ ይህም እንደ ዋቄፈና፣ የግሪካውያኑና የግብፃውያኑ በሙያ የተከፋፈሉ አማልክት "ማሪያም" የወሊድ አምላክ በመደረጓ ምክንያት ነው፡፡

2. <u>**ምስጋና**</u>፡- መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ሰዎች አምልኳዊ ምስጋናቸውን ሲያቀርቡ የነበሩት ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነበረ፣ ኢሳ.42፡8 "አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ብቻ ነኝ፣ የእኔንም ክብር የሚጋራ ሌላ አምላክ የለም፣ <u>ጣኦቶችም ምስጋናዬን እንዲካፈሉ አልፈቅድም</u>፡፡" ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም አምልኳዊ ምስጋና እየተደረገ ይገኛል፣ የእግዚአብሔርን ምስጋና የሚጋራ ደግሞ ጣኦት ነው፣ ይህም በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተደረገ ያለውን ነገር ያሳያል፡፡

3. <u>**መዝሙር**</u>፡- መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሲዘመር አንመለከትም ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተዘመረ ይገኛል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ሲዘመርለት የነበረው ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው፣ እንደልቤ የተባለው ዳዊትም እንደልብ በመሆኑንም ለእግዚአብሔር ብቻ ሲዘምር ነው የተመለከትነው፣ አሁን ግን በቤተክርስቲያኗ የምንመለከተው እንደልቤን ሳይሆን ልብ አድርቅን ነው፡፡

4. **<u>ውዳሴ</u>**፡- ውዳሴ የሚቀርበው መወደስ ለሚገባው አካል ነው፣ ይህም አካል ራሱን ችሎ ስላደረገው ድንቅ ልዕለ ስብዕና ድርጊቱ ነው፣ በዚህም በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ሲወደስ የምንመለከተው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው ራዕ.4፡9-11, ራዕ.7፡12 … ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም በተለያየ መንገድ በመጽሐፍት፣ በቅዳሴ፣ በመዝሙሮች … ውዳሴ ሲደረግ እንመለከታለን፡፡

5. **<u>ስዕለት</u>**፡-"ስዕለት" ማለት ቃልኪዳን ማለት ነው፣ "እንዲህ ካደረከልኝ እንዲህ አደርጋለሁ" የሚል ቃል ኪዳን፣ በዚህም ስዕለት የሚቀርበው ለፀሎት ፈፃሚው አምላክ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይም ስዕለት ሲቀርብ የነበረው ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው(በዘፍ.28፡20-22, ዘሌ.27፡2, ዘኁ.21፡2, መሳ.11፡31, መዝ.42፡8 …) ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ስዕለት ሲደረግ እንመለከታለን፡፡

6. **<u>መስዋዕት</u>**፡- መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት መስዋዕት ሲቀርብ የነበረው ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነበረ(መሳ.13፡16 ,ሐስ.14፡13-15 …) ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም በተዘጋጁ የመታሰቢያ ቀናት፣ ሰንበታትና በዓላት መስዋዕቶች (እርድ፣ ዳቦ፣ ፀበል …) ሲቀርቡ እንመለከታለን፣ በዚህም "የገብሬል ዳቦ፣ የማርያም ፅዋ … እየተመለከትን ነው፡፡

7. **<u>የአምላክ ስም</u>**፡- መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ቅዱሳን የሚያደርጉትን ጦርነት(1ሳሙ.17፡44-45)፣ ጉዞ(ሚክ.4፡5)፣ ቃለመሀላ(ምሳ.30፡9) … በአምላካቸው ስም ነበረ፣ ይህም የሆነው በመንፈሳዊው ዓለም "ስም" ትልቅ ትርጉም፣ ኃይል፣ ስልጣን … ስላለው ነው(ሚክ.4፡5)፣ ጎልያድ ዳዊትን ሊጋጠም የመጣው የአምላኩን ስም እየጠራ ነው፣ ዳዊትም እንደዚሁ፣ በአዲስ ኪዳኑም እንደዚሁ ሁሉም ድርጊት በአምላክ ስም መሆን እንዳለበት ተነግሯል፣

> ቆላ.3፡17 "እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፣ በቃል ቢሆን ወይም በስራ የምታደርጉትን ነገር ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት"

ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የአማልክት ስም ተደርገው ለተለያዩ አገልግሎቶች ሲጠሩ እንመለከታለን፣ በዚህም በማርያም፣ በገብርኤል … ሲባል እንሰማለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው የአምልኮ ክፍሎች በሙሉ ሲከናወኑ የነበረው ለእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነበረ ነገር ግን

ቤተክርስቲያኗ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን በእግዚአብሔር አምላክ ስፍራ በማስቀመጧ ምክንያት በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እነዚህ አምልኮዎች እየተደረጉ ይገኛሉ፣ ይህም የሚያሳየን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን እንደ እግዚአብሔር እየተመለኩ እንደሚገኙ ነው፡፡

ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን "አምልኩን" ባለማለታቸውና እግዚአብሔርም "በነሱ በኩል በውክልና አምልኩኝ" ባለማለቱ አምልኮውን በነሱ ስም እየተቀበለ ያለው ማን ነው?" የሚለውን ጥያቄ ስንመለከት መልሱ ግልፅ ነው፣ እሱም ከላይ በስግደት ክፍል የተመለከትነው እንደ እግዚአብሔር መመለክን ለሚፈልገው ዲያብሎስ ነው፣ የሚገርመው ደግሞ የፉክክሩ መጠን ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ የምንመለከተው ዲያብሎስ በዘዴ ከመመለክ አልፎ አምልኮውን እንኳን የሚቀበለው የእግዚአብሔር የአምልኮ ንብረቶችን በመጋራት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

4.1.3.3. <u>አምልኮው የሚደረገው የእግዚአብሔርን ነገሮች በማጋራት መሆኑ</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ እንደተመለከተው እግዚአብሔር እንዲመለክበት የሚፈልግበትን የራሱ የአምልኮ ነገሮችን ለይቶ አስቀምጧል፣ እነሱም ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን፣ ታቦት፣ ሰንበት፣ በዓል ... የመሳሰሉት ናቸው ነገር ግን ዛሬ በቤተክርስቲያኗ እንደ እግዚአብሔር መመለክ የሚፈልገውና በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሽፋን የሚንቀሳቀሰው ዲያብሎስ የእግዚአብሔርን መመለኪያ ነገሮችን ተካፍሎ ይገኛል፡፡

ይህንን ምስጢር ያልተገነዘቡ አንዳንድ ሰዎች እነዚህ የእግዚአብሔር የአምልኮ ነገሮች ያጋሩበትን ምክንያቶች ሲናገሩ ይሰማል፣ ይህም፣

- በምሳ.10፡7 "... የፃድቅ *መታሰቢያ* ለበረከት ነው" እና መዝ.111፡6 "... የፃድቅ *መታሰቢያ* ለዘላለም ይኖራል" በሚለው *መሠረት* ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን *መታሰቢያ* ለማድረግ፣
- በመዝ.33(34)፡21 " ... ፃድቃንን የሚጠሉ ይፀፀታሉ" በሚለው *መሠረት* ለፃድቃን ያላቸውን ፍቅር ለማሳየት፣
- ማቴ.10፡41 "ነቢይን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፣ ፃድቅን በፃድቅ ስም የሚቀበል የፃድቁን ዋጋ ወስዳል፡፡"

በሚለው *መሠረት* እንደሆነ ይናገራሉ፡፡

ነገር ግን ለፃድቃን የሚደረገው "*መታሰቢያ*፣ ፍቅርን ማሳየትና ፅድቃቸውን መቀበል" አሰራሮች መከናወን ያለባቸው <u>በየራሳቸው</u> መንገድ መሆን አለበት፣ አምልኮም በራሱ መንገድ፣ <u>ሦስቱን የተለያዩ ድርጊቶችን አንድ በማድረግ</u> ተመልሶ ደግሞ "<u>እነዚህን ሦስቱንም የምናከናውነው በእግዚአብሔር የአምልኮ ንብረቶች ነው</u>" ማለቱ ከጀርባ ያለውን ሤራ ያሳያል፣ ለቅዱሳኑ "*መታሰቢያ*፣ ፍቅርን ማሳየትና ፅድቃቸውን መቀበል" መከናወን ያለበት

በየራሱ መንገድ ነው፣ እነዚህ ነገሮች መከናወን በሚገባቸው መንገድ አለመከናወናቸው ደግሞ በራሱ ሌላ ስህተት ነው፣ በዚህም ይህ አሰራር "ከሁለት ያጣ" አሰራር ነው።።

እነዚህን የማይገናኙ ነገሮችን አገናኝቶ፣ ይህንንም መንደርደርያ አድርጎ የእግዚአብሔር የአምልኮ ንብረቶች ላይ የመቀመጡ አሰራር የእግዚአብሔር ተፎካካሪ መንፈስ ሜራ ብቻ ነው።።

እነዚህ የእግዚአብሔር የነበሩ ነገር ግን ዛሬ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ለሚመለኩት የተከፋፈሉትን የእግዚአብሔር መመለኪያዎች ብንመለከት፣

1. **<u>ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን</u>**፡- መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን ሲሰየም የነበረው በባለቤቱ በእግዚአብሔር ስም እንጂ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም አልነበረም ምክንያቱም አንድ ንብረት የሚጠራው በባለቤቱ ስም ስለሆነ፣
   - የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ (ኤር.51፡51, ዳን.5፡3, ማቴ.26፡61 ...)
   - የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን (ማቴ.16፡18, ሐስ.20፡28, ነቆሮ.1፡2 ...)

   መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አንድም ስፍራ ላይ የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የተሰየመ ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን አላየንም ነገር ግን አሁን ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን እየተተከለ ይገኛል።።
2. **<u>ታቦት</u>**፡- ታቦት የእግዚአብሔር ብቻ ነበረ፣ በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ "የእግዚአብሔር ታቦት" ይላል (ኢያ.4፡5, ነሳሙ.3፡3, 2ዜና.8፡11 ...)፣ "የ" የምትለዋ ቃል ባለቤትነትን ታሳያለች።።

   መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አንድም ስፍራ ላይ የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም የተሰየመ ታቦት አላየንም ነገር ግን አሁን ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ታቦት እየተሰየመ ይገኛል።።
3. **<u>ሰንበት</u>**፡- ሰንበት የእግዚአብሔር ብቻ ነበረ(ዘሌ.23፡3, ዘጸ.16፡29 ...)፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እንዲከበር የታዘዘ ሰንበት አንመለከትም።።

   ነገር ግን አሁን ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን ስም በወራት ውስጥ ተራ በማስገባት በተራቸው ቀን ሰንበት(ስራ የማይሰራበትና ለእነሱ ውዳሴ፣ ቅዳሴ፣ ዝማሬ ... የሚደረግላቸው ቀን) ተሰጥቶአቸው እንመለከታለን።።
4. **<u>በዓል</u>**፡- በዓል ሲከበር የነበረው ለእግዚአብሔር ብቻ ነበረ (ዘጸ.10፡9, ዘጸ.13፡6 ...) መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ለማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የታዘዘ በዓል አንመለከትም።።

   ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ለክርስትናው እንግዳ በሆነ መልኩ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም በዓል ታዘጋጃለች፣ ይህንንም የምታደርገው ለነሱ በተሰየሙ ቀናት፣ ታቦታትና አብያተ ቤተክርስያናት ነው።።

በአጠቃላይ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ የእግዚአብሔር *መመለኪያ* ብቻ የነበሩት ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን፣ ታቦት፣ ሰንበትና በዓል በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም መከፋፈሉን ነው፡፡

ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ለመጽሐፍ ቅዱሱ እንግዳ አይደሉም ነገር ግን ለመጽሐፍ ቅዱሱ እንግዳ የሆነው ይህ በነሱ ስም የእግዚአብሔርን *መመለኪያ* ነገሮች የማከፋፈሉ ስራ ነው፣ ይህም እንግዳ አሰራር የመጣው በነሱ ስም ጣልቃ ገብቶ እንደ እግዚአብሔር እየተመለከ ባለው *መንፈስ* ነው፣ እርሱም ዲያብሎስ ነው፡፡

የሚገርመው ደግሞ ይህ *መንፈሳዊው* ምስጢር በደፈናው በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ይቅረብ እንጂ በየአካባቢው የሚመለከው ግን ራሱን የቻለ *መንፈስ* ነው፣ ለምሳሌ ቁልቢ የሚመለከውና አዲስ አበባ የሚመለከው “ገብርኤል” ሁለቱም በደፈናው “ገብርኤል” ይባሉ እንጂ ሁለቱም እኩል *ኃይል* የላቸውም፣ የቁልቢው “ገብርኤል” ከአዲስ አበባው “ገብርኤል” በስልጣን ከፍ ያለ ነው፣ በተመሳሳይ መልኩ ኩክ የለሽ ማርያም ከሌሎቹ ማርያሞች በስልጣን ትበልጣለች … ብዙ ተመሳሳይ በአንድ ስም የሚጠሩ ነገር ግን በስልጣን የተለያዩ *መናፍስት* የሚመለኩባቸውን ስፍራዎች *መመ*ልከት ይቻላል፡፡

ሌላው አስገራሚ ነገር ደግሞ በ4.4.2.1 ክፍል እንደቀረበው፣ *መጽሐፉ* የምስል አምልኮን እየከለከለና ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ምንም አይነት ፎቶግራፍ ባልተነሱበት ሁኔታ ውስጥ አምልኮው እየተከናወነ ያለው የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን የስዕል ጣኦቶችን በመስራት መሆኑ እንደዚሁ በ4.4.2.2 ክፍል እንደተመለከተው የቤተክርስቲያኗ ታቦትም *መጽሐፍ* ቅዱሱ ከሚያዘው ታቦት በመጠን፣ በቅርፅ፣ በይዘት … የሚለይ ለመጽሐፍ ቅዱሱ ባዕድ የሆነ ጣኦት መሆኑን ስንመለከት በቤተክርስቲያኗ እየተፈፀመ ያለው አምልኮው ግልፅ ጣኦታዊ አምልኮ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን፣

- በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሙሉ አምልኮ(ስግደት፣ ፀሎት፣ ምስጋና፣ ዝማሬ፣ ውዳሴ፣ ስለት፣ *መ*ስዋዕት) እየተደረገ መሆኑን፣
- አምልኮውም የሚደረገው እግዚአብሔር ለራሱ እንዲመለክበት በመረጣቸው(ቤተመቅደስ/ቤተክርስቲያን፣ ታቦት፣ ሰንበትና በዓል) በመከፋፈል መሆኑን፣
- የስዕል አምልኮ በተከለከለበት ሁኔታና ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ፎቶግራፋቸውን ባልተውልን ሁኔታ አምልኮው የሚደረገው የስዕል ጣኦትን በመስራት መሆኑ፣
- የሚመለኩበት ታቦትም ለመጽሐፍ ቅዱሱ እንግዳ የሆነ ጣኦት መሆኑ፣
- ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን “አምልኩን” ባላሉበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ፣

- “እናምልካቸው” ቢባል እንኳን እንደ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ የመገኘት ባህሪ ስለሌላቸው ከሰው አምልኮን መቀበል የማይችሉ መሆኑን፣
- እግዚአብሔር በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም በእጃዙር አምልኩኝ አለማለቱን፣
- መመለክ የሚፈልጉት እግዚአብሔርና ዲያብሎስ ብቻ መሆናቸውን

ስንመለከት፣ አምልኮው ለዘመናት እየተደረገ ያለው ዝም ብሎ አለመሆኑን፣ አምልኮውን በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተቀበለ ያለ አካል መኖሩን፣ ይህም እንደ እግዚአብሔር መመለክ የሚፈልገው የእግዚአብሔር ተፎካካሪው መንፈስ፣ ዲያብሎስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ሰይጣን ድሮ ሲመለክ የነበረው በቀጥታ ነበረ ነገር ግን አሁን ከክርስትና መስፋፋት ጋር በተያያዘ ይህ ቀደምት አሰራሩ ተደናቅፎበታል፣ በዚህም አሁን በራሱ ስም ቢንቀሳቀስ ማንም እንደማይሰማው ያውቃል፣ በዚህም ይህን አዲስና “ውጤታማ” ዘዴውን አቀናበረ፣ ተመሳስሎ መገኘት (Camouflage)፡፡

ሰይጣን ራሱን ለውጦ ሌላ ገፀ ባህሪ ለብሶ በቅዱሳኑና በመላዕክቱ ስም እንደሚጫወት መጽሐፍ ቅዱሱ ቀድሞውኑ ተናግሯል(2ቆሮ.11፡14)፣ ሰይጣን ራሱን “ቅዱስ ሚካኤል” ብሎ በሌላ ስፍራ ደግሞ “ቅዱስ ሩፋኤል” ብሎ ሲያጭበረብር እንደነበረ በ4.3.4.7 ክፍል መመልከት ይቻላል፣ እንደዚሁ በ2.5 ክፍል ዲያብሎስ ራሱን “ፈጣሪ ነኝ ብሎ” በዓረቡ ማኅበረሰብ ዘንድ እንዴት እያጭበረበረ እንዳለ ተመልክተናል፣ “ክርስቲያኖች” ጋር ደግሞ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ያጭበረብራል፣ ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱሱ ሰይጣንን “ሽንጋይ” የሚለው(ኤፌ.6፡11)፣ የሚያሳስተው በሽንገላ ስለሆነ ሰዎች መሳሳታቸውን እንኳን ማስተዋል አይችሉም፡፡

ስለዚህ በዚህ ነገር ውስጥ ያላችሁ፣ ይህን የሰይጣንን ሽንገላ በማስተዋል፣ ማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን ወደ ስፍራቸው በመመለስ፣ በነሱ ስም የሚሰራውን ከቤተክርስቲያናችሁ ጠርጎ በማስወጣት እግዚአብሔርን ብቻ ልታመልኩት ይገባል፡፡ እንዲህ በማድረግ ቤተክርስቲያናችሁን ስትቀድሱ እግዚአብሔር ደግሞ በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋል(ኢያ.3፡5)፣ ለነፍሳችሁም ዕረፍትን ታገኛላችሁ(ኤር.6፡16)፡፡

4.2. ብሉይ ኪዳን እያለ አዲሱ ኪዳን የመጣበትን ምስጢር አለማግኘት

አንድ ክርስቲያን "መጽሐፍ ቅዱስ" ከሚለው ቃል ቀጥሎ ማወቅ ያለበት የሁለቱን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ርዕስ፣ "አዲስ ኪዳን" እና "ብሉይ ኪዳን" ትርጉም መሆን አለበት፡፡ ከመነሻው "ኪዳን" ማለት "የሁለት ወገኖች ውል" ማለት ነው፣ ዳዊትና ዮናታን ቃል ኪዳን አደረጉ(1ሳሙ.18፡3-4)፣ ባልና ሚስትም ለትዳር ቃል ኪዳን አደረጉ ይባላል፤ እንደዚሁ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች መዳን ከተለያዩ ትውልዶች ጋር በዋናነት አምስት ጊዜ ቃል ኪዳን አድርጎ ነበረ፣ በአዳም (ዘፍ.2፡16-17)፣ በኖህ (ዘፍ.9፡1-7)፣ በአብርሃም (ዘፍ.17፡1-21)፣ በሙሴ(ዘጸ.24፡7-8) እና በክርስቶስ(1ቆሮ.11፡23-26)

በዚህ ምዕራፍ የምንመለከተው የኋለኞቹን በሙሴና በኢየሱስ በኩል የወረዱትን፣ በተለምዶ "የብሉይ ኪዳን" እና "የአዲስ ኪዳን" ተብለው የሚታወቁትን ኪዳኖችን፣ አንድነትና ልዩነትን ነው፡፡

"ብሉይ ኪዳን" የሚባለው በተለምዶ በሙሴ በኩል የወረደው ኪዳን ሲሆን በኪዳኑም መሠረት ሰዎች ፅድቅን የሚያገኙት እግዚአብሔር ያወረዳቸውን ሕግጋት፣ ትዕዛዛትና የአምልኮ ስርዓቶች በፍፅምና በመጠበቅ ነው፣ "አዲስ ኪዳን" ማለት ደግሞ በኢየሱስ በኩል የወረደው ኪዳን ሲሆን በኪዳኑም መሠረት ሰዎች ፅድቅን የሚያገኙት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው፡፡

ይህ በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ ቀላል ቢሆንም ወደ ዝርዝሩ ሲገባ ግን ልዩነቱ ሊረዱት የሚከብድ ከባዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ሆኖ እናገኘዋለን፣ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያንንም ግራ ያጋባትና በሁለቱ ኪዳናት መካከል እንድትዋልል ያደረጋትም ይኸው እውነታ ነው፣ እነዚህን ግራ አጋቢ ነገሮችንም ስንመለከት፣

- በአንድ በኩል ኢየሱስ "እኔ ሕግን ልሽር አልመጣሁም" እያለ ሐዋርያቱ ደግሞ "የብሉይ ኪዳን ተሽሯል" አሉ(ዕብ.8፡7-13, ዕብ.10፡9 ...)፣
- "ብሉይ ኪዳን ተሽሯል" ሲባል የ39ኙ የብሉይ መጽሐፍት ዕጣ ፋንታ ምንድነው?
- "ብሉይ ኪዳን ተሽሯል ሲባል በብሉይ ኪዳን የታዘዙቱ ታቦት/ፅላት፣ ቤተ መቅደስ፣ ሰንበት ... ዕጣ ፋንታስ ምንድነው?
- በአዲስ ኪዳን ፅድቅ በእምነት ከሆነ ሕግን የሚተላለፍ ሰው ዕጣ ፋንታስ ምንድነው?

እነዚህን ግራ አጋቢ ጥቄዎችን ለመመለስ በመጀመርያ በደፈናው "ብሉይ ኪዳን" የሚባሉትን ሦስት ነገሮች፣ ይህም የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን፣ የብሉይ ኪዳን ሕግ እና የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አንድነትና ልዩነት ለያይቶ መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

4.2.1. “የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን” እና “የብሉይ ኪዳን ሕግ”

የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን ማለት እግዚአብሔር የእስራኤልን ህዝብ ለማፅደቅ በሙሴ በኩል ያወረደው ቃል ኪዳን(ውል) ነው(ዘጸ.24፡7-8, ሮሜ.9፡4 …)፣ በዚህ ቃል ኪዳን(ውል) መሠረትም አንድ ሰው የሚፀድቀው እግዚአብሔር ያወረደውን ሕግጋት፣ ትዕዛዛትና የአምልኮ ሥርአት በፍፅምና በመጠበቅ ነው፡፡

ነገር ግን ሰዎች ይህንን እግዚአብሔር ያወረደውን ሕግጋት፣ ትዕዛዛትና የአምልኮ ስርዓቶች በፍፅምና በመጠበቅ መፅደቅ ስላልቻሉ አዲሱ ቃል ኪዳን(አዲስ ኪዳን) መጣ፣ አዲሱ ኪዳንም ሲመጣ የብሉይ ኪዳኑን ሕግጋት ሳይጥል “ሰዎች የሚፀድቁት በክርስቶስ ሲያምኑ ነው” አለ፣ በዚህም በአዲሱ ኪዳን “ብሉይ ኪዳን ተሽሯል” ሲባል “የብሉይ ኪዳን ሕግ” ተሽሯል ማለት ሳይሆን የተሻረው ሕግን በመጠበቅ ፅድቅ የሚገኝበት ቃል ኪዳን(ውል) ነው፡፡

በአዲስ ኪዳንም ፅድቅ የሚገኘው በኢየሱስ በማመን ነው፣ በአዲሱ ኪዳን የብሉይ ኪዳኑ ሕግ ምን ስፍራ ይኖረዋል? የሚለውን በ4.2.3.5 ክፍል በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

4.2.2. የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን እና 39ኙ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት

ሌላው የ“ብሉይ ኪዳን” ትርጉም በህትመት ቴክኖሎጂ መምጣት ምክንያት በተበታተነ መንገድ በጥቅልል የነበሩት ቅዱሳን መጽሐፍት በአንድ ላይ ሲጠረዙ፣ ክክርስቶስ በፊት ለነበሩት ለ39ኙ መጽሐፍት ስብስብ የተሰጠ ስያሜ ነው፡፡ የእነዚህ መጽሐፍት ይዘትም የስነፍጥረት ታሪኮች፣ ከፈጣሪ የወረዱ የብሉይ ኪዳን ሕግጋት፣ የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን፣ የቅዱሳን የህይወት ምሳሌዎች፣ የእስራኤል ህዝብ ታሪኮች፣ ትንቢቶች፣ ዝማሬዎች … የተፃፉባቸው 39 መጽሐፍት ናቸው፡፡

በዚህም “ብሉይ ኪዳን” በሚለው ቃል ውስጥ ይህንን “የ39 መጽሐፍት” ስያሜንም እናገኛለን፣ በዚህም “ብሉይ ኪዳን ተሻረ” ማለት የተሻረው የብሉይ ኪዳን ቃል ኪዳን(ይህም ሕግን በመጠበቅ መፅደቅ) እንጂ 39ኙ መጽሐፍት አይደሉም፣ ምክንያቱም መጽሐፉ ውስጥ ያለው የስነፍጥረት ታሪክ፣ መዝሙር … አይሻርምና፡፡

ከላይ የቀረቡትን ሁለቱን ሐሳቦች አጠቃለን ስንመለከት “ብሉይ ኪዳን ተሽሯል” ሲባል የተሻረው ሕግን በመጠበቅ ፅድቅ ይገኝበት የነበረው አሰራር እንጂ የብሉይ ኪዳን ሕግና የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አይደሉም፡፡

አሁን “ብሉይ ኪዳን” ከሚለው ቃል ጋር ተያይዞ ያለው ግራ አጋቢ ነገር ግልፅ በመሆኑ ሁለቱን ኪዳናት(ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን) ከቃል ኪዳን/ውልነታቸው አንፃር ወደ ማነፃፀሩ እናልፋለን፡፡

4.2.3. <u>ቤተክርስቲያኗ በአዲሱ ኪዳንና በብሉይ ኪዳን ሽግግር ውስጥ ያላስተዋለችው እውነታ - "ሁለቱ ኪዳናት ተተካኪ እንጂ ተዳባይ አለመሆናቸው"</u>

በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለት የተለያዩ ቃል ኪዳኖች/ውሎች እንደማይኖሩት ሁሉ፣ እግዚአብሔር ሰዎች እንዲፀድቁበት ያስቀመጠው ቃል ኪዳን/ውል አንድ ነው፣ በመጀመርያ የብሉይ ኪዳን ውል ነበረ፣ በዚህ ውልም ሰዎች መዳን ስላልቻሉ ውሉ ተሽሮ አዲሱ ኪዳን ወረደ። አዲሱ ኪዳንም ሲመጣ ሁለት ኪዳኖች(ውሎች) አብረው እንደማይሰሩ ሁሉ፣ አዲሱ ኪዳን የቆመው የቀደመው ኪዳን ሽሮ ነው፣

- ዕብ.10፡9 "... ሁለተኛውን ሊያቆም ፊተኛውን ይሽራል ..."
- ዕብ.8፡7-13 "ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው ለሁለተኛው ስፍራ ባልተፈለገም ነበር ... አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቷል።"
- ዕብ.7፡18-19 "<u>ህጉ</u> ምንም ፍፁም አላደረገምና ስለዚህ የምትደክም የማትጠቅም ስለሆነች የቀደመችው <u>ትዕዛዝ</u> <u>ተሽራለች</u>፣ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።"

በዚህም የሁለቱ ኪዳኖች ውል ተዳባይ ሳይሆኑ ተተካኪ መሆናቸውን እንመለከታለን፣ በኪዳናቱ ውስጥም የተተካኩትን ዋና ዋናዎቹን ነገሮች ስንመለከት፣

ተቁ	ፍሬ ሐሳብ	በብሉይ ኪዳን	በአዲስ ኪዳን
1	ኪዳኑ የመጣበት	በድንጋይ ፅላት(ኢያ.3፡6-8, 1ሳሙ.4፡5)	በኢየሱስ (ሚል.3፡1, ዕብ.12፡24)
2	ኪዳኑ የፀናው	በኮርማ ደም (ዘጸ.24፡7-8)	በኢየሱስ ደም (ማቴ.26፡28, 1ቆሮ.11፡23-26)
3	የኃጢያት ማስተሰረያ	የእንስሳት ደም(ዕብ.10፡11	የኢየሱስ ደም (1ዮሐ.1፡7)
4	ፅላት	የድንጋይ ሰሌዳ (ዘጸ.24፡12)	የሰው ልብ (2ቆሮ.3፡3)
5	ቤተ መቅደስ	በድንጋይ የተገነባ (ማቴ.24፡1-2	የሰው ልጅ (1ቆሮ.6፡19-20)
6	ሰንበት	ቀን (ዘጸ.31፡14-15)	ኢየሱስ (ቆላ.2፡16)
7	ሊቀካህን	ምድራዊ ሰው (ዕብ.7፡28)	ኢየሱስ(ዕብ.4፡14, ዕብ.6፡20)
8	ፅድቅ የሚገኘው	ሕግን በመጠበቅ	በኢየሱስ በማመን (ገላ.2፡16)

ቤተክርስቲያኗ እነዚህ ተተካኪ ነገሮችን ማተካካት ባለመቻሏ አዲሱን ኪዳን መቀበል አልቻለችም እንደዚሁ የኪዳኑንም በረከቶች ማግኘት አልቻለችም፣ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡-

4.2.3.1. <u>የብሉይ ኪዳኑ ፅላት/ታቦት በአዲስ ኪዳኑ ፅላት/ታቦት አለመተካት</u>

በብሉይ ኪዳን "ፅላት" ማለት በእግዚአብሔር እጅ አስርቱ ትዕዛዛት የተፃፈበት የድንጋይ ሰሌዳ ነው፣ ፅላቱም የሚቀመጠው በእንጨት በተሰራ ታቦት ውስጥ ነው፣ በዚህም በተለምዶ "ታቦት" የሚለው ቃል ሰፋ ያለና ፅላትንም የሚያካትት በመሆኑ በዚህ ክፍል ሁለቱም በአንድ ላይ ለመጥራት "ታቦት" የሚለውን ቃል እንጠቀማለን፡፡

በብሉይ ኪዳን በቁሳቁስ የሚሰራው ታቦትና ቤተመቅደስ ተሰጥቶ ነበረ፣ በአዲስ ኪዳኑ የእግዚአብሔር መንፈስ ማደርያ የሰው ልጅ በመሆኑ በቁስ የሚሰራው ታቦትና ቤተመቅደስ አሰራር ተሽሮ ታቦቱና ቤተመቅደሱ የሰው ልጅ ሆነ፡፡

ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ አዲሱ ኪዳን ብሉዩን ስላልተካ ከቁስ የሚሰራው ታቦትና ቤተመቅደስ ለአዲስ ኪዳኑ ታቦትና ቤተመቅደስ ስፍራውን አልለቀቀም፣ የሚገርመው ደግሞ ቤተክርስቲያኗ ለዚህ አሰራሯ የምታቀርበው መከራከርያ በሙሉ የሚያቀርቡት ከብሉይ ኪዳን <u>ብቻ</u> ነው፣ እንደ መከራከርያ የሚያቀርቡትም [97] "ታቦት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው" የሚል እንጂ ብሉይ ኪዳን በአዲሱ ኪዳን ሲተካ ታቦት ከፍ በተደረገበት መንፈሳዊ ትርጉሙ አይደለም፡፡

ይህንን መተካካት ከመነሻው ብንመለከት፣ በመጀመርያ እስራኤላውያን በዘጸ.24 ላይ የተነገረውን ቃል ኪዳን (ብሉይ ኪዳን) በመቀበላቸው በዘጸ.25 ላይ ታቦቱ የቃል ኪዳን ምልክት እንዲሆን ተሰጣቸው፣ በዚህም ታቦቱ ከቃል ኪዳኑ ጋር ስለሚያያዝ "<u>የቃል ኪዳኑ ታቦት</u>" ተባለ (ዘኁ.14፡44, ዘዳ.10፡8, ዘዳ.31፡25, ኢያ.3፡3, 1ሳሙ.4፡4, 2ሳሙ.15፡24, 1ነገ.3፡15, 1ዜና.15፡26, 2ዜና.5፡7 ...)፣ ነገር ግን ህዝቡ በቃል ኪዳኑ ፀንቶ መኖር ባለመቻሉ እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን እንደሚሽርና በዚህም ለቃል ኪዳን የተሰጣቸው የታቦት አሰራር አብሮ እንደሚሻር በነቢያቱ አፍ ቀድሞ ተናገረ፣

> ኤር.3፡16-17 "በበዛችሁም ጊዜ በምድርም ላይ በረባችሁ ጊዜ፣ ይላል እግዚአብሔር፣ በዚያ ዘመን፡፡ <u>የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት</u> ብለው <u>ከእንግዲ ወዲህ</u> <u>አይጠሩም</u>፤ ልብ ብለው ከእንግዲህ ወዲህ አይጠሩም፤ ልብ አያደርጉትም፣ <u>አይሹትምም</u>፣ <u>ከእንግዲህ ወዲህም አይደረግም</u> ... **<u>ከእንግዲህ ወዲህ እልከኛ ልባቸውን ተከትለው አይሄዱም</u>**፡፡"

በዚህም ለብሉይ ኪዳን ዘመን የታዘዘው የቃል ኪዳኑ ታቦት በአዲሱ ኪዳን ስፍራ እንደሌለው ቀድሞ ተነገረ፡፡ ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ(ማሳያ ሞዴል) በመሆኑም(ዕብ.8፡5)፣ የብሉይ ኪዳኑ ታቦት ሲሻር የአዲስ ኪዳኑ ታቦት ማን እንደሆነ? የት እንደሚቀመጥ? ተነገረ፣

---

[97] መምህር ዶ/ር ዘነበ ለማ፣ **የሙሴን ሕግ አስቡ**(VCD)፣ ስለ ታቦት ለሚነሳ ጥያቄ የማያዳግም ምላሽ፣ ዘአብ መዝሙር ቤት

- ኤር.31፡31-33 “እነሆ ከእስራኤልና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል … ከግብፅ ሀገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም … ከነዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው ቃል ኪዳን ይሄ ነውና፣ ይላል እግዚአብሔር፤ ህጌን በልቡናቸው አኖራለሁ፣ በልባቸውም እፅፈዋለሁ…”
- 2ቆሮ.3፡3-7 “እናንተም በህያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፣ ስጋ በሆነ ልብ ፅላት እንጂ በድንጋይ ፅላት ያልተፃፈ … እርሱም ደግሞ፣ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን … ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረፀ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፣ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም፣”
- ሮሜ.7፡6 “አሁን ግን … በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።”

በዚህም በብሉይ ኪዳን ዘመን በድንጋይ ላይ ሲቀረፅ የነበረው የፅላት አሰራር በአዲሱ ኪዳን ዘመን በሰዎች ልብ ላይ በእግዚአብሔር መንፈስ በሚቀረፅበት አሰራር ተተካ፣ ይህም አሰራር በአዲስ ኪዳን “የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ የሰው ልጅ ነው” (1ቆሮ.3፡17፣ 1ቆሮ.6፡19-20፣ 2ቆሮ.6፡16 …) ከሚለው አሰራር ጋር የተያያዘና በአዲስ ኪዳን ያለው አሰራር ከቁሳዊው አሰራር ወደ መንፈሳዊ አሰራር ከፍ የተደረገ በመሆኑ ነው(ዕብ.9፡9-10)።

ለዚህም ነው በአዲሱ ኪዳን ስለ ቁሳዊው ታቦት አጠቃቀም ትዕዛዝ ያልተሰጠው፣ መሪዎቹም ኢየሱስና ሐዋርያቱም ታቦት ሰርተው ሲያገለግሉት፣ ሲገለገሉበትም፣ ሲሰግዱለትም ሆነ ሲሸከሙት ያልታየው፣ ይህም የሆነው ከላይ በተገለፀው የሁለቱ ኪዳናት መተካካት ምክንያት በተተካካው የታቦት ትርጉም ምክንያት ነው።

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ ሁለቱ ኪዳናት ተተካኪ በመሆናቸው ቁሳዊው ታቦት በአዲሱ ኪዳን በመንፈሳዊ ትርጉም የተተረጎመ መሆኑን ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ የብሉይ ኪዳኑ ቁሳዊው ታቦት ባለመነሳቱ የአዲስ ኪዳኑ ታቦት ስፍራውን መያዝ አለመቻሉንና በዚህም ቤተክርስቲያኗ ከአዲስ ኪዳኑ ጋር አለመገናኘቷን እንመለከታለን።

4.2.3.2. የብሉይ ኪዳኑን ቤተመቅደስ በአዲስ ኪዳኑ ቤተመቅደስ አለመተካት

ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን ሲተካ ከተተካኩት ውስጥ ሌላኛው ቤተመቅደስ ነው፣ በአዲስ ኪዳን የቤተመቅደስ ትርጉም ከተለመደው በግንባታ ከሚሰራው ቤተመቅደስ ወደ መንፈሳዊ አተረጓጎም ከፍ ተደርጓል፣ ኢየሱስም በወቅቱ ከአብዛኞቹ አይሁዳውያን ጋር መግባባት ያልቻለው በዚህ ከፍ በተደረገው ትርጉም በመናገሩ ነበረ፡-

- ዮሐ.2፡19-21 “ኢየሱስም መልሶ፣ ይህንን ቤተመቅደስ አፍርሱት በሦስት ቀንም አነሳዋለሁ አላቸው፣ ስለዚህ አይሁድ፣ ይህ ቤተመቅደስ ከአርባ ስድስት አመት ጀምሮ ይሰራ ነበር፣ አንተስ በሦስት ቀን ታስነሳዋለህን? አሉት፡፡ እርሱ ግን ስለ ሰውነቱ ቤተመቅደስ ይል ነበረ፡፡”
- ዮሐ.4፡20-24 “አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፣ እናንተም ሰው ሊሰግድ የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው፣ ኢየሱስም እንዲህ አላት፣ አንቺ ሴት እመኚኝ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል … ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኗል …”

ኢየሱስ ይህንን የተናገረው በብሉይ ኪዳኑ ቤተመቅደስ በሚባለው ግንባታ ሳይሆን በአዲስ ኪዳኑ ትርጉም ነበረ፣ ይህንን የአዲስ ኪዳን አተረጓጎም ሐዋርያቱም ሲያስረዱ፣

- ነቆሮ.3፡17 “… የእግዚአብሔርም ቤተመቅደስ ቅዱስ ነውና ያውም እናንተ ናችሁ፡፡”
- ነቆሮ.6፡19-20 “… ስጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ ውስጥ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተመቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?”
- 2ቆሮ.6፡16 “… እኛ የእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ነንና …”

በዚህም በቁሳዊ ግንባታ የሚሰራው የብሉይ ኪዳን ቤተመቅደስ በአዲሱ ኪዳን በመንፈሳዊው ትርጉም የሰው ልጅ መንፈሳዊ መሰራት ሆኖ እንመለከታለን፣ ይህም በአዲሱ ኪዳን ፅላቱ የሰው ልብ ከሆነበት አሰራር ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ምን ያህል ከአዲስ ኪዳኑ ጋር መሄድ እንዳልቻለች እንመለከታለን፡፡

4.2.3.3. የብሉይ ኪዳኑን የቀን ሰንበት በአዲስ ኪዳኑ ሰንበት አለመተካት

ቤተክርስቲያኗ ሁለቱን ኪዳናት ስለተቀላቀሉባት የሰንበት ጉዳይም ላይ ወጥ አቋም መያዝ አቅቷት በሁለት ልብ ስትሄድ እየተመለከትን ነው፣ ቤተክርስቲያኗ በሰንበት እንደ እርሻ ያሉ ከባባድ ስራዎችን ስትከለክል እንደ ማብሰል ያሉ አነስተኛ ስራዎችን ግን አትቃወምም፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ወይ ብሉይ ኪዳን እንደሚያዘውና ዛሬ አይሁዳውያን አካባቢ እንደምንመለከተው “ምንም ነገር ባለመስራት” አላረፈችም ወይ እንደ አዲስ ኪዳኑ “ሰንበት(እረፍት) ክርስቶስ ነው” ብላ የቀኑን ሰንበት በክርስቶስ አልተካችም፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን “ሰንበት” ማለት ሰባተኛው ቀን ነው፣ ይህም ቀን ፈጣሪ ፍጥረታቱን ፈጥሮ ያረፈበት ቀን ነው(ዘፍ.2፡2)፣ በዚህም መጽሐፉ ይህንን ቀን በሰዎችም ዘንድ የእረፍት ቀን (ዘሌ.23፡3, ዘዳ.5፡14)፣ የሚቀደስ ቀን (ዘጸ.20፡8, ኤር.17፡22)፣ የደስታ ቀን (ኢሳ.58፡13) … መሆን እንዳለበት ይናገራል፣ ይህንንም ትዕዛዝ የሚተላለፍ እስከ ሞት የሚደርስ ብርቱ ቅጣት እንዲጣልበት ያዛል(ዘጸ.31፡14)፡፡

እነዚህ ሁሉ የብሉይ ኪዳን ትዕዛዞች እያሉ ብሉይ ኪዳን በአዲሱ ኪዳን በመተካቱ ምክንያት ኢየሱስ የሰንበትን ቀን አላከበረም(ዮሐ.5፡1-18, ዮሐ.9፡14-16)፣ ሌሎችም እንዳያከብሩ አስተማረ(ማቴ.12፡1-12, ማር.2፡23-28, ሉቃ.6፡1-9 ...)፣ ሐዋርያቱም "የቀኑ ሰንበት *መሠረዙን*" አስተማሩ(ዕብ.4፡9)።

ሰንበትን ማክበር የተላለፈው ያውም በትልቁ የአስርቱ ትዕዛዛት ላይ ነው(ዘጸ.20፡8)፣ ክርስቶስ ደግሞ "ሕግን ልሽር አልመጣሁም" ብሎ ለምን ሕግን ይሽራል? የሚሉ ጥያቄዎች በወቅቱም ሆነ ከዚያ በኋላ በነበረው ትውልድ ውስጥ ጥያቄ አስነስቷል፣ የሚገርመው ደግሞ አሁንም ብዙዎችን ግራ አጋብቷል።

ነገር ግን *መጽሐፍ* ቅዱሱን በማስተዋል ላጠና የሚጋጩ ቃላት አለመኖራቸውንና "ሕግ አይሻርም" እንደተባለው አለመሻሩን ነገር ግን የሰንበት አተረጓጎም እንደ ታቦትና ቤተመቅደስ ትርጉም ከፍ ባለ አተረጓጎም(*መንፈሳዊ* አተረጓጎም) *መ*ተካቱን ነው የሚ*መ*ለከተው፣

> ቆላ.2፡16-17 "እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር *መ*ባቻ ወይም ስለ <u>ሰንበት</u> ማንም አይፍረድባችሁ፣ <u>እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፣ አካሉ ግን ክርስቶስ ነው</u>።"

አካሉ ሲገለጥ ጥላ(*ማ*ሳያ ሞዴሉን) ማንም አይከተለውም፣ በዚህም በአዲስ ኪዳኑ *ማ*ረፊያው በቀን ሳይሆን በክርስቶስ *መ*ሆኑና፣ ክርስቶስን ያገኘ ከሁሉ ነገር እንዳረፈና ሰንበት እራሱ ክርስቶስ *መ*ሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህም በሳምንት አንድ ቀን ከማረፍ የዘላለምን እረፍት ክርስቶስን *መ*ምረጡ የተሻለ ነው።

4.2.3.4. <u>የብሉይ ኪዳኑን የሰው ሊቀካህን በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ሊቀካህን አለመተካት</u>

"ሊቀካህን" ማለት በሰዎችና በእግዚአብሔር *መ*ካከል በመገኘት ስለ ሰዎች ኃጢያት *መ*ስዋዕት በማቅረብ ኃጢያት የሚያስተሰረይ ማለት ነው(ዕብ.8፡3, ዕብ.5፡1, ዕብ.7፡27 ...)፣ የመጀመሪያው ሊቀካህን አሮን ነበረ፣ ከዚያም እስከ ክርስቶስ *መ*ምጣት ድረስ ብዙ ሰዎች በዚህ ስልጣን ሲሾሙ ነበረ፣ በአዲሱ ኪዳን ግን በሊቀካህንነት የተሾመው ኢየሱስ ብቻ ነው፣ ነገር ግን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስም በኋላ ሰዎችን በሊቀካህንነት ትሾማለች፣ ይህ ደግሞ የአዲስ ኪዳኑን አሰራር ያላገናዘበና የክርስቶስን የሊቀካህንነት ሹመት የሚጋፋ አሰራር ነው።

*መ*ጽሐፍ ቅዱሱ ግን በአዲስ ኪዳን ሊቀካህኑ ኢየሱስ ብቻ *መ*ሆኑን ይናገራል፣

- ዕብ.7፡28 "ህጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀካህናት አድርጎ ይሾማል፣ <u>ከሕግ በኋላ የመጣ የመሀላው ቃል ግን</u> ለዘላለም ፍፁም የሆነውን ልጅ ይሾማል።"
- ዕብ.4፡14-15 "እንግዲህ ... ትልቅ ሊቀካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስን ስላለን፣ *ፀ*ንተን ኃይማኖታችንን እንጠብቅ።"

- ነጢሞ.2፡5 “አንድ እግዚአብሔር አለና በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።።”

በዚህም በአዲሱ ኪዳን ሊቀካህን ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ከኢየሱስ ቀጥለው የነበሩት ዋናዎቹ እነ ጳውሎስና ጴጥሮስ እንኳን ሊቀካህን አልተባሉም።።

ስለዚህ በአዲሱ ኪዳን በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል የሚቆመው ሊቀካህን ክርስቶስ ብቻ ነው፣ ሌሎቹ አማኞች በሙሉ “ካህናት” ናቸው(ነጴጥ.2፡5, ነጴጥ.2፡9, ራዕ.ነ፡6, ራዕ.5፡9-ነ0)፣ ስለዚህ የብሉይ ኪዳኑን አሰራር በመተው የሊቀካህንነት ስፍራን ለአዲስ ኪዳኑ ሊቀካህን ለክርስቶስ መተዉ መልካም ነው።።

4.2.3.5. <u>በብሉይ ኪዳኑ “ሕግ በመጠበቅ” ይገኝ የነበረውን ፅድቅ በአዲስ ኪዳኑ “በክርስቶስ ማመን” አለመተካት</u>

ቤተክርስቲያኗ ሁለቱ ኪዳናት ባለማተካካቷ ምክንያት የሁለቱ ኪዳናት የፅድቅ መንገድ ተቀላቅሎባታል፣ በዚህም አንድ ሰው የሚፀድቀው እንደ ብሉይ ኪዳን ህጉን ፈፅሞ በመጠበቅና እንደ አዲሱ ኪዳን በክርስቶስ በማመን እንደሆነ ትናገራለች።። ቤተክርስቲያኗን “ሰዎች በክርስቶስ አምነው ብቻ ይፀድቃሉ” የሚባለው አሰራር <u>የማፅደቅ ብቃቱ አላሳመናትም</u>፣ በዚህም ሰው ለመፅደቅ በኢየሱስ ከማመን በተጨማሪ የብሉይ ኪዳንኑ የሕግ ፍፅምና መጠበቅ እንዳለበት ታስተምራለች።። ለዚህ ማጠናከሪያም፣

> ያዕ.2፡24-26 “ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በስራ እንዲፀድቅ ታያላችሁና … ከነፍስ የተለየ ስጋ የሞተ እንደሆነ እንዲሁም ከስራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።።”

የሚለውን ቃል ታቀርባለች።። በዚህም ምዕመናኖቿዋ ፅድቅን ለማግኘት በክርስቶስ ከማመን በተጨማሪ የሕግን ፍፃሜ በመጠበቅ ለመፅደቅ ሲታገሉ ይታያል ነገር ግን ይህ ስህተት መሆኑና ስህተቱም የመጣው የሁለቱን ኪዳናት ልዩነትና የያዕቆብ መልዕክት የተፃፈበትን <u>አውድ</u> ካለማወቅ የተነሳ ነው።።

የሐዋርያውን የያዕቆብ መልዕክት ከመጀመሪያው አንስተን ስንመለከት፣ ያዕቆብ እያወዳደረ ያለው ጫፍ ለጫፍ ስለወጡት ሁለት ሰዎች ነው፣ እነሱም በያዕ.2፡ነ8 ላይ የተገለፁት፣ “በሕግ ብቻ ነው የምፀድቀው” የሚለውና “በእምነት ብቻ ነው የምፀድቀው ስራ አያስፈልገኝም” ስለሚሉ ሁለት ሰዎች ክርክር፣ ያዕቆብም ሊወቅስ የፈለገው “እኔ እምነት አለኝ ስራ አያስፈልገኝም” የሚለውን በእንግሊዘኛው "antinomian" ስለሚባለው አስተምህሮ ነው፣ ከመግቢያው ይሄ ሰውዬ ምን እንደሚመስል ነግሮናል፣ ያዕ.ነ፡23-26 “ቃሉን የሚሰማ የማያደርገው … እንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ የሚያመልክ የሚመስለው …” በማለት የሰውየውን ማንነት አሳይቶናል።።

እንደዚህ አይነት ሰዎች፣ “<u>ሕግ አታፀድቅም</u>” የሚለውን “<u>ሕግ ተሸራለችን</u>” በማለት <u>የሚያነቡ ናቸው</u> ነገር ግን በአዲሱ ኪዳን ሕግ አልተሻረችም፣ ምንም እንኳን ሕግ ማፅደቅ ባትችልም የማስኮነን አቅም ግን አላት፣ ሕግን የጣሰ ዛሬም ኃጢያተኛ ነው፣ ነገር ግን

በአዲሱ ኪዳን አንድ ሰው ሕግን የሚጠብቀው ሊፀድቅበት ሳይሆን በመፅደቁ ምክንያት ነው፣ በክርስቶስ አምኖ ፀድቆ ሳያስተውል ሕግን የሚጥሰው ሰው ኃጢያት ደግሞ በኢየሱስ የምልጃ አገልግሎት ይሸፈናል፣ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል "አማላጅ" ያስፈለገውም በዚህ ምክንያት ነው::

በዚህም ለተወሰነ አውድ "በእምነት ድኛለሁ መልካም ስራ መስራት አያስፈልገኝም" ለሚል ሰው ተለይቶ የተፃፈውን የያዕቆብን መልዕክት ወስዶ ለሁሉም ሰው እንደተነገረ አድርጎ የአዲስ ኪዳኑን የፅድቅ መንገድ ደካማ አድርጎ፣ ተሞክሮ ያልተቻለውን የብሉይ ኪዳን የፅድቅ መንገድ(የሕግን ፍፅምና መጠበቅ) ማዳበሉ ስህተት ነው፣ አደጋም አለው ምክንያቱም ከመነሻው ህጉን በመጠበቅ መፅደቅ ይቻል ቢሆን ኖሮ የክርስቶስ መምጣት አላስፈላጊና የከፈለውም ዋጋ ከንቱ የሚያደርግ ነውና:: አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ስልት "የተፃፈበት አውድ መመልከት" መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም::

እዚህ ጋር "ፅድቅ" ፅድቅ ሆኖ ሳለ መጽሐፍ ቅዱሱ ስለሚፀድቁት ሰዎች "ፀሐይ፣ ጨረቃ ወይም ከዋክብት"፣ "በወርቅ፣ በብር፣ በከበረ ድንጋይ፣ በእንጨት፣ በሳር ወይም በአገዳ የተሰራ" እያለ ፃድቃንን የሚያወዳድርበትን እውነታም ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው፣

- ነቆሮ.15፡41-42 "የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብት ክብር ሌላ ነው፤ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያያልና:: የሙታን ትንሳኤም እንደዚሁ ነው::"
- ነቆሮ.3፡11-15 "ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሳርም ወይም በአገዳ ቢያንፅ፣ የእያንዳንዱ ስራ ይገለጣል፤ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፣ የእያንዳንዱንም ስራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል:: ማንም በእርሱ ላይ ያነፀወው ስራ ቢፀናለት ደመወዙን ይቀበላል፤ የማንም ስራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል::"

እነዚህ እውነታዎች የሚያሳዩን ሰዎች የሚፀድቁት በእምነት ቢሆንም የፅድቅ ደረጃቸው ግን የሚወሰነው በወርሀ ስጋቸው በሚያደርጉት ጥረት ነው፣ ገብርኤል፣ ሚካኤል፣ ሱራፌል ... በስልጣን፣ በክብር፣ በስራ ድርሻ ... እንደሚለያዩት ሁሉ በክርስቶስ አምነው የፀደቁ ፃድቃንም ባፈሩት መንፈሳዊ ፍሬ ይለያያሉ::

በአጠቃላይ ስንመለከት በአዲስ ኪዳን ዘመን ፅድቅ የሚገኘው በስራ ሳይሆን በክርስቶስ በማመን መሆኑን፣ በክርስቶስ አምነው የፀደቁት ፃድቃን ግን እንደየስራቸው በመንግሥተ ሰማያት የተለያየ ደረጃ የሚኖራቸው መሆኑን ነው::

በተተካኩት ሁለቱ ኪዳኖች ምክንያት የተተካኩትን ሁለቱን የፅድቅ መንገዶች ልዩነት ሰፋ አድርገን ብንመለከት፣

- የሕግን ፍፅምና በመጠበቅ መፅደቅ የማይቻል መሆኑን፣
- በአዲሱ ኪዳን ሰዎች የሚፀድቁት በክርስቶስን በማመን ብቻ መሆኑን፣
- ሕግ በመጠበቅ መፅደቅና በእምነት መፅደቅ የማይዳበሉ መሆኑን፣
- በአዲስ ኪዳን ዘመን በሕግ ለመፅደቅ መሞከር መርገምት መሆኑን፣
- ሕግ ማፅደቅ ባይችልም ማስኮነን የሚችል መሆኑን፣
- አማኝ ሳያስተውል ለሚያደርገው የሕግ ጥሰት ዋስትና መቀመጡን፣

ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

4.2.3.5.1. <u>የሕግን ፍፅምና በመጠበቅ መፅደቅ የማይቻል መሆኑ</u>

በአዳም መውደቅ ምክንያት የሰው ልጅ ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል እየጎረፉ የነበረ በመሆኑ ምክንያት(ማቴ.25፡41) እግዚአብሔር የሰው ልጆች ከሲኦል የሚያድንትን ዘዴ አቀደ፣ ለዚህም በየዘመናቱ ከተለያዩ ትውልዶች ጋር ቃል ኪዳን በማሰር ሰዎች ቃል ኪዳኑን በመጠበቅ ወደ ገነት የሚገቡበትን መንገድ ሲያዘጋጅ ነበረ፣ በዚህም ከአዳም መውደቅ ቀጥሎ በአብርሃም፣ በኖህ፣ በሙሴና በኢየሱስ በኩል የተለያዩ ቃል ኪዳኖችን በማድረግ ሰዎች ወደ ገነት የሚገቡበትን መንገድ ሲቀይስ ነበረ፡፡

ከዚህ ርዕስ ጋር ወደ ተያያዘው በሙሴ በኩል ስለወረደው ኪዳን ስንመለከት፣ በነሙሴ ዘመን እግዚአብሔር ከእስራኤል ህዝብ ጋር ብሉይ ኪዳንን አደረገ፣ በዚህ ቃል ኪዳን መሠረትም ህዝቡ የወረደለትን ሕግ፣ የአምልኮና የመንፃት ስርዓቶችን በመጠበቅ ፅድቅ የሚያገኝበት አሰራር ዘረጋ፡፡ ነገር ግን ፈጣሪ በሙሴ በኩል ያወረደውን የመፅደቂያ መንገድ አንድም ሰው ማሟላት አልቻለም፣ ሁሉም ሰው ኃጢያተኛ ሆነ፣

- ሮሜ.9፡31 “እስራኤል ግን የፅድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም፡፡”
- ያዕ.2፡10 “ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን <u>በአንዱ</u> የሚሰናከል ማንም ቢኖር <u>በሁሉ</u> በደለኛ ይሆናል …”
- ገላ.2፡10-11 “ከሕግ ስራ የሆኑት ሁሉ ከእርግማን በታች ናቸውና፣ በሕግ መጽሐፍ የተፃፉት <u>ሁሉ</u> ፀንቶ የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው…ማንም በእግዚአብሔር ፊትበሕግእንዳይፀድቅግልፅ ነው”
- ገላ.2፡16 “ስጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ስራ ስለማይፀድቅ …”
- ሮሜ.3፡20 “የሕግ ስራ በመስራት ስጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይፀድቅ ነው…”

በዚህም በሙሴ በኩልም የተደረገው የማፅደቂያ መንገድ አለመስራቱ ተረጋገጠ፣ በዚህም የብሉይ ኪዳኑ ማፅደቂያ መንገድ ተሻረ(ዕብ.10፡9, ዕብ.7፡18-19, ዕብ.8፡7-13)፣

“ሕግን በመጠበቅ መፅደቅ” የተባለው የፅድቅ መንገድ ተዘጋ፣ ቀጥለን የምንመለከተው ሌላ ፅድቅ የሚገኝበት መንገድ ተዘጋጀ።።

4.2.3.5.2. <u>በአዲሱ ኪዳን ሰዎች የሚፀድቁት በክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑን</u>

ብሉይ ኪዳን ሰዎችን ማፅደቅ ባለመቻሉ የሰው ልጅ በኃጢያቱ ምክንያት ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል መጉረፉን ስላልቆመ፣ ፈጣሪ ሰዎች የሚድኑበትን ሌላ ቀለል ያለ መንገድ ቀየሰ፣ ይህም ስለ ሰዎች ኃጢያት የሚያስፈልገውን መስዋዕት ክርስቶስ እንዲከፍልና ሰዎች ደግሞ በዚህ በማመን <u>እንዲያው</u> እንዲፀድቁ፣

- ሮሜ.3፡21-24 “አሁን ግን በሕግና በነብያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ፅድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፣ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፣ <u>በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ፅድቅ ነው</u>፣ ልዩነት የለምና ሁሉም ኃጢያት ሰርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው <u>ቤዛነት በኩል እንዲያው</u> በጸጋው ይፀድቃሉ።።”
- ገላ.2፡16 “... ሰው <u>በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲፀድቅ</u> ...”
- ፊሊጵ.3፡8-9 “... በክርስቶስም በማመን ያለው ፅድቅ ...”
- ሐስ.10፡43 “በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢያቱን ስርየት እንዲቀበል ነብያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።።”
- ዮሐ.3፡18 “በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።።”

እነዚህ እውነታዎች የሚያሳዩን በአዲሱ ኪዳን ፅድቅ የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑን ነው።።

4.2.3.5.3. <u>ሕግ በመጠበቅ መፅደቅና በእምነት መፅደቅ ተተካኪ እንጂ ተዳባይ አለመሆናቸውን</u>

ሁለቱ ኪዳናት ተተካኪ እንጂ ተዳባይ ባለመሆናቸው በሁለቱ ኪዳናት የወረዱት ሁለቱ መፅደቂ መንገዶች ተተካኪ እንጂ ተዳባይ አይደሉም፣ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱሱ፣ “ሕግና እምነት”፣ “ሕግና ጸጋ”፣ “ስራና ጸጋ” በማለት ተተካኪነታቸውን እያነፃፀረ ይነግረናል፡-

- ሮሜ.3፡20-22 “... የሕግ ስራን በመስራት ስጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይፀድቅ ነው ... አሁን ግን በሕግና በነብያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ፅድቅ <u>ያለ ሕግ ተገልጦአል</u>፣ እርሱም ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ፅድቅ ነው ...”
- ሮሜ.4፡2-5 “አብርሃም በስራ ፀድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።። መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ፅድቅ ሆኖ ተቆጠረለት።። ለሚሰራ ደመወዝ እንደ እዳ እንጂ እንደ ጸጋ

አይቆጠርለትም፤ ነገር ግን ለማይሰራ፣ ኃጢያተኛውንም በሚያፀድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ፅድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።"

- ሮሜ4፡13-14 "ለዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተስፋ ቃል በእምነት ፅድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም። <u>በሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኖአል</u> የተስፋውም ቃል ተሽሮአል።"
- ሮሜ.9፡30-33 "... ፅድቅን ያልተከተሉ አህዛብ ፅድቅን አገኙ፣ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ ፅድቅ ነው፤ እስራኤል ግን የፅድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ ሕግ አልደረሱም። ይህ ስለ ምንድር ነው? በስራ እንጂ በእምነት ፅድቅን ስላልተከተሉ ነው፤"
- ሮሜ.11፡5-6 "እንደዚሁም በአሁኑ ዘመን ደግሞ በጸጋ የተመረጡ ቅሬታዎች አሉ። <u>በጸጋ ከሆነ ግን ከስራ መሆኑ ቀርቷልና</u>፤ ጸጋ ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቷል።"
- ገላ.2፡16-21 "ነገር ግን ሰው <u>በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲፀድቅ እንጂ በሕግ ስራ እንዳይሆን አውቀን</u>፣ ሲጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ስራ ስለማይፀድቅ፣ እኛ ራሳችን በሕግ ስራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንፀድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል ... የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፣ <u>ፅድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ</u>"
- ገላ.3፡23-26 "እምነት ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበረ። እንደዚህ በእምነት እንፀድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኗል፣ <u>እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚታችን በታች አይደለንም</u>፣ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤"
- ፊሊጵ.3፡8-9 "... ስለእርሱ ሁሉን ተነዳሁ፣ ክርስቶስን አገኝ ዘንድ፣ በክርስቶስም በማመን ያለው ፅድቅ ማለት <u>በእምነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ያለው ፅድቅ እንጂ ከሕግ ለኔ ያለው ፅድቅ ሳይሆንልኝ</u> ..."
- ኤፌ.2፡8-9 "ጸጋው በእምነት አድኖአችሃል፣ ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ እንጂ ከእናንተ አይደለም፣ <u>ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም</u>።"

እነዚህም እውነታዎችም የሚያሳዩን ሁለቱም መፅደቂያ መንገዶች ተተካኪ እንጂ ተደራራቢ አለመሆናቸውን ነው። በዚህም ቤተክርስቲያኗ የሁለቱ ኪዳናት ተተካኪነት ባለማወቅ ለፅድቅ "የሕግ ፍፅምናና በክርስቶስ *ማመን*" ብላ ያስቀመጠችው ተደራራቢ መፅደቂያ መስፈርቶች ስህተት መሆኑና የአዲስ ኪዳን አማኞች ፅድቅን የሚያገኙት "በክርስቶስ በማመን" ብቻ መሆኑን እንመለከታለን።

4.2.3.5.4. <u>በአዲስ ኪዳን ዘመን በሕግ ለመፅደቅ መሞከር መርገምት መሆኑን</u>

በብሉይ ኪዳን ውል ሰዎች መዳን ባለመቻላቸው አዲስ ኪዳን በክርስቶስ በኩል ተደረገ፣ ይህ ኪዳን ምንም እንኳን ክርስቶስን ብዙ ዋጋ ቢያስከፍለውም የኪዳኑ ዓላማ ወደ ሲኦል የሚጎርፈውን ነፍስ ለመታደግ ነው፣ ይሁን እንጂ ይህንን የክርስቶስን መስዋዕትነት አሳንሶ ወደ ቀደመው አሰራር *መመ*ልከቱ፣ መርገምትም መሆኑን መፅሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣

- ገላ.3፡10-11 “ከሕግ ስራ የሆኑት ሁሉ ከእርግማን በታች ናቸው … ፃድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና …”
- ገላ.5፡4 “በሕግ ልትፀድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል፡፡”
- ዕብ.10፡28-29 “የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለርህራሄ ይሞታል፤ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ እርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያከፋፋ፣ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል፡፡”
- ገላ.2፡21 “የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፣ ፅድቅስ በሕግ በኩል ከሆነ እንግዲያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ፡፡”

በዚህም ክርስቶስን የከፈለውን ዋጋ በማቃለል በሱ ላይ ሌላ ነገር መደረብ የዘላለም ቅጣትን በራስ ላይ መጋበዝ ነው፡፡

4.2.3.5.5. <u>ሕግ ማፅደቅ ባይችልም ማስኮነን የሚችል መሆኑን</u>

ሰዎች ሕግን በፍፅምና ጠብቀው ሊኖሩበት አይቻሉ እንጂ፣

- <u>በአዲሱ ኪዳን ህጉ አልተሻረም</u>

  ማቴ.5፡18 “እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈፀም ድረስ፡፡”
- <u>ህጉ አሁንም ቅዱስ ነው</u>

  ሮሜ.7፡12 “… ህጉ ቅዱስ ነው ትእዛዙም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት፡፡”
- <u>ህጉ ዛሬም ያስፈልጋል</u>

  ሮሜ.3፡20 “… ኃጢያት በሕግ ይታወቃልና፡፡”
- <u>ህጉን የተላለፈ ኃጢያተኛ ስለሚሆን ህጉ ዛሬም ሰዎችን ማስኮነን ይችላል</u>

  ሮሜ.6፡23 “የኃጢያት ደመወዝ ሞት ነውና …”

በዚህም ሰዎች ሕግን ጠብቀው በህጉ መፅደቅ ባይችሉም፣ ሕግ ግን ሰዎችን ማስኮነን እንደሚችል እንመለከታለን ነገር ግን በክርስቶስ አምኖ የፀደቀ ሰው ሕግን ተላልፎ ኃጢያት ቢሰራ ምን ይሆናል የሚለውን ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

4.2.3.5.6. <u>አማኝ ሳያስተውል ለሚያደርገው የሕግ ጥሰት ዋስትና መቀመጡን</u>

ብዙዎችን ግራ የሚያጋባውና ሁለቱንም መፅደቂያ መንገድ እንዲይዙ ያደረገው፣ በክርስቶስ አምነው የፀደቁ ሰዎች ሕግን ቢተላለፉ ዕጣ ፋንታቸው ምንድነው? የሚለው ነው፣ ይህንን ለመረዳት ከመነሻው፣ ፣1ዮሐ.1፡8 “ማንም ኃጢያት የለብኝም የሚል ይዋሻል” የሚለውን እውነታ ማስተዋል ያስፈልጋል፡፡

በዚህም ሁሉም ሰው ኃጢያት አለበት ነገር ግን አማኝ **በተቻለው መጠን** ራሱን ከኃጢያት ገድቦ እየኖረ <u>ሳያስተውል ወይንም ከአቅሙ በላይ በሆነ ምክንያት</u> ለሚሰራው ኃጢያት <u>የኢየሱስ አማላጅነት</u>(1ዮሐ.2፡1) እና <u>የእግዚአብሔር ምህረት</u>(ዕብ.8፡12) ከኩነኔ ያድኑታል፡፡

> 1ዮሐ.2፡1 “ልጆቼ ሆይ፣ <u>ኃጢያትን እንዳታደርጉ</u> ይህን እፅፍላችኃለሁ፡፡ ማንም ኃጢያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፣ እርሱም ፃድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡”

ይህ ተፈጥሮአዊውን ሰውኛ ማንነት ያገናዘበ እውነታ ነው፣ አንድ በክርስቶስ አምኖ የፀደቀ ሰው እንዳመነ መልአክ አይሆንም የነበረውን የኃጢያት ህይወት እየተላቀቀ የሚሄደው በሂደት ነው፣ ይህ አባባል ግን “እምነት አለኝ ሕግ አያስፈልገኝም” ከሚለው ያዕቆብ ካወገዘው ትዕቢተኛ ሰው ለይቶ ማየት አስፈላጊ ነው ምክንያቱም ሲጀምር “ወንድሞቼ ሆይ ኃጢያትን አታድርጉ” ብሎ ስለሚጀምር፡፡

በእምነት መፅደቅ እንደ የዩኒቨርሲቲ እስኮላርሺፕ እድል ነው፣ የእስኮላርሺፕ እድል አግኝቶ ዩኒቨርሲቲ የገባ ሁሉ አይመረቅም፣ ወድቆ የሚባረር አለ(ራዕ.3፡16)፣ የሚመረቀውም በተመሳሳይ ነጥብ አይመረቅም፣ በማዕረግ የሚመረቅ አለ፣ ውራ ሆኖ የሚመረቅ አለ(ዝርዝሩን በ6.4.1.4 ክፍል፣ 1ዮሐ5፡16-17 እና 1ቆሮ.11፡12 ይመልከቱ)፡፡

<u>በአጠቃላይ ስንመለከት፣ በአዲሱ ኪዳን፣ ሰው የሚፀድቀው በክርስቶስ በማመን ብቻ መሆኑን ነው</u>፣ “በክርስቶስ ማመን” የሚባለው አራቱ ዋልታዎች ደግሞ ምን ምን እንደሆኑ በ6.4.1.2 ክፍል በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

4.2.4. <u>ቤተክርስቲያኗ ሁለቱን ኪዳናት ባለማተካካቷ ያጣቻቸው የክርስትና እሴቶች</u>

ከላይ እንደተመለከትነው በቤተክርስቲያኗ ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳኑ ስፍራ ባለመልቀቁ ምክንያት ቤተክርስቲያኗ ከመሠረታዊ የክርስትና ዕሴቶች ይህም መንፈስ ቅዱስን መቀበል፣ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎችን መቀበል፣ ክርስቲያናዊ ማህተብ፣ የኢየሱስ ስም ስልጣን እና ዳግም መወለድ ጋር እንግዳ ሆናለች፣ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፣

4.2.4.1. <u>መንፈስ ቅዱስን መቀበል</u>

ሰዎች በክርስቶስ ሲያምኑ ከሚያገኙት ጥቅሞች ዋነኛው መንፈስ ቅዱስን መቀበል ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱን ስንመለከት ሰዎች በክርስቶስ በማመን መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ነበረ፤ ነተሰ.4፡8, ሐስ.8፡15-17, ሐስ.10፡44, ሐስ.19፡6, ሉቃ.11፡13, ዮሐ.20፡22, ሐስ.1፡8, ሐስ.4፡8, ሐስ.4፡31, ሐስ.5፡32, ሐስ.6፡3-5, ሐስ.13፡52, ነዮሐ.4፡13 ...

መንፈስ ቅዱስን መቀበል ጥቅሙ ብዙ ነው፣ በመጀመሪያ የእግዚአብሔር ልጅነት ምስክር ነው(ሮሜ.8፡16)፣ መንፈስ ቅዱስ የሰዎችን ድካም ያግዛል(ሮሜ.8፡26)፣ ኃይልን ይሰጣል(ሐስ.1፡8)፣ የአማኝ መለያ ማህተም ነው(ኤፌ.4፡30)፣ የመዳን ዋስትና ነው(ኤፌ.1፡14)፣ የተለያዩ ጸጋዎችን ይሰጣል(ነቆሮ.14)፣ በአጠቃላይ መንፈስ ቅዱስ በአንድ ሰው ላይ መውረድ ሰውየውን ሙሉ የእግዚአብሔር ልጅ ያደርገዋል፡፡

ነገር ግን ቤተክርስቲያኒቷ አዲሱን ኪዳን ባለመቀበሏ "መንፈስ ቅዱስን መቀበል" ከሚባለው ዋነኛው የክርስትና ዕሴት ጋር በታሪክ እንጂ በተግባር አትተዋወቅም፣ ምክንያቱም፣

- ቤተክርስቲያኗ የኢየሱስን የምልጃና የአዳኝነት አገልግሎት ስላላገኘችና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በኢየሱስ ስራ ያልፀደቀ ላይ ስለማያርፍ፣
- "በኢየሱስ በማመን" መፅደቅን ጎዶሎ በማድረግ በስራ ለመፅደቅ እየሞከረች በመሆኗ፣ ይህ ደግሞ መርገምት ስር እንድትወድቅ ያደረጋት መሆኑ፣
- በቁሳዊው ፅላት ፋንታ ሰጋዊውን ፅላት እንደዚሁ በግንባታው ቤተመቅደስ ፋንታ የሰጋው ቤተመቅደስ ስላላተካካች፣ የመንፈስ ቅዱስ ማረፍያ ቅዱስ ስፍራ ያላዘጋጀች መሆኑን፣
- መንፈስ ቅዱስ ቅድስና የሌለውን ስፍራ የማይወድ መሆኑና በቤተክርስቲያኗ ደግሞ ሰይጣን በስውር በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም እየተመለከ መሆኑ፣ በ4.4.2 ክፍል እንደተመለከተው ጣኦቶች በቅድስና ስም ተጠቅልለው በቤተክርስቲያን መገኘታቸው፣ የሰይጣን ኤጀንቶች ቤተክርስቲያኗን መውረር...

በነዚህ ምክንያቶች ለቤተክርስቲያኗም ሆነ ለምዕመናኖቿ "በመንፈስ ቅዱስ መሞላት" የሚለው ቃል የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ እንጂ በዚህ ዘመን ለአማኝ የሚሰጥ ጸጋ

አይመስላቸውም፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗም ሆነች ተከታዮቿ በመንፈስ ቅዱስ በመሞላት ከሚገኙት በረከቶች ጎድለው እንመለከታለን፡፡

4.2.4.2. <u>የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎችን መቀበል</u>

"ጸጋ" ማለት አምላካዊ ስጦታ ማለት ነው፣ መንፈስ ቅዱስም አምላክ በመሆኑ ሰዎች ላይ ሲያርፍ ለሰዎች የተለያዩ ጸጋዎችን ይሰጣል፣ እነዚህም ጸጋዎች ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ... የመሳሰሉት ሲሆኑ፣ እነዚህ ጸጋዎችም ለአማኞች ሲሰጡ እንደነበረ በመጽሐፍ ቅዱሱ በተለያዩ ስፍራዎች ላይ እንመለከታለን (1ቆሮ.14, ሐስ.2፡4, ሐስ.2፡38, ሐስ.10፡38, ሐስ.11፡24, ሐስ.19፡6, 1ቆሮ.12፡7 ...)

በርግጥ ከላይ እንዳየነው መንፈስ ቅዱስ ከነሱ ጋር ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋዎችን መጠበቅ አይቻልም፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ የጸጋ ስጦታዎች በታሪክ እንጂ በተግባር አታውቃቸውም፣ በዚህም አገልጋዮችዋ የታሪክ መምህራን ሆነው የቀሩባት ቤተክርስቲያን ሆናለች፣ ይህም መጽሐፍ ቅዱሱ፣

2ጢሞ.3፡5 "የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል ..."

በማለት የገለፃቸው አይነት ቤተክርስቲያን ሆናለች ይባሱኑ ደግሞ አሁን ባለንበት በመጨረሻው ዘመን፣

ሐስ.2፡17 "በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ስጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆች ትንቢት ይናገራሉ ..."

ከሚለው ቃል ጋር በተቃርኖ እየሄደች ትገኛለች፡፡

በዚህም ቤተክርስቲያኗ ከጸጋ ስጦታው ጎድላ እንዲሁም ከመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር እቅድ ጋር ጀርባ ለጀርባ ተቀምጣለች፡፡

4.2.4.3. <u>ክርስቲያናዊ ማህተብ</u>

የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በመተላለፏ ምክንያት ከክርስቲያናዊው ማህተብም ጋር ተላልፋለች፣ የክርስቲያን ማህተብ በመንፈስ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት የሚታተም ማህተብ ሲሆን(ኤፌ.1፡13፣ ኤፌ.4፡30 ...) ቤተክርስቲያኗ ግን ከዚህ ማህተብ ጋር ስለማትተዋወቅ ለክርስትና ማህተብ የክርን ማህተብ እየተጠቀመች ትገኛለች፡፡

4.2.4.4. <u>የኢየሱስ ስም ስልጣን</u>

በአዲስ ኪዳን ዘመን ሰዎች መንፈሳዊውን ኃይል መጠቀም እንዲችሉ የተሰጣቸው ቃል(ፓስወርድ) "የኢየሱስ ስም" ነው፣

- ማር.16፡17 "... በስሜ አጋንንት ያወጣሉ፣ በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ፣ እባቦችን ይይዛሉ፡፡"

- ፊልጵ.2፡10 "... በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፡፡"
- ነቆላ.3፡17 "... በቃል ቢሆን ወይንም በስራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት፡፡"

በዚህ ትዕዛዝ መሠረትም ሐዋርያቱ "በኢየሱስ ስም" አጋንንት ሲያወጡ(ሐስ.16፡18)፣ ሲፈውሱ(ሐስ.3፡6) እና የተለያዩ ስራዎችን ሲሰሩ ነበረ፡፡

ዛሬ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን አዲስ ኪዳኑ ስፍራ ባለመያዙ ምክንያት ይህ "የኢየሱስ ስም" ስልጣን አይታወቅም፣ ምዕመናኖቿም "በኢየሱስ ስም" የሚል ሰውን እንደ "መናፍቅ" ነው የሚመለከቱት፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ምን ያህል ከአዲስ ኪዳኑ ጋር እንደተላለፈች እንመለከታለን፡፡ ከዚህ በላይ የከፋው ደግሞ ቤተክርስቲያኗ የተሰጣትን መንፈሳዊ ኃይል ይህም የኢየሱስን ስም ስልጣን መጠቀም ባለመቻሏ ምክንያት ሌላ መንፈሳዊ ኃይል ይህም አጋንንታዊ ኃይልን እንደ አማራጭ የኃይል ምንጭ እየተጠቀመች ትገኛለች፣ በ4.4.2.5 ክፍል በስፋት ተመልክቷል፡፡

4.2.4.5. <u>ዳግም መወለድ</u>

በቤተክርስቲያኗ "ዳግም መወለድ" የሚባለው ቃል እንግዳ ነገር ነው ነገር ግን ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀረ መንግሥተ ሰማያት ሊገባ አይችልም፣

> ዮሐ.3፡3-15 "ኢየሱስም መልሶ፡፡ እውነት እውነት እልሀለሁ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው ... ሰው ከውሀና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም..."

ዳግም መወለድ በዋናነት ሁለት መሠረታዊ ሐሳቦችን ይይዛል፣ ከውሀ መወለድና ከመንፈስ መወለድ፡፡ ከውሀ መወለድ የሚለው የውሀ ጥምቀትን ያሳያል፣ በቤተክርስቲያኗ የጥምቀት ስርዓት እንደሚከናወን ይታወቃል በ4.4.1.3 ክፍል ከተገለፀት መስተካከል ከሚገባቸው ነገሮች በስተቀረ፣ ነገር ግን ከመንፈስ መወለድ የተባለው ለቤተክርስቲያኗ እንግዳ ነገር ነው ምክንያቱም ከላይ እንዳየነው ቤተክርስቲያኒቷ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ግንኙነት ስለሌላት፡፡ በዚህም "ዳግም መወለድ" የሚባለው የክርስትና መሠረት በቤተክርስቲያኗ ተከታዮች ዘንድ አለመሟላቱን እንመለከታለን፣ ዳግም ያልተወለደ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት አይወርስም፣ ይህ የቤተክርስቲያኗ ምዕመናን አሳዛኝ መጨረሻ ነው፡፡

ማጠቃለያ (ብሉይ ኪዳን በአዲስ ኪዳን የተተካበትን ምስጥር አለማግኘት)

ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የብሉይና አዲስ ኪዳን አንድነትና ልዩነት መለየት ባለመቻልዋ ምክንያት አሮጌው አሰራር ለአዲሱ አሰራር ስፍራ ባለመልቀቁ፣ አዲሱ ኪዳን ስፍራውን መያዝ አልቻለም፣ በዚህም ምዕመናኖቿ ከርስቶስ በመስቀል ላይ የከፈለውን ቤዛ ማግኘት አልቻሉም::


ከሁሉ የሚገርመው ደግሞ ነገሮች ምን ያህል የተያያዙ መሆናቸው ነው፣

- መንፈሳዊውን የሰውን ቤተመቅደስነት ባለማወቅ የህንፃውን ቤተመቅደስ ይገነባሉ፣ ፅላቱ የሰው ልብ መሆኑን ባለማወቅ ከእንጨት ፅላትና ታቦት ይሰራሉ፣ የመንፈስ ቅዱስን ማህተብ ትተው የክር ማህተብ ያስራሉ ... በአጠቃላይ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መተዋወቅ አልቻሉም::
- ለታቦቱና ለቤተ መቅደሱ አስተናጋጅ ሊቀካህን ይሾማሉ፣ በዚህም ለኃጢያት ስርየት የቆመው የሊቀ ካህኑን ኢየሱስን የምልጃ አገልግሎት ማግኘት አልቻሉም፣
- የቀኑ ሰንበት ስፍራውን ባለመልቀቁ በክርስቶስ ሰንበትነት(እረፍትነት) ማረፍ አልቻሉም፣

በአጠቃላይ ቤተክርስቲያኗ አዲሱን ኪዳን ባለመቀበሏ ምዕመኖቿ በክርስቶስ በኩል የመጣውን ድነት እንዳልተቀበሉ እንመለከታለን፣፣ መጨረሻውም የነፍስ ጥፋት ነው::

4.3. <u>ያልተቀደሱ “ቅዱሳን መጽሐፍት”</u>


በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ከዋናው መጽሐፍ ቅዱሱ በተጨማሪ ብዙ ያልተቀደሱ መጽሐፍት የቤተክርስቲያን መመርያ መጽሐፍ ተደርገዋል፣ እነዚህ መጽሐፍትም ቅዱስ ባለመሆናቸው በውስጣቸው ብዙ አነጋጋሪ፣ አሳፋሪና አሳሳች አስተምህሮችን ይዘዋል። ለምሳሌ ያህል የተወሰኑትን በ “Screen Shot” ብንመለከት፣



ጌድዐ ፡ ተክል ፡ ሃይማኖት ።

፲፪ ፤ ወነሱ ፡ ዘተቀብረ ፡ ውስተ ፡ መካነ ፡ መቃ ብረ ፡ ኢይትነሣእ ፡ በጎቤየ ፡ ወኢይሬኢ፡ ዩደነ ፡ ወነሱ ፡ ዘኢተጽሕፈ ፡ ስሙ ፡ ውስተ መጽሐፈ ፡ ሕይወት ፡ ኢይትቀበር ፡ ውስተ፡ መካንኪ፡ ወነሱ፡ ዘተቀብረ፡እምፈለገ፡ ጉርዔ፡ እስከ ፡ ፈለገ ፡ ሽምን ፡ መሐርኩ ፡ ለከ ፡ ወወ ሀብኩከ ፡ ኪዳንየ ፡ ይኩንክ ፡ ዘለዓለም ።

፲፪ ፤ አንተ ፡ ክተቀበርክበት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ሀም ፡ በታነጸበት ፡ ቤታ ፡ የተቀበረ ፡ ሁሉ ፡ በኔ ፡ ዘንድ ፡ አይጎዳም ፡ ገሃነመ ፡ እሳትንም፡ ከቶ ፡ አያይም ፡ ስሙ ፡ በሕይወት ፡ መጽ ሐፍ ፡ ያልተጻፈውም ፡ ሁሉ ፡ በቦታህ ፡ አይ ቀበርም ፡ ከጉር ፡ እስከ ፡ ሽምን ፡ ወንዝ ፡ የተ ቀበረውንም ፡ ሁሉ ፡ ምፌልሃለሁ ፡ ላንተም፡ ለዘለዓለም ፡ መታሰቢያ ፡ ይሆንልህ ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ ለጠሁህ ።




ሯ፫ ፤ ወናሁ ፡ ትመውት ፡ በሕማመ ፡ ብድብድ ፡ በእ ኩይ ፡ ሞት ፡ ወእራሲ ፡ ለከ ፡ ኪያሃ ፡ ከመ ስቅስትየ ፡ ወከመ ፡ ደመ ፡ ሰማዕት ፡ እለ ፡ እምቅድሜከ ፡ እኮ ፡ ለባሕቲትከ ፡ አላ ፡ ደቂ ቅከኒ ፡ እለ ፡ ይመውቱ ፡ በሕማመ ፡ ብድብድ በውስተ ፡ ዛቲ ፡ ገጻም ፡ እኁልቁመ ፡ ምስለ ሰማዕታት ፡ ወእወፍሮሙ ፡ ለከ ፡ በመንግ ሥተ ፡ ሰማያት ።

ሯ፬ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ዕዓሞ ፡ ሥልሰ ፡ ወወሀበ ፡ ሰላመ ፡ ወዓርገ ፡ ሰማየ ፡ ወእምዝ ፡ አስተ ጋብያመ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለሁሎሙ ፡ ደቂቁ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ናሁ ፡ ቀርበ ፡ በዓለ ፡ መርዓ ፡ ተደለዉ ፡ ለሐዊር ፡ ወተሰርገዉ ፡ በልብሰ ፡ መርዓ ።

ሯ፫ ፤ እኁሃ ፡ በክፉ ፡ ሞት ፡ በተቅማጥ ፡ በሽታ፡ ጎሞታስሃ ፡ ኀቢንም ፡ እንደሰቅልቲና ፡ ካንተ ፡ በፊት ፡ እንደነበሩ ፡ ሰማዕታት ፡ ደም ፡ ኀቄዋርልሃለሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለብቻህ፡ አይደለም ፡ በዚች ፡ ገጻም ፡ በተቅማጥ ፡ በሽታ ፡ የማሞትን ፡ ልጆችህንም ፡ ቍጥ ራቸውን ፡ ከሰማዕታት ፡ ጋራ ፡ አደርጋለሁ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ላንተ ፡ አሰጣቸ ዋለሁ ፡ አለው ።

ሯ፬ ፤ ይህንንም ፡ ተናግሮ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ስሞት፡ ሰላምታ ፡ ሰጥቶት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይ ማኖት ፡ ልጆቹን ፡ ሁሉ ፡ ሰብስቦ ፡ ንኑሆ ፡ የሙሽርኑቱ ፡ በዓል ፡ ንኑሆ ፡ ቀረበ ፡ የሠርግ ልብስ ፡ በመልበስ ፡ ተሸልማችሁ ፡ ለመሄድ፡ ተዘጋጁ ።




ተወቢ ፡ እምኵሉን ፡ አንስት ።
ሽኔ ፤ ሕሊናሃ ፡ ለእግዝእትነ ማርያም ፡ ሕሊና ፡ አምላክ ።
ሽኔ ፤ ወነሱ ፡ መልክአ ፡ ለ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ መልክ አ ፡ አምላክ ።
ሽኔ ፤ እግዝእትነ ፡ ማርያም ፡ ቀደበቶ ፡ ለአምላክ ፡ በንጽሕ ናሃ ።

ከሉቶች ፡ ሁሉ ፡ ትበልጣለች ።
ሽኔ ፤ የመቤታችንማርያም ፡ አሳብ ፡ አንደ ፡ አምላክ ፡ አሳ ብ ፡ ነው ።
ሽኔ ፤ የመቤታችን ፡ማርያም ፡ መልኳ ፡ አንደ ፡ አምላክ ፡ መ ልክ ፡ ነው ፡ የአምላክን ፡ መል ክ ፡ ይመስላል ።
ሽኔ ፤ እመቤታችን ፡ ማርያ ም ፡ ንጽሕት ፡ በሆኑዋ ፡ አም ላክን ፡ እንዲያድርባት ፡ አደ ረጋችው ።

እስመ ፡ ይእቲ ፡ መድኃኒትክሙ ፡ ወቅድመ ፡ ሥዕላ ፡ ስግ ዱ ፡ ዘኢሰገደሰ ፡ ላቲ ፡ ይደም ሰስ ፡ እምቅዋመ ፡ ወኢ ይትወ ወቅ ፡ ዝክረ ፡ ስሙ ።
ወኔ ፤ ወይበሉ ፡ መላእክተ፡ ሰማይ ፡ ሁሉሙ ፡ አሜን ።

እቲ ፡ መድኃኒታችሁ ፡ናትና ።
ወኔ ፤ በሥዕሏም ፡ ፊት ፡ ስገ ዱ ፡ ለሥዕሏ ፡ ይሰገደ ፡ ግን ከቆመበት ፡ በታ ፡ ይጥፋ ፤ ስም አጠራሩም ፡ አይታወቅ ።
ወኔ ፤ በሰማይ ፡ ያሉ ፡ መላእ ክትም ፡ይደረግ ፡ይሁን ፡ይበሉ ፤

ለኢመቤታችን ፡ ክንጸቅ ፡ እንኋለ ።
ኔ ፤ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ እሰግድለ ሻለሁ ።



እነዚህ ለምሳሌ ያህል ከገድለ ተክለ ኃይማኖት፣ ከተአምረ ማርያምና ከራዕየ ማርያም የቀረቡት ምሳሌዎች ውስጥ የአቡነ ተክለኃይማኖት ቅዘን ከከበረው የኢየሱስ ደም ጋር የተካከለበት፣ ሰው የሚድነው በእምነት ሳይሆን በተክለኃይማኖት ቤተክርስቲያን በመቀበር እንደሆነ፣ ማርያም እግዝእትነ(እግዚአብሔራዊ ማንነት እንዳላት)፣ ለማርያም ስዕል መስገድ እንደሚገባ፣ አንዳንድ ብሔሮች እንደ ብሔር ገነት መግባት እንደማይችሉ ያትታሉ::

እነዚህን እውነታዎች ስንመለከት እነዚህ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ውጪ ያሉት መጽሐፍት ለምን የቤተክርስቲያን መመርያ መፅሐፍት እንደተረጉ በግልፅ እንረዳለን:: የነዚህ መጽሐፍት ዓላማም በ4.1 ክፍል የተመለከተውን አምልኮተ ማርያም/ቅዱሳን/መላዕክት ለማስረፅ፣ የኢየሱስን አዳኝነት ለማሳነስ፣ ለማንቋሸሽና ለመጋረድ እንደዚሁ የክርስትና ኃይማኖትን የተረት ተረት ኃይማኖት ለማስመሰል ነው::

ቤተክርስቲያኗ ከዋናው መጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ለመመርያነት የምትጠቀምባቸውን ሁሉንም መጽሐፍት በዚህ መልክ መዳሰሱ እጅግ ሰፊ ጉዳይ በመሆኑ በዚህ ክፍል ከቤተክርስቲያኗ መመርያ መጽሐፍት ውስጥ በዋናነት የሚታዩትንና ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር እንኳን እንዲቀላቀሉ የተደረጉትን የመጽሐፍ ቅዱሱን ተጨማሪ መጽሐፍት ብቻ እንመለከታን::

*መ*ጽሐፍ ቅዱስ ማለት ቅዱሳን በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት የፃፏቸው መጽሐፍት ስብስብ ነው (ዘጸ.17፡14, ዘጸ.34፡27, ዘኍ.33፡2, ዘዳ.27፡8, ኢሳ.8፡1, ኢሳ.30፡8, ኤር.30፡2, ኤር.36፡1, ኤር.36፡2, ኤር.36፡28, ሕዝ.24፡2, ዕን.2፡2, ራዕ.1፡9, ራዕ.2፡1 ...)፡፡ ሁሉም የክርስትና ተቋማት የጋራ 66 መጽሐፍት የያዘ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ሲሆን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ዘንድ በነዚህ 66ቱ መጽሐፍት ላይ ተጨማሪ መጽሐፍት ተጨምረዋል፣ እነዚህ መጽሐፍት በኦርቶዶክስ አዋልድ(የቀኖና ልጅ) ሲባሉ፣ በካቶሊክ ዲዩትሮካኖኒካል(ሁለተኛ ቀኖና) ሲባል፣ አፖክሪፋ በማለት የሚጠሩትም አሉ፡፡

ቤተክርስቲያኗ እነዚህ ተጨማሪ መጽሐፍት/አዋልድ/ዲዩትሮካኖን በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ በመጨመር በአንድ መጽሐፍ ቅዱሱ ለማሳተሚ የተለያዩ ምክንያቶች ታቀርባለች፣ ዋነኞቹም፣

1. በሌሎቹ ቅዱሳን መጽሐፍት ውስጥ የማናገኛቸው ታሪኮች በነዚህ መጽሐፍት ውስጥ ስለምናገኝ መጽሐፍቱ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ቢጠቃለሉ "እውቀታችንን ሙሉ ያደርጋሉ" በሚል፣
2. ዮሐ.20፡30 "ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ" ስለሚል ተጨማሪ መጽሐፍትን ብናስተናግድ ችግር የለውም በሚል፣
3. ይሁ.1፡14-15 "ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ፣ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፣ በኃጢያተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢያተኛ ስራቸው ሁሉ አመፀኞችም ኃጢያተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭከና ነገር ሁሉ ኃጢያተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአዕላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ፡፡" እንደሚለው የሄኖክ መጽሐፍ ለመጨመሩ ምክንያታዊ ነው በሚል፣
4. 2ጢሞ.3፡16-17 "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡" በሚለው ቃል መሠረት የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን መጽሐፍትን መጨመር ይቻላል በሚል ነው፡፡

እነዚህን መስፈርቶችም ከነዚህ ተጨማሪ መጽሐፍቱ ጋር እያነፃፀርን በዝርዝር እንመለከታለን፤ ለንፅፅር የምንጠቀመው በቀደሙት የኃይማኖት አባቶች የተዘጋጀውን ተጨማሪ መጽሐፍቶችን የያዘውን የ1980 መጽሐፍ ቅዱስ ነው፣ ከሱ በኋላ አቡነ ጳውሎስ ያሳተሙት የ2,000 ህትመት ከታች እንደምንመለከተው፣ የቀደውን መጽሐፍ ቅዱስ ኤዲት በማድረግ የመጨመር፣ የመቀነስ፣ ቃላት የመቀየርና የማደባለቅ ስራዎች ስለሰሩበት መጽሐፉን በእግዚአብሔር ቃልነት መቀበል አዳጋች ነው፡፡

ስለዚህ ለማነፃፀሪያነት ቤተክርስቲያኗ ከአቡነ ጳውሎስ በፊት አሳትማ ስትጠቀምበት የነበረውን የቀደመውን የ1980 መጽሐፍ ቅዱስ እንጠቀማለን፡፡

4.3.1. <u>“እውቀታችንን ሙሉ ያደርጋሉ” መስፈርት</u>

ቤተክርስቲያኗ ስለ ተጨማሪ መጽሐፍቱ መጨመር ትክክለኛነት የምታስረዳው “በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ሳይነገሩ የተዘለሉ ታሪኮች በነዚህ ተጨማሪ መጽሐፍት ላይ ስለምናገኛቸው ተጨማሪ መጽሐፍቱ ከ66ቱ ጋር አብረው መቅረባቸው እውቀታችንን ሙሉ ያደርግልናል” በሚል ምክንያት ነው፡፡

ነገር ግን ተጨማሪ መጽሐፍቱ የተፃፉበትን ምክንያት የነደለ ነገር ኖሮ ያንን ሙሉ ለማድረግ ሳይሆን፡-

> ዕዝራ ሱቱኤል 13፡21-46 “ኦሪት ጠፍታለችና የሰራሃውን ስራ ትሰራው ዘንድ ያለህንም የሚያውቀው የለም፡፡ በፊትህስ ባለሟልነት ካገኘሁ መንፈስ ቅዱስን ላክልኝና ከጥንቱ ጀምሮ በዚህ ዓለም የሆነውን ሁሉ ልፃፍ … መለሰልኝም … በነዚያው በአርባ ቀኖች ሀያ አራት መጽሐፍት ተፃፉ፡፡”

በማለት ተጨማሪ መጽሐፍቱ ለምንና እንዴት እንደተፃፉ መናገሩ፣ ከላይ የቀረበውን መከራከሪያ ውድቅ ያደርጋል፣ ኦሪት አለመጥፋትዋና እስከዛሬም ድረስ መኖሯ ደግሞ በዕዝራ ሱቱኤል ላይ የተነገረውን የተጨማሪ መጽሐፍት አስፈላጊነትን መከራከሪያ ተመልሶ ውድቅ ይሆናል፡፡

ከመሠረቱ ስንመለከትም ይህ “እውቀታችንን ሙሉ ያደርጉልናል” የሚለውና መጽሐፍ ቅዱሱን በጎዶሎነት የሚመለከት መንፈስ ክርስቲያናዊ አይደለም፣ ክርስቲያናዊው መንፈስ መጽሐፍ ቅዱሱን ሙሉና በቂ አድርጎ የሚቀበል መንፈስ ነው፣

> ዮሐ.20፡31 “ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተፅፎአል፡፡”

ይህንን የእግዚአብሔርን ቃል የማይቀበልና መጽሐፍ ቅዱሱን ጎዶሎ አድርጎ የሚመለከት ክክርስትና የነደለ ሰው ብቻ ነው፡፡

4.3.2. <u>በዮሐ.20፡30 መስፈርት</u>

ዮሐ.20፡30 “ኢየሱስ በዚህ መጽሐፍ ያልተፃፈ ሌላ ብዙ ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ” የሚለውን ቃል ምክንያት በማድረግ መጽሐፍቱን መጨመር “መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው” ይባል እንጂ፣ ተጨማሪ መጽሐፍቱ በዚህ መሠረት አልተጨመሩም ምክንያቱም ይህ ክፍል የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ተአምራቶች ነው ነገር ግን ተጨማሪ መጽሐፍቱ የቀረቡት የብሉይ ኪዳን ተጨማሪ መጽሐፍት ተደርገው ነው፡፡

በተጨማሪም ከላይ የቀረበውን ቃል ቀጥለን ስናነብ ዮሐ.20፡31 “ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንለችሁ ዘንድ <u>ይህ ተፅፎአል</u>፡፡” ማለቱ ደግሞ የኢየሱስ ተአምራት ተብለው እንኳን ሌላ መጽሐፍት ተፅፈው ቢመጡ ተቀባይነት እንዳንሰጣቸው ነው የሚነግረን፡፡

ይህም ቃል ዛሬ በሐዋርያት ስም “የጴጥሮስ ወንጌል፣ የያዕቆብ ወንጌል፣ የበርናባስ ወንጌል …” እየተባሉ በግለሰቦች እየተዘጋጁ ያሉት መጽሐፍት እንኳን የሚስተናገዱበት መንገድ አለመኖሩን ያሳየናል።

4.3.3. በይሁ.1፡14-15 መስፈርት

ይሁ.1፡14-15 “ከአዳም ጀምሮ ሰባተኛ የሆነው ሄኖክ፣ እነሆ ጌታ በሁሉ ላይ እንዲፈርድ፣ በኃጢያተኝነትም ስላደረጉት ስለ ኃጢያተኛ ስራቸው ሁሉ አመፀኞችም ኃጢያተኞች በእርሱ ላይ ስለ ተናገሩ ስለ ጭካና ነገር ሁሉ ኃጢያተኞችን ሁሉ እንዲወቅስ ከአዕላፋት ቅዱሳኑ ጋር መጥቶአል ብሎ ለነዚህ ደግሞ ትንቢት ተናገረ።”

በዚህም ቤተክርስቲያኗ “ተጨማሪ መጽሐፍቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድጋፍ አላቸው” ትላለች ነገር ግን ይህንን ቃል እንደ መከራከሪያነት ማቅረብ የሚቻለው ከ15ቱ ተጨማሪ መጽሐፍት ውስጥ አንዱ ለሆነው ለሄኖክ መጽሐፍ እንጂ ለሌሎቹ ተጨማሪ መጽሐፍት መሆን አይችልም።

“መጽሐፈ ሄኖክ” ተብሎ የተጨመረውን መጽሐፍም ስንመለከት፣ መጽሐፉ እንደሚናገረው፣ ይህን መጽሐፍ የፃፈው የአዳም ሰባተኛ ልጅ፣ የያሬድ ልጅ (ሄኖክ 9፡1)፣ የማቱሳላ አባት (ሄኖክ 42፡1) በሆነውና ወደ ሰማይ የተነጠቀው(ሄኖክ 4፡1) ሄኖክ መሆኑን ይናገራል። ሄኖክም እውቀቱን ያገኘው መላዕክት ባሳዩት ራዕይ መሆኑን በመጽሐፉ መጀመሪያ ሄኖክ 1፡2 እና መጨረሻ ሄኖክ 42፡16 ላይ ተገልጿል። ሄኖክም ያየውን ራዕይም ለሰዎች ያስተማረው በማቱሳላ ዘመን መሆኑን(ሄኖክ 34፡35-37)፣ የሚገለጠውም በእግዚአብሔር (ሄኖክ 4፡66-69, ሄኖክ 5፡4 …) እና በመላዕክት(ሄኖክ 4፡5-7, ሄኖክ 27፡15-18) ኃይል መሆኑን ይገልፃል።

ነገር ግን መጽሐፉን በዝርዝር ስንመለከተው በውስጡ ብዙ ችግሮችን ይዟል፣ የመጽሐፉ መቼት(የድረጊቱ ጊዜና ስፍራ) ይፋለሳል እንዲሁም ከ66ቱ መጽሐፍት በተለየ ቅድስና የሌለውና በውስጡ ብዙ ውሸቶችን የያዘ መጽሐፍ ነው፣ ቀጥሎ በዝርዝር ቀርቧል፣

4.3.3.1. የመጽሐፉ መቼት የተፋለሰ ነው

መጽሐፈ ሄኖክ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ እንደሆነ ተደርጎ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍትነቱ ቢቀርብም፣ መጽሐፉ ግን እስከ ሐሳዊ መሲህ(ሐሰተኛው ክርስቶስ) ድረስ ያለውን የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪክ ቀንጨብ ቀንጨብ አድርጎ የያዘ መጽሐፍ ነው(ለምሳሌ ከሄኖክ ምዕራፍ 32 እስከ ሄኖክ 34፡29 ይመልከቱ)

ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፉ የተፃፈው በአዲስ ኪዳን እውቀት እንጂ በብሉይ ኪዳን እውቀት አለመሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ምልክቶችን ይታዩበታል፣ በየትኛውም የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ውስጥ የማናገኛቸውን የአዲስ ኪዳን ቃላትን በሄኖክ መጽሐፍ ውስጥ እንመለከታለን፣ የአዲስ ኪዳን ቃላትን በዚህ “የብሉይ ኪዳን” መጽሐፍ ውስጥ ማግኘት

ማለት መጽሐፉ የተዘጋጀው በአዲስ ኪዳን ዘመን መሆኑን ያሳብቃል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

- ኢየሱስ
  - ክርስቶስ - ሄኖክ 13፡4
  - የአብ የባህሪ ልጅ - ሄኖክ 13፡17
  - አስታራቂ - ሄኖክ 13፡22, ሄኖክ 13፡19, ሄኖክ 13፡31
  - ፈራጅ - ሄኖክ 13፡22
- አብ - ሄኖክ 13፡17
- *መንግሥተ ሰማያት* - ሄኖክ 4፡6, ሄኖክ 13፡34
- ሐዋርያት - ሄኖክ 20፡25
- <u>ሐዋርያው ዮሐንስ</u>፡- ሄኖክ 33፡42

*መ*ጽሐፈ ሄኖክ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ቀንጨብ ቀንጨብ አድርጎ መያዙና የአዲስ ኪዳን ቃላትን ቃል በቃል መያዙ፣ መጽሐፉ የተፃፈው በራዕይ ሳይሆን፣ ሄኖክ የአበውን መጽሐፍ ሲያነብ ነበረ(ሄኖክ 29፡3) እንደተባለው፣ መጽሐፉ የተዘጋጀው 66ቱን መጽሐፍ ቅዱስ ባነበበ የአዲስ ኪዳን ዘመን ሰው መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ይባሱኑ ደግሞ መጽሐፉ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያልተፃፈውና በ325 ዓ.ም በኒቂያ ጉባዔ የተፈጠረውን "ሥላሴ" የሚለውን ቃል መያዙ (ሄኖክ 13፡18-29) የሄኖክ መጽሐፍ የተፃፈው ከኒቂያ ጉባዔ ከ325 ዓ.ም በኋላ መሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህም መጽሐፈ ሄኖክ ስለራሱ የሚናገረውና በውስጡ የቀረቡት እውነታዎች ይፋለሳሉ፡፡

4.3.3.2. <u>ከ66ቱ መጽሐፍት በተለየ ቅድስና የሌለውና በውስጡም ውሸቶችን የያዘ መጽሐፍ ነው</u>

ቅድስናና ውሸት ተቃራኒ አሰራሮች ናቸው፣ ውሸት ከውሸት አባት ሲሆን እውነት ደግሞ ከቅዱሱ ነው፣ የሄኖክ መጽሐፍን ማንነት ስንመለከት መጽሐፉ ቅድስና በራቀው በውሸት አባት መሪነት የተፃፈ መጽሐፍ ሆኖ እንመለከተዋለን፣ የተወሰኑትን ለምሳሌ ያህል ብንመለከት፣

- <u>"የፀሐይ መግቢያና መውጪያ ስድስት ስድስት መስኮቶች በሰማይ ላይ መኖራቸው"</u>

  ሄኖክ 21፡5-6 "<u>የበራ</u> የፀሐይ መውጫ በምስራቅ ባሉ በሰማይ መስኮቶች ነው፣ መግቢያውም በምዕራብ ባሉ በሰማይ መስኮቶች ነው፡፡ ፀሐይ የሚወጣበት ስድስት መስኮቶች አየሁ ፀሐይም የሚገባበት ስፍራ ስድስት መስኮቶችንም አየሁ፡፡"

እውነታው ግን ፀሐይን የምትዞረው መሬት እንጂ ፀሐይ ከመሬት አንፃር ምንም አይነት እንቅስቃሴ የማታደርግ መሆኑን፣ በዚህም "የሄኖክ" መስኮቶች የጋርዮሽ ሰዎች ልበወለድ ብቻ መሆኑን እንመለከታለን፣ ይህ ስህተት መጣው እንደ ቁርአኑ ሰማይን ጠጣር ነገር አድርጎ ከመመልከት ችግር ነው። ከሁሉ የሚያስቀው "የበራ" የሚለው ነው፣ ያልበራው ፀሐይ ምን ይመስል እንደሆነ መስማቱ አጓጊ(Suspense) ልበወለድ ነው።

- "ለድርቅ ምክንያት የሆነው የፀሐይ መስኮት መኖሩ"
  ሄኖክ 24፡9-10 "ዑርኤል በሰማይ ያለ ፀሐይ በሚመላለስባቸው በሰረገላዎች ዙሪያ የፀሐይ እግሮች ከነሱ የሚወጡባቸው የተከፈቱ አስራ ሁለት መስኮቶች እንዲህ አሳየኝ። በታወቁባቸው ዘመኖች በተከፈቱ ጊዜ ከነሳቸው በዚህ ዓለም ድርቅ ይወጣል።"
- "ፀሐይ የምትጓዘው በሰረገላ ላይ ሆና ነው"
  - ሄኖክ 21፡11-12 "ወደ ሚሄድባቸው ሰረገላዎች በወጣ ጊዜ ሰረገላዎችን የሚነዳ ነፋስ ይነፍሳል። ፀሐይም ከምስራቅ ወደ ምዕራብ ይገባል። ወደ ምስራቅም ለመሄድ ከምዕራብ ወደ መስዕ ይመለሳል ወደዚህም መስኮት ሊገባ ይመራል።"
  - ሄኖክ 21፡55 "እንዲህ ሆኖ ይወጣል ይገባል መጉደልም የለበት በሰረገላ ሆኖ በመአልትም በለሊትም ይሮጣል እንጂ አያርፍም።"
- "ጨረቃም የፀሐይን መስኮቶች ለመግቢያና ለመውጫ መጠቀምዋ"
  ሄኖክ 21፡7 "ጨረቃም በነዚያ(በፀሐይ) መስኮቶች ይወጣል ይገባል።"
- "ኮከቦችም በዚያው በፀሐይና ጨረቃ በሚጠቀሙበት መስኮት ይገባሉ ይወጣሉ"
  ሄኖክ 21፡8 "ከሰማይ ኮከቦችን የሚመሩ ኮከቦችም ከሚመራቸው ኮከቦች ጋራ በነዚያ ደጃፎች ይወጣሉ ይገባሉ፣ እኒህም መስኮቶች ስድስቱ በምስራቅ ስድስቱ ፀሐይ በሚገባበት በምዕራብ ናቸው።"
- "የኮከቦችም ሰረገላ መኖሩ"
  ሄኖክ 24፡14 "የማይገቡ ኮከቦች በሚመላለሱባቸው በነዚያ መስኮቶች በበታቻቸውና በበላያቸው ሰረገላዎች ለዘላለሙ በሰማይ ሲሮጡ አየሁ።"
- "ጨረቃና ፀሐይ እኩል መጠን አላቸው"
  ሄኖክ 21፡57 እና ሄኖክ 26፡3 "የሁለቱ ሁሉ የፀሐይና የጨረቃ መጠናቸው የተካከለ ነው።"
- "የጨረቃ ሰረገላ የሚጓዘው በንፋስ ነው"
  ሄኖክ 22፡2 "(ጨረቃ)ክብነቱ እንደ ሰማይ ክብ ነው፣ በሚቀመጥበት በሰረገላው ነፋስ ይነፍሳል።"

- “መብረቅና ነጎድጓድ የሚሄደው በንፋስ ነው”
  ሄኖክ 16፡21-23 “መብረቅና ነጎድጓድ አይለያዩም አንዱም አንዱም ሁለቱ ሁሉ በነፋስ ይሄዳሉ … በመጡበት ጊዜ ስፍራቸው ባሸዋና በድኝ መካከል ነውና መልአኩ በመካከላቸው አስተካክሎ ይከፍላል…”
- “ለነፋስ መውጫና መግቢያም አስራ ሁለት መስኮቶች አሉት”
  ሄኖክ 24፡1-11 “ነፋሶች ሁሉ መውጫ መግቢያ የሚሆኑ ነፋሶች ከነሱ የሚወጡበቸው የተከፈቱ አስራ ሁለት መስኮቶች በምድር ዳርቻ አየሁ፡፡ በዚህም ዓለም ይነፍሳሉ … ሦስቱ በምስራቅ ሦስቱ … በአዜብ በምትቀርበዋ የንፋስ መስኮት መልካም ዝናብ ይመጣል … ለምስራቅ በምትቀርብ በመጀመሪያይቱ መስኮት የድርቅ ነፋስ ይወጣል …”
  ሄኖክ 16፡35 “ዝናሙን የሚያመጣው ነፋስ ከስፍራው በተናወጠ ጊዜ መላዕክት ይመጣሉ ስፍራውንም ከፍተው ያወጡታል፡፡”

ይህ የጋርዮሽ ሰዎች የሚያስቡበት “የተዘረጋች ምድር፣ እንደ ጣርያ የተዘረጋ ሰማይ” በሚለው አስተምህሮ ምክንያት የመጣ ስህተት ሲሆን፣ ሙሐመድም በተመሳሳይ መንገድ መሳሳቱን በምዕራፍ 2 ተመልክተናል፡፡

በአጠቃላይም ስንመለከት መጽሐፈ ሄኖክ ተብሎ የገባው መጽሐፍ መቼቱ የተዛባና ቅድስና የጎደለው በውሸት አባት የተፃፈ ከ66ቱ ቅዱሳን መጽሐፍት ጋር አብሮ መታተም የሌለበት መጽሐፍ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ይህ እውነታ ለሌላውም ጊዜ ትምህርት ሊሆን ይገባል፣ አንድ መጽሐፍ ተመሳሳይ ስም ይዞ ስለመጣ ብቻ መሸወድ አይገባም፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ወደ አንድ መጽሐፍ በሚሰበሰብበት ወቅት፣ እንደ ሄኖክ መጽሐፍ፣ ስማቸው በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተጠቀሱ ነገር ግን ትክክለኛ ኮፒያቸው ስላልተገኘ ብቻ በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ሳይካተቱ የተተው ብዙ ቅዱሳን መጽሐፍት እንዳሉ ማወቅ ያስፈልጋል፣ “የጦርነት መጽሐፍ”(ዘኁ.21፡14)፣ “የያሻር መጽሐፍ”(2ሳሙ.1፡18)፣ “የሰሎሞን ታሪክ መጽሐፍ”(1ነገ.11፡41)፣ “የእስራኤል ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ”(1ነገ.14፡19, 1ነገ.15፡32, 1ነገ.16፡14, 1ነገ.16፡20, 1ነገ.16፡27)፣ “የይሁዳ ነገሥታት ታሪክ መጽሐፍ”(1ነገ.15፡23, 2ነገ.15፡6)፣ “የሳሙኤል፣ የናታን የጋድ ታሪክ መጽሐፍት”(1ዜና.29፡29) መመልከት ይቻላል፡፡

ከሄኖክ መጽሐፍም የምንረዳው ማንም ሰው ተነስቶ በነዚህ መጽሐፍት ስም መጽሐፍ ቅዱሱን አመሳስሎ መጽሐፍ አዘጋጅቶ ቢያመጣ ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይገባ ነው፡፡

4.3.4. በ2ጢሞ.3፡16-17 መስፈርት

ተጨማሪ መጽሐፍቱ ከ66ቱ መጽሐፍት ጋር አብረው ለመታተማቸው የሚቀርበው ሌላው ቃል፣

> 2ጢሞ.3፡16-17 "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።"

የሚለው ነው፣ ነገር ግን ተጨማሪ መጽሐፍቱ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት መፃፍ አለመፃፋቸውን ስንመረምር ነገሩ ሌላ ነው፣ ይህም፣

- መጽሐፍቱ እስራኤል የማታውቃቸው "የብሉይ ኪዳን" መጽሐፍት መሆናቸው፣
- የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ አብያተ ክርስቲያናቱና ጳጳሳቱ እንደፈለጉት "ማስተካከላቸው"፣
- የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚመሰክር መልኩ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ትክክለኛ ስፍራ አጥተው መቸገራቸው፣
- የመጽሐፍቱ መቼት መምታታቱ፣
- ተረቶችና ግራ የተጋቡ ትምህርቶችን እንደ ፈጣሪ ቃል መያዛቸው፣
- እርስ በራስ እንዲሁም ከ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር መጋጨታቸው፣
- ሰይጣናዊ አሻራዎችን እንመለከትባቸዋለን፣

ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

4.3.4.1. እስራኤል የማታውቀው ብሉይ ኪዳን መሆኑ

ብሉይ ኪዳን የወረደው ለእስራኤል ነው(ሮሜ.9፡4, ዘጸ.34፡27 ...)፣ አዲሱ ኪዳን ደግሞ ለዓለም(ማቴ.24፡14, ዮሐ.3፡16 ...)፣ ቤተክርስቲያኗ ተጨማሪ መጽሐፍቱን "የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ናቸው" በማለት ከ39ኙ የብሉይ ኪዳናት መጽሐፍት ጋር ብትቀላቅላቸውም የብሉይ ኪዳን ባለኪዳኖቹ እስራኤላውያኑ ግን እነዚህን መጽሐፍት አያውቋቸውም።

[98] "አይሁዳውያን በ90 ዓ.ም በጀምኒያ ጉባዔ ባስተላለፉት ውሳኔ ተቀባይነት ያላቸው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት 39 መሆናቸውን አሳውቀዋል።" [99] በሂብሩ "ታናክ(Tanakh)" የሚባሉት እንደዚሁ [100] በዘመናዊው ሳይንስ "የዕብራውያን መጽሐፍት" የሚባሉት 39ኙ መጽሐፍት ብቻ ናቸው፣ በዚህም በቤተክርስቲያኗ የተጨመሩት ተጨማሪ መጽሐፍት ምንጭ ከባለ ኪዳኗ ከእስራኤል አይደለም።

---

[98] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን**፣ ገፅ 16

[99] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Hebrew Bible

[100] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Biblical languages

ተጨማሪ መጽሐፍቱ ላይ የተሰሩ ጥናቶችና አንዳንድ ታሪኮችን ስንመለከት የመጽሐፍቱ ምንጭ እስራኤል ሳትሆን ግሪክ፣ ኢትዮጵያና የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት መሆናቸውን ይባሱኑም መጽሐፍቱ የተዘጋጁት በብሉይ ኪዳን ዘመን ሳይሆን ከ325 ዓ.ም ከኒቂያ ጉባዔ በኋላ መሆኑን የሚያሳብቁ ምልክቶችን ይታይባቸዋል፡-

- ብሉይ ኪዳን ያልተገባላት ግሪክ የፃፈችው መሆኑ፣
  [101] የአብዛኞቹ የተጨማሪ መጽሐፍቱ ምንጭም ግሪክ ናት፡፡
- ኢትዮጵያዊ አሻራዎች፣ ለምሳሌ፣
  ሲራክ 4፡6 "... እንደ አባይ ያለውን ውሀ በሐምሌ በነሐሴ እሻገራለሁ አትበል፡፡"
  ይህ ኢትዮጵያዊ አፃፃፍ ነው፣ በባለ ኪዳንዋ እስራኤል ተፅፎ ቢሆን ኖሮ "የዮርዳኖስን፣ የኤፍራጠስን፣ የጢግሮስን ... ወንዝ በአዳር ወይ በኒሳን ወር አትሻገር" ባለ ነበረ፡፡
  በሄኖክ 21-27 ላይ ደግሞ የሀገራችን ካሌንደር፣ ዓለም የማታውቀው የጳጉሜ ወር እንኳን ሳትቀር መገለፁ፣ የመጽሐፉን ኢትዮጵያዊነት ያሳብቃል፡፡
- እስራኤልና ብሉይ ኪዳን የማያውቋቸው የካቶሊክ/ኦርቶዶክስ ዕሴቶች፣
  - ስርዓቶች - ተዝካር(ሲራክ 7፡33)፣ የቅዳሴ ስነ ስርዓት(ሄኖክ 4፡5)፣
  - አገልጋዮች - ባሕታዊ(ሲራክ 11፡5)፣ ደብተራ(ሄኖክ 32፡70)፣
  - ስፍራዎች - ደብር(1ኛመቃብያን 19፡1-12, ሄኖክ 2፡2)፣ ገዳም(ሲራክ 2፡1)
  - መላዕክት - ሩፋኤል(ጦቢት 12፡15, ሄኖክ 31፡7)፣ ዑራኤል(ሄኖክ 5፡37)

  እነዚህ በ39ኙ የብሉይ መጽሐፍት የማናገኛቸው የካቶሊክ/ኦርቶዶክስ ዕሴቶችን በተጨማሪ መጽሐፍቱ ውስጥ ስንመለከት፣ የመጽሐፍቱ ምንጭ የካቶሊክ/ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን እንጂ እስራኤል አለመሆኗን እንመለከታለን፡፡
- መጽሐፍቱ በመጽሐፍ ቅዱሱ አንድም ስፍራ ላይ ያልተጠቀሰውንና በኒቂያ ጉባዔ የተፈጠረውን "ሥላሴ" የሚለውን ቃል መያዛቸው(ዕዝራ ሱቱኤል 4፡5, ዮዲት 11፡19, ሲራክ 3፡22 ...)፣ መጽሐፍቱ የተፃፉት በብሉይ ኪዳን ዘመን ሳይሆን ከ325 ዓ.ም ከኒቂያ ጉባዔ በኋላ መሆኑን ያሳያል፡፡
- ይባሱኑ ደግሞ መጽሐፍቱ የተፃፉት የመጽሐፍ ቴክኖሎጂ ከመጣ በኋላ፣ በጥቅልል ወረቀቶች/ብራናዎች ሲፃፍ የነበረው በመጽሐፍ መልክ ሲሰባሰቡ 39ኙ መጽሐፍት በአንድ ላይ "የብሉይ ኪዳን" 27ቱ መጽሐፍት ደግሞ "የአዲስ ኪዳን" መጽሐፍት ተብሎ ከተሰየሙ በኋላ የተፃፉ መሆኑን የሚያሳዩ ክፍሎች አሉ፣ ይህንንም ዘመናዊውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አጠራር ዕዝራ ሱቱኤል 4፡20 "ብሉያትና ሀዲሳት" እያለ መጥራቱን ስንመለከት ተጨማሪ መጽሐፍቱ የተዘጋጁት በቅርብ ጊዜያት ውስጥ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

[101] https://en.m.wikipedia.org>wiki>Deuterocanonical Books

በዚህም የነዚህ ተጨማሪ መጽሐፍት ምንጭ ግሪክ፣ ኢትዮጵያና ካቶሊክ/ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት እንጂ እስራኤል አለመሆኗን፣ መጽሐፍቱ የተፃፉትም በአዲስ ኪዳን ዘመን፣ ከኒቂያ ጉባዔና የመጽሐፍ ቴክኖሎጂ ከመጣ በኋላ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

4.3.4.2. <u>የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ አብያተ ክርስቲያናቱና ጳጳሳቱ እንደፈለጉት "ማስተካከላቸው"</u>

መጽሐፍ ቅዱስ ፈጣሪ ለሰው ልጆች መመሪያ አድርጎ ያወረደው መጽሐፍ በመሆኑ ቋሚነት ሊኖረው ይገባል፣ 66ቱ መጽሐፍት የፈጣሪ ቃል በመሆናቸው በትውልድና በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ሳይዛነፉ በቋሚነት ይገኛሉ፣ ነገር ግን በ66ቱ መጽሐፍት ላይ የተጨመሩት ተጨማሪ መጽሐፍት በየትውልዱ፣ በየአብያተ ክርስቲያናቱና በየጳጳሳቱ ሲቀያየሩ እንመለከታለን፡፡

ኦርቶዶክስ የምትለው እና ካቶሊክ የምትለው የተጨማሪ መጽሐፍት ብዛት የተለያየ ነው ይባሱኑ ደግሞ [102] "በኦርቶዶክሱ ውስጥም አንድነት የለም የኢትዮጵያው፣ የግብፁ፣ የሶሪያው፣ የህንዱ፣ የአርመኑ፣ የሩሲያውና የግሪኩ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያናት የተለያዩ ቁጥር ያቀርባሉ፡፡ በዓለም ላይ ካሉት የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ብዙ መጽሐፍት አሰብስባ የያዘችው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ስትሆን ቤተክርስቲያኗ 15 ተጨማሪ መጽሐፍትን ይዛለች …"

ከብዛታቸው በተጨማሪም በይዘታቸውም በአብያተ ክርስቲያናቱ መካከል ሰፊ ልዩነት እንመለከታለን፣ ለምሳሌ የመቃብያንን መጽሐፍ ስንመለከት [103] "መቃብያን የሚባሉ ስምንት መጽሐፍት አሉ፣ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ የሚታወቁ አራት ሲሆኑ በግሪክ ኦርቶዶክስ የሚታወቁትም አራት ናቸው፣ የሚያሳዝነው ግን እነዚህ የኢትዮጵያና የግሪክ የመቃብያን መጽሐፍት በስም እንጂ በይዘት አይገናኙም፣ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የምትቀበላቸው ሁለቱን የግሪክ መቃብያን መጽሐፍት ብቻ ነው፡፡"

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሱም ጋር ስንመጣ ተጨማሪ መጽሐፍት ብዛትና አይነት በየተሿሚ ጳጳሳቱና በምሁራኖቹ የተለያዩ ናቸው፣ ምሁራኖቿ [104] "የተለያየ የተጨማሪ መጽሐፍት ብዛት ያስቀምጣሉ"፣ እነዚህን በግለሰብ ደረጃ የተሰጡትን መመሪያዎች ትተን በቤተ ክርስቲያን ደረጃ የታተሙትን እንኳን ብንመለከት ሰፊ ልዩነቶችን በመካከላቸው እንመለከታለን፣

---

[102] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን**፣ ገፅ 15
[103] የኢትዮጵያ መፅሃፍ ቅዱስማኅበር(2008)፣**የመፅሃፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት**፣ገፅ 36-37
[104] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን**፣ ገፅ 29-30

ተ ቁ	የተጨማሪ መጽሐፍቱ ዝርዝር	የተለያዩ የተጨማሪ መጽሐፍት ብዛት የሚናገሩ መጽሐፍት				
		[105] ፍትህ ነገሥት	[106]1953 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስ	[107]የቤተክር ስቲያኗ ስርዓተ አምልኮት መጽሐፍ	የ1980 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስ	የ2000 ዓ.ም. መጽሐፍ ቅዱስ
1	መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል	√	√	√	√	√
2	መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ	√	√	√	√	√
3	መጽሐፈ ጦቢት	√	√	√	√	√
4	መጽሐፈ ዮዲት	√	√	√	√	√
5	መጽሐፈ አስቴር	√	-	-	√	√
6	1ኛ መቃብያን	√	√	√	√	√
7	2ኛ መቃብያን	-	√	√	√	√
8	3ኛ መቃብያን	-	√	√	√	√
9	መጽሐፈ ሲራክ	√	√	√	√	√
10	ጸሎተ ምናሴ	-	-	√	√	-
11	ተረፈ ኤርምያስ	-	-	√	√	√
12	መጽሐፈ ሶስና	-	-	√	√	-
13	መጽሐፈ ባሮክ	-	√	-	√	√
14	መጽሐፈ ጦቢት	√	√	-	√	√
15	መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ	-	-	√	√	-
16	ተረፈ ዳንኤል	-	-	√	√	-
17	መጽሐፈ ኩፋሌ	-	√	√	√	√
18	መጽሐፈ ሄኖክ	-	√	√	√	√

[105] ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ...(1990) **ፍትህ ነገሥት ንባቡና ትርጓሜው፣**
[106] መምህር ያሬድ ሽፈራው (2009) **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክዊ አመጣጥ፣** ገፅ 98
[107] ቴዎድሮስ ደመላሽ(2007)፣ **ሰማንያ አሃዱ በእግዚአብሔር ቃል ሲመዘን፣** ገፅ 29-30

19	መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን	√	-	√	-	-
20	መጽሐፈ ተግሳጽ	-	-	√	-	√
21	ተረፈ ባሮክ	-	-	-	-	√
22	የአባጎር ጥበብ	√	-	-	-	-
የተጨማሪ መጽሐፍቱ ብዛት		**11**	**12**	**16**	**18**	**16**
ከአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ጋር ሲደመሩ ያላቸው ብዛት		**77**	**78**	**82**	**84**	**81**

<u>የግርጌ ማስታወሻ</u>

1. *"የቤተክርስቲያኗ ሰርዓተ አምልኮ" እና "የ2000 ዓ.ም ዕትም" ላይ የተጨማሪዎቹ መጽሐፍት ብዛት እኩል እኩል 16 መጽሐፍት ቢሆኑም፣ አጠቃላይ ድምራቸው ግን የተለያየ ነው ምክንያቱ ደግሞ የ2,000 ዓ.ም ዕትም ላይ ዋናው የቀኖናው "መጽሐፈ አስቴር" ሙሉ በሙሉ ስለወጣ፣*
2. *ፍትህ ነገሥቱ የሚዘረዝረው የመጽሐፍቱን ስም ብቻ በመሆኑ በተጨማሪ ደግሞ የሰም አጠራሩ ከሌሎቹ ለየት ስለሚል፣ ከአንዳንድ አመላካች ነገሮች በመነሳት ከአዲሱ አጠራር ጋር ለማዛመድ ተሞክሯል፣ በዚህም "የሰሎሞን ጥበብ" የሚለው በአዲሱ አጠራር "የጥበብ መጽሐፍ" እንዲሁም "የሲራክ ልጅ የኢያሱ ጥበብ" የሚለው "መጽሐፈ ሲራክ" በሚለው ስር ተቆጥረዋል፣ ይህ ካልሆነ ደግሞ የመጽሐፍቱ ብዛት ልዩነት የባሰ ይሰፋል።።*

የሚገርመው ደግሞ ማሻሻያዎች ሲደረጉ፣ በየመግቢያዎቻቸው ላይ እንደሚታየው፣ ጳጳሳቱ የአንድ ቤተክርስቲያን አባላት ያልሆኑ ይመስል፣ ሁሉም ያሻሻሉት የቀደሙትን አበው በመተቸት ነው፣ እውነታው ግን በቋንቋ ችሎታቸው፣ በቅድስና ሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ እውቀታቸው የቀደሙት አበው ተተኪዎቹን እንደሚበልጡ ነው የሚታወቀው።።

ከሁሉ በተለየ በመጽሐፍ ቅዱስ ህትመት ታሪክ ትልቁን የድፍረት ስራ የሰሩት አቡነ ጳውሎስ ናቸው፣ አቡኑ በ2,000 ዓ.ም ባሳተሙት መጽሐፍ ቅዱሳቸው፣ "በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አትጨምር፣ አትቀንስ"(ራዕ.22፡18-19, ዘዳ.4፡2, ዘዳ.12፡32...) የሚለውን ሕግ በመጣስ በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ጨምረዋል፣ ቀንሰዋል፣ አደባልቀዋል፣ የትርጉም ለውጥ በሚያመጣ መልኩ ቃላቶችን ቀያይረዋል፣ ይህ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተሰራ ትልቅ የድፍረት ስራ ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

1. **<u>መጨመር</u>**
   - በ1980 የታተመው መጽሐፈ ባሮክ 5 ምዕራፎችና 83 ቁጥሮች ሲኖሩት በ2,000 ዓ.ም በታተመው ደግሞ የሚጨመረው ተጨምሮ 5 ምዕራፎችና 141 ቁጥሮች ይዞ፣ በአጠቃለይ 58 ተጨማሪ ጥቅሶች ተጨምረውበት መጥቷል።።
   - በ1980 በታተመው መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፈ ጦቢት ላይ ለመግቢያ ተብሎ በሰዎች የተቀመጠው የመግቢያ ሐሳብ፣ በ2,000 ዕትም ላይ "የፈጣሪ ቃል"

በማድረግ ከምዕራፍ አንድ ጋር በመቀላቀል ቁጥር ሰጥተውታል፣ በዚህም በእነዚህ ሁለቱ መጽሐፍ ቅዱሶች መካከል የሦስት ቁጥሮች መዛነፍ ተፈጥሯል።

2. **<u>መቀነስ</u>**

ዋናው የ66ቱ "መጽሐፈ አስቴር" ሙሉ በሙሉ ከ10 ምዕራፎቹና ከ167 ጥቅሶቹ ጋር ከ2,000 ዓ.ም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተሰርዟል።

3. **<u>ማደባለቅ</u>**

በቀደሙት መጽሐፍ ቅዱሶች ዋናው 66ቱ መጽሐፍትና ተጨማሪ የአዋልድ/ዲዮትሮካኖኒካል መጽሐፍት የሚቀመጡት በተለያየ ክፍል ነበረ ነገር ግን በአቡነ ጳውሎሱ መጽሐፍ ቅዱስ ተቀላቅሎ ታትሟል፣ ይህ የማደባለቅ ስራም ከዚህ ባለፈ መጽሐፍቱ ውስጥ እስከ መነካካት የደረሰ ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

ተቁ	የመጽሐፉ ስም	በ1980 ዕትም	በ2000 ዕትም
1	ፀሎተ ምናሴ	ራሱን የቻለ መጽሐፍ	ከ2ዜና.33፡13 በኋላ ጉብቷል
2	መጽሐፈ ሶስና	ራሱን የቻለ መጽሐፍ	ትንቢተ ዳንኤል 13ኛ ምዕራፍ ሆኗል
3	ተረፈ ዳንኤል	ራሱን የቻለ መጽሐፍ	ትንቢተ ዳንኤል 14ኛ ምዕራፍ ሆኗል
4	መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ	ራሱን የቻለ መጽሐፍ	ትንቢተ ዳንኤል ምዕራፍ 3 ውስጥ ጉብቷል
5	ተረፈ ኤርምያስ	ራሱን የቻለ መጽሐፍ	ተረፈ ኤርምያስ ምዕራፍ 6 ተረፈ ኤርምያስ ምዕራፍ 1 ሲደረግ፣ የቀሩት 5 ምዕራፎች ተረፈ ባሮክ ተብለዋል

2. **<u>ትርጉም በሚያዛንፍ መልኩ ቃላት መቀየር</u>**

- **<u>ከዋናው 66ቱ መጽሐፍት</u>**

ተቁ	ጥቅስ	የ1980 እትም	የ2000 እትም
1	ኢሳ.53፡10	እግዚአብሔርም <u>በደዌ ያደቅቀው</u> ዘንድ ፈቀደ።	እግዚአብሔር <u>ከግርፋቱ ያነፃው</u> ዘንድ ፈቀደ።
2	ኢሳ.53፡12	ስለዚህ እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፣ ከኃያላን ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ ከአመፀኞችም ጋር ተቆጥሮአልና፤ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢያት ተሸከመ፣ <u>ስለ አመፀኞችም ማለደ።</u>	ስለዚህ እርሱ ብዙዎችን ይወርሳል፤ ከኃያላንም ጋር ምርኮን ይከፋፈላል፤ ነፍሱን ለሞት አሳልፎ ሰጥቶአልና፣ እርሱ ግን የብዙ ሰዎችን ኃጢያት ተሸከመ፤ <u>ስለ ኃጢያታችንም ተሰጠ</u>።"

3	ኢሳ.59፡15-16	ወደ እሱ <u>የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ</u>፣ ተደነቀም	<u>የሚረዳም ሰው እንደሌለ</u> ተረዳ
4	ማቴ.5፡6	<u>ፅድቅን</u> የሚራቡና የሚጠሙ ብፁአን ናቸው፣ ይጠግባሉና።	<u>ስለ ፅድቅ</u> የሚራቡና የሚጠሙ ብፁአን ናቸው፤ እነርሱ ይጠግባሉና
5	ሮሜ.8፡33-34	... የሚያፀድቅ እግዚአብሔር ነው፣ የሚኮንንስ ማነው፣ የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፣ ደግሞም <u>ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው</u>።	የሚፈርድስ ማነው፣ የሞተው፣ ይልቁንም ከሙታን ተለይቶ የተነሳው፣ በእግዚአብሔር ቀኝ የተቀመጠው፣ ደግሞ <u>ስለ እኛ የሚፈርደው ኢየሱስ ክረስቶስ ነው</u>።
6	ሉቃ.22፡32	እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ <u>አማለድሁ</u>	እኔ ግን ኃይማኖታችሁ እንዳይደክም ስለ እናንተ <u>ፀለይሁ</u>
7	ዕብ.7፡22	ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኗል	ኢየሱስ ይህን ያህል በምትበልጥና ከፍ ባለች ሹመት ተሾመ
8	ዕብ.7፡25	ስለእነርሱ <u>ሊያማልድ</u> ዘወትር በህይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈፅሞ ሊያድናቸው ይችላል።	ዘወትር በእርሱ በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡትን ሊያድናቸው ይቻለዋል፣ ለዘላለምም ህያው ነውና <u>ያስታርቃቸዋል</u>።
9	፩ጢሞ4፡14	በትንቢት <u>ከሽማግሌዎች</u> እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፣ በአንተ ያለውን የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል።	ትንቢት ከመናገር ጋር <u>በጳጳሳት</u> እጅ መጫን የተሰጠህን በአንተ ላይ ያለውን ፀጋ አታቅልል።
፲0	፩ጢሞ.5፡17	በመልካም የሚያስተዳድሩ <u>ሽማግሌዎች</u> ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት እጥፍ ክብር ይገባቸዋል	በመልካም የሚያስተዳድሩ <u>ቀሳውስት</u> ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል።
፲፩	ቲቶ.1፡5	ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፣ እኔ አንተን እንዳዘዝሁህ፣ <u>ሽማግሌዎችንም</u> እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ።	ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ፣ በየከተማውም እኔ አንተን እንዳዘዝሁህ <u>ቀሳውስትን</u> እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ።

12	ኤፌ.2፡16	ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው	በመስቀሉም በአንድ ስጋው ሁለቱን ወደ እግዚአብሔር አቀረባቸው፣ በእርሱም ጥልን አጠፋ
13	ቆላ.1፡19-20	እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፣ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት የሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዶአልና፡፡	ሁሉ በእርሱ ፍፁም ሆኖ ይኖር ዘንድ ወዶአልና፣ ሁሉንም በእርሱ ይቅር ይለው ዘንድ በመስቀሉ በፈሰሰው ደም በምድርና በሰማያት ላሉ ሰላምን አደረገ
14	ቆላ.1፡21-22	እናንተ ነውርና ነቀፋ የሌላችሁና ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ያቀርባችሁ ዘንድ፣ በበፊት የተለያችሁትን ክፉ ስራችሁንም በማድረግ በአሳባችሁ ጠላቶች የነበራችሁትን አሁን በስጋው ሰውነት በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ፡፡	እናንተም ቀድሞ በአሳባችሁና በክፉ ስራችሁ ከእግዚአብሔር የተለያችሁና ጠላቶች ነበራችሁ፣ አሁን ግን በፊቱ ለመቆም የተመረጣችሁና ንፁኃን፣ ቅዱሳንም ያደርጋችሁ ዘንድ በስጋው ሰውነት በሞቱ ይቅር አላችሁ፡፡
15	1ዮሐ.2፡1	ልጆቼ ሆይ፣ ኃጢያትን እንዳታደርጉ ይህንን እፅፍላችኋለሁ፣ ማንም ኃጢያትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ፃድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡	ልጆቼ ሆይ እንዳትበድሉ ይህን እፅፍላችኋለሁ፣ የሚበድል ቢኖር ከአብ ዘንድ ጻራቅሊጦስ አለን፣ ኢየሱስ ክርስቶስም ኃጢያተኞችንን ያስተሰርይ ዘንድ ፃድቅ ነው፡፡

- **ከተጨማሪ መጽሐፍቱ**

ተቁ	ጥቅስ	የ1980 እትም	የ2000 እትም
1	ኩፋሌ 4፡11	... ሴት ልጅ ብትወልድ ... ሠላሳ ስድስት ቀንም ንጽህ በሚሻው ደምዋ ትቆይ ...	... ሴት ልጅ ብትወልድ ... ስድሳ ስድስት ቀንም በመንፃቷ ደም ትቆያለች
2	አስቴር 9፡16	የቀሩትም ... አይሁድ ተሰብስበው ... ከሚጠሉዋቸው ሰባ አምስት ሺ ገደሉ	የቀሩትም ... አይሁድ ተሰብስበው ... ከሚጠሉዋቸው አስራ አምስት ሺ ገደሉ
3	ሲራክ 4፡27	ፈጣሪ እግዚአብሔር ስላንተ ይከራከርልሀልና እስከምትሞት ድረስ በኃይማኖት አትከራከር	ፈጣሪ እግዚአብሔር ስላንተ ይከራከርልሀልና ለሞት እስክትደርስ ስለ እውነት ተከራከር፡፡

4	ሲራክ 9፡2	ምስጢርህን እንዳታወጣብህ ልብህን ለሴት አትስጣት	ጎይልህን እንዳታደክምብህ ለሴት ልብህን አትስጣት
5	ሲራክ 19፡9	ከሰማ በኋላ ኃጢያትህን አይሰውርልህምና እስክትሞት ድረስ ይጠብቅህልና ስተህ የሰራሽውን ኃጢያት አትናገር፡፡	ቢሰማ አይሰውርልህም፣ እስክትሞት ድረስ ይጠብቁህል
6	ሲራክ 25፡24-25	በቤት አጠገብ ለውሀ መፍሰሻ አታበጅለት ለሴትም የልብህን ምስጢር አታውጣላት፡፡ ግብርዋ እንደ ግብርህ ካልሆነ ፍታት ከሰውነትህም ለያት	በመጀመሪያ ኃጢያት ከሴት ተገኘች፣ በእርስዋም ምክንያት ሁላችን እንሞታለን፡፡ ለውሀ መፍሰሻ አታበጅለት ለሴትም የልብህን ምስጢር አታውጣላት
7	ሄኖክ 13፡19	አስታራቂ ክርስቶስ በመላዕክት ጌታ ፊት ቆሞአልና አሰት ነገርም እንደ ጥላ ያልፋል ቆሞ የሚሰወሩበት ስፍራ የለም	አስታራቂው በመናፍስት ጌታ ፊት ቆማልና አመፅ እንደ ጥላ ያልፋል መቆሚያም ስፍራ የለውም
8	ሄኖክ 13፡22	አስታራቂ ክርስቶስ በመላዕክት ጌታ አብ ፊት እሱ እንደወደደ ነውና የተሰወሩትን ነገሮች ገልጦ የሚፈርድ እሱ ነው በሱም ፊት ዋዛ ነገርን ተናግሮ መዳን የሚችል የለም	እርሱም የተሰወሩትን ይፈርዳል ከንቱ ነገርንም በፊቱ መናገር የሚችል የለም፡፡ እርሱ እንደወደደ በመናፍስት ጌታ ፊት አስታራቂ ነውና
9	ሄኖክ 13፡31	አስታራቂ ክርስቶስ በነዚያ ወራት በዙፋኑ ይቀመጣል የመላዕክት ጌታ ሰጥቶ አክብሮታልና የተሰወረ ጥበብንም ነገር ሁሉ አስቦ ከሚናገርበት ከአንደበቱ ያወጣል	አስተራቂውም በእነዚህ ወራቶች ምድር አደራዋን ትመልሳለች መቃብርም የተቀበለችውን አደራ ትመልሳለች፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ምሪት የፃፉት መጽሐፍ በመሆኑ በማንም ሰው አይታረምም፣ ማስተካከል ይቅርና ትንቢቶቹ ራሱ ዝም ተብሎ አይተረጎምም(2ጴጥ.1፡20)፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ መጨመር መቀነስ አይቻልም እየተባለ(ራዕ.22፡18-19, ዘዳ.4፡2, ዘዳ.12፡32 ...) አቡነ ጳውሎስ ባሳተሙት መጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ በመጨመር፣ በመቀነስ፣ በማደባለቅና በመቀየር በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ አጭበርባሪ ነጋዴ ሆነውበታል፡፡

የሚገርመው ደግሞ በቤተክርስቲያኗ ለወደፊቱም በአዲስ ኪዳኑ ላይ የሚጨመሩ መጽሐፍት ተዘጋጅተዋል እነሱም [108] "1ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን፣ ሥርአተ ጽዮን ሲኖዶስ፣ ትዕዛዝ ሲኖዶስ፣ ግጽው ሲኖዶስ፣ አብጥሊስ ሲኖዶስ፣ ዳድስቅሊያስ እና ቀለምንጦስ" ናቸው፡፡

[108] መምህር ያሬድ ሽፈራው(2009)፣ **የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪከዊ አመጣጥ**፣ ገፅ 104-105

ብዙ ሙስሊም ምሁራን "መጽሐፍ ቅዱሱ የፈጣሪ ቃል አይደለም ምክንያቱም እርስ በርስ ይለያያል" ብለው የሚሟገቱት ይህንን በማስረጃነት በማቅረብ ነው፣ ይህ ደግሞ፣

ሮሜ.2፡24 "በእናንተ ሰበብ የእግዚአብሔር ስም በአህዛብ መካከል ይሰደባልና..."

የሚለው ቃል ፍፃሜ ነው።።

በአጠቃላይ በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጨመሩት ተጨማሪ መጽሐፍት እንደ ፈጣሪ ቃል በብዛትና በአይነት ቋሚ አለመሆናቸውን ስንመለከት ተጨማሪ መጽሐፍቱ የማይለዋወጠው ፈጣሪ ቃል አለመሆናቸውን ያሳያል፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ አለመለዋወጥ ሲናገር፣

> ማር.16፡8 "... ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን <u>የማይለወጠውን</u> ቅዱሱን ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መጥለቂያ ድረስ በእጃቸው ላከው።።"

በዚህም መሠረት እነዚህ ተጨማሪ መጽሐፍት የማይለዋወጠው የእግዚአብሔር ቃል አለመሆናቸውን እንመለከታለን።።

4.3.4.3. <u>የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ትክክለኛ ስፍራ አጥተው መቸገራቸው</u>

ተጨማሪ መጽሐፍቱ የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል ባለመሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ የራሳቸውን ቋሚ ትክክለኛ ስፍራ አጥተው ሲቸገሩ እንመለከታለን።።

በድሮዎቹ ህትመቶች ተጨማሪ መጽሐፍቱ የዲዮትሮፒካኖኒካል መጽሐፍት ተብለው ለብቻቸው በሁለቱ የኪዳን መጽሐፍት መካከል ተቀምጠው ነበረ፣ በ2,000 ህትመት ላይ ደግሞ ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ጋር ተደባልቀው መጥተዋል፣ ከማደባለቁ በላይ ደግሞ የተደባለቁበት መንገድ የመጀመርያውን ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው አይደለም፣ ለምሳሌ በቀደመው አሰራር ተጨማሪ መጽሐፍቱ የተቀመጡት መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል፣ መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ ... ቅደም ተከተል ሲሆኑ በተደባለቀው ውስጥ ደግሞ የአዋልድ የመጨረሻ መጽሐፍት የነበሩት መጽሐፈ ኩፋሌና መጽሐፈ ሄኖክ የተጨማሪ መጽሐፍቱ ቀዳሚና ተከታይ ሆነው መጥተዋል፣ ሌሎቹም መጽሐፍት ላይ ተመሳሳይ የቅደም ተከተል መዘበራረቅ ተፈጥሯል።።

በ4.3.4.2./ማደባለቅ/ ስር እንደቀረበውም ተረፈ ኤርምያስ፣ ተረፈ ዳንኤል፣ መጽሐፈ ሶስና፣ የምናሴ ፀሎትና መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ በሁለቱ በ1980ው እና በ2000ው ህትመት እንዴት ስፍራቸው እንደተቀያየረ ተመልክተናል።። "መጽሐፈ ሄኖክ" በሁለቱም፣ በድሮዎቹም ሆነ በአቡነ ጳውሎሱ መጽሐፍ ትክክለኛ ስፍራውን አጥቶ ሲቸገር ይታያል፣ የ1980ው ህትመት የተጨማሪ መጽሐፍት መጨረሻ ላይ ሲያስቀምጠው የ2000ው ህትመት ደግሞ የተጨማሪ መጽሐፍቱ 2ኛ መጽሐፍ አድርጎ አስቀምጦታል።። ሄኖክ

“ከሙሴ በፊት የነበረና ያስተማረውም በማቱሳላ ዘመን ነው” መባሉን ስንመለከት ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱ በተቀናበረበት ክሮኖሎጂ(የታሪክ የጊዜ ቅደም ተከተል) መሠረት መጽሐፉ ከአሪታት በፊት መሆን ነበረበት፣ እንደዚያ እንዳይደረግ ደግሞ ሙሴ ይህንን መጽሐፍ ትቶ ነው “በመጀመርያ” ብሎ መጽሐፍ ቅዱሱን የጀመረው፣ በዚህም መጽሐፉን ከሙሴ መጽሐፍ ፊት ማስቀመጥ አይቻልም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ መጽሐፈ ሄኖክ ላይ የተፃፉት ታሪኮች የብሉይ ኪዳኑና የአዲስ ኪዳን ታሪኮች በመሆናቸው መጽሐፉ መግባት የነበረበት በአዲስ ኪዳኑ መሆን ነበረበት ነገር ግን መጽሐፉ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍትን የማይመስል በመሆኑ አዲስ ኪዳኑ ውስጥም ማስገባት አይቻልም፡፡

ይህ የሄኖክ መጽሐፍ ትክክኛ ስፍራ አጥቶ መነገላታትም የሚያሳየው መጽሐፉ የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆኑን ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ተጨማሪ መጽሐፍቱ የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ቋሚ ስፍራ አጥተው በየጳጳሳቱ ወዲያ ወዲህ ሲንገላቱ እንመለከታለን፡፡ እጅ የራሱ ስፍራ አለው፣ ዓይን፣ ጆሮ … ሁሉም የሰውነት ክፍሎች የየራሳቸው ስፍራዎች አሏቸው ነገር ግን የሰውነት አካል ያልሆነን ተጨማሪ አካል ሰውነት ላይ ለመጨመር ብንሞክር ማስቀመጫ ስፍራ ያስቸግራል፣ አሸጋሸገን ለማስቀምጥ ብንሞክር እንኳን ተለይቶ ይታወቃል፣ አሁንም እነዚህን መጽሐፍት የገጠመው ችግር ይኸው ነው፣ መጽሐፍቱ የመጽሐፍ ቅዱሱ አካላት ባለመሆናቸው በቅዱሳኑ መጽሐፍት መካከል ትክክኛ ስፍራ አጥተው እየተቸገሩ ይገኛሉ፡፡

66ቱ መጽሐፍት እንደዚህ አይነት ችግር ሳይገጥማቸው በዘመናትና በአብያተ ክርስቲያናቱ ውስጥ የራሳቸውን ቋሚ ስፍራ መያዛቸው የ66ቱን መጽሐፍት ትክክለኛነት የሚያረጋግጥ ሲሆን የተጨማሪ መጽሐፍቱ ትክክለኛ ስፍራ ማጣት ደግሞ የመጽሐፍቱን የመጽሐፍ ቅዱስ አካል አለመሆን ያረጋግጥልናል፡፡

4.3.4.4. <u>የመጽሐፍቱ መቼት መፋለስ</u>

በ4.3.4.1 ክፍል እንደቀረበው ተጨማሪ መጽሐፍቱ ብሉይ ኪዳን ያልተገባላቸው ግሪክና ኢትዮጵያ ከኒቂያ ጉባዔ እና የመጽሐፍ ቴክኖሎጂ መፈጠር በኋላ ማዘጋጀታቸውን ተመልክተናል፣ ከዚህ በተጨማሪ፣ ተጨማሪ መጽሐፍቱ ከላይ በሄኖክ መጽሐፍ ላይ እንደተመለከትነው፣ በብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አንድም ስፍራ ላይ የማንመለከታቸውን የአዲስ ኪዳን ቃላትን እየተጠቀሙ ሲፅፉ እንመለከታለን፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፡-

- ኢየሱስ
  - ክርስቶስ - ዕዝራ ሱቱኤል 5፡28-29
  - ወልድ - ተረፈ ኤርምያስ ፲፡45, ዕዝራ ሱቱኤል ፲2፡26
  - የአብ ልጅ - ሲራክ 24፡3
  - ፈራጅ - ተረፈ ኤርምያስ ፲፡46

- አብ - ተረፈ ኤርምያስ ፲፡45, ዕዝራ ሱቱኤል 12፡26
- ማርያም - ሲራክ 24፡10, ዕዝራ ሱቱኤል 3፡7
- ጴጥሮስ - ሲራክ 24፡28
- ሐዋርያት - ሲራክ 24፡2, ተረፈ ኤርምያስ ፲፡52
- ቤተክርስቲያን - ሲራክ 32፡6
- *መንግሥተ ሰማያት* - ፲ኛ መቃብያን 6፡፲፡
- *መስቀል* - ዕዝራ ሱቱኤል 12፡6-7, ዕዝራ ሱቱኤል 12፡35
- ሐሰተኛው ክርስቶስ - ዕዝራ ሱቱኤል 3፡6

ከነዚህ የአዲስ ኪዳን ቃላት በተጨማሪ የአዲስ ኪዳን ድርጊት ዘገባም በቀጥታ ቀርቧል፣ ለምሳሌ አንድ አረፍተ ነገር ወስደን ብንመለከት፣

> ሲራክ 24፡1-12 “ወላድ ሰውነታን በተዋህዶ ታከብራለች … እኔ ከእግዚአብሔር አብ ተወለድኩ … ካምስት ሺ አምስት መቶ ዘመን አስቀድሞ የህዝቡንና የአህዛቡን ሲጋ አልተዋሃድሁም፡፡ ከዚህ በኋላ እረፍትን ፈለግሁ፣ እንግዴስ የማንን ሲጋ እዋሃዳለሁ፡፡ ከዚህ በኋላ ሁሉን የፈጠረ አብ አዘዘኝ ሁሉን የፈጠረ አብ ሲጋን አዋሀደኝ … በሱ ፈቃድ የከበረ የማርያም ማኅፀን ስጋን ተዋሃድሁ በምኩራብ አስተማርሁ፡፡ በቤተመቅደስም እንደዚሁ አስተማርኩ አብ ባስገዛኝ በኢየሩሳሌምም ወንጌልን አስተማርኩ፡፡ በብዙ የእግዚአብሔር አብ ርስት እድል በሆኑ በሐዋርያት መካከል ቀዳሚነቴን አስተማርኩ፡፡”

ይህ ታሪክ ምንም እንኳን ብዙ ስህተቶች ቢኖሩበትም በውስጡ ግን የምንመለከተው ታሪክ የአዲስ ኪዳን ታሪክ(የኢየሱስ ታሪክ) የድርጊት ዘገባ እንጂ የብሉይ ኪዳን ታሪክ ወይ ትንቢት አይደለም፣ ይህም እውነታ ተጨማሪ መጽሐፍቱ የተዘጋጁት በአዲስ ኪዳን ዘመን መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ተጨማሪ መጽሐፍቱ የያዟቸው ታሪኮች ላይ የመቼት(የጊዜና የስፍራ) መዛባት መታየቱን ይህም ተጨማሪ መጽሐፍቱ የመጽሐፍ ቅዱስ አካል መሆን የማይችሉ ቅድስና የሌላቸው መጽሐፍት መሆናቸውን ያሳያል፡፡

4.3.4.5. ተረቶችና ግራ የተጋቡ ትምህርቶችን እንደ ፈጣሪ ቃል መያዙ

ከላይ በ4.3.3 ክፍል እንደቀረበው “የሄኖክ *መጽሐፍ*” የተባለው መጽሐፍ ተረቶችና ግራ አጋቢ ትምህርቶች የፈጣሪ ቃል አድርጎ ማቅረቡን ተመልክተናል፣ ሌሎቹም መጽሐፍት የተፃፉት በአንድ መንፈስ በመሆኑ እነሱም ጋር ተመሳሳይ ችግር እንመለከታለን፣

- **<u>ተረት ተረቶች</u>**

1. <u>ፀሐይ ትሰማለች፣ አደራም ትቀበላለች</u>
   ተረፈ ኤርምያስ 8፡18-19 "ያን ግዜ ኤርምያስ የቤተመቅደሱን መክፈቻ ይዞ ከከተማ ወደ ውጪ ወጣ፡፡ ይህንንም መክፈቻ ፀሐይን የእግዚአብሔር ማደሪያ የቤተመቅደስ መክፈቻ ተቀበል ብሎ በፀሐይ ፊት ጣለው፡፡"
2. <u>ምድር ትሰማለች፣ ሰምታም ትታዘዛለች</u>
   ተረፈ ኤርምያስ 8፡13 "ባሮክና ኤርምያስ ወደ ቤተመቅደስ ገቡ የሚያገለግሉበትን ዕቃ ሁሉ ... ለምድር ሰጪት ማድርም ያን ግዜ ተቀብላ ዋጠችው፡፡"
3. <u>ጨረቃ ኮከብን ትበልጣለች</u>
   ሲራክ 43፡8 "ጨረቃስ እንደ ስሟ ናት ከዋክብትም እንድትበልጥ ድንቅ ነው፡፡"
   ዛሬ ላይ ፀሐይን ጨምሮ ብዙ ግዙፍ ጨረቃን ይቅርና መሬትን እንኳን የሚበልጡ ከዋክብት መገኘታቸውን ስንመለከት ቃሉ የፈጣሪ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡
4. <u>የሚናገር ይባሱኑም የሚያሾፍ ድንጋይ</u>
   ተረፈ ኤርምያስ 11፡60 "ያን ጊዜም ያ ደንጊያ እናንተ ሰነፎች የእስራኤል ልጆች ኤርምያስን መስያችሁ በደንጊያ ስለምን ትወግሩኛላችሁ፣ ኤርምያስስ እነሆ በመካከላችሁ ቆሟል ብሎ ጮኸ፡፡"
5. <u>ከሰው ጋር የሚነጋገር ኃይማኖተኛ አሞራ</u>
   ተረፈ ኤርምያስ 10፡23-32 "ባሮክም እንዲህ ያለ ፅሀፊት ፅፎ ከመቃብር ቤት ወጣ ንስሩም ኃይማኖትን የምታስተምር ባሮክ ሆይ "ቸር አለህ" አለው፡፡ ባሮክም ከሰማይ አእዋፍ ሁሉ የተመረጥክ አንተ ትናገራለህና ባይኖችህ ብርሃን የታወቅህ ነህ ... ባሮክም ደብዳቤውን ያዘ ከዚያ አቤሜሌክ ከሰጠው ከበለሱ ሙዳይ አስራ አምስቱን በለስ አምጥቶ በንስሩ አንገት ቋጠረው ... ለኤርምያስ ከሱ ጋር ላሉ እስራኤላውያን ውሰድ ... አእዋፍ ሁሉ ቢከቡህ ይገድሉ ዘንድ ወደው የኃይማኖት ጠላት ሁሉ ቢከቡህ በኃይማኖትህ ቀድመኻቸው ሂድ፡፡"
6. <u>ሙታንን የሚያስነሳ አሞራ</u>
   ተረፈ ኤርምያስ 11፡4-6 "ንስሩ በታላቅ ድምፅ "አምላክ የመረጠህ ኤርምያስ ሆይ ላንተ እነግርሀለሁ፣ ሄደህ ህዝቡን ሁሉ ሰብስባቸው ... አለው ... ህዝቡም በተሰበሰበ ጊዜ ንስሩ በሬሳው ላይ ቆመ በዚህ ሰዓት ሙቱ ተነሳ፡፡"
7. <u>66 አመት ተኝቶ እንቅልፉን ያልጨረሰ ሰው</u>
   ተረፈ ኤርምያስ 9፡1-2 "አቤሜሌክም ኤርምያስ ከላከው ስፍራ በቀትር ጊዜ በለሱን አመጣ ጽፍቅ ያለች ዱርንም አገኘ ጥቂትም ያርፍ ዘንድ በጥላዋ ስር ተቀመጠ በለስ ያለባትንም ሙዳይ ተንተርሶ ስድሳ ስድስት አመት ተኛ

ከመኻታውም አልነቃም፡፡ ከዚያ ዘመን በኋላ ከመኻታው ነቅቶ ተነሳ ገና ራሴን ከብደኛልና እንቅልፌን አልጨረስኩምና ጥቂት ብተኛ በጎ ነገር ነው አለ፡፡"

8. በምድረ በዳና በባህር ውስጥ ያሉ ዓለም ያላየቻቸው አውሬዎች

ሄኖክ 16፡12 እና 41 "... ስሟ ሌዋታን የሚባል ሴቲቱ አውሬ በውሀዎች ምንጮች ላይ በባህሩ ጥልቅ ትኖር ዘንድ ተፈጠረች፡፡ የማይታየውን ምድረ በዳ በደረቱ የሚይዝ ስሙ ብሔሞት የሚባል የወንዱም አውሬ ስፍራው በየብስ ነው፡፡"

ዕዝራ ሱቱኤል 4፡49-52 "(በፍጥረት ቀናት) በአምስተኛው ቀን ... የፈጠርካቸው ሁለቱ እንስሳት (ብሔሞትና ሌዋታን) ... አራቱ ተራሮች ባሉበት በዚያ ስፍራ እሱ በውስጡ ይኖር ዘንድ ለብሔሞት ከስድስተኛው እጅ አንዱን እጅ የብስን ሰጠኸው፡፡ ሰባተኛውንም እጅ ባህሩን ለሌዋታን ሰጠኸው፣ ለምትወዳቸው ለፃድቃን ምግብ ይሆኑ ዘንድ ሌዋታንና ብሔሞትን ጠበቅሀቸው፡፡"

9. እንደጎረሰ ተሰንጥቆ የሞተ ዘንዶ

ተረፈ ዳንኤል 13፡26-27 "(ዳንኤልም) ንጉሥ አንተ ይህንን ዘንዶ (ንጉሡ የሚያመልከውን) ያለ ሰይፍና ያለ በትር እገድለው ዘንድ አሰናብተኝ አለው፣ ንጉሡም አሰናበትኩህ አለው፡፡ ዳንኤልም ጠጉርና አደሮ ማር ስብ አምጥቶ አንድነት ቀቀለው ልህሉህ አደረገው ለዘንዶውም በአፉ አጎረሰው፣ ያም ዘንዶ በጎረሰው ጊዜ ተሰንጥቆ ሞተ ዳንኤልም ጣኦቶቻችሁን እዩ አለ፡፡"

10. ሦስት ሺ ክንድ የሚረዝሙ ሰዎች

ሄኖክ 2፡12-16 "እነሱም ፀንሰው ረጃጅሞች አርበኞች ልጆችን ወለዱ ቁመታቸውም ሦስት ሦስት ሺ ክንድ ነው ... ረጃጅሞቹ ልጆች አባት እናቶቻቸውን ይበሉዋቸው ዘንድ ወደ መብላት ተመለሱ ... እርስ በርሳቸውም ስጋቸውን ተባሉ ከሷም ደምን ጠጡ፡፡"

ሄኖክ 4፡85-86 "ከደመና የሚደርሱ ረጃጅም ሰዎችም ፈፅመው ይጠፋሉ እስበሳቸውም ይጣላሉ በዚህ ዓለም ሰውን ያጠፋሉ፡፡ በሰውም ሀዘን ያደርጋሉ እነሳቸውም የሚበሉትን እህል ምንም አያገኙም፡፡"

11. ምድር የታነፀችው ውሀ ላይ ነው

1ኛ መቃብያን 23፡1 "ዓለሙን ሁሉ ካለመኖር ወደ መኖር አምጥቶ ፈጠረ ኮረብቶችንና ተራሮችንም ፈጽሞ አዘጋጀ ምድርንም በውሀ ላይ አፀናት ባህርም እንዳትነዋወጥ ባሸዋ ወሰናት እግዚአብሔር በመጀመርያ ቃሉ ብርሃን ይፈጠር ብሏልና፡፡"

12. ሰው የሚመራመረው በኩላሊቱ ነው

ዕዝራ ሱቱኤል 3፡34 "... የእግዚአብሔርን ስራ መርምሬ አውቅ ዘንድ የፍርዱንም ምስጢር መርምሬ አውቅ ዘንድ ኩላሊቴን ስላተጋኸ ነው እንጂ..."

- **<u>ግራ የተጋቡ ትምህርቶች</u>**
  1. ሲራክ 8፡12-13 “ለባለጸጋ ኢታበድረው … ባለጸጋውን አትዋሰው …”
  2. ሲራክ 13፡9 “ባለጸጋ ያዘዘህን ለጊዜው እሺ በለው …”
  3. ሲራክ 16፡1 “ጥቅም የሌላቸውን ብዙ ልጆችን አትውደድ።”
  4. ሲራክ 26፡16 “የዋህ ሴት ለእግዚአብሔር <u>እድሉ</u> ናት።”
  5. ሲራክ 26፡19 “ነገር ለምትታገስ ሴት ለውጥ የላትም።”
  6. ሲራክ 35፡22 “በፈቃድህ ፀንቶ የሚኖረውን ልጅህን ስንኳ አትመነው።”
  7. ሄኖክ 41፡1-3 “ከብዙ ቀንም በኋላ ልጁ ማቱሳላ ልጁ ላሜህን ሚስት አጋባው፤ ከሱም ፀንሳ ወንድ ልጅ ወለደች። <u>ሰውነቱም እንደ እንቁ ነጭ ሆነ፣ እንደ ፅጌረዳም ቀይ ነው</u> … ዓይኖቹን በገለጠ ጊዜ ቤቱን ሁሉ እንደ ፀሐይ አበራ …”
     የዚህ ህፃን ከለር ነጭ ነው? ወይስ ቀይ?
  8. ሄኖክ 16፡3 “ያን ግዜ እለተ <u>እሁድ ገንዘቡ የሆነች ጌታን</u> በጌትነቱ ዙፋን ተቀምጦ አየሁ።”
     ሌላውስ ቀን ምኑ ነው?
  9. ተረፈ ኤርምያስ 10፡5 “ከዚህ በኋላ የታመነ ክርስቶስ ይመጣል፣ ወደ ሬሳሽም ይመልስሻል፣ መጠርጠር ወደ ሌለው ኃይማኖትሽ ተመልከች።”
  10. እስቲ ይህ ጊዜ መች እንደሆነ አስሉት፣
      ዕዝራ ሱቱኤል 13፡48 “እንዳዘዘኝም አደረግሁ፣ በአራተኛው ዘመን ከሚቆጠሩ ከብዙ ሱባኤ ባምስተኛው ሱባኤ ይህ ዓለም በተፈጠረ ካምስት ሺህ ዘመን ኋላ ጨረቃ ሰርክ ባደረገች ጨለማዋን በአጣች በአስረኛው ቀን በሦስተኛው ወር በዘጠና አንደኛው ይህን ሁሉ ፅፎ…”
  11. ጦቢት 1፡1 “እኔ ጦቢት በህይወት መኖርሁበት ዘመን በሚገባና በውነት ስራ ፀንቼ ኖርሁ።”
      ይህ ሰውዬ “በህይወት በኖርኩበት ዘመን” ማለቱ መጽሐፉን የፃፈው ሞቶ ነው እንዴ?
  12. ፲ኛ መቃብያን 19፡9 “ዳዊት በኃጢያተኛ ዲያብሎስ ትዕቢት አዳም ይጠፋል ብሎ እንደተናገረ አባታችን አዳም በዲያብሎስ ትዕቢት ከእግዚአብሔር በታዘዘ በእውነተኛ ፍርዱ ተፈርዶበታልና አጎሳቆላቸው።”
  13. ፲ኛ መቃብያን 19፡14 “ካባቶቻቸው በህፃንነታቸው አደራ ያልዋቸው ትእዛዙንም አላፈረሱም አባቶቻቸው ካባቶቻቸው የእግዚአብሔር አምልኮት ዘጠኙንም ሕግጋት እንደተማሩ።”

እነዚህና መሰል የተጨማሪ መጽሐፍቱ ግራ የመጋባት ችግሮች በ66ቱ መጽሐፍት ውበት እንድንደነቅና ከእግዚአብሔር የሆነና ያልሆነውን በአፃፃፉ መንፈስ ብቻ መለየት እንድንችል ረድቶናል።

ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ እነዚህና መሰል ተረቶችና ግራ የተጋቡ ነገሮች የገቡበት የራሱ ዓላማ አለው፣ ዓላማውም መጽሐፍ ቅዱሱን የተረት መጽሐፍ በማስመሰል ተቀባይነቱን ማሳጣት ነው፣ ኤቲስቶችም መጽሐፍ ቅዱሱ ብሎም ፈጣሪ ላይ የድፍረት ንግግር እንዲናገሩ እያደፋፈሯቸውም ካሉት ምክንያቶች ውስጥም አንደኛው እነዚህና መሰል ተረት ተረቶችና ግራ የተጋቡ አስተምህሮዎች በመጽሐፉ ውስጥ መግባታቸው ነው::

4.3.4.6. እርስ በራሱ እንዲሁም ከ66ቱ መጽሐፍት ጋር መጋጨቱ

ተጨማሪ መጽሐፍቱ እርስ በርስ እንዲሁም ቅድስናቸው ከተረጋገጡት ከ66ቱ መጽሐፍት ጋር ሲጋጩ እንመለከታለን፣ ይህ ደግሞ መጽሐፍቱ በአንዱ በእግዚአብሔር መንፈስ አመራር አለመፃፋቸውን ያረጋግጥልናል::

4.3.4.6.1. እርስ በራሱ መጋጨቱ

ፈጣሪ ሁሉን አዋቂ በመሆኑ ቃሉን አይለውጥም በዚህም ቃሉ እርስ በርስ አይምታታበትም ነገር ግን የቤተክርስቲያኗ ተጨማሪ መጽሐፍት ላይ ሊታገሱት የማይችሉት እርስ በርስ ግጭት እንመለከታለን:-

1. **ሰይጣን የተጣለበት ምክንያት**

ለአዳም አልሰግድም በማለቱ

3ኛ መቃብያን 1:15 "... ለሚዋረድልኝ ለአዳም አልግድም በማለቱ እግዚአብሔር ስለ አባታቸው ስለ አዳም ከማዕረጌ አዋርዶኛልና::"

ፈጣሪንም ባለማመስገኑ

3ኛ መቃብያን 2:8-9 "... በትዕቢትህና በልቦናህ ፅናት ፈጣሪህንም በማሳዘን ፈጣሪንም ባለማመስገን አንተ ከእግዚአብሔር ትዕዛዝ ወጥተህ በወነጀልህ ጊዜ... ስለ ከፉ ስራህ ከማዕረግህ አዋረደህ ..."

2. **መንግሥተ ሰማያትን ንቀው የተዉት አሉ ወይስ ማንም አላየውም?**

አይተው የተው አሉ(የአዳም ልጅ የሆነው የ"ሴት" ዘሮች ትተውታል)

ሄኖክ 4:69-71 "... ለደቂቀ ሴትም ሄደህ ንገራቸው ... ዘላለም ፀንቶ የሚኖር መንግሥተ ሰማያት ስለምን ተዋችሁ::"

ማንም አላየውም

1መቃብያን 14:20 "... ዓይን ያላየውን ጆሮም ያልሰማውን በሰው ልቡናም ያልታሰበውን እግዚአብሔር በህይወት ሳሉ ደስ ላሰኙት ለሚወዱት ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ ያዘጋጀውን ይሰጣቸው ዘንድ ..."

3. **የመቃቢስ ልጆች ሬሳ ተቀበረ ወይስ ተሰወረ?**

ተቀበረ

1ኛ መቃብያን 4:7 "ምክርንም መከረ የሚያደርገውንም አጣ ከዚህም በኋላ መቃብር ቆፍሮ ያምስቱን ሰማዕታት ሬሳቸውን ቀበረ::"

ተሰወረ

2ኛ መቃብያን 7፡9 “ይቀብራቸው ዘንድ ወደልና ከዚህ በኋላ የፃድቃንን ሬሳ ወደ ጣለበት ስፍራ ሂዶ ሬሳቸውን እንዳይነካ እግዚአብሔር ሰውራቸዋልና ነገር ግን አጣቸው።።”

4. <u>መቃቢስ ቢኒያማዊ ወይስ ሞአባዊ ነው?</u>

<u>ቢኒያማዊ</u>

1ኛ መቃብያን 2፡1 “ከነገደ ቢኒያም የተወለደው ስሙ መቃቢስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ።።”

<u>ሞአባዊ</u>

2ኛ መቃብያን 1፡2-6 “የሶርያና የኤዶምያስ ሰዎች አማሌቃውያን የኢየሩሳሌምን አገር ካጠፋው ከሞዓቡ ሰው ከመቃቢስ … የእስራኤልም ልጆች በበደሉ ጊዜ የሞአብ ሰው መቃቢስን አስነሳባቸው …”

5. <u>ለሞተ ሰው የሚደረግ ስነ ስርዓት ትርጉም አለው ወይስ የለውም?</u>

<u>ትርጉም አለው</u>

ሲራክ 7፡33 “… ለሞተ ሰውም ተዝካር ማውጣት አትተው።።”

<u>ትርጉም የለውም</u>

ሲራክ 17፡28 “የሞተ ሰውን ግን ንስሀ እንደ ኢምንት አለፈው …”

6. <u>በባቢሎን ወረራ ወቅት ንዋየ ቅዱሳቱ እንዴት ሆኑ?</u>

<u>ተደበቁ</u>

ተረፈ ኤርሚያስ 8፡13 “ባሮክና ኤርሚያስም ወደ ቤተመቅደስ ገቡ፣ የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ሰጣት፣ ምድርም ያን ጊዜ ተቀብላ ዋጠቸው።።”

<u>ተዘረፉ</u>

ዕዝራ ካልዕ 1፡54 “እግዚአብሔርን የሚያገለግሉበት ንዋየ ቅዱሳቱን ጥቃቅኑንምና ታላላቁንም ዕቃ ሁሉ የእግዚአብሔር ማደሪያ ታቦትንም ከቤተመንግሥት ዕቃ ቤትም ያለውን ሳጥኑን ሁሉ ማርከው ወደ ባቢሎን ወሰዱ።።”

ዕዝራ ሱቱኤል 9፡21-22 “ቤተ መቅደሳችን እንደፈረሰ … የህጋችን ማደርያ ታቦተ ጽዮን እንደተማረከች … ኢታይምን።።”

7. <u>በባቢሎን ወረራ ወቅት ቤተመቅደሱ ምን ሆነ?</u>

<u>ሰዎች እንዳይደፍሩት ተቆልፎ ተቀመጠ</u>

ተረፈ ኤርምያስ 8፡13 “የቤተ መቅደሱንም መክፈቻ ፀሐይን “የእግዚአብሔርን ማደሪያ መክፈቻ ተቀበል” ብሎ በፀሐይ ፊት ጣለው።።”

<u>ተቃጠለ</u>

ዕዝራ ካልዕ 1፡55 “የእግዚአብሔር ቤት ማደሪያ መቅደስንም አቃጠሉ የኢየሩሳሌምንም ቅፅሯን አፈረሱ ግንቧንም በእሳት አቃጠሉ።።”

8. <u>መጽሐፈ ባሮክ የፃፈው ማነው?</u>

<u>ባሮክ</u>

ባሮክ 1፡1-2 “የኬልቅዩ ልጅ ሴዴቅያስ የሴዴቅዩ ልጅ የማሴው ልጅ ኔርዩ የኔርዩ ልጅ <u>ባሮክ ወደ ባቢሎን የፃፈው መጽሐፍ ነገር ይህ ነው</u>።።”

<u>ኢኮንያን</u>

ባሮክ 1፡3-4 “ከይሁዳ ንጉሥ ከኢዮአቄም ልጅ <u>ከኢኮንያን የተፃፈውን</u> ከህዝቡ ዘንድ ወደሱ የመጣውን።። የባቢሎን ሰዎች የእግዚአብሔር ማደሪያ ንዋየ ቅዱሳቱ ከቤተ መቅደስ በወሰዱ ጊዜ በኢየሩሳሌም ወዳሉ ካህናት የላከውንም <u>ይህንን መጽሐፍ ባሮክ አነበበ</u>።።”

እነዚህ እርስ በርስ መጋጨቶች ተጨማሪ መጽሐፍቱ የእግዚአሔብር ቃል አለመሆናቸውን ያረጋግጥልናል።።

4.3.4.6.2. <u>ከ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር መጋጨቱ</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ተጨማሪ መጽሐፍቱ እርስ በርስ ሲጋጩ ነበረ ነገር ግን ግጭቱ በዚህ የሚያቆም ሳይሆን በቤተክርስቲያኗ እንኳን ቅድስናቸውን ከመሰከረችላቸው 66ቱ መጽሐፍትም ጋርም ነው፣ ይህ ደግሞ ማንነታቸውን በገሀድ እንድናውቅ ያደርጋል፣

1. <u>አዳም ከምን ተፈጠረ?</u>

<u>ከአፈር፣ እሳት፣ ውሀና ንፋስ</u>

3ኛ መቃብያን 4፡10 “በከበሩ እጆቹ <u>ከምድር መሬትን</u> አምጥቶ <u>እሳትና ውሀ ንፋስንም</u> ጨምሮ በሱ ምሳሌና መልክ አዳምን ፈጠረው።።”

<u>ከአፈር</u>

ዘፍ.2፡7 “እግዚአብሔር አምላክም ሰውን <u>ከምድር አፈር</u> አበጀው...”

2. <u>አዳምና ሄዋን የበሉት ከእውቀት ዛፍ ወይስ ከበለስ ዛፍ</u>

<u>ከበለስ ዛፍ</u>

ዕዝራ ሱቱኤል 1፡7 “ዕፀ በለስን አትብላ ብለህ አዘዝከው እሱ ግን ትዕዛዝህን አፈረሰ...”

ነመቃብያን 27፡17-18 “እናታችን ሄዋን በእባብ ማሳት ተሸንግላ ከዚያ ከዕፀ በለስ በልታ ላባታችን ለአዳም ሰጠችው።። አዳምም ከዚያ ዕፀ በለስ በልቶ በልጆቹና በራሱ ሞትን አመጣ።።”

<u>የበሉት ከእውቀት ዛፍ ሲሆን የለበሱት ደግሞ የበለስ ዛፍ ቅጠል ነው</u>

ዘፍ.2፡17 “... መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ ...”

ዘፍ.3፡7 “... የበለስንም ቅጠሎች ሰፍተው ለእነርሱ ለራሳቸው ግልድም አደረጉ ...”

3. <u>ቃየል አቤልን ለምን ገደለው?</u>

<u>በሴት</u>

ነኛመቃቢያን 19፡1-2 “... እርሷ መልከ መልካም ነበረችና ስለ እርስዋ ከገደለው ከደግ ሰው ከአቤል ሚስት ... ልጆች ዳግመኛ ለቃየን ተወለዱለት።። ወንድሙን ከገደለው በኋላ ... እርስዋን ወሰደ።።”

ነኛመቃብያን 23፡1-2 "... (ቃየን)በሴት ቀንዶ ወንድሙን ገደለው።፡"

<u>እግዚአብሔር የአቤልን መስዋዕት ተቀብሎ የቃየልን ስለተወ በዚያ ንዴት</u>

ዘፍ.4፡4-8 "... እግዚአብሔርም ወደ አቤልና ወደ መስዋዕቱ ተመለከተ፤ ወደ ቃየንና ወደ መስዋዕቱ ግን አልተመለከተም።፡ ቃየንም እጅግ ተናደደ ፊቱም ጠቆረ... ቃየንም ወንድሙን አቤልን።፡ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው።፡ በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሳበት፣ ገደለውም።፡"

4. <u>የሰዎችና መላዕክት ጋብቻ?</u>

<u>ይቻላል</u>

ኩፋሌ 6፡9 "የአዳም ልጆች ... ሴቶች ልጆች ተወለዱላቸው ... የእግዚአብሔር መልአክትም ... አገቡዋቸው፣ ወንዶች ልጆችንም ወለዱላቸው እነሱም ረአይት ናቸው።፡"

<u>አይቻልም፣</u> (መላዕክት ተፈጥሮአቸውም ከሰው የተለየ ነው፣ ሰው ቁሳዊ ሲሆን መላዕክት መናፍስት ናቸው፣ መንፈስ ደግሞ እንደ ቁሳዊው አካል ስጋና አጥንት የለውም)

- ማቴ.22፡30 "(ሰዎች) በትንሳኤ እንደ እግዚአብሔር መላዕክት በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም።፡"
- ሉቃ.24፡39 "... መንፈስ ስጋና አጥንት የለውም ..."

5. <u>እስከ ሙሴ ያሉት ፃድቃን በአንድ መቃብር ነው የተቀበሩት ወይስ የተለያየ ስፍራ?</u>

<u>አንድ ስፍራ</u>

ነኛመቃብያን 10፡1-2 "ነገር ግን እንዲህ ካልሆነ የቀደሙት ሰዎች ከአዳም ጀምሮ ከሴትና ከአቤል፣ ከሴምና ከኖህ፣ ከይስሐቅና ከአብርሃም፣ ከዮሴፍና ከያዕቆብ፣ ከአሮንና ከሙሴ ጀምሮ በአባቶቻቸው መቃብር ይቀበሩ ዘንድ ነው፣ እንጂ በሌላ ስፍራ ይቀበሩ ዘንድ ያልወደዱ ለምንድነው? በትንሳኤ ጊዜ ከዘመዳቸው ጋር አንድነት ሊነሱ አይደለምን፣ አጥንታቸውስ ጣኦት ከሚያመልኩ ... ጋር እንዳይቆጠር አይደለምን፣ በሌላ ስፍራ ይቀበሩ ዘንድ ያልወደዱ ለምንድነው?"

<u>የተለያየ ስፍራ</u>

<u>አብርሃምና ያዕቆብ፡-</u> አብርሃም የተቀበረው ከኤፍሮን በገዛው እርሻ ስፍራ በሚገኘው አዲስ ባዘጋጀው የመቃብር ስፍራ መሆኑን በዘፍ.23፡13-20 እና በዘፍ.50፡13 ላይ እንመለከታለን።፡

<u>አሮን፡-</u> በመሪባ ውሀ ዘንድ ስላመፃችሁ ወደ እስራኤል አይገባም ብሎ እግዚአብሔር በመቆጣቱ "ወደ ሖር ተራራ ይውጣ በዚያ ይሙት ወገኖቹ ይከማች" በተባለው መሠረት በተራራው ራስ ላይ እንደሞተና አብረውት የሄዱት ሙሴና ልጁ ... እዚያው ተራራው ላይ ትተውት እንደወረዱ በዘኁ.20፡23-29 ላይ ተጠቅሳል።፡

<u>ሙሴ፡-</u> ሙሴ ወደ እስራኤል ምድር እንደማይገባ እግዚአብሔር በመናገሩ(ዘዳ.34፡4)፣ በሞአብ ምድር መሞቱ(ዘዳ.34፡5)፣ መቀበሩ(ዘዳ.34፡6) እና የመቃብር ስፍራውንም ማንም ሰው እንደማያውቀው(ዘዳ.34፡6) እንመለከታለን።፡

6. ናቡከደነፆር ለምን በእግዚአብሔር ተቀጣ?

“ፀሐይን የማወጣው እኔ ነኝ” ስላለ

ነመቃ.5፡3-4 “… በዚህ ዓለምም ፀሐይ የማወጣ ፈጣሪ እኔ ነኝ ብሎ ኮራ፣ ከትዕቢቱም የተነሳ እንዲህ አለ፡፡ እግዚአብሔርም ከሰው ለይቶ ሰባት አመት ወደ ምድረ በዳ ሰደደው፡፡”

“በታላቂቱ” ባቢሎን በመታበዩ

ዳን.4፡30 “ንጉሡም ይህች እኔ በጉልበቴ ብርታት ለግርማዬ ክብር የመንግሥት መኖሪያ እንድትሆን ያሰራኋት ታላቂቱ ባቢሎን አይደለችምን፣ ብሎ ተናገረ፡፡ ቃሉም ገና በንጉሡ አፍ ሳለ ድምፅ ከሰማይ ወደቀና ንጉሥ ናቡከደነፆር ሆይ … ከሰዎች ተለይተህ ትሰደዳለህ … ሰባት ዘመናትም ያልፉብሃል፡፡”

7. አፍቅሮተ ነዋይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው አይደለም?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው

ሲራክ 5፡ነ “… ገንዘብ በቃኝ አትበል፡፡”

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም

ዕብ.ነ3፡5 “አካሄዳችሁ ገንዘብ ያለመውደድ ይሁን፣ ያላችሁ ይብቃችሁ፡፡”፣

ነጢሞ.6፡6-ነ0 “ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው … የገንዘብ ፍቅር የክፉት ሁሉ ስር ነውና፡፡”

8. ያለዝሙት ችግር መፋታት ይቻላል?

አዎን

- ሲራክ 25፡25 “ግብርዋ እንደ ግብርህ ካልሆነች ፍታት ከሰውነትህም ለያት፡፡”
- ተረፈ ኤርምያስ ነ1፡27-28 “ከናንተ ሴቶችን ያገባ ወንድን፣ ወንዶችንም ያገቡ ሴቶችንም ፍተናቸው አለው፣ ቃልህን የሰሙ ሰዎች ወደ ኢየሩሳሌም መልሳቸው፣ ያልሰሙህንም ሰዎች ግን ወደሷ ይገቡ ዘንድ አትተዋቸው አለው … ይህንንም ነገር ሲነገራቸው ያገቡ ሰዎች … ሊፋቱም አልወደዱም፡፡”
- ሲራክ 25፡ነ6 “ከደረቅ ሴት ጋር ከምትኖር ከምድር አውሬና ከአንበሳዎች ጋር መኖር ይሻላል

ፈፅሞ የተከለከለ ነው

ማቴ.5፡32 “ያለዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ …”

9. ፅላተ ሙሴ የተሰራው በምንድነው?

በዕንቁ ነው

ኩፋሌ ነ፡ነ “… እግዚአብሔር፡- ከእኔ ዘንድ ወደዚህ ተራራ ውጣ፣ በፃፍከው መጠን ልብ ታስደርጋቸው ዘንድ ህጉና ስረአቱ የተፃፈባቸውን ሁለቱን የዕንቁ ፅላት እሰጥሃለሁ ብሎ ለሙሴ ተናገረ፡፡

በድንጋይ ነው

ዘጸ.24፡12 “እግዚአብሔርም ሙሴን … ታስተምር ዘንድ እኔ የፃፍሁትን ሕግና ትዕዛዝ የድንጋይም ፅላት እሰጥሃለሁ፡፡”

ዘጸ.31፡18 “… በእግዚአብሔር ጣት የተፃፈባቸውን ከድንጋይ የሆኑ ሁለቱን የምስክር ፅላቶች ሰጠው፡፡”

10. የያዕቆብ ልጅ የሆነው የብንያም ልጆች እነማን ናቸው?

ኩፋሌ 31፡21 “የብንያምም ልጆች አስቤልና ላውባኤል፣ ንእማንና ጉአው፣ ራኤፍስና አብሮድዮ፣ አፈ፟ምና ያኒም፣ ጋዕሞና የአም ከእርሱ ጋር እነዚህ አስራ አንድ ናቸው፡፡”

ዘፍ.46፡21 “የብንያም ልጆች ቤላ፣ ቤኬር፣ አስቤል፣ የቤላ ልጆችም ጌራ፣ ናዕማን፣ አኪ፣ ሮስ፣ ማንፌን፣ ሑፊም፤ ጌራም አርድን ወለደ፡፡”

11. ንጉሡ አስቴር እንድትገባ መፈቀዱ የታወቀው ዘንጉን አንዴት አድርጎ በማሳየቱ ነው?

(እዚህ ጋር የአስቴር መጽሐፍት በሁለቱም፣ በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስና በተጨማሪው መጽሐፍ፣ ስላሉ ሁለቱን ለመለየት የተጨማሪውን መጽሐፍ አስቴር አዋልድ ሲባል ሌላኛውን ደግሞ አስቴር ቀኖና ተብሏል)

ዘንጉን አንገቷ ላይ አድርጎ

አስቴር(አዋልድ) 5፡2 “(ንጉሡ) የወርቁን ዘንግ አንስቶ በአንገቷ ላይ አኖረው፡፡”

ዘንጉን ዘርግቶ

አስቴር(ቀኖና) 5፡2 “… ንጉሡም በእጁ የነበረውን የወርቁን ዘንግ ለአስቴር ዘረጋላት፡፡”

12. በባቢሎናውያን ወረራ ጊዜ የቤተመቅደሱ እቃዎች ተዘረፉ ወይስ ከዝርፊያ አመለጡ?

አመለጡ

ተረፈ ኤርሚያስ 8፡13 “ባሮክና ኤርሚያስ ወደ ቤተመቅደስ ገቡ፣ የሚያገለግሉበትንም ዕቃ ሁሉ ጌታ እንዳዘዛቸው ለምድር ሰጣት፤ ምድርም ያን ጊዜ ተቀብላ ዋጠችው፡፡”

ተዘረፉ

2ኛዜና.36፡18-19 “የእግዚአብሔር ቤት ዕቃ ሁሉ፣ ታላቁንና ታናሹን፣ የእግዚአብሔርን ቤት መዝገብ፣ የንጉሡንና አለቆቹን መዝገብ፣ እነዚህን ሁሉ ወደ ባቢሎን ወሰደ። የእግዚአብሔርንም ቤት አቃጠሉ፣ የኢየሩሳሌምንም ቅጥር አፈረሱ፣ አዳራሾችዋንም በእሳት አቃጠሉ፣ መልካሙን እቃ ሁሉ አጠፉ፡፡”

13. በባቢሎን ወረራ ወቅት ነብዩ ኤርሚያስ ወደ ባቢሎን ተወሰደ ወይስ እዚያው ይሁዳ ቀረ?

ወደ ባቢሎን ተወሰደ

ተረፈ ኤርምያስ 8፡21 “ኤርምያስም ለወገኖቹ ሲያለቅስ እያዳፉ አወጡት፤ ከህዝቡም ጋር እስከ ባቢሎን ድረስ ወሰዱት፡፡”

ይሁዳ ቀረ

ኤር.40፡2-6 “የዘበኞቹም አለቃ ኤርምያስን ወሰደው እንዲህም አለው … አሁንም እነሆ በእጅህ ካለችው ሰንሰለት ዛሬ ፈታሁህ፡፡ ከእኔ ጋር ወደ ባቢሎን መምጣት መልካም መስሎ ቢታይህ ና … መልካም መስሎ ባይታይ ግን ተቀመጥ፤ እነሆ አገሪቱ ሁሉ በፊትህ ናት … የዘበኞቹም አለቃ ስንቅና ስጦታ ሰጥቶ አሰናበተው፡፡ ኤርምያስም የአኪቃ ልጅ ጎዶሊያስ ወዳለበት ወደ ምፅጳ ሄደ፣ ከእርሱም ጋር በአገሩ ውስጥ በቀሩት ህዝብ መካከል ተቀመጠ፡፡”

14. ዳንኤል አሽከር የነበረው በንጉሥ ቂሮስ ወይስ በንጉሥ ናቡከደነፆር ዘመን ነበረ?

በንጉሥ ቂሮስ

ተረፈ ዳንኤል 13፡1-2 “ንጉሥ ዳርዮስ ሙቶ ባባቶቹ መቃብር ከተቀበረ በኋላ የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ መንግሥቱን ያዘ፡፡ ዳንኤልም የንጉሥ የቂሮስ እልፍኝ የአሽከር ነበር፤ ከባለማሎቹም ሁሉ እሱ ይከብር ነበር፡፡”

በንጉሥ ናቡከደነፆር

ዳንኤል በባቢሎን አሽከር ሆኖ ያገለገለው በልጅነቱ ሲሆን ይህም በናቡከደነፆር የንግሥና ዘመን ነበረ(ዳን.1፡1-21)፣ ከዚያ በኋላ ዳንኤል ንጉሥ ናቡከደነፆር የተጨነቀበትን ህልም ስለገለጠ፣ ዋነኛ አለቃ ተደረገ (ዳን.2፡48) ከዚያም ቀጥሎ የተነሳው ንጉሥ ብልጣሶርም እንዲሁ ዳንኤልን በመንግሥቱ ላይ ሦስተኛ ገዢ አደረገው(ዳን.5፡29)፣ በዳሪዮስ መንግሥት ዘመንም ዳንኤል እንዲሁ ባለስልጣን ነበረ (ዳን.6፡2)፣ በቀጣዩ በቂሮስ ዘመንም ዳንኤል የተቃና ኑሮ ነበረው(ዳን.6፡28)፣ ስለዚህ የዳንኤል የአሽከርነት ዘመን በናቡከደነፆር እንጂ በቂሮስ ዘመን አልነበረም፣ ቂሮስ እንደ ዳንኤል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበረ(ዕዝ.6፡3፣ ኢሳ45፡1 …) እንጂ በተቃርኖ መንገድ አልነበረም፡፡

15. ዳንኤል በአንበሶች ጉድጋድ የተጣለው በማን የንግሥና ዘመን ነው?

በቂሮስ

ተረፈ ዳንኤል 13፡1-29 “ንጉሥ ዳርዮስ ሞቶ በአባቶቹ መቃብር ከተቀበረ በኋላ የፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ መንግሥቱን ያዘ … እጅግ እንዳስጨነቁት ባየ ጊዜ ለንጉሡም ግድ በሆነበት ጊዜ ዳንኤልን ሰጣቸው፡፡ ወደ አንበሶች ጉድጋድ ጣሉት፡፡”

በዳርዮስ

ትንቢተ ዳንኤል 6፡1-6 “ዳርዮስም በመንግሥቱ ሁሉ ዘንድ እንዲሆኑ መቶ ሃያ መሳፍንት በመንግሥቱ ላይ ይሾም ዘንድ ወደደ … ከእነርሱ አንደኛው ዳንኤል ነበረ … የዚያን ጊዜ ንጉሡም አዘዘ፣ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጉድጋድ ጣሉት፡፡”

16. ዳንኤል ወደ አናብስቱ ጉድጓድ የተጣለበት ምክንያት ምንድነው?

ዳንኤል የባቢሎናውያኑን አማልክትና አገልጋዮቻቸውን ስለገደለ

ተረፈ ዳንኤል 13፡28 “ከዚህ በኋላ የባቢሎን ሰዎች በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቆጡ ወደ ንጉሡም በነገር ተመለሱ ቤልን(ጣኦት) ሰበረ ካህናቱንም ገደለ ዘንዶውንም ገደለ … እጅግ

እንዳስጨነቁት ባየ ጊዜ ለንጉሡም ግድ በሆነበት ጊዜ ዳንኤልን ሰጣቸው፡፡ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

<u>ዳንኤል"ስግደት ወደ ንጉሡ ብቻ" የተባለውን ሕግ ተላልፎ ወደ አምላኩ ስለፀለየ</u>

ዳን.6፡11-17 "እነዚያም ሰዎች ተሰብስበው ዳንኤልን ወደ በአምላኩ ፊት ሲፀልይና ሲለምን አገኙት፡፡ ወደ ንጉሥም ቀርበው … ንጉሥ ሆይ ከይሁዳ ምርኮኞች የሆነው ዳንኤል በየእለቱ ሦስት ጊዜ ልመናውን ይለምናል እንጂ አንተንና የፃፍከውን ትዕዛዝ አይቀበልም አሉት … የዚያን ጊዜ ንጉሡም አዘዘ፣ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

17. <u>ንጉሡ ዳንኤል በአናብስት ጉድጓድ እንዲጣል የፈቀደው ለምንድነው?</u>

<u>ህዝቡ የንጉሡን ቤት ለማቃጠልና ለመዝረፍ ስለዛተ</u>

ተረፈ ዳንኤል 13፡29 "ዳንኤልን ይሰጠን ዘንድ ኑ ወደ ንጉሥ እንሂድ፡፡ ይህ ካልሆነ እንገድልሃለን ገንዘብህንም እንዘርፍሃለን ቤትህን በእሳት እናቃጥላለን እንለዋለን አሉ፡፡ ንጉሥም እጅግ እንዳስጨነቁት ባየ ጊዜ ለንጉሥም ግድ በሆነበት ጊዜ ዳንኤልን ሰጣቸው፡፡ ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

<u>ሕግህ "የማይለወጥ ነው" ብለው ስለፈተኑት</u>

ዳን.6፡14-15 "ንጉሡም … ያድነው ዘንድ ልቡን ወደ ዳንኤል አደረገ … የዚያን ጊዜ እነዚያ ሰዎች ወደ ንጉሡ ተሰብስበው ንጉሡን፣ ንጉሥ ሆይ ንጉሡ ያፀናው ትዕዛዝ ወይም ስርዓት ይለወጥ ዘንድ እንደማይገባ የሜዶንና የፋርስ ሕግ እንደሆነ እወቀወ አሉት፡፡ የዚያን ጊዜ ንጉሡ አዘዘ፣ ዳንኤልንም አምጥተው ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት፡፡"

18. <u>ዳንኤል በአናብስቱ ጉድጓድ ውስጥ ስንት ቀን ቆየ?</u>

<u>ሰባት ቀናት</u>

ተረፈ ዳንኤል 13፡30 "ወደ አንበሶች ጉድጓድ ጣሉት በዚያ ሰባት ቀን ተቀመጠ፡፡"

<u>አንድ ለሊት</u>

ዳን.6፡16-22 "… ዳንኤልን አምጥተው በአንበሶች ጉድጓድ ጣሉት … ንጉሡም ወደ ቤቱ ሄደ ሳይበላም አደረ … እንቅልፉም ከእርሱ ራቀ፡፡ በነጋውም ማልዶ ተነሳ፣ ፈጥኖም ወደ አንበሶች ጉድጓድ ሄደ፡፡ ወደ ጉድጓዱም ወደ ዳንኤል በቀረበ ጊዜ በሃዘን ቃል ጠራው … ዳንኤልም ንጉሡን፣ ንጉሥ ሆይ ሺ አመት ንገሥ … የዚያን ጊዜም ንጉሡ እጅግ ደስ አለው፣ ዳንኤልንም ከጉድጓድ ያወጡት ዘንድ አዘዘ፡፡"

19. <u>ቤተመቅደስ እንዲሰራ የታዘዘው ዳዊት? ወይስ ልጁ ሰሎሞን?</u>

<u>ዳዊት</u>

ዕዝራ ሱቱኤል 1፡22-23 "ዘመነ አበው አለፈ ዘመነ መሳፍንትም ተጨረሰ ስሙ ዳዊት የሚባል አገልጋይህን ለመንግሥት አስነሳህ፡፡ ስምህ ሊመሰገንበት መስዋዕትህን ሊሰዋበት ቤተመቅደስ ይሰራ ዘንድ ስራ አልከው፡፡"

ሰሎሞን

1ነገ.8፡19 እና 2ዜና.6፡9 “(እግዚአብሔርም ዳዊትን) ከወገብህ የሚወጣው ልጅህ እርሱ ለስሜ ቤትን ይሰራል እንጂ ቤት የምትሰራልኝ አንተ አይደለህም አለው፡፡”

20. የመጨረሻው ቀን ይታወቃል?

አዎን ይታወቃል

ዕዝራ ሱቱኤል 2፡37 “ይህ ዓለም በሚዛን ተመዝኗል ባህርንም በላዳን ሰፍሮታልና፣ ዘመኑንም በ8 ሺ ወስኖታልና፡፡”

አይታወቅም

ማር.13፡32-33 “ስለዚያች ቀን ወይ ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም፡፡ ጊዜው መች እንደሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፣ ፀልዩም፡፡”

ማቴ.24፡42-43 “ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ፡፡”

21. መላዕክት መቼ ተፈጠሩ?

በስድስቱ የስነፍጥረት ቀናት

ኩፋሌ 2፡5-7 “በመጀመሪያው ቀን (የተለያየ አገልግሎት ያላቸው) መላዕክት ተፈጠሩ፡፡”

ከስድስቱ የስነፍጥረት ቀናት በፊት

በስድስቱ የስነፍጥረት ቀናት ወቅት መላዕክቱ(መናፍስታዊ ፍጡራን) እንደነበሩ መጽሐፍ ቅዱሱ ይናገራል፡፡

ኢዮ.38፡4-7 “ምድርን በመሠረትሁ ጊዜ አንተ ወዴት ነበርህ፣ ታስተውል እንደሆንህ ተናገር፡፡ ብታውቅስ መስፈሪያዋን የወሰነ፣ በላይዋስ የመለኪያ ገመድ የዘረጋ ማነው፣ አጥቢያ ኮከቦች ባንድነት ሲዘምሩ፣ የእግዚአብሔር ልጆች ሁሉ እልል ሲሉ፣ መሠረቶችዋ በምን ላይ ተተክለው ነበር፣ የማዕዘንዋንስ ድንጋይ ያቆመ ማነው፣”

22. ሰው የተፈጠረው ለምንድነው?

ሰይጣን ስለወደቀ

3መቃብያን 2፡11 “አንተ(ሰይጣንን) በተመካህ ጊዜ እግዚአብሔር ክፉ ስራህን አይቶ አንተ ከሰራዊቶችህ ጋራ እግዚአብሔርን ከደሃልና ሳያጓድል ስሙን ያመሰግን ዘንድ ስላንተ ፈንታ የሚያመሰግን አዳምን ፈጠረው፡፡”

የቁሳዊው ዓለም “ገሸ” እንዲሆንና ገነትን “ያበጃትና ይጠብቃት” ዘንድ ነው

ዘፍ. 1፡26 “እግዚአብሔርም አለ፡፡ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤ የባህር አሶችን የሰማይ ወፎችን፣ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፣ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ይግዙ፡፡”

ዘፍ.2፡15 “… እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው፡፡”

23. <u>እግዚአብሔር አብርሃምን የተናገረው በሰይጣን ምክር ነው ወይስ ለራሱ አስቦ</u>

<u>በሰይጣን ምክር</u>

ኩፋሌ 14፡1 "ሁሉን የሚገዛ ሰይጣን መጥቶ በአምላክ ፊት ቆሞ እንዲህ አለ፣ እነሆ አብርሃም ልጁ ይስሐቅን ይወደዋል ከሁሉ ይልቅ እርሱ ደስ ያሰኘዋል በመሰዊያ ላይ መስዋዕት አድርጎ ያቀርበው ዘንድ <u>ንገረው</u>፡፡ ይህን ነገር ቢያደርግ አንተ ታያለህ በምትፈትነው ሁለ እርሱ የታመነ እንደሆነ ታውቃለህ አለው፡፡"

<u>በእግዚአብሔር ሐሳብ</u>

እግዚአብሔር፣ አብርሃም ልጁን እንዲሰዋ ያዘዘው በሰይጣን ምክረ ሐሳብ ሳይሆን ጥልቅ በሆነ መንፈሳዊ አመክንዮ ነው፣ እግዚአብሔር አብርሃም <u>አንድያ ልጁን</u> እንዲሰዋ ያዘዘው በዋናነት የአብርሃምን እምነት ለመመልከት ቢሆንም በልጁ ፋንታ በግን የታረደበት ተምሳሌት ግን ስለሰው ልጆች ኃጢያት ስለሚሰዋው <u>የራሱ አንድያ ልጅ</u> የኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕትነት ለማሳየት ነው፣ በይስሐቅ ፋንታ በጉ እንደተሰዋው በሰው ልጅ ፋንታም ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተዋ ለማሳየት ነው፡፡

24. <u>መንግሥተ ሰማያት በብሉይ ኪዳን ተዘጋጅቶ ነበር ወይስ ኢየሱስ ነው የሚያዘጋጀው?</u>

<u>በብሉይ ኪዳንም ነበረ አይተው የተዉትን ነበሩ</u>

ሄኖክ 4፡71 "... ዘላለም ፀንቶ የሚኖር መንግሥተ ሰማያት ስለምን ተዋችሁ፡፡"

<u>አዲስ ነው የሚያዘጋጀውም ኢየሱስ ነው</u>

ዮሐ.14፡2-3 "(ኢየሱስም) ... ስፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፣ ሄጀም ስፍራ ባዘጋጅላችሁ፣ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛም እመጣለሁ ወደ እኔም እወስዳችኃለሁ፡፡"

1ቆሮ.2፡9 "... ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው ..."

25. <u>አዳምና ሄዋን የተፈጠሩበት ጊዜ የተለያየ ነው? ወይስ አንድ ቀን ነው?</u>

<u>የተለያየ ነው</u>

ኩፋሌ 4፡8 "በመጀመሪያዪቱ ሱባኤ አዳም ተፈጠረ፣ ሁለተኛይቱም ሱባኤ ሄዋንን ፈጥሮ አሳየው ..."

<u>አንድ ነው፣ በስድስተኛቀው ቀን</u>

ዘፍ.1፡2 "እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ ... ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው... ስድስተኛ ቀን፡፡"

26. <u>ሐዋርያት ስጋዊውን ጦርነት ይዋጋሉ?</u>

<u>አዎን ይዋጋሉ</u>

ሄኖክ 33፡58-39 "ለሐዋርያትም ታላቅ ስልጣን እስኪሰጣቸው ድረስ ደርሼ አየሁ ሐዋርያም ከውቀት ምድረ በዳ ወደ ሆኑ ወደ አህዛብ ሁሉ ሊያጠፋቸው ወጡ፡፡ በከፍታ የሚኖሩት አህዛብ ሁሉ ከፊታቸው ሸሹ፡፡"

<u>አይዋጉም</u>

ኤፌ.6፡12 “መጋደላችን ከደምና ከስጋ ጋር አይደለምና ከአለቆችና ከስልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማው ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊውም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።”

27. <u>ኃጢያት ይበላለጣል?</u>

<u>ይበላለጣል</u>

ሲራክ 20፡25-26 “ሐሰት ከመናገር መሥረቅ ይሻላል።”

ሲራክ 18፡15 “ከፉ ነገር ተናግሮ ከመስጠት በጎ ነገር ተናግሮ መንሳት ይሻላል”

<u>አይበላለጥም</u>

ያዕ.2፡8-13 “ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፣ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፣ ባይዋሽ ነገር ግን ብትሰርቅ ያው ሕግ ተላላፊ ሆነህል።”

28. <u>ቀማኛ የቀማውን ገንዘብ መልሶ ንስሃ መግባት አለበት? ወይስ የገንዘቡን አጠቃቀም መማር አለበት?</u>

<u>አጠቃቀሙን ማስተማር</u>

ሲራክ 5፡8 “... ቀምተህ ላመጣኸው ገንዘብ አትሳሳ።”

<u>ለተቀማው ሊመለስና ለራስም ንስሃ እንደሚያስፈልግ</u>

ሚኪ.6፡10 “በውኑ በኃጢያተኛ ቤት የኃጢያት መዝገብ ፣ የተፀየፈም ውሽተኛ መስፈሪያ ገና አለ ይሆን፣”

ሐስ.8፡22 “እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ ...”

29. <u>የሞቱ ፃድቃንን ማመስገን ይገባል አይገባም?</u>

<u>ይገባል</u>

ይህ ሐሳብ በሲራክ መጽሐፍ ብዙ ስፍራዎች ተጠቅሷል፣ “እናመስግናቸው” የሚለውም አብርሃምን (44፡19)፣ ሙሴ (45፡1)፣ አሮን (45፡6)፣ ፊንሀስ (45፡23)፣ ኢያሱ (46፡1)፣ ካሌብ (46፡7)፣ ሳሙኤል (46፡13)፣ ኤልሳዕ (48፡12-16)፣ ሕዝቅያስ (48፡17-25)፣ ኢዮስያስ (49፡1-5)፣ ሕዝቅኤል (49፡8-9)፣ ዘሩባቤል (49፡12)፣ ነህምያ (49፡13)፣ ስምዖን (50፡1-24)።

<u>ትርጉም የለውም</u>

የሞቱትን ፃድቃን እንደ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ስለማይገኙ እነሱን ማመስገን ትርጉም የለውም፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ላይ ስንመለከት ምስጋና የሚቀርበው ለእግዚአብሔር ብቻ ሲሆን ለሌሎች አካላት ማቅረቡም ኃጢያት ነው(ኢሳ.42፡8)።

ተጨማሪ መጽሐፍቱ እንደዚህ ከዋናው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር የመጋጨታቸው እውነታ የመጽሐፍቱ ምንጭ ተቃራኒው መንፈስ መሆኑን ያሳያል።

4.3.4.7. ሰይጣናዊ አሻራዎች

ተጨማሪ መጽሐፍቱ ከእግዚአብሔር ቃላት ጋር የሚጋጩ በመሆናቸው ምንጫቸው ከዲያብሎስ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፣ ይህንንም ግምታችንን የሚያረጋግጡ ሰይጣናዊ አሻራዎችም ደግሞ በመጽሐፍቶቹ ውስጥ ይታያሉ፣ ይህም፣

- ከ66ቱ መጽሐፍት ተቃርነው ከቁርአን ጋር መደጋገፋቸው፣
- ለሰይጣን ሽፋን መስጠታቸው፣
- የጥንቆላ አሰራር ማስተማራቸው

ሲሆን ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

4.3.4.7.1. ከ66ቱ መጽሐፍት ተቃርነው ከቁርአን ጋር መደጋገፋቸው

ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ መሆናቸውን በምዕራፍ 2 ተመልከተናል፣ ተጨማሪ መጽሐፍቱ ቁርአንና መጽሐፍ ቅዱሱ እርስ በርስ ሲጋጩ ቁርአኑን በመደገፍ ሲናገሩ እንመለከታለን፣

- ዲያብሎስ ለአዳም አልሰግድም በማለቱ ተጣለ
  መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ዲያብሎስ የተጣለው ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር በማወዳደሩ ነው(ኢሳ.14፡12-16, ሕዝ.28፡2 ...) ነገር ግን ቁርአኑ ላይ ስንመለከት ዲያብሎስ የተጣለው "ለአዳም አልሰግድም በማለቱ ነው" (2፡34, 17፡61, 7፡11-13 ...) በዚህ አከራካሪ ጉዳይ ላይ ተጨማሪ መጽሐፍቱ የሚወግኑት ለቁርአኑ ነው፣ 3ኛ መቃብያን 1፡15 ላይ ይህንን የቁርአኑን ታሪክ እናገኛለን፡፡
- የሰውና መላዕክት ጋብቻ
  66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ መላዕክት ከሰው ጋር ይቅርና እርስ በርሳቸው ራሱ እንደማይጋቡ ይናገራል(ማቴ.22፡30) ነገር ግን ኩፋሌ 6፡9 ላይ ከዚህ ቃል በተቃራኒ ቁርአኑ 17፡40 ላይ እንደተገለፀው ሰውና መላዕክት እንደሚጋቡ ይናገራል፡፡
- ምንኩስና
  ተጨማሪ መጽሐፍቱ ስለ ምንኩስናና ተያያዥ ጉዳዮች ይነግሩናል ደብር(1ኛ መቃብያን 19፡1-12፣ ሄኖክ 2፡2)፣ ገዳም(ሲራክ 2፡1)፣ ባሕታዊ(ሲራክ 11፡5)፣ ለዚህ አሰራር ድጋፍ የምናገኘው 66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሳይሆን ቁርአኑ ላይ ነው(57፡27) ፣ በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አንድም ስፍራ ላይ ይህንን ታሪክ አናገኘውም፣ በ4.4.1.2 ክፍል እንደተመለከተው እነዚህ አሰራሮች ከ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ተቃራኒ አሰራሮች ናቸው፡፡

- <u>ገዳም</u>
  ተጨማሪ መጽሐፍቱ ስለ ገዳም ያስተምራሉ(ሲራክ 2፡1)፣ ለዚህ ቃል ድጋፍ የምናገኘው ቁርአኑ 22፡40 ላይ ነው ነገር ግን በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ አንድም ስፍራ ላይ ገዳም የሚል ቃል የለም፣ በ4.4.1.2 ክፍል እንደተመለከተው የገዳም አሰራር ከ66ቱ መጽሐፍ አንፃር ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡
- <u>የመላዕክት አማላጅነት</u>
  ተጨማሪ መጽሐፍቱ ስለ መላዕክተ አማላጅነት ያስተምራሉ፣ በ66ቱ መፅፍት አማላጅ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ በ4.1.1.2 ክፍል ተመልክተናል፣ ይህ የመላዕክት አማላጅነት አስተምህሮ ግን የመጣው ከቁርአኑ(53፡26) ነው፡፡
- <u>የቅዱሳን አማላጅነት</u>
  ተጨማሪ መጽሐፍቱ ስለ ቅዱሳን አማላጅነት ያስተምራሉ፣ በ66ቱ መፅፍት አማላጅ ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ በ4.1.1.3 ክፍል ተመልክተናል፣ ይህ የቅዱሳን ሰማያዊ አማላጅነት አስተምህሮ ግን ከርስቲያናዊ ሳይሆን ቁርአናዊ ነው(40፡7)፣
- <u>ለሴቶች ያለው ጥላቻ</u>
  66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ገላ.3፡28 “... ወንድም ሴትም የለም፣ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና፡፡” ቢልም ተጨማሪ መጽሐፍቱ ግን ከዚህ በተቃራኒ፣ ከቁርአኑ ጋር በአንድ መንፈስ፣ ለሴቶች በጾታቸው ምክንያት ብቻ ያለውን ጥላቻ ሲገልፅ እንመለከታለን፣
  - ሲራክ 42፡13 “ከልብስ ብል ይገኛል ኃጢያትም <u>ሁሉ</u> ከሴቶች ይገኛል፡፡
  - ሲራክ 25፡21 “መቅሰፍት ናትና ጥፋትም ናትና ፅኑ ውርደትም ናትና የሴት መልከዋ አያስትህ”
  - ሲራክ 42፡14 “ከሴት ቸርነት የወንድ ንፍገት ይሻላል፡፡”
  - ሲራክ 25፡24“... ለሴትም የልብህን ምስጢር አታውጣላት፡፡”
  - ሲራክ 9፡2 “ምስጢርህን እንዳታወጣብህ ለሴት ልብህን አትስጣት፡፡”
  - ሲራክ 42፡9 “ሴት ልጅ ላባቷ የተሰወረ ቁርጥማት ናት፡፡”

ይህ ተጨማሪ መጽሐፍቱ ከቁርአኑ ጋር አንድ ሆነው ከ66ቱ ቅዱሳን መጽሐፍት ጋር የመጋጨታቸው እውነታ የመጽሐፍቱን ምንጭ ያሳያል፡፡

4.3.4.7.2. ለሰይጣን ሽፋን መስጠታቸው

66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ሰይጣን አሳሳች፣ ክፉ ... መሆኑን ይናገራል ተጨማሪ መጽሐፍቱ ግን ከዚህ በተቃራኒ ሰይጣን እንደ እግዚአብሔር፣ ቅዱሳንና መላዕክት መሆኑን በዘዴ ይነግሩናል፣

1. **<u>ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር? ወይስ ሰይጣን?</u>**
   <u>ሰይጣን</u>
   ኩፋሌ 14፡2 "ሁሉን የሚገዛ ሰይጣን ..."
   <u>እግዚአብሔር</u>
   ራዕ. 19፡6-15 "... ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ..."
2. **<u>ሰውን የሚጠብቀው እግዚአብሔር ወይስ ውቃቢ?</u>**
   <u>ውቃቢ(ሰይጣናዊ ኃይል)</u>
   ኩፋሌ 15፡16 "መልአክ ውቃቢ ለበጎ ነገር ይጠብቅሀልና ..."
   <u>እግዚአብሔር</u>
   መዝ.121፡5 "እግዚአብሔር ይጠብቅሀል፡፡"
3. **<u>በቅዱሳን ስም የሚሰራ የተቃርኖ መንፈስ</u>**
   <u>ሕግን በልቦና መፃፍ የማን ድርሻ ነው?</u>
   <u>የሄኖክ</u>
   ሄኖክ 4፡5 "ሕግን በሰው ልቦና የምፅፍ እኔን ሄኖክን ..."
   ሄኖክ 4፡68 "... ሕግን በሰው ልቡና የምትፅፍ ሄኖክ ..."
   <u>የእግዚአብሔር</u>
   ዕብ.10፡15-16 "ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፤ በልባቸው ህጌን አኖራለሁ በልቡናቸው እፅፈዋለሁ፡፡"
   እዚህ ጋር ራሱን "ሄኖክ" ብሎ የቀረበው ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር የሚያወዳድር የእግዚአብሔር ተፎካካሪ መንፈስ ነው፣ እሱም ዲያብሎስ ነው፡፡
4. **<u>በመላዕክት ስም የሚሰራ የተቃርኖ መንፈስ</u>**
   ሄኖክ 19፡1 "በዚያችም ቀን ቅዱስ ሚካኤል <u>የመንፈስ ቅዱስ እውቀቱ ወደ ሀዘን ይወስደኛል ያበሳጨኛል</u> ብሎ ለቅዱስ ሩፋኤል መለሰለት፡፡"

   እዚህ ጋር በ"ሚካኤል" ስም ራሱን የሰየመው አካል፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በተደጋጋፊነት ሳይሆን በተቃርኖ አሰላለፍ ያለ ኃይል ነው፣ እሱም ዲያብሎስ ነው፣ ብስጭቱም የመጣው መንፈስ ቅዱስ የዲያብሎስን ዕቅድ አስቀድሞ ለቅዱሳኑ ስለሚያሳውቅ ነው፣ በዚህም ዲያብሎስ በ"ሚካኤል" ስም እየተንቀሳቀሰ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡

*መ*ጽሐፍ ቅዱሱ ይህ አሰራር ሊኖር እንደሚችል ቀድሞውኑ በማስጠንቀቁ ግራ መጋባቶች እንዳይፈጠሩ ረድቶናል፣ 2ቆ.11፡14 "ይህ ድንቅ አይደል፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣል::"

5. **<u>ቅዱሱን መንገድ መሳደቡ</u>**

ራዕ.13፡6 "እግዚአብሔርን ለመሳደብ ስሙንና ማደሪያውንም በሰማይ የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ::"

ይህንን ተሳዳቢ *መ*ንፈስ በተጨማሪ *መ*ጽሐፍቶቹ ውስጥም እንመለከተዋለን፣

- ተረፈ ኤርምያስ 7፡2 "... <u>ዋጋ የሌለውን ከርስቶስን</u> ይሸጡታል፣ ከበሽታ የሚያድነውን ጌታን <u>እንዲታመም</u> ያደርጉታል::"

  "ዋጋ የሌለውን ከርስቶስን" ማለት ምን ማለት ነው? "እንዲታመም ያደርጉታል" ሲባልስ፣ ኢየሱስ *መ*ቼ ታመመ የታመሙትን ፈወሰ እንጂ?
- ተረፈ ኤርምያስ 8፡21 "ኤርምያስም ለወገኖቹ ሲያለቅስ <u>እያዳፋ</u> አወጡት፤ ከህዝቡም ጋር እስከ ባቢሎን ድረስ ወሰዱት::"

  የሚገርመው ኤርምያስ በባቢሎን ምርኮ ወቅት ወደ ባቢሎን አልተወሰደም ከቀሪ ሰዎች ጋር ነው በሀገሩ የቀረው(ኤር.40፡2-6)፣ በዚህም ኤርምያስን ያዳፋት *መ*ጽሐፍቱን የፃፉት እንጂ ባቢሎናውያኑ አይደሉም::

6. **<u>ሰይጣን መልአክ መስሎ የሚተውንበት</u>**

*መ*ልአክና ሰው ይለያያሉ ነገር ግን እዚህ ጋር "መልአክ ነኝ" ብሎ የቀረበው "*መ*ልአኩ" ሩፋኤል በሰው አምሳል ከመቅረቡ በተጨማሪ ሌሎች ውሸቶችንም ሲናገር እንመለከተዋለን፣

- ጦቢት 5፡1-2 "እርሱም(ልጁም) ሰውን ሊፈልግ ሄዶ *መ*ልአኩን ሩፋኤልን አገኘው ነገር ግን *መ*ልአክ እንደሆነ አላወቀም... (*መ*ልአኩም) ... <u>በገባኤል ቤት ነበርኩኝ አለ</u>::"
- ጦቢት 5፡12"(*መ*ልአኩም) እኔስ <u>የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ዘመድ አዛርያ</u> ነኝ አለው::"
- ጦቢት 12፡19 "(እኔ *መ*ልአክ ነኝና) ከእናንተ ጋር አልበላሁም አልጠጣሁም ..." ቢልም ከጦቢያ ጋር *መ*መገባቸውን ጦቢት 6፡5 እንዲሁም ጦቢት 7፡14 "... አሳውን ጠብሰው በሉ" በማለት ሁለቱ አብረው መብላታቸውን እንመለከታለን::

*መ*ጽሐፍ ቅዱስ "ምስክር በሁለት ይፀናል"(ማቴ.18፡16) እንደሚለው ይህም "*መ*ልአክ" ሦስት ጊዜ ዋሽቶ ቅድስና የሌለው ውሸታም *መ*ልአክ መሆኑን በራሱ ላይ አስመሰከረ፣ ስለዚህ ይህ ራሱን ሩፋኤል የሚለው *መ*ልአክ ቅዱስ *መ*ልአክ አይደለም፣ አርሱም *መ*ጽሐፉ ዮሐ.8፡44 ላይ "ሐሰተኛ የሐሰት አባት" የሚለው

ዲያብሎስ ነው፣ በዚህም ሩፋኤል ተብሎ የቀረበው መልአክ ዲያብሎስ መሆኑ ጥርጥር የለውም::

7. <u>ሰይጣን መንፈስ ቅዱስን፣ ኢየሱስና አብ መስሎ የሚተውንበት</u>

የዕዝራ ሱቱኤል መጽሐፍ በአብዛኛው ያተኮረው ዕዝራ(ሱቱኤል) የተባለው ሰውና ዑርኤል የተባለው መልአክ ንግግር ዘገባ ላይ ነው፣ እዚህ መጽሐፍ ላይ ዑርኤል በመጀመርያ መልአክ መሆኑን ይናገር እንጂ በሂደት ውስጥ ግን ራሱን እግዚአብሔር፣ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አድርጎ ነው የሚናገረው፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፣

- እግዚአብሔርን ተመስሎ ሲናገር
  3፡42 "በዘመን ወደ ኋላ ያሉት እንዳይዘገዩ የቀደሙትም ፈጥነው እንዳይነሱ ፍርዴን እንደ ቀለበት አንድ ጊዜ አደረግኋት::"
  3፡48 "... እኔም እንደዚሁ የፈጠርሁትን ይህንን ዓለም በየጊዜው አዘጋጀሁት::"
- አብን ተመስሎ ሲናገር
  ዕዝራ ሱቱኤል 5፡29 "ከዚህ በኋላ ልጄ ክርስቶስ ..."
- ወልድን ተመስሎ ሲናገር
  4፡1 "... ሰው ሆኜ ስጋ ለብሼ አስተምራለሁ"
- መንፈስ ቅዱስን ተመስሎ ሲናገር
  ዕዝራ ሱቱኤል 4፡6 "ፍጡር ያልሆንኩት እኔ በኑብያት አድሬ ..."

ይህ በመላዕክት፣ በእግዚአብሔርና በሥስቱ ሥላሴ ስም የሚንቀሳቀሰው አጭበርባሪው ዲያብሎስ ነው::

ከነዚህ እውነታዎች የምንመለከተው ተጨማሪ መጽሐፍቱ ቅድስና የራቃቸው የዲያብሎስ መልዕክቶች መሆናቸውን ነው::

4.3.4.7.3. <u>የጥንቆላ አሰራር ማስተማራቸው</u>

ጥንቆላ ሰይጣናዊ አሰራር መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሱ ያስተምረናል፣ ይሁን እንጂ ተጨማሪ መጽሐፍቱ ውስጥ ይህ የጥንቆላ አሰራር ቅዱስ ተደርገው ሲዘገቡ እንመለከታለን፣

➢ ከላይ የተመለከተው ራሱን መልአኩ ሩፋኤል ነኝ ብሎ ሲሸውድ የነበረው ሰይጣን የጥንቆላ ስራ ሲያስተምር ደግሞ እስቲ እንመልከተው፣
<u>ጦቢት 6፡6-8</u> "... ያም ልጅ መልአኩን አንተ ወንድሜ አዛርያ የዚህ አሳ ሀሞቱና ጉበቱ ለምንድነው አለው:: መልአኩም ክፉ ጋኔን ያደረበት ቢኖር ወይም የረከሰ ረቂቅ ጋኔን ያደረበት ቢኖር (የአሳውን) ጉበቱና ልቡን ለዚያ ሰው በፊቱ ያጤሱለታል ሴትም ብትሆን ያጤሱላታል ከዚያ በኋላ አይታመምም:: ብልዝ ባለበት ሰው አሞቱን ደቁሰው ይኩሉታል::"

ጦቢት 6፡15-17 እና ጦብያ 8፡1-3"... (መልአኩም ጦቢያን) የጋኔኑ ነገር ግን አያሳዝንህ፡፡ ወደ ጫጉላ ቤት በገባህ ጊዜ የደቀቀ ዕጣን ከዚህም አሳ ከልቡ፣ ከጉበቱ አምጥተህ አጢስበት፡፡ ያንን ጋኔኑ በሸተተው ጊዜ ይሸሻል ለዘለአለሙ አይመለስም(አለው)፡፡

ወደርሷም በገባ ጊዜ የሩፋኤልን ነገር አሰበ የደቀቀ ዕጣን አምጥቶ የዚህን አሳ ጉበቱንና ልቡን ጨምሮ አጤሰው፡፡ ያም ጋኔን መዓዛው በሸተተው ጊዜ እስከ ላይኛው ግብፅ አውራጃ ድረስ ሸሸ፡፡ ይኸም መልአክ ጋኔኑ አስሮ አጋዘው፡፡"

- በቀይና በጥቁር የሚፃፈውን የጥንቆላ አሰራር

  ሄኖክ 19፡16-22 "የመቶ አጋንንት አዝማች ... አራተኛውም ስሙ ፔንሙን ይባላል ... (ለሰው ልጆች) የተሰወረ ጥበብን ሁሉ አስተማራቸው ... በጥቁር ቀለምና በቀይ ቀለም ፅፈው ኃይማኖታቸውን ሊያፀኑ ሰው እንዲህ ያለ ስራ አልተፈጠረም ነበርና..." ፔንሙን የተባለው ሰይጣን ጠንቋዮችና ደብተራዎች የሚጠቀሙበት የጥቁርና ቀይ ቀለም አፃፃፍ ዘዴ ማስተማሩ እሱም ደግሞ እግዚአብሔር ሰዎች እንዲሰሩት ላልፈለገው ጥንቆላ (ሰው ላልተፈጠረለት ስራ) ነው ብሎ በግልፅ መናገሩ ይህም ደግሞ ለኃይማኖታቸው ጥቅም ነው ማለቱ አሳዛኝ ነገር ነው፡፡

እነዚህን እውነታዎች ስንመለከት መጽሐፍቱ ቅድስና የራቃቸው፣ ሰይጣን ወደ ቤተክርስቲያኗ ተደግፎ የገባበት መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በዚህም ምንም እንኳን ተጨማሪ መጽሐፍቱ፣

> 2ጢሞ.3፡16-17 "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በፅድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል፡፡"

በሚል ሰበብ 66ቱ ቅዱሳን መጽሐፍት ላይ ቢጨመሩም መጽሐፍቶቹ ግን፣

- ባለኪዳንዋ እስራኤል የማታውቃቸው "የብሉይ ኪዳን" መጽሐፍት መሆናቸው፣
- የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ አብያተ ክርስቲያናቱና ጳጳሳቱ እንደፈለጉት "ማስተካከላቸው"፣
- የመጽሐፍ ቅዱሱ አካል አለመሆናቸውን በሚመሰክር መልኩ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ ትክክለኛ ስፍራ አጥተው መቸገራቸው፣
- የመጽሐፍቱ መቼት መምታታቱ፣
- ተረቶችና ግራ የተጋቡ ትምህርቶችን እንደ ፈጣሪ ቃል መያዛቸው፣
- እርስ በራስ መጋጨታቸው፣

መጽሐፍቱ ከሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱሱ መጽሐፍት ጋር የማይመሳሉና አብረው መደባለው እንደሌለባቸው እንመለከታለን፣ ከሁሉ በላይ ደግሞ መጽሐፍቱ፣

- ከ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ጋር መጋጨታቸው፣
- ሰይጣናዊ አሻራዎች የሚታዩባቸው መሆኑ፣

መጽሐፍቱ 2ጢሞ.3፡16-17 ተደግፈው ቅዱሳኑን መጽሐፍት ይቀላቀሉ እንጂ መጽሐፍቱ “የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት” ሳይሆን በተቃራኒው ሆነው ነው የምንለከተው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የጨመሩት መጽሐፍት የተጨመሩበት አመክንዮም ሆነ የመጽሐፍቱ ይዘት ፍፁም ከ66ቱ መጽሐፍ የተለየ መሆኑን ተመልክተናል፣ በዚህም እነዚህን ቅድስና የጎደላቸውን መጽሐፍት ከቅዱሱ ከ66ቱ መጽሐፍት ጋር መቀላቀሉ ኃጢያት ነው፡፡

ዕርኩሱን ከቅዱሱ የመቀላቀል ታሪክ በመጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ የተለመደ ታሪክ ነው፣ ምክንያቱም ሰይጣን በህይወት ስላለ፣ እንደዚሁ ደግሞ እውነታው ሲገለጥ እርኩሱን ነገር ከቅዱሱ መለየቱና ማስወገዱም የተለመደ የታሪክ ሂደት ነው(2ዜና.29፡5, 2ዜና.34፡33 ...)፣ ስለዚህ እነዚህን ዕርኩስ ፅሁፎች ከቅዱሱ ለይቶ ማስወገድ የቤተክርስቲያኗ ምዕመናን ተቀዳሚ ስራ ሊሆን ይገባል፡፡

4.4. ከዋናው መጽሐፍ ቅዱስ የሚጋጩ ትውፊቶች

[109] ትውፊት ማለት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲወራረድ የመጣ እምነት፣ ስርዓት፣ ባህል፣ ወግና ልማድ ማለት ነው፡፡ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ያልተጠቀሱትን ስርዓቶች፣ ባህሎች፣ ወጎች … ከትውፊት እንዳገኘች ትናገራለች፡፡

ቤተክርስቲያኗ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ቀጥሎ በትውፊት መመራቷ በመርህ ደረጃ ትክክል ቢሆንም በቤተክርስቲያኗ ከትውፊት ጋር በተያያዘ ያለው ትልቅ ችግር ግን አብዛኞቹ ትውፊቶቿ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር የሚጋጩ መሆኑ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ማንኛውም ትውፊት በፅሁፍ ከሚተላለፈው ከዋናው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ሊጋጭ እንደማይገባ ይናገራል(ማቴ.15፡3-6, ማር.7፡9-13 …)፣ በዚህም ትውፊት ከመጽሐፍ ቅዱሱ ከተጋጨ መስተካከል ያለበት ትውፊቱ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በቤተክርስቲያኗ የሚታዩትና መስተካከል የሚገባቸውን ትውፊቶችን ስንመለከት በዋናነት በሁለት ይከፈላሉ፣ እነሱም የተሳሳቱና አጋንንታዊ ትውፊቶች ናቸው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

4.4.1. የተሳሳቱ ትውፊቶች

ዋነኞቹ የተሳሳቱ ትውፊቶች፣ ለሙታን የሚከናወነው ፍትሀትና ተዝካር፣ በገዳምና በበረሀ ከሰው ተለይቶ መኖር፣ የተሳሳተ የጥምቀት ስነ ስርዓት፣ የተሳሳተ የጾም ትርጓሜ፣ ሴቶችን ከአገልግሎት ማግለል፣ ዝማሬን በያሬዳዊ ስልት መገደብ እና የክር ማሀተብ ሲሆኑ ሁሉንም ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

4.4.1.1. ፍትሀትና ተዝካር

ቤተክርስቲያኗ ራሷን በእግዚአብሔር የፈራጅነት ወንበር ላይ በማስቀመጥ ሟቾችን “ቅዱሳንና ኃጢያተኞች” በማለት በሁለት በመክፈል፣ ቅዱሳን ለምትላቸው የአማልዱን ፀሎት፣ ምስጋና፣ ውዳሴ … ስትፈፅም፣ “ኃጥአን” ላለቻቸውን ደግሞ ለኃጥያታቸው ስርየትና ነፍሳቸውን ከሲኦል ወደ ገነት ለማስገባት በቀብር ቀን፣ በ 1ኛ፣ 3ኛ፣ 7ኛ፣ 12ኛ … ቀናት የፍትሀትና ተዝካር ስነስርዓቶችን ታከናውንላቸዋለች፡፡

ይህ የፍትሀትና ተዝካር ትውፊት ትክክለኛ ቢሆን ኖሮ በትጋት ሊከናወን በተገባ ነበረ፣ ከዘመድ አዝማድ ባለፈም ለሌሎች በሲኦል ላሉት ለሰው ዘሮች በሙሉ እንኳን ሊደረግ በተገባ ነበረ ምክንያቱም አንድን ነፍስ ከሲኦል አስወጥቶ ገነት ማስገባት ከፍትሀትና ተዝካር ድካምና ወጪ ጋር የማይነፃፀር ነውና ነገር ግን ይህ ምኞት እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ አይደለም፣ ምክንያቱም፡-

[109] በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን፣ መንበረ ፓትርያርክ ጽ/ቤት፣ የሰንበት ትምህርቶች ማደራጃ መምሪያ፣ https://eotcssd.org

1. ሰዎች የሚድኑት በራሳቸው እምነት፣ ዳግም በመወለድ … እንጂ በሰዎች እምነት፣ ዳግም መወለድ … አለመሆኑ፣
   - ማር. 16፡16 “ያመነ የተጠመቀም ይድናል፣ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።”
   - ዮሐ. 3፡3 “… ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም …”
2. የሰዎች መዳን ወይ በፍርድ ስር መውደቅ የሚወሰነው ሰዎቹ ሲሞቱ ሳይሆን ዛሬውኑ በመሆኑ፣
   መጽሐፍ ቅዱስ፣ የመዳን ቀን ዛሬ ነው(2ቆሮ.6፡2) እንደሚለው፣
   > ዮሐ.3፡18 “በእርሱ የሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስላላመነ <u>አሁን</u> ተፈርዶበታል።”

   በማለት ፍርድ አሁኑኑ የሚታወቅ መሆኑን ይነግረናል። የሰማዩ ፍርድ ቤት ደግሞ እንደ ምድራዊው ፍርድ ቤት የይግባኝ አሰራር የለውም ምክንያቱም ፈራጁ ስለማይሳሳትና ይግባኝ የሚባልበት የበላይ አለቃ ስለሌለው።
3. በአፀደ ነፍስ የሚሰጥ ዕድል አለመኖሩ
   > ዕብ.9፡27 “ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት **<u>ከእርሱ በኋላ</u>** ፍርድ ተመደበባቸው።”

   በዚህም አንድ ሰው ከሞተ በኋላ እኛ እዚህ ሆነን በምናከናውንለት ስርዓት የምንጠቅመው ነገር የለም፣ በአፀደ ነፍስ የሚሰጥ ተጨማሪ እድል የለም።

በዚህም ለሞቱት ሰዎች ተብሎ በየጊዜው በመደገስ ገነት ለማስገባት መሞከር ስህተት ነው፣ በሐብት ብዛት ሆነ እጦት፣ በዘመድ ብዝሀነትና በዘመድ ማጣት፣ የፈጣሪ ፍርድ አይቀየርም። በመንግሥተ ሰማያት በሥለስት፣ በአርባ፣ በሰማንያ፣ በአመትና በሰባት አመት የሚደረግ የይግባኝ አሰራርም የለም፣ <u>በክርስቶስ አምኖ ያልዳነ በፍትህትና ተዝካር ድግስ አይድንም</u>።

ስለዚህ የፍትህትና ተዝካር ድግስ ተማምናችሁ ያላችሁ ከሱ ይልቅ የኃጢያት ስርየት ዋስትና የሆነውን ኢየሱስን ዛሬውኑ በአግባብ መያዝ ነው የሚጠቅማችሁ፣ ቤተክርስቲያንም ብትሆን ምዕመናኖቿ በፍትህትና ተዝካር ድግስ ተማምነው እንዲሄዱ ከማድረግ ይልቅ ትክክለኛውን የፅድቅ መንገድ እንዲያውቁ ብታስተምር ነው የሚሻለው።

4.4.1.2. <u>በገዳምና በበረሀ ለመንፈሳዊ ህይወት ተለይቶ መኖር</u>

እንደ አርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ አንድ ሰው ይህን ህይወት የሚመራው ስጋን በመጨቆን፣ ከኃጢያትና ዓለማዊ ነገር በመራቅ ራስን ለመንፈሳዊው ህይወት ብሎም ለፅድቅ ለመለየት ነው። በገዳማትና አብያተ ክርስቲያናት የሚኖሩት መነኩሴ ሲባሉ በየበረሃው የሚኖሩቱ ደግሞ ባሕታዊ ይባላሉ።

ለዚህ አይነት የገዳምና የበረሀ ህይወት ቀጥተኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝ ባይኖርም በቤተክርስቲያኗ አካባቢ በተምሳሌትነቱ የሚነሳው ኢየሱስና ዮሐንስ ከሰው ተለይተው

በረሀ የኖሩበት ኑሮ ነው፡፡ ነገር ግን ኢየሱስና ዮሐንስ ከሰው ተለይተው ወደ በረሀ የወጡት <u>ለተወሰነ ዓላማና ጊዜ</u> እንጂ ለመፅድቅ ብለው አይደለም፣ ከጊዜ በኋላም ወደ ህዝብ በመውጣት የወንጌል ስብከት፣ የማጥመቅ … አገልግሎት ነው ሲሰሩ የነበሩት፤ የምንኩስናና የባሕታዊነት ህይወት ስንመለከት ግን ከዚህ ይለያል፣ ገዳምና በረሀ የሚኬደው እንደ ኢየሱስና ዮሐንስ <u>ለተወሰነ ዓላማ</u> እና <u>ለተወሰነ ጊዜ</u> ሳይሆን ለዕድሜ ልክ ነው፣ በዚህም በሁለቱ መካከል የዓላማ ልዩነትን እንመለከታለን፡፡

ከዚህ በላይ ደግሞ ይህ አይነት ህይወት ከመጽሐፍ ቅዱሱ መርህ የተቃረነ ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱሱ መርህ አንድ መንፈሳዊ እውነታ የበራለት ሰው ለሌሎች ይህንን ብርሃን በማብራት ከጨለማ ያወጣል እንጂ ብርሃኑን ይዞ አይደበቅም፣

> ማቴ.5፡15 “መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል፡፡”

የያዙትን ብርሃን ለሌሎች አለማብራቱ ደግሞ በራሱ ኃጢያት ነው፣ ይህንንም እውነታ በማቴ.25 ላይ በምንመለከታቸው መክሊት በተሰጣቸው ሰዎች ህይወት ውስጥ መመልከት ይቻላል፣ አንድ መክሊት የያዘው መክሊቱን ደብቆ በማስቀመጡና ነግዶበት ባለማትረፉ “ያለውንም ተቀበሉት” ሲባል እንመለከታለን፡፡

ከዚህ መሠረታዊ ተቃርኖ በተጨማሪም እነዚህ ሰዎች ፅድቅን ለማግኘት የሚከተሉት አሰቃቂ “መዳኛ” መንገዶች አዲስ ኪዳናዊ የፅድቅ መንገድ አይደለም፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፣

- [110] “አቡነ አካለ ክርስቶስ ከአንድ ስፍራ ሳይንቀሳቀስ የወይራ ዛፍ ተደግፎ ለ40 አመት በመፀለይ ከእግዚአብሔር ጋር ተገናኝቷል፡፡”
- [111] “አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ለአርባ ቀን ከባህሩ በራሳቸው ቆመው ይፀልዩ ነበር … እግራቸውንም በገመድ አስረው በታላቅ ገድል ቁቁል ተሰቀሉ ሰይጣንም ገመዱን በጠሰው፡፡ ቅዱስ ሚካኤል ተቀበላቸው “ተወኝ በራሴ ልቁም” አሉት በጥርሳቸው ድንጋይ ነክሰው ሠላሳ አመት አልቅሰዋል፣ ጌታ ምሬሀለሁ ብሏቸው ጥርሶቻቸው በድንጋይ ላይ ተተክለው ቀርተዋል፡፡”
- [112]“አቡነ ተ/ኃይማኖት በቁመታቸው ልክ ጉድጓድ ቆፍረው ከፊት ከኋላቸው ከቀኝ ከግራቸው ስምንት ጦር ተክለው ሱባኤ ያዙ፡፡ ከቁመት ገድል የተነሳ አንድ

---

[110] መ/ር ዐሥራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ት/ም/ተቋ/(የግቢ ጉባዔያት) ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ገፅ 103

[111] መ/ር ዐሥራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ት/ም/ተቋ/(የግቢ ጉባዔያት) ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ ገፅ 71

[112] Ibid, ገፅ 62

እግራቸው ተቆርጦ ወድቋል፣ ከዚህ በኋላ በአንድ እግራቸው ቆመው 7 አመት ኖረዋል፡፡"

- [113] "ቅዱስ ነኩቶ ለአብ በቁመቱ ልክ ጉድጓድ አስቆፍሮ በዙሪያው ጦር አበጅቶ ለአርባ አመት ሲሰግድ ነበረ፡፡"
- [114] "ቅድስት ክርስቶስ ሰምራ ከመከራዋ ብዛት ከገድልዋ ጽናት ሰውነቷ ተበሳስቶ የዓሳ መመላለሻ እስኪሆን ድረስ ከባህሩ ገብታ ወደ ግራና ቀኝ ሳትል አስራ ሁለት አመት ፀልያለች፡፡ በፍፃሜ ዘመኗ በቁመቷ ልክ በዓት ሰርታ ከግራ ከቀኝ ከፊት ከኋላ አስራ ሁለት ጦር ተክላ ወዲህ ወዲያ ሳትል አስራ ሁለት አመት ኖራለች፡፡"
- [115] "ቅድስት አመተ ክርስቶስ ለ48 አመት ያህል ሳትንቀሳቀስ እንደ አቡነ ተ/ኃይማኖት የፀለየች ሰው ናት፡፡"

በርግጥ አንዳንዶቹ ታሪኮች እውነተኛነታቸው አጠራጣሪ ቢሆንም መነኮሳቱና ባሕታውያኑ የሚማሩትና የሚለማመዱት የፅድቅ መንገድ ግን ይህ መንገድ ነው፡፡ ነገር ግን በአዲሱ ኪዳኑ ዘመን ፅድቅ የሚገኘው ለራስ ኃጢያት ዋጋ መክራን በመቀበል ሳይሆን ስለ ሰዎች ኃጢያት መክራን በከፈለው በኢየሱስ በማመን ብቻ እንደሆነ በ4.2.3.5 ክፍል በስፋት ተመልክተናል፡፡

በዚህም የምንኩስናና የባሕታዊነት ህይወት የመጽሐፍ ቅዱሱ አስተምህሮ የተቃርኖ ጉዞ መሆኑና ለራስም ነፍስ መዳን የሚያሳጣ መንገድ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

መንፈሳዊውን ነገር ከሲጋዊው ነገር አስበልጦ ለመንፈሳዊ ነገር መለየት ቆራጥነትን የሚጠይቅ አሰራር ቢመስልም አሰራሩ የመጽሐፍ ቅዱሱ ተቃራኒ አሰራር በመሆኑ "ገዳም"፣ "ምንኩስና" የሚል ቃል የምናገኘው በዋናው መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ሳይሆን የመጽሐፍ ቅዱሱ ተቃራኒ በሆነው በቁርአኑ ላይ ነው፣ ምንኩስና(57፡27)፣ ገዳም(22፡40)፣ በዚህም በተቃራኒው መንፈስ ሜራ ላይ መንቃት ተገቢ ነው፡፡

4.4.1.3. <u>የተሳሳተ አጠማመቅ</u>

ቤተክርስቲያኗ የጥምቀት ስርዓትን በዋናነት ውሀ በመርጨት ትፈፅማለች፣ ለዚህም የምታቀርበው፣

> ሕዝ.36፡25 "ጥሩ ውሀንም እረጭባችኋለሁ እናንተም ትጠራላችሁ፣ ከርኩሰታችሁም ሁሉ ከጣኦቶቻችሁም ሁሉ አጠራችኋለሁ፡፡"

የሚለውን ቃል ነው፣ ይህ ቃል ለብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች በሚገባቸው መንገድ የተነገረ <u>የትንቢት</u> ቃል ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ዘመን የጥምቀት ስነ ስርዓት የሚፈፀመው

---

[113] Ibid, ገፅ 58
[114] Ibid, ገፅ 69
[115] መ/ር ዐሥራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባዔያት)ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ ገፅ 104

ተጠማቂውን ሙሉ በሙሉ ውሀ ውስጥ በማስገባት ነው፣ ዮሐንስ ኢየሱስን፣ ፊሊጶስም ኢትዮጵያዊውን ጃንደረባ ለማጥመቅ ወደ ወንዝ መሄድ ያስፈለጋቸው እንዲሁም "ከውሀው ሲወጣ" የተባለው(ማር.1፡9-10, ሐስ.8፡38-39) በዚሁ ምክንያት ነው።።

በርግጥ ይህ የአዲስ ኪዳኑ ሰውነትን ሙሉ በሙሉ ውሀ ውስጥ በማስገባት የሚፈፀመው አጠማመቅ ዘዴ ዝም ብሎ የመጣ ሰውኛ ስርዓት ሳይሆን የራሱ መንፈሳዊ ትርጉምም አለው፣ ይህም፡-

- ሮሜ.6፡3-4 "... ከክርስቶስ ኢየሱስ *ጋር* አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ *ጋር* አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ህይወት እንድንመላለስ፣ ከሞቱ *ጋር* አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ *ጋር* ተቀበርን።። ሞቱን በሚመስል ሞት ከእርሱ *ጋር* ከተባበርን ትንሳኤውንም በሚመስል ትንሳኤ ደግሞ ከእርሱ *ጋር* እንተባበራለን፤"
- ቆላ.2፡12 "በጥምቀት ከእርሱ *ጋር* ተቀበራችሁ፣ በጥምቀት ደግሞ፣ ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሔር አሰራር በማመናችሁ፣ ከእርሱ *ጋር* ተነሳችሁ።።"

በዚህም በአዲስ ኪዳን *ዘመን* ጥምቀት *መ*ከናወን ያለበት፣ ኢየሱስ ሞቶ እንደ ተነሳው፣ ውሀ ውስጥ ሙሉ በሙሉ በማስገባትና በማውጣት ነው።። የቤተክርስቲያኗ *መመሪያ* "ፍትህ ነገሥት" ምዕራፍ 3 ላይ የታዘዘውም ይኸው ሰውነትን ሙሉ በሙሉ ውሀ ውስጥ በማስገባት የሚፈፀመው የአጠማመቅ ስነ ስርዓት ነው።። በዚህም በቤተክርስቲያኗ እየተተገበረ ያለው የጥምቀት ስነስርአት አዲስ ኪዳናዊ እንዳልሆነ እንመለከታለን።።

በሌላ በኩል ደግሞ ቤተክርስቲያኗ በየአመቱ በምታዘጋጀው የጥምቀት በዓልዋ አማኙን በሙሉ ውሀ በመርጨት ታጠምቃለች፣ ይህንንም የምታደርገው በሕዝ.36፡25 *መሠረት* ለኃጢያት ስርየት *መ*ሆኑን ትናገራለች፣ በርግጥ አንድ ሰው *ለመ*ጀመርያ ጊዜ አምኖ ሲጠመቅ እስከዚያን ጊዜ ድረስ ያለው ኃጢያቱ በጥምቀቱ ይሰረይለታል ነገር ግን ጥምቀት አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ (ኤፌ.4፡5) "ለኃጢያት ስርየት" ብሎ በየጊዜው ማጥመቁ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፣ ከመጀመርያው ጥምቀት በኋላ የኃጢያት ስርየት የሚፈፀመው በንስሃና ከኃጢያት በመመለስ፣ ለበደሉት ይቅርታ በማድርግ(ሉቃ.11፡4)፣ በመመፅወት(ዳን.4፡27)፣ ለሰዎች ፍቅርን በማብዛት(1ጴጥ.4፡8) እና የእግዚአብሔርን ቤት በመቀደስ ነው(ኢሳ.27፡9) ነው።።

ስለዚህ ቤተክርስቲያኗ እያከናወነች ያለችው ጥምቀት በትክክለኛው የአዲስ ኪዳን አጠማመቅ ስርዓትና አንድ ጊዜ በሚከናወን ጥምቀት ሊስተካከል ይገባል።።

4.4.1.4. <u>የተሳሳተ የጾም አተረጓጎም</u>

በመጽሐፍ ቅዱሱ አተረጓጎም ጾም ማለት "አለመብላትና አለመጠጣት" ማለት ነው(አስ. 4፡16) ነገር ግን በቤተክርስቲያኗ ጾም እየተተረጎመ ያለው በዚህ ትርጉም ሳይሆን በምግብ ምርጫነት ነው፣ በዚህም ምግብ የሚጾምና የማይጾም በሚል በሁለት በመክፈል የዕፅዋትና የአተክልት ምግቦችን በመመገብ የእንስሳትና የእንስሳት ውጤቶችን ደግሞ በመተው ትጾማለች፣ ይህ ጾም ሳይሆን የስነ ምግብ ሳይንሱ የሚያዘውና ሁሉም ሰው ሊፈፅመው የሚገባ ጤናማ የአታክልት ተመጋቢነት(Vegeterianism) አመጋገብ ስልት ነው፡፡

በዚህ የቤተክርስቲኗ የተሳሳተ የጾም የአተረጓጎም ምክንያትም ብዙ አከራካሪ ነገሮች እየተነሱ ይገኛል፣ የቤተክርስቲያኗ አበው በጾም ወራት አሳ ሲመገቡ የቆዩ ቢሆንም ዛሬ ላይ "ጾማቸው ትክክል አልነበረም በጾም አሳ መብላት ስህተት ነው" እየተባለ ይገኛል፤ አሁንም ደግሞ ከፊል የእንስሳ ውጤት በሆነው ማርና ቅባታማ የሆነው የለውዝ ቅቤ ጾምነትም እየተነገረ ይገኛል፣ በርግጥ እነዚህ ሁለቱ ምግቦች ከእንስሳቱ ከሚገኙቱ ምግቦች በበለጠ ኃይል ሰጪና ሰውነት ገንቢ ናቸው፡፡

ይህ ሁሉ ችግር እየተፈጠረ ያለው ቤተክርስቲያኗ ትክክለኛውን የጾም ትርጉም ባለመከተሏ ምክንያት ነው፣ በዚህም ይህንን የተሳሳተ የጾምን ትርጉም በትክክለኛው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስተካከሉ ተገቢ ነው፡፡

4.4.1.5. <u>ሴቶችን ከአገልግሎት ማግለል</u>

ቤተክርስቲያኗ ሴቶችን በጾታቸው ምክንያት ብቻ "ከትላልቅ" አገልግሎቶች(መስበክ፣ ማስተማር፣ ማጥመቅ ...) በማግለል "በትናንሽ" አገልግሎቶች (ዝማሬ፣ ፅዳት ...) ብቻ ትገድባቸዋለች፣ ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ለሴቶች የተፈቀደና ያልተፈቀደ የአገልግሎት ዘርፍ ከፍፍል አንመለከትም፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ ለአዲስ ኪዳን አማኞች የወንድና የሴትን ልዩነት ያስቀመጠው "ትዳር" በሚባለው ተቋም ላይ ብቻ ነው፡፡ አንድ ተቋም በሁለት አለቆች ከተመራ የመፍረስ አደጋ ስላለው ፈጣሪ ባል "የቤቱ እራስ" እንዲሆን ነገር ግን ሚስቱን "ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በወደደበት ፍቅር" እንዲወድ ያስተምራል(ኤፌ.5፡25-26)፣ ባል ለቤት እራስነት የተመረጠበት እውነታም ተፈጥሯዊ እውነታ ነው፣ ይህም ሴቶች ከስነወሊድ ጋር ተያይዞ ያለባቸውን ተጨማሪ ኃላፊነትና ወንዶች ያላቸውን የሰውነት ግዝፈት፣ ጥንካሬ ... ግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡

ቤተክርስቲያኗ ሴቶችን ከአገልግሎት ያራቀችው ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ቆሮ.11, 1ጢሞ.2 ... ስፍራዎች ላይ ያስተላለፈውን መልዕክት በመመልከት ነው፣ ይሁን እንጂ እነዚህን መልዕክቶች አስተውለን ስንመለከት ጳውሎስ መልዕክቶቹን የተናገረው ከወትሮ በተለየ "እንዲህ ያለ ልማድ የለንም"(1ቆሮ.11፡16)፣ "ነውር ነውና"(1ቆሮ.14፡35)፣ "እፈቅዳለሁ"(1ጢሞ.2፡8)፣ "አልፈቅድም"(1ጢሞ.2፡12) ... የመሳሰሉ ቃላትን በመጠቀም

ነው፣ ይህም የሆነው መልዕክቱ በወቅቱ ለነበሩት ሴቶች ተለይቶ የተላለፈው መልዕክት በመሆኑ ምክንያት ነው፣ አንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ስልት "የተፃፈበት አውድ" መመልከት መሆኑ ሊረሳ አይገባም፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ከሴቶች ጋር በተያያዘ(ያለ አውድ) ለሁሉም ትውልድ ያስተላለፈውን መልዕክት ግን፣

> ገላ.3፡28 "... ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁም በክርስቶስ አየሱስ አንድ ሰው ናችሁ፡፡"

የሚለው ነው፣ ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ሮሜ መልዕክት ሲፅፍም አገልጋዮች በክንክራኦስ ባለች ቤተክርስቲያን የምታገለግለውን ፌቤንን በሴትነቷ ከአገልግሎት እንዳያገልሏት፣ እንዲቀበሏትና እንዲረዷት ሲናገር ነበረ(ሮሜ.16፡1-2)፣ ሴቶች በትንቢት ጸጋ ሲያገለግሉ መከናነብ እንዳለባቸውም ሲያስተምር ነበረ(1ቆሮ.11፡5)፣ ቀደምት ኑበያቱም በአዲስ ኪዳን ዘመን በጸታ የሚለይ አሰራር እንደማይኖር አስቀድመው በትንቢት ሲናገሩ ነበረ፣

> ኢዩ.2፡28-29 "... መንፈሴን በስጋ ለባሽ ሁሉ ላይ አፈስሳለሁ፤ ወንዶችና <u>ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ</u>፣ ሽማግሌዎቻችሁም ህልምን ያልማሉ፣ ጎበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ፤ ደግሞ በዚያ ወራት በወንዶችና <u>በሴቶች ባሪያዎች ላይ መንፈሴን አፈስሳለሁ፤ በላይ በሰማይ ድንቆችን አሳያለሁ</u> ..."

በዚህም በአንድ አውድ ላይ የተላለፈን መልዕክት፣ ለሁሉም ትውልድ አድርጎ፣ ሴቶችን ከአገልግሎት ማግለል የተሳሳተ አሰራር መሆኑን እንመለከታለን፡፡

እንደ ቤተክርስቲያኗ አሰራር ቢሆን ኖሮ ዲቦራ የምትባል ነቢይ፣ ፈራጅና መሪ(መሳ.4)፣ ከወንጌላዊው ፊሊጶስ ጋር የሚያገለግሉትን አራቱን ደናግል ሴት ነብያት(ሐስ.21፡8-9)፣ በክንክራኦስ የምታገለግለዋን ፌቤን(ሮሜ.16፡1) ... ወዘተ ባልተመለከትን ነበረ፡፡

ይህ ሴቶችን ከወንድ በታች አድርጎ አንኳሶ የመመልከት ችግር የመጣው ከእስልምና አስተምህሮ ነው፣ በ2.2 ክፍል የተመለከትነው የእስልምናን ሴቶችን የማንኳሰስ አስተምህሮ በቤተክርስቲያኗ ተጨማሪ መጽሐፍት ውስጥም ተመልክቷል (4.3.4.7.1 ክፍል ይመልከቱ)፡፡ በዚህም ይህንን ከእስልምና የተቀዳ አሰራር ወደ ቦታው በመመለስ ክርስቲያናዊውን አሰራር መተግበሩ መልካም ነው፡፡

4.4.1.6. <u>የክር መህተብ</u>

ማህተብ ማለት መለያ ምልክት ማለት ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ስለ ክርስቲያን ማህተብ ሲናገር፡-

- ኤፌ 1፡3 "እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፣ ይኸውም የመዳናችሁን ወንጌል፣ ሰምታችሁም ደግሞም በክርስቶስ አምናችሁ፣ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ <u>ታተማችሁ</u>፡፡"

- ኤፌ. 4፡30 “ለቤዛም ቀን <u>የታተማችሁበትን</u> ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ፡፡”

ይሁን እንጂ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህንን ክርስቲያናዊ ማህተብ ባለማወቅ የክር ማህተብን እየተጠቀሙች ትገኛለች፣ በዚህም ምዕመናኖቿ “የናንተ ማህተብ ክር ነው” እያለ ሰዎች ትክክለኛውን ክርስቲያናዊ ማህተብ እንዳያውቁ እና እንዳይታተሙበት እያደረገች ትገኛለች፣ ይህ ሴራ ደግሞ የሰዎችን መዳን የማይፈልገው የዲያብሎስ ሴራ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

4.4.ነ.7. <u>ዝማሬን በያሬዳዊ ስልት መገደብ</u>

ቤተክርስቲያኗ፣ መዝሙር መዘመር ያለበት በያሬዳዊ ስልት (ያሬዳዊ ዜማ፣ እንቅስቃሴና የሙዚቃ መሣርያ) ብቻ መሆን እንዳለበት ትናገራለች ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ያላገናዘበ አስተምህሮ ነው፡፡ ከመነሻው ስንመለከትም መዝሙር መዘመር ያለበት በደስታ መንፈስ ነው፣

- ያዕ.5፡13 “… ደስ የሚለው … ይዘምር፡፡”
- መዝ.95፡1 “ኑ፣ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን፤ ለአምላክ ለመድኃኒታችን እልል እንበል፡፡”
- ዘዳ.28፡47-48 “ሁሉን አብዝቶ ስለ ሰጠህ አምላክህን እግዚአብሔርን <u>በፍስሃና በሃሴት</u> አላመለክምና በራብና በጥማት በዕራቁትነትም ሁሉንም በማጣት እግዚአብሔር ለሚልክብህ ለጠላቶችህ ትገዛለህ፤ እስኪያጠፋህም ድረስ በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር ይጭናል፡፡”

ነገር ግን ሰው ደስታውን የሚገልፀው በራሱ መንገድ ነው፣ ይህ ደግሞ የሚወሰነው ሰውየው ባደገበት ባህል፣ በሰውየው ዕድሜ፣ ጾታ … ነው፣ በዚህም እያንዳንዱ ሰው ባስደሰተው መንገድ በሽብሸባ፣ በጭብጨባ፣ በመዝለል … ደስታውን ሊገልፅ ይችላል፣ ብሔር ብሔረሰቦች ጋር ደግሞ ከዚህ ሌላ የራሳቸውን ደስታ የሚገልፁበት ሌላ አይነት እንቅስቃሴ ሊኖር ይችላል፣ የዝማሬ ሞዴላችን ዳዊት ደስታውን የገለፀው ልብሱን አውልቆ በመዘመር ነበር(2ሳሙ.6፡14-23)፡፡

እግዚአብሔር የሚወደው ይህንን ሰዎች ተፈተው በራሳቸው መንገድ የሚያደርጉትን የደስታ ዝማሬን ነው፣ በዳዊት ዝማሬ እግዚአብሔር እጅግ ተደስቶበታል ነገር ግን የዳዊት ሚስት ሜልኮል ይህንን የዳዊትን ደስታ በሰውኛ አዕምሮ በመመልከት “ለምን በዚህ መልክ ዘመርክ” በማለቷ እግዚአብሔር ሲረግማት እንመለከታለን(2ሳሙ.6፡14-23)፣ ዛሬም ዝማሬን በኛ ስልት ካልሆነ ብሎ ለመገደብ መሞከር <u>መርገምት</u> ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ ዝማሬን ከደስታ ጋር ስለሚያያይዝ፣ እንደ እንቅስቃሴው ሁሉ፣ የሙዚቃ መሣርያንም አልገደበም፣ ማንም ደስ ባሰኘው የሙዚቃ መሣርያ መዘመር እንዳለበት ይናገራል፣ በመዝ.150፡1-6 ላይ እንደምንመለከተው ዳዊት በወቅቱ በእስራኤል

አካባቢ የሚያውቃቸውን የሙዚቃ መሣርያዎች ዘርዝሮ ከዚያም መዝሙርን በዚህ ላለመገደብ "እስትንፋስ ባለው ሁሉ" በማለት መዝሙር በሚመጣውም ዘመን በሚፈለሰፉት መልካም የሙዚቃ መሣርያዎች እንኳን መዘመር እንዳለበት ተናግሯል፣ ይህም ማንኛውም ሰው ደስ ብሎት እንዲዘምር ደስታውን በሙዚቃ መሣርያ እንዳይገደብ በማሰብ ነው።።

ያሬዳዊ ስልት የሰሜን ኢትዮጵያ ስልት ነው፣ በሀገሪቱ ያለው ሌላው ብሔር ይህንን ስልት አያውቀውም፣ ከየትኛውም ህዝብ በፊት እግዚአብሔርን የሚያውቀው የእስራኤል ህዝብም በ6ኛው ክፍለ ዘመን የተደረሰውን የያሬድን ስልት አያውቀውም፣ በዝማሬው መጽሐፍ ቅዱሱ የመሰከረለትና ከያሬድ ከአንድ አምስት መቶ አመታት በፊት የነበረው ዳዊትም የያሬድን ስልት አያውቀውም፣ በአሁኑ ጊዜም ከኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ውጪ ጠቅላላው ዓለም ይህንን ስልት አያውቀውም ... ስለዚህ መዝሙርን በያሬድ ስልት መወሰኑ <u>ጠባብነት</u> ብቻ ነው።።

በዚህም ለእግዚአብሔር መቅረብ ያለበትን ዝማሬ ያሬድ በዘመረበት በሰሜኖቹ ስልት፣ ሙዚቃ መሣርያና እንቅስቃሴ ብቻ ብሎ ዝማሬን መገደብ፣ የብሔር ብሔረሰቦችንና የፈረንጆቹን የሙዚቃ መሣሪያና የዝማሬ ስልት "ስህተት" ማለት መርገምትም ነው ጠባብነትም ነው።። በ6.3.1 ክፍል ከተመለከቱት ከመዝሙር መራቅ ካለባቸው ዝሙታዊና ኢጋንንታዊ እንቅስቃሴዎች በስተቀረ ማንኛውም ሰው እንደ ዳዊት ደስ በሚለው ስልት ለአምላኩ በደስታ ሊዘምር ይገባል።።

በአጠቃላይ በቤተክርስቲያኗ የምንመለከተው የፍትህት፣ የተዝካር፣ የምንኩስና፣ የባሕታዊነት፣ የጥምቀት፣ የጾምና የመዝሙር ትውፊቶች የተሳሳቱ ትውፊቶች መሆናቸውንና እነዚህ የተሳሳቱ ትውፊቶችም በመጽሐፍ ቅዱሱ ዕሴት መሠረት ሊስተካከሉ እንደሚገባ እንመለከታለን።።

4.4.2. <u>ኢጋንንታዊ ትውፊቶች</u>

በቤተክርስቲያኗ የሚታዩት ዋነኞቹ ኢጋንንታዊ ትውፊቶች በስዕል፣ በ"ታቦት" እና በ"መስቀል" ስም የሚከናወኑ የጣኦት አምልኮዎች እና በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የሰይጣን አገልጋዮች ቅዱስ የተደረጉበት አሰራሮች ናቸው።።

4.4.2.1. <u>የስዕል ጣኦት</u>

ቤተክርስቲያኗ ምስሎችን ለአምልኮ አገልግሎት እየተጠቀመች ትገኛለች፣ ለዚህ የምታቀርበው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመክንዮ [116] በነገ.6፡23-35 ላይ የተመለከተው ሰሎሞን በሰራው ቤተመቅደስ ግንብ በውስጥና በውጪ በኩል ያጌጠበት የኪሩቤል፣ የዘንባባንና የፈነዳ አበባ ምስል ነው።።

[116] ቀሲስ ደጀኔ ሺፈራው(2004)፣ **ነገረ ቅዱሳን ፩**፣ ገፅ 33

ነገር ግን አሁን በቤተክርስቲያኗ የምንመለከተው ምስል በአይነቱም ሆነ በዓላማውም ከዚህ የተለየ ነው፣ ዛሬ በቤተክርስቲያኗ የምንመለከታቸው ምስሎች ሰሎሞን የተጠቀማቸው የኪሩቤል፣ የዘንባባና የአበባ ማስጌጫ ምስሎችን ሳይሆን የማርያም/መላዕክት/ቅዱሳንን … ምስሎችን ነው፣ በዚህ ላይ ደግሞ ሰሎሞን ምስሎቹን የተጠቀመው ለማስጌጫነት ነው ነገር ግን ቤተክርስቲያኗ ምስሎቹን የምትጠቀመው ለማስጌጫነት ሳይሆን ለአምልኮ ነው፣ በዚህም ለስዕሎቹ ይማተባል፣ ይሰገዳል፣ ይፀለያል፣ ሻማ ይበራል …

መጽሐፍ ቅዱሱ ምስልን ለአምልኮ መጠቀምን አጥብቆ ያወግዛል፣ የሚያወግዘውም አጥብቆ በመሆኑም ምንም ክፍተት እንዳይኖር በተለያየ መንገድ በመግለፅ ነው፣

- <u>በሰማይም … በምድርም</u>
  ዘጸ.20፡4-5 “<u>በላይ በሰማይ ካለው</u>፣ በታች በምድር ካለው፣ ከምድርም በታች በውሀ ካለው ነገር የማናቸውም ምሳሌ፣ የተቀረፀውንም ምስል ላንተ አታድርግ፤ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውም…”
- <u>በወንድም ይሁን በሴት መልክ</u>
  ዘዳ.4፡15-18 “… የተቀረፀውን ምስል የማናቸውንም ነገር ምሳሌ፣ በወንድ ወይ በሴት መልክ የተሰራውን … እንዳታደርጉ፡፡”
- <u>ለሌላው ይቅርና ለእግዚአብሔር እንኳን ስዕል እንዳይሳል</u>
  ዘዳ.4፡15-18 “እግዚአብሔር በኮሬብ እሳት ውስጥ ሆኖ በተናገራችሁ ጊዜ መልክ ከቶ አላያችሁምና እጅግ ተጠንቀቁ፡፡ እንዳትረክሱ፣ የተቀረፀውን ምስል የማናቸውንም ነገር ምሳሌ … እንዳታደርጉ፡፡”

በዚህም ቤተክርስቲያኗ ለአምልኮ የምትጠቀምባቸው ምስሎች፣ የእግዚአብሔር የሚባሉትን እንኳን ጨምሮ፣ በመጽሐፍ ቅዱሱ የተከለከሉ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

ስዕልን ለአምልኮ የመጠቀሙ ልምምድ የመጣው ከኢጋንንታዊ የአምልኮ ስርዓት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣

> ራዕ.13፡14-15 “… ለአውሬውም <u>ምስል</u> እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል … ለአውሬውም <u>ምስል</u> የማይሰግዱትን ሁሉ …”

በዚህም በስዕል አምልኮን መፈፀም የቅዱሱ መንገድ ሳይሆን ኢጋንንታዊው መንገድ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ የስዕል አምልኮን በግልፅ ቋንቋ እየከለከለ፣ ስእሉም የተሳለው ወረቀትና ቀለም አዋህዶ በሚስል አርቲስት መሆኑ እየታወቀ፣ በተሳለው ስዕልና በተሳዮቹ መካከል ምንም ግንኙነት እንደሌለ እየታወቀ፣ ስእሉም ከሰው ላይ ይቅርና ከራሱ ላይ እንኳን ዝንብ ማባረር የማይችል መሆኑ እየታወቀ፣ የሥዕል አምልኮ ልምድ ኢጋንንታዊ መሆኑ እየታወቀ የስዕል አምልኮ ላይ የሙጥኝ ማለቱ በሥላም አለመሆኑ እንረዳለን፡፡

አምልኮን የሚፈልጉት ሁለት አካላት ናቸው፣ እግዚአብሔርና ሰይጣን፣ እግዚአብሔር በስዕል በኩል አምልኩኝ አለማለቱና ማርያም/ቅዱሳን/መላዕክትም በስዕል አምልኩኝ አለማለታቸውን ስንመለከት በስዕል በኩል አምልኮን እየተቀበለ ያለው ሰይጣን መሆኑ እንረዳለን፡፡

4.4.2.2. <u>በታቦት ስም የሚመለከው ጣኦት</u>

በ4.2.3.1 ክፍል እንደቀረበው በታቦት በኩል የሚደረግ አምልኮ የብሉይ ኪዳን ዘመን አምልኮ እንጂ የአዲስ ኪዳን ዘመን አምልኮ አለመሆኑንና በአዲሱ ኪዳን ፅላቱ/ታቦቱና ቤተመቅደሱ ሰው መሆኑን ተመልክተናል፣ ይሁን እንጂ በቤተክርስቲያኗ አዲሱ ኪዳን ብሉዩን ባለመተካቱ ዛሬም ድረስ የብሉይ ዘመን የታቦት አምልኮ እየተከናወነ ይገኛል፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ከአዲሱ ኪዳን ጋር እንዳልተገናኘችና ይህም ስህተት እንደሆነ ተመልክተናል፣ ከዚህ ስህተት በላይ የከፋው ስህተት ደግሞ ይህ በታቦት ስም የገባው ነገር ጣኦት መሆኑ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን ታቦት እንዲሰራ ያዘዘው እግዚአብሔር ነው፣ ያዘዘውም ዝርዝር የታቦቱን ዲዛይን በመግለፅ(ዘጸ.25) እና ይህ ዲዛይንም በጥንቃቄ እንዲተገበር በማዘዝ ነው(ዘጸ.25፡40)፣ በዲዛይኑ መሠረትም ዛሬ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን አካባቢ የሚታየውን “ታቦት” እና የእግዚአብሔርን ታቦት ስናነፃፅር ሁለቱ ታቦቶች ፍፁም የተለያዩ ሆነው እንመለከታቸዋለን፡-

1. <u>በመጠኑ</u> - እግዚአብሔር ታቦት እንዲሰራ ሲያዝ የታቦቱን ልኬት በመግለፅ ነው፣
   ዘጸ.25፡10 “ከግራር እንጨት ታቦት ይስሩ፣ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን፡፡”
   ይህንን የታቦት መጠን አሁን ካለው ታቦት ጋር ስናነፃፅር አሁን ያለው ታቦት የእግዚአብሔር ታቦት አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡
2. <u>በቅርፁና በመልኩ</u> - ዘጸ.25፡10-20 “ከግራር እንጨት ታቦት ይስሩ፣ ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል፣ ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል፣ ቁመቱም አንድ ክንድ ተኩል ይሁን … አራት የወርቅ ቀለበቶች አድርግለት፣ እነሱንም በአራቱ እግሮቹ ላይ አኑር … መሎጊያዎችንም ከግራር እንጨት ስራ … ለታቦቱ መሸከሚያ በታቦቱ ጎን ባሉት ቀለበቶች መሎጊያዎቹን አግባ … ከጥሩ ወርቅም ርዝመቱ ሁለት ክንድ ተኩል ወርዱም አንድ ክንድ ተኩል የሆነ የስርየት መክደኛ ስራ፡፡ ሁለት ኪሩቤል ከተቀጠቀጠ ወርቅ ስራ፣ በስርየት መክደኛው ላይ በሁለት ወገን ታደርጋቸዋለህ … ኪሩቤልም ክንፎቻቸውን ወደ ላይ ይዘረጋሉ፣ የስርየት መክደኛውንም በክንፎቻቸው ይሸፍናሉ …”
   በዚህም የእግዚአብሔር ታቦት ቅርፅና መልክ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን፣ ይህም እውነታ ዛሬ በቤተክርስቲያኗ ታቦት ተብሎ የሚመለከው የእግዚአብሔር ታቦት አለመሆኑን ያሳየናል፡፡

3. **<u>በይዘቱ</u>** - ዕብ.9፡4 "... ሁለንተናዋ በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት፣ በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ፅላት ነበሩ።።" በዚህም አንድ ታቦት "ታቦት" ለመሆን በውስጡ የአሮን በትር፣ <u>የድንጋይ</u> ፅላት እና መና የያዘ የወርቅ መሶብ ሊኖር ይገባል፣ እነዚህ ሁሉ በታቦት ውስጥ የሚቀመጡት የየራሳቸው ትርጉም ስላላቸው ነው፣ ነገር ግን የቤተክርስቲያኗ ታቦት የእግዚአብሔር ታቦት ባለመሆኑ ከእነዚህ ውስጥ አንዱን እንኳን አልያዘም።።
4. **<u>በስሙ</u>** - እግዚአብሔር ያዘዘው ታቦት አሁን ቤተክርስቲያኗ የምትጠቀምበት አለመሆኑን ከዲዛይኑ በተጨማሪ ከስያሜውም ማስተዋል ይቻላል፣ የድሮው ታቦት ስም "የእግዚአብሔር የቃልኪዳን ታቦት" ነበረ(ዘዳ.10፡8, ዘኁ.14፡44, ኢያ.6፡8 ...) ነገር ግን አሁን በቤተክርስቲያኗ የምንመለከተው ታቦት ስያሜ ይህ አይደለም፣ "የጉበርኤል፣ የሚካኤል፣ የአቦ ... ታቦት" ነው፣ "የ..." ማለት ደግሞ ባለቤትነትን የሚያሳይ በመሆኑ፣ በስያሜ ብቻ፣ አሁን ያለው ታቦት በርግጠኝነት የእግዚአብሔር አለመሆኑን እንመለከታለን።።
5. **<u>በአጋፋሪዎቹ</u>** - የእግዚአብሔርን ታቦት እንዲያጥኑትና እንዲሸከሙት የተመረጡት የሌዊ ዘሮች ብቻ ናቸው፣

    ነዜና.15፡2 "... ከሌዋውያን <u>በቀር ማንም</u> የእግዚአብሔርን ታቦት ሊሸከም አይገባውም።።"

    አሁን የምንመለከተው ታቦት የእግዚአብሔር ታቦት ስላልሆነ የሚሸከሙት ከሌዊ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው።።
6. **<u>በክብሩ</u>** - የእግዚአብሔር የቃልኪዳን ታቦት ትልቅ ክብር አለው፣ በዚህም ወደ ታቦቱ ዝም ተብሎ አይገባም(ዘሌ.16, ዘጸ.28፡34-35 ...)፣ ዝም ብለው የቀረቡ ሰዎች ተቀስፈዋል ዖዛ(2ሳሙ.6፡6-7)፣ ዖዝያን (2ዜና.26፡16-21)፣ ዳጎን የተባለ ጣኦት ተሰባብሯል (1ሳሙ.5፡1-4)፣ ፍልስጤማውያን በበሽታ ተመተዋል (1ሳሙ.5፡6-12) ...
    ዛሬ በቤተክርስቲያኗ የምንመለከተው ታቦት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ታቦት ባለመሆኑ "ታቦቱ" እንደ ማንኛውም እቃ በሌባ ይሰረቃል፣ ተይዞ ፖሊስ ጣብያ ይገባል ... ወዘተ።። በተሳሳቱ አሰራሮች ላይ አስቀድሞ ማስጠንቀቅያ ትንቢት የሚሰጠው መጽሐፍ ቅዱስ ስለነዚህ አይነት "ታቦቶች" ሲናገር፣

    ኤር.10፡3-8 "የአህዛብ ልማድ ከንቱ ነውና፤ ዛፍ ከዱር ይቆረጣል፣ በሠራተኛም እጅ በመጥረቢያ ይሰራል።። በብርና በወርቅ ያስጌጡታል፣ እንዳይናወጥ በችንካርና በመዶሻ ይቸነክሩታል።። እንደ ተቀረጸ አምድ ናቸው እነርሱም አይናገሩም፤ መራመድ አይቻላቸውማን ይሸከሙአቸዋል።። ክፉ መስራት አይቻላቸውምና፣ ደግም መልካም ይሰሩ ዘንድ አይችሉምና **<u>አትፍሩአቸው</u>** ... በአንድ ጊዜ ሰንፈዋል፣ ደንቁረውማል፤ **<u>ጣኦት</u>** የሚያስተምሩት የእንጨት ነገር ብቻ ነው።።"

በርግጥ ይህን እውነታ የሚያውቁት አሁኑን ታቦት በቅርበት የሚያውቁት ቀሳውስቱ፣ ዲያቆናቱ፣ የታቦት ሌቦች፣ የታቦት ገዢዎችና የተሰረቀን ታቦት የያዙ ፖሊሶች ብቻ ናቸው፣ ሌላውማ አሁን ያለውን ታቦት በብሉይ ኪዳኑ ታቦት ከብር ስለሚመለከተው ይህን ቃል ለታቦቱ መነገሩን አይቀበለውም።

በአጠቃላይ ስንመለከት በአዲሱ ኪዳን ታቦት/ፅላት/ቤተ መቅደስ ቁስ ሳይሆን የሰው ልጅ በሆነበት ሁኔታ ውስጥ ቤተክርስቲያኗ አሁን የምትጠቀመው ታቦት ቅርፅ፣ መጠን፣ መልክ፣ ይዘት፣ ስያሜ፣ ኢጋፋሪዎቹና ክብር ከእግዚአብሔር ታቦት ጋር የማይመሳሰል መሆኑን ስንመለከት በቤተክርስቲያኗ "ታቦት" ተብሎ እየተመለከ ያለው ትክክለኛ ከላይ በኤር.10፡3-8 የተገለፀው ጣኦት መሆኑን እንመለከታለን።

ታቦት የሚያስፈልገው ለአምልኮ ነው፣ ከላይ እንደቀረበው ደግሞ አሁን ቤተክርስቲያኗ ለአምልኮ የምትጠቀምበት ታቦት የእግዚአብሔር ታቦት አይደለም፣ በዚህም በታቦቱ በኩል እየተመለከ ያለው እንደ እግዚአብሔር መመለክ የሚፈልገው ሰይጣን መሆኑ ግልፅ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሱ ሊከሰቱ የሚሉትን የስህተት አሰራሮች ቀድሞ በትንቢት ስለሚናገር ይህንን ችግር አስቀድሞ ለሰሚዎች ተናግሮ ነበረ፣

> ኢሳ.45፡20 "እናንተ ከአህዛብ ወገን ሆናችሁ ያመለጣችሁ፣ ተሰብስባችሁ ኑ በአንድነት ቅረቡ የተቀረፀውን የምስላቸውን እንጨት የሚሸከሙና ያድን ዘንድ ወደማይችል አምላክ የሚፀልዩ እውቀት የላቸውም።"

የሚገርመው ደግሞ እዚህ ጋር በዚህ ስህተት ውስጥ የሚወድቁት ህዝቦች ምን አይነት ህዝቦች እንደሆኑ እንኳን ያሳያል፣

- "እናንተ ከአህዛብ ወገን ሆናችሁ" ማለቱ ከእስራኤል ዘር ሃረግ ውጪ ያሉትን ያመለክታል።
- "ያመለጣችሁ" የሚለው ደግሞ በክርስቶስ ስለዳኑት ክርስቲያንኖች ነው፣ እነሱም እነማንን እንደሆኑም እዚያው ምዕራፍ መግቢያው ላይ(ኢሳ.45፡14) "ኢትዮጵያ፣ ሳባና ግብፅ" መሆናቸውን አመልክቷል።

በዚህም ማስጠንቀቂያው የቀረበው ከእስራኤል ዘር ውጪ ሆነው በክርስቶስ አምልጠው ነገር ግን ካመለጡ በኋላ የተቀረፀ የእንጨት ምስል ለሚጠቀሙ "የዘመኑ ታቦት" ተማጋቾች ለኢትዮጵያና ለግብፅ አርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያን እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል።

ሌላው ከታቦት ጋር በተያያዘ ብዙ ሰውን ግራ ያጋባው "የሙሴ የቃል ኪዳን ታቦት በኢትዮጵያ ውስጥ አከሱም ጽዮን ቤተክርስቲያን ይገኛል" የሚባለው ነው፣ ይህ የተሳሳተ አባባል ነው፣ ታቦቱ ኢትዮጵያ ውስጥም የለም ምክንያቱም ቃል ኪዳኑ ለእስራኤል እንጂ ለኢትዮጵያ አይደለምና(ዘጸ.24፡1-8, ሮሜ.9፡1-4 ...)፣ ሰሎሞንም ለልጁ በስጦታ አልሰጠም

ታቦት በስጦታ የሚሰጥ እቃ አይደለምና እንደዚሁ ከሰሎሞን ሞት በኋላም በቤተመቅደስ ውስጥ ነበረና(2ዜና.35፡3)፣ ከዘረፋ እንዲድን በኢትዮጵያ ታቦታት መካከል እንዲደበቅ አልተደረገም ምክንያቱም የኢትዮጵያ ታቦትና የቃል ኪዳኑ ታቦት መካከል ሰፊ ልዩነት አለና፣ ከዚህ በባሰ የሚገርመው ደግሞ ታቦቱ አሁን በምድር ላይ የለም ምክንያቱም ዘመኑ አዲስ ኪዳን ስለሆነ በከብር ወደ ሰማይ ተወስዷልና(ራዕ.11፡19) ።።

4.4.2.3. <u>በመስቀል ስም ተሸፍኖ የገባው ጣኦት</u>

መጽሐፍ ቅዱሱ ሰዎች መስቀሉን መያዝ(ማቴ.10፡38)፣ *መስቀሉን መሸከም*(ማቴ.16፡24) ... እንዳለባቸው ይናገራል ይሁን እንጂ በቤተክርስቲያኗ ይህ የመጽሐፍ ቅዱሱ ጥበባዊ አገላለፅ በተሳሳተ መንገድ ተተርጉሞ ሰዎች በተለያየ ቁስ የተሰራን መስቀል ለአምልኮ እየተጠቀሙበት ይገኛሉ፣ በዚህም በቤተክርስቲያኗ በቁስ ለተሰራ መስቀል የመሳለም፣ የመንበርከክ፣ የመስገድ፣ የመዘመር፣ በዓል የማዘጋጀት ... በአጠቃላይ ለቁሳዊው የመስቀል ምልክት የአምልኮ ስነ ስርአቶች እየተከናወኑ ይገኛል።።

መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ "መስቀል" የሚለውን ቃል በሁለት መንገድ ይተረጎማል፣ ፊት ለፊት ያለው ትርጉም በድሮ ዘመን ሰዎች የሚሰቀሉበት እንጨት ሲሆን ሁለተኛው ትርጉም ደግሞ ክርስቶስን በመከተል የሚመጣ መከራ ማለት ነው።።

መጽሐፍ ቅዱሱ ሰዎች መስቀሉን መያዝ፣ መሸከም ... እንዳለባቸው ያዘዘው አማኞች ለሰው መስቀያነት የሚያገለግል እንጨት ሰርተው ተሸክመው ይዙሩ ማለቱ ሳይሆን በሁለተኛው ትርጉም ይህም ሰዎች ክርስትናን በመከተላቸው ምክንያት የሚመጣባቸውን መከራ እንዲሸከሙ፣ ዓለማዊነትን እንዲተው ... ለማሳሰብ የተነገረ ቃል ነው፡-

- ማቴ.16፡24 "በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፡- እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፣ <u>ራሱን ይካድ</u> <u>መስቀሉንም ተሸክሞ</u> ይከተለኝ።።"
- ገላ.6፡14 "ነገር ግን <u>ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት</u> ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።።"

አንድ ሰው ወደ ክርስትና ሲመጣ ለብዙ መከራ እንደሚጋለጥ *መጽሐፍ ቅዱሱ* ይናገራል፣ ይህ እውነታም በመሪው በክርስቶስም ሆነ በተከታዮቹ ህይወት ላይ ተመልክተናል፡-

- ነጴጥ.2፡21-24 "... ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችኋል ... እርሱም ኃጢያት አላደረገም፣ ተንኮልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፣ ነገር ግን በፅድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤ <u>ለኃጢያት ሞተን ለፅድቅ እንድንኖር</u> ..."
- ነጴጥ.4፡1-2 "... ከእንግዲህ ወዲህ በስጋ ልትኖሩ በቀረላችሁ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ሰው ምኞት እንዳትኖሩ ... በስጋ መከራን የተቀበለ ኃጢያትን ትቶአልና።።"

- ፊልጵ.1፡29 “ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራን ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፡፡”

በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተገለፀት “መስቀል መያዝ፣ መስቀል መሸከም…” የሚሉት ቃላት ይህንን “ስጋዊ/ዓለማዊ ነገርን ትቶ ለክርስትና ዋጋን መክፈል” በሚል ትርጉም የሚተረጎም እንጂ በቁስ የተሰራ መስቀል መያዝ፣ መሸከም እና ከዚያም ባለፈ ለዚህ ቁሳዊ መስቀል መስገድ፣ መዘመር፣ መሳለም … ማለት አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ በቤተክርስቲያኗ “መስቀል መያዝ፣ መስቀል መሸከም …” የሚሉት የመጽሐፍ ቅዱሱ አገላለፆች በመጀመርያ የቃሉን ትክክለኛ ትርጉም በማዛባት በመቀጠል ደግሞ ይህንን የተዛባ ትርጉም ለአምልኮ አገልግሎት እንዲውል በማድረግ ተደራራቢ ስህተቶች ተሰርተው እንመለከታለን፣ በዚህ የተዛባ አካሄድም በቤተክርስቲያኗ ቁሳዊው መስቀል የሚዘመርለት፣ የሚሰገድለት … በአጠቃላይ የሚመለክ ጣኦት ተደርጓል፡፡

ሌላው በዚህ ዘመን በመስቀል ስም የተጨመረው ጣኦት ጥንት ግብፃውያን የሚያመልኩት “Ankh” የሚባለው በ “ቶ” ቅርፅ የሚሰራው ጣኦት ነው፣ ይህ ቅርፅ በጥንታውያኑ የግብፅ አምልኮ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ጣኦት ሲሆን ዛሬ ላይ በቤተክርስቲያኗም ይህ ጣኦት “ተቀድሶ” ገብቷል፣ በዚህም ብዙ የቤተክርስቲያኗ ምዕመናኖች ይህንን የግብፃውያኑን ጣኦት ሲጠቀሙ እየተመለከትን ነው፡፡

መመለክ የሚፈልጉት እግዚአብሔርና ዲያብሎስ ብቻ መሆናቸውን ከላይ ደጋግመን ተመልክተናል፣ በዚህም ይህንን “መስቀል፣ መያዝ፣ መስቀል፣ መሸከም” የተባሉትን ትዕዛዞች አዛብቶ በቁሳዊው መስቀል በኩል እየተመለከ ያለው ማን እንደሆነ ግልፅ ነው፡፡

4.4.2.4. <u>በቤተክርስቲያኗ ውስጥ የተቀመጡ የሰይጣን አገልጋዮች</u>

በቤተክርስቲያኗ ደብተራነት፣ ጥንቆላ፣ አስማት የመሳሰሉ ኢጋንንታዊ ትውፊቶች በደብተራዎች፣ መሪጌታዎች፣ ቆሎ ተማሪዎች እና በመሳሰሉ አገልጋዮች ሲሰሩ መመልከት እንግዳ ነገር አይደለም፤ ከቀላል ገመድ ማቆም፣ ከብቶች በአውሬ እንዳይበሉ ከማስደገም አንስቶ እስከ ደመና ጋላቢነት የሚደርሱ ሰይጣናዊ ስራዎችን የሚሰሩ አገልጋዮች በቤተክርስቲያኗ ሞልተዋል፡፡ በቤተክርስቲያኗም እነዚህ ትውፊቶች ሰይጣናዊ ተደርገው የሚወገዙ ሳይሆን በ“ቅዱሳን” መጽሐፍቶች የሚደገፉና በቤተክርስቲያኗ “ቅዱሳን” ህይወት የተመለከቱ ናቸው፣

- [117] በደመና የሚኬደው “መስተጽዕነ ደመና” በሚባለው አስማት ነው፣ [118] አባ አፍፄ በደመና ተጭነው ይሄዱ ነበረ፣
- በአራዊት የሚጋለበው “መስተጽዕነ አራዊት” በሚባል አስማት ነው፣ [119] አባ ሳሙኤል ዘዋልድባ አንበሳ ይጋልቡ ነበረ፣ [120] አቡነ አረጋዊ ዘደብረ ዳሞ በዘንዶ ይጓዙ ነበረ፣ ለሊት ጅብ የሚጋልቡ ሰዎችም የሚጠቀሙት ይህንኑ አስማት ነው።።
- ሰይጣናዊ አሰራሮችን የሚያስተምሩ እንደ [121] ዐውደ ነገሥት፣ መፍትሄ ስራይ፣ መልክአ ራጉኤል ባለ ጠልሰሙ፣ መልክአ እዮብ፣ ሕልመ ዮሴፍ፣ ሀተታ ዘርአያዕቆበ ... የሚባሉ የቤተክርስቲያኗ “ቅዱሳት” መጽሐፍት መሆናቸው፣
- [122] “መጽሐፈ ቆጽርያኖስ የተባለው መጽሐፍ አስማት፣ ጥንቆላ፣ ድግምት... አሰራርን የሚያስተምር ሲሆን፣ ለትክክለኞነቱም ማርያም በድግምት “መጥቁል” የተባለውን ጠንቋይ እንዴት እንዳሸነፈችው፣ ሰሎሞንም እንዴት 600 አጋንንትን ይዞ ቤተመቅደሱን እንዳሰራ ያስተምራል።።”
  ይህንን የሰሎሞን አጋንንትን መጠቀም ታሪክ የምናገኘው መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ሳይሆን “ቅዱስ” ቁርአን ላይ ነው(34፡12, 21፡82, 27፡15-17...)
- [123]“አንተ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሆይ በእነዚህ አስማት ኃይል ሰባ ነገሥታትን በዱድያኖስ ፊት እንደ ደመሰስካቸው የእኔንም ጠላቶች እንደ እነርሱ ደምስሳቸው።።(ቱላዳን ዘቅዳሜ ገፅ 183)።።
- [124]እነዚህን አስማቶች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚካኤል ክንፍ ላይ ፃፋቸው፣ በእነዚህም አስማቶች ዲያብሎስ ከነሰራዊቱ ጨለማን ተጎናፅፎ ወደቀ።።(ድርሳነ ሚካኤል ገፅ 62)”
- ከላይ በ4.3.4.7 ክፍል እንደተመለከትነው የጥንቆላ ስራ በተጨማሪ መጽሐፍቱ የሚደገፉ መሆኑ፣

---

[117] መሪጌታ ሰረቀ ብርሃነ ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም፣ ገፅ 307
[118] መ/ር ዐሥራት ደስታ et.al(1998) **ነገረ ቅዱሳን ፪**፣ የከፍ/ትም/ተቋ/(የግቢ ጉባዔያት)ተማሪዎች መማሪያ መጽሐፍ፣ ገፅ 39
[119] Ibid, ገፅ 87
[120] Ibid, ገፅ 34
[121] መሪጌታ ሰረቀ ብርሃነ ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም
[122] መምህር ፅጌ ስጦታው(2004)፣ **ወጋግን**፣ ገፅ 32-33
[123] ጸጋአብ በቀለ(2006)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ**፣ ቅፅ ፣ ገፅ 38
[124] Ibid፣ ገፅ 38

በቤተክርስቲያኗ አገልጋዮችም እነዚህን ሰይጣናዊ ስራዎችን መስራት ትክክለኛ ይባሉኑም ወሳኝ ተደርጎ ይታያል፣ ወሳኝነቱም፡-

- [125] “በምድራችን ያለው አስማት እግዚአብሔር ለኖህ ያስተማረው፣ ለሰሎሞንና ለማርያም የተሰጠ፣ በሚካኤል ክንፍ ላይ የተፃፈ … በሚል አስማተኝነትን በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ስፍራ በመስጠት … ከዚህ የተነሳም አስማትን የማያውቅ ተማሪ የእግዚአብሔር ምስጢር እንደተደበቀበት ሆኖ ሲሰማው የአስማት ልምድ የተለማመደ ተማሪ ግን የእግዚአብሔርን ምስጢር እንደተረዳ ያህል ይቆጥረዋል፡፡”
- [126] “የተንኮል ትምህርት ማለት ጥንቆላ ወይንም መጽሐፍ ገለጣ፣ ኮከብ ቆጠራ፣ ስር መማስና ቅጠል መበጠስ በዚያ አጠራር “ጥበብ” … እንደ ግዴታም ነው፣ ምክንያቱም እርስ በርስ ጠብ ይኖራል ያን ግዜ እራስህን ለመከላከልም ሆነ ለመርታት ትንሽም እንኳን እንዳልተማርክ ከተሰማ መጫወቻ ያደርጉሀል፣ በተቃራኒው ከታወቅህ ትከበራለህ … ስለዚህ መማሩ አስገዳጅ ነው፡፡ (ቀሲስ ደረጀ ገዙ፣ ቪዥን ቅፅ ፩ ቁጥር 2 ጥር-የካቲት 2004 ገፅ 5)”
- [127] የገድላትና የድርሳናት ጸሐፊ ደብተራዎች አብዛኞቹ የነገሥታት ፍርፋሪ የለመዱና የነገሥታትን አፍ ጠብቀው የሚናገሩ፣ ለነገሥታቱ መግረፊ ፀር(ጠላት እንዲገዛላቸው የሚያደርግ) ድግምትን እየደገሙ የሚኖሩ ስለነበረ ነው፡፡ በዚህም የድግምት ስራ እንጀራቸው ስለሆነ፣ ከቤተክርስቲያን አገልግሎታቸው ጋር በዚህ ሰይጣናዊ ሙያ አቀላቅለው ይኖራሉ፡፡

በአጠቃላይም በ“ቅድስት” ቤተክርስቲያን፣ ሰይጣናዊ ትውፊቶች በ“ቅዱሳን” መጽሐፍትና አገልጋዮች ተሸፍነውና “ተቀድሰው” መቀመጣቸውን እንመለከታለን፡፡

4.4.2.5. <u>ኢጋንንታዊ ኃይላትን መጠቀም</u>

በ4.2.4.4 ክፍል እንደተመለከትነው በአዲስ ኪዳን ዘመን አማኞች ኢጋንንት ለማውጣት፣ ለፈውስ እና ለተለያዩ መንፈሳዊ ስራዎች እንዲጠቀሙበት የተሰጣቸው መንፈሳዊ ኃይል “የኢየሱስ ስም” ነው፡፡ ይሁን እንጂ በቤተክርስቲያኗ በእጃዙር እየተመለከ ባለው፣ ሜራው እንዳይፈርስ በሚፈልገውና የራሱን አገልጋዮች በቤተክርስቲያኗ ውስጥ ሰግስጎ በሚጠቀመው መንፈስ ምክንያት ይህ ለአዲስ ኪዳን አማኞች የተሰጠው መንፈሳዊ ኃይል ወደ ጎን ተደርጎ ሌሎች አዲስ ኪዳኑ የማያውቃቸውና ይባሉኑ ኢጋንንታዊ የሆኑ መንፈሳዊ የኃይል አማራጮች ስራ ላይ እየዋሉ ይገኛል፡፡

---

[125] መሪጌታ ሰረቀ ብርሃን ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም፣ ገፅ 307-308
[126] ጸጋአብ በቀለ(2006)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ**፣ ቅፅ ፩፣ ገፅ 39
[127] መሪጌታ ሰረቀ ብርሃን ዘወንጌል(2010)፣ **ማሳቀል**፣ ሰባተኛ ዕትም፣ ገፅ 308

በዚህም ቤተክርስቲያኗ ለመንፈሳዊ ኃይልነት “በማርያም፣ በገብርኤል፣ በአቦ… ስም”፣ በጠበል፣ ድግምት፣ አስማት፣ መተት፣ ቅጠል በመበጠስ፣ ስር በመማስ … በደብተራዎች፣ በጥንቆላ ስራ በተካኑ … ከላይ የተመለከትናቸው የሰይጣን አገልጋዮች እየተጠቀመች ትገኛለች፡፡ በዚህም ሰይጣን በዘዴ “ሰይጣንን አስወጡበት” የተባለውን “የኢየሱስ ስም” ስልጣን ሰዎች እንዳይጠቀሙበት በማድረግ ሌላ ሰይጣናዊ መንገድ እያስተማረ ይገኛል፣ ይህ ሰይጣን እራሱ የሚወጣበትን መንገድ የሚያስተምርበትን ዘዴ የእስልምናው ሀዲስ (ሳሂህ ቡኻሪ 3፡38፡505) ላይም ተመልክቷል፡፡ ከሁሉ የሚያስገርመው የታሪክ ሂደት ግን በመንፈሳዊው አሰራር “ስህተት” ስህተት ብቻ አለመሆኑና ከስህተት ጀርባ ስህተቱን ለራሱ አጀንዳ የሚጠቀም ተቃራኒ መናፍስታዊ ኃይል የመኖሩ እውነታ ነው፡፡

<u>እነዚህን ከላይ የቀረቡትን በቤተክርስቲያኗ የተመለከቱትን የተሳሳቱትንና ግልፅ አጋንንታዊ ትውፊቶችን በአንድ ላይ ስንመለከት ቤተክርስቲያኗ ግልፅ አጋንንታዊ አሰራር ውስጥ እንደገባች እንመለከታለን፡፡ በዚህ አጋንንታዊ አሰራርም በቤተክርስቲያኗ በማርያም/መላዕክት/ቅዱሳን ስም ሰይጣን ቢመለክ፣ ክርስቶስ ዋጋ የከፈለበት አዲስ ኪዳን ቢሸፈን፣ ቅድስና የጎደላቸው ተጨማሪ መጽሐፍት “ተቀድሰው” ቢገቡ፣ ከላይ የተመለከትናቸው የጥንቆላ፣ አስማት … መማርያ መጽሐፍት “ተቀድሰው” ቢገቡ፣ ጣኦቶች በስዕል፣ በታቦቱና በመስቀሉ ስም ተሸፍነው ቢገቡ፣ በኢየሱስ ስም አጋንንት ማውጣት ቢከለከል … አያስገርምም፡፡</u>

<u>ማጠቃለያ(ኦርቶዶክስ)</u>

የመጽሐፍ ቅዱሱን ታሪኮች ስናጠና አንድ ተደጋጋሚ ታሪክ እንመለከታለን፣ ቅዱሱ መንገድ በጊዜ ሂደት በዲያብሎስ ሜራ የሚበረዝበትና እግዚአብሔር ደግሞ በቅዱሳን አማካኝነት ተሐድሶ አስነስቶ ቤቱን የሚያፀዳበት የታሪክ ሂደት (ዘጸ.32፡20, መሳ.6፡25-30, 2ነገ.10፡26-28, 2ነገ.23፡4, 2ዜና.29፡5, 2ዜና.34 …)፡፡

“የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን” በሚባሉት የመጀርያዎቹ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ በተፈጠረው መከፋፈል እንደተፈጠሩ በሚታመኑት በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም፣ በዚህ ምዕራፍ የተመለከትናቸው ችግሮች የገቡት ትክክለኛው መንገድ በዲያብሎስ ሜራ በመበረዙ ምክንያት ነው፡፡

ዛሬም ላይ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች እነዚህን ከላይ የተመለከትናቸውን ስህተቶች በቤተክርስቲያኗ ውስጥ መግባታቸውን ያውቃሉ ነገር ግን እውነታውን ለመናገር አይደፍሩም፣ አንዳንዶቹ ያሉበት ስልጣንና ጥቅማ ጥቅም ስለሚያሳሳቸው ሌሎቹ ደግሞ ምስጢሩን ይፋ በማውጣታቸው የሚመጣባቸውን መከራና ስደት ስለሚያውቁ ስህተቱን በዝምታ ያልፉታል፡፡

አንዳንድ ጥቅማ ጥቅሙ ያላሳሳቸው፣ መስቀሉን ለመሸከም ዝግጁ የሆኑና ከምድራዊው ነገር ይልቅ ዘላለማዊውን ነገር የፈሩቱ፣ እውነቱን ሲረዱ ቤተክርስቲያኗን

ጥለው ወደ ትክክለኛው አስተምህሮ ሲሄዱ እየተመለከትን ነው፤ ይህ መልካም ቢሆንም በቤተክርስቲያኗ ውስጥ እንደነሱ መጽሐፍትን ማግኘት፣ ማንበብና መረዳት የማይችሉ ብዙ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወገኖች ባገናዘበ መልኩ ቢንቀሳቀሱ ደግሞ የተሻለ ነበረ፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ ላይም ስንመለከት፣ ብዙዎቹ ቅዱሳን እውነታው ሲገለጥላቸው፣ ቤተክርስቲያናቸውን ለርኩሰት ጥለው አልወጡም፣ ቅዱሱን ከእርኩሱ ለይተው እርኩሱን ሲያስወግዱና የእግዚአብሔርን ቤት ሲያፀዱ ነው የነበሩት፣ ይህንንም እውነታ ከላይ በቀረቡት ጥቅሶች ውስጥ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

ከነዚህ ጥቅሶች ውስጥ አንዱን በምሳሌ ሰፋ አድርገን ብንመለከት፣ በነኢዮስያስ ዘመን በሰማይ ሠራዊት(መላዕክት) ስም አምልኮ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሲደረግ ነበረ፣ ለኢዮስያስም እውነቱ ሲገለጥለት፣ ኢዮስያስ እነዚህን በመላዕክት ስም የተቀመጡትን የአምልኮ እቃዎች ጠራርጎ አውጥቶ አቃጠለ፣

> 2ነገ.23፡4 "... ለሰማይም ሠራዊት ሁሉ የተሰሩትን ዕቃዎች ሁሉ ከእግዚአብሔር መቅደስ ያወጡአቸው ዘንድ አዘዘ፣ ከኢየሩሳሌምም ውጪ በቄድሮን ሜዳ አቃጠላቸው፡፡"

ዛሬ በቤተክርስቲያኒቷ የምንመለከተው ችግር ይህ የመላዕክት አምልኮ ጨምሮ ሌሎች ብዙ የተለያዩ አይነት አምልኮዎች መግባታቸው ነው፣ ይህም ቤተክርስቲያኗ ምን ያህል ሰፊ የእድሳት ስራ እንደሚያስፈልጋት ያሳያል፡፡

በዚህም ይቺ ቤተክርስቲያን መሠረታዊ የተሐድሶ ስራዎች ያስፈልጓታል፣ በዚህም እያንዳንዱ ሰው እውነቱ ሲገለጥለት ቤተክርስቲያኑን ለቆ ከመውጣት የተረዳውን እውነት በጥበብ ለሌሎች በማካፈል፣ እነሱም ለሌሎች እንዲያካፍሉ በማድረግ፣ በተቀናጀ መንገድ በመስራት በቤተክርስቲያኗ ውስጥ አጠቃላይ ተሐድሶን በማንቀሳቀስና ከላይ የተመለከትናቸውን የስህተት ትምህርቶችንና ጣኦቶች በሙሉ ከእግዚአብሔር ቤት በማስወገድ የእግዚአብሔርን ቤት ለእግዚአብሔር ብቻ መቀደስ ይገባል፡፡

- 2ዜና.29፡5 "... የአባቶቻችሁንም አምላክ የእግዚአብሔርን ቤት ቀድሱ፣ ርኩሱንም ነገር ሁሉ ከመቅደስ አስወግዱ፡፡"
- ኢሳ.57፡14 "እርሱም፡- ጥረጉ፣ መንገድን አዘጋጁ፣ ከህዝቤም መንገድ ዕንቅፋትን አውጡ ይላል፡፡"

ይህ እርኩሱን የማስወገድና ቤቱን የማፅዳት ስራ ግን በጥበብ፣ በቅንጅትና በፀሎት ሊመራ ይገባል፣ ቤቱን ስታድሱ ደግሞ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ድንቅ ነገር ያደርጋል(ኢያ.3፡5)፣ ለነፍሳችሁም የኃጢያት ስርየትን(ኢሳ.27፡9) እና ዘላለማዊውን ዕረፍትን ታገኛላችሁ(ኤር.6፡16)፡፡

ምዕራፍ አምስት

5. ከ19ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት

በዚህ ርዕስ ስር ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የተመሠረቱትን የሐዋርያት፣ የጂሆቫ እና የአድቬንቲስት አብያተ ክርስቲያናትን አስተምህሮ እንመለከታለን፡፡

ብዙ ሰዎች እነዚህ ሦስቱ አብያተ ክርስቲያናት በፕሮቴስታንት ስር የሚመደቡ ይመስላቸዋል ነገር ግን ሦስቱም አብያተ ክርስቲያናት ከፕሮቴስታንት በአስተምህሮ የሚለዩና እርስ በርሳቸውም የሚለያዩ የየራሳቸውን አስተምህሮ የሚከተሉ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪም እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በ3.2 ክፍል ስር ከተመለከትናቸው ኃይማኖቶችም የተለዩ ናቸው፣ ልዩነታቸውም እነዚህ ሦስቱም አብያተ ክርስቲያናት በመጽሐፍ ቅዱሱ የሚመሩ ሲሆን መጽሐፍ ቅዱሱንም ከሁሉም መጽሐፍት በላይ አድርገው ይመለከታሉ፣ በ3.2 ክፍል ስር የተመለከትናቸው ኃይማኖቶች ግን የሚመሩት መጽሐፍ ቅዱሱን ከራሳቸው ፍልስፍና ጋር በማዋሀድ ባዘጋጁት “ቅዱስ” መጽሐፍ ነው፡፡

በዚህ ምዕራፍም የነዚህን የሦስቱን ኃይማኖቶች አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር እያነፃፀርን እንመለከታለን፡፡

5.1. የሐዋርያት ቤተክርስቲያን (“Only Jesus”)

[128]“የሐዋርያት ቤተክርስቲያን (United Pentecostalism/Apostolic Pentecostal Christian) አስተምህሮ በ1914 የተጀመረ ሲሆን ቤተክርስቲያኗ ግን እንደ ቤተክርስቲያን የተቋቋመችው በ1945 ዓ.ም ነው፣ ቤተክርስቲያኗ በአሁኑ ጊዜ ከ5 ሚሊየን በላይ ተከታዮች ያሉዋት ሲሆን የቤተክርስቲያኗ ዋና መስርያ ቤትም በቄልደን እስፕሪንግ፣ ሚዙሪ ይገኛል።”

ለቤተክርስቲያኗ ምሥረታ መነሻ የሆነው፣ ሰዎች በቡድን ሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እያጠኑ “ትክክለኛው የውሀ ጥምቀት በማቴ.28፡19 ላይ በተገለፀው በአብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም ነው? ወይስ ሐስ.2፡38 ላይ በተመለከተው መንገድ በኢየሱስ ስም መፈፀም አለበት? በሚለው ሐሳብ ላይ ባነሱት ክርክር ነው።

በዚህም ክርክር ምንም እንኳን ጥምቀት “በአብ በወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም” እንዲደረግ ቢታዘዝም ሐዋርያቱ ያጠመቁት ግን “በኢየሱስ ስም” በመሆኑ፣ “ጥምቀት መፈፀም ያለበት በኢየሱስ ስም ብቻ ነው” በሚለው ድምዳሜ ላይ በመድረስ፣ ከዚህም ድምዳሜ በመነሳት ደግሞ “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” በማለት ከሥላሴያውያኑ(የሥላሴን አስተምህሮን የሚከተሉት አርቶዶክስ፣ ፕሮቴስታንት …) የተነጠለ አዲስ ኃይማኖት መሠረቱ።

እነዚህን ሁለቱን መሠረታዊ ሐሳቦችንም ከመጽሐፍ ቅዱሱ አንፃር ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን።

5.1.1. “ጥምቀት መፈፀም ያለበት በኢየሱስ ስም ብቻ ነው”

ሥላሴያውያን ጥምቀት በማቴ.28፡19 ላይ በታዘዘው መሠረት በ“አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም” የሚያከናውኑ ሲሆኑ የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ደግሞ ሐዋርያቶች ባጠመቁበት መንገድ(ሐስ.2፡38, ሐስ.8፡16, ሐስ.19፡5, ሐስ.22፡16 …) “በኢየሱስ ስም” ብቻ ታጠምቃለች፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ በማቴ.28፡19 ላይ ያለውን በ“አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም” አጥምቁ የሚለውን ትዕዛዝ አትቀበልም፣ ለዚህ ደግሞ የተለያዩ መከራከሪያዎችን ታቀርባለች፣

- [129] “ጥምቀት በኢየሱስ ስም ብቻ መከናወን አለበት … አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም … በአብና በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ማለት በኢየሱስ ስም ማለት ነው።”
- [130] “አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የማዕረግ ስም ነው።”

---

[128]https://en.m.Wikipedia>wiki>United Pentecostal Church International

[129] ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ - *መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህር ማስተማሪያ***፣ ገፅ 25፣ ትምህርተ 18/ሸ/3 እና ትምህርተ 18/ቀ

ነገር ግን እነዚህ መከራከሪያዎች መቀበል ያዳግታል ምክንያቱም፣

1. ሐሳቡ እርስ በርስ ይጋጫል
   - "አብ፣ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም" ይልና ተመልሶ ደግሞ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም ማለት በኢየሱስ ስም ማለት ነው" ይላል፣
   - "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም" ይልና ተመልሶ ደግሞ "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የሚለው የማዕረግ ስም ነው" ይላል፣
2. ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር ይጋጫል
   - ማቴ.28፡19 ላይ ኢየሱስ "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቁ" ከሚለው ትዕዛዝ ጋር ይጋጫል፣ መቼም ኢየሱስ ይህን ትዕዛዝ ሲሰጥ "በስሜ አጥምቁ" ማለት ሲችል እንዲህ ማለቱ ተሳስቶ አይደለም፣
   - ማቴ.28፡19 "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" እያለ መጽሐፍ ቅዱሱን በመቃወም "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም አይደለም" ማለቱ ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር የሚጋጭ አስተምህሮ ነው፣
3. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም

   "በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ" ስም ማለት "በኢየሱስ ስም ማለት ነው" የሚል ሐሳብ መጽሐፍ ቅዱሱ ውስጥ የለም፣

በዚህም የሐዋርያት ቤተክርስቲያን በ"አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ስም ማጥመቅ ለመተው ያቀረበችው ምክንያት ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ ሥላሴያውያን ሐዋርያቱ ባጠመቁበት መንገድ "በኢየሱስ ስም" ጥምቀትን አይፈፅሙም፣ ለዚህም ሁለት የተለያዩ መከራከሪያዎችን ያቀርባሉ፣ ይህም፣

1. "በኢየሱስ ስም ማጥመቅ" የሚባለው የስያሜ ጉዳይ ነው፣ ይህ ስያሜ የተፈጠረው ደግሞ የአዲስ ኪዳኑን ጥምቀት ከብሉይ ኪዳኑ ጥምቀት ለመለየት ነው፣ በሐስ.19፡19፡1-5 ላይ "በዮሐንስ ጥምቀት" እንደተባለው "በኢየሱስ ስም ጥምቀት" የሚባለውም የስያሜ ጉዳይ ነው፣ ይላሉ፡፡

   ነገር ግን ሐስ.2፡38, ሐስ.8፡16, ሐስ.19፡5 እና ሐስ.22፡16 ላይ ስንመለከት፣ "በኢየሱስ ስም ጥምቀት" የሚለው የስያሜ ጉዳይ ሳይሆን ሰዎች የኢየሱስን ስም እየጠሩ ተጠምቀዋል፡፡
2. በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ "በኢየሱስ ስም ተጠመቁ" የተባሉት የብሉይ ኪዳንን ጥምቀት የተቀበሉት አይሁድና የሰማርያ(የአህዛብ አይሁድ ድብልቆች) ብቻ ናቸው፣ የብሉዩን ጥምቀት ያልተቀበሉት አህዛብ "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" መጠመቅ አለባቸው ይላሉ፡፡

[130] Ibid, 43፣ ትምህተ 23/5/በ

ነገር ግን አህዛብም በኢየሱስ ስም መጠመቃቸውን በሐስ.10፡44-48 ስንመለከት መከራከሪያው ውድቅ መሆኑና በዚህም አንዳንድ ሥላሴያውያን "በኢየሱስ ስም" ማጥመቅን የተዉበት አመክንዮም ትክክል አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነታ ስንመለከት ግን የሁለቱም ወገኖች ክርክር "ስልቻ ቀልቀሎ፣ ቀልቀሎ ስልቻ" መሆኑን እንመለከታለን፣ በመጀመሪያ ጥምቀት "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መደረግ አለበት" ያለው ኢየሱስ ሲሆን ይህንንም የተናገረው ከማረጉ በፊት ነው፣ ኢየሱስ ካረገ በኋላ ደግሞ ሐዋርያቱ ጥምቀትን በኢየሱስ ስም አደረጉ፣ በዚህም ልዩነቱ ከምን መጣ? ብለን ስንመለከት፣ ከኢየሱስ እርገት በኋላ በተለወጠው ነገር ነው፣ ይህ ለውጥ ደግሞ፣

ፊልጵ.2፡6-10 "እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቆጠረውም፣ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰው ምሳሌ ራሱን ባዶ አደረገ፣ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፣ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፡፡ በዚህም ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፣ <u>ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም **ሰጠው**፣ ይህ በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፣ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው፡፡</u>"

ከዚህም ቃል የምንረዳው ኢየሱስ ካረገ በኋላ፣ በምድር ላይ በፈፀመው ስራ ምክንያት ለስሙ ትልቅ ስልጣን መሰጠቱን ነው፣ በዚህም **<u>ከስም አንፃር</u>** "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" እና "በኢየሱስ ስም" መካከል ልዩነት አለመኖሩን እንመለከታለን፡፡

ስለዚህ ጥምቀት "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም" ማጥመቁም ስህተትነት የለውም፣ "በኢየሱስ ስም" ማጥመቁም ስህተትነት የለውም፣ ምክንያቱም የኢየሱስ ስምም ከሁሉም ስም በላይ እንደ ሆነው የ"አብ፣ወልድን መንፈስ ቅዱስ" ስም ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣ በዚህም በሁለቱ አሰራሮች ላይ የሚደረገው ክርክር "ጉንጭ አልፋ" ክርክር ብቻ ነው፡፡

ነገር ግን የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ይህንን እውነታ በመለጠጠ "አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" ማለቷ፣ በምታሳትማቸው መጽሐፍ ቅዱሶች ውስጥ ማቴ.28፡19 መሠረዟ እንዲሁም በሌሎች መጽሐፍቶቻቸው ውስጥም "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን "አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ" በማለት "ና" የምትለዋ አያያዥ ቃል ማውጣቷ ትልቅ ኃጢያት ነው፣ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡፡

5.1.2. <u>“እንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ”</u>

ቤተክርስቲያኗ፣ የኢየሱስ የስም ስልጣን ከ“አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ” ስም ስልጣን ጋር እኩል የመሆንን እውነታ በማስፋት፣ “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” የሚለው ድምዳሜ ድረስ ሄዳለች ይህ ደግሞ ትልቅ ስህተት ነው፣ በቀላሉ ከላይ በተመለከትነው በፊልጵ.2፡6-10 ላይ “ሰጠው” በሚለው ቃል ውስጥ እንኳን ሰጪ አካል መኖሩን መመልከት አልቻለችም፣ በተመሳሳይ መንገድም፣

> ነቆሮ.15፡27 “ሁሉን ከእግሩ በታች አስገዝቶአልና፡፡ ነገር ግን ሁሉ ተገዝቶአል ሲል፣ <u>ሁሉን ካስገዛለት በቀር</u> መሆኑ ግልጥ ነው፡፡”

በሚለው ቃል ውስጥም ያለውን ተመሳሳይ እውነታን መመልከት አልቻለችም፡፡

“አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” የሚለው አስተምህሮ ስህተት በመሆኑ ለቤተክርስቲያኗ ይህንን ሐሳብ የማስረዳት ስራ እንደ ጥምቀት ጉዳይ ቀላል አልሆነላትም፤ ቤተክርስቲያኗ ይህንን ከፍተት ለመወጣት ለአዕምሮ የማይያዙ ፍልስፍናዎችንና ከመጽሐፍ ቅዱሱ እንዲሁም እርስ በራሱ የሚጋጩ ትምህርቶችን ትሰጣለች፣ ከሁሉ ከባድ ፈተና የሆነባት ደግሞ “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” ስትል “አብና መንፈስ ቅዱስ” የሚባሉትን የእግዚአብሔር ማንነቶች የምታደርገውን ማጣቷ ነው፡፡

ቤተክርስቲያኗ “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” የሚለውን ለማስረዳት የተፈጠሩባትን የአስተምህሮ ስህተቶች፣ ክፍተቶችና የሐሳብ ግጭቶችን ስንመለከት ሦስት መሠረታዊ እውነታዎችን ከግምት ውስጥ ባለማስገባት እንደተፈጠሩ እንመለከታለን፣ ይህም፣

- እግዚአብሔርና አብ ከኢየሱስ ጋር ያላቸውና አንድነትና ልዩነት ያለማገናዘብ ችግር፣
- አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስን በአንድ ላይ አጠጋግቶ ኢየሱስ ማድረግ የማይቻል መሆኑን፣
- የእግዚአብሔር ሥላሴነትን መሸፈን የማይቻል መሆኑን

ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

5.1.2.1. <u>እግዚአብሔርና አብ ከኢየሱስ ጋር ያላቸውና አንድነትና ልዩነት ያላገናዘበ መሆኑ</u>

“አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” የሚለው አስተምህሮ “እግዚአብሔር”፣ “አብ” እና “ኢየሱስ” የሚባሉትን ማንነቶች አንድነትና ልዩነት ያላገናዘበ አስተምህሮ ነው፡፡

5.1.2.1.1. <u>እግዚአብሔርና ኢየሱስ</u>

ቅዱሳን ከኢየሱስ መገለጥ በፊት እግዚአብሔርን ሲያመልኩ ነበረ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ሙሴ፣ ኤልያስ … የሚያመልኩትን አካል ሳያውቁት ሲያመልኩ አልነበረም፣ ሲያመልኩት የነበረው “ስሜ እግዚአብሔር ነው” ያላቸውን አምላክን ነበረ፡-

- ዘጸ.6፡3 "ለአብርሃም ለይስሐቅም ለያዕቆብም ... <u>ስሜ እግዚአብሔር</u> አልታወቀላቸውም ነበር።"
- ዘሌ.19፡12 "<u>በስሜም በሐሰት አትማሉ፣ የአምላካቸሁንም ስም አታርክሱ፣ እኔ እግዚአብሔር</u> ነኝ።"
- ዘሌ.22፡2 "... የተቀደሰውን ስሜን እንዳያረክሱ ለአሮንና ለልጆቹ ንገራቸው <u>እኔ እግዚአብሔር ነኝ</u>።
- ዘጸ.15፡3 "እግዚአብሔር ተዋጊ ነው፣ <u>ስሙም እግዚአብሔር</u> ነው።"
- ኢሳ.51፡15 "ሞገዱም እንዲተምም ባህርንም የማናውጥ አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ፣ <u>ስሜም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው</u>።"
- ኤር.12፡16 "በበአል ይምሉ ዘንድ ህዝቤን እንዳስተማሩ፣ <u>በስሜም፣ ህያው እግዚአብሔርን!</u> ብለው ይምሉ ዘንድ የህዝቤን መንገድ በትጋት ቢማሩ፣ በዚያን ጊዜ በህዝቤ መካከል ይመሠረታሉ።"
- ሆሴ.12፡6 "... እርሱም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፣ <u>የመታሰቢያውም ስም እግዚአብሔር ነው</u>።"

በዚህም ፈጣሪ አምላክ ስሙ "እግዚአብሔር" መሆኑን እንመለከታለን፣ በዚህ ስሙም የሚጠራው ለብሉይ ኪዳን ዘመን ብቻ ሳይሆን ለዘላለምም ነው፣

> ዘጸ.3፡15 "እግዚአብሔርም ... <u>ይህ ለዘለላለሙ ስሜ ነው፣ እስከ ልጅ ልጅ ድረስ መታሰቢያዬ ይህ ነው</u>።"

በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የተገለጠው ፈጣሪ አምላክ ስሙ "እግዚአብሔር" መሆኑን እንመለከታለን፣ ይህም አምላክ ደግሞ ቅዱስ በመሆኑ ስሙ "ኢየሱስ" ሆኖ ስሜ "እግዚአብሔር" ነው ብሎ አይዋሽም፣ ትክክለኛ ስም የማይነገረው ለማጭበርበር ወይ ደግሞ በፍራቻ ነው፣ እግዚአብሔር ግን ቅዱስና ኤልሻዳይ በመሆኑ ይህንን ልናስብበት አንችልም።

"እግዚአብሔር" የሚባለው ስም በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን የተነገረው በዋናነት የሦስቱ ሥላሴ(አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) የአንድነት ስም ሆኖ ነው፣ ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱሱ "እግዚአብሔር" የሚለው ስም ላይ "አንድ እግዚአብሔር"(ዘዳ.6፡4, ገጣ.2፡5, ገቆሮ.12፡6 ...) ብሎ ተመልሶ ደግሞ ሦስቱን የሥላሴ ማንነቶች "ከእግዚአብሔርነት ማንነታቸው" ሳያወርድ በየስማቸውና በየምግባራቸው ለያይቶ የሚጠራው፣ በዚህም "እግዚአብሔር" የተባለውን ስምና ማንነት የገዘፈ የሥላሴ(የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ) የአንድነት ስምና ማንነት ነው(በሚቀጥለው ክፍል በስፋት ተመልክቷል)።

እግዚአብሔር መጀመሪያ የለውም ነገር ግን "ኢየሱስ" የተባለው ስም የተጀመረበት ጊዜ አለው፣ ኢየሱስ የተባለው ስም የተጀመረው ከሥላሴ አንዱ የሆነው "ወልድ" ሲጋን

ለብሶ መወለድ በመፈለጉ፣ መለኮትና ስጋ ተዋህዶ ሲወለድ፣ ለተዋህዶው ማንነት "ኢየሱስ" የሚለው ስም ተሰጠ(ማቴ.1፡21)። በዚህም "ኢየሱስ" የሚለው ስም የተሰጠበት ጊዜ ያለውና ስሙም የተሰጠው ፍፁም መለኮት ብቻ ለሆነ አካል ሳይሆን ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው ሆኖ ለተወለደው <u>ለተዋህዶው ማንነት ነው</u>።

ይህ ተዋህዶነት(ቆላ.2፡9) ያስፈለገው ደግሞ ለሰው ልጆች ኃጢያት ስርየት በመሆኑም የስሙ አሰያየም ከኃጢያት ስርየት ጋር የተያያዘ ነው፣ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱሱ በግልፅ ኢየሱስ ማለት "የኃጢያት መድኃኒት" ማለት ነው ብሎ ይነግረናል(ማቴ.1፡21)።

በዚህም "አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ" ማለት "እግዚአብሔርን" ስለ ሰው ልጅ የኃጢያት ስርየት ብሎ ከኦሪጂናል ማንነቱ ራሱን ዝቅ አድርጎ በወረደው ወልድ የተዋህዶ ማንነት የሚገድብ፣ የእግዚአብሔርን ማንነት "በኃጢያት ስርየት" ብቻ የሚገድብና ከኢየሱስ መወለድ በፊት የነበሩትን በእግዚአብሔር ስም ሲደረጉ የነበሩትን አምልኮዎችን በሙሉ ባዶ የሚያደርግ የስህተት አስተምህሮ ነው።

5.1.2.1.2. <u>አብና ኢየሱስ</u>

ሥላሴ ማለት "አንድ ውስጥ ያለ ሦስትነት ማለት ነው"፣ ይህ በተፈጥሮ በሰው ልጅ(ነፍስ፣ መንፈስና ስጋ)፣ በፀሐይ(ሰማዩ ላይ በምትታየው፣ በብርሃኗና ኃይሏ) ... ውስጥ ያለ የተዋህዶነት አሰራር መሆኑን በ5.1.2.3.7 ክፍል በዝርዝር ተመልክቷል፣ የፈጣሪ ሥላሴነት አንድ እግዚአብሔር ውስጥ ያሉ አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ የተባሉትን የእግዚአብሔር ማንነቶች ናቸው።

ኢየሱስ የአምላክና የሰው ተዋህዶ ሲሆንም ተዋህዶነቱ የሰውና አምላክ ሥላሴነትን አሰራር ሳይጥስ ነው፣ ይህም ኢየሱስ ሥላሴነትን የያዘው ወልድ በሆነው መለኮትነት፣ ሰው በሆነው ከማርያም በወሰደው ማንነትና በዚህም ስጋ ውስጥ ከአብ በተሰጠው ህይወት ነው(ዮሐ.5፡26)፣ በዚህም ኢየሱስ የሰውና የአምላክ ተዋህዶ በመሆን የሰው-አምላክ መካከለኛነትን ስፍራን ያዘ፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስን "መካከለኛ" የሚልበት(1ጢሞ.2፡5, ዕብ.1፡24 ...) ሁለተኛው ትርጉም ይኸው እውነታ ነው።

ነገር ግን ኢየሱስ በዚህ ሥላሴነቱ ውስጥ ያለውን አምላክነት በሙላት መጠቀም ከመጣለት ዓላማ ጋር ስለማይሄድ፣ ይህን አምላክነቱን ባዶ አደረገ(ፊሊ.2፡7)፣ ከዚህ በተጨማሪም በአምላክነቱ ውስጥ የተዋህደው ስጋዊ ማንነት በሚፈጥረው ውስንነት ምክንያት ኢየሱስ በአብዛኛው ሲኖር የነበረው እንደ የትኛውም የሰው ልጅ ነበረ።

ይህንንም እውነታ ኢየሱስ ከስጋ ካልተዋህዱት መንፈስ ቅዱስና አብ ጋር በነበረው ልዩነትና ግንኙነት ውስጥ መመልከት እንችላለን፤ በዚህም ነው ኢየሱስ "እኔ ሄጄ መንፈስ ቅዱስ ቢመጣላችሁ ይሻላችኋል"(ዮሐ.16፡7-13) ያለው በተመሳሳይ መንገድም ከአብ ጋር በነበረው ግንኙነት ውስጥ ይህንኑ እውነታ ያስመለከተን፣

- **<u>አብ ከእሱ እንደሚበልጥ መናገሩ</u>**
  - ዮሐ.14፡28 "... የምትወዱኝስ ብትሆኑ <u>ከእኔ አብ ይበልጣልና</u> ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር፡፡"
  - ማቴ.24፡36 "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን <u>ከአባት ብቻ</u> በቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ <u>ልጅም ቢሆን</u> የሚያውቅ የለም፡፡"
  - ሉቃ.18፡19 "<u>ኢየሱስም ስለ ምን ቸር ትለኛለህ፣ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም</u> የለም፡፡"
  - ዮሐ.5፡19-20 "... እውነት እውነት እላችኋለሁ አብ ሲያደርግ ያየውን እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ <u>ምንም አይችልም</u>... አብ ወልድን ይወዳልና የሚያደርገውን ሁሉ ያሳየዋል ..."
  - ዮሐ.6፡57 "ሕያው አብ <u>እንደላከኝ</u> እኔም <u>ከአብ የተነሳ</u> ሕያው እንደምሆን...
  - ዮሐ.6፡39 "... <u>የላከኝ</u> አብ ፈቃድ ይህ ነው፡፡"
  - ዮሐ.20፡17 "... እኔ ወደ <u>አባቴና</u> ... ወደ <u>አምላኬ</u> ... አርጋለሁ ብለሽ ንገሪ አላቸው፡፡"
  - ዕብ.5፡7 "እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደ ሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን አቀረበ፣ <u>እግዚአብሔርን ስለመፍራቱ</u> ተሰማለት፡፡"

እነዚህ ቃላትም የአብና የኢየሱስን ግንኙነት ግልፅ ሲያደርጉል በሌላ በኩል ደግሞ የቤተክርስቲያኗ "አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አባባል ውድቅ ያደርጋሉ፣ ይባሱኑ "አንዱን ብቻ ነው የምንይዘው" የሚለው የግዴታ ከሆነ ከኢየሱስ ይልቅ "አብ ብቻ" ቢሉ የሚሻላቸው መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- **<u>ኢየሱስ ወደ አብ መፀለዩ</u>**

ኢየሱስ ብዙ ስፍራዎች ላይ ወደ አብ ሲፀልይ ነበረ፣

- ዮሐ.17፡1-21 " ኢየሱስም ይህ ተናግሮ ወደ ሰማይ አይኖቹን አነሳና እንዲህ አለ፡፡ <u>አባት ሆይ</u> ... እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንክ <u>አንተ የላክኸውን ኢየሱስ ክርስቶስንም</u> ያውቁ ዘንድ ... እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ስራ ፈፅሜ በምድር አከበርሁህ ... አባት ሆይ ... የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት ... ከአንተ ዘንድ እንደወጣሁ በእውነት አወቁ፣ አንተም እንደላክኸኝ አመኑ ... ስለዚህ <u>እለምንህለሁ</u> ... እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ ... ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ ... ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው <u>አልለምንህም</u> ..."

- ማቴ.27፡46 “በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ፣ ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ ፣ ስለምን ተውኸኝ፣ ማለት ነው ።”
- ሉቃ.23፡34 “ኢየሱስም፣ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ።”

ቤተክርስቲያኗ መቼም ኢየሱስ አዕምሮ እንደሌለው ሰው “ከራሱ ጋር ሲያወራ ነበረ” እንደማትል ተስፋ አደርጋለሁ።

- **<u>የኢየሱስ የአማላጅነት እውነታ</u>**

ኢየሱስ በምድራዊ ህይወቱ ወቅት ዋናው የሰራው ስራ የማስታረቅ ስራ ነው፣ አሁን ደግሞ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ አገልግሎቱ የምልጃ አገልግሎት መሆኑን በ4.1.1.4 ክፍል ተመልክተናል ነገር ግን “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” ከተባለ ማን ማንን ከማን ጋር? አስታረቀ፣ አሁንስ ቢሆን ማነው ማንን ከማን ጋር የሚያማልደው? የሚለው መመለስ አለበት።

- **<u>የኢየሱስ የመስካሪነት እውነታ</u>**

- ማቴ.10፡32-33 “ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ <u>እኔ</u> ደግሞ በሰማያት ባለው <u>በአባቴ</u> ፊት እመሰክርለታለሁ፤ በሰው ፊትም ለሚክደኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።”
- ራዕ.3፡5 “ድል የነሳው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጎናፀፋል፣ ስሙንም ከህይወት መጽሐፍ አልደመስስም፣ <u>በአባቴና</u> በመላዕክቱ ፊት ለስሙ <u>እመሰክርለታለሁ</u>።”

እነዚህ አብ ከኢየሱስ እንደሚበልጥ መነገሩና የኢየሱስም የፀሎት፣ የማማለድና የምስክርነት አገልግሎት የቤተክርስቲያኗን “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” አስተምህሮ የተሳሳተ መሆኑን ያሳያል።

5.1.2.2. <u>አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስን በአንድ ላይ አጠጋግቶ ኢየሱስ ማድረግ የማይቻል መሆኑ</u>

ቤተክርስቲያኗ “አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ” በሚለው አስተምህሮዋ ውስጥ ኢየሱስን “ብቸኛው አምላክ” ስትለው ሌሎቹን የሥላሴ አካላት “አብና መንፈስ ቅዱስን” ምን ማድረግ እንዳለባት ትልቅ ፈተና ሆኖባታል፣ በዚህም አብና መንፈስ ቅዱስን በኢየሱስ ውስጥ ለማሸጋሸግ ሞክራለች፣

- [131] “አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ የማይነጣጠሉ በአንድ አካል ውስጥ (በክርስቶስ ፍፁም አካል) የሚኖሩ ናቸው ... እነዚህ ሦስቱ በአካሉ ብቻ ማለትም በሰውነቱ ብቻ

[131] ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፊልጉ - መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማስተማሪያ**፣ ገፅ 36 – 37፣ ትምህርተ 21/4

ተዋህደው እንጂ ለያይተን ልናያቸው አንችልም ... አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ... በአካል አይለያዩም::"

- [132] "(አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ) እንደ (ሰው) መንፈስ እንደ ነፍስ እንደ አካል ስለሆኑ በአንድ በክርስቶስ ሰውነት ተጠቅልለው ይኖራል::"

ትላለች፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ለ"አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮዋ ስትል "አብና መንፈስ ቅዱስ"ን አሳንሳ ተመልክታለች፣ በዚህም፣

- [133] "አብ ማለት አባት ማለት ብቻ ነው፣ የአብ ስም ኢየሱስ ነው"
- [134]"መንፈስ ቅዱስ ማለት ረቂቅ የማይጨበጥ ቅዱስ እስትንፋስ ማለት ብቻ ነው"

በማለት ለዚህም ደግሞ የኢየሱስ ስጋ እነዚህን አምላካዊ ማንነቶች መሸከም እንዲችል ስጋውን መለኮታዊ አድርጋለች ነገር ግን ይህ አብንና መንፈስ ቅዱስን የማሳነስና የኢየሱስን አካል መለኮታዊ አካል ማድረግ ስህተት መሆኑን ቀጥለን እንመለከታለን::

5.1.2.2.1. "አብ ያለው በኢየሱስ አካል ውስጥ ነው"

ይህ የማጠቃለያ ስራ ከመጽሐፍ ቅዱሱም ከቤተክርስቲያኗም አስተምህሮ ጋር የሚጋጭ ነው፣ ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነው ኢየሱስ እራሱ ወደ አብ ሲፀልይ የነበረ መሆኑና አሁንም አማላጅ መሆኑን ስንመለከት አብን አሳንሶ በኢየሱስ ማንነት ውስጥ ማስገባት ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር የሚጋጭ አሰራር ነው::

ከመጽሐፍ ቅዱሱ በተጨማሪ አስተምህሮው ከሌላ የቤተክርስቲያኗ አስተምህሮም ጋር ይጋጫል፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

> [135]"1ጢሞ.3፡16 እግዚአብሔር በስጋ እንደተገለጠ ያስረዳል:: እግዚአብሔር ተጠቃሎ ስጋ ሆነ አይልም እግዚአብሔር <u>አብ ከማርያም አልተወለደምና</u>:: እግዚአብሔር በስጋ ከመገለጡ በፊት መንፈስና ቃል ሆኖ ወይም <u>መለኮትና ቃል</u> ሆኖ ይኖር ነበር:: ስለዚህ ትንቢቱ ሲፈፀም በውስጡ የነበረውን ቃሉን ስጋ አደረገውና ተገለጠበት ... እግዚአብሔር አብ ስጋ ሆነ ማለት አንችልም..."

ይህም አስተምህሮ "መንፈስ/መለኮት" በማለት የገለፁት አብ "ቃል" በሚባለው ማንነት ውስጥ አለመሆኑን ያሳያል::

እነዚህ አብን አሳንሶ ኢየሱስ ውስጥ ለማሸጋሸግ የተደረገው ሙከራ ከመጽሐፍ ቅዱሱም ከቤተክርስቲያኗም አስተምህሮ ጋር የሚጋጭና አብን አሳንሶ የኢየሱስ አካል ውስጥ ማሸጋሸግ የማይቻል መሆኑን ነው የሚያሳየን::

---

[132] Ibid, 42፣ ትምህርተ 23/5
[133] Ibid, ገፅ 41
[134] Ibid, 41፣ ትምህርተ 23/3/ሀ
[135] Ibid, 45፣ ትምህረተ 24/1/

5.1.2.2.2. [136]“መንፈስ ቅዱስ ማለት ረቂቅ የማይጨበጥ ቅዱስ እስትንፋስ ማለት ብቻ ነው”

በርግጥ ይህ ዘዴ የማምለጫ ዘዴ ሳይሆን የመሞቻ ዘዴ ነው ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን ከሙሉ አምላክነቱ ቀንሶ “ብቻ” በሚለው ቃል ገድቦ ማስቀመጡ የማይሰረየውን ኃጢያት “መንፈስ ቅዱስን መስደብ”(ማቴ.12፡31-32) ውስጥ የገባ አባባል ነው፣ እነዚህ ሰዎች ለዚህ አስተምህሯቸውና እምነታቸው የኃጢያት ስርየት የላቸውም፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስን በሙሉ ማንነቱ ካለማየት የመጣ ችግር ነው፣ ሌላው ቀርቶ፣

> ኢሳ.11፡24 “የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኃይል መንፈስ፣ የእውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ …”

የሚለውን ቃል እንኳን ሙሉውን መውሰድ አልፈለጉም ምክንያቱም ሙሉውን ከወሰዱ መንፈስ ቅዱስ አምላክ መሆኑ ይታያል ይህ ደግሞ ወደ ሥላሴ አስተምህሮ ይሄድባቸዋል፣ ስለዚህ ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር የምትሄደዋን “የኃይል” የምትለዋን ብቻ ለይተው ወሰዱ፡፡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በኛ ቋንቋ ልንገልፀው የማንችለው ሙሉ እግዚአብሔር አምላክ ነው፡፡

- **እግዚአብሔር አምላክ በመሆኑም፣**
  - ፈጣሪ ነው - ዘፍ.1፡2, ኢዮ.33፡4, መዝ.104፡30
  - ሁሉን ያውቃል - ኢሳ.40፡13, 1ቆሮ.2፡10-11, ዮሐ.14፡26
  - በሁሉም ስፍራ ይገኛል - ኢዮ.139፡7, መዝ.139፡7
  - ሁሉን ቻይ ነው - ሮሜ.15፡19
  - ዘላለማዊ ነው - ዕብ.9፡14
  - የልብን ያውቃል - ሮሜ.8፡27
  - ኣይታለልም - ሐስ.5፡3-4
  - ህይወት ይሰጣል - ዮሐ.6፡63
- **እንደ አምላክነቱም ለሰዎች ጸጋን ይሰጣል**
  - ኃይልን ይሰጣል - ሐስ.1፡8
  - ጥበብ፣ እውቀትና ማስተዋልን ይሰጣል-ዘጸ.31፡3, ዘጸ.35፡31, ኢሳ 11፡2
  - እምነት፣ የፈውስና የተአምራት ጸጋዎችን ይሰጣል - 1ቆሮ.12፡8-9
  - ትንቢት ይሰጣል - ዘኁ.11፡25-26, 1ሳሙ.10፡10, 1ሳሙ.19፡20-23, ሉቃ.1፡67, ሐስ.19፡6
  - ስብከትን ይሰጣል - ኢሳ.61፡1, ሚኪ.3፡8, 1ጴጥ.1፡12
  - ይቀድሳል - ሮሜ.15፡15-16, 1ቆሮ.6፡11, ቲቶ3፡5

[136] ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ - መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማስተማሪያ**፣ ገፅ 41፣ ትምህርተ 23/3/ሀ

- ብፁአን ያደርጋል - 1ጴጥ.4፡14
- ያስነግሳል - መሳ.3፡10
- ይሾማል - ሐስ.20፡28
- ያድናል - ፊሊ.1፡19
- ያሳርፋል - ኢሳ 63፡14
- መገለጥ ይሰጣል - 1ቆሮ.12፡7
- ቃልን ይገልፃል - ሐስ.4፡31
- ልሳን ይሰጣል - ሐስ.2፡4, ሐስ.19፡6
- ይለውጣል - 1ሳሙ.10፡6
- አርነትያወጣል-2ቆሮ.3፡17

➢ **<u>ሰብአዊ ማንነት አለው</u>**

የሐዋርያት ቤተክርስቲያን "መንፈስ ቅዱስ ኃይል ብቻ ነው" ወይ "እስትንፋስ ብቻ ነው" የሚለው አስተምህሮዋ ስህተት መሆኑና መንፈስ ቅዱስ ህይወት፣ እውቀት፣ ስሜትን፣ ፈቃድን፣ ኃላፊነት ... ያለው ሙሉ "ሰብአዊነት" ያለው አምላክ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፣ በዚህም መንፈስ ቅዱስ፡-

- ያዝናል - ኤፌ.4፡30
- ይናገራል - ሐስ.13፡2
- ይመሰክራል - ዕብ.10፡15-16
- ይመክራል - ኢሳ.11፡2
- ይልካል - ሐስ.13፡4
- ይከለክላል - ሐስ.16፡6
- ይወቅሳል - ዮሐ.16፡8
- ይማልዳል - ሮሜ.8፡26
- ይመራል - ዮሐ.16፡13
- ያስተምራል - ሉቃ.12፡12
- ያስረዳል - ሉቃ.2፡26
- ያሳያል - ዕብ.9፡8
- ያፅናናል - ሐስ.9፡31
- ከቅዱሳን ጋር ኅብረት ያደርጋል - 2ቆሮ.13፡14 ...

በዚህም "አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ" የሚለውን ሐሳብ ለማጠናከር ሲባል መንፈስ ቅዱስን ከሙሉ አምላክነቱ ወደ "ኃይልነት" ብቻ ለመገደብ የተደረገው ሙከራ ስህተትም፣ ይቅር የማይባል ኃጢያትም መሆኑን እንመለከታለን፡፡

5.1.2.2.3. “የኢየሱስ ስጋ መለኮታዊ እንጂ ሰብአዊ አይደለም”

ቤተክርስቲያኗ “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” አስተምህሮዋ ምክንያት ብዙ ነገሮች ተረብሸውባታል፣ ከላይ እንዳየነው አብንና መንፈስ ቅዱስን ኢየሱስ ውስጥ ለማጠቃለል ሞክራለች፣ እንደዚህ ለማድረግ ደግሞ “የኢየሱስ ስጋ እንደ ሰው ስጋ መሆን የለበትም” በማለት ስጋውን መለኮታዊ ታደርጋለች::

- [137] “ክርስቶስ ከሴት ዘር የተወለደ መባል ሲገደድ ከሴት ስጋና ደም ተወለደ ማለት ሳይሆን … ንፁህ መለኮታዊ ሰው ሆኖ ከድንግል ማርያም ማህፀን የተወለደ ማለት ነው::”
- [138] “ኢየሱስ ክርስቶስ የአብርሃም ወይም የዳዊት ወይም የሴት ዘር ተቀላቅሎበት የተወለደ አለመሆኑ ግልፅ ነው::”

ነገር ግን ኢየሱስን የተዋህደው ስጋ የሰው ስጋ እንጂ መለኮታዊ ሰውነት አለመሆኑን መጽሐፍ ቅዱሱ ብዙ ስፍራዎች ላይ በተለያየ መንገድ ተብራርቷል፣

- <u>በስጋ መምጣቱን፣</u>
  ሮሜ.9፡5 “… <u>ከእነርሱም</u>(ከእስራኤላውያን) ክርስቶስ <u>በስጋ መጣ</u> …”
- <u>አብሮ አደጎቹም ሆነ ህዝቡ ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው የለበሰው የሰው ስጋ በመሆኑ እንደ ማንኛውም ሰው ሲመለከቱት የነበረ መሆኑን፣</u>
  - ማቴ.13፡55 “ይህ የፀራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን?”
  - ዮሐ.8፡57 “አይሁድም ገና ሀምሳ አመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት::”
  - ዮሐ.10፡33 “አይሁዳውያኑም፣ ስለ መልካም ስራ አንወግርህም፣ ስለ ስድብ፣ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ::”
- <u>የለበሰው አካል መለኮታዊ አካል ሳይሆን ስጋዊ አካል በመሆኑ ስጋዊ የእድገት ደረጃዎችን፣ ስሜቶችንና መከራዎችን መቀበሉን፣</u>

ተረገዘ - ማቴ.1፡18	ደከመ - ዮሐ.4፡6	አለቀሰ - ዮሐ.11፡35
ተወለደ - ሉቃ.2፡7	ተኛ - ማቴ.8፡24	ተፈተነ-ማር.1፡12-13
አደገ - ሉቃ.2፡52	ተራበ - ማቴ.4፡2	ተደበደበ-ሉቃ.22፡64
ተጠመቀ-ማቴ.3፡13-17	ተጠማ-ዮሐ.19፡28	ተገደለ - 27፡50 …

[137] ቄስ ተክለማርያም ገዛኸኝ(1974)፣ **በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ - መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ማስተማሪያ**፣ ገፅ 33፣ ትምህርተ 21/2/ቸ/ሐ

[138] Ibid 47፣ ትምህርተ 24/3

- <u>የለበሰውም ስጋዊ ማንነት የዳዊት ዘር ሐረግ መሆኑን፣</u>
  ኢየሱስ የተወለደው "ከእስራኤል ዙፋን ከዘርህ ሰው አታጣም"(1ነገ.9፡5, 2ዜና.7፡18 ...) የሚል ቃል ኪዳን ከተገባለት ከዳዊት ዘር መሆኑ ተነግሯል፣
  - ማቴ.1፡1-17 ላይ የኢየሱስ የዘር ሐረግ የዳዊት የዘር ሐረግ መሆኑ በስፋት ተመልክቷል፣
  - ሮሜ.1፡3-4 "ይህም ወንጌል <u>በስጋ ከዳዊት ዘር ስለተወለደ</u> ... ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡"
  - ሐስ.13፡23 "ከዚህም ሰው(ከዳዊት) <u>ዘር</u> እግዚአብሔር ... ኢየሱስን አመጣው፡፡
  - ራዕ.22፡16 "እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ፡፡ እኔ <u>የዳዊት ስርና ዘር ነኝ</u> ..."

በዚህም ኢየሱስ የለበሰው ስጋ የሰው ስጋ እንጂ መለኮታዊ ስጋ አለመሆኑን እንመለከታለን፣ ይህ የሆነው ደግሞ ዝም ብሎ ሳይሆን ኢየሱስ የመጣለት ዋናው አጅንዳ በመሆኑ ነው፣ ኢየሱስ በሰው ስጋ መምጣት ያስፈለገው ስለሰው ልጆች ኃጢያት ዋጋ የሚከፍለው በስጋ በመሆኑ ነው፣

> ዕብ.2፡14-17 "በህይወታቸውም ሁሉ ስለ ሞት ፍርሀት በባርነት ይታሰሩ የነበሩትን ነፃ እንዲያወጣ <u>በስጋና በደም እንዲሁ ተካፈለ</u> ... <u>በነገር ሁሉ ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው</u>፡፡"

ኢየሱስ የመጣው ለሰው ልጆች ኃጢያት ዋጋ ለመክፈል በመሆኑም የሰው ልጆችን ሆኖ ነው የመጣውም እንደዚሁም ዋጋም የከፈለው፡፡

ኢየሱስ የመጣው "በስጋ አካል ነው" የሚለውና "በሌላ አካል" ነው ብሎ ማመን መካከል ደግሞ ከባድ ልዩነት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱሱ ይናገራል፣

- 1ዮሐ4፡2-3 "የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፣ <u>ኢየሱስ ክርስቶስም በስጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤</u> ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚ መንፈስ ነው፤ ይህ እንዲመጣ ሰምታችኋልና፣ አሁንም እንኳን በዓለም አለ፡፡"
- 2ዮሐ.1፡7-8 "<u>ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ **የማያምኑ ናቸው**፣ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው</u>፡፡ ሙሉ ደምወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሰራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፡፡ ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖረው ሰው አምላክ የለውም፣ <u>በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት</u>፡፡ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይንም ትምህርት ባያመጣ <u>በቤታችሁ አትቀበሉት ሠላምም አትበሉት ሠላም የሚለው ሰው በክፉ ስራው ይካፈላልና</u>፡፡"

በዚህም ኢየሱስ በሰው ስጋ እንደመጣ የማይቀበል አስተምህሮ የተሳሳተ መሆኑንና ከሁሉ በላይ ደግሞ እነዚህን ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የማይቀበሉትን ሰዎች "ሠላም" በማለት ብቻ ሰው እግዚአብሔር ካስቀመጠለት ክብር እንደሚጎድል እንመለከታለን።።

በአጠቃላይም፣ አብም መንፈስ ቅዱስም ወደ የትም መጠጋጋት የማይችሉና ሙሉ አምላክነት ያላቸው መሆናቸውን፣ ቤተክርስቲያኗም ለ"አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ" አስተምህሮዋ ብላ አብንና መንፈስ ቅዱስን አሳንሳ የኢየሱስ አካል ውስጥ ለማሸጋሸግ ያደረገችው ሙከራ ስህተትና ከዚያም ባለፈ የማይሰረይ ኃጢያት መሆኑን፣ ቤተክርስቲያኗ የኢየሱስ አካል አብንና መንፈስ ቅዱስን መሸከም እንዲችልላት ብላ አካሉን መንፈሳዊ አካል ያደረገችበት አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና ክርስቲያኖችም ይህንን አስተምህሮ ከሚከተሉት ጋር ግንኙነት ማድረግ የሌለባቸው መሆኑን እንመለከታለን።።

5.1.2.3. <u>የእግዚአብሔር ሥላሴነት ሊሸፈን የማይችል ግልፅ ነገር መሆኑ</u>

እግዚአብሔር ፈጣሪ፣ ሰው ተፈጣሪ በመሆኑ፣ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ሥላሴነት በሙላት ማወቅ አይቻልም ይሁን እንጂ እግዚአብሔር በራሱ ሰዎች እንዲያውቁት በመጽሐፍ ቅዱሱ በኩል ራሱን በገለጠው መጠን ግን ሥላሴነቱን መረዳት ይቻላል።።

የሚገርመው ደግሞ የሰው ልጅ ይህንን እውቀት በአንዴው መረዳት ስለሚከብደው መጽሐፍ ቅዱሱ ይህንን እውቀት ያስተማረው መሠረታዊውን የፔዳጎጂን መርህ ተከትሎ ነው፣ በቀላል ትምህርት ጀምሮ ጠለቅ ያለውን እውቀት በመግለጥ፣ በዚህም የሥላሴ እውቀት ከትውልድ ወደ ትውልድ ግልፅ እየሆነ ሲመጣ እንመለከታለን።።

የቀድሞዎቹ ቅዱሳን በሥላሴ እውቀት ከዚህ ትውልድ በላይ ግራ ተጋብተው ነበረ ነገር ግን እንደ ሐዋርያት ቤተክርስቲያን ሳይሰናከሉበት በገባቸው መንገድ ገልፀው አልፈዋል፣ አንዳንዶቹ አንዱ በሦስት ማንነት የሚሰራበትን አሰራርን መግለፅ አቅቷቸው በነጠላ ቁጥርና በብዙ ቁጥር ሰዋሰው ሲምታቱ፣ ሌሎች ደግሞ "የእግዚአብሔር መልአክ" ብለውት ተመልሶ እሱኑ "እግዚአብሔር" ሲሉት፣ ሌሎቹ ከሦስቱ የአንደኛውን አገልግሎት በመመልከት "መልከ ፄዲቅ" ሲሉት፣ ሌሎቹ ደግሞ በሥላሴ መካከል የነበረውን ንግግር በመመልከት "እግዚአብሔር እግዚአብሔርን፣ ጌታዬ ጌታዬን" ሲሉ፣ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻ ዘመን ነብያት ደግሞ "እግዚአብሔር፣ ባሪያዬ፣ መንፈሴ ..." በማለት ሥላሴነትን በተሻለ መንገድ ሲገልፁ፣ የአዲሱ ኪዳኑ አገልጋዮች ደግሞ በግልፅ "አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ሲሉ እንመለከታለን፣ ሁሉንም በዝርዝር እንመለከታለን፣

5.1.2.3.1. በነጠላ ቁጥርና በብዙ ቁጥር ሰዋሰው የተምታቱ

ይህንን የምንመለከተው በአብርሃም ንግግርና በሙሴ ፅሁፎች ውስጥ ነው፣

- **አብርሃም**

ዘፍጥረት ምዕራፍ 18 ላይ በሦስት ሰው ተመስለው ለአብርሃም የተገለጠው/ጡት ሥላሴ የሆነው እግዚአብሔር ነው፣ አብርሃም በዚህ የሥላሴ ማንነት እንዴት ግራ በተጋባ ሰዋሰው እንዳናገረው/እንዳናገራቸው እስቲ እንመለከት፡-

ዘፍ.18፡1-33 "በቀትር ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር ... ተገለጠለት፣ ዓይኑንም አነሳና እነሆ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ ... ወደ ምድርም ሰገደ እንዲህም አለ፣ አቤቱ በፊትህ ሞገስ አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ፣ ጥቂት ውሀ ይምጣላቸሁ ... እነርሱም ሚስትህ ሳራ ወዴት ናት አሉት፣ እርሱም በድንኳን ውስጥ ናት አላቸው፡፡ እርሱም የዛሬ አመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ ሚስትህ ሳራም ልጅን ታገኛለች አለ ...

ሰዎቹም ተነስተው ወደ ሰዶም አቀኑ አብርሃምም ሊሸኛቸው አብሮአቸው ሄደ ... እግዚአብሔርም አለ፣ የሰዶምና ገሞራ ጮኸት እጅግ በዝቷልና ... ሰዎቹም ከዚያ ፊታቸውን አቀኑ፣ ወደ ሰዶምም ሄዱ አብርሃም ግን በእግዚአብሔር ፊት ገና ቆሞ ነበር ..."

ከዚያ ምዕራፍ 19 ላይ ሁለቱ ለሎጥ ተገለጡለት፣ ምክንያቱም አንደኛው (እግዚአብሔር) በ18፡22 አብርሃም ጋር ስለቀረ፡፡

- **ሙሴ**

ሙሴ የአሪት መጽሐፍትን የፃፈው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ነው ነገር ግን ከፍጥረት ታሪክ ጋር የተገለጠለትን የእግዚአብሔርን ሥላሴነት ማንነት ለመግለፅ በነጠላ ቁጥርና በሙሉ ቁጥር አነጋገር መካከል ሲቸገር ነበረ፡-

- ዘፍ.1፡26-27 "እግዚአብሔርም አለ፡፡ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር፤"
- ዘፍ.3፡22 "እግዚአብሔር አምላክም አለ፡፡ እነሆ አዳም ከፉውንና መልካሙን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤"
- ዘፍ.11፡6-7 "እግዚአብሔርም አለ ... ኑ እንውረድ ..."

ሙሴ ይህን በመንፈስ ቅዱስ ምሪት የተመለከተውን እውነታ ለመፃፍ ከሰውኛ ቋንቋ በላይ ሆኖበት የቋንቋውን ሰዋሰው በመጣስ ነጠላ ቁጥርንና ብዙ ቁጥርን በማደባለቅ ሲፅፍ እንመለከተዋለን፡፡

5.1.2.3.2. <u>“እግዚአብሔርም ከእግዚአብሔር ዘንድ”፣ “ጌታዬ ጌታዬን” ያሉም ነበሩ</u>

የሥላሴን ማንነት ባለማስተዋል ሌላ ግራ መጋባት የፈጠሩት ደግሞ ሙሴና ዳዊት ናቸው፣

- <u>**ሙሴ**</u> - “እግዚአብሔርም ከእግዚአብሔር ዘንድ አለ”

ከላይ ያየውን ታሪክ ሙሴ በዘፍጥረት ምዕራፍ 18 እና 19 ላይ ሲፅፈው በመጀመሪያ “ሦስት ሰዎች” አላቸው(ዘፍ. 18፡2)፣ መልሶ እነሱኑ መላዕክት አላቸው(ዘፍ.19፡1)፣ በመጨረሻ (ዘፍ.19፡24) ሥላሴነትን በሚያሳይ መልኩ “<u>እግዚአብሔርም ... ከእግዚአብሔር</u> ዘንድ” በማለት የሥላሴን ምስጢራት በገባው መንገድ ገለጠው፡፡

- <u>**ዳዊት**</u> - “ጌታ ጌታዬን አለ”

የሥላሴ ምስጢር ሙሴ እንደ ገባው “እግዚአብሔር ከእግዚአብሔር ዘንድ” እንዳለው ዳዊትም “ጌታ ጌታዬን” በማለት በገባው መንገድ ሁለቱንም ጌቶች ገለፃቸው፡፡

> ማር.12፡36 “ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ <u>ጌታ ጌታዬን</u>፣ ጠላቶችህን የእግርህ መርገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው፣ አለ፡፡”

ዳዊት ከሙሴ በተሻለ መንገድ ገልጾታል/ገልጿቸዋል፣ ይህ እውነታም መገለጥን መመልከትና በሰውኛ ቋንቋ መግለጥ መካከል ሰፊ ልዩነት እንዳለ ያሳየናል፡፡

5.1.2.3.3. <u>አንዴ “መልአክ” ብለውት መልሰው እሱኑ “እግዚአብሔር” ያሉም ነበሩ</u>

የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች የሥላሴን አሰራር እንደ እኛ በተሻለ መንገድ ባያውቁትም እውነታውን ግን ተረድተውታል፣ በዚህም ወደ ምድር ወርዶ ሲሰራ የነበረውን አንዱን ሥላሴ በመጀመሪያ “መልአክ” ብለውት መልሰው እሱኑ “እግዚአብሔር” ብለውታል፣ ያዩት ሰማያዊ ማንነትም የሚናገራቸው እንደ ተላከ መልአክ ሳይሆን በራሱ ፍቃድ ሁሉንም እንደሚያደርገው እንደ እግዚአብሔር ነበረ፡-

- <u>**ኢጋር**</u>

  ዘፍ.16፡9-13 “<u>የእግዚአብሔር መልአክም</u>፣ ወደ እመቤትሽ ተመለሺ ከእጅዋም በታች ሆነሽ ተገዢ ... እርስዋም ይናገራት የነበረውን <u>የእግዚአብሔርን ስም</u> <u>ዔልሮኢ</u> ብላ ጠራች፣ የሚያየኝን በውኑ እዚህ ደግሞ አየሁትን? ብላለችና፡፡”

- <u>**አብርሃም**</u>

  ዘፍ.22፡11-12 “<u>የእግዚአብሔር መልአክም</u> ከሰማይ ጠራና አብርሃም አብርሃም አለው፣ እርሱም፣ እነሆኝ አለው፣ እርሱም በብላቴናው ላይ እጅህን አትዘርጋ አንዳችም አታድርግበት፣ አንድ ልጅህን <u>ለኔ አልከለከልከምና</u> እግዚአብሔርን የምትፈራ እንደሆንህ አሁን አውቄአለሁ አለ፡፡”

- **<u>ያዕቆብ</u>**

  ዘፍ.31፡11-13 “<u>የእግዚአብሔርም መልአክ</u> በህልም፡፡ ያዕቆብ ሆይ አለኝ፤ እኔም፡፡ እነሆኝ አልኩት … ሐውልት የቀባህበት በዚያም ለእኔ ስለት የተሳልህበት <u>የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ</u> …”

- **<u>ጌዴዎን</u>**

  መሳ.6፡12-14 “<u>የእግዚአብሔር መልአክ</u> ለእርሱ ተገልጦ … <u>እግዚአብሔርም</u> ወደ እርሱ ዘወር ብሎ …”

- **<u>ሆሴዕ</u>**

  ሆሴ.12፡5-6 “(ያዕቆብ) ከ<u>መልአኩም</u> *ጋር* ታግሎ አሸነፈ፣ አልቅሶም ለመነው… <u>እርሱም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፣ የመታሰቢያውም ስም እግዚአብሔር ነው</u>፡፡”

እነዚህ ነብያት ከሥላሴ የተገለጠላቸውን ማንነት “የእግዚአብሔር መልአክ” ብለው መልሰው እሱኑ “እግዚአብሔር” ሲሉት እንመለከታቸዋለን፡፡

5.1.2.3.4. <u>ከሦስቱ የአንዱን አገልግሎቱ ተመልክተው “መልከፄዲቅ” እንዳሉት</u>

ከላይ የተመለከትነው ይህንን በሰው መልክ ነገር ግን በሰማያዊ ማንነት እየመጣ እንደ እግዚአብሔር የሚናገረውን አካል ሰዎች በተለያየ ስም ይግለፁት እንጂ ትክክለኛ ስሙ በወቅቱ አልታወቃቸውም ነበረ፣ ከቅዱሳኑ ደፈር የሚለው ያዕቆብ ስሙ ማን እንደሆነ ጠይቆት ነበረ፡-

> ዘፍ.32፡29 “ያዕቆብም፣ ስምህን ንገረኝ ብሎ ጠየቀው፣ እርሱም ስሜን ለምን ትጠይቃለህ? አለው በዚያም ስፍራ ባረከው፡፡”

በርግጥ በዚያን ስፍራ ስሙን ሊነግረው አልፈለገም ምክንያቱም ቢነግረው ያዕቆብ የባሰ ብዙ ጥያቄዎች ይፈጠርበትና እንደ ሐዋርያት ቤተክርስቲያን የ “አንድ አምላክ ኢየሱስ ብቻ” አስተምህሮን ይጀምር ነበረ፣ አንዳንዶቹ በወቅቱ ይህን ሰማያዊ ማንነት ስሙን ባይገልፅም በአገልግሎቱ ስሙ “መልከፄዲቅ” ብለው መጥራቱን መርጠዋል፣

> ዘፍ.14፡18-20 “የሳሌም ንጉሥ መልከፄዲቅም እንጀራንና የወይን ጠጅ አወጣ፣ እርሱም የልዑል እግዚአብሔር ካህን ነበረ፣ ባረከውም፣ አብራም ሰማይንና ምድርን ለሚገዛ ለልዑል እግዚአብሔር የተባረከ ነው፣ ጠላቶችህን በእጅህ የጣለልህ ልዑል እግዚአብሔርም የተባረከ ነው አለውም፣ አብራምም ከሁሉ አስራትን ሰጠው፡፡”

አብርሃም ለመልከፄዲቅ አስራት ሰጠው፣ “አስራት” የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፣ አብርሃምም አልተሳሳተም ምክንያቱም በሰው <u>መልክ</u> የተገለጠው አምላክ፣ መልከፄዲቅ፣ ከሥላሴ አንዱ የሆነው ኢየሱስ ነበረና፣

ዕብ.7፡1-3 “የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከዔዲቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፣ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አስራትን አካፈለው … (እርሱ) በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል፡፡”

“የዘላለም ካህን” የሚባለው፣ በእግዚአብሔር ልጅ የሚመሰለውና ለዘመኑ ቁጥር የሌለው ኢየሱስ መሆኑን በአዲስ ኪዳን እውቀታችን እናውቃለን፣ በወቅቱ ቅዱሳኑ ስሙን መግለፅ ባይችሉም በአገልግሎቱ “መልከዔዲቅ” ብለውት ነበረ፡፡

5.1.2.3.5. በጊዜ ሂደት የሥላሴ ማንነት ግልፅ እየሆነ መምጣት

በጊዜ ሂደት ውስጥ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ራሱን እየገለጠ ሲመጣ ሰዎች ስለ ሥላሴ የተሻለ መረዳት ሲይዙ ነበረ፣ በዚህም የኋለኞቹ ነብያት፣ የሥላሴን ማንነት ከላይ ካየናቸው ቅዱሳን በተሻለ መንገድ ገልፀውታል፡፡

- **ኢሳያስ**
  - ኢሳ.42፡1 “(እግዚአብሔርም) እነሆ ደግፌ የያዝሁት ባሪያዬ፣ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ፣ እርሱም ለአህዛብ ፍርድን ያወጣል፡፡”
  - ኢሳ.48፡12-16 “… እኔ ፊተኛውም ነኝ ኋለኛውም ነኝ፡፡ እጄም ምድርን መስርታለች … ቀኜም ሰማያትን ዘርግታለች … እኔ ከጥንት ጀምሮ በስውር አልተናገርኩም … አሁንም ጌታ እግዚአብሔርና መንፈሱ ልከውኛል፡፡”
  - ኢሳ.59፡15-21 “እግዚአብሔርም አየ … ወደ እርሱ የሚማልድ እንደሌለ ተረዳ ተደነቀም፣ ስለዚህ የገዛ ክንዱ መድኃኒት አመጣለት … በአንተ ላይ ያለው መንፈሴ…”

እነዚህ በየጥቅሱ ውስጥ የተመለከቱት ሦስቱ ማንነቶች በአዲስ ኪዳኑ “አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ” የተባለውን የሥላሴ ማንነት በብዥታም ቢሆን ማመልከት ችለዋል፡፡

- **ዳንኤል**

ዳንኤልም የተመለከተውም ራዕይ ተመሳሳይ ነው፣

- ዳን.2፡34-35 “እጅም ሳይነካው ድንጋይ ከተራራው ተፈንቅሎ ከብረትና ከሸክላ የሆነውን የምስሉን እግሮች ሲመታና ሲፈጭ አየሁ … ምስሉን የመታ ድንጋይ ታላቅ ተራራ ሆነ ምድርንም ፈፅሞ ሞላ፡፡”
- ዳን.2፡44 “… እነዚያንም መንግሥታት ሁሉ ትፈጫቸዋለች ታጠፋቸውማለች ለዘላላምም ትቆማለች፡፡”
- ዳን.4፡17 “ልዑሉ በሰዎች መንግሥት ላይ እንዲሰለጥን …”

እዚህ ጋር ዳንኤል አንድ ተራራን በራዕይ ተመለከት፣ የተመለከተውን ራዕይ ስናስተውል “ተራራው ተነቅሎ” አይደለም፣ የተራራው አንድ ከፍል የነበረ ድንጋይ ተፈንቅሎ ነው የወጣው፣ ወጥቶ ደግሞ ነገሥታትን ፈጨ፣ ከዚያም ነገሥታቱን ፈጭቶ እስከ ዘላለም ነገሠ፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ኢየሱስ ብዙ ስፍራዎች ላይ በዓለት/በድንጋይ ተመስሏል (ሉቃ.20፡17, ሮሜ.9፡32-33, ኤፌ.2፡20, 1ቆሮ.10፡4, 1ጴጥ.2፡4, 1ጴጥ.2፡6-7 ...)፣ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን በአርማጌዶን ጦርነት የዓለም መንግሥታትን በማሸነፍ የራሱን መንግሥት እንደሚመሠርት መጽሐፍ ቅዱሱ ይናገራል(ማቴ.21፡42-44, ራዕ.11፡15-18, ራዕ.19፡15-21 ...)፣ በዚህም ነገሥታትን ፈጭቶ የሚነግሠው፣ ከተራራው ላይ የተፈነቀለው ድንጋይ/ዓለት፣ ኢየሱስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

5.1.2.3.6. <u>የሥላሴ እውቀት በአዲስ ኪዳኑ በተሻለ መንገድ ግልፅ መሆኑ</u>

"ሥላሴ" የሚለው ቃል የተፈጠረው መጽሐፍ ቅዱሱ ከተፃፈ በኋላ በኒቂያ ጉባዔ 325 ዓ.ም ነው፣ ቃሉም የተፈጠረው <u>አንዱ</u> እግዚአብሔር <u>በሦስት ማንነቶቹ</u> "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ" ተገልፆ የሚሰራበትን <u>አሰራርን</u> ለመግለፅ በሚል ነው፣ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? የሚለውን በቀጣዩ 5.1.2.3.7 ክፍል የምንመለከት ቢሆንም ሦስቱም የእግዚአብሔር ማንነቶች በሥላሴነት ሲሰሩ እንደነበረ ግን መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ በግልፅ ተመልክቷል፡-

- ማቴ.3፡16-17 "<u>ኢየሱስም</u> ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሀ ወጣ፤ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ <u>የእግዚአብሔርም መንፈስ</u> እንደ ርግብ ሲወርድ በርሱ ላይም ሲመጣ አየ፤ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ፣ <u>በእርሱ ደስ የሚለኝ</u> የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ፡፡"
- ማቴ.28፡192-20 "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ <u>በአብ</u>፣ <u>በወልድና</u> <u>በመንፈስ ቅዱስ</u> ስም እያጠመቃችኋቸው ..."
- ዮሐ.14፡15-17 "ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ፡፡ <u>እኔም</u> <u>አብን</u> እለምናለሁ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አፅናኝ ይሰጣችኋል፡፡ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ስለሆነ ሊቀበለው የማይቻለው <u>የእውነት መንፈስ</u> ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ስለሚኖር በውስጣችሁም ስለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ፡፡"
- ዮሐ.14፡26 "(ኢየሱስም) <u>አብ</u> <u>በስሜ</u> የሚልከው ግን <u>መንፈስ ቅዱስ</u> የሆነው አፅናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችሃል ..."
- ሐስ.2፡32-33 "ይህን <u>ኢየሱስን</u> <u>እግዚአብሔር አስነሳው</u> ... ስለዚህ <u>በእግዚአብሔር</u> ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና <u>የመንፈስ ቅዱስን</u> የተስፋ ቃል <u>ከአብ</u> ተቀብሎ ይህን እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው፡፡"
- ሐስ.10፡38 "<u>እግዚአብሔር</u> የናዝሬቱን <u>ኢየሱስን</u> <u>በመንፈስ ቅዱስ</u> በኃይል ቀባው ..."
- ዮሐ.15፡26 "ዳሩ ግን <u>እኔ ከአብ</u> ዘንድ የምልክላችሁ <u>አጽናኝ</u> እርሱም ከአብ የሚወጣ <u>የእውነት መንፈስ</u> በመጣ ጊዜ፣ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፡፡"
- 2ቆሮ.13፡14 "የጌታ <u>የኢየሱስ ክርስቶስ</u> ጸጋ <u>የእግዚአብሔርም</u> ፍቅር <u>የመንፈስ ቅዱስም</u> ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን፡፡ አሜን፡፡"

- ነጴጥ.፲፡1-2 “... እግዚአብሔር አብ አስቀድሞ እንዳወቃቸው፣ በመንፈስም እንደሚቀደሱ፣ ይታዘዙና በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይረጩ ዘንድ ...”

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱሱ ቃላት የሥላሴን አሰራር ለሚቃወሙት ከባድ ፈተና ናቸው፡፡

5.1.2.3.7. ሥላሴነት በተፈጥሮ ውስጥ መመልከቱ

ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔር የሥላሴ ማንነት እንግዳ ይሆንባቸዋል ነገር ግን ይህ አሰራር እንግዳ ሳይሆን በተፈጥሮ እንኳን የተለመደ አሰራር ነው፣ ይህንን አሰራር ለመመልከት ለምሳሌ ያህል በሰውና በፀሐይ ውስጥ ያለውን ሥላሴነት እንመልከት፡-

- **የሰው ልጅ ሥላሴነት**

እግዚአብሔር የሰው ልጅን ሲፈጥር “በመልካችን” እንዳለው በመልኩ የሰውን መንፈስ ፈጠረ(ዘፍ.፩፡27)፣ “እንደ ምሳሌአችን” እንዳለውም ደግሞ ሰው ሥላሴነት እንዲኖረው ለተፈጠረው መንፈሳዊ አካል ስጋ አበጀለት(ዘፍ.2፡7) ከዚያ በውስጡ ነፍስን አኖረ(ዘፍ.፩፡27)፣ በዚህም ሰው በሥላሴ ምሳሌ ስጋ፣ ነፍስና መንፈስ ሆነ፡፡

ይህ እውነታ በአዲስ ኪዳኑም ተመልክቷል፡-

ነተሰ.5፡23 “የሠላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈፅመው ይጠበቁ፡፡”

እዚህ ጋር እንዴት አንዱ ሰው ውስጥ ሦስት ማንነት(ሥላሴነት) እንደሚገኝ እንመለከታለን፣ ይህም እውነታ፣ የእግዚአብሔርን ሥላሴነት ለመረዳት በመጀመርያ በእጃችን ያለውን ሥላሴነት እንድናስተውል ያግዘናል፡፡

- **የፀሐይ ሥላሴነት**

ፀሐይም ላይ በአንድነት ውስጥ ሦስትነትን እንመለከታለን፣ እነሱም በሰማዩ ላይ ያለችው ክብ ሆና የምትታየን አካል፣ ወደ ምድር ወርደው የሚሰሩት ብርሃንና ኃይል ናቸው፣ ሦስቱም አንድ ሆነው ነገር ግን በሦስት “የተለያዩ መንገዶች የተለያዩ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ ሰማዩ ላይ ያለቸው ፀሐይ እንደ ንግሥት በአከባቢው ያሉትን የተለያዩ ኃይላትን(የግራቪቲን፣ የሴነተሪፉጋል፣ የሴንትሪፔታል ...) አሸንፋ ምህዋርዋን አስጠብቃ በአካባቢው ነግሣ ትኖራለች፡፡

ብርሃንዋ ደግሞ እንደ ኢየሱስ በሚታይ መንገድ ለዓለም ያበራል፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ኢየሱስን የዓለም ብርሃን ይለዋል(የሐ.፩፡8-9, ዮሐ.8፡12...)፣ ኃይልዋ ደግሞ እንደ መንፈስ ቅዱስ በማይታይ መንገድ የህያዋንን የኃይል ምንጭ ሆኖ ህይወትን ተሸክሞ ይኖራል፣ በምድር ላይ ያለው ህይወታዊ ተንቀሳቃሽ ሁሉ በፀሐይ ኃይል ላይ እንደተመረኮዘው ሁሉ ህይወትም በእግዚአብሔር መንፈስ ላይ እንደተመረኮዘ መጽሐፍ ቅዱሱ “መንፈስህን

ብትወስድ ፍጥረት ሁሉ በጠፋ ነበረ" (ኢዮ.34፡14-15) ይላል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የፀሐይ ብርሃንና የፀሐይ ኃይል ከፀሐይ ወጥተው ወደ ምድር መጥተው ስራ እንደሚሰሩት ሁሉ ከእግዚአብሔር ሥላሴ ማንነት ውስጥም ኢየሱስ(ዮሐ.13፡3, ዮሐ.16፡27-28, ዮሐ.17፡8, ዮሐ.8፡42 ...) እና መንፈስ ቅዱስ(ዮሐ.15፡26, ዮሐ.14፡16, ሐስ.2፡3-4 ...) ወደ ምድር የወረዱት ከአብ ወጥተው ነው፡፡

በዚህ የፀሐይ ተፈጥሮ ውስጥ አንዱ እንዴት በሦስት ማንነት (ሥላሴነት) እንደሚሰራ በተሻለ መንገድ እንመለከታለን፡፡

የፀሐይን ሦስትነት መለየት የምንችለው በሦስቱም የተለያያ ሦስት <u>ምግባር</u> ነው፣ ግን ተመልሰው ሦስቱም አንድ ናቸው፣ ፈጣሪም ጋር ተመሳሳይ ነገርን ነው የምንመለከተው፣ አንድ ፈጣሪና ሦስት የተለያየ ምግባር፣ አንድ እግዚአብሔርና ሦስት አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ፡፡

የሥላሴነት አሰራር የሰው ልጅንና ጸሐይን በምሳሌነት አንስተን ተመልክተናል፣ የሰው ልጅና የፀሐይ ሥላሴ ተፈጥሮን በአንድ ላይ አጣምረን መመልከት ስንችል ደግሞ በእግዚአብሔር ውስጥ ያለውን ሥላሴነት በተሻለ መንገድ እንረዳለን፡፡ እነኚህ ሁለቱ የሰውና የፀሐይ ሥላሴነት ተፈጥሮና አሰራር የሥላሴ አሰራር እንዲገባን ለምሳሌ ይቀረቡ እንጂ በሁሉም ስፍራ የሚገኘውን፣ "በማን ትመስሉታላችሁ? በምን ምሳሌ ታስተያዩታላችሁ?" የሚለው እግዚአብሔር ትክክለኛ መግለጫዎች አይደሉም፣ እግዚአብሔርን በራዕይ ያዩትም እነ ዮሐንስ፣ ዳንኤል ... ያዩትን በሰው ቋንቋ መግለፅ አቅቶአቸው "እንደ"፣ "ይመስላል" ... እንዳሉት አሁንም በ"እንደ" እና "ይመስላል" ብቻ በመውሰድ ነገር ግን በዚህ እውነታ ውስጥ አንዱ በሦስት ማንነት የሚሰራበትን እውነታ መመልከት ይቻላል፡፡

<u>ማጠቃለያ (ሐዋርያት)</u>

በሥላሴ ጉዳይ፣ ከላይ በተመለከትናቸው እውነታዎች፣ በአደናጋሪዎች ከመደናገር የሚጠብቀንን እውቀት አግኝተናል እንደዚሁ ደግሞ የእግዚአብሔር ማንነት ሙሉ በሙሉ መግለፅ እንደማይቻልም ተመልክተናል፡፡

የፈጣሪን ማንነት ሙሉ በሙሉ መግለፅ የማይቻለውም በምክንያት ነው፣ ጀበናን ጀበና እንደማይሰራው ሁሉ፣ ፈጣሪ ሰውን የፈጠረው ከሰው ማንነት የላቀ በመሆኑ ምክንያት ነው፣ በዚህም በማንነት ልዩነት ብቻ ተፈጣሪ የሆነው ሰው ፈጣሪውን አምላክ ሙሉ በሙሉ ሊገልፀው አይችልም፡፡ ተፈጣሪ የሆነው የሰው ልጅ ፈጣሪን መጾ በመጾ መግለፅ ከቻለ ይህ በሰው ሙሉ በሙሉ የተገለፀው አካል የሰው ፈጣሪ ሊሆን አይችልም፣ ይህ ተፈጥሯዊ እውነታ፡፡

ፈጣሪ እንደ ሰው ስጋና ደም የሌለው መሆኑ(ሉቃ.24፡39) እና በአንድ ጊዜ በሁሉም ስፍራ (መዝ.139፡7-8) የሚገኝ መሆኑ ፈጣሪን፣ ቁሳዊ ነገሮች በሚገለፁበት መንገድ

“አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት …” እያልን እየቆጠርን ልንገልፀው አንችልም፡፡ በዚህም የቱንም ያህል ብንመራመር ፈጣሪ በፍጥረቱ በሰው ሙሉ በሙሉ ሊታወቅ አይችልም፣ ይህ በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል ያለ ተፈጥሮአዊ ልዩነት ነው፣ ፈጣሪ ይቅርና ስለራሳችን ሥላሴ ተፈጥሮ(ሲጋ፣ ነፍስና መንፈስ) ያለን እውቀት እንኳን ውሱን ነው፡፡

ይህ የሰው ልጅ የእውቀት ክፍተት ግን ለሐዋርያት ቤተክርስቲያን መስፋፋት የመሠረተ ድንጋይ ነው፣ የቤተክርስቲያኗ ሰባኪዎች ለአንድ ክርስቲያን ኃይማኖታቸውን ሲሰብኩ በመጀመሪያ “በአዲስ ኪዳን ዘመን ጥምቀት ለምን በኢየሱስ ስም ብቻ ተፈፀመ?” በሚለው ጥያቄ ቀድመው ያደናብራሉ፣ ከዚያም የራሳቸውን መልስ፣ “ይህ የሆነው አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ በመሆኑ ነው” በማለት የክርስትና መሠረት የሌለውን ሰው በቀላሉ በመማረክ ወደ ኃይማኖታቸው ይቀላቅላሉ፡፡

ይህንን ከባድ ጥያቄ ተገን በማድረግ መሠረታዊ እውቀት የሌለውን ክርስቲያን በራሳቸው መንገድ ይዘው ይሂዱ እንጂ፣ ይህ “አንድ አምላክ - ኢየሱስ ብቻ” አስተምህሮ ከላይ እንደተመለከትነው ስህተት በመሆኑ እያደር ሌሎች መቶ ጥያቄዎችን ይዞ ይመጣል፡፡ ይህም ሰይጣን ሄዋንን፣ እራሱ አደናባሪ ጥያቄ ጠይቆአት የራሱን ትንታኔ በመስጠት ከነበረችበት ገነት እንድትወጣ አድርጎ ከዚያ ከሌሎች ብዙ ተከታይ ጥያቄዎች ውስጥ የከተተበትን አጋጣሚ ይመስላል፡፡

ሌላው ከነ ሄዋን ታሪክ ጋር የሚመሳሰልበት ደግሞ ሰይጣን በገነት ውስጥ ያሉትን አዳምና ሄዋንን ታርጌት እንዳደረገው የቤተክርስቲያኗ ታርጌትም ክርስቲያኖች ናቸው፣ የሚገርመው ደግሞ አዳምና ሄዋን በመሳሳታቸው ከገነት ከተባረሩ በኋላ ወደ ገነት መመለስ እንዳይችሉ እንደተደረገው፣ እነዚህ ከክርስትናው የወጡት ሰዎችም ወደ ክርስትናው መመለስ ሲያዳግታቸው እንመለከታለን ምክንያቱም ከላይ እንደተመለከትነው አስተምህሯቸው የእግዚአብሔር መንፈስ ላይ በመናገር የማይሰረይ ኃጢያት ውስጥ የሚያስገባ በመሆኑ፣ አዳም ወደ ኤደን ገነት እንዳይመለስ እግዚአብሔር መንገዱን እንደ ዘጋው የነዚህ ሰዎች መንገድም የተዘጋ ይመስላል፡፡

በዚህም ማንኛውም ሰው ከዚህ አሳሳች አስተምህሮ ራሱንና ሌሎችንም ሊጠብቅ ይገባል፣ ከላይ በ5.1.2.2.3 ክፍል እንደተመለከትነውም ዮሐንስ ይህንን አይነት አስተምህሮ የሚከተሉትን “በቤታችሁ አትቀበሉት ሠላምም አትበሉት ሠላም የሚለው ሰው በክፉ ስራው ይካፈላልና፡፡” በሚል ከባድ መልዕክት የተናገረው መንገዱ መሄጃው እንጂ መመለሻ የሌለው በመሆኑ ምክንያት ነው፡፡

5.2. የይሖዋ ምስክሮች (Jhova Witness)

[139] "የይሖዋ ምስክሮች ቤተክርስቲያን በ1870 ዓ.ም በአሜሪካዊ ፒትስበርግ ቼንስልቫኒያ ተመሠረተች፣ የምሥረታዋ መነሻም የመስራቹ የቻርለስ ታዝ ራስልና ጓደኞቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድን ከብዙ ጥናት በኋላ "ነባሩ የክርስትና አካሄድ የተሳሳተ ነው" የሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሳቸው ነው።።

ይህንንም ድምዳሜያቸውንም በመጀመርያ በ"Herald of the Morning" በሚባል ጋዜጣ ከዚያም "Zion`s Watch Tower and Herald of Christ`s Presence" በሚባል መፅሄት በማሳተም ሰዎችን በመስበክ፣ በተለያዩ ስፍራዎችም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ማኅበሮችን በማቋቋም፣ ከዚያም በይፋ ቤተክርስቲያኗን መሠረቱ፤ ቤተክርስቲያኗ በአሁኑ ወቅት በዓለም ላይ 8.45 ሚሊየን በላይ ተከታዮች አሏት።።"

ቤተክርስቲያኗ እንደዚህ በቀላሉ ትመሥረት እንጂ ከተመሠረተችበት ጊዜ ጀምሮ ብዙ ፈታኝ ችግሮች አጋጥሟታል፣ ከነዚህም ውስጥ ዋነኛው ችግር በቤተክርስቲያኗ ነብያት የተተነበዩት ትንቢቶች በተደጋጋሚና በአስደንጋጭ ሁኔታ አለመፈፀማቸው ነው፣ [140] ዋና ዋናዎቹን ብንመለከት፡-

1. "የጌታ ምፅአት **በ1874 ዓ.ም** ነው።።" (Creation, Brooklyn: watch tower bible and tract society, 1927, 289)
2. "በመጪዎቹ 26 አመታት ውስጥ አሁን ያሉት መንግሥታት እየሚሙ ያልቃሉ ... የእግዚአብሔር መንግሥት **በ1914 ዓ.ም** መጨረሻ ላይ ሙሉ በሙሉ ይመሠረታል።።" (Studies in scriptures, Vol. 2 , Brooklyn: watch tower Bible and tract society, 1888, 98-99)
3. "ታማኝ እስራኤላውያን **በ1925 ዓ.ም** ትንሳኤ ያገኛሉ ... ከሙታንም እንደተነሱ ምልክት የሚያደርጉበት ጊዜ ነው።።" (Millions now living will Nevere Die, Brooklyn: Watch tower Bible and tract Society, 1920, 88-90)
4. በራዕ.7፡1-8 ላይ የተገለፀው የ144,000 ሰዎች ጉዳይ አስመልክቶ ቁጥሩ መች እንደሚሞላ የተተነበዩ ትንቢቶች፣
   - በ1881 ዓ.ም፣ የቤተክርስቲያኗ መስራች ቻርለስ ታዝ ራስል (The kingdome come, p. 362)፣
   - በ1931 ዓ.ም፣ ጆርጅ ፍራንክሊን ራዘር ፎርድ (Let God be true, 1946, p. 298)፣
   - በ1935 ዓ.ም፣ ናታን ሆመር ኖር (watchtower 2007,may 1, p.30)

[139] https://en.m.Wikipedia>wiki>Jehovah`s witnesses

[140] ዶክተር ተስፋዬ ሮበሌ(2016)፣ **አርዮሳውያን "የይሖዋ ምስክሮች" አስተምህሮ በቃለ እግዚአብሔር ሲመዘን**፣ ገፅ 131, 155-160

5. “**በ1975 ዓ.ም** የሰው ልጆች የ6,000 አመታት ኑሮ ያበቃል።” (Awake, 8 october, 1894, 1675)

በነዚህ ባልተሳኩ ትንቢቶች ምክንያት ቤተክርስቲያኗ ብዙ ምዕመናኖችን አጥታ ብዙ ችግሮችም ተፈጥሮባት ነበረ፣ በዚህም ሰበብ ቤተክርስቲያኗ አስተምህሮዎችዋን በየጊዜው ስትቀያየር ቆይታ በመጨረሻም በቤተክርስቲያኗ ምንም አይነት ትንቢት እንዳይነገር እስከማገድ ደረሰች።

ቤተክርስቲያኗ ከሌሎች ቤተክርስቲያናት የምትለይበት ብዙ አስተምህሮዎች አሏት፣ “ፈጣሪን ከትክክለኛ ስሙ “ይሖዋ/ጀሆቫ” ውጪ ልንጠራው አይገባም፣ የሥላሴ ትምህርት ስህተት ነው፣ ዓለም ለዘላለም ናት፣ ገነት ምድር ናት፣ ሰው ከሞተ በኋላ በህይወት የምትቀጥል ነፍስ/መንፈስ የሚባል ነገር የለም፣ ሲኦል የሚባል ዘላለማዊ የስቃይ ስፍራ የለም፣ ኢየሱስ ሚካኤል ነው፣ ኢየሱስ “ክርስቶስ” የሆነው ሲጠመቅ ነው የነገሠውም በ1914 ዓ.ም ነው፣ ክርስቶስ የተሰቀለው በአንድ እንጨት መስቀል ላይ እንጂ “ † ” ተደርጎ በተሰራ የመስቀል እንጨት አይደለም፣ የሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ፣ ደም መለገስና መውሰድን ኃጢያት ነው፣ በውትድርናና በፖለቲካ መሳተፍ (የፓርቲ አባልነት፣ ለምርጫ መወዳደርና ድምፅ መስጠት ...) ኃጢያት ነው፣ የሰንደቃላማ መዝሙር ላይ መሳተፍ ኃጢያት ነው” የመሳሰሉት ናቸው።

ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹን፦

- “አምላክን ይሖዋ/ጀሆቫ ከሚለው ስም ውጪ ልንጠራው አይገባም”
- “የሥላሴ አስተምህሮ ስህተት ነው”፣
- “የሰው ልጅ ከሞተ በኋላ በህይወት የምትቀጥል ነፍስና መንፈስ የሚባል ማንነት የለውም”፣
- የመጨረሻ ዘመን (“1914 ዓ.ም ኢየሱስ የነገሠበት አመት ነው፣ በሺሁ አመት 144,000 የጀሆቫ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ይፈርዳሉ፣ የሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ፣ ገነት ምድር ናት፣ “ነፍስ ለዘላለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ስፍራ የለም”)፣

የሚሉትንና ለነዚህ አስተምህሮዎች ድጋፍ እንዲሆን የተዘጋጀውን የቤተክርስቲያኗን “የአዲሱ ዓለም መጽሐፍ ቅዱስ” ይዘት እንመለከታለን።

5.2.1. “አምላክን ይሖዋ/ጂሆቫ ከሚለው ስም ውጪ ልንጠራው አይገባም”

የጂሆቫ ቤተክርስቲያን “ትክክለኛው የፈጣሪ ስም “ይሖዋ/ጂሆቫ” ነው፣ ከዚህ ስም ውጪ ልንጠራው አይገባም፣ ከዚህ ስም ውጪ ብንጠራው አይሰማን ...” በማለት ታስተምራለች፣ “የአዲስ ዓለም ትርጉም” በማለት ባሳተመችው መጽሐፍ ቅዱሷም “እግዚአብሔር፣ አምላክ ...” የሚሉትን ቃላት “ይሖዋ/ጂሆቫ” በሚለው ቃል ቀይራለች፡፡

ቤተክርስቲያኗ ይህንን ሐሳብ ያነሳችው መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ተንተርሳ ሳይሆን “ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጀርባ ያለውን ታሪክ አጥንተን ነው” የምትለው፣ ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያኗ “መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ የጨመረ፣ ከዚህ ካስተማርናቸው ውጪ ያስተማረ ...” የሚሉትን ትዕዛዞች ተላልፋ አዲስ ሐሳብ መጨመሯ ኃጢያት የመሆኑ ነገር እንዳለ ሆኖ የቀረበውን ሐሳብ አጥርቶ ማለፍ አስፈላጊ በመሆኑ የፈጣሪን ስም ጉዳይ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

ከመነሻው ፈጣሪ በተለያዩ ስሞች ሲጠራ እንደነበረ መጽሐፉ ላይ እንመለከታለን፣ “ኤልሮኢ”(ዘፍ.16፡13)፣ ኤሎሄ(ማቴ.27፡46)፣ የሴም አምላክ(ዘፍ.9፡26)፣ የሰማይ አምላክ(ዘፍ.24፡7) ... እግዚአብሔርም በራሱ ስሙን ሲናገር ለሰዎች በሚገባ መልክ ነበረ ሲናገር የነበረው “ኤልሻዳይ”(ዘፍ.17፡1)፣ “የቤቴል አምላክ”(ዘፍ.31፡13)፣ የአብርሃም የይስሐቅ የያዕቆብ አምላክ ... ሲል ነበረ፣ እኛ ኢትዮጵያውያንም በገባን መንገድ “ሁሉን የፈጠረ፣ ሁሉን የሚገዛ ...” ለማለት “እግዚአብሔር” እንለዋለን፣ ኢየሱስ ደግሞ “አባቴ፣ አባት፣ አባ ...” ሲል ነበረ፣ አማኞችም በዚሁ መልክ እንዲጠሩት “አባታችሁ” እያለ ሲያስተምር ነበረ፣ እነዚህን እውነታዎች በአንድ ላይ ስንመለከት ልክ ህፃናት አባታቸውን በተለያየ ስም እንደሚጠሩት ሰዎችም ይህንን አምላክ በተለያየ ስም ሲጠሩት እንደነበረና እሱም በራሱ ስሙን ለሰዎች በሚገባ ስም ሲያስለዋውቅ ነበረ፡፡ በዚህም “ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጀርባ” ተደረገ የተባለው ጥናት ትርጉም የሌለውና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነታ ያላገናዘበ አባባል መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በተመሳሳይ መልኩም ቤተክርስቲያኗም በራሷ የምትጠቀመው አንድ ወጥ ስም ሳይሆን በተለያዩ ቋንቋዎች ይሖዋ፣ ጂሆቫ ... እያለች መጥራትዋ “ከትክክለኛ ስሙ ውጪ ልንጠቀም አይገባም፣ በትክክለኛ ስሙ ካልጠራነው አይሰማንም” የሚለው አስተምህሮዋን ትርጉም አልባ ያደርገዋል፡፡

5.2.2. “የሥላሴ አስተምህሮ ስህተት ነው”

የጂሆቫ ቤተክርስቲያን የሥላሴን አስተምህሮን ትቃወማለች፣ ለዚህም ዋነኛ ምክንያትዋ ከላይ ሐዋርያቶች ጋር እንደተመለከትነው “እግዚአብሔር አምላክ አንድ ነው” ከሚለው መነሻ ነው ነገር ግን የጂሆቫ ቤተክርስቲያን ከሐዋርያት ቤተክርስቲያን በተለየ መጽሐፍ ቅዱሱ “አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ” የሚለው ውስጥ፣ አብን በቀጥታ እግዚአብሔር በማድረግ ሌሎቹን የእግዚአብሔር የሥላሴ ማንነቶችን ወልድንና መንፈስ

ቅዱስን ደግሞ አምላካዊ ማንነት በመከልከል፣ ወልድ የተባለው ኢየሱስ "መልአኩ ሚካኤል ነው" በማለት መንፈስ ቅዱስን ደግሞ እንደ ሐዋርያቱ "ሰብአዊ ማንነት የሌለው የእግዚአብሔር ኃይል ነው" ትላለች፣ ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

5.2.2.1. <u>ኢየሱስ</u>

ቤተክርስቲያኗ የአብ ወልድና መንፈስ ቅዱስን "የሥላሴን አስተምህሮ" በመቃወም፣ ለአብ የፈጣሪን ስፍራ በመስጠትና "ኢየሱስ እግዚአብሔር አምላክ አይደለም" በማለት ኢየሱስን ከፈጣሪ ስፍራ አንስታው የሚካኤል ቦታ ላይ አስቀምጣዋለች ይሁን እንጂ ኢየሱስን ከአምላክነት ስፍራ ማንሳቱም ሆነ በሚካኤል ቦታ ላይ ማስቀመጡ ቀላል ስራ አልሆነላትም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

5.2.2.1.1. <u>"ኢየሱስ እግዚአብሔር አምላክ አይደለም"</u>

የጂሆቫ ቤተክርስቲያን የሥላሴን አስተምህሮ በመቃወም የሥላሴ አንዱ አካል የሆነውን ኢየሱስን ከእግዚአብሔር አምላክነት አውርዳዋለች፣

> [141] "ኢየሱስ በተጠመቀበት ዕለት የአምላክ መንፈስ ወይም ኃይል በላዩ ሲወርድበት መሪና ንጉሥ እንዲሆን ተሾመ መሲህ ወይም ክርስቶስ ሆነ … ኢየሱስ እጅግ ተወዳጅ የሆነ የይሖዋ ልጅ ነው፤ ይህም የሆነበት በቂ ምክንያት አለ፡፡ ከአምላክ የፍጥረት ስራዎች የመጀመርያ በመሆኑ "ከፍጥረታት ሁሉ በፊት በኩር" ተብሎ ተጠርቷል፡፡ ይህ ልጅ ልዩ የሚያደርገው ሌላም ነገር አለ "አንድያ ልጅ ነው" ይህም በአምላክ በቀጥታ የተፈጠረው ኢየሱስ ብቻ እንደሆነ የሚያመለክት ነው … ስለዚህ ኢየሱስ መጀመርያ አለው ማለት ነው፤ ይሖዋ አምላክ ግን መጀመርያም ሆነ መጨረሻ የለውም፡፡"

ቤተክርስቲያኗ ለዚህ አስተምህሮ እንዲያመቻት መጽሐፍ ቅዱሱንም "እስከማስተካከል" ሄዳለች፣ ለምሳሌ ያህል ዮሐ.፩፡1-3 ላይ የተደረገውን ለውጥ ብንመለከት፣

<u>በዋናው መጽሐፍ ቅዱስ</u>

> "በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ <u>ቃልም እግዚአብሔር ነበረ</u>፡፡ ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡፡ <u>ሁሉ በእርሱ ሆነ</u> ከሆነው አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም፡፡"

[141] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 41-42

<u>በጂሆቫ መጽሐፍ ቅዱስ</u>

"በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ ቃልም ከአምላክ <u>ጋር</u> ነበረ፣ ቃልም <u>አምላክ</u> ነበረ። እሱም በመጀመሪያ ከአምላክ ጋር ነበረ። ሁሉም ነገሮች ወደ ህልውና የመጡት በእሱ <u>በኩል</u> ነው፣ ያለ እሱ ወደ ህልውና የመጣ አንድም ነገር የለም።"

እነዚህ ከስር የተሰመሩባቸው "ጋር"፣ "በኩል" እና "አምላክ" የሚሉት ቃላት የገቡበት ተልዕኮ አላቸው፣ ይህም "ኢየሱስ እግዚአብሔር አይደለም" ለማለት እንዲያመች ነው፣ ለቅንብሩ አማርኛው ባይመቻቸውም በእግሊዘኛው መጽሐፍ ቅዱሳቸው ላይ ቅንብሩ በግልፅ ተመልክቷል፣

"Joh.1:1 "In the beginning was the word, and the word was with <u>God</u>, and the word was <u>a god</u>."

እዚህ ጋር "God" የሚለው ዋናው አምላክ ሲሆን "ኢየሱስ ዋናው አምላክ አይደለም" ለማለት ደግሞ ኢየሱስን "a god" በሚለው አነስተኛ አማልክት በሚጠሩበት ስም ጠርተውታል፣ ይህም ኢየሱስ አምላክ ቢሆንም "ዋናው አምላክ አይደለም" በሚለው ለመፍታት እንዲያመቻቸው ነው።

ይሁን እንጂ ኢየሱስ ሲወለድም ክርስቶስና ንጉሥ እንደነበረ፣ ተፈጣሪም ሳይሆን ፈጣሪ መሆኑን፣ መጀመርያ የሌለው መሆኑንና ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ መሆኑን የሚያሳዩ ብዙ ማስረጃዎችን መመልከት ይቻላል፣

- **<u>ኢየሱስ ሳይጠመቅ በፊትም ክርስቶስ መሆኑ፣</u>**
  - ሉቃ.2፡11 "ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም <u>ክርስቶስ</u> ጌታ የሆነው ተወልዶላችኋልና።"
  - ማቴ.2፡4 "የካህናትንም አለቆች የህዝቡንም ፃፎች ሁሉ ሰብስቦ <u>ክርስቶስ</u> ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው።"
  - ሮሜ.9፡5 "... ከእነርሱም(ከእስራኤላውያን) <u>ክርስቶስ በስጋ መጣ</u>..."
  - ፩ዮሐ.2፡22 "ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን የሚክድ በቀር <u>ውሸተኛ</u> ማነው?"
- **<u>ኢየሱስ ሳይጠመቅ በፊትም ንጉሥ መሆኑ፣</u>**
  - ማቴ.2፡1-2 "... የተወለደው የአይሁድ ንጉሥ ወዴት ነው?"
  - ዕብ.7፡1-4 "የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን ... የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የፅድቅ ንጉሥ፣ ኋላ ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሠላም ንጉሥ ነው፣ አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም፣ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍፃሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።"

- **<u>ኢየሱስ ፈጣሪ መሆኑ፣</u>**
  - ዮሐ.1፡1-3 “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፣ <u>ቃልም እግዚአብሔር ነበረ</u>። ይህ በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ። <u>ሁሉ በእርሱ ሆነ</u> ከሆነው አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም።
  - ቆላ.1፡15-17 “እርሱ የማይታይ አምላክ ምሳሌ ነው፤ የሚታዩትም የማይታዩትም፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይንም ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት፣ በሰማይና በምድር ያሉት <u>ሁሉ በእርሱ ተፈጥረዋልና</u> ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኩር ነው፤ <u>ሁሉ በእርሱና ለእርሱ ተፈጥአል</u>። እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ ተጋጥሞአል።”
  - ዮሐ.5፡21 “አብ ሙታንን እንደሚያስነሳ ህይወትም እንደሚሰጣቸው፣ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ህይወትን ይሰጣቸዋል።
  - ዮሐ.10፡28 “እኔም የዘላለም ህይወት እሰጣቸዋልሁ …”
- **<u>ወልድ መጀመርያ የሌለው መሆኑ፣</u>**

  ኢየሱስ የተባለው ወልድ የሰውን ስጋ ተዋህዶ የተወለደበት የተዋህዶ ስም ነው(ማቴ.1፡21)፣ በዚህም ኢየሱስ የሚለው ስም መነሻ ጊዜ ቢኖረውም ኢየሱስ ውስጥ ያለው አምላክ የሆነው ወልድ ግን ዘላለማዊ በመሆኑ መነሻ ጊዜ የለውም፣ ወልድ ወደዚህ ምድር የመጣው ሥላሴ ከሆነው የእግዚአብሔር ማንነት ወጥቶ በመሆኑም(ዮሐ.13፡3, ዮሐ.16፡28, ዮሐ.17፡8 …) የኢየሱስ አምላካዊ ማንነት መነሻ ጊዜ የለውም፣ መጽሐፍ ቅዱሱም ይህንኑ ነው የሚነግረን፣
  - ዕብ.7፡3 “አባትና እናት <u>የትውልድም ቁጥር የሉትም</u>፣ ለዘመኑም <u>ጥንት</u> ለህይወቱም ፍፃሜ የለውም …”
  - ዕብ.1፡4-6 “… ስለ ልጁ ግን <u>አምላክ ሆይ ዙፋንህ ለዘላለም ይኖራል</u> … ይላል”
  - ራዕ.1፡17 “… ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ …”
  - ራዕ.22፡13 “አልፋና አሜጋ፣ ፊተኛውና ኋለኛው፣ መጀመርያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።”
  - ሚክ.5፡2 “… አወጣጡ <u>ከቀድሞ ጀምሮ ከዘላለም የሆነ</u>፣ በእስራኤል ላይ ገዢ የሚሆን ይወጣልኛል።”
- **<u>ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር አንድ መሆኑ፣</u>**
  - ሙሉ አምላክ ነው - 1ዮሐ.5፡20, ሮሜ.9፡5, 2ጴጥ.1፡1, ቲቶ.2፡12-13, ኢሳ.9፡6, ዕብ.1፡4-6 …
  - እግዚአብሔር ነው-ዮሐ.1፡1-14, ማቴ.1፡23, ዮሐ.16፡30፣ ቆላ.1፡19…
  - ከአብ ጋር አንድ ነው - ዮሐ.10፡30
  - “ጌታ” ነው - ኢየሱስ ብዙ ስፍራዎች ላይ ጌታ ተብሏል ነገር ግን የኢየሱስ ጌትነት እንደ እግዚአብሔር ጌትነት ከሌሎቹ ጌትነት የላቀ በመሆኑ “ጌታ”

ለተባሉት እንኳን ጌታ መሆኑን ለማሳየት "የጌቶች ጌታ" መሆኑን የተመሰከረለት መሆኑ(ራዕ.17፡14)

- ሁሉን ቻይ ነው - ዮሐ.1፡3
- ሁሉን አዋቂ ነው - ዮሐ.2፡25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.21፡17, ዮሐ.1፡48-50, ዮሐ.2፡24-25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.6፡64, ዮሐ.21፡17, ማር.2፡8...
- በሁሉም ስፍራ ይገኛል - ማቴ.18፡20, ማቴ.28፡20 ...
- የልብን ያውቃል - ዮሐ.4፡29፣ ማቴ.26፡21-25 ...
- ስግደትን ተቀብሏል - ስግደት የሚደረገው ለአምላክ እግዚአብሔር ብቻ ነው (ዘጸ.34፡14)፣ ኢየሱስም አምላክ እግዚአብሔር በመሆኑ ስግደትን ተቀብሏል በዚህም ሰብአ ሰገል(ማቴ.2፡11)፣ ደቀመዛሙርቱ(ማቴ.14፡33, ማቴ.28፡17 ...)፣ ከለምፀ የዳነው ሰው(ማቴ.8፡2)፣ ዓይኑ የበራለት ሰው(ዮሐ.9፡38)፣ ከእብደት የዳነው የጌርጌሴኖኑ ሰው(ማር.5፡6) ...
- ፀሎት ወደሱ የሚደረግ መሆኑ - ፀሎት የሚደረገው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ኢየሱስም እግዚአብሔር በመሆኑ ወደሱ ፀሎት ይደረጋል(ዮሐ.14፡14)
- መስዋዕት የሚቀርብለት አምላክ መሆኑ (ማቴ.9፡13)
- ኃጢያት መሠረዩ - ከአንዱ እግዚአብሔር በቀር ኃጢያት የሚሰርይ በሌለበት(ማር.2፡7) ኢየሱስ እግዚአብሔር በመሆኑ በራሱ ኃጢያት ይቅር ብሏል(ማቴ.9፡2-6)።

እነዚህን ህልቆ መሳፍርት ማስረጃዎችን ስንመለከት ወልድ(ኢየሱስ) እራሱ ሙሉ እግዚአብሔር አምላክ መሆኑና የሥላሴን አስተምህሮ ለመቃወም ብቻ ወልድን ከአብ ነጥሎ ለማሳነስ የተሰራው አስተምህሮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን።

5.2.2.1.2. <u>"ኢየሱስ መልአኩ ሚካኤል ነው"</u>

ቤተክርስቲያኗ ኢየሱስን ከእግዚአብሔር አምላክነቱ ስታነሳው የሚካኤልን ቦታ ሰጥታው ነው፣

> [142]"ሚካኤል የሚባለው ስም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊትም ሆነ ወደ ሰማይ ከሄደ በኋላ የሚጠራበት ሌላ መጠሪያ ስሙ ነው።"

ነገር ግን ኢየሱስ መልአኩ ሚካኤል አለመሆኑና ከአጠቃላይ መላዕክቱም እንደሚለይ መጽሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል።

ሚካኤል የመላዕክት አለቃ ነው(ይሁዳ 1፡9)፣ ዳንኤል ስለ ሚካኤል ሲናገር "ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ"(ዳን.10፡13) በማለት ሚካኤል "አለቆች" ከሚባሉት

[142] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 218

በከፍተኛ ስልጣን ላይ ከሚገኙ መላዕክት ውስጥ አንዱ መሆኑን ይነገረናል፤ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር ግን "አንድያ ልጁን"(ዮሐ.3፡16) ይላል እንጂ እንደነ ሚካኤል "ከአለቆች መካከል" ወይ "ከልጆቹ መካከል" አይለንም፣ በዚህም ሚካኤል የሚገኝበት የመላዕክቱ ጎራና የኢየሱስ ጎራ የተለያየ መሆኑን እንገዘባለን፡፡

ከዚህ በተጨማሪም መጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስ ከመላዕክት እንደሚለይ በግልፅ እያነፃፀረ ይናገራል፣

- ዕብ.1፡4-6 "... ከመላዕክትስ፣ አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ፣ ደግሞም እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጄ ይሆነኛል ያለው ለማን ነው? ደግሞም በኩርን ወደ ዓለም ሲያስገባ፣ የእግዚአብሔር መላዕክት ሁሉ ለእርሱ ይስገዱ ይላል፡፡ ስለ መላዕክትም፣ መላዕክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ ይላል፣ ስለ ልጁ ግን አምላክ ሆይ ዙፋንህ ለዘላለም ይኖራል ... ይላል ... ነገር ግን ከመላዕክት፣ ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ ከቶ ለማን ብሎአል ... "
- ዕብ.2፡7-16 "ከመላዕክት ይልቅ በጥቂት አሳነስኸው ... ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ስለሰው ሁሉ ሞትን ይቀምስ ዘንድ ከመላዕክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሳ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን ... የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የመላዕክት አይደለም፡፡"

በዚህም ኢየሱስና መላዕክት የተለያዩ መሆናቸውን እንመለከታለን፡፡

በአጠቃላይም ስንመለከት የሥላሴ አንዱ አካል የሆነውን ኢየሱስን ከእግዚአብሔርነቱ ማንሳትም ሆነ ሚካኤል ቦታ ላይ ማስቀመጥ የማይቻል መሆኑን ነው፡፡

5.2.2.2. መንፈስ ቅዱስ

ቤተክርስቲያኗ የሥላሴ አስተምህሮን በመቃወም ከሥላሴ ውስጥ "አብን አምላክ" በማለት፣ "ወልድን ሚካኤል" ብላዋለች፣ ከሥላሴ አንዱ የሆነውን መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ምን ማለት እንዳለባት ሌላ ፈተና ሆኖባታል፣ በዚህም [143] "መንፈስ ቅዱስ ማለት በስራ ላይ ያለ የእግዚአብሔር ኃይል ነው፣ ሰብአዊ ማንነት የለውም" ብላዋለች፡፡

ቤተክርስቲያኗ ኢየሱስን ከአምላክነቱ ለማውረድ አዲስ ባሳተመችው "የአዲስ ዓለም ትርጉም" መጽሐፍ ቅዱሷ ላይ ማስተካከያ እንዳደረገችው፣ ይህን የመንፈስ ቅዱስ አስተምህሮዋንም የሚደግፍላትን "ማስተካከያዎች" አድርጋለች፣ ለምሳሌ ያህል፣ ዘፍ.1፡2 "የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሀ ላይ ሰፍፎ ነበረ፡፡" የሚለውን ቃል "የአምላክም ኃይል በውሀው ላይ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡" በሚል ቀይራዋለች፡፡ ይህም መንፈስ ቅዱስን በሙሉ ማንነቱ ካለማየት የመጣ ችግር ነው፣ ሌላው ቀርቶ፣

[143] https://www.jw.org/bible-teachings

ኢሳ.11፡24 “የእግዚአብሔር *መንፈስ*፣ <u>የጥበብና የማስተዋል</u> *መንፈስ*፣ <u>የምክርና የኃይል</u> *መንፈስ*፣ <u>የእውቀትና</u> <u>እግዚአብሔርን የመፍራት</u> *መንፈስ*...”

የሚለውን እንኳን ሙሉውን መውሰድ አልቻሉም ምክንያቱም ሙሉው ከተወሰደ *መንፈስ* ቅዱስ ሙሉ አምላክ ይሆንባቸዋልና ስለዚህ ከራሳቸው አስተምህሮ ጋር የምትሄደዋን “የኃይል” የምትለዋን ብቻ ለይተው አወጡ፡፡

ነገር ግን በ5.1.2.2.2 ክፍል እንደተመለከተው *መንፈስ* ቅዱስ ሙሉ ሰብአዊ ማንነት ያለው ሙሉ አምላክ ነው ይባሱኑ ከሙሉ ማንነቱ ዝቅ ማድረጉ የማይሰረይ ኃጢያት መሆኑን ተመልክተናል(ማቴ.12፡32)፣ ይህም የቤተክርስቲያኗና የምዕመናኖቸዋ አሳዛኝ መጨረሻ ነው፡፡

<u>ማጠቃለያ (የሥላሴ አስተምህሮ)</u>

የይሖዋ ቤተክርስቲያን የሥላሴን አስተምህሮ በመቃወም “አንድ አምላክ አብ ብቻ” በማለቷ የሥላሴ አካላት የሆኑት ኢየሱስንና *መንፈስ* ቅዱስን የምታደርገው ግራ ገብቷት ስህተት ውስጥ ስትገባ ተመልክተናል፣ በርግጥ የሥላሴ አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱሱ መገለጦች ውስጥ ከባዱ ክፍል መሆኑን በ5.1.2.3 ክፍል በስፋት ተመልክተናል፡፡

ከሁሉ የሚገርመው ግን የ“ሥላሴ” አስተምህሮ የተቃወሙት የአብርሃም ኃይማኖቶች በሙሉ የተሳሳቱት በተመሳሳይ መንገድ ነው፣ የሦስቱን አምላካዊ ማንነት ለአንዱ ብቻ በመስጠት ለሁለቱ ሌላ ምደባ መስራት፣ ጂሆቫ “ኢየሱስ ሚካኤል ነው” ስትል እስልምናው ደግሞ “*መንፈስ* ቅዱስ ጅብሪል(ገብርኤል) ነው” አለ፤ የሐዋርያትና የጂሆቫ አብያተ ክርስቲያናት በተመሳሳይ መልኩ *መንፈስ* ቅዱስን “ኃይል” በማለት ችግራቸውን ለመወጣት ሞክረዋል፡፡

በዚህም እነዚህ ሦስቱ የሥላሴን አስተምህሮ የተቃወሙት የአብርሃም ኃይማኖቶች መካከል ተመሳሳይ *መንፈስ* እንመለከታለን፡፡

5.2.3. <u>“ሰው ሲሞት በህይወት የምትቀጥል ነፍስ ወይንም *መንፈስ* የለውም”</u>

የይሖዋ ቤተክርስቲያን “ሰው ከሞተ ሞተ ነው `ነፍስ` እና `*መንፈስ*` የሚባል ነገር የለም” ትላለች፣ [144] “ስጋችን ሲሞት በህይወት የምትቀጥል ረቂቅ አካል በውስጣችን የለችም፡፡ የማይሞት ነፍስ ወይንም *መንፈስ* የለንም ... ሟቾች በመሆናችን ስጋችን ሲሞት በህይወት የምንቀጥልበት ምንም አይነት መንገድ የለም... ሰይጣን `... ሰዎች ስጋችን ከሞተ በኋላ በመንፈሳዊ ዓለም እንኖራለን` የሚል እምነት እንዲያድርባቸው ለማድረግ የሐሰት ኃይማኖትን መሣሪያ አድርጎ ይጠቀማል፡፡” ሲሉ በትንሳኤ ቀን ስለሚነሳው አካልም ሲናገሩ

[144] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 58-64፣ 152

[145] "በመቃብር ውስጥ ያሉት ከሞት ሲነሱ ፈጣሪ ህይወትን መልሶ ይፈጥርላቸዋል።" ይላሉ፣

ነፍስና መንፈስ የሚባሉትን ቃላት ሲፈቱም [146]"ነፍስ የሚለው ቃል ህይወትን ያመለክታል ለምሳሌ ዘጸ.4፡19 "ነፍስህን የሚሹአት ሰዎች ሞተዋል።" ማለቱ "ህይወቱን ለማጥፋት የሚሹ ማለት ነው" ሲሉ፣ በሌላ ትርጉሙ ደግሞ "ነፍስ ማለት ሰውን የሚያመለክት ቃል ነው፣ ይህንንም በዘጸ.16፡16 "በድንኳኑ ባሉት ነፍሶች ቁጥር ... ውሰዱ።" የሚለው ላይ ተመልክቷል" ይላሉ፤ መንፈስ ማለት ደግሞ [147] "የራሱ ስብዕናና ባህሪ የሌለው የህይወት ኃይል ነው" ይላሉ።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱን ስንመለከት የነፍስና መንፈስ ትርጉም <u>በዚህ የማይወሰንና ከዚህ ሰፋ ያለ ትርጉም ያለው መሆኑን ነው</u>።

በመጀመሪያ እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ሲፈጥር ሦስት የተለያዩ ስራዎች ሲሰራ እናየዋለን፣ በመጀመሪያ እራሱ መንፈስ ስለሆነ "በመልካችን" እንዳለው መንፈስ የሆነውን የሰውን ማንነት በስድስተኛው ቀን ፈጠረ(ዘፍ.1፡27)፣ ይህንንም መንፈስ ከአፈር ስጋ አበጀው(ዘፍ.2፡7)፣ ከዚያ ይህንን ስጋ ህያው ነፍስ በውስጡ አደረገ(ዘፍ.2፡7)፣ በዚህም "በምሳሌያችን" እንዳለውም የሰው ልጅ ሥላሴ በሆነው በፈጣሪ ምሳሌ መፈጠሩን እንመለከታለን። ይህንን እውነታም ነተሰ.5፡23 "የሠላምም አምላክ ራሱ <u>ሁለንተናችሁን</u> ይቀድስ፤ <u>መንፈሳችሁም፣ ነፍሳችሁም ሥጋችሁም</u> ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለነቀፋ ፈፅመው ይጠበቁ።" በሚለው ቃል እናረጋግጣለን።

በዚህም የሰው ልጅ ከሰጋው በተጨማሪ መንፈስና ነፍስ የሚባሉት ማንነቶች እንዳሉት እንረዳለን፣ ስለነዚህ ማንነቶች በዝርዝር ብንመለከት፡-

5.2.3.1. <u>የሰው ነፍስ</u>

ቤተክርስቲያኗ ከምትሰጠው ትርጉም በተጨማሪ የሰው ነፍስ የራስዋ ማንነት ያላት፣ ዘላለማዊ የሆነችና ስጋም ሲሞት ወደ ፈጣሪ የምትሄድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፣

- <u>**ነፍስ ህያው ማንነት ያላት መሆኑ**</u>
  - ማቴ.10፡28 "*ሥጋንም* የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ..."
  - ዘፍ.2፡7 "እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት፤ ሰውም <u>ህያው ነፍስ</u> ያለው ሆነ።"

[145] Ibid 71
[146] Ibid 208-211
[147] Ibid 210-211

- ዘፍ.9፡15 "በእኔና በእናንተ መካከል፣ ህያው ነፍስ ባለውም ስጋ ሁሉ መካከል ያለውን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ …"

➢ **ሰው ሲሞት ከስጋ የምትለይ መሆኑ**

- ዘፍ.35፡18 "እርስዋም ስትሞት ነፍስዋ በምትወጣበት ጊዜ ስሙን ቤን ኦኒ ብላ ጠራችው፤ አባቱ ግን ቢኒያም አለው፡፡"
- ዮና.4፡3 "አሁንም፣ አቤቱ፣ ከህይወት ሞት ይሻለኛልና እባክህ ነፍሴን ከእኔ ውሰድ አለው፡፡"
- ሐስ.7፡59 "እስጢፋኖስም፡፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር፡፡"
- ነገ.17፡21-22 "በብላቴናውም ላይ ሦስት ጊዜ ተዘረጋበት፣ ወደ እግዚአብሔርም፡፡ አቤቱ አምላኬ ሆይ፣ የዚህን ብላቴና ነፍስ ወደ እርሱ ትመለስ ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ጮኸ፡፡ እግዚአብሔርም የኤልያስን ቃል ሰማ፤ የብላቴናውም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች፣ እርሱም ዳነ፡፡"

➢ **ከስጋ ስትለይም ወደ ፈጣሪ የምትሄድ መሆኑ**

- መክ.3፡21 "የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳት ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው፣"
- መክ.12፡7 "አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፣ ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ፡፡
- ሉቃ.23፡46 "ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ፡፡ አባት ሆይ፣ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ፡፡ ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ፡፡"
- ራዕ.6፡9 "አምስተኛውም ማህተም በፈታ ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሰዊያ በታች አየሁ፡፡"

በአጠቃላይ ስንመለከት በሥላሴነት በተፈጠረው የሰው ልጅ ውስጥ ነፍስ የራሷ ማንነት ያላት፣ ስትወጣም ስጋ ሙት እንደሚሆን፣ ከስጋ ወጥታም እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላት ስፍራ እንደምትሄድ እንመለከታለን፡፡

5.2.3.2. የሰው መንፈስ

ብዙዎች የሰው ነፍስና መንፈስ አንድ ይመስላቸዋል ነገር ግን ሁለቱም የተለያየ ማንነት ያላቸው ሲሆን ሁለቱን ግን ለያይቶ መግለፅ ከሰው ልጅ አቅም በላይ ነው፣ ለዚህም ነው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ቃል ችሎታ ሲናገር፣ ዕብ.4፡12 "የእግዚአብሔር ቃል ህያው ነውና የሚሰራም፣ ሁለት አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፣ ነፍስንና መንፈስንም … እስኪለይ ድረስ ይወጋል …" የሚለው፡፡

በዚህም ምንም እንኳን የሰውን ነፍስና መንፈስ ለያይቶ መግለፅ ባይቻልም፣ ሰው ግን ከስጋ በተጨማሪ "ነፍስና መንፈስ" የሚባሉ ሁለት የተለያዩ ማንነቶች እንዳሉት መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ እንመለከታለን፡-

- ኢሳ.57፡16 "<u>መንፈስም</u> የፈጠርሁትም <u>ነፍስ</u> ከፊቴ እንዳይዝል ለዘላለም አልጣላም፣ ሁልጊዜ አልቆጣም፡፡"
- ዳን.7፡15 "በእኔም በዳንኤል <u>በስጋዬ ውስጥ</u> <u>መንፈሴ ደነገጠች</u> ..."
- ኢዮ.7፡11 "ስለዚህ <u>አፌን</u> አልከለክልም፣ <u>በመንፈሴ</u> ጭንቀትን እናገራለሁ፣ <u>በነፍሴ</u> ምሬት በኃዘን አንጎራገራለሁ፡፡"
- ሉቃ.1፡47 "<u>ነፍሴ</u> ጌታን ታከብረዋለች፣ <u>መንፈሴም</u> በአምላኬ በመድኃኒቴ ሀሴት ታደርጋለች፤"
- ፩ቆሮ.14፡14 "በልሳን ብፀልይ <u>መንፈሴ</u> ይፀልያል አዕምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው፡፡"
- ፩ተሰ.5፡23 "የሠላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ <u>መንፈሳችሁም</u>፣ <u>ነፍሳችሁም</u>፣ <u>ስጋችሁም</u> ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈፅመው ይጠበቁ፡፡"

በዚህም ሰው የራሱ መንፈስ እንዳለው እንገነዘባለን፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ቤተክርስቲያኗ "ስጋችን ሲሞት በህይወት የምትቀጥል የማትሞት ነፍስ ወይንም መንፈስ የለንም" የሚለው አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና የሰው ልጅ እንደ እግዚአብሔር ሥሉስነት በስጋ፣ ነፍስና መንፈስ እንደተዋቀረ እንመለከታለን፡፡

5.2.4. <u>የመጨረሻው ዘመን</u>

ቤተክርስቲያኗ ስለ መጨረሻው ዘመን ያላት አስተምህሮ ከሁሉም የክርስቲያን እምነት ተቋማት ይለያል፣ እነዚህም ልዩ አስተምህሮዎች፡-

- "1914 ዓ.ም ኢየሱስ የነገሠበት አመት ነው"
- "በሺሁ አመት 144,000 የጂሆቫ ተከታዮች ከኢየሱስ ጋር ይፈርዳሉ"
- "የሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ"
- "ምድር ገነት ናት"
- "ነፍስ ለዘላለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ስፍራ የለም"

ሲሆኑ ሁሉንም ከመጽሐፍ ቅዱሱ አንፃር በዝርዝር እንመለከታለን፡፡

5.2.4.1. "1914 ዓ.ም ኢየሱስ የነገሠበት አመት ነው"

እንደ ቤተክርስቲኗ አስተምህሮ [148]"*መንግሥተ ሰማይ በሰማይ ያለ መስተዳድር ነው፣ የዚህ መንግሥት ንጉሥ ኢየሱስ ሲሆን መንግሥቱን መግዛት የጀመረው ከ*1914 *ጀምሮ ነው፣ ከዚህም ጊዜ አንስቶ ሰይጣን ወደ ምድር ተጥሎአል::*"

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ስንመለከት ሰይጣን ወደ ምድር የሚጣልበትና ኢየሱስ የሚነግስበት ጊዜ ገና ነው፣ እነዚህ ሁለቱ ክስተቶች የሚከናወኑት በእስራኤል ላይ የሚነሱት ሁለት ነብያት መገደልና የአውሬው መንፈስ(666) ከሚገዛበት ዘመን በኋላ ነው::

- ራዕ.11፡2-15 "... እነርሱም አርባ ሁለት ወር የተቀደሰችውን ከተማ ይረግጧታል፣ ለሁለቱ ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ ... ምስክራቸውን ከፈፀሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፍማቸዋል ይገድላቸዋማል ... ከእግዚአብሔር የወጣ የህይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸው ቆሙ ... በዚያ ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ ... የዓለም መንግሥት ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ሆነች፣ ለዘላለም እስከ ዘላለም ይነግሳል::"
- ራዕ.12፡5-10 "አህዛብን ሁሉ በብረት ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፣ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔር ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ፣ ሴቲቱም ሺ ከሁለት መቶ ስድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ስፍራ ወደ በረሀ ሸሸች:: በሰማይም ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላዕክቱ ዘንዶውን ተዋጉ፣ ዘንዶውም ከመላዕክቱ ጋር ተዋጋ፣ አልቻላቸውም፣ ከዚያ ወዲያ በሰማይ ስፍራ አልተገኘላቸውም:: ዓለሙን ሁሉ የሚያስተው ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፣ ወደ ምድር ተጣለ መላዕክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ:: ታላቅ ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል፣ አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስ ስልጣን ሆነ፣ ቀንና ለሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞችን ከሳሽ ተጥሎአልና::"

እነዚህ ሁለቱም ጥቅሶች የሚናገሩት በአንድ ላይ ስለሚፈፀሙ ሁለት ክስተቶች ነው፣ ስለ ሰይጣን ከሰማይ መጣልና ስለ ኢየሱስ ንግሥና፣ ሁለቱም ክስተቶች ከመፈፀማቸው በፊት ግን የ666 መንፈስ ይነግሣል፣ ይህ ክስተት ደግሞ በ1914ም ሆነ እስካሁን አልተፈፀመም (በምዕራፍ ሰባት ክፍል በስፋት ቀርቧል)፣ ከ666 መንፈስ መገለጥ በኋላ ደግሞ ኢየሱስ ይገለጣል፣ ይህ ደግሞ የሚፈፀመው በታላቅ ምልክት ነው፣

[148] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 74, 78, 84

ማቴ 24፡27-30 "... መብረቅ ከምስራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፣ <u>የሰው ልጅ መምጣት</u> እንዲህ ይሆናልን ... ከዚያችም ወራት በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፣ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፣ ከዋክብት ከሰማይ ይወድቃሉ፣ የሰማይም ኃይላት ይናወጣሉ፡፡ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል..."

እነዚህም ምልክቶች በ1941 ያልተፈፀሙ፣ እስካሁን ያልተፈፀሙና ገና ለወደፊት የሚፈፀሙ ክስተቶች መሆናቸውን ስንመለከት ይህንን ገና የሚፈፀም ታሪክን በ1914 ዓ.ም እንደተፈፀመ አድርገው ማቅረቡ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

5.2.4.2. <u>"ከኢየሱስ ጋር የሚፈርዱት 144,000 የጂሆቫ ተከታዮች ናቸው"</u>

[149]"*መንግሥተ ሰማይ* በሰማይ ያለ መስተዳድር ነው፣ የዚህ *መንግሥት* ንጉሥ ኢየሱስ ሲሆን *መንግሥቱን* መግዛት የጀመረው ከ<u>1914</u> ጀምሮ ነው ... በዚህ *መንግሥተ* ሰማያትንም ከኢየሱስ *ጋር* እንዲገዙ <u>144,000</u> ሰዎች ከሐዋርያት *ዘመን* ጀምሮ *ታማኝ* ክርስቲያኖችን ሲመርጥ ቆይታል፡፡ በኛ *ዘመን* ያሉት የ144,000 ጥቂት ቀሪዎች በሚሞቱበት ጊዜ በቅፅበት ተነስተው ሰማያዊ ህይወት ያገኛሉ፡፡"

እንደ ቤተክርስቲያኗ አስተምህሮም ይህ 144,000 ቁጥር ዛሬ ላይ እየተሟላ ያለው ከጂሆቫ እምነት ተከታዮች እንደሆነ ትናገራለች፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ቤተክርስቲያኗ "ሰው ከሞተ በኋላ በህይወት የምትቀጥል ነፍስም ሆነ መንፈስ የለውም" እያለችና የየትኛውም የጂሆቫ እምነት ተከታይ አስከሬን ሲያርግ በማንመለከትበት ሁኔታ ውስጥ "በሚሞቱበት ጊዜ በቅፅበት ተነስተው" ማለቷ አስተምህሮው የውሸት አስተምህሮ መሆኑን እንመለከታለን፡፡

በመቀጠል 144,000 ሰዎችን የመለየት ስራ የሚሰራው የአርማጌዶን ጦርነት ሊካሄድ ሲል እንጂ ከሐዋርያት ዘመን አንስቶ አይደለም፣ የሚለዩትም ከስጋዊዋ እስራኤል ዘር የሆኑት ብቻ ናቸው፣

ራዕ.7፡1-8 "ከዚህም በኋላ በአራቱ ምድር ማዕዘን አራት መላዕክት ቆመው አየሁ ... ሌላ መልአክም ... ለአራቱ መላዕክት በታላቅ ድምፅ እየጮኸ፡- የአምላካችንን ባሪያዎች ግንባራቸውን እስክናትማቸው ድረስ ምድርንም ቢሆን ወይንም ባህርን ወይም ዛፎችን አትጉዱ አላቸው፡፡ የታተሙትን ቁጥር ሰማሁ፡፡ ከእስራኤል ነገዶች ሁሉ የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺ ነበሩ፣ ከይሁዳ ነገድ አስራ ሁለት ሺ፣ ከሮቤል ነገድ አስራ ሁለት ሺ፣ ከጋድ ነገድ አስራ ሁለት ሺ ..."

[149] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 74፣ 78፣ 84

እነዚህ 144,000 ሰዎችም ከእስራኤል ቤት ብቻ መሆኑንና ከየነገዱም ምን ያህል እንደሆኑ በግልፅ ቁጥሩን ዘርዝሮ ይነግረናል፣ በዚህም የጂሆቫ ተከታዮች እዚህ 144,000 ውስጥ የሚገቡበት አሰራር የለም፡፡

እዚህ ጋር "ከአህዛብ ወገን የሆኑቱ ፃድቃን ምን ይሆናሉ?" ለሚለው፣ አህዛብ ከጦርነቱ በፊት አስቀድሞ የሚነጠቁ (1ተሰ.4፡17) በመሆኑ፡-

> ራዕ.7፡9 "ከዚህም በኋላ አየሁ፣ እነሆም አንድ ስንኳ ሊቆጥራቸው የማይችል ከህዝብና ከነገድ ከወገንም ከቋንቋም እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፣ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባ ዝንጣፊ በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ ..."

ይላል፣ በዚህም የ144,000 ሰዎችን ጉዳይ ከአህዛብም ሆነ ከጂሆቫ ቤተክርስቲያን ጋር ማገናኘቱ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

5.2.4.3. "ምድር ገነት ናት"

እንደ ቤተክርስቲያኗ፣

> [150] "የምድር ነገሥታት በክፉ መናፍስት አነሳሽነት አርማጌዶን በሚባል ስፍራ ይሰበሰባሉ፣ በዚህም መሠረት በሰብአዊው መንግሥታትና በአምላክ መንግሥት መካከል በዚህ ስፍራ የመጨረሻ ውጊያ ይካሄዳል፣ በዚህ ጦርነትም ክፉ ሰዎች፣ ሰይጣንና ኢጋንንቱ ይወገዳሉ፣ ሰብአዊ መስተዳድሮች ይጠፋሉ፣ ዘላለማዊው የአምላክ መስተዳድር ይጀምራል፣ ከዚያ በኋላ ምድር ገነት ትሆናለች፡፡"

ለዚህም አስተምህሮ ማጠናከሪያ፣

- መክ.1፡4 "ምድር ግን ለዘላለም ናት"
- መዝ.37፡29 "ፃድቃን ምድርን ይወርሳሉ በእስዋም ላይ ለዘላለም ይኖራሉ"
- መዝ.104፡5 "ለዘላለም እንዳትናወጥ ምድርን በመሠረቷ ላይ መሠረታት፡፡"

የሚሉቱን ይጠቅሳሉ፡፡

እዚህ ጋር የምንመለከተው ስህተት መነሻ፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ "ሁለት ምድር" የመጀመርያዋና ተተኪ ምድር መኖሯን ካለማወቅና "ዘላለም" የሚለው ቃል ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጉሞችን ካለማወቅ የተከሰተ ስህተት ሲሆን ከነዚህ ስህተቶች የተነሳው ድምዳሜ ደግሞ የተለያዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ኩነቶችን በአንድ ላይ ያደራረበ የተሳሳተ ድምዳሜ ነው፣ ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

---

[150] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 81-85

- **<u>“ሁለት ምድር” የመጀመርያዋና ተተኪ ምድር መኖሯን ካለማወቅ</u>**

አዲሱ ኪዳን ይህቺ ምድር በሌላ ምድር እንደምትተካና ይህም መቼ እንደሚሆን ጭምር ዘርዝሮ ይነግረናል፡-

- <u>አሁን ያሉት ሰማይና ምድር የሚያልፉ መሆኑ፣</u>
  - ዕብ.1፡10-12 “... አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ ሰማዮችም የእጆችህ ስራ ናቸው፣ እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ፀንተህ ትኖራለህ፣ ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፣ እንደ መጎናፀፊያም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጡማል፣ አንተ ግን አንተ ነህ አመቶችህ ከቶ አያልቁም፡፡”
  - ማቴ.24፡35 “ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም፡፡”
  - ራዕ.20፡11 “ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፣ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ስፍራም አልተገኘላቸውም፡፡”
- <u>የሚያልፉትም መቼ እንደሆነ መገለፁ፣</u>
  - 2ጴጥ.3፡7 “አሁን ያሉ ሰማያና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል፡፡”
  - 2ጴጥ.3፡10-12 “የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፣ በዚያን ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፣ የሰማይ ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፣ ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል ... ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይፈታል፡፡”
- <u>የምትተካዋ አዲሲቷ ሰማይና ምድር</u>
  - ራዕ.21፡1 “አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርን አየሁ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና ...”
  - 2ጴጥ3፡13 “ነገር ግን ፅድቅ የሚኖርባትን አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር እንደ ተስፋ ቃሉ እንጠብቃለን፡፡”
  - ኢሳ.66፡22 “እኔ የምሰራቸው **<u>አዲስ</u>** ሰማይና **<u>አዲስ</u>** ምድር ከፊቴ ፀንተው እንደሚኖሩ ...”

በዚህም ቅዱሳን የሚኖሩባት አዲስ፣ ንፁህ(ያልተበከለች)፣ ቅድስት(ያልተረገመችና በሰይጣን የማትገዛ)፣ የተባረከች ... በሁለንተናዋ ፍፁም የሆነችና ፈጣሪ ለቅዱሳን በሽልማት ያዘጋጃት ምድር ትመጣለች፣ በዚህም ይህቺ “ምድር ገነት ሆና ለዘላለም ትኖራለች” የሚለው የቤተክርስቲያኗ አስተምህሮ ስህተት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

- **<u>“ዘላለም” የሚለው ቃል ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቺዎች አለማወቅ</u>**

በ4.ነ.3.2 ክፍል እንደተመለከተው ብሉይ ኪዳን “ስግደት” የሚለው ቃል በሁለት መንገድ እንደተጠቀመው እንደዚሁ ብሉይ ኪዳን “ዘላለም” የሚለውን ቃል በሁለት መንገድ ይጠቀመዋል፣ የመጀመሪያው አብዛኛው ሰው የሚያውቀው “በጊዜ አለመገደብ” የሆነው ትርጉሙ ሲሆን ሁለተኛው ትርጉሙ ደግሞ “ዕድሜ ልኩን” ማለት ነው፣ ይህንን ሁለተኛውን ትርጉም ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱሱ እንዴት እንደሚጠቀመው እስቲ እንመልከት፣

- ነሳሙ.27፡12 “... ስለዚህ ለዘላለም ባርያዬ ይሆነኛል ብሎ ዳዊትን አመነው፡፡”
- ነሳሙ.ነ፡22 “ሀና ግን አልወጣችም ባልዋንም፡፡ ህፃኑ ጡት እስኪተው ድረስ እቀመጣለሁ፣ ከዚያ በኋላ በእግዚአብሔር ፊት ይታይ ዘንድ፣ በዚያ ለዘላለም ይሆን ዘንድ አመጣዋለሁ አለች፡፡”
- ዘጸ.21፡6 “... ለዘላለም ባርያው ይሁን፡፡”
- 2ዜና.10፡7 “(ሽማግሌዎቹም ለንጉሥ ሮብአም) ለዚህ ህዝብ ቸርነት ብታደርግላቸው፣ ደስም ብታሰኛቸው፣ በገርነትም ብትናገራቸው፣ ለዘላለም ባሪያዎች ይሆኑልሀል፡፡”
- መዝ.12፡7 “አቤቱ አንተ ጠብቀን፣ ከዚህችም ትውልድ ለዘላለም ታደገን፡፡”
- ዮና.2፡7 “(ዮናስም በአሳ ሆድ ውስጥ ሆኖ ሲፀልይ) ወደ ተራሮች መሠረት ወረድሁ፣ በምድርና በመወርወሪያዎች ለዘላለም ተዘጋሁ ...”

ይህ የመጽሐፍ ቅዱሱ “ዘላለም” አተረጓጎም “በተሰጠው ዕድሜ ውስጥ” የሚል ትርጉም የያዘ ሲሆን የመጀመርያዋ “የምድር ዘላለማዊነት” ጉዳይም የተነገረው በዚህ አውድ ነው፣ ይህም የመጀመርያዋ ምድር በተሰጣት ዕድሜ ውስጥ ፀንታ የምትኖር መሆንዋን ለማሳየት ነው፡፡

- **<u>ኩነቶችን በአንድ ላይ ማደራረብ</u>**

የቤተክርስቲያኗ “ከአርማጌዶን ጦርነት በኋላ ምድር ገነት ትደረጋለች” አስተምህሮ ሰፊ ኩነቶችን በአንድ ላይ የጨፈለቀ አስተምህሮ ነው፣ በአርማጌዶን ጦርነት(ራዕ.16፡16 - ራዕ.20፡3) እና ገነት መካከል ብዙ ክስተቶች ይስተናገዳሉ፣ አንኳር አንኳሮቹን ብንመለከት፣ የሺ አመት የዲያብሎስ እስርና የቅዱሳን ንግሥና(ራዕ.20፡4-6)፣ ሰይጣን ከእስራት ተፈትቶ የሚቆይበትና ጊዜ(ራዕ.20፡7-9)፣ ሰይጣን ላይ የሚፈረድበት ጊዜ (ራዕ.20፡10) እና የመጨረሻው የፍርድ ቀን(ራዕ.20፡11-15) ናቸው፡፡

በዚህም ይህ የቤተክርስቲያኒቷ መለያ የሆነው “ገነት በምድር” አስተምህሮ የሁለቱን ተተካኪ ምድሮች እውነታ ያላገናዘበ፣ “ዘላለም” የሚለውን ቃል ሁለት ብሉይ ኪዳናዊ አተረጓጎምን ያላገናዘበና ብዙ ኩነቶችን በአንድ ላይ ያደራረበ የስህተት አስተምህሮ ነው፡፡

5.2.4.4. "ሺ አመታት የትምህርትና የፍርድ ጊዜ"

እንደ ቤተክርስቲያኗ [151]"የፍርድ ቀን የሚጀምረው በምድር ላይ ያለው የሰይጣን ስርዓት በአርማጌዶን ጦርነት ከጠፋ በኋላ ነው። ከአርማጌዶን በኋላ ሰይጣንና አጋንንቱ በጥልቁ ውስጥ ለሺ አመት ይታሰራሉ። በዚያን ጊዜ 144,000 ተባባሪ የሰማይ ወራሾች ፈራጆች ይሆናሉ፣ እንዲሁም ነገሥታት ሆነው ከክርስቶስ ጋር ሺ አመት ይገዛሉ። የፍርድ ቀን ለ24 ሰዓት ብቻ የሚቆይ በጥድፊያ የሚከናወን ነገር አይደለም። ለሺ አመት የሚዘልቅ ነው። በሺሁ አመት ጊዜ ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ በህያዋንና በሙታን ላይ ይፈርዳል። ፍርዱ የሚሰጠው ሰዎች ቀደም ሲል በፈፀሟቸው ድርጊቶች ላይ ተመርኩዞ አይደለም፣ ከአርማጌዶን የሚተርፉትም ሆነ ከሞት የሚነሱት ሰዎች ለዘላለም መኖር እንዲችሉ ይሖዋ በሺሁ አመት ወቅት ሊያወጣቸው የሚችላቸውን መስፈርቶች ጨምሮ ሁሉንም የአምላክ ትዕዛዛት ማክበር ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ ሰዎች ፍርድ የሚሰጣቸው በፍርድ ቀን የሚፈፅሙትን ድርጊት መሠረት በማድረግ ነው። በፍርድ ቀን በቢሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ አምላክ ፈቃድ መማርና ከፍቃዱ ጋር ተስማምተው መኖር የሚችሉበት አጋጣሚ ያገኛሉ። በመሆኑም መጠነ ሰፊ የማስተማር ስራ ይካሄዳል ማለት ነው።"

ይህንን መቀበሉ አዳጋች ነው፣ አስተምህሮው እርስ በራሱ እንዲሁም ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር ይጋጫል፡-

1. "የፍርድ ቀን" ብሎ እሱም "ሺ አመት ነው" ይላል

   መጽሐፍ ቅዱሱ የፍርድ ቀንን የሚጠራው፣ የፍርድ ቀን(ማቴ.11፡24)፣ የመጨረሻው ቀን(ዮሐ.6፡54)፣ የኋለኛው ቀን(ያዕ.5፡3)፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ቀን(1ቆሮ.1፡8፣ ፊልጵ.1፡6)፣ የጌታ ቀን(2ጴጥ.3፡10)፣ የእግዚአብሔር ቀን(2ጴጥ.3፡11-12) የቤዛ ቀን(ኤፌ.4፡30)፣ ታላቁ ቀን(ይሁ.1፡6) ... በማለት ሁሉንም "ቀን" በማለት ነው፣ ይባሱኑ "ቀን" ተባለ እንጂ ይህ በቅፅበት የሚደረግ ነገር ነው ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ በመሆኑ(1ሳሙ.2፡3)፣ ምስክር የማይፈልግና ቀድሞውኑ የተዘጋጀ መዝገብ በመኖሩ(ራዕ.20፡12)፣ አማኞች ቀድሞውኑ ተለይተው የታተሙ በመሆኑ(ኤፌ.4፡30) ... ይባሱኑ የትኛውም ሰው ዛሬ ላይ ሆኖ በሱ ላይ የሚፈረደውን ፍርድ የሚያውቅበት ሁኔታ መነገሩ(ዮሐ.3፡18) ስንመለከት፣ እግዚአብሔር እንደ ሰነፍ ዳኛ ይባሱኑም ከሰነፍ ዳኛ ባነሰ "የፍርዱ ሂደት አንድ ሺ አመታት ይፈጅበታል" ማለቱ ስህተት ነው።

[151] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 214

2. “የፍርድ ቀን” ብሎ ተመልሶ ደግሞ ሰዎች ፍርድ የሚሰጣቸው “በፍርድ ቀን በሚፈፅሙት ድርጊት ነው” በማለት ኃጢያተኞች ሌላ እድል እንዳላቸው ይናገራሉ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱ ሰዎች ከሞቱ በኋላ ምንም ሌላ እድል እንደማይሰጣቸው ይናገራል፣

ዕብ.9፡27 “ለሰዎች አንድ ጊዜ መሞት **ከእርሱ በኋላ** ፍርድ ተመደበባቸው።።”

በዚህም ይህ “አሁን ኃጢያት መስራት ችግር የለውም፣ ገነት ለመግባት ሌላ ሁለተኛ የመማርና የማመን እድል አለ” የሚለው አስተምህሮ ሰዎችን ለሲኦል የሚመለምለው መንፈስ ብቻ ነው።።

3. በሺሁ አመትም(በፊተኛው ትንሳኤ) ሁሉም ሰው ከሞት እንደሚቀሰቀስ ይናገራል ነገር ግን ይህ ስህተት መሆኑና “ፊተኛው ትንሳኤ” የሚባለው ለሺ አመት ኑሮ ከሞት የሚቀሰቀሱት ቅዱሳን፣ ያውም ሰማዕታት ብቻ ናቸው፣

ራዕ.20፡4-6 “ዙፋኖችንም አየሁ፣ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፣ ለውሬውና ለምስሉ ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺ አመት ኖሩና ነገሡ።። የቀሩት ሙታን ግን ይህ ሺ አመት እስኪፈፀም ድረስ በህይወት አልኖሩም።። ይህ የፊተኛው ትንሳኤ ነው።። በፊተኛው ትንሳኤ እድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በነርሱ ላይ ስልጣን የለውም ...”

እነዚህን እውነታዎችንም በአንድ ላይ ስንመለከት ቤተክርስቲያኗ ምን ያህል የመጽሐፍ ቅዱሱን መንገድ እንደሳተች እናስተውላለን።።

5.2.4.5. “ነፍስ ለዘላለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ስፍራ የለም”

እንደ ቤተክርስቲያኗ አባባል [152] “አንዳንዶቹ ኃይማኖቶች አንድ ሰው አኗኗሩ መጥፎ ከሆነ ከሞተ በኋላ እሳታማ ወደ ሆነ መሰቃያ ስፍራ ገብቶ ለዘላለም ይሰቃያል ብለው ያስተምራሉ።። ይህ ትምህርት የአምላክን ስም የሚያጠፋ ነው።። ይሖዋ (እግዚአብሔር) የፍቅር አምላክ በመሆኑ ሰዎችን ፈፅሞ በዚህ መንገድ አያሰቃይም።።” ይላሉ፣ ነገር ግን ይህ ስህተት መሆኑና ስህተቱም የመጣው፣

- የእግዚአብሔርን ሙሉ ማንነት ካለማወቅ፣
- የሰው ነፍስን ዘላለማዊነት ካለማወቅ፣
- የሲኦልን ሙሉ ትርጉም ካለማወቅ፣

መሆኑን ቀጥለን በዝርዝር እንመለከታለን፣

[152] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 64፣ 72 እና 212-213

- **<u>እግዚአብሔርን በሙሉ ማንነቱ ካለማወቅ</u>**

ቤተክርስቲያኗ "እግዚአብሔር ፍቅር ስለሆነ ጨክኖ ሰውን ለዘላለም በእሳት ውስጥ አይቀጣም ትላለች" በርግጥ እግዚአብሔር ፍቅር በመሆኑ ከመጀመሪያው ሲኦልን ለሰው ልጆች አላዘጋጀም፣

> ማቴ.25፡41 "በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል፡፡ እናንተ ርጉማን፣ <u>ለሰይጣንና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ</u> ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ (ይላቸዋል)፡፡"

ነገር ግን ሰይጣን የሰው ልጆችን አሳስቶ በራሱ የርኩሰት መንገድ ስላስገባ፣ <u>የረከሰ ደግሞ ገነት ስለማይገባ፣</u> እግዚአብሔር ባዘጋጀው የፅድቅ መንገድ መሄድ ያልቻለ የሰው ልጅም ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦል መግባቱ የግድ ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ሊታወቅ የሚገባው እግዚአብሔር "ፍቅር" ብቻ ሳይሆን ለሕግ አልገዛ የሚሉትን የሚቀጣ(ዘሌ.26፡28)፣ የሚያጠፋ እሳት(ዕብ.12፡29) ለተነዱ የሚበቀል(ዕብ.10፡30) … በአጠቃላይ ከፍቅሩም በተጨማሪ በቁጣም የሚገለጥ አምላክ ነው፡፡ በዚህም እግዚአብሔርን "ፍቅር ነው" በሚለው ብቻ አይወሰንም፣ እግዚአብሔር በብዙ መንገድ ይገለጣል፣ ለያንዳንዱ ሰው የሚገለጠውም እንደ ሰውየው ስራ ነው፣ በትዕዛዙ የሚሄዱት ፍቅሩን ያጣጥማሉ፣ ኃጢያተኞች ደግሞ ቁጣውን፡፡

- **<u>የሰው ነፍስን ዘላለማዊነት ካለማወቅ</u>**

ቤተክርስቲያኗ ሰውን በሁለት በመክፈል "ፃድቅ ለዘላለም ይኖራል ኃጢያተኛ እንዲሁ ሞቶ ይቀራል እንጂ ለዘላለም አይቀጣም" ትላለች፣ ለዚህም የምታቀርበው መከራከሪያ፣

> ሮሜ.6፡23 "የኃጢያት ደሞዝ <u>ሞት</u> ነውና የእግዚአብሔር የጸጋው ስጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን <u>የዘላለም ህይወት</u> ነው፡፡"

የሚለውን ነው፣ የዚህ ስህተት መነሻ የነፍስን ሞት በስጋ ሞት ዓይን የመመልከት ችግር ነው፣ ነገር ግን የነፍስ ሞትና የስጋ ሞት የተለያዩ ናቸው፣ የስጋ ሞት ማለት የነፍስና የስጋ መለያየትና የስጋ ህልውና መቆም ማለት ሲሆን የነፍስ ሞት ማለት ደግሞ "ሁለተኛው ሞት የሚባለውና ነፍስ ከፍርድ አለማምለጥና በሲኦል ውስጥ መጣል" ማለት ነው(ራዕ.2፡11, ራዕ.20፡6, ራዕ.20፡14, ራዕ.21፡8 …)፡፡

በዚህም የስጋና የነፍስ ሞት የተለያዩ ሲሆኑ የስጋ ሞት ማለት "የስጋ ህልውናውን ማቆም" ማለት ሲሆን የነፍስ ሞት ማለት ደግሞ የ"ነፍስን ህልውና ማጣት" ሳይሆን "ነፍስ ወደ ሲኦል መጣል" ማለት ነው፣ በዚህም "የኃጢያት ደሞዝ ሞት ነው" የሚለው የነፍስ ወደ ሲኦል መውረድን ያመለክታል፡፡

ነፍስ የማትሞት ህያው ተደርጋ ስለተፈጠረች(ዘፍ.2፡7, ዘፍ.9፡15…)፣ ነፍስ ከስጋ በምትለይበት ጊዜ መኖሪያ ስፍራ ያስፈልጋታል፣ በዚህም እስከ ፍርድ ቀን በጊዜያዊው መኖሪያ በገነትና በሲኦል ትቀመጣለች(ሉቃ.16፡23-24) ለዚህ ነው ኢየሱስ ሉቃ.23፡43

“አንተ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት …” ያለው እንዲሁም በሌላ ስፍራ መጽሐፉ በፍርድ ቀን “ሲኦል ነፍሳትን ሰጠች”(ራዕ.20፡13) የሚለው።

➢ **<u>የሲኦልን ምንነት ካለማወቅ</u>**

ቤተክርስቲያኗ “ሲኦል” የሚለውንም ቃል ስትፈታ [153] “ሲኦል ቃል በቃል በአንድ የተወሰነ ስፍራ የሚገኝ ስፍራን የሚያመለክት ቃል ሳይሆን ምሳሌያዊ አነጋገር ነው። አብዛኞቹ ሰዎች ሲሞቱ ወደዚህ ምሳሌያዊ ስፍራ እንደገቡ ይቆጠራል።”

ነገር ግን ቅዱሳን በገነት(መንግሥተ ሰማያት) ለዘላለም እንደሚኖሩት ሁሉ ኃጢያተኞችም ኃጢያታቸውን ተሸክመው ለዘላለም ሲኦል(ገሀነብ) ይገባሉ፣ ይህ እውነታም መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ በብዙ ስፍራዎች ላይ ተመልክቷል፡-

- <u>ሲኦል የሚባል የኃጢያተኞች ነፍስ የምትቀጣበት ስፍራ መኖሩን፣</u>

ከመነሻው ሲኦል የምትባለው መቀጣጫ ስፍራ ለሰው ልጆች አልተፈጠረችም፣ ሲኦል የሰው ልጆች ሳይፈጠሩ በፊት ላልታዘዙት መላዕክት የተፈጠረች መቀጣጫ ስፍራ ናት ይሁን እንጂ የሰው ልጆችም በማይታዘዙት መላዕክት መንገድ ሲሄዱ ወደዚህ መቀጣጫ ስፍራ እንዲወርዱ ተወሰነባቸው(ማቴ.25፡41)፣ ይህ የሰው ልጅ ወደ ሲኦል የሚወርድበት እውነታም ብዙ ስፍራዎች ላይ ተመልክቷል፡-

- ማቴ.25፡41 “በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተ ርጉማን፣ ለሰይጣንና ለመላዕክቱ ወደ ተዘጋጀ <u>ወደ ዘላለም እሳት</u> ከእኔ ሂዱ (ይላቸዋል)።”
- ማቴ.25፡46 “እነዚያ <u>ወደ ዘላለም ቅጣት</u>፣ ፃድቃን ግን ወደ ዘላለም ህይወት ይሄዳሉ።”
- ሉቃ.16፡23-24 “<u>በሲኦልም</u> ስቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ… እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ ማረኝ፣ በዚህ ነበልባል እሰቃያለሁና የጣቱን ጫፍ በውሀ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልአዛርን ስደድልኝ አለ …”
- ማቴ.13፡40-42 “… በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል … አመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፣ <u>ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል</u>፣ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፏጨት ይሆናል።”
- መዝ.9፡17 “<u>ኃጢያተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ</u>፣ እግዚአብሔርን የሚረሱ አህዛብ ሁሉ።”
- ሕዝ.32፡21 “የኃያላን አለቆች <u>በሲኦል ውስጥ ሆነው</u> ከረዳቶቹ ጋር ሆነው ይነግሩታል፤ በሰይፍም የተገደሉት ያልተገረዙት ወርደው ተኝተዋል።”

[153] Watch tower bible and tract society of Pennsylvania(2009)፣ **ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድነው?**፣ ገፅ 212

- ራዕ.20፡15 “በህይወትም መጽሐፍ ተፅፎ ያልተገኘ ማንኛውም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣለ።።”
- መዝ.49፡15 “ነገር ግን እግዚአብሔር ይቤቃኛልና ነፍሴን ከሲኦል እጅ ይቤዣታልና።።”

- <u>ቅጣቱም ለዘላለም መሆኑ</u>
  - ማቴ.25፡46 “እነዚያ <u>ወደ ዘላለም ቅጣት</u>፣ ፃድቃን ግን <u>ወደ ዘላለም ህይወት</u> ይሄዳሉ።።”
  - ዳን.12፡1-2 “በዚያም ዘመን … በምድር ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ህይወት፣ እኩሌቶቹ ወደ እፍረትና ወደ <u>ዘላለም</u> ጉስቁልና።።”
  - ሉቃ.3፡17 “መንሹ በእጁ ነው፣ አውድማውንም ፈፅሞ ያጠራል፣ ስንዴውንም በጎተራ ይከታል፣ ገለባውን <u>በማይጠፋ እሳት</u> ያቃጥለዋል አላቸው።።”
  - ራዕ.20፡10፡- “… ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባህር ተጣለ፣ <u>ለዘላለም እስከ ዘላለም</u> ቀንና ለሊት ይሰቃያሉ።።”

በዚህም ሲኦል የኃጢያተኛ ሰዎች ነፍስ ለዘላለም የምትቀጣበት ስፍራ መሆኑን እንመለከታለን ስለዚህ ትክክኛውን አስተምህሮ የሚከተለውን መንገድ በጊዜ መፈለጉ መልካም ነው።።

5.2.5. <u>አዲሱ የጂሆቫ መጽሐፍ ቅዱስ- “የአዲስ ዓለም ትርጉም”</u>

ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ቤተክርስቲያኗ በራስዋ ደንብና ስርዓት ላይ ተመርኩዛ ዋናውን መጽሐፍ ቅዱስ “በማስተካከል” ያዘጋጀችው “መጽሐፍ ቅዱስ” ሲሆን፣ በእንግሊዘኛ በ2013 “The new world translation” ተብሎ የታተመ ሲሆን በአማርኛ ደግሞ በ2014 ዓ.ም “አዲሱ ዓለም ትርጉም” ተብሎ ታትሟል(ሁለቱንም መጽሐፍ ቅዱሶች በሶፍት ኮፒ ከድርጅቱ ዌብ ሳይት(www.JW.org) ላይ በነፃ ማግኘት ትችላላችሁ።።)

ዋናው መጽሐፍ ቅዱስ፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ መጨመርም መቀነስንም እንደማይቻል ቢናገርም (ራዕ.22፡18-19, ዘዳ.4፡2, ዘዳ.12፡32 …) ቤተክርስቲያኒቷ ግን ይህን ተላልፋ በመጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ብዙ ለውጥ አድርጋለች፣ በዚህም ሙሉ በሙሉ የተሰረዙ፣ በከፊል የተሰረዙና የተቀየሩ የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍሎች እንመለከታለን።።

5.2.5.1. ሙሉ በሙሉ የተሰረዙ

በ"መጽሐፍ ቅዱሱ" ላይ በግልፅ እንደሚታየው ማቴ.17፡21, ማቴ.18፡11, ማቴ.23፡14, ማር.7፡16, ማር.9፡44, ማር.9፡46, ማር.11፡26, ማር.15፡28, ማር.16፡9-20, ሉቃ.17፡36, ሉቃ.23፡17, ዮሐ.8፡1-11, ዮሐ.5፡4, ዮሐ.7፡53, ሐስ.8፡37, ሐስ.15፡34, ሐስ.24፡7, ሐስ.28፡29, ሮሜ.16፡24 ... ሙሉ በሙሉ ተሰርዘው ወጥተዋል።

5.2.5.2. በከፊል የተሰረዙ

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የተወሰነው በመፃፍ ከፊሉን የመሠረዝ ስራ የተሰራባቸው ናቸው፣ ለናሙና የተወሰዱ ክፍሎች ብንመለከት፣

ተ.ቁ	የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል	ተሰርዞ የወጣው ቃል
1	ሉቃ.1፡28	"... አንቺ ከሴቶች መሃል የተባረክሽ ነሽ።"
2	ሐስ.24፡6	"... እንደ ህጋችንም እንፈርድበት ዘንድ ወደድን"
3	ሐስ.24፡8	"... ከሳሾቹንም ወደ አንተ ይመጡ ዘንድ አዘዘ፤"
4	ቆላ.1፡2	"... ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ..."

5.2.5.3. የተቀየሩ

የተቀየሩትን ቃላት በተመለከተ ቤተክርስቲያኗ "የተደረገው ለውጥ ጌታ፣ እግዚአብሔር ... የሚለውን በትክክለኛው የእግዚአብሔር ስም "ይሖዋ" ነው የቀየርነው" ብትልም በመጽሐፍ ቅዱሱ በዝርዝር እንደምንመለከተው የተደረገው ኤዲቲንግ ከዚህ ውጪ ብዙ ነገሮች ላይ ነው፣ በምሳሌ ብንመለከት፣

ተ.ቁ	ጥቅስ	በኦሪጅናሉ መጽሐፍ ቅዱስ	በጄሆቫ መጽሐፍ ቅዱስ
1	ዘፍ.1፡2	... የእግዚአብሔርም መንፈስ በውሀ ላይ ሰፍፎ ነበረ።	... የአምላክም ኃይል በውሀው ላይ ይንቀሳቀስ ነበር።
2	ዮሐ.1፡18	መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ስንኩዋ የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።	... አምላክን ያየው አንድም ሰው የለም፣ ስለእሱ የገለፀልን ከአብ ጎን ያለውና አምላክ የሆነው አንድያ ልጁ ነው
3	ፊሊጵ.2፡9	ከስም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው	ከሌላ ከማንኛውም ስም በላይ የሆነ ስም በደግነት ሰጠው
4	ሐዋ.4፡31	ከፀለዩም በኋላ ...	ምልጃ ካቀረቡም በኋላ...

መጽሐፍ ቅዱሱ “መጨመር፣ መቀነስ …” እየከለከለ ቤተክርስቲያኗ የመጽሐፉን ቃል በሙሉና በከፊል እየሰረዘችና ትርጉም በሚያዛባ መልኩ ቃላትን እየቀየረች አዲስ “መጽሐፍ ቅዱስ” ማዘጋጀቷ፣ የቤተክርስቲያኗን ኢክርስቲያናዊ አካሄድና የቤተክርስቲያኗን “የአዲስ ዓለም ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስን” የእግዚአብሔር ቃል አለመሆንን እንመለከታለን፡፡

<u>ማጠቃለያ(ጂሆቫ)</u>

የጂሆቫ እምነት ተከታዮች ከየትኛውም የክርስትና ተቋማት በላይ ስለ ኃይማታቸው ምስክርነት ሲተጉ ይታያሉ ነገር ግን “ምን ያህሉ ማኅበረሰብ ወደዚህ ኃይማኖት ተቀላቀለ” ተብሎ ሲታይ ኢምንት ነው ምክንያቱም ዛሬ ወንጌል በሰማ ማኅበረሰብ ውስጥ እነዚህን ከላይ ያየናቸውን ስህተቶች ይዞ ተቀባይነት ማግኘት አይቻልም፡፡ ተከታዮቻቸውም ስለ ኃይማኖታቸው ከሚሰጣቸው የ“ንቁ”፣ “መጠበቂያ ግንብ” እና መጽሐፍቶቻቸው ውጪ ስለሌላው እንዲያነቡ ስለማይፈቀድላቸው እንደ ጋሪ ፈረስ በመፅሄቶቹ ከሚሰጠው አቅጣጫ ውጪ እውነታውን ማወቅ አይችሉም፡፡

ከላይ በዝርዝር እንደተመለከትነውም የኃይማኖቱ አስተምህሮ በብዙ ስህተቶችን የተሞላ ነው፣ ከሁሉ ስህተቶች ደግሞ የከፋው በመንፈስ ቅዱስ ክብር ላይ የተሰነዘረው አስተያየት ነው፣ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚናገር አይሰረየለትም፣ በዚህም የዚህ ኃይማኖት ተከታዮች ዕድልም እንደ የሐዋርያት ቤተክርስቲያን ተከታዮች የተዘጋ ነገር ነው፡፡

5.3. <u>አድቬንቲስት(Adventism)</u>

[154] "የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን አስተምህሮ የተጀመረው በአሜሪካን ሀገር በ1830 ዓ.ም ዊሊያም ሚለር በሚባል የባፕቲስት ቤተክርስቲያን ሰባኪ ሲሆን አስተምህሮውም በግልፅ መነገር የተጀመረው ግን ከ1833 ዓም ጀምሮ ነው፣ የአስተምህሮው መነሻም ሚለር በዳን.8፡14-16 ላይ ተመስርቶ "የኢየሱስ ዳግም መምጫ ጊዜ በ1843 እና በ1844ዓ.ም መካከል ነው" በማለት በሰራው ስሌት ነው፣ የቤተክርስቲያኗ ስያሜ "አድቬንቲስት" የሚለው የእንግሊዘኛ ቃልም ከዚህ ጋር ተያይዞ የተሰጠ ስያሜ ሲሆን ትርጉሙም "የክርስቶስ መምጫ ቀርቧል" የሚል ነው።።

የሚለር ትንቢትም ከ1830 እስከ 1844 ዓ.ም ለ14 አመታት ሲጠበቅ ቆይቶ በተሰላው ጊዜ ኢየሱስ ዳግም አልመጣም፣ ትንቢቱም ባለመስራቱ በተከታዮቹ ላይ ትልቅ የሞራል ውድቀት ደረሰ፣ ቀኑም በቤተክርስቲያኗ ታሪክ "ትልቁ አሳዛኝ ቀን" ተባለ።።

ከዚህም በኋላ የሚለር አስተምህሮ ተከታዮች(ሚለራውያን) መካከል ከፍተኛ ክፍፍል ተፈጠረ፣ የተወሰኑት ወደነበሩበት የፕሮቴስታንትና የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ሲመለሱ ሌሎች ደግሞ እንደየልዩነቶቻቸው በየፊናቸው የተለያዩ የአድቬንቲስት ስም የያዙ አብያተ ክርስቲያናትን መሠረቱ፣ በዚህም የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት፣ አድቬንት ክርስቲያን ቸርች፣ ጥንታዊቷ አድቬንት ክርስቲያን ቸርች፣ የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን(ሰባተኛ ቀን)... የሚባሉ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተፈጠሩ።። ከክፍፍሉ በፊት የነበረችው ቤተክርስቲያን መስራች የነበረው ሚለር ግን በነዚህ ክፍፍሎች ውስጥ ያልገባ ሲሆን እስከሞተበት ጊዜ ድረስም አብያተ ክርስቲያናቱ ወደ አንድነት እንዲመጡ ሲጥር ነበረ።።

በክፍፍሉ ከተፈጠሩት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ዋነኛዋና ዛሬ በዓለም ዙሪያ ተስፋፍታ የምትገኘው "የሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት" ቤተክርስቲያን ስትሆን ቤተክርስቲያኗም በ1863 ዓ.ም በነ ኤለን ጂ ኋይት መሪነት በይፋ ተመሠረተች።። ኤለን የቤተክርስቲያኗ የጀርባ አጥንት ስትሆን ለቤተክርስቲያኗም ከ40 በላይ መጽሐፍትንና በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ፅሁፎችን አበርክታለች፣ ቤተክርስቲያኗም የኤለንን መጽሐፍት "የነቢይነት ስልጣን አላቸው" በማለት መጽሐፎቹን ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጎን ለጎን ትጠቀምበታለች፣ ቤተክርስቲያኗም በአሁኑ ጊዜ 22 ሚሊየን በላይ አባላት እንዳሏት ይነገራል።።

እነዚህ ከላይ የቀረቡትን ታሪኮች ስንመለከት የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ምሥረታ ከየትኛውም የኃይማኖት ተቋም ምሥረታ ታሪክ የተለየ መሆኑን ነው፣ ሌሎቹ የኃይማኖት ተቋማት የተመሠረቱት አዲስ "ነቢይ/ቅዱስ መጽሐፍ" ሲወርድላቸው ወይ በነበሩበት ቤተእምነት ውስጥ የተመለከቱትን "የስህተት" አስተምህሮ በትክክለኛ አስተምህሮ

[154] https://en.m.Wikipedia>wiki>Adventism

ለመተካት በሚል ነው፣ የዚህች ቤተክርስቲያን ምሥረታ መነሻ ግን ዊሊያም ሚለር “የክርስቶስ ዳግም መምጫ ጊዜ ተገለጠልኝ” በማለቱና በዚህም ሐሳቡን የሚደግፉ ሰዎች በሰሩት ስብስብ ነው።።

ነገር ግን ለቤተክርስቲያኗ መመሥረት መሠረት የነበረው የሚለር ስሌት ስህተት በመሆኑ ምክንያት ቤተክርስቲያኗ ከፍተኛ ውድቀት ውስጥ ገብታ ነበረ፣ በዚህም የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ቤተክርስቲያኗን ከመዘጋት ለማዳን የተለያየ ዘዴዎችን ተጠቀሙ፣ በዚህም በመጀመሪያ የሚለር ስህተቶች ላይ ማስተካያ ማድረግ፣ በመቀጠል ደግሞ ምዕመናኖቿ ወደ ፕሮቴስታንትና ካቶሊክ እንዳይሄዱባት እነዚህ ሁለቱ ኃይማኖቶች “በተሳሳተ መንገድ ላይ መሆናቸውን” የማስተማር አቅጣጫን ተከተለች፣ በነዚህ የቤተክርስቲያኗ መሪዎች ዘዴም ቤተክርስቲያኗ ከውድቀት ድና ወደ መስፋፋት ምዕራፍ ተመለሰች።።

እነዚህ መፍትሄዎች ቤተክርስቲያኗን ከመዘጋት ቢያድኗትም በውስጣቸው ብዙ ስህተቶችን ይዘዋል፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

5.3.1. <u>የሚለርን ስህተት “ማስተካከል”</u>

በሚለር ራዕይ አለመሳካት የደረሰውን ምስቅልቅሎሽ የማስተካከል ስራ በዋነኝነት የተሰራው የቤተክርስቲያኗ መሪዎች በሆኑት በሂራም ኤድሰን እና ኤለን ጂ. ኋይት ነው።።

ሂራም ኤድሰን(1806-1882) “በበቆሎ ማሳ ውስጥ ስሄድ ራዕይ አየሁ፣ ሚለር በተነበየው ቀን ኢየሱስ ተገልጦልኝ ከአንዱ የመንግሥተ ሰማያት ክፍል ወደ ሌላኛው ሲሄድ አየሁት፣ ስለዚህ ሚለር ቀኑን አልተሳሳተም ነገር ግን ሚለር ያላስተዋለው ኢየሱስ ያደረገው እንቅስቃሴ ወደዚህ ምድር ሳይሆን ወደ ሁለተኛ የመንግሥተ ሰማያት ክፍል መሄዱን ነው” በማለት አከራካሪውን ጉዳይ ማንም ሰው ማረጋገጥ ወደማይችለው ስፍራ አርቆ አስቀመጠው።።

ኤለን ጂ. ኋይትም “እኔም ራዕይ ተመልክቻለሁ” በማለት የሄራም ኤድሰንን ራዕይ የሚያጠናክር ቃል ጨመረች “ኢየሱስ ወደዚህ ሁለተኛው ክፍል የሄደው “የፍርድ ምርመራ” ለማድረግ መሆኑንና ይህም ለወደፊት ለፍርድ ሲመጣ ለመፍረድ እንዲያመቸው የሰዎችን መዝገብ ለመመልከት ነው” አለች።።

እነዚህ አስተምህሮዎች ለመጽሐፍ ቅዱሱ እንግዳ ሲሆኑ ይባሱኑም ከመጽሐፍ ቅዱሱ ጋር የሚጋጩና የኢየሱስን ክብር የሚነኩ አስተምህሮዎች ናቸው፣ ይህም፣

- ኢየሱስ ለሚፈርደው ፍርድ እንደ የሰው ዳኛ ገና “መዝገብ ቤት ገብቶ ይመረምራል” ማለቱ ስህተት ነው፣ ምክንያቱም፣
  - ኢየሱስ ሁሉን አዋቂ በመሆኑ የመዝገብ ምርመር ውስጥ አይገባም፣ ዮሐ.2፡25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.21፡17, ዮሐ.1፡48-50, ዮሐ.2፡24-25, ዮሐ.16፡30, ዮሐ.6፡64, ዮሐ.21፡17, ማር.2፡8 ...

- የሚተላለፈው ፍርድም ኢየሱስ ይቅርና ማንኛውም ሰው ዛሬውኑ በራሱ ላይ ሊያውቅ የሚችል መሆኑ፣

  ዮሐ.3፡18 “በእርሱ የሚያምን አይፈረድትም፣ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።”

- የሚፈረድበትና ነፃ የሚሆነው ከፍርድ በፊት ቀድሞውኑ በመንፈሳዊ ማህተም የታተመ በመሆኑ፣

  ኤፌ.4፡30 “ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታስዝኑ።”

በዚህም ኢየሱስ ምንም የመዝገብ ጥናት የማያስፈልገው መሆኑና በዚህም “የምርመራ ጊዜ” የተባለው ስህተት መሆኑን እንመለከታለን።

- ኢየሱስ ወደዚህ ስራው ገባ ከተባለ ከ1844 እስከ ዛሬ 2023 ድረስ ለ179 አመታት እዚያው መዝገብ ቤት ውስጥ እንደ ሰነፍ ዳኛ “እያጠና ነው” ማለቱ ክርስቶስን የሚሳደብ ለወንጌሉም እንግዳ የሆነ አስተምህሮ ነው። መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ከተነገረው ሐሳብ ውጪ እንግዳ አስተምህሮ ማስገባትም ደግሞ መርገምት ነው፣

  ገላ.1፡8-9 “ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፣ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን፣ አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ <u>የተረገመ</u> ይሁን።”

በዚህም “ስህተትን ስህተት” ማለቱ ሲሻል ስህተትን በሌላ “መልካም” ስህተት መሸፈን ውጤቱ የከፋ ነው። የሚገርመው ደግሞ ሦስቱንም የቤተክርቲያኒቱን መሪዎች ለስህተት የዳረገው ከመነሻው ሰው ኢየሱስ ተመልሶ የሚመጣበትን ቀን ሊያውቀው የማይችል መሆኑን አለመረዳታቸው ነበረ፣

- ፪ተሰ.5፡1-2 “ወንድሞች ሆይ፣ ስለ ዘመናትና ወራት ምንም እንዲፃፍላችሁ አያስፈልጋችሁም፤ የጌታ ቀን፣ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፣ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና።”
- ማቴ.24፡36-42 “ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት በቀር የሰማይ መላዕክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም፣ የኖህ ዘመን እንደነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና። በዚያች ወራት ከጥፋት ውሀ በፊት ኖህ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፣ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደነበሩ፣ የጥፋት ውሀ መጥቶ ሁሉን እስከወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፣ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል ... ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና <u>እንግዲህ ንቁ</u>።”

  ተመሳሳይ ሐሳብም ሉቃ.12፡39, ራዕ.3፡3, ራዕ.16፡15 ... ላይ ቀርቧል

በዚህም የኢየሱስ ዳግም መምጫ ቀን የሰው ልጅ ሊያውቀው አይችልም፣ በዚህም ሚለር "የኢየሱስ ዳግም መምጫ ቀን" ብሎ የሰራው ስሌት በምንም ዘዴ ሊስተካከል አይችልም።

5.3.2. ካቶሊክን ማንቋሸሽ

ፕሮቴስታንት ከካቶሊክ በመውጣቷና ከዚያም አድቬንቲስት ከፕሮቴስታንት ወጥታ ይህን ውርደት መከናነቧ በነማርቲን ሉተር ለተወገዘችው ካቶሊክ የአድቬንቲስት ስህተት "ሰርግና ምላሽ" ሆነ፣ ለዚህም የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን ራስዋን ከካቶሊክ ነቅራ ለመጠበቅና አባላቶቿም ወደ ካቶሊክ እንዳይፈልሱባት ለመጠበቅ ዘዴ ቀየሰች፣ ዘዴውንም በአስተምህሮ ላይ እንዳታደርግ ከመጀመሪያው ማርቲን ሉተር በካቶሊክ ስህተቶች ላይ ጠንካራ ሂሶች ስለሰነዘረ በአስተምህሮ ካቶሊክን ለመንቀፍ አላመቻትም፣ በዚህም በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ ጭፍን የስም ማጥፋት ዘዴን ተከተለች፣ በዚህም፣

- መጽሐፍ ቅዱሱ "አውሬው" የሚለው መንፈስ ባልተገለጠበት ጊዜ ጳጳሱን "አውሬው ናቸው"፣
- የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሱ የሚያወግዛት "አዲሲቱ ባቢሎን ናት"፣
- ሰንበትን በእሁድ ቀን የሚያከብር "የአውሬው ምልክት የተቀበለ ነው"፣

የሚሉ ከፍተኛ የስም ማጥፋት ስራዎችን በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ ሰነዘረች።

ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱሱ የሚያስጠነቅቀው አውሬም ሆነ "አዲሲቱ ባቢሎን" የተባለችው ከተማም ሆነ የአውሬው ምልክት የተባሉት በምዕራፍ 7 ላይ እንደተመለከተው በወቅቱ ያልተገለጡ መሆኑና መንፈሱ ሲገለጥም የሚሰራው ለሰባት አመታት/አንድ ሱባኤ(ዳን.9፡27) እንጂ ለዚህን ያህል ክፍለ ዘመናት አለመሆኑን ስንመለከት በካቶሊክ ላይ የተሰነዘረው ጥቃት ተራ አሉባልታ መሆኑን እንመለከታለን ይባሱኑ ደግሞ ከካቶሊክ በላይ አርማዋ 666 የሚመስለው የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን መሆኗ ነው።

5.3.3. ከፕሮቴስታንት በአስተምህሮ ተለይቶ መገኘት

ቤተክርስቲያኗ ከምሥረታዋ ከፕሮቴስታንት የወጣችበት ምክንያት "የኢየሱስ መምጫ ቀን" ላይ በተፈጠረ የሐሳብ ልዩነት ቢሆንም ክርስቶስ በተባለው ቀን ባለመምጣቱ ምክንያት የቤተክርስቲያኗ አባላት ጠቅልለው ወደ ፕሮቴስታንት እንዳይመለሱ፣ ቤተክርስተያኒቷ ከፕሮቴስታንት የሚለያትን የተለየ ዶክትሪን በማስቀመጥ የልዩነት መስመር ማኖር እንዳለባት ተመለከተች።

በዚህም ከፕሮቴስታንት ጋር የልዩነት መስመር ሊሰሩ የሚችሉ "የፕሮቴስታንት ስህተቶች" መፈለግ የግዴታ ሆነ ነገር ግን የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በወቅቱ በተሐድሶ የተመሠረተች አዲስ ቤተክርስቲያን ስለነበረች ለትችት የማትመች ሆነች፣ ነገር ግን ከተደረጉት ጥናቶች "የፕሮቴስታን ስህተት" ተብሎ ጎልቶ የወጣው "ፕሮቴስታንት የሰንበት ቀንን አታከብርም" የሚለው ሆነ፣ በዚህም የ"ሰንበትን ማክበር" ጉዳይ ቤተክርስቲያኗ

ከፕሮቴስታንት የምትለይበት ዋነኛ መለያ ሆነ፣ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ከፕሮቴስታንት የተለየችና የተሻለች መሆኗን ለማሳየት ስሟን "ሰባተኛው ቀን አድቬንቲስት ቤተክርስቲያን" እስከ ማለት ደረሰች፡፡

ሁለተኛው "ፕሮቴስታንትን በአስተምህሮ መለየት" ተብሎ የተሰራውና እምብዛም ተቀባይነት ያላገኘው አስተምህሮ "እግዚአብሔር የፍቅር አምላክ በመሆኑ ሰዎችን በሲኦል እሳት አይቀጣም" የሚለው ነበረ፣ በአስተምህሮውም [155] "ነፍስ ለዘላለም የምትቀጣበት ሲኦል/ገሀነም የሚባል ስፍራ የለም"፣ [156] "በዘሌ.16፡21-22 ላይ እንደተገለፀው ፍየል (Escape goat)፣ በመጨረሻው ቀን ኃጢያተኛ ሰው ለዘላለም ሲሞት(ሮሜ.6፡23) ኃጢያቱ ደግሞ በሰይጣን ላይ ተደርጎ ሰይጣንም የሰውየውን ኃጢያት ተሸክሞ ወደ ሲኦል ይወርዳል" የሚል ሐሳብ ነበረ፡፡ ነገር ግን ይህ መጽሐፍ ቅዱሱን ለያዘው ጎብረተሰብ እምብዛም አሳማኝና እትኩሮት የሚስብ ነገር አልነበረም፣ በ5.2.4 ክፍልም እንደቀረበው "የነፍስ ሞት" የሚባለው "የነፍስ መጥፋት" ማለት ሳይሆን የነፍስ ወደ ሲኦል መውረድ መሆኑ፣ ኃጢያተኛ ሰውም ስለራሱ ኃጢያት ሲኦል እንደሚገባ፣ በፍርድ ቀንም በሲኦል የተከማቸው ኃጢያተኛም ሆነ ዲያብሎስ ተጠርገው ገሀነም ውስጥ እንደሚጣሉ መጽሐፍ ቅዱሱ በማያሻማ መንገድ የሚናገር በመሆኑ ይህ ነጥብ እምብዛም አትኩሮት ሳቢ አልነበረም፤ በዚህም ጠንከር ያለው የልዩነት መስመር፣ የሰንበት ጉዳይ ሆኖ ቀጠለ፡፡

የቤተክርስቲያኗ መጠርያ የሆነውን፣ ዋናውን የልዩነት መስመር፣ የሰንበትን ጉዳይንም ጠለቅ አድርገን ስንመለከት እሱም ብዙ ስህተቶችን ይዟል፡፡ ከመነሻው "ሰንበት" ማለት "ዕረፍት" ማለት ነው፣ በስነ ፍጥረት ታሪክ ፈጣሪ የስድስቱን ቀናት የፍጥረት ስራው ሰርቶ ያረፈው በሰባተኛው ቀን ነው፣ በዚህም ፈጣሪ በሰባተኛ ቀን እንዳረፈው ሰዎችም በዚህ ቀን እንዲያርፉ አዘዘ፣

- ዘጸ.20፡11 "እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማይንና ምድርን፣ ባህርንም፣ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ በሰባተኛው ቀን አርፎአልና፤ ስለዚህ እግዚአብሔር የሰንበት ቀን ባርኮታል ቀድሶታልም፡፡"
- ዘጸ.20፡8 "የሰንበትን ቀን ትቀድሰው ዘንድ አስብ፡፡"
- ዘጸ.35፡3 "በማደሪያዎቻችሁ ውስጥ በሰንበት ቀን እሳትን አታንድዱ፡፡"

በዚህም የሰንበት ቀን ምንም ስራ የማይሰራበት የተቀደሰ የዕረፍት ቀን ነው፣ ያላከበረውም፡-

> ዘጸ.31፡14 "ስለዚህ ለእናንተ ቅዱስ ነውና ሰንበትን ጠብቁ ፣ የሚያረክሰው ሰው ሁሉ ፈፅሞ ይገደል፣ ስራንም በእርሱ የሰራ ሰው ሁሉ ከህዝቡ መካከል ተለይቶ ይጥፋ፡፡"

የሚደረስ ትልቅ ቅጣት አለው፡፡

---

[155] Ellen G. White, **The Great controversy**, chapter 33, page 531-550
[156] ibid, Chapter 23, page 422

ነገር ግን እነዚህ “የሰንበትን ቀን ቀድሰው፣ አከብረው፣ በዚያን ቀን አትስራ …” የሚሉት ጥቅሶች በሙሉ የሚጠቀሱት ከብሉይ ኪዳን ብቻ ነው፣ አዲስ ኪዳኑን ላይ እነዚህን ትዕዛዞች አንመለከትም ይባሱኑም ኢየሱስና ሐዋርያቱ በሰንበት ቀን ሲሰሩ ነበረ(ማቴ.12፡1-5, ማቴ.12፡10-12 …) በዚህም አይሁዶች ዮሐ.9፡16 “… ይህ ሰው ሰንበትን አያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም አሉ፡፡”፣ ሌሎቹ ደግሞ በዘጸ.31፡14 ህጋቸው መሠረት ዮሐ.5፡16 “… በሰንበት ይህን ስላደረገ አይሁድ ኢየሱስን ያሳድዱት ነበረ ሊገድሉትም ይፈልጉት ነበረ፡፡” ኢየሱስና ሐዋርያቱ ግን “የቀኑ ሰንበት ቀርቷል” ብለው ሲያስተምሩ ነበረ፣

- ማቴ.12፡12 “… ስለዚህ በሰንበት መልካም መስራት ተፈቅዶአል አላቸው፡፡
- ዕብ.4፡9 “እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ህዝብ ቀርቶላቸዋል፡፡”

የሰንበት ትዕዛዝ የተሰጠው በዋናው አስርቱ ትዕዛዛት ነው፣ ኢየሱስ ደግሞ “ሕግን ልሽር አልመጣሁም” እንዳለው ህጉን አልሻረም ነገር ግን በ4.2 ክፍል እንደተመለከተው አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ሲተካ የብዙ ቃላቶች አተረጓጎም ከፍ ተደረገ፣ በዚህም የፅላት፣ ቤተ መቅደስ፣ መስዋዕት፣ ሰንበት … የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን አተረጓገሞች መካከል ልዩነቶችን ተመለከትን፣ ከፍ የተደረገውን የሰንበት ትርጉም ስንመለከት፣

> ቆላ.2፡16-17 “እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፡፡ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ጥላ ናቸውና አካሉ ግን የክርስቶስ ነው፡፡”

በዚህም በብሉይ ኪዳን ቀን የነበረው ሰንበት፣ በአዲሱ ኪዳን፣ ህጉ ሳይሻር የሰንበቱ ትርጉም ወደ ክርስቶስ ከፍ ተደረገ፣ በዚህም በአዲስ ኪዳን ዘመን ሊታረፍበት፣ ሊቀደስ፣ ሊከበር … የሚገባው ክርስቶስ ኢየሱስ መሆኑን እንመለከታለን፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያኗ በፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ላይ ያነሳቸው ትችት ትክክል አለመሆኑና የቤተክርስቲያኗ መለያ እስኪሆን የደረሰው “ሰባተኛው ቀን” ጉዳይም የአዲሱ ኪዳን እውቀት ጎዶሎነት መሆኑን እንመለከታለን፡፡

ማጠቃለያ

በመግቢያው ላይ እንደተመለከትነው የአድቬንቲስት ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በሁሉም በተረጋገጠ በሚለር ውሸት ነው፡፡ በሚለር ውሸት ምክንያት በአድቬንቲስትነት የተሰባሰበው ማኅበረሰብ ወደ ሌሎች ኃይማኖቶች እንዳይሄድ እነ ኤለን ጂ. ኋይትና ሂራም ኤድሰን ደግሞ የሚለርን ውሸት በሌላ ሁለት ውሸቶች ለመሸፈን ሞከሩ፣ በርግጥ በውሸት የተጀመረ በእውነት ይጨርሳል ተብሎ አይታሰብም፣ ምክንያቱም መነሻው የውሸት አባት ነውና፡፡ በዚህም አዕምሮ ያለው ሰው በነዚህ የሚለር፣ ኤድሰንና ኤለን ሰንሰለታማ ውሸቶች መሠረት ላይ በቆሙት ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ሳይታለል በጊዜ ሚለር ወደወጣበት ፕሮቴስታንት ቢመለስ መልካም ነው፡፡

ምዕራፍ ስድስት

6. ፕሮቴስታንት

ከመቅድም ክፍል ጀምሮ በስፋት ስንመለከት እንደመጣነው “ፈጣሪ አምላክ የለም” የሚለው የኤቲዝም አስተምህሮ ስህተት መሆኑንና አማኞችን እንደሚሉት ፈጣሪ አምላክ መኖሩን፣ በመቅድም ክፍል እንደተመለከትነውም ፈጣሪ አምላክ የሚገኘው “የአብርሃም ኃይማኖቶች” በሚባሉት በኩል መሆኑን፣ ከነዚህ ውስጥም ከመጽሐፍ ቅዱሱ በኋላ ሌላ መጽሐፍ በማዘጋጀት አዲስ መንገድ የተከተሉት(እስልምና፣ ባኢ፣ ሞርሞን …) የተሳሳቱ መሆናቸውንና ትክክለኛው መንገድ የመጽሐፍ ቅዱሱ መንገድ መሆኑን ተመልክተናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱንም ከያዙት ውስጥ፣ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሱ ግለሰቦች እጅ እንዲገኝ ካደረጉበት ከ9ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ በተለያየ ፍልስፍና የተመሠረቱት የሐዋርያት፣ የጂሐቫና የአድቬንቲስት አስተምህሮዎች በተሳሳተ መንገድ መሄዳቸውን በስፋት ተመልክተናል፡፡

እንደዚሁ የኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በጊዜ ሂደት በገቡባት የሰይጣን ሤራዎች ምክንያት በተሳሳተ መንገድ እየሄደች መሆኗን ተመልክተናል፣ እነዚህን የቤተክርስቲያኗ ስህተቶችም ለማረም በተሀድሶ መንፈስ የተነሳችው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን የተከተለችው መንገድ ይህም፣ ክርስቲያናዊ መመርያ የ66ቱ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ፣ መመለክ ያለበት እግዚአብሔር ብቻ፣ መዳን በኢየሱስ በማመንና በጸጋ ብቻ የሚለው መንገድ ብቻ ትክክል መሆኑን በብዙ ማስረጃዎች በስፋት ተመልክተናል፡፡

መጽሐፍ ቅዱሱን አስተውሎ ለተመለከተ በዘመናት ውስጥ አንድ የታሪክ ድግግሞሽ አለ፣ ሰይጣን የስህተት ትምህርቶችን ወደ ቤተክርስቲያን በማስገባት ሰዎችን ከትክክለኛው መንገድ ሲያስወጣ የነበረበትና እግዚአብሔር ደግሞ ቅዱሳንን ተጠቅሞ ተሐድሶን በማንቀሳቅስ፣ በሰይጣን የገቡትን እርኩሰቶችን ጠራርጎ ሲያወጣና ቤቱን ሲያድስ የነበረበት ተደጋጋሚ የታሪክ ሂደት(ዘጸ.32፡20, መሳ.6፡25-30, 2ነገ.10፡26-28, 2ነገ.23፡4, 2ዜና.29፡5, 2ዜና.34 …)፡፡

እግዚአብሔር አሳሳች ትምህርቶች እንዲስተካከሉ ተሐድሶ ሲያስነሳ እንደነበረው በ16ኛው ክፍለ ዘመንም እንደነ ጢተር ዋልዴስ፣ ጆን ዋይክሊፈ፣ ጆን ሁስ፣ ማርቲን ሉተር… የመሳሰሉ ጠንካራ የኃይማኖት መምህራኖችን በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ በተሐድሶ መንፈስ አስነሳ፡፡ ከነዚህ ውስጥም [157] በጀርመን ሀገር በነማርቲን ሉተር የተነሳው የተሐድሶ እንቅስቃሴ 95 ተሐድሶ የሚፈልጉ የቤተክርስቲያኗን ስህተቶች በማሳየት በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ውስጥ ያለውን የተሳሳተ አሰራር ግልፅ አደረገ፣ እንቅስቃሴውም

[157] https://en.m.Wikipedia>wiki>Protestantism

እነዚህን ስህተቶች ማረም በሚያስችል መልኩ፣ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንን በአምስት የእምነት ዋልታዎች/Five Solae ላይ መሠረተ፣ ይህም [158]

- “መመሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ(Sola Scriptura)፣
- አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ(Soli Deo gloria)፣
- ድነት በጸጋ(Sola Gratia)፣
- ድነት በእምነት(Sola Fide) እና
- ድነት በኢየሱስ ክርስቶስ(Solus Cristos) ብቻ”

በዚህም የተሐድሶ ቡድኑ ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ዘንድ ያለውን ኮተት ቆርጦ በማስወገድ፣ አዲስ ኪዳናዊ መሠረት ላይ የመጀመርያዋን የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በ1517 ዓ.ም መሠረተ።።

የእነ ሉተር ቡድን ያነሷቸው 95ቱ የተሐድሶ ነጥቦችና አምስቱ የቤተክርስቲያኗ የእምነት ዋልታዎችም ግልፅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦች በመሆናቸውም በወቅቱ በአብዛኛው ክርስቲያን ዘንድ በአንዴው ነበር ተቀባይነት ያገኙት፤ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ያለ ምንም ጦርነት፣ አስተባባሪ ሰውና መዋቅር ነበረ በአጭር ጊዜ ውስጥ፣ በግለሰቦች እንቅስቃሴ ብቻ ከዓለም ጥግ እስከ ጥግ መዳረስ የቻለችው።። በዚህም በአሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያኗ ከጥንታዊያኑ የኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ እስልምና፣ ሂንዱ ... ኃይማኖቶች በሚተካከል መልኩ እስከ አንድ ቢሊየን የሚገመቱ አባላት የያዘች ሲሆን የመስፋፋት ፍጥነቷ ደግሞ ከሁሉም ኃይማኖቶች ልቆ ነው የሚታየው።።

በዚህ ምዕራፍም በዚህች የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያንን ስር ያሉትን አብያተ ክርስቲያናትንና ሰይጣን በህይወት በመኖሩ ምክንያት ቤተክርስቲያኗን እንደ ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ከመንገድ ሊያስወጧት የሚችሉ፣ በጊዜ ሊታረሙ የሚገቡ የተሳሳቱ አሰራሮችንና ክፍተቶችን በስፋት እንመለከታለን፣ በዚህም፡-

- ፕሮቴስታንት ኃይማኖት ስር የሚመደቡ አብያተ ክርስቲያናት፣
- አብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ እየታየ ያለ የአሰራር ችግር፣
- በፕሮቴስታንት ላይ እየተነሱ ያሉ ትክክኛና የተሳሳቱ ሂሶች፣
- የቤተክርስቲያኗ ድክመቶች፣

በስፋት እንመለከታለን።።

[158] https://en.m.Wikipedia>wiki>Protestantism/Five Solae

6.1. <u>በፕሮቴስታንት ኃይማኖት ስር የሚመደቡ አብያተ ክርስቲያናት</u>

የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በነማርቲን ሉተር ኪንግ መሪነት በተነሳ የተሐድሶ እንቅስቃሴ ስትመሠረት የተሐድሶ ነጥቦቹ ግልፅና አሳማኝ ስለነበሩ ተሐድሶው ያለመስራቾቹ አስተባባሪነት ነበረ በየስፍራው እንደ ሰደድ እሳት የተቀጣጠለው፣ በዚህም በአውሮፓና በአሜሪካ የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት ተቋቋሙ፣ ሉትራኒዝም፣ አንግሊካኒዝም፣ ካልቪኒዝም፣ ሜቶዲዝም፣ ፕሪስብቴሪአኒዝም ... የሚባሉ አብያተ ክርስቲያናት በየሀገራቱ እየተፈጠሩ ሄዱ፡፡ በሀገራችንም ከነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በተነሱ ሚሽነሪዎች የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ ስፍራዎች ላይ መስፋፋት ጀመሩ፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የሚገኙ ሲሆን እነዚህ አብያተ ክርስቲያናትም ከአደረጃጀት አንፃር በአምስት ይከፈላሉ፣ እነሱም፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት፣ የኢትዮጵያ ቪዥነሪ አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት፣ የጴንጤቆስጤ አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት፣ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስና የኢትዮጵያ ቃለ ህይወት ቤተ ክርስቲያን በመባል ይታወቃሉ፡፡

ከነዚህ ውስጥ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ስር የተደራጁት ሙሉ ወንጌል፣ መሠረተ ክርስቶስ፣ የህይወት ብርሃን ... የመሳሰሉት በደርግ ዘመን የተመሠረቱ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ ሌሎቹ በደርግ ዘመን የተመሠረቱት መካነ ኢየሱስ እና የቃለ ህይወት አብያተ ክርስቲያናት ግን በአሁኑ ጊዜ ራሳቸውን ከአብያተ ክርስቲያኑ ጎብረት አግልለዋል፣ እነዚህ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናትም በአባላት ብዛትም በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን 90% የፕሮቴስታንት ማኅበረሰብን ይወክላሉ፡፡

የእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት የልዩነት ምክንያትም ሚሽነሪዎች ተሐድሶውን ወደ ኢትዮጵያ ሲያስገቡ በተደራጀ መንገድ ሳይሆን በግለሰቦች በሚመሩ ቡድኖች በመሆኑና እነዚህ ቡድኖችም በተሰማሩበት ክፍለ ሀገር የተለያዩ አብያተ ክርስቲያናትን በመመሥረታቸው ምክንያት ሲሆን እንደነ ሙሉ ወንጌል ያሉት ሀገር በቀል አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ "የሚሽነሪዎቹ አስተምህሮ ትክክለኛ ወንጌል ቢሆንም ካሪዝማቲክ(የጲጋ ስጦታ) መንገድ የተከተለ አይደለም" በማለት ቤተክርስቲያንን በካሪዝማቲኩ መንገድ የመሠረቱ ናቸው ነገር ግን በሂደት ሁሉም፣ በሚሽነሪዎች የተመሠረቱት አብያተ ክርስቲያናት እንኳን፣ ይህንኑ የካሪዝማቲኩን መንገድ ተቀላቅለዋል፡፡

ከነዚህ ቀደምት አብያተ ክርስቲያናት መካከል የመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን ከሁሉም የምትለይ ስትሆን፣ ቤተክርስቲያኗ በኦርቶዶክስ/ካቶሊክ ዘንድ ያለውን የህፃናትን ጥምቀት፣ ጥምቀትን በውሀ በማበስ የማከናወንና የቅስና ሹመት ትውፊቶችን ይዛለች፤ ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ግን ሰዎችን የሚያጠምቁት አስተምረው ነው፣ ጥምቀትን የሚያከናውኑትም

ሙሉ በሙሉ ውህ ውስጥ በማስገባት ሲሆን በቄስ ፋንታም የፓስተር/መጋቢ ሹመትን ይጠቀማሉ፡፡

“ባለራዕይ” እና የጴንጤቆስጤ አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት የሚባሉት ከደርግ ውድቀት በኋላ በግለሰቦች የተመሠረቱት አዳዲስ አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈጣን እንቅስቃሴ በማድረጋቸው ይታወቃሉ፡፡ እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት እጅግ ብዙ ሲሆኑ በየጊዜውም ቁጥራቸው እየጨመረ ይገኛል፣ የመብዛታቸው ምክንያትም ከአስተምህሮ ልዩነት ወይ ከሚሺነሪዎች ልዩነት ወይ ከካሪዝማቲክነት ጉዳይ ጋር የተያያዘ ሳይሆን “በተቀበሉት ራዕይ”፣ በነበሩበት ቤተክርስቲያን በደረሰባቸው መገፋት፣ ለኪራይ ሰብሳቢነት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር(ከታች በዝርዝር እንመለከተዋለን) እና በመሳሰሉት ምክንያቶች ነው፡፡

6.2. <u>አብያተ ክርስቲያናቱ አካባቢ እየታየ ያለ የአሰራር ችግር</u>

የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን የተመሠረተችባቸው የተሐድሶ ነጥቦች ግልፅና አሳማኝ ስለነበሩ የተሐድሶ ነጥቦቹ ያሳመናቸው ሰዎች በየስፍራው አብያተ ክርስቲያናትን መትከል ጀመሩ፣ ይህም አሰራር የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት እንደ ኦርቶዶክስና ካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ቤተክርስቲያኗ በአንድ መዋቅር ስር እንዳትሰባሰብ አደርጓታል፡፡

ይህ ሁኔታም በቤተክርስቲያኗ ላይ ብዙ በጎና መጥፎ አጋጣሚዎችን ፈጥሮባታል፣ በጎ አጋጣሚዎቹ የቤተክርስቲያኗ የተሐድሶ እንቅስቃሴ በአንድ ጊዜ ዓለምን እንዲያጥለቀልቅ ያደረገ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ቤተክርስቲያን ለአፋኝ ሜራዎች እንዳትጋለጥና አንዱ ሲደክም ሌላው አልፎ የሚሰራበትን መልካም አጋጣሚ ፈጥሯል፡፡ የአካሄዱ መጥፎ ጎን ደግሞ አብያተ ክርስቲያናት ያለምንም ተጠያቂነት በየስፍራው በግለሰቦች እየተከፈቱ ያሉበት ሁኔታ እየፈጠረ ያለው ችግር ነው (ከታች በስፋት ቀርቧል)፡፡

በሀገራችን የሚገኙት ሁሉም የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት፣ ማርቲን ሉተር ባስቀመጣቸው፣ በአምስቱ የእምነት ዋልታዎች ላይ አንድ ቢሆኑም ከአደረጃጀትና አደረጃጀቱን ተከትሎ በመጣው የአሰራር ልዩነት ምክንያት <u>በተለምዶ</u> በሁለት ይከፈላሉ፤ “ወንጌላውያን” እና “ባለራዕይ” በሚል፣ በተለምዶ “ወንጌላውያን” የሚባሉት የመካነ ኢየሱስና የቃለ ህይወት አብያተ ክርስቲያናት ጨምሮ በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ስር የተደራጁት <u>ቀደምት</u> አብያተ ክርስቲያናት ሲሆኑ “ባለራዕይ” የሚባሉት ደግሞ <u>ከደርግ ውድቀት በኋላ የተደራጁ</u> የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናትና የጴንጤቆስጤ አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት ስር ያሉ አዳዲሶቹ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡

ይህ ነባሮቹን “ወንጌላውያን” አዳዲሶቹን ደግሞ ”ባለራዕይ” ተብሎ የሚጠራበት ተለምዷዊ አጠራርም ከታች ለምንመለከተው ጉዳይ አመቺ ስለሆነ ይህንን ተለምዷዊ አጠራር እንጠቀማለን፡፡

የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናትና የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚታየው ዋናው ልዩነት የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት የተደራጁት እንደሀገር በተዘረጋው ኃይማኖታዊ መዋቅር ስር ሲሆን የእያንዳንዱ ቤተክርስቲያን የበላይ አስተዳደርም በቤተክርስቲያኗ ምዕመን የሚመረጡ ሽማግሌዎች ናቸው፣ የቤተክርስቲያኗ አስተዳዳሪ ፓስተር/ቄስም ተጠሪነቱ ለቤተክርስቲያኗ ሽማግሌዎች ነው፡፡ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ የሚመሠረቱት በአንድ ግለሰብ ሲሆን የቤተክርስቲያን ሽማግሌ የሚባሉትም የሚመረጡት ሆነ የሚመሩት በባለራዕዩ ነው፡፡

ይህ የሁለቱ አብያተ ክርስቲያኑት የአሰራር ልዩነትም ወንጌላውያኑ ጋር ልክ እንደ ሶሻሊዝም የኮማንድ ኢኮኖሚ ስርአት ከመጠን ያለፈ የአሰራር ጥብቅነት የተፈጠረ ሲሆን ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ደግሞ እንደ ካፒታሊዝሙ ነጻ ገበያ ስርአት ከመጠን ያለፈ የአሰራር ልቅነት እንዲፈጠር አድርጓል፣ የሁለቱም መልካምና መጥፎ ጎን ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡፡

6.2.1. <u>ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት</u>

የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በደርግ ዘመን በጭንቅ ውስጥ ተመሥርተው በጭንቅ ውስጥ ያለፉ እንደመሆናቸው መጠን አደረጃጀታቸውም እንደዚሁ ጥብቅ ነው፣ አሁንም የሚከተሉት ይህንኑ ጥብቅ አሰራር ነው፣ በዚህም ምንም እንኳን አሰራሩ፣

- ለአጭበርባሪዎች ምንም ክፍተት የማይሰጥ፣
- "ገብያ መር" መርህን የተከተለ ባለመሆኑ አዳዲስ ሰዎች ገብቷቸው አምነው ወደ ክርስትና እንዲቀላቀሉ የሚያደርግና ያመኑትም በትክክለኛ መንፈሳዊ እድገት ውስጥ እንዲያልፉ የሚያደርግ፣
- የትኛውም አገልጋይ ህዝቡን መስሎ እንዲኖር የሚያደርግ፣

ቢሆንም ይህ አካሄድ ደግሞ ሌሎች የጎንዮሽ ችግሮች አሉበት፣

- ጥብቅ ቢሮክራሲው መሪዎችን የደንብና የመመሪያ ባርያዎች በማድረግ መሪዎቹ እንደ ባለራዕዮቹ አብያተ ክርስቲያናት በባለቤትነት ስሜት አዳዲስና ከአካባቢው ጋር የሚመጥኑ አካሄዶችን ፈጥረው እንዳይንቀሳቀሱ ይዟቸዋል፣ ይህ ደግሞ ወንጌል ሊሄድ በሚገባበት ፍጥነት እንዳይሄድ አድርጓል፣
- አንድን ሰው ወደ አገልጋይነት ለማሳደግ የተቀመጡት መስፈርቶች እጅግ አድካሚ በመሆናቸው ይህ አሰራር በተለየ ቅባት የሚነሱ ወጣቶች ወደ አገልግሎት አንገታቸውን ማስገባት እንዳይችሉ አድርጓል፣ በዚህም ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር መተላለፍ እየተፈጠረ ይገኛል፣
- በስራና በተለያዩ ምክንያቶች ከሌላ ስፍራ የሚመጡትን አማኞች ለመቀበል "ከሊራንስ አምጣ፣ በኛ ቤተክርስቲያን መርህ ተምረህ ካልተጠመቅክ ..." የሚሉ መስፈርቶችን ማስቀመጣቸው ብዙዎችን በቤተክርስቲያን እንዳይጠለሉ አድርጓል፣

- አዲስ ቤተክርስቲያን ለመትከል የተቀመጠው መስፈርትና ቅድመ ሁኔታ የህዝብ መብዛትና የከተማ መስፋፋትን ግምት ውስጥ ያላስገባ በመሆኑ በርቀት ያሉ ምዕመኖቻቸው አማካይ ስፍራ ቤተክርስቲያን ወደሚከፍቱ ባለራዕይ አብያተክርስቲያናት እንዲኮበልሉ አድርጓል፣

እነዚህ ችግሮችም የወንጌል ስርጭቱን ፍጥነት አፍኖ ይዟል።

6.2.2. <u>ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት</u>

ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት በካፒታሊዝሙ "ጉብያ መር" መርህ፣ ቤተክርስቲያን ያልተከፈተበት አማካይ ስፍራ በመመልከት ቤተክርስቲያን መክፈታቸው፣ በቀላል መስፈርቶች ሰዎችን ወደ አገልጋይነት ማምጣታቸው፣ ከሌላ ስፍራ የሚመጡ ምዕመናንን "ከሊራንስ፣ እኛ አስተምረንህ ካላጠመቅንህ ..." ሳይሉ መቀበላቸው፣ አገልግሎታቸውም የህዝቡን የልብ ትርታ ብቻ በመመልከት በትንቢትና ፈውስ ላይ ብቻ ማተኮራቸው፣ ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያናቸው እንዲመጡ ሰፊ ራስን የማስተዋወቅ ስራ መስራታቸው፣ ወንጌል በሳተላይት ዲሽ እንዲሰራጭ ማድረጋቸው ... ብዙ የተዳከሙና ግራ የተጋቡ አማኞችን በማነሳሳት ወደ ቤተክርስቲያን እንዲመለሱ ከማድረግ አልፎ አጠቃላይ የፕሮቴስታንት ማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ መነሳሳት እንዲፈጠር አድርገዋል፤ በተለይ ደግሞ ጀማሪ መስራቾች ቤተክርስቲያናቸውን ለማሳደግ የሚያደርጉት ትጋት ሌሎችም ክርስቲያኖችም ዘንድ ትልቅ መነሳሳት እንዲፈጠር አድርጓል።

ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ያለውን ችግር ስንመለከት ችግሩ ዘርፈ ብዙ ነው፣ "ባለራዕይ" የሚለው ስያሜ የተሳሳተ ስያሜ የሆነበትን፣ አብያተ ክርስቲያናቱም የታላቁ ተልዕኮ አካል ያልሆኑበትን፣ አንዳንድ ስፍራዎች ላይ ደግሞ ቤተክርስቲያን የወንበዴዎች ዋሻ የተደረገችበትን፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎችን የተስፋፋበትን፣ የቤተክርስቲያን ክብር የተዋረደበትና ባለራዕይ የሚባሉት ሰዎችም ወደ መመለክ ደረጃ እየሄዱ ያለበትን ሁኔታ ተፈጥሯል፣ ሁሉንም ቀጥለን እንመለከታለን፣

6.2.2.1. <u>የስያሜ ችግር</u>

የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ችግር "ባለራዕይ" ከሚለው ስያሜ ይነሳል፣ ስያሜው እንደ መጽሐፍ ቅዱሱም እንደ አመራር ሳይንሱም የተሳሳተ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ፣

> ነሳሙ.9:9 "ዛሬ <u>ነቢይ የሚባለው ቀድሞ ባለራዕይ ይባል ነበርና</u> አስቀድሞ በእስራኤል ዘንድ ሰው እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሲሄድ፣ 'ኑ ወደ ባለራዕይ እንሂድ ይባል ነበር።"

በዚህም እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ባለራዕይ ማለት ድሮ የቀረ የነቢይ መጠሪያ ስም እንጂ ቤተክርስቲያን መስራች ማለት አይደለም።

በአመራር ሳይንሱም ስንሄድ ባለራዕይ የሚሆነው ባለቤት ነው፣ የቤተክርስቲያን ባለቤት ደግሞ እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም፣ እግዚአብሔርም ለቤተክርስቲያን ያስቀመጠው ራዕይ(vision) "ወንጌል ለዓለም ህዝብ ማድረስ" የሚል ሲሆን እያንዳንዱ አገልጋይ የሚያገለግለው በዚህ ራዕይ ስር በተቀመጠው በታላቁ ተልዕኮ(Mission) ውስጥ ሚሽነሪ በመሆን ነው፡፡ ዛሬ እያንዳንዱ አገልጋይ የሚሰራው ስራ የተጀመረውን ስራ የማስቀጠል ስራ እንጂ አዲስ ራዕይ አዘጋጅቶ አዲስ ስራ የሚጀምርበት አሰራር አይደለም፤ የኛ ትውልድ ይቅርና የፐሮቴስታንት ተሐድሶን ወደ ሀገራችን ያስገቡት እንኳን ሚሽነሪዎች እንጂ ቪዢነሪዎች አልነበሩም፡፡ "ታላቁ ተልዕኮ" የሚባለው ማቴ.28፡19-20 ላይም "ሂዱና" የሚለው ቃል ይህንኑ የሰዎች በባለራዕይነት ሳይሆን የሚሽነሪነት አገልግሎት የሚያመለክት ቃል ነው፡፡

አንዳንዶቹ ከዚህ ሐሳብ ጋር ላለመጋጨት በማለት የቃሉን አተረጓጎም ለወጥ በማድረግ "ባለራዕይ" የሚለውን ቃል "ይህንን ቤተክርስቲያን በዚህ ስፍራ እንድተክል ራዕይ ተሰጥቶኝ ነው" በሚለው ሲተረጉሙ ይሰማል ነገር ግን አብዛኞቹ ባለራዕዮቹ ቤተክርስቲያናቸውን የሚመሠርቱት በአካባቢው ሌላ የፐሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በስራ ላይ እያለች መሆኑ እያወቁ፣ የሚከፍቱበት ስፍራም በገብያ መር እስትራቴጂ ብዙ አማኞችን ማግኘት በሚችሉበት በትላልቅ ከተሞች አማካይ ስፍራዎች እየፈለጉ መሆኑና "በዚህ ስፍራ እንድከፍት ራዕይ ተሰጠኝ" የሚለውን አልፈው በሌሎች ስፍራዎችም ቅርንጫፎችንም እየከፈቱ የሚሄዱበትን እውነታ ስንመለከት ለወጥ የተደረገው አተረጓጎም አሳማኝ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

ነባራዊውን እውነታ ስንመለከት የአብዛኞቹ ምሥረታ ምክንያት ከእግዚአብሔር በመጣ ራዕይ ሳይሆን፣

- አገልጋዮች በተለያየ ምክንያት ከክፍለ ሀገር ወደ ትላልቅ ከተሞች ሲመጡ በአካባቢው በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ማገልገል አለመቻላቸው፣
- ሰውን በስጋ ዓይን በሚመዝኑት በእነኤልያብ የተገፉ ዳዊቶች(1ሳሙ.17፡28)፣
- አገልጋዮች በላያቸው ላይ ትልቅ ጸጋ ሲገለጥ በሽማግሌዎች ስር ከመመራት "የራሴን በራሴ" ከሚል ስሜት በመነሳት፣
- አገልጋዮች በነበሩበት ቤተክርስቲያን የሚያገኙት የኢኮኖሚ ጥቅማ ጥቅም አነስተኛ በመሆኑ ኢኮኖሚያቸውን ለማሻሻልና ከተቻለም በዚሁ ስራ ለመክበር፣
- ከላይ የተመለከቱት መስራቾች በቀላሉ ቤተክርስቲያን አቁመው "ፀዳ" ያለ ህይወት መጀመራቸውን በመመልከት "ማን ከማን ያንሳል" በሚል ስሜት በሚነሱ አገልጋዮች ነው፣

ይህም እውነታ "የእግዚአብሔር ራዕይ" ከሚባለው በላይ "የግለሰብ ራዕይ" የሚለውን እውነታ ያሳያል፡፡

6.2.2.2. <u>የታላቁ ተልዕኮ አካል አለመሆን</u>

የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናትን ባለባቸው የአሰራር ችግር ምክንያት የዋናው ተልዕኮ "ታላቁ ተልዕኮ"(ማቴ.28፡19-20) አካል መሆን አይችሉም፣ ምክንያቱም፡-

- አብያተ ክርስቲያናቱ ያለባቸውን ከፍተኛ ወጪ ለመሸፈን በሚከተሉት "ገቢያ መር እስትራቴጂ" ቤተክርስቲያን የሚከፍቱት ሰፊ ገቢያ(ብዙ አማኝ) ማግኘት በሚችሉበት ትልልቅ ከተማ አማካይ ስፍራዎች ላይ በመሆኑ፣ አብያተ ክርስቲያናቱ በአዳዲስ የወንጌል ግንባሮች ላይ አንመለከታቸውም፣ ይህ እውነታም አብያተ ክርስቲያናቱ ወንጌል የማስፋት ስራ(የታላቁ ተልዕኮ) አካል አለመሆናቸውን ያሳያል፡፡
- አብያተ ክርስቲያናቱ የተመሠረቱት በአንድ ሰው ሆኖ የቤተክርስቲያኗም ባለቤት ይህ ግለሰብ መሆኑ፣
  - በመስራቹ ስር የሚሰሩት አገልጋዮች ከተከታይነት ይልቅ ተቀጣሪነት መንፈስ እንዲሰሩ የሚያደርግና እነሱም የሰውን ከመከተል የራሳቸውን ቤተክርስቲያን የሚተክሉበትን መንገድ እንዲያስቡ ያደርጋቸዋል፣ ይህ እውነታ ደግሞ ባለራዕዩ ተከታይ ማፍራት እንዳይችል ያደርገዋል፣ ተከታይ ማፍራት ያልቻለ "ባለራዕይ" ደግሞ የራሱ ራዕይ ቢኖረው እንኳን ራዕዩን ማሳካት አይችልም፣
  - ቤተክርስቲያንን የግለሰብ ድርጅት በማድረግ ቤተክርስቲያን እንደ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን ከመቆም ይልቅ ህልውናዋ በአንድ ሰው ላይ እንዲንጠለጠል አድርጓል፣ በዚህም ባለራዕይ ያለና የሌለ ቀን የቤተክርስቲያኗ ገፅታ የተለያየ ነው፤ ባለራዕዩ ውጭ ሀገር ቢሄድ፣ ቢታመም፣ ከክርስትናው ቢወድቅ፣ ቢሞት … ቤተክርስቲያኗም አብራ እንደዚያው ትሆናለች፡፡

  እነዚህ እውነታዎች ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱ የሚያወግዘው "የእከሌ ቤተክርስቲያን"(1ቆሮ1፡11-13) አሰራር ማሳያ ነው፡፡
- አብያተ ክርስቲያናቱ በሚከተሉት "ገበያ መር" እስትራቴጂ በፈውስና ትንቢት ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ ምዕመናኖቻቸው ፅኑ ክርስቲያናዊ መሠረት እንዳይኖራቸው አድርጓል፣ ይህም ደግሞ፣
  - ምዕመኑ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በ"ሰጥቶ መቀበል" መርህ እንዲመሠረት አድርጓል፣ በዚህም ምዕመኑ የተነገረው "ትንቢት" ሆነ "ፈውስ" ሳይፈፀም ሲቀር ወይንም ሲዘገይ ዋናውን ነገር ይህም "የነፍስን መዳንና የእግዚአብሔር ልጅነትን" እንደዋዛ ጥሎ ሲሄድ ይታያል፡፡
  - ወንጌልን በእውቀት መመስከር የማይችሉ ክርስቲያኖችን እየፈጠረ ይገኛል(1ጴጥ.3፡15)፣

  እነዚህም እውነታዎች ደግሞ ሆሴ.4፡6 "ህዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቶአል…" ምክንያት እየሆኑ እንዳለ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናቱ ወንጌልን ወደ አዲስ ስፍራ የማስፋት ስራ የሚሰሩ አለመሆናቸው፣ የሚሰሩትንም ስራ ከመስራቹ ሁኔታ በላይ አስፍቶ የሀገራዊው ሆነ የዓለማቀፋዊው የወንጌል ስራ አካል ማድረግ የማይቻል መሆኑና ባሉበት ሁኔታም ከነሱ ጋር ያሉት ምዕመናኖች ፅኑ ክርስቲያናዊ መሠረት የሌላቸው መሆኑን ስንመለከት፤ የባለራዕይ ቤተክርስቲያናት የ"ታላቁ ተልዕኮ" አካል አለመሆናቸውንና በዚህም የነዚህ የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አደረጃጀት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አለመሆኑን እንመለከታለን፡፡

6.2.2.3. <u>ቤተክርስቲያን የዘራፊዎች ዋሻ የተደረገችበት</u>

ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት በችግር ጊዜ ድጋፍ የሚያደርግላቸው የበላይ መዋቅር የሌላቸው በመሆኑ፣ በሚመርጡት ማዕከላዊ ስፍራ ምክንያት ባለባቸው ከፍተኛ የቤት ኪራይ፣ ቤተክርስቲያኗ አዲስ እንደመሆኗ ለቤተክርስቲያኗ ዕቃ ግዢ የሚያስፈልገው ከፍተኛ ወጪ፣ ለአገልጋዮች ደሞዝ፣ ራስን ለማስተዋወቅ፣ በኮንፍራንሱ ለሚጋበዙ ትልልቅ አገልጋዮች የሚከፈለው ትልቅ ገንዘብ፣ ለትልልቅ እስፒከሮች፣ ኪቦርዶችና ሳዎንድ ሲስተሞች ግዥ/ኪራይ የሚወጣው ወጪ፣ ከዚህም ባለፈ ከሌሎች ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት እኩል ለመሆን ቻናል ለመክፈት ወይ የአየር ሰዓት ለመግዛት የሚያደርገው ሩጫ፣ ቻናል የከፈቱትም ይህን ብዙ ሚሊየን ብር የሚያስወጣን ወጪ ለመሸፈን የሚያደርጉት ሩጫ፣ ለችግር ጊዜ ዋስትና የሚሆን ትልቅ ካፒታል ለማከማቸት የሚደረገው ሩጫ፣ ላልተሰቀለው ስጋዊ ማንነት ምቾት የሚደረገው የሐብት ማካበት ሩጫ ... አብያተ ክርስቲያናቱን ከፍተኛ የወጪና የገንዘብ ማከማቸት ሩጫ ውስጥ ከቷቸዋል፡፡

በዚህም አብዛኞቹ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ይህንን ወጪያቸውንና ፍላጎታቸውን ለመሸፈን መጽሐፍ ቅዱሱ ከሚያዘው የገቢ ምንጮች ውጪ፣ "በነፃ ያገኛችሁትን በነፃ ስጡ" ከሚለው ቃል በተቃራኒ እየሰሩ ይገኛሉ፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፣

- የተፀለየበት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ጨው፣ ዘይት፣ ውሀ፣ ብር፣ እስክሪብቶ፣ ቲሸርት፣ ኮፍያ ... ንግድ፣
- ገስት ሀዎስ፣ በልዩ ክፍያ "እጅ ጭኖ መፀለይ"፣ ልዩ የባለሐብቶች ፕሮግራም፣ የኮንትራክተሮች ፕሮግራም፣ የዲያስፖራ ፕሮግራም፣ የነጋዴዎች ፕሮግራም ... የተለያዩ "ነፍስ ማዳን መር" ያልሆኑ ገቢያ መር ፕሮግራሞች፣
- "የፍቅር ስጦታ" (ይህ የገቢ አይነት ሰው ብር በፖስታ በመያዝ መድረክ ላይ በመውጣት ተፀልዮለት የሚሰጠው አይነት ስጦታ ነው፣ ያልሰጠ አይፀለይለትም፣ በጉባዔውም አይባረክም)፣

  አስራት፣ መባና በኩራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተክርስቲያን የገቢ ምንጮች በመሆናቸው ለቤተክርስቲያን ሲሰጡ የራሳቸው አሰጣጥ ስነ ስርዓት አላቸው፣ ይህ አዲስ የተፈጠረው አሰራር ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም ይባሱኑ አሰራሩ

ማቴ.6፡2-6 ላይ የተነገረውን ማስጠንቀቂያ ችላ ያለ በመሆኑ የሰጪው ስጦታ እንኳን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት የሌለው መሆኑ::

- ስሙ የማይታወቀው የስጦታ አይነት፣ ይህም ነብዩ ለዚያ ሰው ለይቶ "ትንቢት" እንዲያመጣለት በነብዩ እጅ፣ ኪስ ወይንም በጉባዔው ፊት ለፊት በተዘጋጀ ስፍራ ላይ ተነስቶ ገንዘብ የማስቀመጥ አሰራር፣

እየተመለከትን ነው::

ይህ በቤተክርስቲያን ስም የግል የዝርፊያ ማዕከላትን መክፈት በሁሉም ሀገራት እየተስፋፋ ያለ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ፈተና ነው፣ [159] "አሜሪካዊው ኢኮኖሚስት ቶማስ ሼይቨሊ ባደረጉት ጥናት፣ ቤተክርስቲያንና ኣጋር አገልግሎቶች (ሚኒስተሪ) መክፈት፣ "አዋጭ የቢዝነስ ዘርፍ" እየሆነ እንደመጣ ተናግረዋል::" የጀርመን ድመፅ ራዲዮ እንግሊዘኛ ፕሮግራም በ15/04/2018 በሰራው ዘገባ [160]"ጋና ውስጥ የቸርች ቢዝነስ እያደገ ያለና የብዙ አገልጋዮችን ሻንጣዎቻቸውን በገንዘብ እየሞላ ያለ አዋጭ ቢዝነስ ሆኗል" ይላል፣ [161]ኮንጎ ውስጥ ኣጋንንት ለማስወጣት ከ24-27 ፓዎንድ የሚያስከፍሉ አገልጋዮች እንዳሉ፣ በሀገራችንም [162] ቤተክርስቲያን መክፈት ቀረጥ የማይከፈልበት በአቋራጭ የሚያበለፅግ ንግድ እየሆነ እንደመጣ እየተመለከትን ነው::

ይህንን አሰራር ቀደም ብለው የጀመሩቱ የውጪ ሀገራት አገልጋዮች ጸጋቸውን "በመሸቀጥ" ግዙፍ ካፒታሊስቶች ሆነዋል፣ በሀገራቸው የቢሊየነሮች ዝርዝር ውስጥ ገብተዋል፣ የግዙፍ ኢንቨስትመቶች፣ የግዙፍ የንግድ መርከቦችና አማራጭ የግል ፕሌን ባለቤቶች ሆነዋል፤ ኢትዮጵያ ውስጥም በዚህ መንገድ እየሄዱ ያሉት ዛሬ ላይ መልቲ ሚሊየነሮች ናቸው፣ በቦዲ ጋርድ እንጂ አይንቀሳቀሱም፣ በዚህ ዳቦ በልቶ ባልጠገበ ህዝብ መካከል የሚይዙት "አለ" የተባለ መኪና ነው፣ በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገርም ኢንቨስትመንት እየሞካከሩ ያሉትን ሁላ እየተመለከትን ነው::

በዚህም ክርስቶስ ደሙን ያፈሰሰው ለነሱ ካፒታሊስትነት እስኪመስል እየደረሰ ይገኛል፣ አላወቁም እንጂ፣

> ማቴ.7፡22-23 "በዚያን ቀን ብዙዎች፣ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህስ ኣጋንንትን አላወጣንምን? በስምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፣ የዚያን ጊዜም፣ ከኖ አላወቅኋችሁም፣ እናንተ አመፅኞች፣ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባችኋለሁ::"

---

[159] **ማቴቴስ መፅሄት**, ግንቦት 2003, ገፅ 10

[160] http://p.dw.com/p/2w3TK

[161] ጸጋአብ በቀለ(2009)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ**፣ ቅፅ 2፣ ገፅ. 273

[162] ጸጋአብ በቀለ(2009)፣ **የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ተሐድሶ**፣ ቅፅ 2፣ ገፅ. 224

የሚለው ቃል የተነገረው ላላመኑት ወይ ለተራው ክርስቲያን አይደለም ነገር ግን በተለየ ቅባት ስለተነሱትና አጋንንት ስለሚያወጡ፣ ተአምራት ስለሚያረደርጉት ነገር ግን ከነሱ የማይጠበቅ ነገር እየሰሩ ላለት ዋናዎቹ አገልጋዮች እንጂ።

አንዳንድ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ከዚህ ህገወጥ የገቢ መሰባሰብና ፀጋን የመሸቀጥ አሰራር ባለፈ በኃይማኖት ስም ግልፅ የዝርፍያ ስራዎችንም ሲሰሩ ይታያሉ፣ ከነዚህ ውስጥ የስም አጥፊዎችን ወሬ ትተን ከታማኝ ምንጮች የሚሰሙትን ጥቂቶቹን ብንመለከት፣

- አገልጋዩ እንደሌለ እየታወቀ ሰዎችን ገስት ሀዎስ አስገብቶ ብዙ ሺ ብሮች ማስከፈል፣
- አገልጋይም እያለ ሰዎች ብራቸውን ከፍለው ሳይፀለይላቸው መቅረት፣
- አዳዲስ አማኞችን "እንፀልይላችኋለን" በማለት ያላቸውን ሐብት አጭበርብሮ መውሰድ፣
- በቻናል ላይ ለሚለቀቅ ማስታወቂያ ክፍያ ተቀብሎ መካድ፣
- "እፀልይበታለሁ" ብሎ የአትሌቶችን ሽልማት ተቀብሎ መካድ፣
- ብር ተበድሮ መካድ ...

የመሳሰሉ ብዙ በቤተክርስቲያን ስም የሚሰሩ የዝርፊያ ስራዎችን እየተመለከትን ነው።

ከታሪክ እንደምንማረው የፐሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ምሥረታ የእግዚአብሔር የተሐድሶ ሐሳብ ቢሆንም ሰዎች ግን በዋነኛነት በዚህ የተሐድሶ መስመር ውስጥ የገቡት በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ የነበረውን የእግዚአብሔርን ነገር የመሸቀጥ ችግር በመቃወም ነበረ፣ ቤተክርስቲያኗ "ፐሮቴስታንት" የተባለችውም በዚህ ምክንያት ነበረ።

በአሁኑ ጊዜ ሰይጣን በፐሮቴስታንት በኩል የተነሳውን ተሐድሶ ለመቀልበስ እየሰራ ያለው ቤተክርስቲያኗ ተቃውማ ወደ ተነሳችበት "የእግዚአብሔርን ነገሮች መሸቀጥ" እንድትመለስ በማድረግ ነው። በዚህም ይህ ቤተክርስቲያኗን እየፈተነ ያለው የእግዚአብሔርን ጸጋ የመሸቀጥና ቤተክርስቲያንን ለዝርፊያ ማዕከልነት የመጠቀም አዝማሚያ አደገኛ አጋንንታዊ ሜራ መሆኑና ሰይጣን ነፃነት ነፍጓት ማፍረስ ያቃተውን ቤተክርስቲያን አሁን ደግሞ ከአቅሟ በላይ ነፃነት ሰጥቷት በልቅነት ሊጥላት እየሰራ እንደሆነ እንመለከታለን።

በአጠቃላይ ስንመለከት ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ በተፈጠረው የአሰራር ክፍተት ምክንያት ቤተክርስቲያን ህጋዊ የዝርፊያ ማዕከል እየሆነች እንደሆነ እንመለከታለን።

6.2.2.4. ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች ቤተክርስቲያን የገቡበት

ግለሰቦች እንደፈለጉ በሚያሸከረክሩት ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ ባለው ልቅ አሰራር ምክንያት ብዙ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች ወደ ክርስትና እየገቡ ይገኛሉ፣ ዋና ዋናዎቹን ብንመለከት፣

- ኢየሱስ በወርሀ ስጋው አምላክነት አልነበረበትም፣
- የኢየሱስ ስጋ ከማርያም አይደለም፣
- የብልፅግና ወንጌል፣
- አምስቱ የአገልግሎት ቢሮዎች፣
- ሰው መንፈስ ነው፣
- የፀደቅነው በጸጋ ነው ስለዚህ ኃጢያት ብንሰራም ችግር የለውም"

የመሳሰሉት ሲሆኑ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን::

6.2.2.4.1. "ኢየሱስ በወርሀ ስጋው አምላክነት አልነበረበትም"

እነዚህ አስተማሪዎች "ኢየሱስ በወርሃ ስጋው ከሰው ማንነት በተጨማሪ ደርቦ የያዘው መለኮታዊ ማንነት የለውም" ይላሉ፣ ለዚህም የሚያቀርቡት መከራከሪያም፣

- ዮሐ.1፡14 "ቃልም ስጋ ሆነ ..."
- ፊሊጵ.2፡7 "ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰው ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አረደገ::"

የመሳሰሉት ቃላት ሲሆኑ፣ እነዚህ ቡድኖችም "ቃልም ስጋ ለበሰ" ሳይሆን "ቃልም ስጋ ሆነ ነው" የሚለው እና "ባዶ" የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ "ኢየሱስ በወርሀ ስጋው አምላካዊ ማንነት አልነበረበትም፣ አምላካዊ ማንነት ስላነበረበትም ኢየሱስ ተደብድቧል፣ ተገርፏል፣ ተገድሏል ...፣ አምላክ እንደዚህ አይደረግበትም ስለዚህ ኢየሱስ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ አምላክነት አልነበረበትም" ይላሉ:: ስለ አምላካዊ ድርጊቶቹ ሲጠየቁም "አምላካዊ ትውስታው በሰብአዊ ማንነቱ ውስጥ ነበረ፣ ካረገም በኋላም ከሰውነት ትዝታ በቀር እሱ ላይ የሰው ማንነት የለም" ይላሉ፣ እነዚህን መከራከርያዎች በዝርዝር ብንመለከት፣

- ኢየሱስ አምላካዊ ማንነት እንዳለው በ5.2.2.1 ክፍል በስፋት ቀርቧል፣ ፊሊጵ.2፡7 ላይ የምንመለከተው "ራሱን ባዶ አረደገ" የሚለው ቃል የቀረበው ኢየሱስ ለመጣለት ዓላማ ሲል አምላካዊ ኃይሉን አለመጠቀሙን ለማሳየት እንጂ አምላካዊነት አልነበረበትም ለማለት አይደለም፣ የኢየሱስ ስጋዊ ማንነት ስለ ሰው ልጆች ኃጢያት እስከ መገደል ድረስ እንኳ ዋጋ ሲከፍል የኢየሱስ አምላካዊ ማንነት ዝም ነው ያለው::

  ይህን ባዶነት በምሳሌ ብንመለከት፣ ለምሳሌ አበበ ጴንጤ ዶክተር ነው፣ ቸርች ስለፈውስ ሲፀልይ ዶክተርነቱን ባዶ አድርጎ ነው፣ ሆስፒታል ውስጥ በዶክተርነቱ

ሲሰራ ጴንጤነቱን ባዶ አድርጎ ነው፣ አበበ አንዱን ማንነቱን ባዶ ባደረገበት ወቅት ግን "ባዶ የተደረገው ማንነት በውስጡ አልነበረም" ማለት አይደለም::

- ዮሐ.1፡14 "ቃልም ስጋ ሆነ ..." የሚለውንም ለመረዳት ከላይ ይህንኑ ጴንጤውን ዶክተር መመልከት እንችላለን፣ አበበ ጴንጤ ነበረ ከዚያ ተምሮ ዶክተር ሆነ፣ እዚህ ጋር "ቃልም ስጋ ሆነ" የሚለውን "አማልክታዊ ማንነቱን ተወ" ብሎ መተርጎም፣ "አበበ ዶክተር ሲሆን ጴንጤነቱን ይሰረዛል" እንደማለት ነው::

ኢየሱስ ተዋህዶ በመሆኑ፣ በሰዎች የተደበደበው፣ የተገደለው ... ስቃዮች የተቀበለው ስጋዊ ማንነቱን ነው፣ ስጋውያን ጠላቶች የሚጎዱት ስጋዊ ማንነት ብቻ ነው(ማቴ.10፡28):: በዚህም "አምላክ አይደበደብም፣ አምላክ አይሞትም..." ከሚል መነሻ "አምላክነት አልነበረበትም፣ አምላካዊ ትውስታ እንጂ ..." የሚሉት አስተምህሮች ስህተት መሆናቸውን እንመለከታለን::

አንዳንዶች "አምላካዊ ትውስታ" የሚለውን "አምላካዊ ባህሪ" ሲሉም እንመለከታለን፣ ይህም የተሳሳተ ነው፣ አምላካዊ ማንነት ሳይኖረው አምላካዊ ባህሪውን ከየት እንደሚያመጣ ግልፅ አይደለም፣ በ5.2.2.1.1 ክፍል እንደተመለከተውም ኢየሱስ ሙሉ አምላካዊ ማንነት አለው፣ ይህም እውነታ የሚያሳየን በስጋ የተገለጠው ኢየሱስ ውስጥ ከአምላካዊ ትውስታና ከአምላካዊ ባህሪ ያለፈ ሙሉ አምላካዊ ማንነት ነበረ::

እነዚህን ከላይ የቀረቡትን እውነታዎች በአንድ ላይ ስንመለከትም ኢየሱስ ፍፁም አምላክና ፍፁም ሰው የሆኑ ማንነቶች ተዋህደውበት እንዳለ እንረዳለን፣

ቆላ.2፡9 "በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ ይኖራልና::"

ይህ "ኢየሱስ አምላክነት የለውም" ትምህርት አይሁዶችን ያሳሳተው መንፈስ ነው፣

- ዮሐ.8፡57-59 "አይሁድም፣ ገና ሀምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሀልን፣ አሉት ... ስለዚህም ሊወግሩት ድንጋይ አነሱ፤"
- ዮሐ.10፡33 "አይሁድም ስለ መልካም ስራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት::

በዚህም ይህ "ኢየሱስ አምላክነት አልነበረበትም" አስተምህሮ ሊወገዝ የሚገባው ክርስቲያናዊ ያልሆነ አስተምህሮ ነው::

6.2.2.4.2. <u>"የኢየሱስ ስጋ ከማርያም አይደለም"</u>

እነዚህ ቡድኖች መዝ.40፡6 "መስዋዕትንና ቁርባንን አልወደድክም ስጋን አዘጋጀህልኝ..." ከሚለው ሐሳብ በመነሳትና "ኢየሱስ የለበሰው የሰው ስጋ ከሆነ ከአዳም የመጣ የውርስ ኃጢያት ሊኖርበት ነው፣ ስለዚህ ኢየሱስ የለበሰው ስጋ ምንም ኃጢያት የሌለበት ከማርያም ያልሆነ ስጋ ነው::" በሚል "ኢየሱስ የለበሰው መለኮታዊ ስጋ ነው" ይላሉ::

ነገር ግን “ስጋንም አዘጋጀህልኝ” የሚለው መለኮታዊ ስጋ ማዘጋጀትን የሚያመለክት ሳይሆን የኢየሱስ ስጋ የሚዘጋጀው በተለመደው መንገድ(የአባትና የእናት ዘር ተቀላቅሎ ልጅ በሚፈጠርበት መንገድ) ሳይሆን በእግዚአብሔር ተአምራዊው አሰራር ከማርያም መሆኑን ለማሳየት ነው። በዚህም የኢየሱስ ስጋ ከሰው ስጋ የሚለየው በአዘገጃጀቱ እንጂ በስብዕናው አይደለም፣ ኢየሱስ የለበሰው የሰውን ስጋ ነው። የኢየሱስ ስጋ ከሰው ስጋ የሚለይ መለኮታዊ አካል ባለመሆኑም አብሮ አደጎቹ፣ ህዝቡ፣ ፈሪሳውያኑ … ኢየሱስን በሰውኛ ማንነቱ ሲናገሩት ነበሩ፡-

- ማቴ.13፡55 “ይህ የፀራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን?”
- ዮሐ.8፡57 “አይሁድም ገና ሀምሳ አመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት።”
- ዮሐ.10፡33 “አይሁዳውያኑም፣ ስለ መልካም ስራ አንወግርህም፣ ስለ ስድብ፣ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ።”

ኢየሱስ የለበሰው ስጋ የሰው ስጋ ስለነበረ በዚህ ስጋ ማንነቱ እንደ ሰው ተርቧል፣ ተጠምቷል፣ ደክሟል፣ ተኝቷል … ይህም የሆነው ኢየሱስ ስለሰው ልጆች ዋጋ መክፈል ያለበት የሰውን ስጋ በመልበስ መሆን ስላለበት ነው፣

- ዕብ.2፡17 “… <u>የህዝብን ኃጢያት ለማስተሰረይ</u> … <u>በነገር ሁሉ</u> ወንድሞቹን ሊመስል ተገባው።”
- ነጴጥ.4፡1-2 “ክርስቶስ <u>በስጋ</u> ስለእኛ መከራን ስለተቀበለ፣ ከእንግዲህ ወዲህ <u>በስጋ</u> ልትኖሩ በቀረላችሁ ዘመን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ እንጂ እንደ ሰው ምኞት እንዳትኖሩ…”

ሌላው እነዚህ ቡድኖች የሚያነሱት መከራከርያ “የኢየሱስ ስጋ ከሰው ከሆነ የውርስ ኃጢያት ሊኖርበት ነው” የሚለው ነው፣ በርግጥ ኢየሱስ ኃጢያትን አላደረገም(ዕብ.4፡15, ዮሐ.8፡46 …) ነገር ግን የአዳም ኃጢያት ይቅርና የሁሉም ሰዎች ኃጢያት እንኳን በሱ ላይ ተደርጎ ነበረ(ኢሳ.53፡12, 2ቆሮ.5፡21, ነጴጥ.2፡24 …)፣ ይህ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ኢየሱስ ስለ ሰዎች አጠቃላይ ኃጢያት ዋጋ መክፈል ስለነበረበት ነው። በዚህም “ሰዎች በኢየሱስ በማመን ከኃጢያታቸው ይድናሉ” ማለት ከድርጊት ኃጢያታቸው ብቻ ሳይሆን ከአዳም የወረሱትንም ኃጢያት ጨምሮ ነው፣ ስለዚህ የአዳም ኃጢያት በኢየሱስ ላይ መደረጉ ስህተትነት የለውም።

እውነታው በእንዲህ እንዳለ “ክርስቶስ በሰው ስጋ ነው የመጣው” ወይ “በሌላ አካል” ብሎ ማመን መካከል ግን ከባድ የትርጉም ልዩነት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱሱ ይናገራል።

- ነዮሐ4፡2-3 “የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፣ <u>ኢየሱስ ክርስቶስም በስጋ እንደመጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፣</u> ይህም የክርስቶስ

ተቃዋሚ መንፈስ ነው፤ ይህ እንዲመጣ ሰምታችኋልና፣ አሁንም እንኩዋን በዓለም አለ።።"

- 2ዮሐ.1፡7-8 "<u>ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በስጋ እንደመጣ የማያምኑ ናቸው፣ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው</u>።። ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሰራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።። ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖረው ሰው አምላክ የለውም፣ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት።። ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይንም ትምህርት ባያመጣ <u>በቤታችሁ አትቀበሉት ሠላምም አትበሉት ሠላም የሚለው ሰው በክፉ ስራው ይካፈላልና</u>።።"

እነዚህ እውነታዎችም አስተማሪዎቹ ያሉበትን የስህተት መንፈስ በግልፅ ያሳዩናል።።

6.2.2.4.3. <u>የብልፅግና ወንጌል</u>

"የብልፅግና ወንጌል" የሚባለው አስተምህሮ "ድህነት መርገምት ነው፣ ክርስቶስ ከመርገምት ሁሉ ነፃ አውጥቶናል፣ ዛሬ በድህነት ውስጥ ያለነው በራሳችን የተሳሳተ እምነት ነው፣ ስለዚህ ሐብታምነት ተኮር ስብከት፣ አስተምህሮና የእምነት እንቅስቃሴ ብናደርግና ሐብታምነትን በራሳችን ላይ ብናውጅ ሐብታም እንሆናለን" የሚል አስተምህሮ ነው።። በዚህ አስተምህሮም ቁሳዊው ብልፅግና የክርስትናን ማዕከላዊ ጉዳይ ተደርጎ ሰዎች ቁሳዊ ሐብታምነት ላይ ብቻ ትኩረታቸውን እንዲያደርጉ እየተደረገና ድህነት እርኩስነት ሐብታምነት ደግሞ ጽድቅ እንደሆነ እየተነገረ ይገኛል።።

ይህ የብልፅግና ወንጌል አስተምህሮ ያተኮረበት ቁሳዊ ሐብታምነት የሚደገፈው በብሉይ ኪዳን ሲሆን ከአዲስ ኪዳኑ ምንም ድጋፍ የለውም፣ የብሉይ ኪዳን ፃድቃን በሙሉ ትልልቅ ከበርቴዎች ነበሩ በተቃራኒው ደግሞ ኢየሱስና ሐዋርያቱን ጨምሮ ሁሉም የአዲስ ኪዳን መሪዎች የሚታወቁት በቁሳዊ ሐብታቸው ሳይሆን በመንፈሳዊ ሐብታቸው ነው።። በብሉይ ኪዳን ዘመን ፅድቅ የሚታየው በቁሳዊው ባለጠግነት ነበረ በአዲስ ኪዳኑ ደግሞ ባለጠግነት የሚታየው ከምድራዊው ትርጉም ከፍ ባለው ዘላለማዊው መንፈሳዊ ሐብት ነው፣ ይህም ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ(ማሳያ ሞዴል) በመሆኑ ምክንያት ነው፣ እነዚህን ሁለቱን የባለጠግነት ትርጉሞችም ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡-

- <u>ባለጠግነት በብሉይ ኪዳን</u>

የብሉይ ኪዳን የወረደው እስራኤላዊነታቸው በስጋ ለሆኑት፣ ለ12ቱ የያዕቆብ ልጆች ዘሮች፣ አምልኳቸው በሚታይ ቁስ(ፅላት/ታቦት፣ ቤተመቅደስ ...) ለነበሩ፣ ሰንበታቸው በሰባተኛው ቀን ለነበረ፣ ጠላቶቻቸውም ስጋውያን ለነበሩ፣ በረከቶቻቸውም ምድራዊ ለነበረ ህዝቦች ነው፣ ይህንን በረከቶቻቸውንም ብንመለከት፡-

ዘዳ.28፡2-14 "የአምላህንም የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡልሃል ... በከተማ ብሩክ ትሆናለህ፣ በእርሻ ብሩክ ትሆናለህ።። የሆድህ ፍሬ፣

የምድርህም ፍሬ፣ የከብትህም ፍሬ፣ የላምህም ርቢ፣ የበግህም ርቢ ... እንቅብህና ቡቃያህ ... መግባት መውጣትህ ቡሩክ ትሆናለህ፣ ጠላቶችህ በፊትህ የተመቱ ያደርጋቸዋል ... እግዚአብሔር በረከቱ በአንተ ላይ በጎተራህ በእጅህም ስራ ሁሉ እንዲወርድ ያዛል፣ የሚሰጥህን ምድር ይባርካል ... ለእርሱ የተቀደሰ ህዝብ አድርጎ ያቆምሃል ... የምድር አህዛብ ... ይፈሩሀል ... ታበድራለህ አንተ ግን አትበደርም ..."

በዚህም የብሉይ ኪዳን ፃድቃን በረከታቸው እንደዚሁ ነበረ፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ኢዮብ፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን ... ሁሉም በዘመናቸው "አሉ" የተባሉ ከበርቴዎች ነበሩ::

- **<u>ባለጠግነት በአዲስ ኪዳን</u>**

በአዲስ ኪዳን እስራኤላዊነት በመንፈስ ነው፣ በ12ቱ ሐዋርያት *መሠረት* ላይ የተመሠረተች፣ አምልኮዋ በመንፈስ የሆነ፣ ፅላት/ታቦትና ቤተመቅደሷ መንፈሳዊው ሰው የሆነ፣ ሰንበቷ ክርስቶስ የሆነ፣ ጠላቶቿ መንፈሳዊያን የሆኑና በረከቶቿም መንፈሳዊ የሆነ ...

ኤፌ.1:3 "በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ::"

እነዚህ መንፈሳዊ በረከቶችም የዘላለም ህይወት(ዮሐ.3:16)፣ የእግዚአብሔር ልጅነት(ዮሐ.1:12)፣ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ(ሐዋ.2:38) ... የመሳሰሉት ናቸው::

በዚህ አተረጓጎሙ ከፍ በተደረገው የአዲስ ኪዳኑ የበረከት ትርጉም *መሠረት* የአዲስ ኪዳን ቅዱሳን ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በተቃራኒ "እዚህ ግባ" የሚባል ምድራዊ ሐብት ሳይኖራቸው በመንፈሳዊ ሐብታምነታቸው ብቻ ነበረ የሚታወቁት፣ ኢየሱስን ብንመለከት፣

ሉቃ.9:57-58 "እነርሱም በመንገድ ሲሄዱ አንድ ሰው፣ ጌታ ሆይ ወደ ምትሄድበት ሁሉ እከተልሀለሁ አለው:: ኢየሱስም ለቀበሮዎች ጉድጓድ፣ ለሰማይ ወፎችም *መሳፈሪያ* አላቸው፣ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አላቸው::"

በዚህም ኢየሱስ በዚያ ዘመን የግል ንብረት *መነሻ* የነበረውን የራሱ ቤት እንኳን አልነበረውም:: ኢየሱስ ሐዋርያቱንም ያዘዘው እንደዚሁ ነው፣

ሉቃ.9:1-3 "አስራ ሁለቱም ሐዋርት በአንድነት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይ ደዌንም ይፈውሱ ዘንድ ኃይልና ስልጣን ሰጣቸው፣ የእግዚአብሔርንም *መንግሥት* እንዲሰብኩና ድውዮችንም እንዲፈውሱ ላካቸው፣ እንዲህም አላቸው፣ በትርም ቢሆን፣ ከረጢትም ቢሆን፣ እንጀራም ቢሆን፣ ብርም ቢሆን ለመንገድ ምንም አትያዙ፣ ሁለት እጀ ጠባብ ዓይንላችሁ::"

ሐዋርያቱም ለክርስቲያኑ ያስተላለፉት ተመሳሳይ መርህን ነው፣

ዕብ.13:5-9 "<u>አካሄዳችሁ ገንዘብ ያለመውደድ ይሁን፣ ያላችሁ ይብቃችሁ</u>... የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩዋችሁን <u>ዋኖቻችሁን አስቡ፣ የኑሮዋቸውን ፍሬ</u>

እየተመለከታችሁ በእምነት ምሰሉአቸው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ዘላለምም ያው ነው፡፡ ልዩ ልዩ አይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ ..."

እዚህ ጋር አዲሱ ኪዳን "ቁሳዊው በረከት አያስፈልግም" እያለ አይደለም ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ዋና ዓላማ መንፈሳዊ በረከት እንጂ ቁሳዊው በረከት አለመሆኑን ለማስረዳት ነው፡፡ በአዲሱ ኪዳን ቁሳዊው በረከት ዋና ነገር ሳይሆን ተከታይ እንደሆነና ቁሳዊውን በረከት የክርስትና ማዕከል አድርጎ መንቀሳቀስ መንፈሳዊ በረከትን እንኳን ሊያሳጣ የሚችል አደገኛ ነገር እንደሆነ ነው የተነገረው፣

- ማቴ.6፡31-33 "እንግዲህ፡፡ ምን እንበላለን፣ ምንስ እንጠጣለን፣ ምንስ እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፤ ይህንስ ሁሉ አህዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና፡፡ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ፅድቁንም ፈልጉ፣ ይህ ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡"
- ማቴ.6፡19-24 "ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦች ቆፍረው በሚሰርቁት ዘንድ ለእናንተ ምድር ላይ መዝገብ አትሰብስቡ፤ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው በማይሰርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ መዝገብ ሰብስቡ ... ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም የለም፣ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውን ይወዳል፣ ወይም ወደ አንዱ ጠጋል ሁለተኛውን ይንቃል፤ ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም፡፡"
- ማር.10፡21-25 "ኢየሱስም ... ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ፣ በሰማይ መዝገብ ታገኛለህ፣ መስቀሉንም ተሸክመህ ና ተከተለኝ አለው፣ ነገር ግን ስለዚህ ነገር(ሰውየው) ፊቱ ጠቆረ፣ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ፡፡ ኢየሱስም ዘወር ብሎ አይ ደቀ መዛሙርቱን፡- ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆናል አላቸው ... ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል አላቸው፡፡"
- ፤ጢሞ.6፡6-11 "ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤ ወደ ዓለም ምንም እንኩዋን አላመጣንምና፣ አንዳችን ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና መጠጥ ከኖረን ግን፣ እርሱ ይበቃናል፡፡ ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰምጥና በሚያሰጉፍ በሚጎዳም በብዙ ምኞት ና በፈተና በወጥመድ ይወድቃሉ፡፡ ገንዘብ መውደድ የክፋ ሁሉ ስር ነውና፤ አንዳንዶች ይህንን ሲመኙ፣ ከኃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ፡፡ አንተ ግን የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፣ ከዚህ ሽሽ ..."

ከአዲስ ኪዳኑ ቅዱሳን መካከል ይህንን የአዲስ ኪዳኑን የበረከት ትርጉም አልቀበል ብሎ የአዲስ ኪዳኑን በረከት ለብሉይ ኪዳኑ ምድራዊ ሐብት ማሰባሰቢያነት ሲያውል የነበረው ይሁዳ ነበረ፣ የይሁዳም መጨረሻ ሳያምር እንደቀረው ሁሉ በአዲስ ኪዳኑ በረከት

ምድራዊ ሐብት ለማካበት የተሰራው የብልፅግና ወንጌል አስተምህሮ ተከታዮች መጨረሻ እንደዚሁ እንደሚሆን ግልፅ ነው::

ከሁሉ የሚያሳዝነው ደግሞ ለምድራዊው ህይወታችን አስፈላጊ የሆነው ቁሳዊው ሐብትም የሚገኘውም እንደ ብልፅግና ወንጌል አስተምህሮ "በመተንበይ"፣ በማወጅ፣ በመመኘት፣ "የእምነት ልምምድ" በማድረግ ... ሳይሆን ጠንክሮ በመስራት ነው፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ማድረግ ቢችልም ሰዎችን በቁሳዊው ሐብት ሲባርክ የነበረው ግን ሰዎች በሰሩት ላይ በሚጨምረው የማባዛት ስራ ነው፣ የያዕቆብ በጎች የተባዙበት፣ ኤልሳዕ የነበዩን ሚስት ቤት ዘይት ያባዛበት፣ ሩት በረከቷ ጋር የደረሰችው ነዶዋን እየለቀመች ነው ... ብዙ ተመሳሳይ ታሪኮችን ማንሳት ይቻላል:: በዚህም የብልፅግና ወንጌል ምድራዊ ሐብት ማካበቻ መንገድ አስተምህሮ በራሱ የአዲስ ኪዳኑ ይቅርና የብሉይ ኪዳኑን መስፈርት እንኳን አያሟላም::

በዚህም በብሉይ ኪዳን ቃላት ተደግፎ በአዲስ ኪዳኑ ዘመን የመጣው የብልፅግና ወንጌል ምን ያህል ከአዲሱ ኪዳን ጋር በተቃርኖ መንፈስ ውስጥ እንደሚገኝና ከብሉይ ኪዳኑ ጋር እንኳን እንደማይገናኝ እንለከታለን::

እነዚህን በመሠረተ ሐሳብ ደረጃ አነሳናቸው እንጂ ይህንን የከፋት ሁሉ ምንጭ የሆነውን "ገንዘብ" ተኮር ስብከት ላይ የተጠመዱት የብልፅግና ወንጌል ሰባኪዎችን ስንመለከት ዋናው አስተምህሮታቸው "<u>ስጡ ይሰጣችኋል</u>" የሚለው በተግባር "<u>ስጡኝ ይሰጣችኋል</u>" አድርገውት ነው የምንመለከተው፣ በዚህም የ"ብልፅግና ወንጌል" ብልፅግናን የሚያመጣው ለመሪዎቹ እንጂ ለተከታዮቻቸው አይደለም፣ ተከታዮቻቸው ልክ እንደ ደርግ ስብሰባ አዋጅ ሲያዉጁና መፈክር ሲያሰሙ ውለው ይገባሉ፣ <u>በመንፈሳዊ ብልፅግና መሙላት የነበረባቸውን አዕምሮ በኮልኮሌ ነገሮች ምኞትና ቅዠት ሞልተውት ይኖራሉ</u>፣ እነዚህ የብልፅግና ወንጌል ተከታዮችም የሚባንኑት ጠብ የሚል ነገር ሲጠፋና ተስፋቸው ተሟጦ ከእኩዮቻቸው ወደ ኋላ መቅረታቸው ሲመለከቱ ብቻ ነው፣ የሚያሳዝነው ደግሞ እነዚህ ሰዎች ከቅዠታቸው ሲባንኑ፣ በመታመን እንደተዘረፉት ሁሉ እነሱም በዚህ ልምድ የራሳቸው ቸርች በመመሥረት የለየላቸው ዘራፊዎች ሆነው ይመጣሉ::

የብልፅግና ወንጌል አስተምህሮ ሳይስተዋል በአጠቃላይ ፕሮቴስታንቱም ላይ ጫና አሳርፏል፣ በዚህም በአሁኑ ጊዜ ብዙ ስብከቶች፣ ፀሎቶችና መዝሙሮች የስጋ ፍላጎት ጉዳዮች እየሆኑ ያሉበት ሁኔታ፣ ከአስተማሪና ሰባኪዎች ይልቅ motivational speakers ተፈላጊ የሆኑበት ሁኔታ፣ ከዘማሪዎች ይልቅ አሟሟቂዎች መድረኩን የሚቆጣጠሩበት ሁኔታ፣ ፕሮግራም መሪዎች ፕሮግራም መሪ ከመሆን ይልቅ መፈክር መሪ የሆኑበት ሁኔታ ነው እየተፈጠረ ያለው:: በዚህም የቀድሞ የነበረው የአምልኮ መልክ እየተቀየረና አማኙም እግዚአብሔርን መፈለግ ያለበት ለመንፈሳዊ በረከት ሳይሆን ስጋዊ ጉድለቱን ብቻ እንዲያሟላለት እንዲሆን እየተደረገ ይገኛል:: በዚህም አማኞች ስጋዊ ጥያቄዎቻቸው ሳይሟሉላቸው ሲቀር ዋናውን ዘላለማዊ በረከታቸውን እንደዋዛ ጥለው ሲሄዱ

እየተመለከትን ነው፣ ዛሬ ላይ ሮሜ.8፡35 “ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ ወይስ ጭንቀት ወይስ ስድብ ወይስ ራብ ወይስ ራቁትነት ወይስ ፍርሀት ወይስ ሰይፍ ነውን?” የሚለው ትምህርት ሰሚ የለውም፡፡

6.2.2.4.4. <u>አምስቱ የአገልግሎት ቢሮዎች</u>

በዚህ አስተምህሮ *መሠረት* አንድ ቤተክርስቲያን *መመራት* ያለባት አምስቱን የአገልግሎት ጸጋዎች፣ በነሱ አባባል “ቢሮዎች” በተሾሙ አገልጋዮች መሆን ይገባል፣ እነዚህ ቢሮዎችም ሐዋርያት፣ ነብያት፣ ወንጌል ሰባኪዎች፣ እረኞችና አስተማሪዎች ናቸው፣ ለዚህም *መነሻ* የሚያደርጉት ቃል፡-

> ኤፌ.4፡11 “እርሱም አንዳንዶቹ <u>ሐዋርያት</u> ሌሎቹም <u>ነብያት</u> ሌሎቹም <u>ወንጌል ሰባኪዎች</u> ሌሎቹም <u>እረኞችና አስተማሪዎች</u> እንዲሆኑ ሰጠ፡፡”

የሚለው ቃል ነው፡፡ በርግጥ ይህ ቃል እነሱ በተረጎሙት አቅጣጫ በቀጥታ የታዘዘ ቃል ባይሆንም፣ አንድ ቤተክርስቲያን በነዚህ በአምስቱም ጸጋዎች የተቀቡ አገልጋዮች ብታሟላ መልካም ነው፣ ከዚያም ባለፈ *መጽሐፍ* ቅዱሱ በተለያዩ ስፍራዎች ላይ ከተገለፀት ከ20 በላይ የሆኑት የጸጋ ስጦታዎችን የተቀቡ ሰዎች ብታሟላ መልካም ነው፡፡

ነገር ግን ይህ በቀጥታ ያልተላለፈ ትዕዛዝ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ እየገነነ የመጣው በምክንያት ነው፣ ይህም ባለራዕዮች በቤተክርስቲያናቸው ሐብትና ንብረት ላይ እንደፈለጉ ለማዘዝ እንዲያመቻቸው የቤተክርስቲያኗን ስራ አስፈፃሚዎችን በራሳቸው ለመምረጥ እንዲያስችላቸው ነው፡፡ በዚህም፣ ያው ባለራዕዩ እያለ ሌላ ሰው በሐዋርያነት “እንደማይቀባው” ሁሉ፣ ባለራዕዩ “ሐዋርያ” ይሆናል፣ ከዚያም ይህ “ሐዋርያ” የሚፈልጋቸውን የራሱን ሰዎችን በተቀሩት አራቱ ሹመቶች በመሾም ከዚያ በዚህ *መጽሐፍ* ቅዱሳዊ ቃል *መሠረት* ያለተቃውሞ የቤተክርስቲያኑን አመራሮች ይሾማል፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የሹመት ክፍፍል *መፅሐፍ* ቅዱሳዊ *መሠረት* የለውም፣ ሐዋርያነት የሚገኘው በመንፈስ ቅዱስ እንጂ በመስራችነት አይደለም፣ ሌሎቹንም በተለያዩ አገልግሎቶች የሚቀባው *መንፈስ* ቅዱስ እንጂ ባለራዕይ አይደለም፣ የአገልጋዮቹን ጸጋ እየተመለከቱ አገልጋዮቹ በተቀቡበት አገልግሎት ላይ ሹመት መስጠት የሚገባቸው ደግሞ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች እንጂ ባለራዕይ አይደለም፡፡ ይህም የሚያሳየን የአምስቱ ቢሮዎች አካሄድ *መሠረታዊ* የአካሄድ ችግር ያለበት አሰራር *መሆኑን* ነው፡፡

ከሐዋርያ ሹመትም ጋር በተያያዘ፣ የሐዋርያነት ጸጋ ነቢይነት፣ የፈውስ፣ ተአምራት የማድረግ፣ ሚስጥራትን የመግለጥ … ብዙ ጸጋዎችን ጠቅልሎ የያዘ ጸጋ በመሆኑ ሐዋርያዶች አንድ ቤተክርስቲያን ላይ ከመቀመጥ ይልቅ ወንጌል ያልተሰፋፋባቸውን አዲስ ግንባሮች ላይ ነው አዝማች ሆነው መስራት የሚገባቸው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስን ስንመለከት አዲስ ስፍራ ይሄዳል ቤተክርስቲያን ይተክላል፣ ከዚያ ሰዎችን ለአገልግሎት ብቁ አድርጎ ሽማግሌዎች፣ ነብያት፣ *መጋቢዎች* … ሾሞላቸው ወደ ሌላ አዲስ ግንባር ይሄዳል፣ እዚያም

ተመሳሳይ ስራ እየሰራ ቀድሞ የመሠረታቸውን አብያተ ክርስቲያናት በደብዳቤ፣ ሰዎችን በመላክና ሲያመቸው ደግሞ ሄዶ እየነበኘ እንቅስቃሴያቸውን ይደግፋል፡፡ ይህ ከእስራኤል የሚወለደው ነገር ግን "የአህዛብ ሐዋርያ ነኝ" የሚለው ጳውሎስ እንደዚህ ግንባር ቀደም ዘማች ሆኖ ሲሰራ ከአህዛብ የመጡት ሐዋርያቶች እውነተኛ ሐዋርያት በሆኑ ኖሮ አዲስ አበባ ቁጭ ብለው፣ ማኪያቷቸውን እየጠጡ፣ በዘመናዊ መኪና ከመንሸራሸር ይልቅ፣ ምን ያህል በዘማችነት መንፈስ መስራት እንደነበረባቸው ነው የምንመለከተው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት ይህ ኤፌ.4፡11 ን ያለአግባብ ጠምዝዞ እየተጠቀመበት ያለው የአምስቱ የአገልግሎት ቢሮዎች አስተምህሮ ለባለራዕዮች ግለሰባዊ ጥቅም የተሰራ አስተምህሮ እንጂ ክርስቲያናዊ መሠረት ያለው አስተምህሮ አይደለም፡፡

6.2.2.4.5. <u>"ሰው መንፈስ ነው"</u>

"ሰው መንፈስ ነው" የሚለው አስተምህሮ ፊት ለፊት ሲታይ ከባድ ስህተት ያለው አስተምህሮ ባይሆንም ብዙ አሳሳች አስተምህሮዎች ግን መሠረት ያደረጉት ይህንን አስተምህሮ ነው፡፡

ፊት ለፊት ያለውን ስህተት ስንመለከት "ሰው መንፈስ ነው" የሚለው አስተምህሮ የሰው ማንነት ሙሉ በሙሉ የሚገልፅ አስተምህሮ አይደለም፣ ሰው መንፈስ ብቻ ሳይሆን፣ ስጋና ነፍስም ነው፣ ዝርዝሩን በ5.2.3 ከፍል መመልከት ይቻላል፡፡ "እንደምሳሌያችን" ተብሎ በሥላሴ ምሳሌ የተፈጠረው የሰው ልጅ "ሥላሴነትም" ከትንሣኤም በኋላ የሚቀጥል እውነታ ነው፣ ከትንሣኤ በኋላ ያለው "ሥላሴነት" አሁን ካለው "ሥላሴነት" የሚለየውም በአዳም ምክንያት "ሞትን እንዲሞት" የተፈረደበት ስጋ በዘላለማዊ ስጋ የሚለወጥበት እውነታ ብቻ ነው(1ቆሮ.15፡53-54)፡፡

"ሰው መንፈስ ነው" የሚለው አስተምህሮ አደገኛነት የሚገለጠው አስተምህሮውን መሠረት አድርገው እየተነሱ ባሉት ተከታይ፣ ሰውን የማግዘፍ የስህተት አስተምህሮዎች ነው፣ እነዚህን የስህተት አስተምህሮዎችን፣ እንደ ኒቂያው ጉባዔ፣ የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ጎብረት በ23ኛው መደበኛ ጉባዔዋ ያወገዘቻቸው ሲሆን፣ እነዚህን የተወገዙትን አስተምህሮዎች ብንመለከት "እኛ እና አብ አንድ ነን፣ እኛ እና ክርስቶስ አንድ ነን፣ እኛ ትንንሽ አማልክት ነን፣ እኛ ካልፈቀድንለት በቀር እግዚአብሔር በምድር ላይ መስራት አይችልም፣ የኛ እምነት እንደ እግዚአብሔር ያለ እምነት ነው፣ በስጋ የሚሰራ ኃጢያት ችግር የለውም ..." ናቸው፣ ከነዚህ ውስጥ የሰው ልጅንና አብን እንደዚሁ የሰው ልጅንና ክርስቶስን የማተካከሉ ነገር ምንም ተጨባጭነት ያለው ነገር ባይሆንም ብዙዎችን እያሳሳተ ያለውን "ኃጢያት ብሰራ ችግር የለውም" የሚለውን አስተምህሮን ግን ሰዎችን ለሲኦል የሚያዘጋጀው መንፈስ ሄራ በመሆኑ ቀጥለን በስፋት እንመለከተዋለን፡፡

6.2.2.4.6. “ኃጢያት ብንሰራም ችግር የለውም”

“ሰው መንፈስ ነው” የሚለው አስተምህሮ ለሰው ስጋዊ ማንነት ስፍራ ስለማይሰጥ “ሰው ምድር ላይ በሚቀረው በስባሽ ስጋው ኃጢያት ቢሰራ ችግር የለውም” ይላል፣ በዚህ ላይ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሱ “ድነት በጸጋ” እንደሆነ የሚያስተምርበትን እውነታ በመለጠጥ “የዳነው በጸጋ እንጂ ህግን በመጠበቅ አይደለም ስለዚህ ህግን መጠበቅ አስፈላጊ ነገር አይደለም” ይላል፡፡

በርግጥ በአዲስ ኪዳኑ ዘመን ፅድቅ በጸጋ ብቻ ነው ይሁን እንጂ “ፅድቅ በጸጋ ብቻ ነው” ብሎ “ሕግ አያስፈልገኝም” በማለት ከኃጢያት ህይወት ውስጥ ለመውጣት አለመሞከር የክርስቶስን የምልጃ አገልግሎትና በጸጋ የተሰጠውን ፅድቅ እንኳን እንደሚያሳጣ በ4.2.3.5 ክፍል በስፋት ተመልክተናል፡፡

ይህ “ኃጢያት ብንሰራ ችግር የለውም” አስተምህሮ ከላይ በተመለከተው “ሰው መንፈስ ነው ስለዚህም በስጋው በሚሰራው ኃጢያት አይኮነንም” በሚለው አስተምህሮ ተሸፍኖ ስለመጣ እንጂ አስተምህሮው በግላጭ ቢመጣ ኖሮ ማንም አይጭበረበርም ነበረ፣ ነገር ግን አማኞችን ለሲኦል የሚመለምለው መንፈስ የሚሰራው በአደገኛ የአሳሳችነት “ጥበብ” በመሆኑ “ትላልቅ” የምንላቸው እንኳን በዚህ ትምህርት ተጭበርብረዋል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ እየተሰሙ ያሉት እንግዳ አስተምህሮዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች አይደሉም፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ዕብ.13፡9 “ልዩ ልዩ አይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት አትወሰዱ …” እንደሚለው ማኅበረሰቡ ራሱን ከእንደነዚህ አይነት እንግዳ አስተምህሮዎች ሊጠብቅ ይገባል፡፡

6.2.2.5. የቤተክርስቲያንን ክብር ያወረዱበት

አንዳንድ ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ የሚሰራው ስራ ደግሞ የቤተክርስቲያንን ክብር እንኳን የሚያዋርድ አሰራር ነው፣ የተወሰኑትን ብንመለከት፣ የሰዎችን መረጃ ከሌላ ስፍራ ለሚመጣ አገልጋይ ቀድሞ በመንገር ይህንን መረጃ ትንቢት አስመስሎ እንዲነገር ማድረግ፣ ተከፍሏቸው በሚመጡ ሰዎች የውሸት የፈውስና የትንቢት ድራማ መስራት፣ የውሸት “ጌታን መቀበል” ድራማ መስራት፣ በፈለጉት ሹመት “ፓስተር፣ ነቢይ፣ ሐዋርያ …” እያሉ መሸጧም፣ ደረጃቸውን ያልጠበቁ ኮሌጆችን በመክፈት ዲግሪና ዲፕሎማ አየር ባየር መሸጥ፣ በተለያየ መንፈስ(ግብረሰዶም፣ ዮጋ …) ለሚሰሩ ከውጪ ሀገር ለሚመጡ ሰዎች የቤተክርስቲያንን ፍቃድ ማከራየት፣ በቤተክርስቲያናቸው አርማ ውስጥ 666 በምስጢር የተቀመጠባቸው፣ በኢጋንጋዊው ኃይል የሚሰሩ፣ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች፣ ሰዎችን በህገ ወጥ መንገድ የማዘዋወር ወንጀሎች፣ አስቂኝና አሳፋሪ ስሞችና ማስታወቂያዎች በመጠቀም በማኅበራዊ ሚዲያዎችና በተለያዩ መድረኮች ኃይማኖቱን ማላገጫ ያስደረጉ ብዙ ጉዶችን እየተመለከትን ነው፡፡

6.2.2.6. <u>ባለራዕዩ እንደፈጣሪ መመለክ የደረሰበት</u>

በብዙ የአፍሪካ ሀገራት “የተቀቡ” አገልጋዮች እንደ ፈጣሪ ተደርገው የሚመለኩበትን ሁኔታ እየተመለከትን ነው፡፡ በዚህም ምንጣፍ እየተዘረጋላቸውና አበባ እየተጎዘጎዘላቸው የሚሄዱ፣ አንዳንድ ስፍራዎች ላይ ደግሞ ሰው መሬት ላይ እየተነጠፈላቸው ላዩ ላይ የሚሄዱ፣ እንደ እግዚአብሔር “ባንተ ቸርነት፣ ባንተ ጥበቃ …” የሚሉ፣ የስዕል ጣኦቶችን እንደሚጠቀሙት አብያተ ክርስቲያናት፣ ሰዎች የነሱን ፎቶግራፍ በልብስ፣ በኮፍያ … አሳትሞ እንዲለብስና በመኪኖቻቸው እንዲለጥፍ የሚያደርጉ፣ “ካለከበራችሁኝ ከእግዚአብሔር “Disconnect” አደርጋችኋለሁ እያሉ አማኙን የሚያስፈራሩ፣ ሰው ሲያያቸው እንዲንበረከክላቸውና ጫማቸው ላይ እንዲሰግድ እንደዚሁ ዕቃ ሲያቀብላቸው በእንበርከክ እየሄደ እንዲያቀብላቸው የሚያደርጉ … በአጠቃላይ እንደ ፈጣሪ ለመመለክ የሚዳዳቸውን አገልጋዮች እየተመለከትን ነው፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ራሳቸውን ከኢየሱስ ጋር በማስተካከል “ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ ነው እኔም የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፣ ክርስቶስ ማለት የተቀባ ማለት ነው እኔም የተቀባሁ በመሆኔ ክርስቶስ መባል እችላለሁ፣ ሐዋርያቱ መጽሐፍ ቅዱሱን እንደፃፉት እኔም ሐዋርያ ስለሆንኩ የምናገረውን ቃል እንደ መጽሐፍ ቅዱሱ ቃል ተቀበሉ …” የመሳሰሉ የድፍረት ንግግሮችን ሲናገሩ እየተመለከትን ነው፡፡

በሀገራችንም እነዚህን የመመለክና ከኢየሱስና ከሐዋርያቱ ጋር የመተካከል ፍላጎቶችን በብዙ “ሀይ” ባይ የበላይ መዋቅር በሌላቸው የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ እየተመለከትን ነው፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት አንድ ግለሰብ እንደፈለገው የሚያሽከረክረው የባለራዕይ ቤተክርስቲያን አሰራር የስያሜ ችግር ያለበት፣ የታላቁ ተልዕኮ አካል መሆን የማይችል፣ አደረጃጀቱ የሚፈጥረው ክፍተትም ቤተክርስቲያንን የዘራፊዎች ዋሻ የሚያደርግ፣ የስህተት ትምህርቶችን የሚያስገባ፣ ቤተክርስቲያንን የሚያዋርድና “ባለራዕዮችን” ጣኦት የሚያደርግ ሁኔታን እየተመለከትን ነው፡፡

በዚህም ነገሮች ከቁጥጥር ውጪ ሳይወጡ፣ ቤተክርስቲያንን ለልቅነት እያጋለጠ ያለውን በአንድ ሰው የሚሽከረከረው የባለራዕይ አደረጃጀት እንዲሁም አሳሪ አሰራርን በመከተል የወንጌሉን እንቅስቃሴ ያፈነውን የወንጌላውያኑን አሰራር በመቀየጥ እንደ ቅይጥ ኢኮኖሚው(Mixed Economy) ለዚህ ጊዜ ተስማሚ የሆነ ቅይጥ አደረጃጀትና አሰራር መከተሉ የግድ በሆነበት ጊዜ ላይ እንገኛለን፡፡

አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ሁሉንም አብያተ ክርስቲያናት በአንድ አደረጃጀት ስር ማስገባቱ አይመከርም፣ ለዚህ ደግሞ ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ መርሆችን ማስተዋሉ አስፈላጊ ነው፣ ይህም፣

- ይስሐቅ አማራጭ የውሀ ምንጭ ጉድጓድ በመቆፈሩ ምክንያት ጠላቶቹ አንዱን ሱደፍኑበት እሱ አልፎ ሌላውን ሲጠቀም ነበረ፣ በዚህም አንዷን ቤተክርስቲያን ዘረኝነት፣ ቢሮክራሲ ... ቢደፍናት ሌላው አልፎ ይሰራል፣ የፐሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ለሰይጣን አፈና እንዳትመች ያደረጋትም ይህ መብዛትዋ ነው፣
- በነገ.19፡16-17 እንደተመለከተው "ከአዛሄልም ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ ኢዩ ይገድለዋል ከኢዩ ሰይፍ ያመለጠውን ሁሉ ኤልሳዕ ይገድለዋል" መንፈስ አብያተ ክርስቲያናቱ በተለያየ ዘዴ በሚሰሩት የወንጌል ማስፋፋት ስራ ሁሉንም ጎብረተሰብ ተደራሽ ያደርጋሉ፣

ከነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆች በመነሳት አንዱ ቤተክርስቲያን ለብቻው የሚቆምበት አሰራርን መደገፍ ባይቻልም፣ የሁለቱን፣ የባለራዕይንና የወንጌላውያኑን አሰራር በማዋሃድ፣ የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናትን አካባቢ የሚታየው አንድ ግለሰብ ለብቻው ቤተክርስቲያንን እንደፈለገ የሚያሽከረክርበትን ልቅ አሰራርና የወንጌላውያኑን ወንጌልን አፍኖ የያዘውን አሰራር ላላ የሚያደርግ ቅይጥ የሆነ አሰራርን በማስፈን የአብያተ ክርስቲያናቱን አደረጃጀት እንደገና መከለስ የግድ ይላል፡፡

በዚህም አንድ ግለሰብ ብቻውን ቤተክርስቲያንን የሚያሽከረክርበትን አሰራርን በማስቀረት የወንጌላውያኑን የሽማግሌዎችን አሰራር እንደ መልካም ተሞክሮ በመውሰድ እንደዚሁ በትልቁ አቁማዳ ያለውን በትንሹ መገልበጥ የማይቻልበትን እውነታ በመመልከት፣ ሁሉም ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት <u>ባሉበት ስፍራና ሁኔታ፣</u> ወደ ወጡበት እናት ቤተክርስቲያናቸው ወይንም ወደፈለጉት የወንጌላውያን ቤተክርስቲያን እንዲመለሱ እንደዚሁም ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናቱ ያለባቸውን ችግር በማስተካከል (ከታች ተመልክቷል) እነዚህን ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናትን ምንም ጉዳት በማይደርስባቸው ሁኔታ በራሳቸው ስር ማደራጀት በሚችሉበት መንገድ ሊዋሀዱ ይገባል፡፡

ውህደቱ እንዴት መፈፀም እንዳለበትም ሁለቱ አብያተ ክርስቲያናት ሊነጋገሩ የሚገባ ቢሆንም፣ አጠቃላይ ውህደት በሚከብዱባቸው ስፍራዎች ላይ ግን ፖለቲካው አካባቢ የምንመለከተውን የፌዴሬሽንና የኮንፌዴሬሽን አይነት ትስስር በመፍጠር፣ ለምሳሌ የባለራዕይ ቤተክርስቲያኗን ስም የአጥቢያ ስም በማድረግ፣ ባለራዕዩነ በቤተክርስቲያኗ ላይ በመሪነት በመሾም ... በመሳሰሉት መንገዶች ጥምረተ ሊፈፀም ይችላል፡፡

ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ማስተካከል የሚገባቸው ነገር፣

- የየትኛውም ቤተክርስቲያን፣ ጎብረት፣ አጥብያ ... መሪዎች በባለቤትነት ስሜት በራሳቸው መንገድ እንዲሄዱ ከአሳሪ ደንብና መመርያ ነፃ ማድረግ፣
- አዲስ ቤተክርስቲያን፣ ጎብረት፣ አጥብያ ... ለመከፈት የተቀመጡትን አሳሪ መስፈርቶችና ቅድመ ሁኔታዎችን ቀለል ማድረግ፣ የከተሞች መስፋፋትን ግምት ውስጥ በማስገባት ቤተክርስቲያንን ተደራሽ ማድረግ፣ የትኛውም አማኝ ልቡ

በተነሳሳበት ስፍራ ላይ ቤተክርስቲያን መትከል ቢፈልግ በቤተክርስቲያኗ አሰራርና ደንብ እንዲሰራ ፍቃድ መስጠት፣ መከታተልና መደገፍ፣

- የእግዚአብሔርን ቅዱስ አሰራር መቀበል፣ ኤልያብ እያለ ዳዊት ቢቀባ ዳዊትን አለመግፋትና የዳዊትን ቅባት መርምሮ ዳዊትን ወደ አገልግሎት ማሳለፍ፣
- ሰዎችን ወደ ተለያየ አገልግሎት ለማሳደግ የሚከተሉትን ጥብቅ አሰራር ቀለል ማድረግ፣
- ከሌላ ስፍራ የሚመጡ አማኞች ላይ መስፈርት አለማብዛት፣ የዚያን ሰው ማንነት ማጣራት ካስፈለገ እንኳን በአብያተ ክርስቲያናቱ ጎብረት በኩል ባለው የመረጃ ስርዓት የሰውየውን ማንነት ማጣራት፣
- በስፈር የሚቀራረቡ ሰዎች ተሰባስበው በራሳቸው መንገድ አገልጋይ ጠርተው ለሚያደርጉት አምልኮ እውቅናና ድጋፍ መስጠት፣
- አገልጋዮች በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲደግፉ በትርፍ ጊዜያቸውና ፍቃድ እየወሰዱ የፈለጉበት ስፍራ ሄደው ማገልገል እንዲችሉ ማመቻቸትና ምዕመኑ ለቤተክርስቲያን የሚያደርገውን ድጋፍና አክብሮት በማቴ.10፡40-42, ማር.9፡41 ... መንፈስ ለአገልጋዮችም እንዲያደርግ ማስተማር፣

በዚህም ወንጌላውያኑ ጥብቅ አሰራራቸው ለቀቅ በማድረግ ያፈኑትን ወንጌል የሚፈታበትንና ባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናቱን የሚያስተናግዱበትን አሰራርና መዋቅር መፍጠር ይገባቸዋል፡፡

እዚህ ጋር አንዳንድ የባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት አመራሮች ከነበራቸው ስልጣንና ጥቅማ ጥቅም አንፃር ውህደቱ እንዳይሳካ የሚያንገራግሩ ወይ የማይመቹ ውሳኔዎችን የሚያሳልፉ ከሆነ ወይ "እኛ በቅድስና እየሰራን ነው ሌላው ራሱን ያስተካክል" በማለት ለዘራፊዎቹና ለወንበዴዎቹ ሽፋን የሚሰጡ ከሆነ በነሱ ስር ያለው ህዝብ ከላይ የተመለከትናቸውን ችግሮችንና በዚህ የተሐድሶና የአንድነት ጥሪ የሚፈጠረውን የቤተክርስቲያን ቅድስናና አንድነት በማስተዋል፣ እንደ ኢየሱስ በ"የቤትህ ቅናት ይበላኛል"(ዮሐ.2፡17) መንፈስ፣ እንደ ነህምያ "... ከእንግዲህ ወዲህ መሳለቂያ እንዳንሆን..." (ነህ.2፡17) መንፈስ ... ይህንን የቅድስናና የአንድነት ጥሪን በግሉ ስኬታማ ሊያደርግ ይገባል፡፡

መንግሥትም ማንም ሰው ተነስቶ የኃይማኖት ድርጅት ለማቋቋ ፍቃድ ስለጠየቀ ብቻ ፍቃድ ከመስጠት ይልቅ አንድ አዲስ የኃይማኖት ድርጅት ሲቋቋም የኃይማኖት ድርጅቱ እንዲቋቋም ምክንያት የሆነውን፣ ይህም የኃይማኖት ድርጅቶቱ ከነባር የኃይማኖት ድርጅቶች የሚለይበትን ነገር ሳያስቀምጥ እንዲቋቋም መፍቀድ የለበትም፣ ያለበለዚያ ምንም ልዩነት ሳይኖር ለስም ለውጥ ብቻ የኃይማኖት ድርጅት እንዲቋቋም የሚፈቀድበት አሰራር ሊቀየር ይገባል፡፡

በአንዳንድ ሀገራት ላይ የምንመለከተው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ዝቅጠት በኛ ሀገር ላይ ሊደገም አይገባም፣ ሀገሪቱ ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ፕሮግራሞች አሏት፣ ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን "ከተከፋፈለች መንግሥትነት"(ማር.3፡24)፣ ከዘራፊዎች፣ ከወንበዴዎችና ከእርኩሶች ተላቃ በቅድስናና በአንድነት እግዚአብሔርን የምታመልክበት፣ በቄስ በሊና በኩል የተተነበየውን ተሐድሶ የምትቀበልበት፣ እግዚአብሔር ከ3,000 አመታት በፊት በነብዩ ዳዊት በኩል ለሀገሪቱ የተናገረውን "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች"(መዝ.68፡31) ትንቢት ፍፃሜ የምትቀበልበት፣ ከ2,000 አመታት በፊት በመንፈስ ቅዱስ ምሪት፣ በመልአኩ ትዕዛዝና በሐዋርያው ፊሊጶስ አገልግሎት በጋዛ ምድረበዳ ስለ ኢትዮጵያ የተጀመረው ስራ ፍፃሜ የሚያገኝበት(ሐስ. 8፡26-39)፣ ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር የምትሰግድበት(መዝ.72፡9)፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ለእግዚአብሔር ምልጃና ቁርባን የሚያቀርቡበት(ሶፎ.3፡10) ብሎም ህዝቦቿ ለኢየሱስ ዳግም ምፅአት የሚዘጋጁበት ጊዜ ሊደረግ ይገባል፡፡

ፈጣሪ ለኢትዮጵያ ያዘጋጀው የክብር ጊዜ እጅግ ድንቅ እንደሆነ፣ ሌላው ይቅርና እስራኤል እንኳን ኢትዮጵያ ላይ በሚገለጠው የእግዚአብሔር እጅ የምትገረምበት ጊዜ እንደሚመጣ መጽሐፉ ይናገራል፣

> አሞ.9፡7 "የእስራኤል ልጆች ሆይ፣ እናንተ ለኔ እንደ ኢትዮጵያ ልጆች አይደላችሁምን? ይላል እግዚአብሔር ..."

ነገር ግን ሀገሪቱ እነዚህ የተስፋ ቃሎቿ ጋር የምትደርሰው እንደዚህ ተወዛግባ ሳይሆን ወደ ህግና ስርአት በመመለስ ነው፡፡

6.3. በፕሮቴስታንት ላይ እየቀረቡ ያሉ የተሳሳቱና ትክክለኛ ትችቶች

በፕሮቴስታንት ላይ እየተሰጡ ያሉት ትችቶች በዋናነት የሚያተኩሩት ከመዝሙርና ቤተክርስቲያኗ ከተከተለችው የካሪዝማቲክ(የጸጋ) አገልግሎት ይህም አዲስ ቋንቋ(ልሳን)፣ ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ጋር በተያያዘ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ ትክክለኛ የሆኑትንና ስህተት የሆኑትን ትችቶችን ለያይተን እንመለከታለን፡፡

6.3.1. መዝሙር

ከመዝሙር ጋር በተያያዘ በፕሮቴስታንት ላይ የሚቀርበው ሂስ "መዝሙሮቻቹ ያሬዳዊውን ስልት አይከተሉም፣ በዚህም መዝሙሮቹ ከመዝሙርነት ይልቅ ዘፈን ይመስላሉ" የሚል ነው፡፡

- የተሳሳተ ትችት

መዝሙርን በሰሜን ኢትዮጵያው ያሬዳዊ ስልት መገደቡ ጠባብተኝነት ይባሱኑም መርገምት መሆኑን 4.4.1.6 ክፍል ተመልክተናል፣ በዚህም መዝሙርን ያለ ያሬዳዊ ስልት "ውግዝ ከም አርዮስ" የሚባለው የተሳሳተ ትችት ነው፡፡

- ትክክለኛ ትችት

አንዳንድ ዘማሪያን በታወቁ ዘፈኖች ዜማና ከላሲካል መዘመራቸው ስህተት ነው፣ ይህ ተለይቶ መወገዝ አለበት፣ ለሰይጣን በቀረበ የመስዋዕት ዕቃ ለቅዱሱ ማቅረብ ስህተት ነው፣ መስዋዕቱም መልካም መዓዛ እንደሌለው እንደ ቃየል መስዋዕት ነው::

- ለወደፊት ሊስተዋል የሚገባ

በ4.4.1.6 ክፍል እንደተመለከተው ሰው በውስጥ በመንፈሱ ባስደሰተው መንገድ መዘመሩ ችግር የሌለው መሆኑ እንዳለ ሆኖ ለወደፊቱ ጥንቃቄ ሊደረጉባቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ፣ ይህም ለአዕምሮ የማይመቹ(ሮሜ.12፡1)፣ አርኩሳኑ መናፍስት አካባቢ የሚታወቁ እስታየሎችና ዝሙታዊ ዳንሶች ከመዝሙር ሊርቁ ይገባል::

ይህንን ወደ ሀገራችን አውርደን ስንመለከተው የመንዙማና የቃልቻ ቤት የድቤ አመታቶችና ዜማዎች፣ ደቡብና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ አካባቢ ያሉት መቀመጫ ተኮር እንቅስቃሴዎች፣ ኦሮሚያ ውስጥ የምናየው በዛር የተያዘች ሴት የምታደርገው አይነት እራስን እንደ እንዝርት የማሾር እንቅስቃሴ፣ አማራ አካባቢ ያለው የእባብ አንገት እንቅስቃሴ አይነት እስክስታ፣ ትግራይ አካባቢ ያለው የአንድ ወንድ አንድ ሴት ለብቻ ተነጥለው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንደዚሁም በውጪ ሀገር ባህል ተፅዕኖ ምክንያት ወደ ሀገራችን እየገቡ ያሉ ዝሙታዊ ዳንሶች፣ እጅን የኩብራ እባብ እንቅስቃሴ አስመስሎ የሚከናወኑ ዳንሶች፣ እንደ እባብ ከእግር አንስቶ እስከራስ ድረስ የሚደረግ ዝግዛጋማ ዳንሶች ... በሙሉ ከዝማሬ ሊርቁ ይገባል::

ስለዚህ ትክክለኛውን፣ ስህተቱንና ለወደፊት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡትን የዝማሬ እስታየሎች ተለይተው ሊታወቁ ይገባል::

6.3.2. <u>የካሪዝማቲክ መንገድ (መንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች - አዲስ ቋንቋ(ልሳን)፣ ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ...)</u>

በፐሮቴስታንቱ አካባቢ የምንመለከተው የካሪዝማቲክ እንቅስቃሴ ላይ ብዙ ትችቶች ሲሰጡ ይታያል፣ ከነዚህ ሂሶች ውስጥ ትክክለኛ የሆኑት፣ የተሳሳቱትንና ለወደፊት ጥንቃቄ ሊደረግባቸው የሚገቡትን ለይተን እንመለከታለን::

6.3.2.1. <u>አዲስ ቋንቋ (ልሳን)</u>

"ልሳን" ማለት አዲስ ቋንቋ ማለት ነው፣ ከልሳንም ጋር በተያያዘ እንደ መዝሙሩ የተሳሳቱ ሂሶች፣ ትክክለኛ ሂሶችና ለወደፊቱ ጥንቃቄ ሊወሰድባቸው የሚገቡ ነገሮችን እንመለከታለን::

- <u>የተሳሳቱ ትችቶች</u>

ከልሳን(አዲስ ቋንቋ) *ጋር* በተያያዘ የሚሰጡቱ ሂሶች በዋናነት ልሳን *መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሆኑን ባለማወቅ ነው፤ ይህንንም* ከስር *መሠረቱ ብንመለከት፣ እግዚአብሔር የሰው ልጅን ሲፈጥር በመጀመሪያ በራሱ መልክ መንፈስ የሆነውን የሰውን ማንነት በስድስተኛው ቀን ፈጠረ(ዘፍ.1፡27)፣ ከዚያ ይህን መንፈስ ከአፈር ስጋ አበጀው(ዘፍ.2፡7)፣ ከዚያ በዚህ ስጋ ውስጥ ህያው ነፍስ አደረገ(ዘፍ.2፡7)፣ ይህ የስነ ፍጥረት ታሪክ ነው፣ በመጀመሪያ "ፈጠረ" ከዚያ "አበጀው" ከዚያ "እስትንፋስ እፍ" አለበት፣ በዚህም ሰው በሥላሴ ምሳሌ ስጋ፣ መንፈስና ነፍስ ሆኖ ተፈጠረ፡፡*

አብዛኛው ክርስቲያን ስለ ስጋና ነፍስ ማንነቱ እንጂ ስለ መንፈስ ማንነቱ ብዙም አያውቅም ነገር ግን መንፈስ የሆነችው የሰው ማንነት መንፈስ በመሆኗ ዓለሟ መንፈሳዊው ዓለም ነው፣ መንፈስ ከሆነው እግዚአብሔርም ጋር(ዮሐ.4፡24) በልሳን ትነጋገራለች(1ቆሮ.14፡2)፣ በልሳን ፀሎትም ታቀርባለች(1ቆሮ.14፡14) ...

በርግጥ ይህ ስጦታ የሚገለጠው ሰዎች ትክክለኛው የእምነት መስመር ውስጥ ሲገቡ ነው፣

ማር.16፡17 "<u>ያመኑት</u> እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል ... <u>በአዲስ ቋንቋ ይናገራሉ</u> ..."

በዚህም ይህን አዲስ ቋንቋ መናገር የማይችሉት በሙሉ ትክክለኛውን እምነት ያልያዙና መንግሥተ ሰማያትን የማይገቡ(ዮሐ.3፡3) ሰዎች ናቸው፣ በዚህም ልሳን የሚባለው አዲስ ቋንቋ የሚያስወግዝ ሳይሆን ትክክለኛ መንገድ ላይ የመሆን አለመሆን ማረጋገጫ ጸጋ ነው፡፡

- <u>ትክክለኛ ትችቶች</u>

ከልሳን *ጋር* በተያያዘ ትክክለኛ ሂሶችም ሲሰጡ እንመለከታለን፣ እነዚህም ቀድሞውኑም በመጽሐፍ ቅዱሱም እንዲስተካከሉ የተነገሩና አሁንም ሳይስተካከሉ የቀሩ ናቸው፣ እነሱም፣

- 1ቆሮ.14፡23 "እንግዲህ ማኅበር ሁሉ ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ፡፡ አብደዋል አይሉምን?"
- 1ቆሮ.14፡27 "በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጉም፤"
- 1ቆሮ.14፡19 "ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአዕምሮዬ ልናገር እወዳለሁ፡፡"

እነዚህ ዛሬም የሚስተዋሉና መስተካከል ያለባቸው ችግሮች ናቸው፡፡

- <u>ለወደፊቱ ሊስተዋል የሚገባ</u>

ከትክክለኞቹ ልሳናት ጋር በተያያዘ አንዳንድ ሰዎች አግባብ ያልሆነ ሂስ ሲሰጡ እንመለከታለን፣ ከነዚህ ከመንፈስ ጋር የሚገናኙ አሰራሮች ላይ ያለ እውቀት ሂስ መስጠት አደጋው የከፋ ነው፣

- ማቴ.12፡32 "በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም፡፡"
- ዕብ.10፡28-29 "የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርህራሄ ይሞታል ... የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ እንዴት የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል፡፡"

ስለዚህ ከመንፈስ ቅዱስ አሰራር ጋር በተያያዘ ያለ እውቀት ሂስ ከመስጠት ዝም ማለቱ የተሻለ ነው፣ እግዚአብሔር በቅድስናው ላይ ለሚናገሩት ምህረት የለውም፣ መንፈስ ቅዱስ ላይ የተናገረ ፍርዱ ሲአል መሆኑን አሁኑኑ መረዳት አለበት፣ ስለዚህ እውነታ እስኪገባን ድረስ አስተያየት ከመስጠት መቆጠቡ የተሻለ ነው፡፡

6.3.2.2. <u>ሌሎች የጸጋ ስጦታዎች - ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ...</u>

- <u>የተሳሳቱ ትችቶች</u>

የጸጋ ስጦታ የሌለባቸው አብያተ ክርስቲያናት በነዚህ ፕሮቴስታንት አካባቢ በሚታዩት የጸጋ ስጦታዎች ላይ የተለያዩ ሂሶችን ሲሰጡ ይታያል፣ ይህ ስህተት ሲሆን ከስህተትም አልፎ ከላይ እንደተመለከትነው የማይሰረይ ኃጢያት ነው፡፡

- <u>ትክክለኛ ትችቶች</u>

የሐሰተኛ ነብያቶች የመበራከት ችግር እንዳለ ሆኖ ከትክለኛ ትንቢቶች ጋር በተያያዘ "ሰዎች በሚሰሙት ትንቢት በመያዝ ሐሳባውያን፣ ሰነፍና ብቸኛ እየሆኑ ይገኛሉ" እየተባለ ያለው ሂስ ትክክለኛ ሂስ ነው፡፡

"ትንቢት" ማለት በህይወት ውስጥ በሆነ ጊዜ የሚደረስበት ራዕይ እንጂ የዛሬ ጉዳይ አይደለም፣ ትንቢት የሚነገረውም ሰው ባለበት ሁኔታ ተስፋ ሳይቆርጥ በያዘው ነገር እንዲበረታ እንጂ በምኞት ባህር ሰጥሞ ከህይወት ሩጫና ውድድር ገለል እንዲል አይደለም፣ ሰው የተነገረውን ትንቢት ብቻ እያየ በስንፍና የዛሬውን በርትቶ አለመያዙ በራሱ ከተነገረው መንገድ እንኳን ያወጣዋል፣

ምሳ.19፡3 "የሰው ስንፍና መንገዱን ታጣምመበታለች ..."

ከሁሉ በላይ ደግሞ ደግሞ ሊስተዋል የሚገባው ነገር ትንቢት ሕግ አይደለም፣ የተነገረው ትንቢት ሊሻር እንኳን ይችላል(1ቆሮ.13፡8)፡፡

በዚህም የትኛውም አማኝ የተነገረውን ትንቢት በልቡ ይዞ፣ ዛሬ ላይ ማግኘት ያለበትን ጥቃቅን ጥቅሞችን ሳይንቅ፣ በህይወቱ ውስጥ ያሉትን ዕድሎች አሟጦ በመጠቀም፣ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ራስን በማስተካከል፣ ከማኅበረሰቡ ጋር ተሳስሮ በመኖርና በ1.4.2 ክፍል በቀረበው የመጽሐፍ ቅዱሱን የጠንካራ ሠራተኛነት መርህ በመተግበር እንጂ ሐሳባዊ የምኞት ባህር በመዋኘት አይደለም።

ይህ ሂስ በአብዛኛው የሚመለከተውም የክርስትናን አስተምህሮ በሂውማኒዝም አስተምህሮ ቀይጦ የመጣውን የብልፅግና ወንጌል ተከታዮችን ነው፣ በብልፅግና ወንጌል አስተህሮ ሰዎች የሚባረኩት ሰርተው ሳይሆን በተአምራዊ መንገድ በሚወርድ ሐብት እንደሆነ የሚያስተምር ሲሆን፣ አምልኮቱም የፉከራ፣ የሽለላና "የእምነት ልምምድ" በሚባለው ሰዎች ከተነገራቸው ትንቢት ጋር በሐሳብ የሚያስዋኝ አምልኮ ነው።

ማንም ሰው እግዚአብሔር "መኪና እሰጥሃለሁ" ስላለ የሰው መኪና ሲመኝ፣ በሐሳብ ቁጭ ብሎ መሪ እያዞረ፣ ነዳጅ እየሰጠ ... መቃገጥ የለበትም፣ ይህ "የእምነት ልምምድ" ለመጽሐፉ እንገዳ አሰራር ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነት መጠን እንዳካፈለው <u>እንደ ባለአዕምሮ</u> እንዲያስብ እንጂ ማሰብ ከሚገባው በላይ አልፎ እንዳያስብ ይመክራል(ሮሜ.12፡3)፣ ሰው የተነገረው ትንቢት ጋር የሚደርሰው የእግዚአብሔርን <u>ጊዜ</u> በመጠበቅ፣ በመፀለይና በ1.4.2 ክፍል እንደተመለከተው በያዙት ስራ ጠንክሮ በመስራት ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ "እባርክሀለሁ" ተብለው በሐብት የተባረኩትን ሰዎችን ሐብት ስንመለከት ሐብታቸው በተአምራዊ መንገድ የወደቀላቸው ሳይሆን በያዙት ስራ ላይ እግዚአብሔር በሰራው የማባዛት ስራ ነው።

ሌላው ከጸጋ ስጦታ አጠቃቀም ጋር እየተፈጠረ ያለው ችግር በቤት ለቤት ከሚደረጉ ፀሎቶች ጋር የተያያዘ ችግር ነው፣ ይህም አገልጋዮች እንደ በዓል ነብያት(1ነገ.18፡25-39) በከባድ ድምፅ ጎረቤትና ሰፈሩን የሚረብሹበት፣ አንድ ሚርተኛ፣ ቡዳ ... በራዕይ ተመልክተው ያለ ጥበብ በመናገር ቤተሰቡን ከጎረቤቶቹ በሙሉ የሚያጣሉበት፣ ለአማኙ የመጣውን የትንቢት ቃል አማኝ-አህዛቡ ሁሉ እየሰማ በመናገር፣ ዕንቁዎቻቸውን በዕርያ ፊት እየጣሉባቸው የሰዎችን ማኅበራዊ ህይወት እየነዱ ያሉበት አሰራር ነው።

ከፈውስም ጋር በተያያዘ ባዩት መገለጥ የራስን ዋጋ ከፍ ለማድረግ የሚደረገው ሩጫ ስህተት ነው፣ በአደባባይ "ከኤች አይ ቪ፣ ጉበት ... በሽታ ተፈወስክ" ከማለት ለሰውየው በግሉ መንገር፣ ሰውየው በፈለገበት ጊዜ እንዲመሰክር ማድረግ የተሻለ ነው።

- <u>ለወደፊቱ ሊስተዋል የሚገባ</u>

ከሁሉም የኃይማኖት ተቋማት በተለየ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰፊ መንፈሳዊ እንቅስቃሴዎችን (ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ...) እንመለከታለን፣ ይህ ደግሞ እየሆነ ያለው ስር ሳይምሱ፣ ቅጠል ሳይበጥሱ፣ የጅብ ቅንድብ ... ሳይሉ መጽሐፍ ቅዱሱ

እንደሚያዘው “በኢየሱስ ስም” ስልጣን መሆኑን ስንመለከት የጸጋውን ቅዱሳዊነት ብሎም የቤተክርስቲያኗን ትክክለኛነት ያረጋግጣል።

የሚገርመው ደግሞ አብዛኞቹ የእምነት ተቋማት እነዚህ የጸጋ ስጦታዎች መኖራቸውን ያውቃሉ ነገር ግን እውቀታቸው በታሪክ እንጂ በተጨባጭ አይደለም፣ በዚህም እነዚህ የእምነት ተቋማት ከኔትዎርክ ውጪ የሚሰሩ፣ የድሮውን ታሪክ ብቻ የሚያወሩ “የታሪክ አስተማሪዎች” ብቻ ሆነው እንመለከታለን፣ መጽሐፍ ቅዱሱ፣

2ጢሞ.3፡5 “የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ከደዋል።”

የሚላቸው እነዚህን ከኔትዎርክ ውጪ የሚሰሩትን የታሪክ አስተማሪዎችና ትምህርት ቤቶቻቸውን ነው፣ ይህ ደግሞ እየሆነ ያለው “ጸጋው ይበዛል” በተባለበት በመጨረሻ ዘመን(ሐስ.2፡17-18) መሆኑን ስንመለከት በአሁኑ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ(ትንቢት፣ ተአምራት፣ ፈውስ ...) በተጨባጭ የሌላት ቤተክርስቲያን “ቤተክርስቲያን” መባል የሌለባት ከመስመሩ ውጪ ያለች መሆንዋን እርግጠኛ መሆን አለባት።

በርግጥ ፕሮቴስታንት ጋር የምንመለከታቸው እነዚህ ጸጋዎችም መቶ በመቶ የጠሩ አይደሉም፣ ሐሰተኞችም ተደባልቀው እየሰሩ ናቸው፣ ልክ በነኤርምያስ ዘመን እንደነበረው ሐሰተኛና ትክክለኛውን ነቢይ መለየት እንደከበደበት ወቅት(ኤር.28) ወይንም 1ነገ.13፡1-31 ላይ እንደተመለከተው ሐሰተኛ ነቢያት ትክክለኛ ነቢያትን እንዳሳሳቱበት ጊዜ፤ ነገር ግን የጸጋ ስጦታ ከሌላት እያለት ከስህተቶችና ከአሳሳቾች ጋር የምትንደፋደፈው የተሻለች ናት ምክንያቱም ያለው ችግር የመደባለቅ ጉዳይ እንጂ ከኔትዎርክ ውጪ የመሆን ችግር አይደለምና።

በረሀ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ምንጭን ሳየዩ ከርቀት፣ ጭው ካለው በረሀ መካከል የበረሀ ምንጭ(Oasis) ያለበትን ስፍራ ለይተው ያውቃሉ፣ አረንጓዴ ዛፎች ጭው ካለው በረሀ ተለይተው በተሰበሰቡበት ስፍራ ምንጭ አለ፣ እነዚህ ዛፎች ውስጥ ከላይ በ6.2.2 ስር እንደተመለከተው መልካምም መጥፎውም ዛፍ ይሰብሰቡበት እንጂ ምንጩ ያለው እዚያው ነው፣ እንደዚሁ ጥሩም መጥፎም ሰዎች ይሰብሰቡበት እንጂ የትኛውም ሰው ትክክለኛው የመንፈሳዊው ህይወት ምንጭ የቱ ጋር እንዳለ ጭው ካለው መንፈሳዊ በረሀ ውስጥ መለየት መቻል አለበት።

ስለዚህ ማንም ሰው መጥፎው ዛፍ የራሱን ቅጣት እንደሚሰጠው አውቆ፣ በረሀውንና ምንጩን ለይቶ ሊመለከትና ከበረሀው ወደ ምንጩ፣ ብሎም ወደ ኔትዎርኩ ሊጠጋ ይገባዋል።

6.4. የቤተክርስቲያኗ ድክመቶች

ከላይ እንደቀረበውም ቤተክርስቲያኗ በትክክለኛ መንገድ ላይ በመሆኗ የእግዚአብሔር እጅ በሷ ላይ እየሰራ እንደሆነ ተመልክተናል ይሁን እንጂ ቤተክርስቲያኗ እየኖረች ያለችው የእግዚአብሔርን እጅ ፈፅሞ አይተው ከማያውቁት ከሌሎቹ ኃይማኖቶች ተመሳስላ ነው፣ ይህ ደግሞ ትልቅ ድክመት ነው፣ ይህ ድክመትም እየታየ ያለው በእያንዳንዱ ምዕመን፣ በአብያተ ክርስቲያናቱና በአብያተ ክርስቲያናቱ ጎብረት ነው፣ ቀጥለን በስፋት እንመለከታለን፡፡

6.4.1. የምዕመናን ድክመቶች

ምዕመኑ ጋር የሚታየው ድክመት መጽሐፍ ቅዱሱን በየአውዱ ያለመመልከት ችግር፣ “በኢየሱስ ማመን” የሚለውን መሠረታዊ እውቀት ያለመረዳት ችግር፣ ጠንካራ ኃይማኖተኛነትን ለሌላ ጊዜ ፕሮግራም የማድረግ ችግርና የወንጌል ምስክርነት ስራን የሁሉም አማኝ ስራ አድርጎ ያለመመልከት ችግሮች ናቸው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

6.4.1.1. መጽሐፍ ቅዱሱን በየአውዱ ያለመመልከት ችግር

ኃይማኖቶች መካከል የተፈጠረው መሠረታዊ ልዩነት በዋናነት መጽሐፍ ቅዱሱን በየአውዱ ባለመመልከት የመጣ ችግር መሆኑን ከላይ በቀረቡት አምስቱ ምዕራፎች ውስጥ በስፋት ተመልክተናል፣ “ኢየሱስ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት ነው ወይስ ለዓለም፣ ሰንበት በሰባተኛው ቀን ነው ወይስ በኢየሱስ ነው፣ ጽድቅ በስራ ነው ወይስ በኢየሱስ በማመን ነው፣ ገነት በዚህች ምድር ነው ወይስ በተተኪዋ ምድር፣ ጥምቀት በአብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ስም ነው ወይስ በኢየሱስ ስም ነው … የመሳሰሉትን መመልከት ይቻላል፡፡

በዚህ ዘመንም ብዙዎች አውዳዊ የሆኑትን የመጽሐፍ ቅዱሱን ክፍሎች በግርድፉ በመመልከት ሲፈተኑ እየተመለከትን ነው፣ ለምሳሌ “የወር አበባ የተመለከተች፣ የዘር ፈሳሹ የፈሰሰው፣ ቁላው የተቀጠቀጠ፣ ለምጻም … እርኩስ ነው፣ ቤተመቅደስ እንዳይገባ …” የመሳሰሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት በሌሎች ኃይማኖት ተከታዮች ሲጠቀሱ አማኞች ሲደናገጡ እየተመለከትን ነው፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ኃይማኖታዊ ስርአቶች የተደነገጉት በራሳቸው አውድ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ የሁለት ኃይማኖቶች መመርያ ነው፣ የአይሁድና የክርስትና፤ ክርስትና ሳይመጣ በፊት የአይሁድ የኃይማኖት ስርአቶች ሲከናወኑ የነበሩት በሚታዩና በሚጨበጡ ነገሮች ነበረ፣ የድንጋይ ፅላት፣ የተገነባ ቤተመቅደስ፣ የሚሰዋ እንስሳ፣ የሚቃጠል መስዋዕት…፣ ዛሬ እነዚህ የአይሁድ ኃይማኖታዊ ስርአቶች በክርስትናው በሌላ ነገር ተተክተዋል፣ ኃይማኖታዊ ስርአት፣ ወግ … ሊሻር ይችላልና፣ የማይሻረው ህግ ብቻ ነው፡፡ የአይሁድ ኃይማኖት ስርአትና የክርስትና የኃይማኖት ስርአት የተለያየ ነው፣ ከላይ የተመለከትናቸው ቤተመቅደስን ያረከሳሉ የተባሉቱ ኃይማኖታዊ ስርአቶች የተደነገጉት ለአይሁድ ኃይማኖት ነው፡፡ ለአይሁድ የተሰጠ የአምልኮ ስርአትና ለክርስትና የተሰጠው

ስርአት ይለያል፣ እነዚህ ቤተመቅደስ እንዳይገቡ የተከለከሉት ሰዎች ክልከላ ትክክኛ ትርጉም የሚኖረው በብሉይ ኪዳን ዘመን አሰራር ነው፣ በአዲሱ ኪዳን ቤተክርስቲያን እንጂ ቤተመቅደስ እራሱ የሰው ልጅ ነው፣ በዚህም እነዚህ ሰዎች "ቤተመቅደስ እንዳይገቡ" ሲባል ለብሉይ ኪዳኑ አሰራር እንጂ ለአዲስ ኪዳኑ አሰራር እንዳልሆነ ግልፅ ነው።።

ከክርስትናም ጋር ተያይዞ "ኢየሱስ አምላክ ሆኖ እንዴት ተገደለ" የሚሉ እና በተቃራኒ ደግሞ "ኢየሱስ ሰው ሆኖ እንዴት ይመለካል"፣ "እግዚአብሔር አንድ ሆኖ እንዴት ሦስት ይሆናል" የሚሉ እና በተቃራኒ ደግሞ እግዚአብሔር ሦስት ሆኖ እንዴት አንድ ይሆናል" ... በመሳሰሉት ጥያቄዎች ብዙዎች ግራ ሲጋቡ እየተመለከትን ነው።።

እነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ የተሰሩትን ማደናገሪያዎች ለመረዳት አንዱን ለምሳሌ ብንወስድ፣ "ኢየሱስ አምላክ ሆኖ እንዴት ይደበደባል፣ ይራባል፣ ይገደላል ..." የሚለውን ብንመለከት፣ ማደናገሪያ ጥያቄው የተመሠረተው የኢየሱስ የሰው-አምላክ <u>ተዋህዶነት</u> ውስጥ ያለውን የስጋዊ ማንነትን ባህሪ ለአምላካዊው ማንነት በመስጠት ነው ነገር ግን የተደበደበው፣ የተራበው፣ የተገደለው ... የኢየሱስ ስጋዊ ማንነት እንጂ አምላካዊ ማንነቱ አይደለም፣ የኢየሱስን አምላካዊ ማንነት ይቅርና የሰውን ነፍሳዊ ማንነት እንኳን ማንም ሊጎዳት አይችልም፣

ማቴ.10፡28 "ስጋን የሚገድሉት ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ።።"

ዕውቀት የሌለውን ሰው ማደናገር የፈለገ ሰው ግን ይህንን የአንድ ነገር ሁለት ማንነቶች አንስቶ አንዱን ማንነት ከሁለተኛው ማንነት ጋር አያይዞ ማምታታት ይችላል፣ ነገር ግን ክርስትና የገባው አማኝ እንደዚህ አይነት አደናጋሪ ጥያቄዎች ሲነሱበት አስቀድሞ ጥያቄውን በየአውዱ ነው የሚመለከተው።።

"እግዚአብሔር አንድ ሆኖ እንዴት ሦስት ይሆናል ወይንም እግዚአብሔር ሦስት ሆኖ እንዴት አንድ ይሆናል" የሚለውም ማምታቻ በተመሳሳይ መልኩ የሚታይ እውነታ ነው፣ ይህንን የአንድነትና ሦስትነት አሰራር በ5.1 ክፍል በስፋት ስለተመለከተ እዚህ ጋር ባንደግመውም በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሰዎች ግራ እየተጋቡ ያሉት መጽሐፍ ቅዱሱን በአውዱ ባለመመልከት ነው።።

6.4.1.2. <u>"በኢየሱስ ማመን" የሚለውን መሠረታዊ እውቀት ያለመረዳት ችግር</u>

ይህንን መሠረታዊ እውቀት በማስያዝ ላይ ወንጌላውያኑ አብያተ ክርስቲያናት ባይታሙም ከላይ እንደተመለከትነው በባለራዕይ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እየተፈጠረ ባለው የአየር ባየር አሰራር ምክንያት "በኢየሱስ ማመን" የተባለው መሠረታዊ ነገር ላይ ሁሉም አማኝ መሠረታዊ ግንዛቤ እየያዘ አይደለም፣ ትክክለኛ እምነት የሌለው ደግሞ ገነት ስለማይገባ ይህንን "በኢየሱስ ማመን" የሚባለውን አሰራር አጥርቶ ማየቱ ወሳኝ ነው።።

ከመነሻው ስንመለከት፣ የሰው ልጅ በኃጢያት ከመውደቁ በፊት በኤደን ገነት ውስጥ ይኖር ነበረ፣ ከዚያም በሰይጣን ተታሎ ኃጢያት በመስራቱና ኃጢያተኛ ደግሞ ገነት ውስጥ

መኖር ስለማይገባው፣ የሰው ልጅ ከኤደን ገነት ተባረረ፣ ከዚያም እንዲሞትና ሲሞትም ለሰይጣን ወደ ተዘጋጀው ሲኦልም እንዲገባ ተፈረደበት፣ ይሁን እንጂ ፈጣሪ ወደ ሲኦል እየጎረፈ ላለው የሰው ልጅ በማዘን መጀመሪያ ወደ ፈጠረለት የገነት ህይወት ለመመለስ አሰበ፣ ለዚህ ደግሞ የሰው ልጆችን አጠቃላይ የኃጢያት ዋጋ መክፈል የሚችለውን ኢየሱስን ላከ፣ ኢየሱስም ሰዎች "የኃጢያት ዋጋ ሞት ነው" የሚለውን ሕግ አልፈው ገነት መግባት እንዲችሉ፣ የአጠቃላይ የሰው ልጆች ኃጢያት ምትክ ሆኖ በመስቀል ላይ ዋጋ ከፈለ፣ በዚህም ሰዎች እንዲያው በዚህ በኢየሱስ ስራ አምነው ገነት የሚገቡበት መንገድ ተዘጋጀ።።

በዚህም "በኢየሱስ ማመን" የሚለው ሐሳብ በዋናነት አራት <u>ተከታታይነት ያላቸውን የኢየሱስ ማንነትና አገልግሎቶችን የያዘ ሐሳብ ነው፣ ይህም የኢየሱስ ኦሪጂናል ማንነት፣ ኢየሱስ በምድር ላይ የሰራው ስራ፣ ኢየሱስ አሁን እየሰራ ያለው ስራና ኢየሱስ ለወደፊት በሚሰራው ስራዎቹ ማመን ማለት ነው፣ ይህም፣</u>

- ኢየሱስ ማን እንደሆነ? <u>ኢየሱስ ጌታ ነው፣</u>
- ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ ምን ሰራ? <u>የኃጢያቴን ዋጋ በመስቀል ላይ ከፍሎልኝ አፀደቀኝ፣</u>
- ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ምንስ እየሰራ ነው? <u>ያማልድልኛል፣</u>
- ኢየሱስ ለወደፊቱ ምን ይሰራል? <u>ለፍርድ ይመለሳል።።</u>

ስለዚህ የትኛውም ሰው ከሲኦል ለመዳን በዋናነት በነዚህ አራቱ የኢየሱስ ማንነትና አገልግሎቶች ማመን አለበት፣ እነዚህ አራቱ ቁም ነገሮች ሰፋ ያሉ ትንታኔ ቢኖራቸውም በዋናነት ግን "በኢየሱስ ማመን" የተባለው ትዕዛዝ አራቱ ዋልታዎች እነዚህ ነጥቦች ናቸው፣ በዚህም እያንዳንዱ አማኝ በእነዚህ አራቱ የእምነት ዋልታዎች ላይ መመሥረቱን ሊያረጋግጥ ይገባል።።

ከዚህ በመቀጠል፣ እያንዳንዱ አማኝ ሊያስተውል የሚገባው ቤተክርስቲያን የሰዎችን መዳን እንድታግዝ የተቋቋመች ተቋም በመሆኗ የትኛውም አዲስ አማኝ በኢየሱስ ሲያምን የትኛውም የፐሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በመሄድ ኃይማኖታዊ ስነ ስርዓቶችን መፈፀም አለበት፣ እነዚህም ስርዓቶች አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን የሚያደርግበት፣ የክርስቶስ ተከታይ መሆኑን በጥምቀት የሚያረጋግጥበትና የክርስቶስ አካል ለመሆን ቅዱስ ቁርባን የሚቀበልበት ስነ ስርዓቶች ናቸው።።

እምነቱ ገብቷቸው እነዚህን ኃይማኖታዊ ስነ ስርዓቶች መፈፀም ያልቻሉ፣ የመጀመርያውንና ዋናውን "ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረገውን ቃል ኪዳን" ለራሳቸው መፈፀም ይችላሉ፣ በቤተክርስቲያኗ እምነት መሠረት የሚደረገው ቃል ኪዳንም የሚከተለው ነው።።

"በሰማያት ያለኸው እግዚአብሔር ሆይ፣ እውነቱን እንድረዳ ስለረዳኸኝ አመሰግንህለሁ፣ አሁን እውነቱ ገብቶኝ ሰይጣንንና ዓለማዊነትን ክጇ አንተን ልከተል ወስኛለሁ፣ ተቀበለኝ፣ ኃጢያቴን ሁሉ ይቅር በለኝ፣ ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ፣ ስለኔ ኃጢያት በመስቀል ላይ እንደሞተ፣ አሁንም ስለኔ እንደሚያማልድ፣ ለፍርድም እንደሚመለስና እኔንም ከፍርድ እንደሚያድነኝ አምኛለሁ፣ በዚህ እምነቴም ስላፀደከኝ፣ ልጅህ ስላደረከኝ፣ በከበረው መዝገብህም ስለፃፍከኝ አመሰግንህለሁ፣ በጌታ በኢየሱስ ስም፣ አሜን።"

ከዚህ ቃልኪዳን በኋላ አማኙ በተመቸው ጊዜ የተቀሩትን ሁለቱን ኃይማኖታዊ ስነ ስርዓቶች በቤተክርስቲያን ተገኝቶ መፈፀም ይችላል።

በአጠቃላይ ስንመለከት፣ የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በትክክለኛ መንገድ ላይ እንዳለች እንደተመለከትነው ሁሉ፣ እያንዳንዱ ሰው በዚህ መስመር ድነቱን ማግኘት የሚችለው "በኢየሱስ ማመን" የሚባለውን መሠረታዊ ነገር በአግባቡ ሲረዳና የዚህ ተያያዥ ኃይማኖታዊ ስርአቶችን ሲፈፅም ነው።

6.4.1.3. <u>ጠንካራ ኃይማኖተኛነትን ለሌላ ጊዜ ፕሮግራም ማድረግ</u>

ከላይ እንደተመከተው አንድ ሰው በክርስቶስ አምኖ ሁለቱን ኃይማኖታዊ ስርዓቶች ሲፈፅም ሙሉ ክርስቲያን ይሆናል፣ ይህ ሰው ከዚያ በኋላ መኖር ያለበት በተቻለው መጠን ከኃጢያት በመራቅ፣ በመልካም ስነ ምግባር በመመላለስ፣ በቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች በመካፈል፣ መጽሐፍ ቅዱሱን በማጥናት፣ መንፈሳዊ ቻናሎች፣ መዝሙሮች፣ መጽሐፎችን... በመከታተል መንፈሳዊ ማንነቱን በማበልፀግ ሊሆን ይገባል።

ይሁን እንጂ ዛሬ ላይ አብዛኛው አማኝ ይህንን ራስን በመንፈሳዊ ነገር የማበልፀግና ለአገልግሎት የመነሳት ጊዜን ፕሮግራም የሚያደርገው ለሌላ ጊዜ ነው፣ ልክ ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ አካባቢ የሚታየው "ሰዎች አሁን ለምድራዊ ነገር ተሯሩጠው ሲያረጁ ነው ለመንፈሳዊው ነገር ራሳቸውን መለየት ያለባቸው" አይነት አመለካከት እዚህም ጋር ተፅዕኖ እያደረገ ይገኛል።

ይህ የህይወት መርህ የተሳሳተ የህይወት መርህ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣ ፈጣሪ ሰዎችን የሚፈልገው አሁን ባሉበት በጉብዝናቸው ወቅት እንዲያመልኩትና እንዲያገለግሉት ነው(መክ.12፡1, 2ቆሮ.6፡2 ...)፣ በዚህ ላይ እነዚህ ሰዎች ይህ መርህ "የቃየን መስዋዕት" አለመሆኑን መመርመር አለባቸው <u>"ቃየን ከሰብሉ እንዳደረገው እኔም ከጊዜዬ እንዲህ እያደረኩ ይሆን እንዴ?" ብለው ራሳቸውን መመርመር አለባቸው፣</u> እግዚአብሔር ቃየንን ሲረግመውም "ኮብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ" እንዳለው እነዚህ ሰዎችም ቤተክርስቲያንን ትተው የሚኮበልሉበት አሰራር ደግሞ ተጨማሪ መመሳሰልን ይፈጥራል፣ በዚህም በቃየል መንገድ ከመሄድ ከነአቤል ጋር መስዋዕት ማቅረቡ ብልህነት ነው።

6.4.1.4. <u>የወንጌል ምስክርነት የሁሉም አማኝ ስራ አድርጎ አለመመልከት</u>

በዚህ ዘመን አብዛኛው አማኝ የወንጌል ምስክርነትን ስራ የወንጌላውያን ስራ ብቻ አድርጎ ይመለከታል ይሁን እንጂ ወንጌልን መስክሮ አዳዲስ አማኞችን ማፍራት የእያንዳንዱ ክርስቲያን የውዴታ ግዴታ ስራ ነው።

ማቴ.10፡32 "... በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማይ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ።" እንደሚለው ስለ ኢየሱስ የሚመሰክር የኢየሱስን ምስክርነት ያገኛል የማይመሰክረው ደግሞ ምስክርነቱን አያገኝም፣ የእሱ ምስክርነት የሌለው ደግሞ መጨረሻው ሲኦል ነው።

ስለ ክርስቶስ አዳኝነት አማኝ ላልሆኑት ሰዎች መስክሮ ከሲኦል እንዲድኑ የማይረዳ ሰው እራሱም የተሰጠው መዳን እንኳን እንደሚወሰድበት መጽሐፍ ቅዱሱ ይነግረናል፣ ማቴ.25፡14-30 ላይ ስንመለከት፣ አንድ መክሊቱን ያልነገደባትና ያላተረፈባት ሰው በመጨረሻው ዘመን "ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት ... የማይጠቀመውንም ባሪያ በውጪ ወዳለው ጨለማ አውጡት..." እንደሚባል ይናገራል።

ኢየሱስ ብዙ ስፍራዎች ላይ ስለ ክርስትና ምንነት ሲያስረዳ የወይን እርሻን በምሳሌነት በመውሰድ ነው(ሉቃ.13፡7, ዮሐ.15፡1-5, ማቴ.21፡33, ማቴ.7፡16 ...)፣ ስለ ወይኑ ማሳና ስለ ገበሬውም ሲናገር፣

- ዮሐ.15፡1 "እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፣ ገበሬውም አባቴ ነው።"
- ዮሐ.15፡5 "እኔ የወይን ግንድ ነኝ፣ እናንተ ቅርንጫፎች ናቸሁ።"
- ማቴ.3፡10 "አሁንስ ምሳር በዛፎች ስር ተቀምጧል፣ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።

ከነዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የምንረዳው የወይኑ እርሻ ክርስትና ሲሆን ገበሬው ደግሞ እግዚአብሔር ነው፣ ገበሬው የወይኑን ሁኔታ በጥንቃቄ ይከታተላል፣ <u>ፍሬ የማያፈራውን ቅርንጫፍ</u> አይሳሳለትም ቆርጦ ይጥለዋል፣ ገበሬውም ቅርንጫፉን ቆርጦ አይተወውም በእሳት ያቃጥለዋል፣ ይህም ሲኦል ነው፣ የሚገርመው ደግሞ ገበሬው ምሳሩን(መጥረቢያውን) የሚያስቀምጠው በዛፉ ስር ነው።

እዚህ ጋር "ይቆርጣል" የሚለው ቃል የተነገረው በመንፈሳዊ ትርጉሙ ነው፣ ይህም "የተሰጠው እምነት ከውስጡ ሚምቶ ይጠፋል" ማለት ነው፣ በዚህም እነዚህ ሰዎች በውስጣቸው የነበረው ጨዉ ሚምቶ ያልቅና ሳያስተውሉት ክርስትና "ውሀ ውሀ" ብሏቸው ክርስትናቸውን ይተዋሉ።

ከዚህ በተቃራኒ ደግሞ ገበሬው የከበደ ፍሬ ላፈራው ቅርንጫፍ በከበደ ሸለማት ይሰጠዋል፣ በፍርድ ቀን "እንደ ስራቸው <u>መጠን</u>" የሚባል አሰራር እንደሚኖር ራዕ.20፡12-13 እና ራዕ.22፡12 ላይ እንመለከታለን፣ በዚህም መንግሥተ ሰማያት የሚገቡት አማኞች ሽልማታቸው አንድ አይነት እንደማይሆን መጽሐፍ ቅዱሱ ላይ ተመልክቷል፣

> ፩ቆሮ.15፡41-42 “የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብት ክብር ሌላ ነው፤ በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያያልና፡፡ <u>የሙታን ትንሳኤም እንደዚሁ ነው</u>፡፡”

እዚህ ጋር “ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ኮከብ” የሚለው ቃል የሚናገረው ስለተፈረደባቸው ሰዎች አይደለም፣ በብርሃን አካላት ስለተመሰሉት የፀደቁ ሰዎች እንጂ፣ በብርሃን አካላት ድምቀት ልዩነት የተገለፀው ደግሞ በነዚህ ፃድቃን መካከል የሚኖረው <u>ዘላለማዊ</u> የማንነት ልዩነት ነው፣ የገብርኤል፣ የሚካኤል፣ የኪሩቤል፣ የሱራፌል እና ስማቸውን ስለማናውቃቸው ዕልፍና አዕላፍ መላዕክት ማንነት፣ ክብር፣ ስራ … እንደሚለያየው ሁሉ በመጪዋ ዓለም ውስጥ የሚኖረው የሰው ልጆች ማንነት የሚለያየው አሁን በሚያደርጉት ትጋት መጠን ነው፡፡ ይህ እውነታ ፩ቆሮ.3፡11-15 ላይም ተገልጿል፦

> ፩ቆሮ.3፡11-15 “ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፣ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሳርም ወይም በአገዳ ቢያንፅ፣ የእያንዳንዱ ስራ ይገለጣልና፤ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና ፣ የእያንዳንዱንም ስራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል፡፡ ማንም በእርሱ ላይ ያነፀወው ስራ ቢፀናለት ደመወዙን ይቀበላል፤ የማንም ስራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፣ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል፡፡”

በዚህም ከሲኦል ቅጣት ከመዳን በተጨማሪ እያንዳንዱ አማኝ ዘላለማዊው ማንነቱ ምን እንደሚመስል እየገነባ ያለው በዚህ በስጋው ወራት በሚያፈራው መንፈሳዊ ፍሬ ነው፡፡

6.4.2. <u>የአብያተ ክርስቲያናቱና የጎብረቱ ድክመት</u>

በአብያተ ክርስቲያናትና ጎብረቱ ጋር ያለውን ችግር ስንመለከት ሀገራዊ ስራዎችን ማቀናጀት አለመቻል፣ የቤተክርስቲያንን ፕሮግራም ይዘቶች ወጥ ማድረግ አለመቻል እና በዓልን ለአዲስ ኪዳናዊ አገልግሎት መቅረፅ አለመቻል ናቸው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፣

6.4.2.1. <u>ቅንጅታዊ ስራ አለመኖር</u>

አብያተ ክርስቲያናቱ/ጎብረቱ ካላቸው አቅም፣ ልምድና ጠንካራ አደረጃጀት አንፃር፣ ተቀናጅተው መተግበር የሚገባቸው ብዙ ሀገራዊ ስራዎች አሉ፣ እነዚህም፡-

- መጽሐፍ ቅዱሱን በተለያየ የሀገራችን ቋንቋዎች ተርጉሞ በማሳተም ለሁሉም ማዳረስ በሚቻልበት መንገድ ላይ መጽሐፍ ቅዱስ ከሚያሳትሙ አካላት ጋር መስራት፣ መጽሐፍ ቅዱሱንም በኡዲዮና የተለያዩ አገልግሎት በሚሰጡ አፕሊኬሽኖች ማዘጋጀት፣
- ከጥንት ጀምሮ ሲወጡ የነበሩትን አሁንም በተበታተነ መንገድ እየወጡ ያሉትን መዝሙሮችን፣ ጋዜጦችን፣ መፅሄቶች፣ መጽሐፍት ... በማዕከላዊነት የሚሰባሰቡበትና ህዝቡ የሚያገኝበትን ላይብረሪ፣ ዌብሳይት፣ ሱቆች ... ማደራጀት፣ ቀደምት መዝሙሮች ለአሁኑ ትውልድ በሚያመች መልኩ በዘመናዊ መሣርያ አድሶ ማቅረብ፡፡

  መጽሐፍ ቅዱሱ በእግዚአብሔር መንፈስ ምሪት ስለተዘጋጀ እንደማያረጀው ሁሉ እነዚህ ስራዎችም "አርጅተዋል" ተብለው ሊተው አይገባም፣ እንደ ዓለማዊው ዝም ብለው ስላልመጡ ዝም ተብለው ሊጣሉ አይገባም፣ ለሌላውም ትውልድ ሊደርሱ ይገባል፡፡

- በሀገሪቱ ውስጥ ከዕድሜ መግፋት፣ ከአዕምሮ ችግር፣ ከወላጅ ማጣት፣ ከመበለትነት... ጋር ተያይዞ ያሉትን ችግሮች የሚረዱ ለረጂውም ሆነ ለተረጂውም ተደራሽ ድርጅቶችን ማቋቋም፣ በዚህም አማኙ "ተርቤ አላበላችሁኝም..." በሚለው ቃል ሳይጠየቅ፣ "ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ" ከሚለውም ቃል ጋር ሳይጋጭ፣ ከገቢው በቋሚነት የሚቆርጠውን መድቦ መቁረጥ የሚችልበትን፣ ችግረኞችም ከነችግራቸው በአደባባይ ሳይበተኑ በተለያየ መንገድ ይህም፣ በፀሎት፣ በህክምናና በሌሎች ግብረ ሰናይ ድርጅቶች መረዳት የሚችሉበትን መንገድ በማመቻቸት የረጂውንም፣ የተረጂውንም ሆነ የሀገርን ጥቅም ያማከሉ አሰራሮችን መዘርጋት፣
- በሀገር ውስጥና በውጪ ሀገራት የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም ምዕመናንን እርስ በርስ የሚያገናኝና መረጃ የሚሰጥ ማዕከላዊ የሆነ የቴሌቪዥን፣ የዌብሳይት፣ የማኅበራዊ ሚዲያ እንዲሁም የጂ.አይ.ኤስ. የመረጃ ስርዓት ማደራጀት፣

በዚህም አብያተ ክርስቲያናቱ/ጎብረቱ እነዚህን አሰራሮች በማቀናጀት አማኙን፣ ራሳቸውምንም ሆነ ሌላውን ማጎበረሰብ እርስ በርስ በማስተሳሰር የተቀናጀ ማዕከላዊ አሰራርን ማስፈን ይጠበቅባቸዋል፡፡

6.4.2.2. <u>የቤተክርስቲያን ፕሮግራም ይዘቶችን ወጥ ማድረግ አለመቻል</u>

የቤተክርስቲያን ፕሮግራሞች ይህም የአምልኮ፣ የፈውስ፣ የቀብር፣ የጥምቀት … ፕሮግራሞች ይዘት በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የተለያየ ነው፣ ይህንን ወጥ መልክ ማስያዝ ያለበት የአብያተ ክርስቲያናቱ ጎብረት ነው፡፡

ብዙዎች ጋር የአምልኮ ፕሮግራም በፀሎት ይጀመራል፣ ይዘመራል፣ ይሰበካል ከዚያም በ“አባታችን ሆይ” ፀሎት ፕሮግራም ይቋጫል፣ ይህ መልካም አሰራር ቢሆንም ሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናትም ተመሳሳይ መንገድ እንዲከተሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የመካነ ኢየሱስ ቤተክርስቲያን አካባቢ ያለው “የእምነት ቃል” የሚባለው አሰራር ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ እንዲለመድ ቢደረግም መልካም ነው፣ ይህ አሰራርም ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች አሉት፣ አማኙ የራሱን እምነት ጠንቅቆ እንዲረዳ ያደርገዋል፣ “የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን እምነት ምንድነው?” የሚሉ ሰዎችም በአጭሩ መልሱን እንዲያገኙ ይረዳል፣ ከቤተክርስቲያኗ እምነት ውጪ በሚያስተምሩ ሰዎች ምክንያትም ቤተክርስቲያን እንዳትወቀስ ያደርጋል …

ከቀብር፣ ከጥምቀት፣ አራስን ከመመረቅ … ጋርም በተያያዘ ልክ በትምህርት ቤት ምርቃት ላይ እንደምንመለከተው፣ ለፕሮግራሙ የሚመጥን፣ ለየት ያለ፣ ጥልቅ መልዕክት ያለው፣ አጠር አጠር ያሉ መዝሙሮች ቢዘጋጅና ሁሉም እንዲጠቀሙበት ቢደረግ በፕሮግራሙ ሰበብ የሚተላለፈውን መልዕክት በማይረሳ መንገድ በሰው አዕምሮ ውስጥ እንዲቀረፅ ማድረግ ይቻላል፡፡

6.4.2.3. <u>በዓልን ለአዲስ ኪዳናዊ አገልግሎት መቅረፅ አለመቻል</u>

አዲሱ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ሲተካ ከተተካኩት ውስጥ አንደኛው “በዓል” ነው፣ በብሉይ ኪዳን ዘመን በዓል ቀን የነበረበት አሰራር በአዲሱ ኪዳን በዓል ኢየሱስ ሆነ(ቆላ.2፡16-17)፣ ልክ የቀን ሰንበት በክርስቶስ ሰንበትነት(ዕረፍትነት) እንደተተካው፣ ይሁን እንጂ በዚህ በአዲስ ኪዳን ዘመን ሰዎች በተለምዶ “በዓል” ብለው በለዩት ቀን የኢየሱስ በዓልነት ቀርቶ የቀን በዓል እየተከበረ ይገኛል፣ ይህ ደግሞ ስህተት ነው፡፡

በዚህም በተለምዶ “በዓል” ተብለው በተሰየሙት ቀናት ከመብላት፣ መጠጣቱ፣ መልበሱ፣ መገባበዙ … በላይ ቀኑን ሰበብ አድርጎ በቀኑ የተፈፀመውን ድርጊት መታሰቢያ ቀን በማድረግ የኢየሱስ አዳኝነት ስራ ገላጭ በሆነ መልክ ለሰዎች የሚመሰከርበት፣ እግዚአብሔር የሚከብርበት፣ የፕሮቴስታንት አንድነት የሚንፀባረቅበት፣ ደከም ያሉ

አማኞችም ራሳቸውን የሚያዩበት … ቀን በማድረግ በዓላቱን ወጥ ክርስቲያናዊ ቀለምና ባህል በሚፈጥር [163] "የመታሰቢያ ስርዓት" መቅረፅ አስፈላጊ ነው።

የበዓል ስነ ስርዓቶችን ወጥ በሆነ ክርስቲያናዊ ቀለምና ባህል የመታሰቢያ ስነስርአት ማድረጉ ከላይ ከተመለከቱት መንፈሳዊ ጥቅሞች በተጨማሪ ሌሎች አስተዳደራዊ ጥቅሞችም እንዳሉት ከጥንታውያኑ ኃይማኖቶች(አርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ እስልምና …) መማር ይቻላል።

ጥንታዊያኑ ኃይማኖቶች በግዝፈትና በትውልድ ቅብብሎሽ ውስጥ ፀንተው ሊቆሙ የቻሉት ምዕመናኖቻቸው ጋር ባለው መንፈሳዊ እውቀት ሳይሆን በኃይማኖታዊ ትውፊቶቻቸው፣ በተለይ ከበዓላቶቻቸው ጋር በተያያዘ በፈጠሩት ኃይማኖታዊ ባህል ነው። የነዚህ ቤተ እምነቶች አብዛኛው ምዕመን ስለኃይማኖቱ አስተምህሮ ምንም ሳያውቅ ነው ለኃይማኖታዊ በዓል ብቻ ኃይማኖተኛ የሚሆነው፣ ይህንን ችግር እንደ ችግርነቱ መመልከቱ ተገቢ ቢሆንም በኃይማኖታቸው ደከም ያሉ ሰዎች በዓልን እንኳን ሰበብ አድርገው ራሳቸውን በአንድ ኃይማኖት አውድ ውስጥ የሚያስገቡበት ሁኔታ ግን አሁን ፕሮቴስታንት አካባቢ የምንመለከተውን "በእምነት የደከመ ጠፋ" ሁኔታን ያስቀራል።

ፕሮቴስታንቱ አካባቢ ሁሉም ነገር መንፈሳዊ ብቻ በመሆኑ፣ በኃይማኖት ደከም ያሉ ሰዎች የሚስተናገዱበት ስፍራ የለም፣ አንድ ሰው በኃይማኖቱ ደከመ ማለት ወይ በፖለቲካው መንፈስ ወደ ብሔር ኃይማኖት ይሄዳል ወይ "በፍልስፍና" መንፈስ ወደ ኤቲዝምና ሂውማኒዝም ይሄዳል፣ ይህ ኪሳራ ደግሞ የአንድ ሰው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከዚያ ሰው በኋላም ያለው ቤተሰብም ጉዳይ ነው።

የፕሮቴስታንት ኃይማኖት ተሐድሶ በስፋት ተንቀሳቅሶ የነበረባቸው ሀገራት ዛሬ ላይ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት፣ ኃይማኖቷ የአንድና ሁለት ትውልድ ጉዳይ ብቻ ሆና ነው የቀረችው፣ ሌላውን ትውልድ በአብዛኛው በኤቲዝምና ሂውማኒዝም መንፈስ ውስጥ ነው የሚገኘው። የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በተሐድሶ በመመሥረቷ ምክንያት አማኞቿ የሌሎች ኃይማኖት ተቋማትን ድክመት በዝርዝር ስለሚያውቁ በሚደክሙበት ጊዜ ወደ ሌላ ኃይማኖት አይሄዱም፣ ቤተክርስቲያኗ ጋር ደግሞ ሰነፎችን የሚስተናገዱበት ክፍል ባለመኖሩ ይህን ደካማ አማኝ የሚጠብቀው "በእምነት ደከመ - ጠፋ" የሆነው የኤቲዝም፣ የሂውማኒዝም፣ የዮጋ … ሜዳ ነው።

የኢትየጵያ ቤተክርስቲያንም ይህንን ነባራዊ ሂደት በመመልከት በዓላትን ለመንፈሳዊ ጥቅም ከማዋሉ በተጨማሪ የደካማ አማኞች መሰባሰቢያ መንገድ በማድረግ፣ ቤተክርስቲያኗ በትውልድ መካከል ያላትን ህልውናና ግዝፈት የምታስጠብቅበት አንዱ

[163] *መታሰብ* ለሚገባው *መታሰቢያ* ማድረግ እንግዳ ወንጌል ሳይሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሰራር ነው (ዘፀ.12፡14, ዘፀ.28፡12, ዘኁ.10፡10, መዝ፡102፡12, ምሳ.10፡7, ማቴ.26፡13, ነቆሮ.11፡25 … *መመልከት* ይቻላል።)

መንገድ አድርጋ ልትጠቀምበት ይገባል፡፡ በዚህም ምንም እንኳን በአዲሱ ኪዳን በዓል ክርስቶስ ቢሆንም ሰዎች በተለምዶ በዓል ብለው የለዩዋቸው ቀናት ለየት ላለ አዲስ ኪዳናዊ አገልግሎት መቅረፁ አስፈላጊ ነው፡፡

በዚህ መነሻም፣ ይህቺ መጽሐፍ፣ በአብያተ ክርስቲያናቱና ጎብረቱ ሊዳብሩ የሚገቡ፣ አዲስ ኪዳናዊ መሠረት ያላቸውን፣ በዓልን ለአዲስ ኪዳናዊ አገልግሎት መቅረፅ የሚቻልባቸውን መንገዶች ተመልክታለች፣ ቀጥሎ በስፋት ተመልክቷል፣

1. <u>ገና</u>

ገና ኢየሱስ የተወለደበት ቀን በመሆኑ ኢየሱስ በስጋ የመጣው ለምን እንደሆነ በሚያስረዳ መልኩ፣ ኢየሱስ የዓለም ብርሃን መሆኑን፣ የሰው ልጆችን ለማዳን ራሱን ዝቅ አድርጎ በማርያም ማህፀን አድሮ በከብት በረት መወለዱን <u>ሁሉንም</u> ሊያስገነዝብ በሚችል መልኩ ቀኑ ሊታሰብ ይገባል፡፡

በዚህም መታሰቢያው ከዋዜማው ጀምሮ የነማርያም ቤተሰብና እረኞቹ የነበሩበትን ድባብ በሚያሳይ መልኩ መጀመር አለበት፤ በዚህም በዋዜማው ቀን ህፃናት የእረኛ ወይንም ባህላዊ ልብስ በመልበስ፣ ጅራፍ ወይንም ዱላ በመያዝ፣ ቤተሰብም ለህፃናቱ እረኞች ወደ መስክ ይዘውት የሚሄዱት ባህላዊውን ሙልሙል ዳቦ በማዘጋጀት፣ ህፃናቱም የኃይማኖት አባቶችና አገልጋዮች ቤት በመሄድ የ“እንኳን አደረሳችሁ” ፖስት ካርድ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ አበባ፣ የአበባ ስዕል … የመሳሰሉ ስጦታዎችን የሚሰጡበት፣ ስጦታ የሚበረከትላቸውም በቤታቸው ህፃናቱን የሚባርኩበትና የሚፀልዩላቸው ቀን ተደርጎ ሊታሰብ ይገባል፡፡

በቤት ወይ በቤተክርስቲያን አካባቢም እንደ ግርግም አይነት በመስራት ሳር መሬት ላይ ጎዝጉዞ ወደ አመሻሽ ላይም የእረኞች እሳት አይነት ችቦ፣ ደመራ፣ እንጨት … በማንደድ ወይንም የብርሃን አካላት በማብራትና በመተኮስ፣ ዕጣንና ከርቤ በማጤስ ከጎረቤት ወይንም ዘመድ አዝማድ ጋር የወላድ ገንፎ በመብላት፣ ቡና በመጠጣትና በዝማሬ ዋዜማው ሊታሰብ ይገባል፡፡

በገና ጠዋት ቤት ውስጥ የሳር ጉዝጓዝ፣ ለልደት በሚቆረስ ኬክ/ድፎና ስንተኛ የልደት አመት እንደሆነ በሚያሳይ ፅሁፍ፣ ጌጦችና ሻማ በማብራት ስነ ስርዓት የኢየሱስ ልደት ትክክለኛ የልደት በዓል ተደርጎ ሊታሰብ ይገባል፣ በዚያን ቀን ህፃናቱም የበዓል ልብስ በመልበስ ለጎረቤትና ለዘመድ አዝማድ የ“እንኳን አደረሳችሁ” ፖስት ካርድ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ፣ አበባ፣ የአበባ ስዕል … የሚያበረክቱበትና ይህ ስጦታ የተበረከተላቸውም ህፃናቱን ኬክ፣ዳቦ፣ ፍራፍሬ፣ ከረሜላ፣ ቸኮሌት … በመጋበዝ ህፃናቱን ባርከው የሚሸኙበት ቀን በማድረግ ቀኑ ሊታሰብ ይገባል፡፡

የገናን በዓል በዚህ መልክ ሲታሰብ አማኝ አህዛቡ በሙሉ የክርስቶስን መወለድ እውነታና ዓላማ ላይ ጥልቅ ግንዛቤ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

2. <u>የፋሲካ ሳምንት</u>

ኢየሱስ ከመሰቀሉ በፊት ቀድሞ ባለው ሳምንት ውስጥ ብዙ ጉልህ ክንውኖች ተከናውነዋል፣ እነዚህን ክንውኖቹንም በተግባር በማሰብ፣ ለአህዛብ ገላጭ በሆነ መልክ ቀናቱን ለምስክርነት ስራ ማዋል ይቻላል፣ በዚህም፣

➢ **<u>ሆሳዕና (ዕሁድ)</u>**

በሆሳዕና ቀን ኢየሱስ ራሱን ዝቅ አድርጎ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ህፃናቱ ደግሞ የኢየሱስን ጌትነትና ንጉሥነት ያወደሱበት፣ ኢየሱስን የባረኩበት፣ አዋቂዎች ደግሞ ዘንባባና የተለያየ ነገር እያነጠፉ ኢየሱስን እንደ ንጉሥ አክብረው የተቀበሉበት ቀን ነው፡፡

ስለዚህ፣ በዚህ ቀን የኢየሱስ ጌትነት፣ ስራ … በአደባባይ የሚነገርበት ቀን በማድረግ መታሰብ አለበት፣ በዚህም መታሰቢያው የኢየሱስን ጌትነት፣ አዳኝነት … አጉልቶ በሚመሰክር መልኩ በየአብያተ ክርስቲያናቱ የመዘምራን ቡድኖችና በመንገድ ላይ ካርኒቫል(ከተቻለ በማርሽ ባንድ፣ በትርኢቶች … በማጀብ) … በዋና ዋና መንገዶች ላይ በማቅረብ ሊከናወን ይገባል፡፡ ፕሮግራሙ ከየት ተጀምሮ የትና የት በመሄድ እንደሚከናወን፣ የት ስፍራ ላይ የማጠቃለያ ፕሮግራም እንደሚዘጋጅ በአብያተ ክርስቲያናቱ ጎብረት ሊመራ ይገባል፡፡

በዚህም ቀን ኢየሱስ በሆሳዕና ቀን የተናገረውን “ሠላም እራሱ ኢየሱስ መሆኑን” (ሉቃ.19፡42) በማወቅ፣ እያንዳንዱ አማኝ ሠላሙን ክርስቶስን መያዙን ለማሰብና ለመመስከር የሠላም ምልክት የሆነውን ዘንባባ በመያዝ፣ በዘንባባ የሚሰሩ ኮፊያዎችን፣ ቀለበቶችን፣ አምባሮችን … በመጠቀም፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በቤታቸው ውስጥ፣ በጎበናቸው፣ በመኪናቸው … ላይ በማሰር መታሰቢያውን ሊያስቡ ይገባል፡፡

➢ **<u>የፅዳት ቀን(ሰኞ)</u>**

ይህ ቀን ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊት ከእግዚአብሔር ቤተመቅደስ ውስጥ የሚሸቅጡትን ያባረራቸው ቀን ነው፡፡ አማኝም የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደመሆኑ መጠን በዚህ ቀን ማንኛውንም ቂም፣ ጥላቻ፣ ዘረኝነት፣ ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ አለማዊነት፣ ጣኦት ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅንአት፣ ቁጣ፣ አድመኝነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት … ነፃ መሆኑን ራሱን የሚፈትሽበትና ቤተመቅደሱን የሚያፀዳበት ቀን ሊያደርግ ይገባል፤ በዚሁ መንፈስም፣ ይህንን ሳምንት ለጾም ለሚጠቀሙት ሰዎች በሚመች መልኩ፣ ከሰዓት በኋላ የግቢ የሰፈር፣ ከተቻለ ከተማ አቀፍ የፅዳት ዘመቻ በማድረግ ቀኑ መታሰብ አለበት፡፡

➢ **<u>የፍሬ ቀን(ማክሰኞ)</u>**

ይህ ቀን መታሰብ ያለበት፣ ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊት ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ርቦት ከበለስ የሚበላውን ፍሬ ፈልጎ ስላላገኘባት ረግሟት የሄደበት ቀን በማሰብ ሊሆን ይገባል። ስለዚህ በዚህ ቀን ሰዎች ለቤተሰባቸው፣ ለወዳጆቻቸው … ፍራፍሬ የሚሰጡበት፣ በቤተክርስቲያን፣ በትምህርት ቤቶች፣ በመስርያ ቤት … አብሮ ፍራፍሬ የመብላት ፕሮግራም የሚካሄድበት ቀን በማድረግ ቀኑ ሊታሰብ ይገባል።

የትኛውም አማኝ በዚህ ቀን ለእግዚአብሔር ያፈራውን የመንፈስ ፍሬ፣ ይህም ፍቅር፣ ደስታ፣ ሠላም፣ ትዕግስት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሀት፣ ራስን መግዛት(ገላ.5፡22) እንዲሁ እግዚአብሔርን ወደ መምሰል(1ጢሞ.4፡7) ውስጥ እንዴት እያደገ እንዳለና ወንጌልን ለስንት ሰው እንደመሰከረ ያለፈበትን ጊዜያት የሚገመግምበትና ለወደፊቱም እንዴት እንደሚንቀሳቀስ ዕቅድ የሚያወጣበትና እንደ በለሷ ፍሬ ጠፍቶበት እንደማይረገም ራሱን የሚመለከትበት ጊዜ በማድረግ ቀኑን ሊያሰብ ይገባል።

➢ **<u>የሽቶ ቀን(ሮብ)</u>**

ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊት ማርያም የተባለች ሴት መጥታ እግሩን ሽቶ ቀባቸው፣ ድርጊቷም "መታሰቢያነቱ ለትውልድ ነው(ማቴ.26፡13)" በተባለው መሠረት በዚህ ቀን ሰዎች ለቤተሰቦቻቸውና ለትዳር አጋራቸው የሽቶ ስጦታ በማበርከት የሚያስቡት ቀን ሊደረግ ይገባል።

➢ **<u>የእስራት ቀን(ሐሙስ)</u>**

ኢየሱስ አርብ ሊሰቀል ሐሙስ ዕለት ታሰረ፣ ስለዚህ በዚህ ቀን የሚለበሰው በተለምዶ የእስረኛ ልብስ ተደርጎ የሚወሰደውን ቢጫ ልብስ (ሙሉ ወይንም ግማሽ ቢጫ ልብስ) ሲሆን በዚህን ቀን የሚበላውም ምግብ እስረኛ እንደሚበላው አይነት ተራ ምግብ (ለምሳሌ ሽሮ፣ ፍርፍር፣ የሱፍ ፍትፍት፣ ቲማቲም …) ይሆናል፣ ኢየሱስ ከመታሰሩ በፊትም የደቀ መዛሙርቱን እግር እንዳጠበው ሁሉ አመሻሽ ላይ በቤተክርስቲያንና በቤተሰብ ደረጃ እርስ በርስ የእግር መተጣጠብ ስነ ስርዓት ሊተገበር ይገባል።

➢ **<u>የይቅርታ ቀን(አርብ)</u>**

አርብ ዕለት ኢየሱስ ስለ ሰዎች ኃጢያት ዋጋ የከፈለበት ቀን በመሆኑ ስለ ኃጢያት ስርየት የፈሰሰውን ደሙን ለማስታወስ የሚለበሰው ሙሉ ወይንም ግማሽ ቀይ ልብስ ሲሆን ኢየሱስ በራሱ ላይ የተሸከመውን የእሾህ ጉንጉን በማሰብም በራስ ላይ የቁጠማ፣ ዘንባባ፣ ሳር፣ ክር፣ ጨርቅ … በማሰር ቀኑ ሊታሰብ ይገባል። ኢየሱስ ከተገደለበት ዘጠኝ ሰዓት በኋላ እንደ ባህላችን የሀዘን ንፍሮ በመመገብና ወደ መዝናኛ ስፍራዎች ባለመሄድ ሞቱ ሊታሰብ ይገባል። ቀኑ የሰው ልጆች የኃጢያት ይቅርታ ያገኙበት ቀን በመሆኑም በዚህም ቀን "በደላችንን ይቅር በለን እኛን የበደሉንን ይቅር እንደምንል" መንፈስ ቀኑ በግለሰብ ሆነ በሀገር ደረጃ የይቅርታና የዕርቅ ቀን መደረግ አለበት፣ በዚህም ሰዎች

የበደሉትን፣ የተጣሏቸው ወይንም የተቀየሟቸው ሰዎች ካሉ ስልክ ደዋውለው ይቅር የሚባባሉበት ቀን በማድረግ፣ መንግሥትም ባለው አሰራር እስረኞችን በይቅርታ የሚፈታበት ቀን ሆኖ ሊታሰብ ይገባል።

➢ **<u>የሀዘን ቀን(ቅዳሜ)</u>**

ኢየሱስ በመቃብር ውስጥ የቆየበት ቀን በመሆኑ ዕለቱ የሚታሰበው ሙሉ ወይንም ግማሽ ጥቁር ልብስ በመልበስና ወደ መዝናኛ ስፍራዎች ባለመሄድ ሊሆን ይገባል።

በዚህ ቀን እያንዳንዱ አማኝ እራሱም አንድ ቀን እንደሚሞትና እንደሚቀበር ቆም ብሎ የሚያስብበትና ስጋዊው ሞቱም ሳይመጣ እራሱ ለዓለማዊነት መሞቱንና ለዘላለማዊው መንፈሳዊ ነገር መለየቱን የሚመለከትበት ቀን መሆን አለበት።

➢ **<u>የትንሳኤ ቀን/ፋሲካ(እሁድ)</u>**

የትንሳኤ ቀን(ፋሲካ) ምህረት የወረደበት፣ የክርስትና ዘመን መለወጫ ቀን በመሆኑ፣ አማኙ በሙሉ አዲሱን የክርስትና አመት መጀር ያለበት ከፈጣሪ ጋር ያለውን ቃል ኪዳን በማደስ ስጋ ወደሙን በመውሰድ ሊሆን ይገባል፣ በዚህም ሁሉም አማኝ ጠዋት 12፡00 ሰዓት ላይ በቤተክርስቲያን በሚደረግ ስነ ስርዓት ወይንም በቀጥታ የቴሌቪዥ/ሬዲዮ/ኢንተርኔት ስርጭት የቅዱስ ቁርባን ስነ ስርዓት ሊፈፅም ይገባል።

ቀኑም የትንሳኤ ቀን እንደመሆኑ መጠን የሚለበሰው ነጭ ልብስ ሲሆን ቀኑም ሊታሰብ የሚገባው በትንሳኤ አዕምሮ፣ በትንሳኤ ልቦናና በትንሳኤ መንፈስ ሊሆን ይገባል።

ከአለባበስ ጋር በተያያዘ አቅም የሌላቸው፣ ዩኒፎርምና የስራ ልብስ አስገዳጅ በሚሆንባቸው ስፍራዎች ... በዚያን ቀን የሚለበሰው ልብስ ቀለም የሆነ ክር፣ ፈትል፣ ጨርቅ ... የተመቻቸውን በእጃቸው ላይ አስረው ማሰብ ይችላሉ፣ በተጨማሪም ከላይ "የፅዳት ቀን፣ የፍሬ ቀን፣ የይቅርታ ቀንና ለ"ዓለምና ለስጋዊ ፍላጎቶች መሞት" የሚባሉት እዚህ ጋር የቀረቡት ለመታሰቢያነት እንጂ በተቻለ መጠን የእያንዳንዱ አማኝ የየዕለት ተግባር መሆናቸው ሊዘነጋ አይገባም።

በአጠቃላይ እነዚህን ከላይ የቀረቡትን እውነታዎች በአንድ ላይ ስንመለከት ስምንቱ የፋሲካ ቀናት በአግባ ሲታሰቡ አብዛኛው አማኝ ራሱን እንዲመለከትና አህዛቡም የኢየሱስን ስራ በግልፅ እንዲገነዘብ ያደርጋል።

3. <u>የዘመን መለወጫ</u>

በብሉይ ኪዳን ዘመን አዲስ አመት የሚከበረው ከፋሲካ ሁለት ሳምንት በፊት ሲሆን (ዘጸ.12፡2, ዘኁ.28፡16 ...) በአዲስ ኪዳን ዘመን መለወጫ የፋሲካ ቀን መሆን የሚገባው ቢሆንም፣ በሀገሪቱ ከወቅቶች መፈራረቅ ጋር ተያይዞ፣ በብሔር ብሔረሰቦችም ሆነ እንደ ሀገር የዘመን መለወጫ በዓል የሚከበረው በመስከረም ወር ነው።

ማንኛው ክርስቲያንም፣ መጽሐፍ ቅዱሱን በማይፃረር መልኩ፣ ከሚኖርበት ማኅበረሰብ ጋር መመሳሰል እንዳለበት ሁሉ፣ የዘመን መለወጫውን ለየትኛውም ብሔር ባልወገነው በሀገራዊው የዘመን መለወጫ ቀን፣ በመስከረም አንድ ማክበር ይገባዋል።

በዚህም ለአዲስ አመት የተጀመረው ሙሉ የጳጉሜ ጾም ፀሎት እንዳለ ሆኖ በጳጉሜ መጨረሻ ቀን ጾም ፀሎቱ ካለቀ በኋላ አጠቃላይ የራስ ግቢ፣ የሰፈር፣ የቤተክርስቲያን አካባቢ ከተቻለ ከተማ አቀፍ የፅዳት አገልግሎት ሊሰራ ይባል። መስከረም አንድ ቀን ቄስ ቶለሳ ጉዲና ያወጁት የእስታዲየም የአጠቃላይ ቸርቾች የኅብረት ፕሮግራም ላይም አብያተ ክርስቲያናት ወደ እስታዲየም የሚመጡት በተበታተነ መልኩ ሳይሆን ከየቸርቾቻቸው መዘምራኖቻቸውንና ምዕመናኖቻቸውን ይዘው በዋና ዋና መንገዶች እየዘመሩ መሆን አለበት።

የዚህ ቀን ፕሮግራም በአብያተ ክርስቲያናቱ ኅብረት መመራት ያለበት ሲሆን ከ12 ሰአቱ የአዲሱ አመት ብስራት የመድፍ ተኩስ ስነ ስርዓት በኋላ የአብያተ ክርስቲያናቱ ኅብረት በሚያዘጋጃቸው የኃይማኖት አባቶች በቀጥታ የቴሌቪዥን፣ የሬዲዮ፣ የኢንተርኔት... ስርጭት ሀገርን፣ መንግሥትን፣ ፓርቲዎችን፣ ህዝቡን፣ ሠራተኛውን ... በመባረክና ለደቂቃዎችም "ኢትዮጵያ ለእግዚአብሔር ትሰግዳለች" በሚለው ቃል መንፈስ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚሰግድበት ጊዜ መፈጠር አለበት።

በአጠቃላይ "በዓላት" ተብለው በተሰየሙት ቀናት የኢየሱስ ስራዎችን በአግባቡ የሚመሰከርበት፣ እግዚአብሔር የሚከብርበት፣ የፕሮቴስታንት አንድነት የሚታይበት፣ አማኞችም ራሳቸውን የሚያዩበትና ለደካማ አማኞችም መጠለያ ስፍራ የሚፈጠርበት በማድረግ ማሰቡ ለጠንካራውም፣ ለደካማውም፣ ለወንጌል ምስክረነትም በአጠቃላይ ለቤተክርስቲያኗ ጠንካራ መሠረት ማስቀመጥ በመሆኑ ቤተክርስቲያን በአግባቡ ልትመለከተው ይገባል።

ማጠቃለያ(ፕሮቴስታንት)

ከመቅድም ከፍል ጀምሮ ስንመለከት የመጣነው “ፈጣሪ አለ የለም” ከሚለው የብዙዎች ጥያቄ በመነሳት ትክክለኛዋን ኃይማኖት የመለየት ስራን ነው፣ በዚህም በተጨባጭ መንገድ ትክክለኛውን መንገድ ይዛ ያለችው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን መሆኗን ተመልክተናል፡፡

ይህንን ትክክለኛዋን የኃይማኖት ተቋም በመለየት ሂደት ውስጥ ሳልናገር ማለፍ የማልፈልገው እውነታ መጽሐፍ ቅዱሱ “መዳን በኢየሱስ ነው”(ሐዋ.4፡12) እያለ ሁሉም የአብርሃም ኃይማኖቶች ደግሞ በኢየሱስ ላይ ያላቸው እምነት ፈፅሞ የተለያየ መሆኑ ነው፣

- አይሁድ - “ኢየሱስ አልተወለደም ገና ይወለዳል”
- ሙስሊም- “ኢሳ ተወልዷል ነገር ግን እንደኛው ሰው ብቻ ነው”
- ሐዋርያት - “ኢየሱስ ፍፁም አምላክ እንጂ ሰውነት የለውም”
- ጂሆቫ - “ኢየሱስ መልአኩ ሚካኤል ነው”
- ሥላሴያውያን (ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮቴስታንት) - “ኢየሱስ የሰውና የአምላክ ተዋህዶ ነው”

“ተዋህዶ ነው” ብለው አንድ የሚመስሉት ሥላሴያውያን ደግሞ ተመልሰው በአገልግሎቱ ላይ ያላቸው እምነት የተለያየ ነው፡-

- ኦርቶዶክስ/ካቶሊክ - “ኢየሱስ አሁን ፈራጅ እንጂ አማላጅ አይደለም”
- አድቬንቲስት - “ኢየሱስ አሁን የምርመራ ፍርድ እየሰራ ነው”
- ፕሮቴስታንት - “ኢየሱስ አሁን አማላጅ ነው የፍርድ ጊዜ ገና ነው”

ይህ ሁሉም የአብርሃም ኃይማኖቶች በዋናው መስፈርት ላይ የተለያየ አቋም መያዛቸው አንዷን ትክክለኛዋን ኃይማኖት ለይቶ ለማውጣት ትልቅ እገዛን ያደርጋል፡፡

በዚህ በመረጃ ዘመን ማንም ሰው የሁሉንም ኃይማኖቶች ቅዱስ መጽሀፍና አስተምህሮን አሰባስቦ ማንበብ፣ ማነፃፀርና መተንተን ይቻላል፣ ይህ ትልቅ ዕድል ነው፡፡ ያለፈው ትውልድኮ የሌላውን ይቅርና ስለራሱ ኃይማኖት እንኳን በቅጡ የሚማርበት ኃይማኖታዊ መጽሐፍ አልነበረውም፣ ይህ ትውልድ ግን የተመረጠ ትውልድ በመሆኑ የፈለገውን መጽሐፍ ከጉበያ ላይ ገዝቶም ሆነ ከኢንተርኔት ላይ አውርዶ በማንበብ፣ በማነፃፀርና በማሰላሰል እውነት የቱ ጋር እንዳለች መረዳት ይችላል፣ መጽሐፍ ቅዱሱም፣

ዮሐ.8፡32 “እውነትም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል”

ብሏል፡፡ እኔም በኃይማኖት ጉዳይ ጥያቄ በተፈጠረብኝ ጊዜ፣ ከየትኛውም ኃይማኖት አስተምህሮ ገለልተኛ ሆኜ፣ የኤቲዝምንና የየኃይማኖቶቹን ቅዱሳን መጽሐፍት በማጥናት እዚህ ግኝት ላይ መድረስ መቻሌ ለኔ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቁርአን ... ወዘተ የማንበብና መረጃዎችን የማጠናከር የአመታት ድካምና opportunity cost እንድረሳ አድርጎኛል፡፡

ምዕራፍ ሰባት

7. መጪው የአንድ ዓለም አንድ ኃይማኖት

የስነፍጥረት አጀማመር፣ የአዳም መሳሳትና ከገነት መባረር፣ የኖህ ዘመን የጥፋት ውሀ፣ የእስራኤላውያን ከግብፅ ሀገር ባርነት በተአምራዊ እጅ መውጣት፣ የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ፣ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የተከናወኑ አንኳር ታሪኮች ናቸው፣ ከነዚህ ተርታ የሚሰለፍ ሌላ አንኳር ታሪክ ደግሞ ከፊት ለፊታችን ተቀምጧል፣ የዓለም ኃይማኖቶችን በሙሉ አንድ በማድረግ ዓለም በአንድ ኃይማኖት እንድትኖር የሚያደርግ በከፍተኛ መንፈሳዊ ኃይል ተሞልቶ የሚነሳ ሰው ታሪክ።

ይህም ሰው በመናፍስታዊ ኃይል እገዛ "እኔ ክርስቶስ ነኝ" በማለት(ሉቃ.21፡8) ዓለምን ለሰባት አመታት(ለአንድ ሱባኤ) ይገዛል(ዳን.9፡27, ዳን.11፡36, 2ተሰ.2፡4, ራዕ.13፡4 ...)፣ እስራኤልን ደግሞ ለሦስት አመት ከግማሽ(ራዕ.11፡2, ራዕ.13፡5 ...) ይገዛል። መጽሐፍ ቅዱሱ ይህንን ሰው "የጥፋት ልጅ"(2ተሰ.2፡3)፣ "ሐሰተኛው ክርስቶስ"(ማቴ.24፡24)" ሲለው በሰውየው ላይ የሚያድረውን መንፈስ ደግሞ "አውሬው"(ራዕ.11፡7, ራዕ.19፡20) ይለዋል፤ በሚገርም መልኩ ደግሞ ይህንን ሰው ሁሉም ኃይማኖቶች እየጠበቁት ይገኛሉ።

እስልምና ይህንን ሰው "ኢማም ማህዲ" ይለዋል፣

> የአቡ ዳውድ ሱና 4283-4286 "<u>ለጊዜው አንድ ቀን ሲቀረው</u> አላህ ከዘሬ ሰው ይልካል ... በዓለም ላይ እኩልነትና ፍትህ ያሰፍናል፣ ዓለም ላይ <u>ለሰባት አመታት ይነግሳል</u> ... <u>በነዚህ አመታት እስልምና በዓለም ላይ ይነግሳል</u>።"

ይህ ከመጽሐፍ ቅዱሱ የሐሰተኛው ክርስቶስ ታሪክ ጋር የሚመሳሰል ታሪክ ነው፣ ንግሥናው ሰባት አመታት መሆኑና "ለጊዜው አንድ ቀን ሲቀረው" ይህም ከኢየሱስ መምጫ በፊት መሆኑ፣ ይህ የሀዲስ መጽሐፍ የሚናገረው ስለ ተመሳሳይ ጉዳይ እንደሆነ እንመለከታለን፤ ቁርአኑም፣

> 97፡1 "እኛ (ቁርአኑን) በመወሰኛይቱ ሌሊት አወረድነው። መወሰኛይቱም ሌሊት ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ፣ መወሰኛይቱ ለሊት ከሺ ወር በላጭ ናት ... <u>እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሠላም ብቻ ናት</u>።"

ይላል፣ እዚህ ጋር "እርስዋ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ ሠላም ብቻ ናት" የሚለው መጽሐፍ ቅዱሱ "ብርሃን" የሚለው ኢየሱስ እስከሚመጣበት ጊዜ መሆኑን ያሳያል፣ በዚህም የዚህ መንፈስ አሰራር የሚሰራው ያ ጎህ እስከሚቀድበት ቀን ድረስ ብቻ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በመጨረሻው ዘመን "አውሬ" የሚባል መንፈስ እንደሚነሳ ይናገራል በተመሳሳይ መንገድም ቁርአኑም በመጨረሻው ዘመን የቁርአንን አንቀፅ የምትናገር አውሬ እንደምትመጣ ይናገራል(27፡82)፣ በርግጥ አውሬ እንደ ሰው አይናገርም ነገር ግን ቁርአኑ የሚናገረው በመንፈሳዊ ትርጉም ነው።

[164] አንዳንድ የሂንዱ ኃይማኖቶች ይህንን በመጨረሻ ዘመን የሚነሳውን ሰው “ክሪሽና” ይሉታል፣ [165] “ካልኪ” ብለው የሚጠሩትም አሉ፣ “ካልኪ” ማለት [166] ቪሽኑ ለመጨረሻ ጊዜ በስጋ የሚወለድበት ማንነት ነው፣ ቪሽኑ ለ10ኛ ጊዜ ካልኪ በሚባል ማንነት ሲወለድ፣ የሚመጣው ከባህር ውስጥ ነው፣ የሚወለደውም ዓለም ለመጥፋት ጫፍ ላይ ስትደርስ ዓለምን ለማዳን ነው።።

ይህ ካልኪ(ቪሽኑ) ዓለም ልትጠፋ ስትል የሚወለድ መሆኑና የሚመጣውም ከባህር መሆኑ ከፊል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ ስለ መጨረሻው ዘመን በሚያስተምርበት ክፍል፣

ራዕ.13፡1 “አንድም አውሬ ከባህር ሲወጣ አየሁ …”

ይላል፣ በዚህም ሁለቱም ኃይማኖቶች “በመጨረሻው ዘመን” እና “ከባህር የሚወጣ” በሚለው ሐሳብ ላይ አንድ መሆናቸውን እንመለከታለን።።

[167]ቡድሂስቶች “ሚየትራ” ይሉታል፣ “ሚየትራ” ማለት … “ቡድሃ” ለአምስተኛ ጊዜ ሲወለድ የሚገለጥበት ስም ነው፣ [168] “ከሚየትራ በኋላም ዓለም በሰባት ፀሐዮች እንድትጠፋ ይደረጋል” ይላሉ፣ ይህ ስለ መጨረሻው ቀን የተነገረው አነጋገር ከፊል መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው፣

> ኢሳ30፡26 እግዚአብሔርም የህዝቡን ስብራት በጠነ ዕለት፣ መቅሰፍቱ የቆሰለውንም በፈወሰ ዕለት፣ የጨረቃ ብርሃን እንደ ፀሐይ ብርሃን፣ <u>የፀሐይም ብርሃን እንደ ሰባት ቀን ብርሃን ሰባት እጥፍ ይሆናል</u>።።”

በ3.2 ክፍል ስር የተመለከትነው “የአዲሱ ትውልድ እንቅስቃሴ” ኃይማኖትም በፊናው ይህንን ሰውና መንፈስ እየጠበቀ ነው፣ እንደ ኃይማኖቱ አስተምህሮ [169]ዓለም ልትገባበት እያለች ያለችው የ“አኩዋሪስ ዘመን ነው”፣ ዘመኑም የሚመሠረተው እንዴት እንደሆነ የተለያዩ ሐሳቦች የሚሰነዘሩ ሲሆን አንዳንዶቹ “human agency” እንደሆነ ሲናገሩ፣ ሌሎች ደግሞ “non human forces such as spirits or extra terrestrials” ሲሉ ሌሎች ደግሞ ምጡቅ በሆነ ሰው “aquarum conspiracy” ነው ይላሉ፣ ስለ ዘመኑም ሲናገሩ “በዚያ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች ፍፁም በሆነ ሠላም፣ ደስታ፣ ፍቅር፣ መትረፍረፍ … ውስጥ ይኖራሉ” ይላሉ።።

---

[164] ግደይ ገ/ኪዳን(2007)፣ **የኢሉሚናቲ የቁጥጥር ዘዴዎች**፣ ገፅ 53

[165] https://en.m.Wikipedia>wiki>end time

[166] በሂንዱ እምነት ዓለምን የሚያስተዳድሩት ሦስት አማልክት ናቸው፣ ብራህማ(የሚፈጥር)፣ ቪሽኑ(የሚያድን) እና ሺቫ(የሚቀጣ)፣ ቪሽኑ ዓለምን ለማዳን የሚሰራው በተለያየ መንገድ ደጋግሞ በመወለድ ነው፣ ቪሽኑ ለ10ኛ ጊዜ የሚወለደው ካልኪ በሚባል ማንነት ነው።።

[167] ግደይ ገ/ኪዳን(2007)፣ **የኢሉሚናቲ የቁጥጥር ዘዴዎች**፣ ገፅ 53

[168] https://en.m.Wikipedia>wiki>end time

[169] https://en.m.Wikipedia>wiki>New age movement

ይህንን ዋነኞቹ ኃይማኖቶች በጉጉት የሚጠብቁት ሰው በዘመናዊ ፊልሞችም እየተተነበየ ይገኛል፣ ልክ “Contagion” የተባለው ፊልም የኮረና በሽታ ሳይመጣ በፊት በሽታውን በትንቢት እንደተናገረው፣ አሁንም አስገራሚ ኃይልና ጥበብ ያለው፣ ልዕለ ስብዕናነት ያለው፣ ከዓለም ውጪ የሚመጡትን ኃይላት የሚከላከል፣ ሰዎች ሊወዱትና ሊከተሉት የሚገባው ልዩ ሰው እንደሚነሳ የሚናገሩ ብዙ ፊልሞችን እየተመለከትን ነው፣ በርግጥ 1.4.2.3/3 ክፍል እንደተመለከተው ኢየሱስ ከሰራዊቱ ጋር በደብረ ዘይት ተራራ የሚወርደው የዓለምን ሠራዊት ለመግጠም ነው፣ በዚህም የፊልም ኢንደስትሪው ትንቢት ግማሽ እውነታነት አለው፣ የፊልም ኢንደስትሪው ይህንን ሰው በተለያየ ስም ይጥራው እንጂ ይሄ ልዕለ ስብዕና ያለውና “ድንቅ” የተባለው ሰው እንደሆነ ሁሉም የሚስማማበት ሀቅ እየሆነ ነው።።

መጽሐፍ ቅዱሱ በዚህ ሰው ጥበብና ችሎታ እንዳንገረም ቀድሞ አስጠንቅቋል ራዕ.13፡13-15 “እሳትንም ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እስኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል ...” ስለ ኃይሉና ብርታቱም ሲናገር ራዕ.13፡7 “ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው።።” በዚህ ብቃቱም 2ተሰ.2፡4 “እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በቤተ መቅደስ እስከሚቀመጥ ድረስ፣ አምላክ ከተባለው ሁሉ፣ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው።።” በማለት ራሱን “እግዚአብሔር” እስከማለት እንደሚደርስ ይናገራል።።

የሚገርመው ደግሞ ስለዚህ ሰው መጽሐፍ ቅዱሱ፣ ሌሎች ኃይማኖቶችም ሆኑ ዘመናዊው ፊልሞች በጉጉት የሚጠብቁት ሆኖ፣ ከመጽሐፍ ቅዱሱ በስተቀረ ሁሉም አድናቆታቸውን የሚቸሩት መሆኑን ስንመለከት እነዚህ አካላት የተለያየ ስም ይንቀሳቀሱ እንጂ ዞረው ዞረው በክርስትና ተቃዋሚ መንፈስ የሚመሩ አንድ ቡድኖች መሆናቸውን እንመለከታለን።።

በዚህ ምዕራፍም ይህን መንፈስ ለመቀበል እየተደረጉ ያሉትን ዓለማቀፋዊ ቅድመ ዝግጅቶችንና ሀገራዊ አሰራሮች፣ መንፈሱ ሲገለጥ የሚከተለው አሰራር፣ የቁጥጥር እስትራቴጂና የመንፈሱ መጨረሻ ምን እንደሚሆን በዝርዝር እንመለከታለን።።

7.1. <u>የዓለም ቅድመ ዝግጅቶች</u>

ዓለም በግሎባላይዜሽን ሂደት አንድ መንደር እየሆነች ትገኛለች፣ በዚህ ሂደትም ሀገራት በቴክኖሎጂው እገዛ በማኅበራዊው፣ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው ዘርፍ ጠንካራ ትብብሮሽና ውህደትን እየፈጠሩ ወደ አንድነት እየሄዱ ይገኛሉ።።

በሌላ በኩል ደግሞ ይህን ዓለም ወደ አንድ መንደርነት እየሄደች ያለችበትን እውነታ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂው በቁጥጥሩ ስር እያስገባ ይገኛል፣ ከተራው የፅሁፍ አገልግሎትና የማኅበራዊ ሚዲያ አንስቶ የዓለምን ስርዓት ተቆጣጥረው እስከሚገኙት የቴሌኮምኒኬሽን፣ መብራት ኃይል፣ ባንክ፣ ኢንሹራንስ እስከ ጅምላ ጨራሽ ኒውክለር ቦንቦች፣ የኒውክለር

ኃይል ማመንጫዎች፣ ሚሳኢሎችና የሳተላይት ሲስተሞች በኮምፒውተር አሰራር ቁጥጥር ስር ወድቀው ይገኛሉ፣ በዚህም ዓለም ሳይስተዋል በአንድ ስርዓት ስር እየወደቀች ትገኛለች።

ይህ ደግሞ የራሱን የጎንዮሽ ጉዳት አለው፣ ለምሳሌ እንኳን በመንፈሳዊ ኃይል የሚንቀሳቀሰውን ልዩ የሆነውን ሰው ትተን፣ በአንድ የሶፍትዌር አምራች ድርጅት በሚሰራ የኮምፒውተር ፕሮግራም ብቻ ይህን በአንድ ስርዓት ውስጥ የወደቀውን ዓለም በቀላሉ በቁጥጥር ስር ማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፣ ለምሳሌ በቅርብ ጊዜ እንኳን “Ransom ware” የተባለው ቫይረስ ዓለምን እንዴት በአንድ እግር እንዳስቆመ ማስታወስ ይቻላል፣ ከዚህ የተራቀቀ የሁሉንም ኮምፒውተር ስርዓቶች የሚቆጣጠር ቫይረስ በአንዱ ግለሰብ ወይ ድርጅት ቢለቀቅ ይህ አካል በቀላሉ ዓለምን መቆጣጠር ይችላል፣ ይህን ሰው “የዓለም ንጉሥ ነኝ፣ አምላካችሁ ነኝ፣ ባታነግሡኝና ባትሰግዱልኝ የባንክ፣ የኒውክለር ... ስርዓቱን አጠፋዋለሁ” ቢል አብዛኛው ሰው ይህንን ከማረግ ወደ ኋላ አይልም።

በዚህም ማንም ዓለምን መግዛት የፈለግ አካል ይህን ዓለም በአንድ ስርዓት ውስጥ እየገባች ያለችበትን ሂደት ይጠቀምበታል፣ ከላይ የተመለከትነው በመናፍስታዊ ኃይል የሚንቀሳቀሰው ሰውም ሌላ ምንም ትግል ሳይፈጥር ይህንኑ ሲስተም በቀላሉ በመያዝ ዓለምን በቀላሉ መግዛትና ማስገድ ይችላል፣ በዚህም አሁን ዓለም በአንድ ስርዓት ውስጥ እየወደቀች ያለችበት ሁኔታ ከላይ ለተመለከትነው ኃይል እየተሰራ ያለ ቅድመ ዝግጅቶች ነው።

አባማ፣ ዙከርበርግ፣ ቢልጌትስን ጨምሮ ብዙ ኤቲስቶች የሚያደንቁት፣ የ“Sapience” መጽሐፍ ደራሲ የሆነውና በሂብሩ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ፕሮፌሰር የሆነው Yuval Noah Harari እንደተነበየው በመጪው ዘመን ኮምፒውተር የግለሰቦችን እንቅስቃሴ ጨምሮ ሁሉንም ነገር በቁጥጥሩ ስር ስለሚያስገባ በዓለም ላይ ገዢ የሚሆነው የኮምፒውተር ስርዓት፣ አልጎሪዝም፣ ነው በማለት፣ [170] የመጪው ዘመን አምላክ አልጎሪዝም እንደሚሆን የራሱን ትንቢት አስቀምጧል።

የዚህ ግብረሰዶማዊ የሆነው እስራኤላዊ ሰው ትንቢት እውነት ይሁን ውሸት አንድ ማንኛችንም የምንገነዘበው ሂደት ግን አለ፣ የዓለም ስርዓት በኮምፒውተር ቴክኖሎጂው ቁጥጥር ስር እየገባ ያለበት ሂደት።

ከዚህ አጠቃላይ ዓለማቀፋዊ ሂደት ወረድ ብለን ይህንን ስርዓት እየመሩ ያሉት መሪዎች በሀገራቸው ውስጥ እያካሄዱ ያሉትን ነገር ስንመለከት ደግሞ መሪዎቹ በጥብቅ መናፍስታዊ ትስስር ሂደቱን በአንድ መንፈስ እያመቻቹ እንደሆነ እንመለከታለን።

[170] https://m.youtube.com/watch?v=g6BK5Q_Dblo&t=229s (Religions of the 21st century)

መሪዎቹ በምን አይነት *መንገድ ሀገራቸውን* እያመቻቹ እንደሆነ *ለመመልከት* እንዲያመቸን በመጀመሪያ *መንፈሱ* የሚፈልገውን አሰራር ለይተን እንመልከት፤ *መንፈሱ* የእግዚአብሔር ተቃራኒ *መንፈስ* በመሆኑ ተቃራኒ አሰራሮችን ይከተላል፣ በዚህም በዋናነት ለመጽሐፍ ቅዱሱ፣ ለእስራኤልና ለተፈጥሯዊው አሰራር ተቃራኒ አሰራሮችን ይከተላል፡፡ እዚህ *ጋር* ለተፈጥሯዊው አሰራር ተቃራኒነት(ኢ-ተፈጥሮአዊነት) ማለት እንደ ውርጃ፣ ግብረ ሰዶማዊነት(Homosexuality)፣ ከተፈጥሮው ጾታ በተቃራኒ ሌላ ጾታ *መሆን*(Transgender)፣ ከሁለቱም *ፆታ ጋር መተኛት*(Bisexuality)፣ የሰውን ልጅ አእምሮን ከአርቴፊሻል ኢንተሌጀንስ ቴክኖሎጂ *ጋር* ማያያዝ(Transhumanism)፣ በትዳር ውስጥ በፈጣሪ እንዲሁም በተፈጥሮ የተቀመጠውን የትዳር *መዋቅር* በመተው ባልና ሚስትን በአንድ ስልጣን ላይ እኩል አድርጎ ማስቀመጥ … በአጠቃላይ በፈጣሪና በስነ ተፈጥሮ ተቀምጠው ያሉ ህጎችን *መቃወምና* እነዚህን ኢተፈጥሯዊ አሰራሮችን ማበረታታትና ለመብታቸው መቆምን ያጠቃልላል፡፡

በመሪዎች *መ*ካከል ያለውን መናፍስታዊ ትስስር *ለመመ*ልከት ለምሳሌ ያህል ዋናዎቹን የዓለም የፖለቲካና የኃይማኖት *መሪዎችን* አሜሪካን፣ የአውሮፓ ኅብረትንና ቫቲካንን የምንመለከት ሲሆን አካሄዱን ተጨባጭ በሆነ መልኩ ለመገንዘብ እንዲረዳንም በሀገራችን ላይ ያለውንም አሰራር በተጨማሪም እንመለከታለን፡፡

1. <u>አሜሪካ</u>

የአሜሪካ *መ*ንግሥት የሚመራው በሁለቱ በዲሞክራትና ሪፐብሊካን ፓርቲዎች ነው፣ ሁለቱ ፓርቲዎች ፍፁም ተቃራኒ በመሆናቸው የሚሰሩዋቸው ስራዎችም ተቃራኒ ናቸው፣ ይህ ተቃርኖም የመጣው ከጀርባቸው ባለው ተቃራኒ *መንፈስ* ነው፣ ይህንን ተቃርኖ በቀላል ምሳሌ በኦባማና በትራምፕ *መ*ካከል ባለው ልዩነት *መመ*ልከት ይቻላል፡፡

ኦባማ በስልጣን ዘመኑ ግብረ ሰዶማዊነትን ህጋዊ አደረገ፣ ዓለማቀፉ ማኅበረሰብም እንዲቀበለው ብዙ ተፅዕኖ አደረገ፣ ውርጃን በሀገሩና በዓለማቀፍ ደረጃ በከፍተኛ ደረጃ ፈንድ ሲያደርግ ነበረ፣ በቤተ *መንግሥት* ውስጥ በክብር ሲቀመጥ የነበረውን የአስርቱን ትዕዛዛት ቅርፃ ቅርፅ ከቤተ *መንግሥቱ* እንዲወጣ አደረገ፣ ለክርስትና ትልቅ ስፍራ የሚሰጠውን አሜሪካዊነት እንዲበረዝ የግሎባላይዜሽንንና የአሜሪካን ድንበር ክፍት የማድረግን አሰራር ተከተለ፣ *መ*ጽሐፍ ቅዱሱ “እስራኤላውያን ከዓለም ሁሉ ይሰበሰባሉ” እንደሚለው ለዚህም ትንቢት ማስፈፀሚያ የእስራኤል *መንግሥት* የሚሰራውን የአዳዲስ ቤቶች ግንባታ ከለከለ፣ የእስራኤልን ብሔራዊ ጥቅም የሚጎዱትን የ“two state solution” እና የኢራን የኒውክለር ውል አንቀሳቃሽ ነበረ፣ እስራኤል በዓረቡ *መ*ካከል ተገልላ እንድትኖር ሲያደርግ ነበረ፣ በ2.3.2.5 ክፍል የተመለከተውን ቁርአናዊ የሽብር ስራ ለመሸፋፈን ድርጊቱን “Violent Extremism” በማለትና በስልጣን *ዘመ*ኑም በነዚህ ኃይላት ላይ እርምጃ እንዳይወሰድ ሲያደርግ የነበረ ሲሆን ትራምፕ እነሱን የሚጠራበትን “Radical Islamic Terrorism” አባባልን ሲቃወም ነበረ፡፡

ትራምፕ ደግሞ ሲመረጥ ከአባማ በተቃራኒ የሆሞሴክሹዋል ህጉን በተቻለው መንገድ ጫና አደረገበት፣ የውርጃ በጀቶችን በተቻለው መጠን ቆራረጠ፣ አባማ ከቤተ መንግሥቱ ያስወጣውን አስርቱ ትዕዛዝ ቅርፃ ቅርፅ ወደ ቤተ መንግሥቱ መለሰ፣ [17]መጽሐፍ ቅዱስ ሆስፒታሎች ውስጥ ተመልሶ እንዲታደል አደረገ፣ አባማ ያዘጋጀውን የኢራን የኒውክለር ውል በመሠረዝ አባማ ያነሳውን ማዕቀብ መልሶ አስቀመጠ፣ በ2.3.2.5 ክፍል የተመለከተውን ቁርአናዊ የሽብር ስራ በግልፅ "Radical Islamic Terrorism" በማለት የአባማን የመሸፋፈን አባባል "Violent Extremism" በመቃወምና በነዚህ ኃይላት ላይ በተከተለው አሳሪ አካሄድ ከዓለም ላይ ድምፃቸው እንዲጠፋ አደረገ፣ የእስራኤል የሰፈራ ቤቶችን ግንባታ ፈቀደ፣ በኤር.29፡10 መንፈስ በእስራኤል ሰባኛ አመት ምሥረታ በዓል ቀን ላይ የኢየሩሳሌም የእስራኤልን ዋና ከተማነት አረጋገጠ፣ ለእስራኤል ወታደራዊ እስትራቴጂ ጉልህ ሚና የሚጫወተውን የጎላን ኮረብታዎች የእስራኤል አካል መሆናቸውን አወጀ፣ እስራኤልን በጠላትነት የሚመለከቱት የዓረብ ሀገራት ላይ ጫና በመፍጠር ብዙ የዓረብ ሀገራት ከእስራኤል ጋር እንዲታረቁ አደረገ፡፡

እነዚህ ሁለቱ ሰዎች ፊት ለፊት እንደዚህ ተቃራኒ ሆነው ይታዩ እንጂ የጀርባ አጥንታቸው የፓርቲያቸው ርዕዮተ ዓለም ነው፣ በዚህም ሁለቱ ፓርቲዎች በምን አይነት ተቃራኒ መንፈስ እየተነዱ እንዳለ መመልከት ይቻላል፡፡

2. <u>የአውሮፓ ኅብረት</u>

የአውሮፓ ኅብረት ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሆኑት የምዕራብ አውሮፓ ሀገራት ከላይ የተመለከትነውን የአባማን መንገድ ይከተላሉ፤ በተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ፣ በውርጃ፣ በእስራኤል ፍልስጤም ጉዳይ፣ በኢራን የኒውክለር ጉዳይ፣ በግሎባላይዜሽንና የስደተኞች ጉዳይ፣ በሽብርተኝነት ጉዳይ ላይ ከአባማ ተመሳሳይ አቋም አላቸው፡፡

በኅብረቱ ውስጥ የምስራቅ አውሮፓ ሀገራት ተፅዕኖ ፈጣሪ ባይሆኑም የትራምፕ ፖለቲካ መስመርተኞች ናቸው፣ እነዚህ ሀገራት የክርስትና ዕሴቶችና የእስራኤል ብሔራዊ ጥቅም ደጋፊዎች ሲሆኑ የኢ-ተፈጥአዊነት(ግብረ ሰዶም፣ ውርጃ ...) እንደዚሁ የእስልምና አክራሪነትን ይቃወማሉ፣ አንዳንዶቹ የእስልምናን አክራሪነት ከመቃወም አልፈው "እስልምና አሸባሪ ኃይማኖት ነው" እስከማለት ሲደርሱ ይታያሉ፡፡

ከምዕራብ አውሮፓውያኑ እንግሊዝ ተፅዕኖ ፈጣሪዎቹ ሀገራት የአውሮፓ ኅብረትን እያስኬዱበት ያለው መንገድ አልተመቻትም፣ በዚህም ህዝቡ በብሬግዚት ውሳኔ ከኅብረቱ ለመውጣት ውሳኔ ላይ ደርሷል፣ በርግጥ ህዝቡ ከአውሮፓ ለመገንጠል ውሳኔ ላይ ይድረስ እንጂ ትስስሩ መናፍስታዊ በመሆኑ ብሬግዚት በቀላል የሚከናወን ነገር አልሆነም፣ ጠቅላይ ሚስትሯ፣ ቴሪሳ ሜይ፣ በዚሁ ምክንያት ስልጣኗን ለቃለች፣ ተተኪው ቦሪስ ጆንሰንም

[17] የአሜሪካው ምክትል ፕሬዚዳንት፣ Mike pence, August/29/2019, facebook ገፃቸው ላይ ያስነበቡት ፅሁፍ ነው፡፡

ይህንን ጉዳይ ማስፈፀም አቅቶት ስልጣኑን ለቋል፣ አሁን የተተካው ሪቺ ሱናክም ተመሳሳይ ነገር እንደሚገጥመው ግልፅ ነው።።

የብሬግዚት ምርጫ ሲካሄድ በነበረበት ወቅትም ያለውን ዓለማቀፋዊ መንፈሳዊውን ትስስር በግልፅ በሚያሳይ መልኩ ብሬግዚት በትራምፕና በእስራኤል ሲደገፍ በተቃራኒው ደግሞ አባማ፣ የኢትዮጵያ መንግሥት፣ ቫቲካን ... የመሳሰሉት የብሬግዚት እንቅስቃሴ ተቃዋሚዎች ነበሩ፣ በዚህም በዓለማቀፍ ደረጃ ያለውን መናፍስታዊ ትስስር ማስተዋል ይቻላል።።

3. <u>ቫቲካን</u>

ኢየሱስ ተቀምጦ ሳለ ወሬ ነጋሪዎች አንድ ነገር በጆሮው ሹክ አሉት፣ "ከዚህ ስፍራ አምልጥ ሄሮድስ ሊገድልህ ይፈልጋል አሉት" ኢየሱስ ግን ከወትሮው በተለየ አነጋገር ፣

> ሉቃ.13፡32 "... ሄዳችሁ ለዚያች ቀበሮ፣ እነሆ ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ በሽተኞችንም እፈውሳለሁ፣ በሦስተኛውም ቀን እፈፀማለሁም በሉአት (አለ)።።"

እዚህ ጋር ይህ የኢየሱስ እንግዳ አነጋገር የመጣው፣ የታቀደበትን ሤራ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ነው ነገር ግን "ቀበሮ" ያለው ማንን ነው? የሚለውን ለማወቅ የሮማን ታሪክ ከስር መሠረቱ መመልከት ያስፈልጋል፣ እንደ ሮማውያን አባባል፣

> [172] "ሮም የተመሠረተችው ሮሙለስና ሬሙስ በተባሉ ሁለት ሰዎች ነው፣ እነዚህ ሰዎች በህፃንነታቸው ቲበር በሚባለው ወንዝ ውስጥ በተጣሉ ጊዜ በአካባቢው የነበረች ቀበሮ እነዚህን ህፃናት ከውሀው አውጥታ ወደ ቤትዋ በመውሰድ አጥብታ ታሳድጋቸዋለች፣ ህፃናቱም ካደጉ በኋላ በአካባቢው የተመለከታቸው እረኛ ህፃናቱን ይወስዳቸዋል፣ እነዚህ ወንድማማቾችም ካደጉ በኋላ ታላቅ ህዝቦች በመሆን ያሁኗን ሮም መሠረቷት።።"

ይላሉ ለዚህም መታሰቢያነት በኢጣልያን "The capitolina Wolf" የሚባል አንድ ቀበሮ ሁለት ህፃናትን ስታጠባ የሚያሳዩ ሀውልቶች ይሰራሉ፣ ታሪኩ እውነትም ይሁን ውሸት ህዝቡ ግን በዚያን ወቅት በቀበሮ ባለውለታነትና እናትነት ያምን ስለነበረ፣ ኢየሱስም ህዝቡን የጠራው ህዝቡ ራሱን በሚመለከትበት መንፈስ ነው "ለዚያች ቀበሮ" ያለው።።

ያቺ ቀበሮ ዛሬም የዓለም አንደኛ የሆነው ኃይማኖት መሪ በሆነችው በቫቲካን በኩል በጎቹ ላይ አድብታለች።።

[173] ቫቲካን ማለት በ44 ሄክታርና በ1,000 ህዝብ ብዛት በሮም ከተማ ውስጥ የምትገኝ የራሷ መንግሥት፣ ባንዲራና ብሔራዊ መዝሙር ያላት ሉአላዊ ሀገር ናት፣ ሀገሪቱም የምትመራው የዓለም ካቶሊክ ኃይማኖት መሪና የሮማው ጳጳስ ሆነው በሚሾሙት ሰው

[172] https://en.m.Wikipedia>wiki>The capitolina Wolf

[173] https://en.m.Wikipedia>wiki>VaticanCity

ነው፡፡ ይህቺ ከዓለም የመጨመረሻ ትንሿ ሀገር የነ.3 ቢሊየን ተከታይ ያላት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሪ በመሆኗ ያላት የፖለቲካ ጉልበት ከኃያላኑ ሀገራት ጋር የሚስተካከል ነው፡፡

የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጥንታዊ ቤተክርስቲያን ስትሆን እንደ ጥንታዊነቷም በጊዜ ሂደት ውስጥ ብዙ የተሳሳቱ ትምህርቶች ወደ ቤተክርስቲያኗ እንደገቡ በምዕራፍ 4 በዝርዝር ተመልክተናል፡፡

የሁለቱም የኦርቶዶክስና የካቶሊክ አስተምህሮ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ በመሆኑ ሁለቱም በተመሳሳይ የስህተት መንገድ ላይ የሚገኙ ቢሆንም የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግን ከስህተቱም አልፋ <u>በይፋ</u> የጥልቁ መንፈሳዊ አሰራር ውስጥ ገብታለች፡፡ በዚህም ቤተክርስቲያኗ ዛሬ ላይ የሰይጣን እጆች ወደ ክርስትና ማስገቢያ በር ሆናለች፣ የሰይጣንን ዕቅዶች የክርስትና ካባ የሚደረብላቸው በዚች ቤተክርስቲያን ነው፣ ዛሬ በቤተክርስቲያኗ ግብረሰዶም ህጋዊ ጋብቻ ተደርጎ ተፈቅዷል፣ ቤተክርስቲያኗም ብዙ ታዋቂ ግብረሰዶም ቀሳውስት አሏት፣ ብዙ ህፃናትም በግብረ ሰዶማውያኑ ቀሳውስት ተደፍረዋል፡፡

የአማኞችን ጭንቅላት ያዞሩትን፣ የቢግ ባንግ እና የዝግመተ ለውጥ ፅንሰ ሐሳቦችን ለዓለም ያስተዋወቁትና ያስተማሩት የቤተክርስቲያኗ የኃይማኖት አባቶች ናቸው፡፡ በፖለቲካው መስክም ከቅዱሱ በተቃራኒው ተሰልፋለች፣ የእስራኤል - ፍልስጤም ጉዳይ ላይ እስራኤልን የሚጎዳው የሁለት ሀገሮች መፍትሄ(two state solution) ደጋፊ ስትሆን ይህንኑ የሚያጠናክር የፍልስጤምን ነፃ ሀገርነት ስምምነት ከፍልስጤማውኑ የነፃነት ድርጅት(PLO) ጋር ተፈራርማለች፣ የኢየሩሳሌም የእስራኤል ዋና ከተማነትን ትቃወማለች፣ አባማ ያዘጋጀው እስራኤልን የሚጎዳው የኢራን የኒውክለር ውል ትደግፋለች፣ የግሎባላይዜሽን ደጋፊ ስትሆን በዚህም የትራምፕን “አሜሪካ ትቅደም” እና የአሜሪካን ድንበር ለስደተኞች ዝግ የማድረግ ፖሊሲን ትቃወማለች፣ ብሬግዚትን ትቃወማለች፣ የወደፊቱ ሐሰተኛው ክርስቶስ የሚመራው “አንድ ዓለም አንድ ኃይማኖት” መርህ በመቀበል ኃይማኖታትን አንድ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰች ትገኛለች፡፡

6. <u>ኢትዮጵያ</u>

ከላይ የተመለከትነው የመንፈስ አሰራር ኢትዮጵያ ላይም እየሰራ ይገኛል፣ ኢትዮጵያ ላይ የሚሾሙት መንግሥታት በሙሉ ለእርዳታ፣ ለፖለቲካ ጥቅም … ወዘት በማሰብ ከላይ ከተመለከትናቸው መናፍስታዊ አሰራሮች ጋር መስመርተኛ በመሆን ተመሳሳይ አሰራሮችንና አቋሞችን በሀገር ውስጥና በዓለማቀፍ ጉዳዮች ላይ ሲያራምዱ ይታያል፡፡

ከዓለማቀፍ እውነታ ብንነሳ ኢትዮጵያ በተባበሩት መንግሥታት ስብሰባ ላይ ሁል ጊዜ ዓረቦችን በመደገፍና እስራኤልን በመቃወም በቋሚነት ድምፅ የምትሰጥ ሀገር ናት፣ በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ ኅብረት [174] የፀረ ፅዮናዊነትን ውሳኔዎች ደጋፊ ሆና ድምፅ የሰጠች ሀገር ናት፣ እስራኤልን የሚጎዳውን "የእስራኤልና የፍልስጤም ሁለት ሀገር መፍትሄ" (two State Solution) ከመደገፍ አልፋ ፍልስጤም ሀገር ሳትሆን እንደ አንድ ሀገር አዲስ አበባ ላይ ኤምባሲ ከፍታላታለች፣ አባማ ያዘጋጀውና እስራኤልን የሚጎዳው የኢራን የኒውክለር ውል ደጋፊ ናት፣ ከአሜሪካው ዲሞክራት ፓርቲ ጋር ፍቅር በፍቅር ስትሆን ከሪፐብሊካን ፓርቲ ጋር ግን ተቃራኒ ናት፣ ሂላሪና ትራምፕ ለምርጫ ሲወዳደሩ ትራምፕ እንዳይመረጥ የወቅቱ የኢትዮጵያ መንግሥት በዲያስፖራው ማኅበረሰብ በኩል ብዙ ዘመቻዎች ሲያካሄድ ነበረ፣ ለትራምፕ ተቃራኒዋ ሂላሪ የምርጫ ዘመቻ ወጪ በነህላሙዲን በኩል የገንዘብ ድጋፍ ሲያስደርግ ነበረ፣ አሁን "ለውጥ" በተባለበት ዘመን እንኳን ሀገሪቷ እየተጓዘች ያለችው በቀደመው መንገድ ነው፣ በዚህም ከለውጡ በኋላ በተከሰተው የኢየሩሳሌምን የእስራኤል ዋና ከተማነት ጉዳይ ላይም ኢትዮጵያ የትራምፕን ውሳኔ ስትቃወም ነበረች::

በሀገር ውስጥ ጉዳይም ስንመለከት፣ መንግሥት ውርጃን ህጋዊ ያደረገ ሲሆን በዚህም [175] በመንግሥት ጤና ተቋማት በኩል በአመት 221,533 ህፃናትን እንዲሁ በሜሪስቶፕስ በኩል በአመት 504,000 ህፃናትን፣ እንደዚሁ በብሉስታር በኩልም ተመሳሳይ መጠን ውርጃ ይከናወናል፣ በዚህም በአመት ከአንድ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያንን በውርጃ በመግደል ሀገሪቱ በውርጃ በአፍሪካ አንደኛ ደረጃን ይዛለች:: ሆሞሴክሹዋሊቲ በግልፅ ባይፈቅድም ሲከለከል ግን አይታይም ይባሱኑ በማረሚያ ቤቶች እንዲስፋፋና በጸታና ስነተዋልዶ ትምህርቶች በሚሰጡት ድርጅቶች በኩል የሆሞሴክሹዋሊቲን ማበረታቻ ትምህርቶችና ልምምዶች ሲሰጡ እየተመለከትን ነው::

ባንዲራና ዓርማ የተለያዩ ነገሮች ሆነው ሳለ በሀገሪቱ ባንዲራ ላይ በህገ መንግሥቱ ያልተደነገገው ዓለማቀፋዊው ሰይጣናዊ ዓርማ ነው የተቀመጠው፣ [176] በክብ ውስጥ የተቀመጠ አምስት ጎን ያለው ኮከብ ማለት ዓለማቀፋዊ የሰይጣን ምልክት ነው፣ የ666 መንፈስ አካል የሆነው የኢሉሚናቲ ኃይማኖትም ዓርማው አድርጎ የሚጠቀመው ይህንኑ ዓርማ ነው፣ ትርጉሙም የፍየል ሁለቱ ቀንዶች፣ ሁለቱ ጆሮዎችና ፂሙ ሲሆን ያው

[174] ብዙዎቻችን "ፅዮናዊነት" የሚለውን ቃል በመንግሥት ሚዲያዎች ሲወገዝ ብቻ ስለሰማን ቃሉን ልክ እንደ አሸባሪነት ነው የምንመለከተው፣ ይሁን እንጂ "ፅዮናዊነት" ማለት የእሥራኤላውያኑ "ወደ ሀገራችን እንመለስ" እንቅስቃሴ ስያሜ ነው::

[175] የኢትዮጵያ ጉባዔ እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን፣ **የጊዜው ድምፅ** (መፅሄት)፣ 2010፣ ቁጥር 8፣ ገፅ 37

[176] https://en.m.Wikipedia>wiki>satanism

መጽሐፍ ቅዱሱ ኢየሱስን "በጉ" እንደሚለው ሐሰተኛውን ክርስቶስ ደግሞ በፍየል እንደሚመሰለው ነው።።

የሚገርመው ደግሞ ይህ ዓርማ በባንዲራውና ከህገ መንግሥቱ አንስቶ ባሉት ህጎች ላይ ጎልቶ ተቀምጧል፣ "ኢትዮጵያ" ሲባል በዋናነት የሚታየው ባንዲራዋ ነው፣ በዚህም ባንዲራዋ ግንባርዋ ነው፣ ሀገሪቱ የምትተዳደረው በሕግ ነው፣ በዚህም ህጉ የሀገሪቱ ቀኝ እጅ ነው፣ በዚህም በራዕ.13፡16-18 ላይ የተገለፀውን የአውሬውን ምልክት በሀገሪቱ ግንባርና ቀኝ እጅ ላይ ተቀምጧል፤ ከዚህ በተጨማሪም ባንዲራው ላይ የተመለከተው ሦስት የቀለም እስትራይፖችን ከክብ ቅርፅ ጋር የሚቀናበርበት አሰራርም "አዕምሮ ያለው ይቁጠረው" የተባለው የ666 ቁጥር አንዱ የአፃፃፍ ስልት ነው።።

በአጠቃላይ ስንመለከት በዓለምአቀፍ ደረጃ ለሐሰተኛው ክርስቶስ መንገድ ጠራጊ የሆኑት ሐሰተኛ "መጥምቁ ዮሐንሶች" ጠንካራ ዝግጅት እያደረጉ እንደሆነ እንመለከታለን።።

7.2. <u>መንፈሱ በሙላት ሲገለጥ የሚከተለው አሰራር</u>

ከላይ እንደተመለከትነው መንፈሱ ዛሬ ላይ በነገሥታት በኩል ግልፅ ባልሆነ መንገድ ውስጥ ለውስጥ እየሰራ ቢሆንም፣ እንደዚሁ በአንዳንድ ሰዎች በኩል ኢሉሚናቲ፣ ሳታኒዝም ... በሚሉ መንፈሳዊ ስሞች ጥቂት እንቅስቃሴዎችን ቢጀምርም፣ መንፈሱ ግን በግልፅ በዓለም ላይ በአሸናፊነት የሚሰራበት የራሱ ዘመን አለው፣ ይህም ለሰባት አመታት(አንድ ሱባኤ) ሲሆን(ዳን.9፡27) በዚህ ሰባት አመት ሁለተኛው መንፈቅ ላይ(42 ወራት/1260 ቀናት) መንፈሱ በሙላት ይነግሳል(ዳን.11፡36, ራዕ.13፡5-7)፣ እስራኤልን ይወርራል(ራዕ.11፡2, ራዕ.13፡5)፣ በእስራኤል ላይ የሚነሱትን ሁለቱን ነብያት ይገድላል(ራዕ.11፡3-10)፣ ወደ እግዚአብሔር የሚደረገውን አምልኮ ያስቀራል(ዳን.11፡31)፣ "እግዚአብሔር እኔ ነኝ" በማለት(2ተሰ.2፡4) ብቻውን የሚመለከበት(ራዕ.13፡4) ሁኔታ ይፈጥራል።።

ይህንንም የሚያደርገው ከላይ የተመለከትናቸውን ሁኔታዎችን እያመቻቸለት በሚገኙት "ሐሰተኛ ዮሐንሶች" በመጠቀምና ቀጥሎ በምንመለከታቸው በግለሰቦች ሰውነት ውስጥ በሚቀበር ረቂቅ ቁስና ድርጅቶችንም ደግሞ የራሱን ምልክትና ዓርማ እንዲጠቀሙ በማድረግ ሁሉንም ሰውና አሰራር በራሱ ቁጥጥር ውስጥ በማስገባት ነው፣ ቀጥለን እንመለከታለን፡-

1. <u>*በግለሰቦች ላይ በሚቀበር ምልክት</u>

መንፈሱ በግልፅ መስራት ሲጀምር የዓለምን ህዝብ የሚቆጣጠረው በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ እንዲቀበር በሚያደርገው አሰራሩ(ቴክኖሎጂው) ነው፣

ራዕ.13፡16 "ታናናሾችም ታላላቆችም ባለጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎች ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ(ያደርጋል)"

ራዕዩን የተቀበለው ዮሐንስ የተመለከተውን ራዕይ በወቅቱ በነበረው ሰውኛ ቋንቋ ችግር ምክንያት የሚገልፅበት ቃል ባለመኖሩ፣ በገባው መንገድ “ምልክት” ብሎ ገልጾታል፣ ቴክኖሎጂው አሁን በሙከራ ላይ በመሆኑ አሁንም አንድ ቋሚ ስም አልያዘም፣ በዚህም አሁንም በተለያየ ስም እየተጠራ ይገኛል፣ RFID Chips, Bio chips, micro chips, brain chip ... ወዘተ፣ ለዚህም ቀለል ባለ ቋንቋ ለጊዜው “ቺፕስ” ብለን እንጠራዋለን፡፡

ቺፕስ በአነስተኛ መጠን ተሰርቶ በሰውነት ውስጥ የሚቀበር የመረጃ ስርዓት ሲሆን ቺፕሱ እንዴት ወደ ሰው ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ሳይንቲስቶች ብዙ ጥናት እያደረጉ ሲሆኑ ከሁሉ ጎልተው እየወጡ ያሉት ግኝቶችም ቺፕሱ በቀላሉ እንደ መድኃኒት በመርፌ፣ በንቅሳት መልክ በመንቀስ ወይ በጨረር ማስገባት እንደሚቻል ነው፡፡ ቺፕሱንም አንባቢ መሣርያዎች በቀላሉ ማንበብ እንዲችሉ መቀበር ያለበት በቀኝ እጅ ወይንም በግምባር ላይ መሆን እንዳለበት እየተነገረ ይገኛል፣ ይህም በራዕዩ ላይ የተገለፀው እውነታ ነው፡፡ ስርዓቱ ይህንን የሚቀበረውን ቺፕስ ለማንበብ የሚጠቀመው የ“Computer እና RFID scanner” ቴክኖሎጂ ጥምርታን ሲሆን እነኚህ ስሞች ደግሞ ከታች በቀረበው ፎርሙላ ስናሰላው ስሌቱ “የአውሬው ቁጥር” የተባለውን 666 ቁጥር ነው፡፡

ቺፕሱን ማስቀበር ላይ ላዩን ሲታይ ብዙ ጥቅሞች አሉት፣ ይህም በዋናነት የገንዘብ ኖት፣ የባንክ ደብተር፣ መታወቂያ፣ የመንጃ ፍቃድ፣ የህክምና ታሪክ፣ የትምህርት ማስረጃ ... በአጠቃላይ የወረቀት ዶክመንቶችን ሽክም የሚያስቀር፣ በፎርጀሪ፣ ስርቆት፣ ዝርፊያ፣ ቃጠሎ ... ምክንያት የሚመጡ ችግሮችን የሚያስቀርና ሰዎች ግብይትንና ኑሯቸውን በቀላሉ እንዲያከናውኑ የሚረዳ “ቴክኖሎጂ” ነው፣ ነገር ግን ዋናው ስራው ከላይ የተመለከትነው ዓለምን በአንድ ስርዓት ውስጥ እያስገባው ያለው መንፈስ ግለሰቦችንም በዚሁ ቁጥጥር ስር የሚያስገባበት አሰራር ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሱ ግን በዚያን ወቅት የሚኖሩት ቅዱሳን ይህንን ምልክት እንዳይቀበሉ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

2. <u>ድርጅቶች በሚጠቀሙት ዓርማና የንግድ ምልክት</u>

መንፈሱ በሙላት በሚሰራበት ወቅት ድርጅቶች ለአርማ ወይንም ለንግድ ምልክታቸው የአውሬውን ምልክት ወይንም የስሙን ቁጥር እንዲያደርጉ ያስገድዳቸዋል፣

> ራዕ.13፡17-18 “<u>የአውሬው ምልክት</u> ወይም <u>የስሙ ቁጥር</u> ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል፡፡ አዕምሮ ያለው የአውሬውን <u>ቁጥር</u> ይቁጠረው፤ <u>ቁጥሩ</u> የሰው <u>ቁጥር</u> ነውና፣ <u>ቁጥሩም</u> ስድስት መቶ ስድሳ ስድስት ነው፡፡”

እዚህ ጋር “የአውሬው ምልክት” የሚለው በራዕ.13፡1 ላይ በቀጥታ የተመለከተው “አስር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ያለው አውሬ” የሚለውን ምስል አንስቶ ሰይጣን የሚመሰልበት የእባብ፣ ዘንዶ፣ ጊንጥ ... ምስሎች እንዲሁም ጥርሳቸው፣ ጥፍራቸው ... የጎሉ አውሬዎች፣ እስከ የእስራኤላውያን የውርደት ምልክቶች፣ የግብፁ ፒራሚድ፣ የናዚ አርማ... ምስሎች የሚደርስ ነው፡፡

“የስሙ ቁጥር” የሚለው የአውሬው አሃዛዊ መገለጫ ሲሆን ይህም የአውሬው ቁጥር “666” ጋር ግንኙት ያለው ቁጥር ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሱ “አዕምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው፣ ቁጥሩ የሰው ቁጥር ነውና” ይላል እንጂ ሙሉ መረጃውን አይሰጥም ምክንያቱም ቁጥሮቹ በተለያዩ ዘዴ የሚቀናበሩ በመሆኑና ማንም አዕምሮ ያለው ሰው ከቅንብሩ ውስጥ ቁጥሩን ማንበብ የሚችል በመሆኑ፡፡

ዛሬ ላይ ሰዎች ለራሳቸውና ለድርጅታቸው ስኬት ሲሉ ከመናፍስታዊው አሰራር ጋር እየፈጠሩት ባለው ጎብረትም ቁጥሩን በድርጅቶቻቸው ዓርማዎችና የንግድ ምልክቶች በተለያየ ቅንብር እያሳዩን ይገኛሉ፣ ዋነኞቹ የቅንብር ዘዴዎችም፣

1. ቁጥሩን በቀጥታ፣ በተለያየ አቅጣጫ ወይም በተለያየ ዘዴ በማደራረብ በመፃፍ፡- 666፣ 999 ...
2. ቁጥሩን ከምልክቶች፣ ከዓርማዎች ... ውስጥ በዘዴ በማስቀመጥ፣ ለምሳሌ
   - አንዱን ስድስት በተለያየ ዘዴ በሦስት ቀለሞች፣ መስመሮች ... በመስራት፣
   - የእስፕሪንግ ጥቅልል በማስመሰል የተያያዙ ስድስቶችን በመስራት፣
   - ሦስት ስድስትን እንዲፈጥሩ አንድ ዜሮን የሚጋሩና በዙርያቸው በተለያየ ዘዴ የተቀናበሩ ሦስት መስመሮች፣ ጭረቶች፣ ቅንፎች ጥቅልሎች፣ ሬክታንግሎች፣ ቀለሞች ... በመስራት፣
   - ሦስት ስድስቶችን እንዲፈጥሩ ሦስት ዜሮዎችን በተለያየ መንገድ በአንድ ጭረት በማገናኘት፣
   - ሦስት ጎን፣ ሦስት ቀለም ... ሦስት ነገሮችን በተለያየ ዘዴ ከስድስት ጎን፣ ስድስት ቁጥር፣ ስድስት ቀለም ... ጋር በማጣመር፣
   - ሦስት ስድስት ጎን ያለውን ፖሊጎን(Hexagon) በተለያየ ዘዴ በመሳል፣ አንዱን ሄክሳ ጎን በሦስት ቀለማት በመቀባት ...
3. በእጅ ጣቶች በተለያየ መንገድ በሚሰሩ የ666 ቅርፅ፣ የግብፅ ፒራሚድ ...





4. መነሻው ባይታወቅም አንዳንዶች “የስሙ ቁጥር” የሚለውን፣ የእንግሊዘኛ ፊደሎችን በቁጥር በመተካት ሲያሰሉ ይታያሉ፣

በዚህም ከA-Z ያሉትን የእንግሊዘኛ ቃላትን በስድስት ብዜት ቁጥር በመተካት (A=6, B=12, C=18, D=24, E=30, F=36, G=42, H=48, I=54, J=60, K=66, L=72, M=78, N=84, O=90, P=96, Q=102, R=108, S=114, T=120, U=126, V=132, W=138, X=144, Y=150, Z=156)፣ ከዚያም የተፈለገውን ቃል የፊደላት ቁጥሮችን በመደመር ውጤቱን ያሰላሉ፣

ለምሳሌ “Computer” የሚለውን ቃል በዚህ ዘዴ ብናሰላ፣

C=18, o= 90, m=78, p= 96, u= 126, t= 120, e= 30, r= 108

18+90+78+96+126+120+30+108

= 666

በዚህ ዘዴም Computer, mark of beast, RFID scanner, Newyork … የመሳሰሉ ስሞች ስሌት 666 ይመጣል፡፡ የዚህን ዘዴ አሰራር መነሻ ማረጋገጥ ባይቻልም በዚህ ስሌት 666 የመጡትን ስንመለከት ከ666 መንፈስ ጋር የሚገናኙ ናቸው፣ “The end justifies the means” እንደሚባለው አባባል የውጤቱ ትክክለኛነት የስሌቱን ትክክለኝነት ሲያሳይ እንመለከታለን፡፡

በዚህም መጽሐፍ ቅዱሱ “አዕምሮ ያለው የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው” የተባለውን ማስተዋል ይችላል፡፡

7.3. <u>የመንፈሱ የቁጥጥር እስትራቴጂ</u>

ከላይ እንደተመለከትነው ዓለም በግሎባላይዜሽን ሂደትና በኮምፒውተር ቴክኖሎጂ እገዛ አንድ መንደር እየሆነች ትገኛለች፣ በዚህም ሁሉም ነገር በአንድ ስርዓት ውስጥ እየተጠቃለለና መንፈሱ ዓለምን በቁጥጥሩ ስር ለማስገባት የሚያስችሉት አመቺ ሁኔታዎች እየተፈጠሩለት ይገኛል፡፡

ነገር ግን ስለ መንፈሱ አሰራር መጽሐፍ ቅዱሱ አስቀድሞ ስላስጠነቀቀና በቴክኖሎጂው እንግዳነት ምክንያት ቺፕስ በሰውነት ውስጥ የማስገባቱ ሂደት ቀላል ሂደት አይሆንም፣ በዚህም መንፈሱ ሰዎች አሰራሩን አካብደው እንዳያዩ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል፣ ዘዴዎቹም፣

- <u>ማለማመጃዎችን በመጠቀም</u>

ሰዎች ገንዘብ የሚያክልን ነገር በትንሽ ማይክሮ ቺፕስ ማስቀመጥ ላያምኑ ስለሚችሉ ወደዚህ ቴክኖሎጂ ከመገባቱ በፊት፣ ሰዎች ብዙ ብር እንዴት በቀላሉ በግብይት ካርድ በመያዝ መገበያየት እንደሚችሉ ማለማመድ፡፡

- <u>ስነልቦናዊ አካሄዶች በመጠቀም</u>
  - አሰራሩን መንፈሳዊ ሳይሆን ቴክኖሎጂያዊ በማስመሰል፣ ይህንን የሚቃወሙ ሰዎች ቴክኖሎጂ ያልገባቸው “መሀይሞች” በማስመሰል፣
  - የግብይት ስርአቱ “የዘመናዊነት” ምልክት በማድረግ ይህንን ያልተቀበሉ ሰዎች “ኋላቀሮች” በማስመሰል፣
- <u>አስገዳጅ ሁኔታዎችን በመፍጠር</u>
  - መግዛትም መሸጥን በዚህ ዘዴ ብቻ በመገደብ ምልክቱን የማይቀበሉ ከገበያው፣ ከኢኮኖሚው፣ ከማኅበራዊ ህይወት … እንዲነጠሉ በማድረግ ምልክቱን እንዲቀበሉ ማስገደድ፣

- ሰዎች የሚከፈላቸውን ክፍያ እንዲሁም በባንክና በቁጠባ ተቋማት ያስቀመጡትን ገንዘብ ማግኘት የሚችሉት በዚህ ስርዓት በማድረግ ምልክቱን እንዲቀበሉ ማስገደድ፣

መጽሐፍ ቅዱሱ ግን አስቀድሞ ሁሉንም በዝርዝር ስላስጠነቀቀ ምልክቱን በመቀበል ለሚመጣው ኪሳራ ኃላፊነቱ የባለቤቱ ነው።።

7.4. <u>የአሰራሩ መጨረሻ*</u>

አሁን የዚህ መንፈስ አሰራር ውስጥ ለውስጥ እንጂ በግልፅ አልተጀመረም፣ ከመንገድ ጠራጊዎቹ "ሐሰተኛ ዮሐንሶች" በስተቀር ዋናው መንፈስ አልተገለጠም ነገር ግን ጊዜው እየደረሰ እንደሆነ ከላይ ከተመለከትነው ዓለማቀፋዊና ሀገራዊ ትስስሮሽ፣ ቴክኖሎጂያዊ ትስስሮችና የግብይት ልምምዶች ማስተዋል ይቻላል።።

ከላይ እንደተመለከትነው የመንፈሱ አሰራር አንዱ መገለጫው ለእስራኤል ያለው ጥላቻ ነው፣ ይህ ሂደት በ1.4.2.3/3 ክፍል እንደተመለከትነው በዓለም ላይ እየተስፋፋ ያለ ሂደት ነው፣ ግለሰቦች፣ ሀገራት፣ ቀጠናዊና ዓለማቀፋዊ ጎብረቶች በእስራኤል ላይ ያላቸው ጥላቻ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ይገኛል፣ ይህም ጥላቻ እየጨመረ በመሄድ ከዓለም የተውጣጣ "ማን እርሱን ሊዋጋ ይችላል" የሚባል ጦር(ራዕ.13፡4) በሐሰተኛው ክርስቶስ/ማህዲ/ክርሽና/ሚየትራ/ካልኪ/ቪሽኑ/ልዕለ ሰው መሪነት እስራኤልን ለ42 ወራት ይወራል(ራዕ.11፡2, ራዕ.13፡5 ...)።።

በዚህ እስራኤልን መፈናፈኛ በሚያሳጣው ከአቅም በላይ በሚሆን ችግር መካከል በሚነሱት ሁለቱ ነብያት(ራዕ.11፡3-7) ምክንያት እስራኤል የገደለችውን ኢየሱስን ትቀበላለች፣ ከከበባትም ጭንቅ የተነሳ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ታነሳለች፣ በዚህም ኢየሱስ በደብረ ዘይት ተራራ ላይ እስራኤልን ሊረዳ ይገለጣል(ዘካ.14፡1-4, ማር.13፡3-37)፣ በዚህም በሐሰተኛውና በእውነታኛው ክርስቶስ መካከል ውጊያ ይካሄዳል(ራዕ.19፡15-21)፣ ኢየሱስም ይህንን የዓለምን ሠራዊት በመደምሰስ፣ መንፈሱንና አጠቃላይ ዲያብሎስን ለሺ አመት በማሰር ለእስራኤል ብሎም ለዓለም ሠላምን ያወርዳል(ራዕ.20፡3)፣ በዚህም የመንፈሱ አሰራር መቋጫ ያገኛል።።

ማጠቃለያ

ወርቅን ወርቅ ያደረገው፣ አልማዝን አልማዝ ያደረገው … በአጠቃላይ ብርቅዬ ነገሮችን ብርቅዬ ያደረጋቸው በብዛት አለመገኘታቸውና የሚገኙትም በብዙ ፍለጋ መሆኑ ነው፣ የዓለም ምስጢርም ብርቅዬ ነገር በመሆኑ ለሁሉም ሰው አልተገለጠም፣ በዓለም ላይ “ፈጣሪ የለም” ከሚለው አንስቶ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ኃይማኖቶች አሉ፣ ከነዚህ ህልቆ መሳፍርት መንገዶች ውስጥ ትክክለኛዋን መለየት የሚችሉት ጥቂቶች ብቻ ናቸው፣ ልክ ሁሉም ሰው መሬት ስለቆፈረ ብቻ አልማዝ፣ ወርቅ … ማውጣት እንደማይችለው ሁሉ።

ኢየሱስ ስለ መንግሥተ ሰማያት ምንነት ሲያስረዳ “ዕንቁ”፣ “የተሰወረች መዝገብ”፣ “በጠበበው ደጅ” … በማለት አስተዋይ ብቻ የሚያገኛት አድርጎ ነው የተናገረው፣ ይህ የብርቅዬነት አሰራርም አጠቃላይ የፈጣሪ የአሰራር በመሆኑም በስነ ፍጥረት ውስጥም ተመልክቷል፣ ለምሳሌ፣ ከሚሊዮን ፕላኔቶች ተለይታ ህይወትን የያዘችው አንዷ ምድር ናት፣ ከሚሊየን የሴት አቫሪ ውስጥ ልጅ የሚሆነው ጥቂቱ ነው፣ ከሚሊዮን የወንድ የስነተዋልዶ ዘር ውስጥ ልጅ የሚሆነው አንዱ ብቻ ነው … ወዘተ

በመጽሐፏ ውስጥም በስፋት እንደተመለከትነውም፣ አምላክ አለ? ወይስ የለም? ከሚለው አከራካሪ ጉዳይ ተነስተን የየኃይማኖቶችን አስተምህሮ ፈትሸን፣ ልክ እንደ አልማዝ ቆፋሪ ሰው አድካሚ ቁፋሮ አድርገን፣ አንዷ እውነት የትኛዋ እንደሆነች ለይተን አውጥተናል።

በዚህ ሂደትም የኤቲስቶች “ፈጣሪ አምላክ የለም” የሚለው ፍልስፍና የተሳሳተ ፍልስፍና መሆኑና ፈጣሪ አምላክ መኖሩን፣ ዋናውንም ፈጣሪ የምትከተለው ኃይማኖትም የምትገኘው በጂኦግራፊ/በብሔር በማይወሰኑትና የአንዱ ዋናው አምላክ ተከታዮች በሆኑት በአብርሃም ኃይማኖቶች ውስጥ መሆኑን፣ ከአብርሃም ኃይማቶች ደግሞ የቁርአን፣ ሞርሞን… መንገድ የስህተት መንገድ መሆኑንና ትክክኛው የመጽሐፍ ቅዱሱ መንገድ መሆኑን፣ መጽሐፍ ቅዱሱንም ከያዙት አብያተ ክርስቲያናት ጥንታውያኑ ኦርቶዶክስና ካቶሊክ በቆይታቸው ውስጥ በገቡባቸው የስህተት ትምህርቶች ከትክክለኛ መንገድ የወጡ መሆኑን፣ አዳዲሶቹ የሐዋርያት፣ ጀሆቫና የአድቬንቲስት አብያተ ክርስቲያናት ደግሞ በተሳሳተ ፍልስፍና የተመሠረቱ መሆኑን ነገር ግን <u>አሁን ባለችበት አቋሟ</u> በተሐድሶ የተመሠረተችው የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በትክክለኛ መንገድ ላይ መሆኗን ተመልክተናል።

እዚህ እውነታ ጋር ለመድረስ፣ ልክ እንደ አልማዝ ቆፋሪ፣ ተነበው ይቅርና ተገልጠው እንኳን የሚያልቁ የማይመስሉ የየኃይማኖቶችን መመርያ መጽሐፍትን፣ በግለሰቦች የተፃፉትን የየኃይማኖቶችና የፍልስፍና መጽሐፍትን፣ ተጓዳኝ መፅሄቶችን፣ ቪሲዲዎችን፣ ማኅበራዊ ሚዲያዎችንና ድረ ገፆችን በመጎብኘት፣ ከተለያዩ የኃይማኖት ሰዎች ጋር በመወያየት በብዙ አመታት ጥናት በተሰበሰቡ እውነታዎች መሆኑ አስረጂ አያስፈልገውም።

ይህንን ሁሉ መንገድ መሄድ ያስፈለገውም በግል በተፈጠረብኝ የኃይማኖት ጉዳይ ጥያቄ ምክንያት በገለልተኛ አእምሮ ባደረኩት ጥናት ነው፣ የጥናት ውጤቱም በዚህ መልክ ተቀናብሮ የቀረበው የውሸት መጋረጃዎችን በመግለጥ፣ አንዷን እውነት ለሁሉም በግልፅ ለማሳየት፣ ሰዎች በኃይማኖት ልዩነት ምክንያት እየደረሰባቸው ያለውን ችግር ለመፍታትና ሰዎች አንዷን እውነት ባለማወቅ በስጋም ሆነ ነፍስም ሊቀበሉት ከሚሉት መከራ መታደግ ይችላል በሚል እምነት ነው፡፡ በዚህም ሁሉም ሰው መጽሐፏን ለሌሎች በማዳረስና እውነታውን በማስረዳት የድርሻውን እንዲወጣ አሳስባለሁ።



አባሪ(Annex)

አባሪ - 1 (Annex-I) - የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ምህፃረ ቃል

ብሉይ ኪዳን

1. ዘፍ. - ኦሪት ዘፍጥረት
2. ዘጸ. - ኦሪት ዘጸአት
3. ዘሌ. - ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ዘኍ - ኦሪት ዘኍልቁ
5. ዘዳ. - ኦሪት ዘዳግም
6. ኢያ. - መጽሐፈ ኢያሱ
7. መሳ. - መጽሐፈ መሳፍንት
8. ሩት. - መጽሐፈ ሩት
9. 1ሳሙ.-መጽሐፈሳሙኤል ቀዳማዊ
10. 2ሳሙ.- መጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ
11. 1ነገ. - መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ
12. 2ነገ. - መጽሐፈ ነገሥት ካልዕ
13. 1ዜና.-መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ
14. 2ዜና.-መጽሐፈዜና መዋዕል ካልዕ
15. ዕዝ. - መጽሐፈ ዕዝራ
16. ነህ. - መጽሐፈ ነህምያ
17. አስ. - መጽሐፈ አስቴር
18. ኢዮ. - መጽሐፈ ኢዮብ
19. መዝ. - መዝሙረ ዳዊት
20. ምሳ. - መጽሐፈ ምሳሌ
21. መክ. - መጽሐፈ መክብብ
22. መኃ.-መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን
23. ኢሳ. - ትንቢተ ኢሳያስ
24. ኤር. - ትንቢተ ኤርምያስ
25. ሰቆ. - ሰቆቃወ ኤርምያስ
26. ሕዝ. - ትንቢተ ሕዝቅኤል
27. ዳን. - ትንቢተ ዳንኤል
28. ሆሴ. - ትንቢተ ሆሴዕ
29. አሞ. - ትንቢተ አሞፅ
30. ሚክ. - ትንቢተ ሚክያስ
31. ኢዩ. - ትንቢተ ኢዩኤል
32. አብድ. - ትንቢተ አብድዩ
33. ዮና. - ትንቢተ ዮናስ
34. ናሆ. - ትንቢተ ናሆም
35. ዕን. - ትንቢተ ዕንባቆም
36. ሶፎ. - ትንቢተ ሶፎንያስ
37. ሀጌ - ሀጌ
38. ዘካ. - ትንቢተ ዘካርያስ
39. ሚል. - ትንቢተ ሚልክያስ

አዲስ ኪዳን

1. ማቴ. - የማቴዎስ ወንጌል
2. ማር. - የማርቆስ ወንጌል
3. ሉቃ. - የሉቃስ ወንጌል
4. ዮሐ. - የዮሐንስ ወንጌል
5. ሐስ. - የሐዋርያት ስራ
6. ሮሜ. - ወደ ሮሜ ሰዎች
7. 1ቆሮ. - 1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
8. 2ቆሮ.-2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች
9. ገላ. - ወደ ገላትያ ሰዎች
10. ኤፌ. - ወደ ኤፌሶን ሰዎች
11. ፊልጵ. - ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች
12. ቆላ. - ወደ ቆላስይስ ሰዎች
13. 1ተሰ.- 1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች
14. 2ተሰ.-2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች
15. 1ጢሞ. - 1ኛ ወደ ጢሞቲዎስ ሰዎች
16. 2ጢሞ. - 2ኛ ወደ ጢሞቲዎስ ሰዎች
17. ቲቶ. - ወደ ቲቶ
18. ፊልሞ. - ወደ ፊልሞና
19. ዕብ. - ወደ ዕራውያን
20. ያዕ. - የያዕቆብ መልዕክት
21. 1ጴጥ. - 1ኛ የጴጥሮስ መልዕክት
22. 2ጴጥ.-2ኛ የጴጥሮስ መልዕክት
23. 1ዮሐ. - 1ኛ የዮሐንስ መልዕክት
24. 2ዮሐ.- 2ኛ የዮሐንስ መልዕክት
25. 3ዮሐ. -3ኛ የዮሐንስ መልዕክት
26. ይሁ. - የይሁዳ መልዕክት
27. ራዕ. - የዮሐንስ ራዕይ

አባሪ-II(Annex-II) - የቁርአን ምዕራፎች

1. አል ፈቲሀ
2. አል በቀራህ
3. አል አእራፍ
4. አል ዒምራን
5. አል ማኢዳህ
6. አል ዓንአም
7. አል አዕራፍ
8. አል አንፋል
9. አል ተውባህ
10. የኑስ
11. ሁድ
12. ዩሱፍ
13. አል ረዕድ
14. ኢብራሂም
15. አል ሒጂር
16. አል ነህል
17. አል ኢስራዕ
18. አል ከህፍ
19. መርየም
20. ጣሀ
21. አል አንቢያ
22. አል ሐጅ
23. አል ሙዕሚኑን
24. አል ኑር
25. አል ፉርቃን
26. አል ሹአራዕ
27. አን ነምል
28. አል ቀሶስ
29. አል አንከቡት
30. አል ሩም
31. አል ሉቅማን
32. አል ሰጅዳህ
33. አል አህዛብ
34. ሰብእ
35. አል መላይካ (አል ፈጢር)
36. ያሲን
37. አል ሳፋት
38. ሷድ
39. አል ዙመር
40.አል ጋፊር
41. ፋሲለት
42. አል ሹራ
43. አል ዙኽሩፍ
44. አል ዱኻን
45. አል ጀሲያህ
46. አል አህቃፍ
47. ሙሀመድ
48. አል ፈትህ
49. አል ሑጅራት
50. ቃፍ
51. አል ዛሪያት
52. አል ጡር
53. አል ነጂም
54. አል ቀመር
55. አል ረህማን
56. አል ዋቂዓህ
57. አል ሐዲድ
58. አል ሙጀደላ
59. አል ሐሽር
60. አል ሙምተሒናህ
61. አል ሶፍ
62. አል ጁሙዓህ
63. አል ሙናፊቁ
64. አል ተጋቡን
65. አል ጠላቅ
66. አል ተህሪም
67. አል ሙልክ
68. አል ቀለም
69. አል ሓቃህ
70. አል መዓሪጅ
71. ኑህ
72. አል ጂን
73. አል ሙዘሚል
74. አል ሙደሲር
75. አል ቂያማህ
76. አል ደህር
77. አል ሙርሰላ
78. አል ነበዕ
79. አል ናዚዓት
80. ዐበስ
81. አል ተክዊር
82. አል ኢንፊጣር
83. አል ሙጠፊፉን
84. አል ኢንሺቃቅ
85. አል ቡሩጅ
86. አል ጣሪቅ
87. አል አዕላ*